አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረምረቃ መርሓ ግብር

# በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ውስጥ የአገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ

በ

ተክለሃይማኖት ገብረፃዲቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2007 ዓ.ም.

# በኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ውስጥ

# የኣገር በቀል እውቀት ኣካትቶ ፍተሻ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረምረቃ መርሓግብር

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር

የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በ

ተክለሃይማኖት ገብረፃዲቅ

አማካሪ:- ዶር. ኑሩ መሓመድ

ሰኔ 2007 ዓ.ም.

# ማረጋገጫ

በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ውስጥ የአገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ካሁን በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ፣ ለማንኛውም ተቋም ያልቀረበና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፤ የጠቀስኳቸው ድርሳናትም በትክክል በዋቢነት ያገለገሉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ።

ስም፦ ተክለሃይማኖት ገብረፃዲቅ

ፊርማ፦

ቀን፦ 17/10/2007

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሐግብር

ይህ በተክለሃይማኖት ገብረፃዲቅ ተዘጋጅቶ 'በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የአገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ' በሚል ርእስ የቀረበው የዶክተርነት ዲግሪ ማሟያ ጥናት (በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር) ዩኒቨርሲቲው ያወጣውን መስፈርት ያሟላ፣ ወጥነትና የጥራት ደረጃውን ተጠብቀ መሆኑን እናረጋግጣለን።

አማካሪ፡- ዶ.ር. ኑሩ መሓመድ ፊርማ ------------ ቀን ሰኔ 18/2007

ፈታኝ፡- [illegible] ፊርማ ------------ ቀን ሰኔ 18,2007

ፈታኝ፡- [illegible] ፊርማ ------------ ቀን ሰኔ 18/2007

# ምስጋና

እንደ ወንድም፣ እንደ ጓደኛና  እንደ አማካሪ ሆነህ ከሶስቱም አካላት ላገኛቸው የምፈልጋቸውን ሁሉ በማድረግ ተንከባክበህ እዚህ ላደረስከኝ አማካሪየ ዶ/ር. ኑሩ መሓመድ ላቅ ያለ ምስጋና ላቀርብልህ እወዳለሁ። አማከሪየ፣ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ሳትመርጥ ወረቀቴን በማየት፣ በማስተካከልና አስፈላጊ መረጃ በመስጠት ባታግዘኝ ኖሮ ጥናቱ እዚህ ደረጃ ባልደረሰም ነበር።

አቶ ጌታቸው ወልዱ፡- ወደመስክ ለመውጣት ስዘጋጅ ሊያጋጥመኝ የሚችለውን የገንዘብ እጥረት ሳዋይህ "በገንዘብ ምክንያት ትምህርትህ አይቋረጥም" በማለት ላበረከትክልኝ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ከፍያለ ምስጋና አቀርብልሃለሁ።

ዶ/ር. አብርሃ አስፋው፡- ከፊት እየመራህ፣ ከጐን እየደገፍክ፣ ስጠፋብህ እየፈለግክ ልዘረዝራቸው የማልፈልጋቸው ውለታዎች ውለህልኛል። ፈጣሪ ውለታ ከፋይ ያድርገኝ። ወንድሞቼ፡- ኪዳነማርያም ገ. ህይወት፣ ተኽሉ ገ. ማርያም፣ ገብረኢየሱስ በየነ፣ ብርሃነ እና ተስፋይ ገብረፃዲቅ እኔን ለማስተማርና እኔን ተክታችሁ ቤተሰቤን ለማስተዳደር በገንዘብና በማተሪያል ለመደገፍ ብዙ ጥራችኋል። የጥረታችሁ ውጤት የሆነው ፍሬ ይኸውና! ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ።

ባለቤቴ ትርሓስ፣ ልጆቼ ሊዲያ፣ ፍኖት እና ብሩክ፣ ሁሉንም ነገር ችላችሁ እዚህ አድርሳችሁኛል። ስለትእግስታችሁ ከልብ አመሰግናችኋለሁ።

# አበርክቶ

ለሁለቱም ወላጆቼ

ወላጅ አባቴ ገብረፃዲቕ ረዳ፡- ልጆችህን ለማስተማር ያልከፈልከው መስዋእትነት ኣልነበረም። ሁሌም "ተማሩ" ነበር ቃልህ።

የመንፈስ ኣባቴ መኰነን ገ. ህይወት፡- መሬት ጨልሞብኝ ለመውደቅ ስንገዳገድ እጄን ይዘህ "ተማር" ነበር ያልከኝ። ሁለታችሁም ሳትተዋወቁ ኣንድ ዓይነት ኣደራ ሰጣችሁኝ። ኣደራችሁ እዚህ ደረጃ ደርሷል። ውጤቱም እኔም የናንተው ነን፤ ኣበረከትኩላችሁ።

# ኣሕፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ትኩረት በትግራይ ክልል በኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋን ለማስተማር በተዘጋጁት መፃሕፍት ኣገር በቀል እውቀት መካተቱና በኣግባቡ መቅረቡ መፈተሽ ላይ ነው። በሃገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረበት ከ19ኛው መቶ ክፍለዘመን መጨረሻ እስከ 1983 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ኣገር በቀል ቋንቋ እና ኣገር በቀል እውቀት የውጪ ቋንቋ ተፅእኖ ያጠላባቸው ነበሩ። የተጋሩ እውቀትና ቋንቋም በመደበኛው ትምህርት ውስጥ ቦታ ኣልነበራቸውም። የጥናቱ ዓላማም ህዝቦች በቋንቋቸው ባህላቸውን ማሳደግና እውቀታቸውን ማስተማር እንደሚችሉ ከታወጀበት ከ1987 ዓ.ም. በኋላ የተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃሕፍት (ከ1ኛ- 4ኛ ክፍል) ኣገር በቀል እውቀትን ማስተማር በሚያስችል ዘዴ መዘጋጀታቸውን መፈተሽ ነው።

ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሆኖ ለደረጃው በተዘጋጁ ስርዓተትምህርቶች ላይ የይዘት ትንተና ተካሂዷል። የእውቀቱ ተግባሪ ከሆኑት መምህራን ውስጥ በይሁነኝ የንሞና ዘዴ የተመረጡ 12 መምህራን በቃለመጠይቅ፣ 8 ደግሞ በተኮር የቡድን ውይይት ተሳትፈዋል። ኣንድ የስርዓተትምህርት ባለሙያም በወሳኝ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። የእውቀቱ ፈጣሪ ከሆነው ህዝብ ደግሞ በሰንሰለታዊ ጥቈምታ የንሞና ዘዴ 49 በቃለመጠይቅ፣ 27 በተኮር የቡድን ውይይት በድምሩ ከ76 የእድሜ ባለፀጋዎች መረጃ ሰጥተዋል። በኣጠቃላይ ከ97 ሰዎች በተሰበሰበው መረጃ ላይ ትንተና ተካሂዷል።

ጥናቱ የኣገር በቀል ቋንቋ ስርዓተትምህርት፤ ህፃኑ ከቤት ይዞት የመጣውን እውቀት በመነሻነት ካልተጠቀመ ኣንፃራዊ ዘላቂነት ያለው እውቀት ማስተማር ኣይችልም የሚል መነሻ ሐሳብ ኣለው። ምክንያቱም ኣበእ የህብረተሰብ እውቀትንና የቋንቋ ክህሎትና እውቀትን ለማስተማር በመሳሪያነት ስለሚያገለግል ነው። ይህንን ሃሳብ ለማጉላትም የጥናቱን ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍና የእውቀት ግንባታ የሚያሳዩ ሞዴሎች ቀርበዋል። ከትምህርት ቤት የሚገኘው የቋንቋ ትምህርት፣ የተማሪዎችን ቀዳሚ እውቀት መነሻው የሚያደርግ ከሆነ ህፃናት ቀደም ሲል የሚያውቁትን ሃሳብ ለመግለፅ ሲሉ ቋንቋውን

ይጠቀሙበታል። ሃሳባቸውን አደራጅተው ለሌሎች ለማስረዳት ሲለማመዱ ክሂላቸውን ያዳብሩበታል።

ፍትሻ የተካሄደባቸው የትምህርት እቅድ አመልካች ሰነዶቹ ግን ህፃኑ ምን እውቀትና ክህሎት ተምሮ ምን ለውጥ እንዳሳየ አያመለክቱም። አገር በቀል እውቀት ትኩረታቸው እንዳልሆነም ተረጋግጧል። በመርሃትምህርቱ ውስጥ የተዘረዘሩት ዓላማዎችም አገር በቀል እውቀትን (አበእ) የማስተማር ግብ የላቸውም። በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የህብረተሰቡን እውቀት የሚያስተላልፉ ጥቂት ተረቶችና እንቆቅልሽ ቢኖሩም አንብቦ መረዳትን ከማዳበር ያለፈ ድርሻ የላቸውም። ተማሪዎች በእውቀቱ ላይ በመወያየት ግንዛቤአቸውን እንዲያሳድጉ የሚያግዙ መልመጃዎች የሉም።

የህብረተሰቡ የዳበረ የግብርና እውቀት በእውቀትነቱ እንዲሰርፅ በማድረግ ፈንታ የህብረተሰቡ የአለማወቅ መግለጫ ሆኖ ቀርቧል። የተወሰኑ ተረቶች በምንባብነት የቀረቡ ቢሆንም ከቤት የተገኘውን እውቀት በትምህርት ቤት ከሚሰጠው እውቀት ጋር ለማገናኘት ድልድይ ሆነው እንዳላገለገሉ ተረጋግጧል። አገር በቀል የእድሜ ባለፀጋዎች ዋናዎቹ የእውቀት ምንጮች ቢሆኑም የሽማግሌዎቹ ቦታ ዘመናዊ ትምህርት በቀሰሙ ሰዎች ተይዟል። ያስተላለፏቸው መልእክቶች ግን ህብረተሰቡ መሃል ገብቶ ለመኖር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ስላልሆኑ ተቀባይነት እንደሌላቸው ጥናቱ አሳይቷል።

የይዘቶቹ አቀራረብ በመምህራኑ የግል ፍላጎት ብቻ ተወስኗል። ምንባቦች በተወሰኑ ተማሪዎች ወይም በመምህራን በድግግም ይነበባሉ፤ ተማሪዎች በድግግም አንብበው ወይም አድምጠው በቃል ይናገራሉ። ይህ አቀራረብ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበርም አያግዝም። በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት፣ አበእ ትኩረት እንዳልተሰጠው አመልክቷል። ስለዚህ የትምህርት ባለሙያዎች፣ የስርዓተትምህርት አዘጋጆችና የባህል ቢሮዎች አበእ የሚሰበሰብበትና ከመደበኛው ትምህርት ጋር ተዋህዶ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊያመቻቹ ይገባል።

ማውጫ


ይዘት ገጽ

ማረጋገጫ-----------------------------------------------------------------------iii
ምስጋና-----------------------------------------------------------------------iv
አበርክቶ-----------------------------------------------------------------------v
አሕፅሮተ ጥናት -------------------------------------------------------------vi
የምስሎችና ሰንጠረዦች ዝርዝር---------------------------------------------------xi
የአህፅሮተ ቃላት መፍቻ--------------------------------------------------------xii
ሙዳየ ቃላት------------------------------------------------------------------xiii

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ----------------------------------------------------------------1

1.1. የጥናቱ ዳራ-----------------------------------------------------------1

1.1.1. የኢትዮጵያ ትምህርት ታሪክ ዳሰሳ--------------------------------------------1

1.1.2. የጥናቱ አካባቢና ቋንቋው የሚገኝበት ሁኔታ-------------------------------------8

1.1.3. የተጋሩ አበእ እና መገለጫዎች----------------------------------------------11

1.2. ጥናቱን ያነሳሱ ችግሮች------------------------------------------------------32

1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች---------------------------------------------------34

1.4. የጥናቱ ወሰን--------------------------------------------------------------35

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ------------------------------------------------------------36

1.6. በጥናቱ የቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ፍቺ------------------------------------37

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን---------------------------------------------------------------39

2.1. መግቢያ-----------------------------------------------------------------39

2.2. የንድፈ ሃሳባዊ ዕሑፎች ዳሰሳ---------------------------------------------- 39

2.2.1. የስርዓተ ትምህርት ምንነት--------------------------------------------- 39

2.2.2. የስርዓተ ትምህርት ፍልስፍናዎች--------------------------------------------40

2.2.3. የአገር በቀል እውቀት ምንነት----------------------------------------------44

2.2.4. የአበእ መለያ ባህርያት ---------------------------------------------------48

2.2.5. አገር በቀል ትምህርት--------------------------------------------------- 51

2.2.6. አገር በቀል እውቀትና የቋንቋ ትምህርት-------------------------------------58

2.2.7. የትውፊት ሚና በአገር በቀል እውቀት ትምህርት ውስጥ------------------------67

2.2.8. የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በአራቱ የትምህርት ዓምዶች ውስጥ-------------------70

2.2.9. ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ-------------------------------------------------- 81

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ-------------------------------------------------91

ምዕራፍ ሶስት

3. የአጠናን ዘዴ -------------------------------------------------------------96

3.1. መግቢያ-----------------------------------------------------------------96

3.2. ጥናቱ የተከተለው ስነዘዴ---------------------------------------------------96

3.3. የመረጃ ምንጮችና የናሙና አወሳሰድ ዘዴ---------------------------------------98

3.4. መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች---------------------------------------------103

3.4.1. ቃለመጠይቅ --------------------------------------------------------103

3.4.2. የተኮር የቡድን ውይይት ምንነትና አስፈላጊነት ----------------------------107

3.4.3. የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ------------------------------------------108

3.4.4. ፍተሻና ትንተና የተካሄደባቸው ሰነዶች -----------------------------------111

3.5. የመረጃ ምንጮች ---------------------------------------------------------112

3.5.1. የእቅድ ሰነዶችና ስርዓተትምህርቶች------ ----------------------------114

3.5.2. መምህራን -----------------------------------------------------------116

3.5.3. የስርዓተትምህርት ባለሙያ ------------------------------------------- 117

3.5.4. የህብረተሰብ አባላት ከሆኑ የዕድሜ ባለፀጋዎች ------------------------------118

3.6. ትክክለኛነትና አስተማማኝነት---------------------------------------------119

3.7. ከምርምር ስነምግባር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች-------------------------------------121

3.8. ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች-------------------------------------122

3.9. የሙከራ ጥናት-----------------------------------------------------------123

ምዕራፍ አራት

4. መረጃዎች፤ የመረጃዎች ትርጎማና ትንተና------------------------------------------128

4.1. መግቢያ -----------------------------------------------------------------128

4.2. የአበእ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ መካተት አስፈላጊነት--------129

4.3. ከእቅድ ሰነዶችና ከመፃሕፍት የተገኙ መረጃዎች -------------------------------134

4.3.1. በሃገር ደረጃ በወጡ እቅዶች ውስጥ አበእ የተሰጠው ቦታ------------------------134

4.3.2. በክልል ደረጃ በተዘጋጁ የትምህርት እቅዶች ውስጥ አበእ የተሰጠው ቦታ---------135

4.3.3. ከመርሃ ትምህርት፣ ከተማሪዎች መጻሕፍትና ከመምህር መምሪያዎች

የተገኙ መረጃዎች- --------------------------------------------------137

4.3.3.1. በመርሃ ትምህርት ውስጥ አበእን ማስተማር ትኩረታቸው

ያደረጉ ዓላማዎችና ይዘቶች-------------------------------------------138

4.3.3.2. በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ አበእን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ

ምንባቦችና መልመጃዎች-------------------------------------------141

4.3.3.3. ከመምህር መምሪያ የተገኙ መረጃዎች----------------------------------196

4.4. በተጋሩ ዓይን በመጻሕፍቱ ውስጥ ያሉ እውቀቶች አገር በቀልነት-----------------201

4.5. የምንባቦችና የመልመጃዎች አቀራረብ ተገቢነት አበእን ከማስተማር አኳያ --------209

4.6. የምዕራፉ ማጠቃለያ------------------------------------------------------215

ምዕራፍ አንድ

5. ማጠቃለያና ጠቋሚ አስተያየቶች ------------------------------------------218

5.1. የጥናቱ አቀራረብ ሂደት----------------------------------------------------218

5.2. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች---------------------------------------------------219

5.3. ይሁንታዎችና የቀጣይ ጥናት ጥቆማዎች-----------------------------------225

5.3.1. ይሁንታዎች--------------------------------------------------------------225

5.3.2. የቀጣይ ጥናት ጥቆማዎች---------------------------------------------------227

ዋቢ ፅሁፎች ------------------------------------------------------------------229

አባሪዎች--------------------------------------------------------------------238

## የምስሎችና ሰንጠረዦች ዝርዝር


ምስል 1፡- የኣሁንም ሆነ መጪ እውቀት የሚመሰረተው ባለፈ ልምድ ላይ መሆኑ ኣመልካች---84

ምስል 2፡- የጥናቱ ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ ኣመልካች ንድፍ --------------------------------88

ሰንጠረዥ 3፡- የጥናት ጥያቄ፣ የመረጃ ኣይነት፣ የትኩረትና የኣፈፃፀም ቅደም
ተከተል ኣመልካች---------------------------------------------------114

ሰንጠረዥ 4፡- በእቅድ የተያዙና በተግባር በተከናወነ የቡድን ውይይትና በቃለመጠይቅ የተሳተፉ
የመረጃ ኣቀባይ ሰዎች መጠን ኣመልካች ------------------------------119

ሰንጠረዥ 5፡- በመርሃትምህርት ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች ኣይነትና መጠን የሚያመለክት----139

ሰንጠረዥ6፡- ከመሃትምህርት የተወሰዱ ዓላማዎችና ይዘቶች ኣመልካች-------------------140

ሰንጠረዥ 7፡- እውቀትን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና ዓለመዎቻቸው ኣመልካች ------142

ሰንጠረዥ 8፡- ስብእና ግንባታን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና
ዓላማዎቻቸው ኣመልካች -------------------------------------------178

ሰንጠረዥ 9፡- ማህበራዊ ግንባን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና
ዓላማዎቻቸው ኣመልካች --------------------------------------------187

**የኣህፅሮተ ቃላት መፍቻ**

| | |
|---|---|
| ህወሓት | ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ |
| መም. | መምህራን |
| ማእ. | ማእከላዊ |
| ምስ. | ምስራቃዊ |
| ሲቋት | ሲለበስ ቋንቋ ትግርኛ |
| ራዓ. | ራያ ዓዘቦ |
| ቃመ. | ቃለ መጠይቅ |
| ቅጥምባ | ቅርስ ጥናትና ምርምር ባለስልጣን |
| ቆተ | ቆላ ተምቤን |
| ቢትክት | ቢሮ ትምህርቲ ክልል ትግራይ |
| ቢትፋ | ቢሮ ትልሚን ፋይናንስን |
| ባቱሚ | የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር |
| ተቡወ | ተኰር የቡድን ውይይት |
| ታምፀ | ታሕታይ ምጋሪያ ፀምሪ |
| ኣበህ | ኣገር በቀል ህዝብ |
| ኣበእ | ኣገር በቀል እውቀት |
| ኣበባ | ኣገር በቀል ባህል |
| ኣበቋ | ኣገር በቀል ቋንቋ |
| ኣኣበእስ | ኣፍሪካ ኣገር በቀል እውቀት ስርዓት |
| ኢፌዲሪ | የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ |
| ወለኸ | ወርዒ ለኸ |
| ገኢልሚ | የገንዘብና ኢኮኖሚያዊ ልማት ሚኒስቴር |
| ጉምኪጥመቋ | ጉጅለ ምስፍሕፋሕ ኪነጥበብን መፅናዕቲ ቋንቋን |
| ደቡ | ደቡባዊ ዞን |
| ጥ.ጥ | የጥናት ጥያቄ |
| EBE | Educational Broadcasting Corporation |
| PHC | Population and Housing Census |
| MDG | Millennium Development Goal |
| MLC | Minimum Learning Competency |
| MoE | Ministry of Education |
| SDPRP | Sustainable Development & Poverty Reduction Program |
| MFED | Ministry of Finance & Economic Development |
| CFEE | Curriculum Framework for Ethiopian Education |
| EFA | Education For All |
| ESDP | Educational Sector Development Program |
| CDICP | Curriculum Development & Implementation Core Process |
| FDREPCC | Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission |

## ሙዳየ ቃላት

ረውሓ ቅብቅብ፣ ለስልሶ ለዘር የተዘጋጀ እርሻ

ዕግኢ፣ ፈግዓ ግምሻ፣ ለአንድ ዓመት ያህል ሳይታረስ የቆየ የእርሻ መሬትአለፍ አለፍ እያሉ ፈር ማውጣት

ተስላስ ለሶስተኛ ጊዜ ማረስ

ፉርማ ማይ በመጋቢት መጀመሪያ የሚጥል የአዝመራ ዝናብ

ጉሲያ ተጨናንቆ የበቀለን እህል መስመር ለማስያዝ፣ ለመቀነስና እንዲጎመራ የሚካሄድ ሽልሽላ

ምግብላው የታጨደን እህል በእቅፍ እየመጠኑ ፀሓይ እንዲመታው መዘረር

ቅሚጦ አምስትና ስድስት እቅፍ ሊይዝ የሚችል ክምር

ናዕሪ ከአስር እስከ አስራ አምስት ሸክም ሊይዝ የሚችል ክምር

ኩልሳስ ለመወቃት የተዘጋጀና አውድማ አካባቢ የተቀመጠ ትልቅ ክምር

ሶጮቢ ሃረግ መሰል ዱር በቀል የነቀዝ ማጥፊያ መድሃኒት

ጎንብሳ/ ሓላፊን ፀጉር በማቆምና አፍ አካባቢ ሙቀት በመፍጠር የሚታወቅ የከብቶች በሽታ

ጭልዓም የከብቶችን እግርና አፍ የሚያቈስል በሽታ

ቃርሳ ከእንጨት ተፈልፍላ የምትሰራ ክብ ቅርፅ ያላት ሩር ወይም ጥንግ

ቀብቀብቲ ሩርዋን እየመቱ ወደፊት የሚበሩ ፈጣን ሯጭ ወጣቶች

ፅድያ በተለይ የሓምሌ የመጀመሪያ ሁለት ሳምንታትን የሚያመለክት ጊዜ

መስቀል ብራኽ ከመስቀል ወይም ከመስከረም 16 በኋኋላ እንደማለት ነው

ፅባሕ ጥቢ፣ ከመስከረም 16 እስከ መስከረም መጨረሻ ያለ ጊዜ

ርፍዶት የማርፊጃ ስራ፣ መደበኛ የውሎ ስራ ከመጀመሩ በፊት የሚሰራ

ምስዮት ከመደበኛ ስራ መልስ ኣመሻሽ ላይ የሚሰራ ስራ

ጠበኽ እንጋግራ ወይም ገበሎ

ኣሓትና/ደቂሕድርትና ተሰውረው የሚኖሩ የማይታዩ ግን ሰውን የሚመስሉ ሴት ፍጡራን

ሕጊ ገረብ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ አባላት የሚዳኙበት ሕግ
ስነኑረት Ontology
ስነእውቀት Epistemology
ጠማሪ Inductive

| | |
|---|---|
| ዘርዛሪ | Deductive |
| ፍትነታዊ | Positivism |
| ዕንሰሓሳባዊ ማእቀፍ | Conceptual Framework |
| ገለፃዊ | Interpretive |
| ጉቡ | Imported |

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በዚህ ርእስ ስር የቀረበው ፅሑፍ የኢትዮጵያን የትምህርት ታሪክ ባጭሩ ቃኝቷል። ሃገራዊና ገብ የትምህርት አመራር አንድነትና ልዩነት ለማሳየት ሞክሯል። ኢትዮጵያውያን ህፃናት በውጪ ቋንቋ በመማራቸው ምን ጠቀሜታ ወይም ጉዳት እንደተገኘ፣ የሃገራችን መንግስታት ሲለዋወጡ በስርዓተትምህርት ላይ የታየው ለውጥ ምን እንደሚመስል ባጭሩ ይጠቁማል። በመጨረሻም ጥናቱ የሚካሄድበትን አካባቢና ህብረተሰብ ካስተዋወቀ በኋላ ባሁኑ ጊዜ የትግርኛ ቋንቋ የሚገኝበት ደረጃና እየሰጣቸው ያሉ ግልጋሎቶችንም ጠቁሟል። ጥናቱ ሊሞላው የሚችለውን ክፍተትንም አመላክቷል።

### 1.1.1. የኢትዮጵያ ትምህርት ታሪክ ዳሰሳ

በኢትዮጵያ ሃገራዊ ትምህርት ታሪክ የሚጀምረው ክርስትና ተሰብኮበታል ተብሎ ከሚታመንበት ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ነው። የዘመኑ ትምህርት ትኩረት በሃይማኖት ላይ በመሆኑና ይመራ የነበረውም በሃይማኖት ተቋማት ስለነበር "የሃይማኖት ትምህርት" በሚል ጥቅል ስም ይጠራ ነበር (Adane, 1991; Gebremdhen 1993; Girma et al. 1974)። በ7ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ሃገራችን የገባው የእስልምና ሃይማኖትም ተመሳሳይ የትምህርት አቋም ይዞ መቀጠሉ ይታወቃል (ሃይለገብርኤል፤ 1961)።

በተለይ የቤተክርስቲያኑ ትምህርት በአንድ ቋንቋ (ግእዝ) ብቻ የሚሰጥና "ዘመናዊ" ከሚባለው የምእራባውያን ትምህርት ስርዓት በተለየ በቃል ጥናት ያተኩር የነበረ ቢሆንም ተማሪዎችን ከአንዱ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ለማሸጋገር ግን በምእራባውያኑ ዘንድ እንኳ የማይታወቅ በጣም ጥሩ ስርዓት ይከተል ነበር (Adane, 1991)። ተማሪ ከነበረበት ደረጃ ወደ ቀጣዩ የሚሸጋገረው ወራትን ወይም ዓመታትን ጠብቆ በጅምላ ሳይሆን በግል ሆኖ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት ጨብጫለሁ ብሎ ባመነበት ጊዜ ለፈተና ሲቀርብና በመምህሩ

ሲረጋገጥ ነው፡፡ ስለዚህ ፊጣኑ ቶሎ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ሲሸጋገር ዘገምተኛው ደግሞ የራሱን አቅም ጠብቆ ባጠናቀቀበት ጊዜ ይሸጋገራል፡፡

በኢትዮጵያ የምዕራባውያን "ዘመናዊ" ትምህርት የተጀመረው በ1900 ዓ.ም. ነው (Caulk, 1975፤ ሃይለገብርኤል፣ 1961 ዓ.ም.)፡፡ ኢትዮጵያ ለውጪው ዓለም የነበራት ተጋልጦ እስከ 1900 ዓ.ም. ድረስ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ከምክንያቶቹ አንዱም የሀገሪቱ መልክአምድራዊ አቀማመጥ ነበረ፡፡ የሀገሪቱ አብዛኛው ቦታ በተራራ የተከበበ፣ ወንዞች ሸለቆዎች የሚበዙበት ስለሆነ፣ ዘመናዊ የሚባል መገናኛ ዘዴ ስላልነበራት ተጋልጦዋ ዝቅተኛ ነበር (Gebremedhin, 1993)። ይህ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ከሌላው አለም ጋር እንዳትገናኝ ሌላውም ዓለም በስፋት እንዳያውቃት ካደረጉ መጋረጃዎች አንዱ ነበረ።

ይህ የተገደበ የውጪ ግንኙነት የራስዋ የሆነ ማህበረ ባህላዊ ስርዓት እንድታዳብር ረድቷታል፡፡ በተራሮች የመታጠሯ ሁኔታ ዜጎችም እርስ በርስ እንዳይገናኙ አግዶ ኖሯል፡፡ በዚህ ምክንያት ደግሞ በክልል፣ በአውራጃ፣ በወረዳ፣ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ዘዬዎች፣ ባህሎች፣ ፍልስፍናዎች፣ የአኗኗር ዘይቤዎች ሊያዳብሩ ችለዋል (Gebremedhin, 1993)። አገሪቱ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች በፈረንሳዮች አማካይነት በፈረንሳይኛ ቋንቋ የተጀመረው "ዘመናዊ" ትምህርት በሃገሪቱ ከሚነገሩት በርካታ ቋንቋዎች ውስጥ አንዳቸውንም በትምህርትነት ወይም በማስተማሪያነት አልተገለገለም (Caulk, 1975; Gebremedhin, 1993; Germa, et al. 1974; Teklehaimanot, 1999)፡፡ በዚያ ዘመን የነበረው ገብ ስርዓተትምህርት (Imported Curriculum) በሃገር በቀል ምትክ በርካታ የውጪ ዜጎችን በመምህርነት ለመቅጠርና የውጪ መፃህፍትን፣ የውጪ ባህልንና የአስተሳሰብ ዘይቤን ለማስፋፋት አገልግሏል (Gebremedhin, 1993)።

የትምህርት አሰጣጥ ስርዓቱ ምዕራባዊ ስለነበረ ከመሰረታዊ የህብረተሰቡ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አልነበረም (Teklehaimanot, 1999)። በማስተማሪያነትና በትምህርትነት ያገለግሉ የነበሩት ቋንቋዎች ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ ወይም አረብኛ ነበሩ። በነዚህ ቋንቋዎችና እነዚህን ቋንቋዎች በሚናገሩ መምህራን አማካይነት ደግሞ ሀገራዊ እውቀት ወይም ባህል ይቀርባል፤ ተማሪውም ሀገራዊ እውቀትን ይገበያል ተብሎ አይገመትም።
እዚህ ላይ ጐልቶ እየታየ ያለው ጉዳይ፣ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በውጭ ቋንቋ በፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ወይም አረብኛ ሃሳባቸውን ለመግለፅ መቸገራቸው አይደለም።

ዋነኛው ችግር ይዘቱን የሚያስተላልፈው መምህር የራሱን /የውጪ/ ባህል፣ እምነት፣ ልማድ እያሰበ ማስተማሩ ነው (Caulk, 1975)። ኢትዮጵያውያኑ ደግሞ ይዘቱ ቀድሞ ከሚያውቁት የተለየና አዲስ ስለሚሆን ላይጥማቸው ብሎም ላይገባቸው ይችላል።

በ1930 ዓ.ም. የወጣ የመጀመሪያው የተፃፈ ህገመንግስት በጊዜው ለነበረው ፖርላማ ስብሰባ ከመቅረቡ በፊት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ነበር (Caulk, 1975)፡፡ ትምህርት ነክ የሆኑትን አንቀፆች በጊዜው የትምህርት ሚኒስቴር አማካሪ ለነበረው አሜሪካዊ (F. Ernestwork) ተሰጥቶ ካነበበው በኋላ ያቀረበው አስተያየት ኢትዮጵያ ባህልዋን እንድታዳብር ሊፈቀድ እንደሚገባ፣ ትምህርት በአውሮፓ ቋንቋዎች መሰጠት እንደሌለበት ይገልፃል፡፡ ቢያንስ በፅሁፍ ላይ ውሎ በሚታየው የአማርኛ ቋንቋ ሊማሩ እንደሚገባም ይጠቁማል፡፡ የErnestwork ሃሳብ ስለናፖሊዮን፣ ስለጋሪቫልዲ ወይም ስለ ግላርድስተን ለማወቅ ከእንግሊዝኛ፣ ከፈረንሳይኛ፣... ቋንቋ ጋር እየታገሉ መዋል ሃገራዊ እርባና እንደሌለው፣ ፅሁፎቹ ስለኢትዮጵያዊ ሰውና ምድር ካላወሩ ትምህርቱ ተማሪውን፣ ህብረተሰቡን፣ በአጠቃላይ ሀገሪቱን ያገለለ እንደሚሆን የሚያሳስብ ነበር።

በ1986ም Stoddart የተባለ እንግሊዛዊ በትምህርት ሚኒስቴር በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ አገልግሎትን ለመገምገም ቅኝት አካሂዶ ነበር። ባቀረበው የቅኝቱ ማጠቃለያ ሰነድም ልክ እንደ Ernestwork ሁሉ በተለይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (1-8) ሙሉ በሙሉ በአማርኛ መሰጠት እንዳለበት ያሳስባል። ምክንያቱን ሲገልፅም፡-

- ህፃናቱ የእንግሊዘኛ ቋንቋው ስለማይገባቸው፣
- መምህራን፣ በእንግሊዘኛ ካስተማሩ በኋላ በአማርኛ ተርጉመው በማስረዳት ብዙ ጊዜ ስለሚፈጁ፣
- የአመቱን ትምህርት መሸፈን ስለማይችሉና በበላይ አለቆች ስለሚነቀፉ፣
- በቋንቋው ምክንያት ህፃናቱ የሚቀርብላቸውን የክፍልም ሆነ ብሄራዊ ፈተና ማለፍ ስለማይችሉ (ብዙዎቹ ስለሚደግሙ) መሆኑን ይገልፃል።

ህፃናቱ በየቋንቋቸው የመማር መብት እንዳላቸውና በየቋንቋቸው ቢማሩ ይበልጥ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግን አልጠቀሰም። በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ህፃናት በአማርኛ ሲማሩ ተመሳሳይ ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል ያጤነ አይደለም ።

አብዛኞቹ ህፃናት (ተማሪዎች)፣ የሚቸገሩት፣ ክፍል የሚደግሙትና ከትምህርት ገበታ የሚገለሉት ለቋንቋው እንግዳ በመሆናቸው ነው። አዲስ እውቀት በአዲስ ቋንቋ መሳሪያነት ስለሚቀርብላቸው ነው። ትግርኛ አፍ ፈት የሆነ ህፃንም ከትግርኛ ውጪ በሆነ ቋንቋ እንዲማር ሲደረግ ተመሳሳይ ችግር ይገጥመዋል። ሆኖም የቋንቋው አገር በቀል መሆን ብቻውን አገርበቀል እውቀትን ለመማራቸው ማረጋገጫ ዋስትና አይሆንም። በዚያ ቋንቋ ምን ይዘት ቀረበ? ብሎ መመርመር አስፈላጊና አስገዳጅ ተግባር ይሆናል።

ኢትዮጵያ በቅኝ ገዢዎች ስር ስላልወደቀች የቅኝ ገዢዎች (የአንድ ሃገር) ስርአተ ትምህርት ብቻ አልነበረም ይሰራበት የነበረው (Girma, 1964) ። በርካታ የአውሮፓና የአሜሪካ ሃገሮች በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች፣ በተለያዩ ተቋማት፣ በተለያዩ ጊዜያት የየራሳቸውን ስርአተትምህርቶች በተግባር ላይ አውለዋል። በዚሁ አጋጣሚ የቻሉትን ያህል የየራሳቸውን እውቀትና እሴት በኢትዮጵያዊው ህፃን አእምሮ ውስጥ እንዲሰርፅ አድርገዋል (Germa, 1964; Mcnab, 1989; Tekeste 1990; ሙሉጌታ፣ 2002 ዓ.ም.)። እንደዚህም ሆኖ ግን ሁሉም ገብ ስርአተትምህርቶች ኢትዮጵያዊ መሰረት አላገኙም ነበረ። አውሮፓውያኑ አገር በቀል ትምህርት እንዲኖር አልፈቀዱም። የአገሪቱን ባህልና እውቀት ረግጠው ምዕራባዊ ባህል ነው ለማስፋፋት የሞከሩት (Germa et al. 1974; Tekeste, 1990)። ከነዚህ ተቋማት የሚፈልቀው ሃይል ከራሱ ባህልና ልማድ የተነጠለ፣ በማህበረሰቡ መሃል መኖር የማይችል ወይም ለመኖር የሚያስችል አገር በቀል እሴት የሌለው (Germa, 1964) ሰው ይሆናል። የስርአተትምህርቱ ሃገራዊ አለመሆን በተማረው ሰው ውስጥ ሌላ የሚፈጥረው ቅራኔ አለ። ይኸውም የተማረው “ዘመናዊ” አስተሳሰብና የሚገኝበት ህብረተሰብ ተጨባጭ ሁኔታ ላይጣጣሙለትና እውቀቱን ወደ ተግባር ለመለወጥ ሊቸገር ይችላል።

በ1940 የትምህርት ስርዓት የማሻሻል ስራ የተካሄደውና ስርዓተትምህርቱ የተቀረፀውም በሃገሪቱ ውሰጥ ስላሉት ቋንቋዎችና ስለ ክልሎቹም ሆነ ስለስርዓተትምህርት እውቀት በሌላቸው የውጪ ሀገር ዜጎች ነበር (Gebremedhen, 1993)። በ1958 ዓ.ም. የተሻሻለው ስርአተትምህርትም አማርኛ ቋንቋ በሁሉም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቸኛ የማስተማሪያ ቋንቋ መሆኑን ይወስናል (የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር 1998 ዓ.ም.)። እስከ 1962 ዓ.ም. የነበረው የኢትዮጵያ ትምህርት በአገሪቱ ውስጥ ያሉ አገር በቀል እውቀቶችን

ማንሳት፡ ይቅርና ኢትዮጵያዊ የቋንቋ ስርዓተትምህርት፡ የመማሪያ መፃህፍትና የማስተማር ዘዴ መኖራቸውም አጠራጣሪ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በጊዜው "የትምህርት ኮሚሽን" ተብሎ የተቋቋመው አካል ባካሄደው ጥናት በትምህርቱ አመራር ሁለት ዓበይት ክፍተቶች እንደነበሩ አመልክቷል (Germa et al.1974)፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ፣ የትምህርቱ ስርዓት በውጪ መማሪያ መፃህፍት፣ ማስተማሪያ ዘዴና የአቀራረብ ስልት ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ፣ ለኢትዮጵያ ባህልና በሀገሪቱ ለሚነገሩ ቋንቋዎች ("ብሄራዊ" ተብሎ አዋጅ ለወጣለት ቋንቋም ጭምር) ተገቢ ቦታና ክብር አለመስጠቱ ነው፡፡ ስለሆነም በዚያ ዘመን ስለሃገር በቀል እውቀትና መማሪያ መፃህፍትን ስለማዘጋጀት ማሰብ የሚቻል አይመስልም፤ ቢታሰብም እንኳ ውጤታማ አይሆንም ነበር።

ምሁራትም ቢሆኑ በውጪ መማሪያ መፃህፍት፣ ማስተማሪያ ዘዴና የአቀራረብ ስልት ሊማሩ አይገባም የሚለውን የትምህርት ኮሚሽኑን ሃሳብ አንፀባረቀዋል፡፡ በመላ ኢትዮጵያ አንድ ቋንቋ በትምህርትና በማስተማሪያነት ማገልገሉ ግን ትክክል ነው የሚል አቋም የያዙ ይመስላል፡፡ በዘመኑ አማርኛ የመማር-ማስተማር ቋንቋ መሆኑ ሶስት ትላልቅ ጠቀሜታዎች እንዳስገኘ Germa et al. (1974) ይጠቅሳሉ፡፡ ይኸውም:-

- የአማርኛ ቋንቋን በሚገባ ማወቅ ማለት፤ ሌሎች ትምህርቶችን ለመቅሰም የሚያስችል መሳሪያ መታጠቅ ማለት እንደሆነ፤
- የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት፤ በሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ለመሆንም አስፈላጊ መሳሪያ እንደሆነ፤ እና
- ያለአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ማንኛውንም ቢሮ መምራት፣ ጠቃሚ መረጃዎችንም ማግኘት እንደማይቻል ያስረዳሉ።

የነዚህ ሶስት ነጥቦች ይዘት ሲጨመቅ፤ የየትኛውም ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ለመማር፣ ስለሃገሩ ጉዳይ ለመናገርና በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ለመስራት አማርኛን የማወቅ ግዴታ እንደነበረበት ያመለክታል፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ህፃንም ወደደም አልወደደ በአማርኛ ቋንቋ ማሰብ፣ መናገርና መማር ነበረበት፡፡ ሰለሃገር ለማሰብና ለመናገርም በአማርኛ መገልገል የግድ ይላል። ይህ አገላለፅ ሃገራዊ ጉዳይ ከቤት፣ ከመንደር፣ ከቀበሌና ከወረዳ ሊጀምር እንደሚችል የዘነጋ ነው። ህብረተሰቡም ስለሃገሩ ለመነጋገር ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮቹን አስመልክቶ ለመወያየት በአገር በቀል ቋንቋ መገልገል የሚቃወም አስተሳሰብ ነው። ቋንቋው በትምህርት ቤት ደረጃ በስፋት

እየተሰራበት ስለቆየና ስላደገ ለብሄራዊ አንድነት መጠበቅ መሰረት መጣሉን ያብራራሉ፡፡ ይህ ሃሳብ በትምህርት ቤት ያለፉትን ኢትዮጵያውያን ብቻ እንጂ የሌላውን አገር በቀል ቋንቋ ተጠቃሚ ህዝብ ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። ብሄራዊ አንድነታችን የተጠበቀው በአንድ ቋንቋ በመማራችን ስለመሆኑም በጥናት የተረጋገጠ አይመስልም። በአንፃሩ አገር በቀል ቋንቋን በማስተማሪያነትና በትምህርትነት ይገለገሉ የነበሩ ህዝቦች በግድ በሌላ ቋንቋ እንዲማሩ ተደርገዋል (Adane, 1991; Mcnab; 1989; ትሚ፤ 1983 ዓ.ም.)።

ለምሳሌ በትግራይ ከ1960 ዋዜማ ጀምሮ የነበረው የወቅቱ የተማሪዎች ንቅናቄ ያነሳ የነበረው የብሄርተኝነትና በቋንቋ የመገልገል መብት ጥያቄ ነበረ (Heugh et al, 2007)። በኦሮሚያ፣ በኤርትራና በሌሎች አካባቢዎችም የተቃውሞ ንቅናቄዎች እንደነበሩ ይታወቃል (Ghermai, 1998)። አንዳንዶቹም የቋንቋና የባህል እኩልነት ጥያቄውን በማንገብ የትጥቅ ትግል አካሂደዋል። ለስርአቶች ሹምሽርና ለአንዱ በሌላው መተካት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ በራስ ቋንቋ የመማርና የራስን ባህል የማንፀባረቅ ጥያቄ ሆኗል። ይህ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በአማርኛ በመማራቸው ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚገልፀው አስተሳሰብ መሰረታዊ ፖለቲካዊ መፍትሄ ያልሰጠ፣ የህዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት ያላረጋገጠ መሆኑን የሚያመላክት ይመስላል።

በ1967 ዓ.ም. ዘውዳዊውን ስርዓት የተካው ወታደራዊ መንግስት ትምህርትን በተመለከተ ቅድመ 1967 ዓ.ም. ከነበረው መንግስት የሚለየው ገና ከመነሻው አላማና ግብ ይዞ መነሳቱ ነው። የትምህርት ሚኒስቴር ሰኔ 28 ቀን 1967 ባወጣው መመሪያ መግቢያ ላይ፡-

> *ትምህርት ያለፉት ትውልዶች አካባቢያቸውን ለማሸነፍ በስራ ከተፈጥሮ ጋር ሲታገሉ ያቆዩዋቸው የዕውቀት ቅርሶችን፣ ጠቃሚና ተራማጅ ባህሎችን ለማስተላለፍና ለማስፋፋት ዓይነተኛ መሳሪያ ስለሆነ...* የሚል ሃሳብ ሰፍሮ ይገኛል (ትሚ፤ 1967፡ 1)።

ከቀረበው ሃሳብ መገመት የሚቻለው ከፊውዳሉ ስርዓት በተለየ ሁኔታ አገር በቀል ቋንቋዎች፣ የብሄሮችና ብሄረሰቦች ባህሎችና እውቀቶች ስራ ላይ እንዲውሉ የሚፈቅድ ስርዓተትምህርት ሊኖር እንደሚችል ነው፡፡ የስርዓተትምህርት ዝግጅቱም በማእከልና በአካባቢ ደረጃ እንደሚካሄድና ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቦታ እንደማይሰጥ ስለሚገልፅ ግምቱን ያጠናክረዋል። ይህ ሁኔታ ግን ብዙም ሳይሄድ የትምህርት መስጫ ቋንቋ በሚል ርእሱ ስር አማርኛ ቋንቋ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርትነት እንደሚሰጥና የአንደኛ ደረጃ የማስተማሪያ ቋንቋም አማርኛ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል (MCnab, 1989; Heugh et

al, 2007)። የትምህርቱ ዓላማም የወዛደሩንና የአፈር ገፊውን የመደብ ትግል ለማፋፋም በመሳሪያነት ማገልገል እንደሆነ ያስረዳል (ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1967)።

እዚህ ላይ የሚነሳ ጥያቄ ይኖራል። የመማሪያና የማስተማሪያው ቋንቋ አንድ ብቻ ከሆነ፤ እንደትምህርት የሚሰጠውም ይኸው ቋንቋ ብቻ ከሆነ "ከዘውዳዊው የትምህርት ስርዓት በምን ይለያል?" የሚል ነው። ሁለቱም የአንድ ቋንቋ የበላይነትን ያቀነቅናሉ። ሌሎች ቋንቋዎች ስራ ላይ ከዋሉ የሃገር አንድነት ይናዳል ብለው ያምናሉ (ነጋሪት ጋዜጣ 1947 ዓ.ም.፤ የትምህርት ሚኒስቴር፣ 1967 ዓ.ም.፤ Teklehaimanot, 1999)። በእንደዚህ አይነቱ ስርዓተትምህርት ደግሞ ኣገር በቀል ቋንቋና ዕውቀት ትኩረት አግኝተው በክፍል ውስጥ በሚደረግ ተራክቦ ተማሪዎች ይገለገሉባቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

በኣጠቃላይ በቅድመ 1966 ዓ.ም. የነበረውም ሆነ ከዚያ በኋላ (በዘመነ ኣብዮት) የተነደፉት ስርኣተ ትምህርቶች በኢትዮጵያ የተለያየ ኣገር በቀል ዕውቀትና ኣገር በቀል ቋንቋ ያለቸው ኣገር በቀል ህዝቦች መኖራቸውን ግምት ውስጥ ያስገቡ ኣይመስልም። በእርግጥ በእድገት በህብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻ ጊዜ፣ በጎልማሶች ትምህርት ባህሪ ኣስገዳጅነት (Mcnab, 1989; Heugh et al, 2007) በ15 ቋንቋዎች መሰረታዊ ትምህርት ይሰጥ እንደነበረ ይታወሳል። ሆኖም የቋንቋዎቹ ግልጋሎት ከዚያ ያለፈ ኣልነበረም። የዘመነ ኣብዮቱ ስርኣተትምህርት ቀድሞ የነበረውን ኣምርሮ ከነቀፈ በኋላ ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥና ታሪክ እንዲሆን ነው ያደረገው። ኣዲሱ ደግሞ የህብረሰብኣዊነት (Socialism) ኣተያይ የማጠናከር ኣላማ ይዞ ነው የተነሳው (Ghermai, 1998 )። ሁለቱም ስርኣቶች የኣንድን ቋንቋ (ኣማርኛ) የበላይነት ከማጠናከርና የኣገልግሎት ኣድማሱን ከማስፋት በቀር ያመጡት ለውጥ ኣልነበረም። ስለሆነም በመደበኛው ትምህርት ስርኣተትምህርት ውስጥ የትምህርት ኣላማ ሆኖ ሊቀርብ ኣልቻለም። በኣላማነት ካልተነደፈ ደግሞ ዝርዝር ይዘት ሆኖ በክፍል ውስጥ በተግባር ሊታይ ኣይችልም።

አገር በቀል ትምህርት ሲታሰብ አብረው ሊታሰቡ የሚገቡ ነጥቦች አሉ። እነሱም፡- መሬት፣ ውሃ፣ እንሰሳትና ፈጣሪ፡፡ እነዚህ የማህበረሰቡ ኑሮ የተመሰረተባቸው በመሆናቸው ኣገር በቀል ትምህርት ሲታሰብ ትኩረት የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው። የቋንቋ ትምህርቱም ከነዚህ መሰረቶችና ከማህበረሰቡ ኑሮ ውጪ የሆነ የሚነጋገርበትና የሚፅፍበት ጉዳይ ሊኖረው አይችልም (Elleny, 1996; Hooley, 2009)። የኣገር በቀል ህዝቦች ወግና ተረት የሚመሰረተው በፈጣሪና በፍጡራን ላይ ነው። ምርምር የሚያካሂደውም በነሱ ላይ

ነው። የህልውናው ማለትም የኑሮ መሰረቱ የሆኑት መጠለያ፣ ምግብና ልብስ የሚገኙትም ከነዚሁ ነው። የሚማረውም ስለነዚህ ነገሮችና ስለራሱ ነው። ተፈጥሮም፣ ፍጡራንም የፈጣሪ ውጤቶች ስለሆኑ (Elleny, 1996) ተፈጥሮን ከሰው ልጅ፤ የሰውን ልጅ ደግሞ ከተፈጥሮ ለይቶ ማየት አይቻልም። ሆኖም ሁሉም ህዝቦች ተፈጥሮን፣ ፍጡራንና ፈጣሪን በተመሳሳይ ሁኔታ አያገኟቸውም፤ አይገለገሉባቸውም፤ አይገልጿቸውም። በፈጣሪና በአምልኮ ስርዓት ላይ ያላቸው ፍልስፍናም የተለያየ ነው። ስለሆነም የያንዳንዱን ጐሳ፣ ብሄር፣ አገር በቀል ህዝብ (አበህ) ሁኔታ የሚያንፀባርቅ የትምህርት ስርዓት ሊኖር የግድ ይሆናል።

### 1.1.2. የጥናቱ አካባቢና ቋንቋው የሚገኙበት ሁኔታ

ይህ ርእስ ጥናቱ የሚካሄድበትን የትግራይ አካባቢ በአጭሩ ያስተዋውቃል። የትግራይን መልክአምድራዊ አቀማመጥ፣ የዞኖች አከላለል፣ አጠቃላይ የህዝቡ መጠንና በክልሉ የሚነገሩ ቋንቋዎች የተናጋሪዎቻቸውን መጠን ያመላክታል። እንዲሁም በክልሉ፣ የትግርኛ ቋንቋ በምን ደረጃ እንደሚገኝና ምን ምን ተግባራትን ለማከናወን እያገላገለ እንደሚገኝ ይጠቁማል።

***የጥናቱ አካባቢ፡*** የትግራይ ክልል በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ ክልሎች አንዱ ነች፡፡ በሰሜን ከኤርትራ፣ በደቡብ ከአማራ ክልል፣ በምስራቅ ከአፋር ክልልና በምዕራብ ከሱዳን ጋር ትዋሰናለች፡፡ የአየር ሁኔታዋ ሶስቱንም የአየር ንብረት የያዘ ነው፡፡ ደጋማ፣ ወይናደጋና ቆላማ ቦታዎች ይገኙባታል፡፡ በሶስቱም የአየር ንብረቶች ሊበቅል የሚችል ሰብል ሁሉ ይመረትባታል።

በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ (Population and Housing Census (PHC, 2008) መሰረት በትግራይ ክልል 4,314,456 ህዝብ ይኖራል። ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ 5.8% መቶኛውን ይይዛል። በየአመቱም የ2.5% እድገት ያሳያል። ከክልሉ ህዝብ ውስጥ 19.5% በከተማ፤ 80.5% ደግሞ በገጠር ይኖራል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ (95.6%) የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን 0.1% የፕሮቴስታንት፣ 0.4% የካቶሊክ እና 4% የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ከዚህ አጠቃላይ ቁጥር ትግራዋይ 96.55%፣ ኢሮብ 0.71%፣ ኩናማ 0.07% ሲሆን የቀረው 2.67% ደግሞ የአማርኛ፣ ጉራግኛ፣ ኦሮምኛ እና ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተናጋሪ ህዝብ ነው።

የትግራይ ክልል፤ መቐለ ልዩ ዞንን ጨምሮ ሰባት ዞኖች አሏት፡፡ ከመቐለ ከተማ በስተቀር የዞኖቹ ስያሜዎች የተፈጥሮ አቅጣጫ ማመልከቻዎችን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ደቡባዊ፣ ደቡባዊ ምዕራብ፡ ምስራቃዊ፣ ማእከላዊ፣ ምዕራባዊ እና ሰሜናዊ ምዕራብ በመባል ይጠራሉ፡፡ መቐለ ደግሞ ልዩ ዞን ሆና ሓድነት፣ ሓወልቲ፣ ቀዳማይ ወያነ፣ ዓይደር፣ ኲሓ፣ ሰሜን እና ዓዲ ሓቂ የሚባሉ ክፍለከተሞችን ይዛለች። የህዝቡ የአሰፋፈር ስርጭት ሲታይ አብዛኛው ህዝብ በሶስት ዞኖች ይገኛል። በማእከላዊ 1,242,233፣ በደቡብ 1,004,558፣ በምስራቅ 755,633፣ በሰሜን ምዕራብ 735,951፣ በምዕራብ 375,545፣ በመቐለ ልዩ ዞን 215,546 ህዝብ ሰፍሮ ይገኛል (PHC 2008)። ደቡባዊ ምዕራብ ዞን አዲስ የተዋቀረ በመሆኑ የህዝብ ቁጥሩ ተለይቶ ስላልተቀመጠ ከደቡብ ጋር ተጣምሮ ቀርቧል።

በመጀመሪያዎቹ ስድስት ዞኖች ውስጥ ያሉ ወረዳዎች አርባ አምስት ናቸው፡፡ በያንዳንዱ ዞን ውስጥ ያሉ ወረዳዎች ቁጥር ሲታይ፤ደቡባዊ **ስምንት**፣ ደቡባዊ ምዕራብ **አራት**፣ ምስራቃዊ **ዘጠኝ**፣ ማእከላዊ **አስራ ሁለት**፣ ምዕራባዊ **አራት**፣ እና ሰሜናዊ ምዕራብ **ስምንት** ናቸው ፡፡ መቐለ፣ ቀደም ሲል ሰሜን እና ደቡብ በመባል የሚጠሩ ሁለት ወረዳዎች ነበሯት። ባሁኑ ጊዜ ግን የተሸነሸነችው በወረዳ ሳይሆን በሰባት ክፍለከተማ ነው።

የትግራይ ህዝብ ከዚህ ቦታ በዚህ ዘመን መጣ፤ ቋንቋውም በዚህ ጊዜ በንግግር ላይ ዋለ ብሎ ለመናገር የሚያስችል ጠንካራ መረጃ ማግኘት አልተቻለም። በሰሜን ኢትዮጵያ ቀዳሚ ነው ከሚባለው ከግእዝ ቋንቋ የተገኘ ወይም አብሮ ያደገ እንደሆነ ይገመታል (መስፍን 1997፣ ካሳና አማኑኤል 2000 ዓ.ም.)። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በ3500 ዓመተዓለም አካባቢ ነገደ አግአዚ የሚባል ህዝብ፣ ልሳነ አግአዚ የሚባል ቋንቋ ይጠቀም ነበረ። የቋንቋው ስያሜ ከጎሳው ስያሜ የተወረሰ ነው። ነገደ አግአዚ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ስለመሆኑ ግን የታወቀ ነገር የለም። ነገደ አግአዚ ከደቡብ ዓረብ ተሰዶ የመጣ ነው ብለው የሚያምኑ የታሪክና የቋንቋ ሊቃውንት እንዳሉ ሁሉ ይህንን ሃሳብ የሚቃወሙም በርካታ ናቸው (ፍስሃጊዮርጊስ፣ 1887 ዓ.ም.፣ ሃብተማሪያም 1986 ዓ.ም.፣ ካሳና አማኑኤል 2000 ዓ.ም.)። በተለይ ፍስሃጊዮርጊስ አግአዚያን ከደበቡብ ዓረብ ተሰደው እንደመጡ የሚያስረዳውን ሃሳብ እንዲህ በማለት አጥብቀው ይነቅፋሉ።

> *እኚህ ያሁን ኢትዮጵያውያን፤ በሃድራሞትና የማን መካከል ማህራ ከምትባል አገር የመጡ እንጂ ተወላጅ አይደሉም የሚለው የኢዱአርዶ ግላዘር ሃሳብ የ 'ገዓዝ፣ ጐዓዝ፣ ገዐዝ' ልዩነት ካለማወቅ የመጣ ነው። ግእዝ ማለት ስደተኛ ማለት ነው ብሎ መፃፍ*

> *ትልቅ ስህተት ነው። ... ኢትዮጵያውያን ወደ ኣረቡ ዓለም ተሻግረው የእርሻና የግንብ ስራ ሲያካሂዱ ኖረው ከዘመናት በኋላ ወደ ሃገራቸው መመለሳቸውን እንጂ ኣረቦች ወደ ኢትዮጵያ መሻገራቸውን ታሪክ ኣይነግረንም (ፍስሃጊዮርጊስ 1887 ዓ.ም.፣ 18- 19)።*

ሃብተማርያም (1986 ዓ.ም.) ካሳና ኣማኑኤል (2000 ዓ.ም.) ኣግኣዚያን ከደቡብ ዓረብ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ የሚለውን ሃሳብ ኣይቀበሉም። ግእዝ የሚለው ስያሜም ጀማሪነትን እንጂ ስደተኝነትን ኣያመለክትም። Hailu (1981) የትግርኛ ቋንቋ ስያሜ፣ ከነገዱ ስያሜ የተገኘ እንደሆነና ራሳቸውን ትግራዋይ (ተጋሩ)፣ ኣካባቢያቸውን ትግራይ፣ ቋንቋቸውን ደግሞ ትግርኛ ብለው እንደሚጠሩ ይገልፃሉ። የቃሉ ኣመጣጥ በተመለከተ ግን የጠቀሱት ነገር የለም። ኣግኣዚ የሚለው ስያሜ እንዴት ወደ ትግራዋይ እንደተሸጋገረ ለማሳየት የሚከተሉት መረጃዎች በዋቢነት ቀርበዋል፡፡ በ5180 ዓመተ ዓለም በሰሜኑ ክፍል ኣዲስ ክስተት ተፈጠሮ ነበር (ልሳነወርቅ፤ 2000ዓ.ም.፣ መስፍን፤ 1997)። ታላቁ እስክንድር (ግሪክ) የኢትዮጵያ ንግስት ለነበረችው ሳምር (ህንደኬ) ግብር እንድታስገባለት በደብዳቤ ያዛታል። ንግስቲቱም እምቢታዋን ስለገለፀችለት ጦር ይዞ ለወረራ ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ጦርነቱ እንደተጀመረ ንጉሱ በደረሰበት ያልተጠበቀ ጥቃት ሸሸት ጀመረ። ኣግአዚያን ከኋላ እየተከተሉ ሲወጉት እየሸሸ “**ኣፍቶስኢነ ትግሪ** - እነዚህስ ነምሮች ናቸው፤ **ትግረ ተጋሩ** - የነምሮች ነምር ናቸው” ኣለ። ከዚያ ጊዜ በኋላ ሰዎቹ ተጋሩ፣ ቋንቋቸው ትግርኛ፣ ኣካባቢያቸው ደግሞ ትግራይ እንደተባለ ልሳነወርቅ (2000 ዓ.ም.) እና መስፍን (1997) ያስረዳሉ። **ትግሪ፣ ተጋሩ** የሚሉት ቃላት ከጊዜ በኋላ የጎሳው መጠሪያ ሆነው ቢያገለግሉም ከመነሻው የቋንቋ፣ የጎሳ ወይም የቦታ መጠሪያ ሳይሆን የጎሳው ኣባላት ላሳዩት ጀግንነት የተሰጠ ቅፅል ነበር። የትግርኛ ቋንቋ ግእዝ በሚነገርበት ኣካባቢ ይነገር ስለነበረ፤ በርካታ የሚጋሯቸው ፊደሎችና ቃላት ስላሉት የግእዝ ኣካል ወይም ክፋይ ነው ማለት ይቻላል። ኣግኣዚያን የሚለው ስያሜም ለሁለቱም ቋንቋዎች ተናጋሪ ህዝቦች ያገለግል እንደነበረ መገመት ይቻላል። [1]

**ቋንቋው የሚገኝበት ሁኔታ፣** በሃገራችን ውስጥ እስከ 1986 ዓ.ም. ድረስ ይሰራበት የነበረው ስርዓተትምህርት ከምዕራባውያን የተቀዳ (ገብ) ነበረ (Gebremedhin, 1993;TeKlehaimanot, 1999)። በ1983 መጨረሻ በተደረገው የመንግስት ለውጥ

---

[1] (ፍስሃ እና ልሳነወርቅ በታሪኩ ኣንድ ኣይነት ሃሳብ ቢኖራቸውም በዘመን ኣቈጣቀጠር ግን ይለያያሉ። ፍስሃ 3500 ዓመተ ዓለም ሲሉ ልሳነወርቅ 5180 ዓመተ ዓለም ብለዋል። ሌላ ኣስታራቂ ሃሳብ ስላልተገኘ ሁለቱም ተጠቅሰዋል።)

ምክንያት ክልሎች፣ ብሄሮችና ብሄረሰቦች በቋንቋቸው እንዲማሩ የሚፈቅዱ የትምህርትና ስልጠና፣ እንዲሁም የባህል ፖሊሲዎች ወጥተው ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ፖሊሲውን መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ የሚገመቱ ስርዓተትምህርቶች፣ መርሃትምህርትና የመማሪያ መፃህፍትም ተዘጋጅተው ግልጋሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

በቅድመ 1984 ዓ.ም. በነበሩ መንግስታት የአገር በቀል ቋንቋ ትምህርት ጥያቄ በአዋጆችና ድንጋጌዎች አማካይነት ታግደው (ምላሽ ሳያገኙ) ቆይተዋል። በትግራይ ክልልም የአገር በቀል ቋንቋ በመደበኛ ትምህርት ቤት፣ በመማር ማስተማር ስራ ላይ የማዋል ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ ቆይቷል። ስለሆነም አንዳንድ የስነፅሁፍ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች ጥቂት ግጥሞችና ልቦለዶች ይፅፉ እንደነበር ቢታወቀም ቋንቋው ሰፊ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው በንግግር ቋንቋነት ነበረ። ከ1987 ዓመተምሕረት በኋላ ግን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማሪያ መፃህፍት ተዘጋጅተውለት በስራ ላይ ውሏል፡፡ እንደብዙዎቹ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የትግርኛ ቋንቋም ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ድረስ በማስተማሪያ ቋንቋነት፣ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ እንደአንድ የትምህርት አይነት፣ በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲ ደግሞ በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ በዋና ትምህርትነት በመሰጠት ላይ ይገኛል። እንዲሁም በክልሉ የመንግስት የስራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ነው።

ቋንቋው በመደበኛ ትምህርት ውስጥ እነዚህን ግልጋሎቶች እየሰጠ መሆኑ ቢታወቅም የተጋሩን አገር በቀል እውቀት ወደተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ በኩል ምን ድርሻ እየተወጣ እንዳለ የታወቀ ነገር የለም። በዚህ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶችም አላጋጠሙም። በዚህ ጥናት ዙሪያ በርካታ መሞላት ያለባቸው ክፍተቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢገመትም ይህ ጥናት አንድ ክፍተት ለመሙላት ተነስቷል። ይኸውም የትግርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጀው ስርዓተትምህርት የተጋሩን እውቀት ወደቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ በመሳሪያነት ማገልገል መቻሉን ማረጋገጥ ነው።

### 1.1.3. የተጋሩ አበእ እና መገለጫዎች

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች አለምን የሚያዩዋት እንዴት ነው? በአካባቢያቸው ያሉ ህዝቦችን የሚያዩበት መነፅር ምን ይመስላል? ከሌሎች ህዝቦችና ከአለም ህዝብ ጋር በማነፃፀር ራሳቸውን ምን ውስጥ ይመድባሉ? እነዚህ የህብረተሰቡን አጠቃላይ ሁኔታ ለመገንዘብና የትምህርት ሂደቱን ለማወቅ መልስ ማግኘት ያለባቸው

ጥያቄዎች ናቸው። ለምሳሌ ቀቀጥሎ የሚከተለው ኣብነት በትግራይ የሚታይ ባይሆንም በኣፍሪካውያን ዘንድ፤ በሙታን፣ በህይወት ባሉትና ባልተወለዱ ህፃናት መካከል ጠንካራና ተለጣጣቂነት ያለው ትስስር መኖሩ በጣም ኣስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል (Hurreiz, 2006)። ኣያቶች ወይም ቅድምኣያቶች የሆኑት ሙታን የህብረተሰቡ ደህንነት ጠባቂዎች ናቸው። በህይወት ያሉትን ሁሉ ይጠብቃሉ። ለድልና ሽንፈታቸው ሁሉ ሃላፊነት ይወስዳሉ። የተወለዱትንና ያልተወለዱትን የልጅ ልጆቻቸውንም ደህንነት ይጠብቃሉ። ኣያቶችም ሆኑ ከነሱ በፊት የነበሩት (ቅድመኣያቶች) በጋራና በዘመን ቅብብሎሽ የነዋሪዎችን ደህንነት ይከታተላሉ።

የዛሬዎቹ ነዋሪዎች ነገ ኣያቶች (ሙታን) ይሆናሉ። ዛሬ የሌሉት (ያልተወለዱት) ደግሞ የነገው ኣለም ነዋሪዎች ይሆናሉ። በነዚህ ሶስት ኣካላት መሃል በሚፈጠር የተግባራት መቀባበል የኣፍሪካውያን ትምህርት እውን ይሆናል (Hurreiz, 2006)። የኣፍሪካ እውቀት ወይም ልማዳዊ ትምህርት የሚባለውም ይኸው  በሶስቱ ትውልዶች (ያለፉት፣ ያሉትና መጪዎቹ ሰዎች) የሚደረግ የመረጃ ቅብብል ነው።

ኣፍሪካውያን በሰውና በኣካባቢው ባሉ ነገሮችና ክስተቶች መሃል ግንኙነት እንዳለ ብቻ ሳይሆን ኣንዱ በሌላው ላይ ኣዎንታዊ ወይም ኣሉታዊ ተፅእኖ እንደሚኖረውም ያምናሉ። በኣፍሪካውያን ኣተያይ፤ ሶስቱን ኣካሎች ነጣጥሎ ማየት በጣም ኣስቸጋሪ ነው። ሙታኑ በህይወት ላሉት (ላሁኖቹ ኣባቶች) መሰረቶች ናቸው። ለሚወለዱት ህፃናት መሰረታቸው ደግሞ ያለው ትውልድ ነው። በሶስቱ መካከል ቁርኝት የለም ማለት የእውቀትና የልምድ ሽግግር የለም ማለት ነው። ኣንዱ ስለሌላው እሚያውቀው ነገር የለም ማለት ነው። በግንባታዊ (constructivism) ኣተያይ የእውቀት ቀጣይነት እንዲኖር ከተፈለገ የነበረው ትውልድ እውቀት ላሆኑ መነሻ ሆኖ ማገልገል ኣለበት። በትውልዶች መካከል የእውቀት ቀጣይነት (መወራረስ)፤ መግባባት መኖር ኣለበት። መግባባቱ ግን በሰዎች መሃል ብቻ የሚወሰን ኣይደለም። ሰዎች፣ እንስሳት፣ እፀዋት፣ ድንጋይም ጭምር ይግባባሉ (Hurreiz 2006)። በኣጠቃላይ ከሰው ግንዛቤ ውጪ የሚሆን ነገር የለም። ዛፉም፣ እንስሳውም፣ እፀዋቱም ይናገራሉ። ሰውም ያደምጣቸዋል። የሚነፍሰው ነፋስ፣ የተከማቸው ወይም ኣልፎ ኣልፎ የሚታየው ዳመና፣ የፀሃይና የጨረቃ ብርሃን ወደ ሰው የሚያስተላልፉት መልእክት ኣላቸው። ሰዉም መልእክቱን ተገንዝቦ ተግባራትን ያከናውናል፤ ወይም ከማከናወን ይቆጠባል።

ትግራዋይ ማሕበረሰብም ከሌሎቹ የአፍሪካ ህዝቦች የሚጋራቸው እውቀቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ የኔ የሚላቸው እውቀቶች ሊኖሩት ግን የግድ ነው፡፡ በጉርብትና በባህል መወራረስ፣ በንግድም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች የባህል መመሳሰል እንደሚኖር ሁሉ የእውቀት መወራረስም ሊኖር እንደሚችል ይታመናል፡፡ ሆኖም ትግራዋዩም ሆነ ሌሎቹ ህዝቦች የየራሳቸው የሆነና እንደመታወቂያ የሚያገለግል ባህል፡ ፍልስፍና፣ እውቀት ይኖራቸዋል፡፡

ለምሳሌ ከብቶች የተለመደ የተፈጥሮ ፀጉር አላቸው። ፀጉራቸው ሲቆም፣ ሲረግፍ ወይም የተለየ ምልክት ሲያሳይ የትግራይ ህብረተሰብ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ይገባዋል። አስፈላጊ መድሃኒት ሰጥቶ ጤናቸውን ይመልስላቸዋል። በቡቃያ ላይ የሚታይ ምልክት ተገንዝቦ ውሃ ያጠጣዋል፤ አረሙን ያነሳለታል፣ ጥላውን ያስወግድለታል፤ አለያም ተባይ ያራግፍለታል። የአየሩን ሁኔታ ተገንዝቦ ይዘራል፤ ይወቃል፤ ወይም ተግባራትን ከመፈፀም ይቆጠባል። እንስሳት አየሩን በማሽተት የተለያዩ የስሜት ወይም የአካል ለውጥ ሲያሳዩ ማህበረሰቡም ምን እንደሆኑ፣ ምን እንደተረዱ፣ ምን ሊከሰት እንደሆነ አውቆ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። መሬት በውስጧ ከያዘቻቸው ነገሮችና ከስተቶች ጋር ያለው ተግባቦት በዚህ መልክ ይገለፃል። እነዚህ የማንም ሳይሆኑ የተወላጁ እውቀቶቹ ናቸው። የአገር በቀል እውቀት መተላለፊያ መንገድ ቃላዊ ተግባቦትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው። ሕብረተሰቡም እነዚህን ተጨባጭ እውቀቶች በመረጣቸውና ተገቢ ናቸው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ወደቀጣዩ ትውልድ ያስተላልፉቸዋል፡፡

አበእ፣ በተጋሩ ውስጥ የችግር መፍቻ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ የባህል ጥበቃ፣ የፖለቲካ አቋም ለውጥ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ በአረም፣ በእርሻ፣ በአዝመራ ስብሰባ ወይም በሌላ መሰል የስራ ዘርፍ ውስጥ የግለሰብን ወይም የቡድንን የስራ ተሳትፎ በማየት በዘፈን፣ በምሳሌ፣ በቀረርቶና ሽለላ ያሞግሳል፤ ልዩ ክብርና ቦታ እንዲኖረው ያደርጋል። በአንፃሩ፣ ደካማውን፣ ልግመኛና ሰነፉን ያንኳስሳል። ጋብቻ ሲጠይቅም ወጣቱ ስራ የማይወድ ከሆነ በዘመኑ ሴት አታርስም የሚል እምነት ስለነበረ **"ንሰበይቲዶ ሰበይቲ ትምርዐዋ እያ?"** (ሴቶች አይጋቡም) የሚል የሰውየውንና የወላጆችን ሞራል ከሚጎዳ ምላሽ ጋር ልጃቸውን እንደማይሰጡ ለሽማግሌዎቹ ይነግሯቸዋል። ይህ ትምህርት በቀጥታ በግለሰቡና ስራን

ባላስተማሩት ወላጆቹ ላይ ብቻ ያረፈ ይመስላል። ግለሰባዊ እሚመስለው ነቀፋ በማህበረሰቡ ውስጥ የስራ ባህል እንዲከበር ያደርጋል፤ ስራ አለመናቅንና በስራ መከበርን ያስተምራል። ይህ ተግባር ባህል ሲሆን በድህነት ቅነሳ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል።

ትግራዋይ፤ እንደማንኛው ኣገር በቀል ህዝብ የራሱ የሆነ ባህልና እውቀት ኣለው፡፡ በበጋ ወራት ወይም የዝናም መምጣት ምልክት በሌለበት ወቅት የቀንድ ከብቶች ኣንገታቸውን ቀና ኣድርገው ረጅም ትንፋሽ ወደ ውስጥ ሲስቡ (ሲያነፈንፉ) ካየ በቅርቡ ዝናብ ሊዘንብ መሆኑን ይገነዘባል። ይህንን መረጃ መሰረት በማድረግ ኣስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል። የተለያዩ ወፎች፣ ቀበሮ፣ ጅብ፣ ወዘተ. የሚያሰሟቸውን ድምፆች በማዳመጥ የተለየ መልእክት ይገነዘባል። ይህም ህብረተሰቡ እንስሳቱን በተግባራቸውም ሆነ በድምፃቸው ምን እንደፈለጉና እንዳዩ የሚረዳ መሆኑ ያመላክታል። ይህ ተግባቦት በማህበረሰብ እንጂ በኣንድ ሰው፣ ወይም ቡድን ብቻ የሚፈፀም ኣይደለም። ምክንያቱም ቀደም ሲል የተፈፀመው ተግባቦት በተረት፣ በምሳሌ፣ በዜማ፣ በሽለላና በሌሎች ቃላዊ መግባቢያወችና ድምፃዊ ምልክቶች ወደሌላ ያስተላልፋቸዋል። ሌሎቹም በተግባር ሞክረው ያረጋግጡና ህዝባዊ እውቀት ይሆናል።

ኣገር በቀል እውቀት  የሚቀሰመው በምልከታ፣ በመቅዳት (ኩረጃ) እና በኣካባዊ ተሳትፎ ሲሆን፣ ቃላዊና እይታዊ ኣውታሮች በማስተላለፊያነት ያገለግላሉ። የእነዚህ ማስተላለፊያ ኣውታሮች ቀዳሚ ተግባር በእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ህብረተሰቡን ማገልገል ነው።

ልማዳዊ ትምህርት ከማስተላለፊያ ኣውታሮቹ በተጨማሪ የህብረተሰቡ ኣባል የሆነ፣ ይዘቱን የሚያወጋ ወይም የሚተርክ ግለሰብ ወይም ቡድን ያስፈልገዋል። ተራኪዎቹ ቤተሰቦች፣ የእድሜ ጓደኞች፣ የጎሳው ኣባላት የሆኑ ኣዛውንቶች ሊሆኑ ይችላሉ። በኣቀራረብ ከይዘቱ ይልቅ ጎልቶ የሚታየው ውበቱ ነው። ስለሆነም የትውፊት ማስተላለፊያ መሳሪ የሆኑት የኣፍ ታሪኮች፣ የህፃናት ጨዋታ፣ ወጎች፣ ፉከራዎች፣ የስራ ግጥሞች፣... ሳቢና ኣዝናኝ ናቸው። ለምሳሌ ህፃናት የማህበረሰቡን ታሪክ መማር ካለባቸው ማቅረቢያው ነገራ ሳይሆን መዝሙር፣ ተውኔት ወይም ተረት ነው መሆን ያለበት። ህፃናቱም መዝሙሩን እየዘመሩ፣ ተረቱን ለጓደኞቻቸው እየነገሩ (እየተሳሳቁና እየተጫወቱ) እግረመንገድ ታሪኩን

ያውቋታል፤ ያጠኑታል (Hurreiz, 2006)። በዚህ መልክ የሚቀርብ ትምህርት ሰፊና በርካታ ነገሮችንና ሁነቶችን ይነካል። ለምሳሌ፡-

- **አካባቢን ያስተዋውቃል** (environmental education)፡- ስለወንዙ፣ ስለተራራው፣ ስለአዝርእት አይነትና ጠቀሜታ የሚያወሱ ተረቶችን ወይም እንቆቅልሾችን በመንገር ህፃናት እየተዝናኑ አካባቢው ምን እንደሚመስል እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡
- **ማህበራዊና ስነምግባራዊ ትምህርትን ያስተላልፋል** (social and moral education)፡- አዲሱ ትውልድ ከታላላቆቹ ጋር የሚያግባቡት ስነምግባሮችን፣ ልምዶችን፣ የአነጋገር ዘይቤዎችን እንዲያውቅ በማድረግ ከማህበረሰቡ ጋር ተዋህዶ እንዲኖር፤ ህብረተሰቡ ጥሩና መጥፎ የሚላቸውን ተግባራት አስቀድሞ እንዲለይ ያግዛል።

ታላላቆችንና ወላጆችን ማክበር የሚያስመሰግን ስነምግባር እንደሆነ የማህበረሰቡ አባላት ያምኑበታል፡፡ ስነምግባሩን ወደተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ያገለገለው ዘዴ ደግሞ ነጋሪ ሳይሆን ስእላዊ ነው፡፡

"**ጥንቅልዒት ሃሪሱ ዝሽይንን ንወለዱ ዝረግምን ሓደ እዮም**" (ተንጋሎ የሚሸናና ወላጁን የሚረግም ሰው አንድ ናቸው) ይህንን ተረትና ምሳሌ የሚሰማ ሰው መጀመሪያ ተንጋሎ የመሽናት ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ያስባል። ስእሉም በሚገባ ይታየዋል። ወላጅን ወይም አዛውንትን መድፈር ማንቋሸሽም ልክ ተንጋሎ እንደመሽናት ነው፤ ራስን መጉዳት እንደሆነ ይገነዘባል። ተረቱ፤ ማህበረሰቡ ለእድሜ ባለፀጎች የሚሰጠው ክብር የቱን ያህል ከፍ ያለ እንደሆነ ያመለክታል።

በተጋሩ ዘንድ፤ ሃይማኖታዊ ስነምግባርም ከዓለማዊው የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ተነጥሎ አይታይም። ህግና ደንቦቹን የማክበር ወይም የአለማክበር ውጤቱ ከህልፈት በኋላ ሳይሆን ከመቅፅበት የሚታይ ነው ብሎ ያምናል። እምነቱንም በእውቀትነቱ ወደተተኪው ትውልድ ያስተላልፋል። **"እግዚኦ ስምአኒ በእለተ ምንዳቤየ" (መዝ.101 ቁ.2)** የሚለው የመዝሙረዳዊት ፀሎት ከስነምግባር ማስተማሪያ ተረት ጋር ተያይዞ ቀርቧል። (ሙሉው ተረት በአባሪ ቸ ስር ይገኛል)

ተረቱ ሃቀኛ ሰው ምንጊዜም ኣይጠቃም፤ ሃቅ ኣሸናፊ ነች የሚል ትምህርት ኣስተላልፏል። ፀሎቱ እንዴት ብሎ ወደማህበረሰብ ሰርፆ በስነምግባር ማስተማሪያነት እንዳገለገለ ኣይተናል። ትግራዋይ ህፃን ይህን ከመንፈሳዊና ኣለማዊ ህይወት ጋር ተዋህዶ የቀረበውን ታሪክ ሲሰማ በስሜት ከቅኑና ታማኙ ሰው ጎን ይቆማል። ባለታሪኩ ሲጎዳ፣ ሲጠቃ፣ ወይም ጉዳት ሊደርስበት ሲል ለመከላከልና ምክር ለመስጠት ይሞክራል። ጎጂዎቹን ለመበቀል ባይችል እንኳ በስሜት ይጠላቸዋል።

ታማኙ ሰው ሲያሸንፍና ሲሸለም እሱ የተሸለመ ያህል ደስ ይለዋል። ቀስ በቀስም የየዋሁን ሰው ባህሪ ከራሱ ጋር ያዋህደዋል፤ የኔ ብሎ ይይዘዋል። ህብረተሰቡ ይህንን እውቀቱን በተረትና ምሳሌም እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፤

**በትሪ ሓቂ ትምንምን እምበር ኣይትስበርን** (የእውነት በትር ትመነምናለች እንጂ ኣትሰበርም) ይህ ተረትና ምሳሌም ቢሆን ትግራዋይ ለሃቅ የሚሰጠውን የላቀ ግምት ያመለክታል። ሃቅን ምርኩዝ ያደረገ ሰው ምንም ኣይነት ኣደጋ ኣያጋጥመውም ወይም ከላይ በተረቱ እንደታየው በሃሰት ቢወነጀል እንኳ ሃቀኛነቱ ከየትኛውም ኣደጋና ቅጣት ሊያድነው ይችላል። ምክንያቱም ፈጣሪ ከሃቀኞች ጎን ይቆማልና  የሚል የፀና እምነት እንዳለው ያሳያል።

ህብረተሰቡ ህፃናትን የሚያስተምረው ኣዝናኝና ኣጓጉ በሆነና ሊረሳ በማይችል ዘዴ ነው። ኣይነግርም ወይም ኣይሰብክም። ለምሳሌ ህብረተሰቡ ስስትንና ስስታምን ይጠየፋል። ሆኖም ህፃናቱን ስስት ጥሩ ኣይደለም በሚል መልክ ለማስተማር ኣይሞክርም። ከዚህ ይልቅ እያሳሳቀ እውቀቱን በሚከተለው መንገድ ለማስተላለፍ ነው የሚሞክረው።

## ይልቅ እንካ በሉት

*በኣንድ ኣካባቢ ኣንድ  ከልክ ያለፈ ስስታም ሰው ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት ሰው ስጠኝ፣ ኣምጣ ሲለው የማይወድ፤ በኣንፃሩ እንካ ሲሉት ኣይንና ጆሮው የሚከፈት ሰው ነበረ፡፡ ከእለታት ኣንድ ቀን ሰውየው ጎርፍ ውስጥ ገብቶ ሲወራጭ በቅርበት ሆነው ያዩ የነበሩ ሰዎች እጅህን ኣምጣ፣ እጅህን ስጠንና እናውጣህ እያሉ ይጮሁ ጀመር፡፡ ሰውየው ግን እየተንፈራገጠ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ በዚህ መሃል ሚስቱ ጫጫታውን ሰምታ እየሮጠች ደረሰችና ባልዋ በጎርፍ እየተወሰደ መሆኑን ኣየች፡፡ እስዋም የባልዋን ባህሪ ስለምታውቅ ኣምጣ ኣትበሉት ይልቅስ እንካ እጃችንን*

*በሉትና ከሞት ይትረፍ ኣለቻቸው፡፡ ሰዎቹም እንካ እጃችንን ያዝና እናውጣህ ሲሉት እጁን ሲዘረጋ ትተተው በማውጣት ህይወቱን አተረፉት ይባላል፡፡*

ህፃናት ከዚህ ተረት የሚማሩት ምንድነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ተጋሩ ንፉግነትን አጥብቀው የሚቃወሙ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ ተረቱን ለተተኪው ትውልድ በመንገር ንፉግነትን እንዲጠየፍ ለማስተማር ማለማቸውንም ያሳያል፡፡

**ስነቃል ኣበእን ብቻ ሳይሁን ቋንቋንም ያስተምራል፡-** ኣንድ ሙሽራ ጎጆ ከወጣ ከወራት በኋላ ድንገት ኣማቾቹ ቤት ይሂዳል። የሙሽሪት እናት የልጃቸው ባል ባልተዘጋጁበት ጊዜ መምጣቱ ደስ ኣላላቸውም። ቤት ያፈራውን እንጀራም ጠላም አቅርበውለት እየበላ ነው። ጠላውን ግን አንዴ ተጎንጭቶ ኣልደገመለትም። ቢያዩት ኣይጠጣም። እየደጋገሙ 'ጠጣ እንጂ' ይሉታል። እሱም 'እሺ እየጠጣሁ ነው' ይላል ግን ኣይጠጣም። ኣማት፣ የልጃቸው ባል ጠላው እንዳልጣፈጠው ገባቸውና ለማባበልና ለማግባባት ሲሉ **"ወደይ ዕጥናት ውሒዱዎ እምበር ፅቡቕ ስዋ እኮ እዩ።"** (በደንብ ስላልታጠነ ነው እንጂ ቆንጆ ጠላ እኮ ነው)[2] ይሉታል። እሜቴ ምን በወጣዎት ስንቱን ወንዝ ኣጥነው ይዘልቁታል?። በማለት መለሰላቸው ይባላል። ሙሽራው ለሴትዮዋ የተቆረቆረና በድካማቸው የተቆጨ በሚያስመስል የቋንቋ ኣጠቃቀም የወንዝ ውሃ ቀድተው እንዳቀረቡለት ነገራቸው።

በድሮ ዘመን **ጠበቕ** (እንጋግራ) የእንስሳት ሁሉ ንጉስ ነበረ ይባላል። ወፍ ለክረምት መውጫ የሚሆናትን የገብስ ብቅል ትሰበስባለች። ጎረቤት ኣይጥ ደግሞ እምትበላው ስላጣች ከወፍ ትበደራለች። ኣይጥ ብድርዋን መመለስ ኣልቻለችም። ወፍም ብዙ ከጠበቀች በኋላ እንድትመልስላት ትጠይቃታለች። "የለኝም" ትላታለች። ወፍ ክስ ልትመሰርት ወደ እንጋግራ ሄደች። እንደደረሰችም **"ኣያ ጠበቕ"** ብላ ትጣራለች። እሱም በጣም በተናደደ ስሜት 'ኣንዳች ከምድር ጋር ያጠብቅሽ' በማለት ይጮህባታል። እስዋም ምንም ሳትተነፍስ ወደቤትዋ ትመለሳለች።

ኣይጥ ደግሞ በተራዋ ትሂድና ገና ከሩቅ ስታየው፡-

> ***"ደሓንዶ ውዒልካ ኣያ ሹም ብሃገራ"*** *(የመላ ሀገሪቱ ሹም እንደምን ዋልክ)*
> ***"ደሓንዶ ውዒልኪ እዛ ጥዕምቲ ነገራ"*** *(እንደምን ዋልሽ ባለለዛዋ)*
> ***"ዓርከይ ዒፍ ብቑሊ ኣብቍለን "*** *(ጓደኛየ ወፍ ብቅል ኣበቀለች)*

---

[2] የጠላ እህል ቂጣ ከመሆኑ በፊት ቡኮው በወይራ እንጨት ጢስ ይታጠናል

*"ዋሕሊላ" (ባለሙያ ሆነች)*
*"ኣልቅሓኒ በልኩወን" (ኣበድሪኝ ኣልኳቸው)*
*"ጠምዩኪ" (ቢርብሽ)*
*"ምለሳለይ በላኒ" (መልሺልኝ ኣለችኝ)*
*"ክሪምኪ" (ክርመሽ)*

ይህ ተረት በተወሰነ መልኩም ቢሆን የህብረተሰቡን ስነልቡና ለማሳየት ይሞክራል። ወፍ ንብረትዋን ለማስመለስ ሹሙ ፊት ስትቀርብ ስድብ የጠበቃት ደረጃውን የጠበቀ ቋንቋ ባለመገልገሏ ነው። በአንፃሩ አይጥ የሰው ገንዘብ በልታ ተቀባይነት ያገኘችው በለዛዋ ነው። በሌላ በኩል አይጥ "ወፍ ብቅል አበቀለች" ብላ ስትናገር ሹሙ የወፍን ባለሙያነት ነው የመሰከረው። የተራበ መበደሩ፣ ያለው ደግሙ ማበደሩ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ተግባር መሆኑ ከምልልሱ መረዳት ይቻላል። ነገር ግን አበዳሪ ብድር እንዲመለስለት መጠየቅ ያለበት በፈለገው ጊዜ ሳይሆን መክፈል ይቻልበታል ተብሎ በሚገመት ጊዜ ብቻ መሆኑንም ያስገነዝባል።

በዚህ ተረት አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገው እውቀት ምንድነው? ቢባል አንዱ፣ የአነጋገር ለዛና ማህበረሰባዊ እርከኑን የጠበቀ የቋንቋ አጠቃቀም አስፈላጊነት ነው። ሰዎች የሚግባቡት አንድ አይነት ቋንቋ በመናገራቸው ሳይሆን አናጋሪያቸውን (አውድን) መሰረት ያደረገ ቋንቋ በመጠቀማቸው ነው። ሁለተኛው፡ ሙያተኛ ሰው ምንጊዜም የተከበረ ነው። አያ ጠቦች ወፍን በስነምግባር ጉድለት ቢነቅፏትም ብቅል ማብቀልዋን ሲሰማ ግን ሙያተኛነትዋን ነው ያደነቀው። ስለዚህ ህብረተሰቡ ሙያተኛን ማክበር እንደሚገባ ያሳስባል። ሶስተኛው ነጥብ፡- ብድርና የብድር አመላለስን የተመለከተ ነው። ህብረተሰቡ ኑሮውን የሚመራው እርስ በርስ በመደጋገፍና በመበዳደር ነው። አብዛኛው ሰው ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ ከአመት አመት የሚያዘልቅ ገቢ የለውም። ችግሩን የሚያልፈው ካለው በመበደር ነው። በተለይ ገበሬው ብድር የሚጠይቀው ክረምት መግቢያ አካባቢ ነው። ብድር እንዲመልስ የሚጠበቀው ደግሞ አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ ነው። ክረምት ግን ማንም አበዳሪ እህሌን መልሱ ብሎ አይጠይቅም።

*ዘየለቅሕ ቀታሊ፤ (እማያበድር ገዳይ)*
*ዘይመልስ ከታሪ። (የተበደረውን እማይመልስ ቀማኛ ነው።)*

በማለት እሚተርተውም ተተኪው እንዲወርሰውና መርሁን እንዲከተለው ለማድረግ ይመስላል (ሞገስ፣ 1958፡)።

ተረቱን የሚያደምጡ ህፃናት የመጀመሪያ ትኩረታቸው በባለታሪኮቹና በተግባራቸው ላይ ነው። እያንዳንዳቸው የፈፀሟቸውን ተግባራት በመስማት ይስቃሉ፣ ይዝናናሉ። ግጥማዊ በሆነው የእንስሳቱ ምልልስም ይሳባሉ። አይጥ በብልጠትና ለዛ ባለው የቋንቋ አጠቃቀም ሹሙን እንዴት እንደማረከችው ሊገነዘቡ ይችላሉ። ጭብጡን አስመልክተው ሲወያዩ ደግሞ በተረቱ ውስጥ ሳጋ ሆነው የገቡትን የማህበረሰቡን እውቀቶች ይገነዘባሉ።

**የባህላዊ ልዩ ሙያዎች ትምህርት፡-** ከላይ የተዘረዘሩት የትምህርት ሂደቶቹ የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሁሉ ሊገበያቸው የሚችሉ ናቸው። ለማስተማሩም ሆነ ለመማር የተለየ ጥረት ላይደረግ ይችላል። አብሮ በመኖርና አንዱ አባል ተግባራትን ሲፈፅም ሌላው በመታዘብ ወይም በማዳመጥ ሊቀሰሙ ይችላሉ።ከዚህ በተለየ መልክ የሚሰጡና ልዩ ክትትልና ረጅም ጊዜ የሚፈልጉ የእውቀት አይነቶች ደግሞ አሉ። መምህራኑ፤ ተራ የማህበረሰቡ አባላት ሳይሆኑ በሙያው የሰለጠኑ (Experts) ናቸው። ትምህርቱ፤ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ሆኖ ፍፁም ትክክለኛነትን የሚፈልግ ነው። ተማሪዎች ከስልጠናው በኋላ የተማሩትን ያለምንም ማዛባት ወይም እንከን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ ለነዚያ አይነት ሰራዎች ይበቃሉ ተብለው የተመረጡ ናቸው። በህብረተሰቡ ውስጥ ለሙያው ልዩ ተሰጥዎ የሚያሳዩ ሰዎች በዚያው እንዲቀጥሉና ባለሙያዎች ሆነው እንዲወጡ ይደረጋል። አንድ ሰው ልዩ ስልጠና ካላገኘ በቀር፤ በአንዱ ሙያ ስለሰለጠነ ብቻ የሌሎችም ሙያዎችም ባለቤት መሆን አይችልም፡፡ በሌላ አገላለፅ ሁሉም ሙያ የየራሱ ሙያተኛ ይፈልጋል ማለት ነው፡፡ ተጋሩም ይህንን እውነታ በተረትና ምሳሌ አማካይነት እንዲህ በማለት ይገልፁታል፤

**ሰራሒ ገንኢ መጎስ ምስራሕ ይኣብዮ፡፡** (ጋንን የሚሰራ ሰው ምጣድ መስራት አይችልም)

(ሞገስ፣ 1958 ዓ.ም.)፡፡

በትግራይ ውስጥ ልዩ ትምህርት ከሚያስፈልጋቸው እውቀቶች ውስጥ፣ የብረታብረትና የጌጣጌጥ ስራ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ስራ፣ የአናጢነትና የግንበኝነት ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የአጥንት ህክምና (ወጌሻ) ስራና የቤተክርስቲያን/መስጊድ አገልግሎት ስራ ይገኙባቸዋል። ሙያተኞች ለመሆን የሚሰለጥኑት ተማሪዎች ሙያዎቹን በምልከታ፣ በመቅዳትና አብሮ በመስራት ይቀስሟቸዋል። ልምምዱ ፋታ የማይሰጥ፣ ብዙ ጉልበትና ረጅም ጊዜ የሚፈልግ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ተማሪዎቹ ፍፁም የሆነ ችሎታ ያለው ሰው (ሙያተኛ) መሆን እስከፈለጉ ድረስ አድካሚና አሰልቺ በሆነ ጥረት ውስጥ ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች

ከኣሰልጣኞች ወይም ከመምህራን ያገኙትን እውቀት በትክክል መጨበጣቸውን በተግባር እንዲያሳዩ ይደረጋል። ህብረተሰቡም የሰሩትን መሳሪያ በመጠቀም፣ ብቃታቸውን ለሌሎች በመንገር ሙያተኞች መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል።

ለምሳሌ በእደጥበብ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ስራ ካየ በኋላ "ወርቂ ኢዱ፣ ኢደ ሰለሞን" 'የሱ ኣይነት ስራ የትም ኣይገኝም' በማለት ያደንቃቸዋል። የቤተክህነት ተማሪዎች ከሆኑም ድምፃቸውን፣ ኣካላዊ እንቅስቃሴያቸውን፣ ኣንደበተ ርቱእነታቸውን በማየትና በመስማት "ይበል፣ ይበል" በማለት ብቃታቸውን ይመሰክርላቸዋል። ህብረተሰቡም በየኣጋጣሚው ሁሉ በምሳሌዎች፣ በተረቶች፣ በዘፈን፣ በቀረርቶ ወይም በፉከራ ሙያተኞቹንና ሙያቸውን ያወድስላቸዋል። ውደሳው ሙያተኞቹ ሙያውን እንዲወዱት እዚያው ውስጥ እነዲቆዩ ያደርጋቸዋል። ሌሎች ኣባላትም ወደሙያው እንዲሳቡ የማድረግ ሚና ይጫወታል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው፤ ትውፊት ኣገር በቀል እውቀትን በማስተዋወቅ፣ በማስተላለፍና በማጠናከር ወሳኝ ድርሻ የሚጫወት መሆኑ ነው። ከተግባራዊ ልምምድ መማር የሚለውን ሃገር በቀል የማስተማር ዘዴን (Hurreiz, 2006: 72) ለመተግበር የሚያስችል መሳሪያ ነው። ስለሆነም በመደበኛው ትምህርት ውስጥ ኣገር በቀል እውቀትን ለማስተማር ትውፊት ስርኣተትምህርት ውስጥ ቢካተት ደግሞ ጠቀሜታው ከፍ ይላል። የዘመናዊው ትምህርት ጠቀሜታና ተቀባይነትም የዚያኑ ያህል ከፍ ይላል።

የሃገራችን "ዘመናዊ" ትምህርት የምእራባውያን ኣስተሳሰብና ፍልስፍና የገነነበት ገብ ስርኣተትምህርት እንደነበረ ብዙዎች ይስማማሉ (Germa, et al. 1974: Caulk, 1975; Gebremedhin, 1993; Teklehaimanot, 1999)። ግለኝነትን የሚያራምድና ኣግላይም ነበረ። በሌላ በኩል ልማዳዊው ትምህርት በይዘትም ሆነ በማስተማር ዘዴው እውቀትን ቀላል ግልፅና ኣዝናኝ በሆነ መንገድ በማስተላለፍ ረገድ ጠቀሜታዎች እንዳሉት እየታየ ነው። በባህሪውም፤ ማህበራዊነትን መርሁ ያደረገ ነው (Hurreiz, 2006: 74)።

በሁለቱ መካከል ደግሞ ግልፅ የሆነ ልዩነት ኣለ። በኣህጉራችን በኣፍሪካም ሆነ በሀገራችን ኢትዮጵያ እንዲሁም በትግራይ "ዘመናዊ" እውቀት የቀሰሙ ቢኖሩም በቁጥር ኣናሳ ናቸው። የፖለቲካ ስልጣንና የኢኮኖሚው ባለቤቶች እነዚያው "ዘመናዊውን" እውቀት የቀሰሙት ናቸው። ኣብዛኛው ህዝብ ግን በባህላዊ ትምህርት ውስጥ ያለፈ ነው። በመካከላቸው ባህላዊና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ልዩነትም ኣለ። ይህ ክፍተት ሊጠብና ጨርሶ

ሊጠፋ የሚችለው፤ ከኣገር በቀሉ ትምህርት የማህበራዊነት፣ የተግባራዊ ትምህርት ዕንሰሃሳብና በህዝቡ ውስጥ ባህላዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ ኣሰራሮችን በማምጣት ሁለቱን የትምህርት ስልቶች ማዋሃድ ሲቻል ነው (Hurreiz, 2006)።

**ኣገር በቀል ሕክምና ትምህርት፡-** እውቀት ተቀባይነት የሚያገኘው በተለያዩ ጊዜያት ተሞክሮ ተተግባሪነቱ ሲረጋገጥ ነው። ለምሳሌ ኣንዲት ሴት እንደወለደች የጡትዋ ጫፍ ወተት ኣላፈልቅ ቢል፤ ሙቅ ውሃ ውስጥ በመንከር፣ ጫፉን ደጋግሞ በመጫን የተደፈኑት ቀዳዳዎች እንዲከፈቱና ወተት እንዲያመነጭ ማድረግ እንደሚቻል ሴት ኣያቶች ያስተምራሉ። ይህ ኣገር በቀል ህክምና ከየትኛውም የምዕራባውያን ትምህርት ያገኙት ሳይሆን በሙከራና ልምምድ ያዳበሩት ኣገር በቀል እውቀት ነው (Negussie, 1994)። ይህ እውቀት ስላልተፃፈ ብቻ እንደ እውቀት ላይወሰድና ቀስበቀስም ሊጠፋ ይችላል።

ኣገር በቀል እውቀት በጥልቀት ቢጠና፤ ምእራባውያኑ እንደሚሉት የኋላ ቀር ህዝቦች መገለጫ ሳይሆን የኣብዛኛው ዘመናዊ የሚባል እውቀት መገኛ ምንጭ ሆኖ ሊገኝ ይችላል (Negussie, 1994: 517)። የትግራይ ማህበረሰብ ለዘመናት የቆየና ሲወራረስ የመጣ የህፃናት ህክምና፣ የእናቶች ማዋለድ የባህላዊ ህክምና እውቀት ኣለው። ይህ በመላ ኢትዮጵያ ብሎም በኣፍሪካ ስር የሰደደ እውቀት ከዘመናዊው ህክምና የተገኘ ነው ለማለት የሚያስችል ኣንዳች ምክንያት የለም። ይልቅስ ኣገር በቀል ህዝቦች ከዘመናዊው ህክምና መምጣት በፊት ይገለገሉበት ስለነበረ በመገኛነት ያገለገለ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል ።

**ኣገር በቀል ክትባት፡-** ለምሳሌ ያህል በትግራይ ህዝብ ለብዙ ዘመናት ያገለግል የነበረን የክትባት ስርዓት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተጋሩ ዘንድ **ውሽን፣ ንፍዮ፣ ፍረ ማይ (ፈንጣጣ፣ ኩፈኝና ጉድፍ)** የህፃናት በሽታዎች በመባል ይታወቃሉ። ከ50 እና 60 ኣመታት በፊት ህፃናትን በመፍጀት የሚታወቁ የበሽታ ዓይነቶች ነበሩ። በሽታዎቹ በተለዩ ሃይሎች ወይም ስውር መናፍስት **(ኣሓትና፣ ደቂሕድርትና)** የሚመጣ እንደሆነ ይታመናል። መናፍስቱ በህፃናቱ ላይ ያድራሉ። የፈለጉትን ነገር ካላቀረቡላቸው ወይም ካስቆጧቸው በህፃናቱ ላይ፣ የኣካል ጉዳትንና ሞትን ያስከትላሉ (**ሃብተማሪያም** 1986 **ዓ.ም.**)።

ኣንዱ መንደር ውስጥ በሽታው ከተከሰተ ሌላው መንደር ወደዚያ ኣይሄድም። ሰውን ተከትለው ስለሚሄዱና በዚያ መልክ ከመጡ ደግሞ ጉዳታቸው የከፋ ስለሚሆን ራሳቸው እስኪመጡ መጠበቅ ይገባል። በሌላ በኩል ጥንቃቄ የተመላበት ባህላዊ ክትባት በማካሄድ

በህፃናት ላይ ጉዳት ሳይደርስ በሽታው እንዲያልፍ ይደረግ እንደነበረ ይታወቃል። ክትባት የተለያዩ በሽታዎች ሰዎችን ከማጥቃታቸው በፊት በሽታ አምጪውን ህዋስ የሰዎቹ አካል ውስጥ በመጠኑ እንዲኖርና አካል ደግሞ ፀረጥቃት ህዋሳት እንዲያዳብር በማድረግ በሽታን የሚከላከሉበት ተግባር ነው። ተጋሩ በሽታን የሚከላከሉት በክትባት ብቻ አይደለም። ንፅህና መጠበቅ አንዱ የበሽታ መከላከያ ዘዴ እንደሆነ ያምናሉ። ይህንን እምነታቸውንም በሚከተለው ተረትና ምሳሌ አማካይነት ያንፀባርቁታል።

> *ንመስከረም ዝቖስል እግሪ ሰነ ሃመማ ይዓርፎ። (መስከረም የሚቆስል እግር ሰኔ ላይ ዝንብ ይወረዋል)* (ሞገስ፣ 1958 ዓ.ም.)።

የሰዎች ጤንነት የሚጠበቀው በህክምና ወይም በክትባት ብቻ አለመሆኑ ያስረዳል። ራስንና አካባቢን ንፁህ በማድረግ በሽታን መከላከል እንደሚቻልም ያስገነዝባል። የቆሸሸ ሰው ወይም አካባቢ በሽታ ማስከተሉ እንደማይቀር የሚያስጠነቅቅ ትምህርት ነው።

**ኣገር በቀል የኣካልና የኣዕምሮ ማጠንከሪያ ጨዋታዎች፡-** ጨዋታዎች የህፃናትን ኣእምሮ የማነቃቃት ድርሻ ኣላቸው። በህፃናቱ ላይ የተዝናኖት ስሜት ከፈጠሩ በኋላ ሌላውን እውቀት እንዲቀበሉ የማድረግ ሃይል ኣለው። ሆኖም ጨዋታዎች እንደየኣካባቢውና እንደየባህሉ የተለያየ መልክና ኣፈፃፀም ይኖራቸዋል። ተጋሩም የህፃናትን ኣካልና ኣዕምሮ ለማጠንከር የሚያግዙ ጨዋታዎች ኣሏቸው። ለምሳሌ ኣከካልን ለማዳበር ከሚያገለግሉት ውስጥ፡- ቃርሳ፣ ያህለላ፣ እምኒ ሓይሊ፣ ቅልስ፣ መኸተ፣ ሓመሳን ሃደንን (ገና፣ ክብደት ማንሳት፣ ትግል፣ ምክቶሽ፣ ዋና፣ ኣደን) ይጠቀሳሉ (**ገብረፃዲቕ፣ 1995፤ ሞገስ፣ 1958 ዓ.ም.**)።

የኣእምሮ ማንቂያ ከሆኑት ውስጥ ደግሞ እንቆቅልሾችና የገበጣ ጨዋታ ተጠቃሾች ናቸው (ገበጠ - ኣሰላ፣ ደመረ፣ ቀነሰ፣ በስሌቱ መሰረት መጠኑ ስንት እንደሆነ ኣወቀ)። ተጋሩ፤ ሁሉም ሙያ እቅድ ይፈልጋል የሚል እምነት ኣላቸው። ያለእቅድና ያለስሌት የተሰራ ስራ ውጤቱ ኣያምርም። ይህንን እምነታቸውም በተረትና ምሳሌና በተረት ይገልፁታል። ለምሳሌ **'ዘይሓስብ ኣይንገድ'** ይህ ተረትና ምሳሌ *ማሰብ የማይችል ሊነግድ ኣይገባም* የሚል የኣማርኛ ትርጉም ኣለው፡፡ *ተረቱ ከላይ ሲታይ* ስለንግድ የሚያወሳ ቢመስልም ሁሉም የስራ መስክ ሙያተኛ የሚፈልግ እንደሆነና ያለሙያና ያለእቅድ የሚገቡበት ስራ

ውጤት እንደማያስገኝ የሚያስገንዝብ እውቀት ነው። ተጋሩ ይህንን እውቀታቸውን በተረት መልክም ወደተከታዩ ትውልድ ያስተላልፉታል።

*ተረት ተረት        የላም በረት*

*ኣንድ ኣያ ኣባድር የሚባሉ ነጋዴ ነበሩ። ኣያ ኣባድር ሁሌም ይህንን እገዛለሁ ብለውና ኣቅደው ወደገበያ ሄደው ኣያውቁም። ኣንድ ቀን እንደልማዳቸው ገበያ ሄዱና ድንገት ጥሩምባ ኣዩና ደስ ስላለቻቸው ገዟት። በመቀጠል ጥሩ ድመት ኣዩና እሷንም ገዟት። በግ ተራ ገብተው ደግሞ በጣም ትልቅ የፍየል ሙክት ገዙ። ድንገት ቅቤ ስላዩ እሱንም ገዝተው ወደኣገራቸው ጉዞ ጀመሩ፡፡ ሲሄዱ፣ ሲሄዱ፣ ሲሄዱ ደከማቸውና ኣንድ ትልቅ ዋርካ ዛፍ ስር ኣረፍ ኣሉ።*

*ጥሩምባዋን ሳይሞክሩ መግዛታቸው ትዝ ስላላቸው ብድግ ኣድርገው በሃይል ኣስጮኧት። ሙክቱ ድምፁን ሲሰማ ደንግጦ ከእጃቸው ኣምልጦ መብረር ጀመረ፡፡ ኣያ ኣባድር ቢከተሉትም ሊደርሱበት ኣልቻሉም። ተስፋ ቆርጠው ሲመለሱ ድመቷ ቅቤውን በሙሉ በልታ መስኩ ላይ ተኝታ ኣገኟት። ድሮውኑ ተናደው ነበርና በያዟት ጥሩምባ ኣናቷን ሲሏት ወዲያው ሙትት ኣለች። ኣያ ኣባድር የሆነውን ሁሉ ማሰብ ሲጀምሩ ለዚህ ሁሉ ችግር የዳረገቻቸው ጥሩምባዋ መሆኗ ትዝ ኣላቸው። ይቺ የተረገመች ኣሉና ከድንጋይ ጋር ኣጋጭተው ሰበሯት ይባላል።ይህንን የረሳ ሞት ይርሳው። የኣነባበሮ እሾኽ ይውጋው። የወንጠፍት ደም ያስጠማው።*

ተጋሩ ኣያ ኣባድርን ምሳሌ በማድረግ በእቅድ መመራት፣ መቼ፣ ለምን፣ ምን መስራት እንደሚገባ ኣውቆ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ። ህፃናት ስራቸውን በተገቢ መንገድና በጥንቃቄ እንዲሰሩ ያስተምራሉ። እንደ ኣያ ኣባድር ሳያስቡና ጥቅምና ጉዳቱን ሳያውቁ ድንገት ያገኙትን መስራት ግን ለችግር እንደሚያጋልጥ ያስገነዝባሉ። የማያስብ ሰው መነገድ እንደሌለበት የተጠቀሰውም በዚህ ምክንያት ይመስላል።

**ኣገር በቀል ልኬትና ስፍር፡-** ህብረተሰቡ፣ በርካታ የልኬትና ስፍር መግለጫ ቃላትና መለኪያ መሳሪያዎች ኣሉት፡፡ ከፈሳሽ፣ ከክብደት፣ ከርቀት፣ ከጊዜ ጋር የተያያዙ መለኪያዎችና ስያሜዎች ኣሉት። በጊዜ ርዝመት ምክንያት እነዚህ ኣገር በቀል መለኪያዎች ባይጠፉም በኣውሮፓዊ መለኪያዎች እየተተኩ ያሉ ይመስላል። ለምሳሌ

ያህል እህልን ለመስፈር የሚያገለግሉ፣ ምን ያህልነትን የሚያሳዩ፣ ከእጅ ዝግን ጀምሮ እስከ 20 ኩንታል ድረስ የሚያመለክቱ የመስፈሪያ ዓይነቶች እንዳሉ ይታወቃል። (ዝርዝር መለኪያዎቹን ከአባሪ ነ ይመልከቱ)

መስፈሪያዎቹ አገር በቀል ከመሆናቸውም በላይ ዳብረዋል ከሚባሉት ቋንቋዎች በተሻለ ሁኔታ ሰፊ ግልጋሎት መስጠት የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አውሮፓዊ መለኪያዎች ሀገራዊውን መለኪያ በአቻ መተካት የሚችሉ አይደሉም። ሃገራዊው መለኪያ በመጠንም በስያሜም ሰፋ ብሎ ይታያል። ለምሳሌ ከኪሎ ቀጥሎ ኩንታል የሚል መለኪያ እናገኛለን፡፡ በሃገራዊው ውስጥ ግን በኪሎና በኩንታል መካከል ስምንት ንኡሳን ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ የአሃገር በቀሎቹ መለኪያዎች ከግልጋሎት እየቀነሰ ሲመጣ ግን ስያሜዎቻቸውም አብረው ሊጠፉ ይችላሉ።

**ጀግንነትን ማውረስ (ማስተማር)**፡- ጀግንነት በብዙ መልክ ሊገለፅ ይችላል፤ ጀግና ገበሬ፣ ጀግና ነጋዴ፣ ጀግና የሃገር አስተዳዳሪ፣ ጀግና ወታደር፣ ወዘተ.። ተጋሩ ሁሉንም ጀግኖች የሚያደንቁ ቢሆንም በተለይ ለጦር ሜዳ ጀግኖች ታላቅ ክብር ይሰጣሉ። በተለያየ አውደውጊያ የተሳተፉትንና ጀብድ የፈፀሙ ግለሰቦችን ያወድሳሉ። በአፀደህይወት የሌሉትንም ቢሆን የፈፀሟቸውን የጀግንነት ተግባራት እየዘረዘሩ ጎልተው እንዲታዩና ተከታዩ ትውልድም አርአያቸውን እንዲከተል ለማነሳሳት ይጠቀሙበታል። ታዳጊዎችና ወጣቶችም ጨዋታዎች የሚመስሉ፣ ነገር ግን ድፍረትን የሚያስተምሩና አካልን የሚያዳብሩ ልምምዶችን እንዲያካሂዱ ያደርጓቸዋል። የውጊያ ስልትንና ድፍረትን ለማስተማር ከሚያገለግሉ ልምምዶች ውስጥ **የግጠት** (**ደጋፌ**፣ 2001) ጨዋታ ይጠቀሳል። የግጠት ጨዋታ፣ የአንድ አካባቢ ወጣቶች ተሰባስበው የሚያከሂዱት ሆኖ ዓልሞ መምታትንና ድፍረትን የሚማሩበት ነው። ወጣቶቹ ዘንጎቻቸውን ይዘው የቁልቋል ተክል ወደአለበት ቦታ ይሄዳሉ። ከዚያም ከቅርብ፣ ከመካከለኛ ርቀትና ከርቀት ሆኖ ቁልቋሉን አልሞ የመምታት ልምምድ ያካሂዳሉ። ከዚህ ልምምድ በኋላ ጋሻና ዘንግ ይዘውና ፈረስ ላይ ሆነው እርስ በርስ አባራሪና ተባራሪ እየሆኑ ይለማመዳሉ። በዚህ ደረጃ የታየው ብቃት ዘንጋቸው ላይ ጦር ለመሰካትና አደን ለመሰማራት ያበቃቸዋል። በተደጋጋሚ የአደን ዘመቻ ወቅት ጥሩ ብቃት ያሳዩ ወጣቶች በጀግንነት ስማቸው ይነሳል። ቀስ በቀስም በተለያዩ ዘመቻዎች ለምሳሌ በጋዝ ዘመቻ የውጭ ጥቃትን ለመከላከል በሚደረግ ዘመቻ፣ በቀዳማይ ወያነ ዘመቻ፣ ወዘተ. እንዲሳተፉ ሲደረግ ኖሯ።

ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት መገንዘብ የሚቻለው ተጋሩ፤ እንደሌላው የእውቀት መስክ ሁሉ ጀግንነትንም ከልጅነት ጀምሮ የሚያስተምሩ መሆናቸው ነው። በአንፃሩ ፈሪን እንዲጠየፍና ፍርሃትን እንዳያስተናግድ የሚያደርጉባቸው ስልቶች አሏቸው። ለምሳሌ በዚያ ዘመን አንድ ሰው የወንዶች ተግባር ተብሎ ከሚታንበት ከዘመቻ ከቀረ፣ ከአውደውጊያ ሸሽቶ ከተመለሰ፣ በሱ ምክንያት ሌላ ወገን ከተጠቃ ያ ሰው ከዚያ በኋላ ወንድ አይባልም። በገረብ ህግ መሰረት በገረብ ዳኞች አማካይነት ቀሚስ ለብሶ ወደ ገበያ እንዲወጣና ህዝብ እንዲያየውና እንዲስቅበት ይደረጋል። ተተኪው ትውልድም ፈሪን የሚጠየፍ ስነልቡና ይዞ ያድጋል፤ ጀግንነትንም እንደ አንድ የሙያ ዘርፍ ይማረዋል።

የትግራይ ህዝብ ኣፄ ሃይለስላሴ ከስደት እንደተመለሱ ሊቀበላቸው ያልፈለገውና በቀዳማይ ወያነ ስም ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የወሰነው ህዝቡን ጦርነት ውስጥ ማግደው በመሸሻቸው ነው። ህዝቡ አቅም ኖሮት ንጉሱን ቀሚስ አልብሶ ገበያ ማዞር ባይችልም በፈሪ ላለመገዛት ወስኖ ነበር (Gebru, 1996)።

***ዘፍረሰ ቀሺ ኣይቕድስን፤*** *(የፈረሰ ቄስ ኣይቀድስም)*
***ዝሃደመ ንጉስ ተመሊሱ ኣይነግስን*** *(የሸሸ ንጉስ ተመልሶ ኣይነግስም) በማለት*

በኣካቢ ህግ "ሕጊ ገረብ" ለመመራት ወስኖ እንደነበረ ይታወሳል (የማነ፣ 2005 ዓ.ም.)። ኣገር በቀል እውቀት የሚተተላለፈው በቃላዊ ተግባቦትና በተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው። ተጋሩም ጀግናንና ጀግነትን በፉከራ፣ በሙሾ፣ በቀረርቶ ሲገልፁና ጀግና የሚባለው እንዴት ያለ እንደሆነ ሲያስተምሩ ኖረዋል፡፡ ለኣብነት ያህል ጥቂቶቸን እንመልከት።

*ኽልተ ዓውዲ ኣውደቕካ ሓንቲ ቓትሪ*

*ሓዲኡ ኣጋምሸት ሓዲኡ ቕድሚ ቓትሪ*

*ሓጋዚ ዘይብሉ ባዕልኻ መዞሪ ባዕልኻ በርባሪ*

*ባዕልኻ ፈላሺ ባዕልኻ መሃሪ*

*ጎዛ ደይታሕድር ኽስታር ደይታቕሪ፡፡* *(ደጋፊ፣ 2001 ዓ.ም. ፡228)*

***ትርጉም፡-*** *ሁለት ኣውድማ ላይ ጣልክ ኣሉ ሁለት ክምር*
*ኣንዱን በማለዳ ኣንዱን ቀትር*
*ኣጋዥ በሌለበት ራስህ ኣዟሪ ራስህ በርባሪ*
*እራስህ ኣፍርሰህ ራስህ ዘርዛሪ*
*ግርድም ኣታሳድር ከቶም ፍንጣሪ፡፡*

በተጋሩ ዘንድ ጀግና ማለት በዚህ መልኩ ጠላትን ለብቻ ገጥሞ ጠራርጎ ድልን የሚቀዳጅ ነው። ኣልቃሽ በሁሉም የትግራይ ኣካባቢዎች ይታወቃል። በአሁኑ ጊዜ በተፅእኖ ምክንያት እየቀነሰ ያለ ቢመስልም ጨርሶ ኣልጠፋም። እንደ ኣዲስ ኣበባ ባሉ ትላልቅ ከተሞች ኣካባቢ የሚታዩ ኣስለቃሾች በገንዘብ ተገዝተው የሚመጡና 'እንዲህ በልልን' እየተባሉ ሰዉን ለማስለቀስ ጥረት ስለሚያደርጉ ይመስላል ኣስለቃሽ የሚባሉት። በተጋሩ ዘንድ ኣልቃሽ የሚባሉት ግን የሟች ሚስት፣ ልጆች፣ ዘመድ፣ ጎረቤት፣ ጓደኛ፣ ወይም የሟችን ማንነት ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች (ወንድ ወይም ሴት) ሊሆኑ ይችላሉ። ኣልቃሾች ለሚዘረዝሯቸው የጀግንነት ውሎዎችና ተግባራት ማስረጃ የሚያቀርቡ መሆን ኣለባቸው። ስሜታቸው ሲነካ የሟችን ያለፈ ህይወት ትዝ ሲላቸው ትውስታቸውን በግጥም ከእንባ ጋር የሚያፈሱ ልዩ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ናቸው። በኣልቃሾች የሚደረደረው ግጥም ሌላውን የሕብረተሰብ ኣባል ለማስተማር ያገለግላል። እከሌ ጀግና በመሆኑ እንዲህ ተባለለት፤ እኔም... የሚል ስሜት እንዲያሳድርና ለኣገር፣ ለወገን ደህንነት ጥብቅና እንዲቆም ያደርጋል።

ሟች በህይወት ዘመኑ መጥፎ ተግባራት ፈፅሞ ከሆነም ተግባሩን የሚያወሱ ግጥሞች በመደርደር ይለቀስለታል፡፡ ከዚህ ኣይነቱ ለቅሶም ቢሆን በቂ እውቀት ይገኝበታል፤ ይኸውም ከመጥፎ ምግባር እንዲታቀቡ ያደርጋል።

ሟች (ሴት ወንድ) ያልሰሩት ጥሩም ሆነ መጥፎ ተግባር ተገልፆ ከሆነ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠየቃል። ካልሆነም ስህተቱ እንዲታረም ይደረግና ኣልቃሹ ይቀጣል። ምሳሌ

| | |
|---|---|
| *ዳሕናዶ እነአኺ ርእሲ ዋልታ* | *ደህና ነሽ ወይ የሁሉም የበላይ* |
| *ደይትርታዕያ እንድሕ መጒታ* | *ተሟግታ እማትረታ* |
| *ኣሽኡን ደይትሪኦም ህንዲ ኣኸታ* | *ተኣክታ ያህል እማትቆጥር ወንዶችን* |
| *ሃምትቖነናያ ሃምትቐነታ* | *ፀጉራቸው ቢሰሩ ቢታጠቁም* |
| *ኣይመልኣይያ ህንዲ ዕላሎታ* | *የጥላዋን ያህል እንኳ ኣይሞሉም* |
| *ድህገሞ ታልቅሖ ጉድጓዳኸፍታ* | *ለተቸገረ ትሰጣለች ቀፎ ከፍታ* |
| *ኣይራኣናይ ስብኣያ ትሓታ* | *ባልም ለምን ኣላላትም* |
| *ማኣዚ ሃምበሊያ ድዓመታ* | *ካመት በኋላ ቢከፈል ግድ የላትም* |
| *ድፎታውኣ ታብልዕ ፈትታ* | *ለወደደችው ታበላለች ፈትፍታ* |
| *ድፀላእኣለ ያ ሃምጨለውታ።* | *ለጠላችው ተላላፊ በሽታ* (ደጋፌ፣ 2001 ዓ.ም. 324) |

**መልቀስ ለወልዱ ፈርዳ፡-** ወልዱ ፈርዳ፤ በኣምስት ዓመቱ የተጋድሎ ዘመን ጣልያን ሁለት ወንድሞቻቸውን ኣፍኖ ወስዶ ገደለባቸው። ወልዱም ከጓደኞቻቸው በመምከር ጣልያን ሰራዊት ላይ ጥቃት ለመፈፀም ተስማሙና እለተ ዓርብ መነሻ ቀን እንዲሆን ተስማሙ።

እንሂድ ሲሏቸው ግን ጓደኞቻቸው አንሄድም፣ ሓሳባችንን ቀይረናል አሏቸው። **ወልዱ** ግን ብቻቸውን ሜካ ገቡና በአካባቢው ወደነበረው የጣሊያን ሰራዊት አዛዥ ግጠም ብለው ላኩበት። ሰውየውም አድብተው በመጠበቅ የቦታ መሪ ሆኖ የመጣውን ጭቃሹምና አራት ጣሊያናውያንን ገድለው ራሳቸውን ገደሉ። በቀብራቸውም እንዲህ ተለቀሰላቸው፤

*ሰብኢይዶ ርኢኹም ኩርፋ መሳይ*
*ሃምደበና ጥሪ መዕበስበሳይ*
*ሃም ንህቢ መስከረም ፀውዑ ተናኻሳይ*
*ብወሸል ትገብኦም ሃም ሓራሳይ*
*ብማእኸል ትገብኦም ሃም ሓማሳይ*
*ኻልእማ ምሕሉ ተመሳሳይ*
*ጓሓት ዓርቢ ማዕተቡ ቓንጣሳይ*
*ወጨፎኻ ድጭቃ መሳሳይ*
----------------------
*ሓሙሽተ ቓትሉ ኩያ ባዕሉ ሻድሻይ*
(ደጋፊ፣ 2001 ዓ.ም. 375-6)፡፡

*ኢየችሁት ወይ ያንን ፋንጋ መሳይ*
*እንደጥር ዳመና ሄደት መለስ*
*እንደመስከረም ንብ ደርሶ የሚናከስ*
*መም ጠብቀህ እንዳአራሽ*
*መሃል ትገባለህ እንደ ዋናተኛ*
*ሌላ ምሎ ይመለሳል*
*ዓርብ ማለዳ ማተቡን ይበጥሳል*
*ወጨፎህ በጭቃሹም ይቃመሳል*
--------------------------
*አራት ነጭ ገድሎ በራሱ ይጨርሳል።*

በዚህ ግጥም እንዲጎሉ የተፈለጉ ነጥቦች አሉ። አንዱ ነጥብ ጀግንነት በመልክ እንደማይገለፅና ከመልከመልካምነት ግንኙነት እንደሌለው ማሳየት ነው። ወልዱ ምንም እንኳን መልከጥፉ ቢሆኑ በተለያዩ ጊዜያት በጠላት ላይ ድል የተቀዳጁ ሰው እንደነበሩ ያስረዳል። ሰውየው ሽሽትን አይወዱም። ይልቅ እንደጥር ዳመና በጠላት ምሽግ ዙሪያ መለስ ቀለስ የሚሉ ጀግና ነበሩ።

ተናዳፊ አጥቂ እንደነበሩም ተግባራቸው ከመስከረም ንብ ጋር እየተነፃፀረ ቀርቧል። የመስከረም ንብ በቂ ምግብ ስለሚያገኝና አካባቢው በአበቦች መአዛ ስለሚታወድ ሌላ ጊዜ ካልተጠጉትና ቀፎውን ካልነኩት በቀር ጉዳት የማያደርሰው ንብ መስከረም ላይ አድኖ ነው የሚናደፈው። በርሀም ከሌላው ጊዜ ንብ ሳይሆን ከመስከረም ንብ ጋር ነው የተነፃፀሩት። በተጋሩ ዘንድ ጀግንነት በብዙ መንገድ ነው የሚገለፀው። በድፍረት፣ በአሰላለፍ (የማጥቂያ አቅጣጫ)፣ በእምነት ፅናት፣ እና በምት ሊገለፅ ይችላል። ጀግና የተባለው ሰውም እነዚህን የጀግንነት መስፈርቶች ስላሟላ የጀግኖች ጀግና ሊባል ችሏል፡፡ ነባሩም ሆነ አዲሱ ትውልድ ይህንን ግጥም ሲያነብ 'ጀግና' የሚያሰኙ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ በሚገባ ይገነዘባል። ጀግናው በወራሪው የጣሊያን ወታደሮችና በመሪው ጭቃሹም ላይ አደጋ ከጣለ በኋላ አልተደበቀም። ምክንያቱም እሱ ሸሽቶ ካመለጠ ሌላውና ንፁሁ ህዝብ እንደሚጨፈጨፍ ያውቃል። ስለዚህ የሚቆችን ደም ተበቅሎ ለኗሪዎች ህይወትም መድህን

ለመሆን ራሱን አጥፍቷል። ስለዚህ ግጥሙ በወቅቱ የሰውየውን ጀግንነት ለማወደስ የቀረበ ቢሆንም ምን ምን ተግባራት ያከናወነ ጀግና እንደሚባል ለማስተማርም አገልግሏል።

ተተኪው ትውልድ ፈሪ የሚባለው እንዴት ያለ እንደሆነና ሕብረተሰቡ ፈሪን እንዴት እንደሚጠየፈው ከሚደረደሩት ግጥሞች እንዲያውቅ ይደረጋል። ለምሳሌ አንድ ሰው ዘመቻ ሄደው አንዲትም ጥይት ሳይተኩሱ በመመላሳቸው እንዲህ ተብሎላቸው ነበር።

| | |
|---|---|
| *ካሕሳይ ጉማ ኣታ ካሕሳይ ጉማ* | *ካሕሳይ ጉማ ኣንተ ካሕሳይ ጉማ* |
| *በቕልኻ ትመልሳ ደኸማ* | *በቅሎህ ተመለሰች ደክማ* |
| *ጠበንጃኻ ኣትዋ ብልጉማ።* | *ጠመንጃህም ኣለች ጥይቷን ቅማ* (ደጋፊ 2001 ዓ.ም.)። |

ተጋሩ፣ ጀግናውንም ፈሪውንም በግጥም ሲገልፁዋቸው ኣይተናል። በሌላ በኩል ጀግነትም ፍርሓትም በዘር እንደማይወረስና ግላዊ ባህሪ እንደሆነ ለማመልከት ቀጥሎ የሚቀርበውን ኣይነት ተረትና ምሳሌ በማቅረብ እምነታቸውን ለማስረፅ ጥረት ያደርጋሉ።

**ሕማቕ ንፋዕ እንተወለደ ተቐለተ፤ ንፋዕ ሕማቕ እንተወለደ ተዘምተ** (ሞገስ፣ 1958፡7)። ተረትና ምሳሌው፣ ጀግንነት ምን ያህል ኣኩሪ ተግባር እንደሆነ ነው የሚያመለክተው። ሰነፍ ወይም ፈሪ ሰው ጀግና ከወለደ፣ ትልቅ ካሳ እንደተከፈለው፤ ጀግና ፈሪ ከወለደ ግን መላ ንብረቱ እንደተዘረፈ እነደሚቆጠር ያስረዳል። በኣጠቃላይ ጀግንነት ክብር ነው የሚል መልእክት ያስተላልፋል።

**ኣገር በቀል ሕግ (ሕጊ ገረብ)**፡- በተጋሩ ዘንድ 'ገረብ' የሚለው ቃል ቤተሰብነትን፣ ኣንድነትን፣ የኣገር ልጅነትን የሚያመለክት ፍቺ ኣለው። የራስ ወገን ያልሆነን ወይም የማይዛመድን ሰው ለመግለፅም ያገለግላል፤ **ስግር ገረብ** (ከወንዝ ወዲያ የሆነ) በማለት ይጠሩታል። ስለዚህ **ሕጊ ገረብ** ማለት የኣንድ ኣካባቢ ሰዎች ተስማምተው፣ መተዳደሪያችን ይሁን ብለው የሚፀድቁት፣ ከዚያ ውጪ ለሆኑ ሰዎች ግን የማያገለግል ህግ ማለት ነው (Gebru, 1996)። በተለያዩ የትግራይ ኣካባቢዎች **ሕጊ እንዳ ኣባ** እየተባለም ይጠራል። (ከትውልድ ወደትውልድ) እየተወራረሰ የመጣና የማሕበረሰቡ ኣባላት እየተቀባበሉ የሚዳኙበትና ደህንነታቸውን የሚያስጠብቁበት ህግ የሚል ፍቺ ኣለው።

ተጋሩ የህግ የበላይነትንና ለህግ መገዛትን የሚያውቁት ከዘመናት በፊት ነው (ገብረፃዲቕ፣ 1995 ዓ.ም.)። በቃላዊ ህብረተሰብ ውስጥ ሕግና ደንብ የሚገኘው ደግሞ የቃላዊ እውቀት መግለጫና ማስተላለፊያ በሆኑት ስነቃሎች ውስጥ ነው። የተጋሩ ኣገር በቀል ህግ

የሚገኘውም በተረቶቹ፣ በምሳሌዎቹ እና በመሳሰሉት ውስጥ ነው። ትግራዋይ፣ ህጋዊ መስመር የያዘ ሁሉ ትክክል ነው ብሎ እንደሚያምንና ከህግ ውጪ የሚፈፀም ሁሉ ደግሞ ጥቃት በመሆኑ እንደሚያንገበግበው በሚከተለው መንገድ ተጠቁሟል።

| | |
|---|---|
| *ካብታ ብፍርዲ ዝተወስደት መሬተይ፣* | *በፍርድ ካጣኋት መሬቴ* |
| *ብሓይለመልጢ ዝኸደት ቆርበተይ።* | *በሃይል የተወሰደች ቁርበቴ* |

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሕብረተሰቡ በሃይል የተፈፀመን ነገር ከቀጥተኛ ጥቃት ጋር እንደሚያመሳስለውና እንደማይቀበለው ተጠቁሟል። ተጋሩ ህግንና ህጋዊነትን ሲያከብሩ ፍትሃውያን ሰዎችንም ያደንቃሉ። ለምሳሌ የሚከተለው ግጥምም ራእሲ ኣሉላ ኤርትራን ያስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ ላሳዩት ሃቀኛና የማያዳላ ፍርድ የቀረበ መወድስ ነው (ሞገስ፣ 1958 ዓ.ም.)።

| | |
|---|---|
| *ዳጉሻ ከምቆላ* | *ዳጉሳ እንደቆላ* |
| *ጣፍ ከምተኸላ* | *ጤፍ እንደተኸላ (ተቦታ ስም)* |
| *ክፍሊ ከምሓበላ* | *ክብት እንደ ሓበላ (ተቦታ ስም)* |
| *ዕድቂ ከምላሊበላ* | *ዕድቅ እንደላሊበላ* |
| *ፍትሒ ከምኣሉላ።* | *ፍትሕ እንደ ኣሉላ።* |

በህብረተሰቡ ዘንድ ዳጉሳ የሚበቅለውና ጥሩ ምርት የሚሰጠው በቆላ መሬት እንደሆነ ሁሉ ለክብትም ተስማሚ ቦታ ኣላቸው። በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ደግሞ ንጉስ ላሊበላ የሚያስቀና ተግባር እንደፈፀመና በዚህ ተግባሩ ፃዲቅ እንደተባለ ይታወቃል። ራእሲ ኣሉላም በፍትሓዊነታቸው ተወዳጅ እንደነበሩ ያሳያል። በዚህ ግጥም የተንፀባረቀው ሓቀኝነት ብቻ ሳይሆን የኣገር በቀል እውቀት መገኛ የሆኑት ተፈጥሮ፣ ሰው፣ ፈጣሪ እና የሰው ልጅ ምርቶችም ጭምር ናቸው (Grenier, 1998; LittleBear, 2009; Msuya, 2007; Ossai, 2010; Semali and Kincheloe, 1999)። እነዚህ የሁሉም ነገር ምንጮች ስለሆኑ በኣገር በቀል ህዝቦች ዘንድ ተነጣጥለው ኣይታዩም፤ ህብረተሰቡ የህግና ፍትህ ኣስፈላጊነት በተረትና ምሳሌም ይገልፀዋል፤ በሚከተለው መንገድም ወደቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ጥረት ያደርጋል።

- **ሃፀይ እንድሕርሞቱ ኣብመን ይማጎቱ፡፡** (ህግ ከሌለ ፍትህ ኣገኛለሁ ብሎ መከራከር ዋጋ የለውም)።

'ሃፀይ' በህብረተሰቡ ዘንድ ንጉስ ወይም መሪ የሚለውን ይተካል፡፡ ህግ ወይም ፍትህ የሚል ፍቺም አለው። አንድ ሰው በሌላ ግለሰብ ወይም ቡድን ጥቃት ሲደርስበት ወይም ጥቃት ሲቃጣበት ዝባን ንጉስ፣ ዝባን ሕጊ (በህግ፣ በንጉስ አምላክ) በማለት ይገዝታል። ሰዉ በሰላም ውሎ የሚገባው የሕግ ጥላ ሲኖር ብቻ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ንጉስ ወይም ህግ ከሌለ ግን መጠፋፋት እንጂ በሰላም ውሎ ማደር ሰርቶ መብላትና ሃብት ማፍራት አይታሰብም።

- **ንጉስ ዘይሓዝካሉ አይንብረትካ፣ እዝጊ ዘይሓዝካሉ አይህይወትካ።** (መንግስት የሌለበት ንብረት፣ ፈጣሪን የካደች ህይወት አንድ ናቸው።)

በዚህ ተረትና ምሳሌም ተመሳሳይ መልእክት ነው የተላለፈው። ንብረት ማፍራትና ያፈሩትን ንብረት የኔ ነው ማለት የሚቻለው ህግ ሲኖር ብቻ ነው። ካልሆነ ግን በማንም ሰው ሊዘረፍ ይችላል። ህልውና የተመሰረተው ደግሞ በፈጣሪ ሃይል ነው። አለሁ ማለት የሚቻለው በፈጣሪ ላይ እምነት ሲጣል ነው። መንግስት አልባ ሃብትና እምነት አልባ ህይወት የሚያስመካ አለመሆኑ ነው የሚያስረዳው።

- **ዳኛ ዘይብሉ ነገር ጥፉእ፣ ማሕለኻ ዘይብሉ ፀባ ድፉእ**

ዳኛ የሌለው ሙግት ዋጋ አልባ እንደሆነ ሁሉ መሞደሪያ (ጋዲ) የሌለው ወተትም መደፋቱ እንደማይቀር ይገልፃል። ስርዓት የሚያስጠብቅ ሃይል ከሌለ በሃይልና በኣመፅ መመራት ይከተላል። ሓቅ ይዞ ቢከራከር እንኳ ሓቀኛነቱን የሚያይለት ኣያገኝም። ቢበደልም ሰሚ ኣያገኝም። በኣጠቃላይ ህግና ደንብን የሚያስከብር ሓይል ከሌለ ተከራክሮ መብትን ማስከበር ኣይኖርም። ያለመሞደሪያ የሚታለብ ወተት መደፋቱ ኣይቀርም። እንደእንደወተቱ ሁሉ ማንኛውም ምርትም በኣግባቡ ካልተያዘ በስርዓትና በወግ ካልተሰበሰበ ኣምራቹ የምርቱ ተጠቃሚ ሊሆን ኣይችልም የሚል መልእክት ኣለው። በሁሉም ተረትና ምሳሌዎች ሌሎች ጉዳዮችም በንፅፅር የቀረቡ ቢሆንም በዋናነት ትኩረት የተሰጠው ግን የፍትህ አስፈላጊነት ነው።

ኣገር በቀል ህግና ደንቦቹ በተረትና ምሳሌዎች ውስጥ እንደሚገኙ ቢጠቆምም በዚሁ የተገደቡ ናቸው ማለት ኣይደለም። አሁን ስራ ላይ እንዳለው የወንጀለኛና የፍትሓብሄር ህግ ሁሉ በተለያዩ ኣካባቢዎች ራሳቸውን ችለው እያገለገሉ ነበረ። አሁንም በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ለኣብነት ያህል በምስራቃዊ ዞን ወይም በድሮ የዓጋመ አውራጃ ኣካባቢ ይሰራበት የነበረ **'ጥንታዊ ስርዓት ኣብዕሊኸን ሓሪሻይን፡ ስርዓት ፍትሓብሄርን ወግዒ ባህሊን'** (በዕሊኸና ሓሪሻይ ጊዜ የፍትሃብሔር ስርዓትና ወግና ባህል ህግ) የሚል ርእስ ያለው ህግ

ነበረ (ገብረፃዲቅ፡ 1995 ዓ.ም.)። ሕጊ ገረብ በራያ አሁንም እየተሰራበት ያለ ቃላዊ ሕግ ነው።

ህሕጎቹ በውስጡም ከስርቆትና ስድብ እስከ ነፍስ ማጥፋት ወንጀል ለሚደርሱ ጥፋቶች ተመጣጣኝ ቅጣይተ አስቀምጠዋል። በፍትሓብሄር ለሚያስጠይቁ ግድፈቶችም መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን ዘርዝረዋል።

ምንም እንኳን አውሮፓውያን የኋላ ቀርነት መግለጫ ነው ቢሉትም (Grenier, 1998; Semali and Kincheloe, 1999) አፍሪካውያን የኛ የሚሉት እውቀትና እንደተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ተረትና ምሳሌ የመሳሰሉ የእውቀቱ ማስተላለፊያ ዘዴዎች አሏቸው። እውቀቱን በማስተላለፉ ስራም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሓላፊነት እንዳለበት አውቆ ድርሻውን ይወጣል። ከላይ እንደተመለከተው እውቀትን ለማስተላለፍ ቋንቋ በግንባር ቢጠቀስም ምልክቶችና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችም በማስተላለፊያነት አገልግለዋል።

በዚህ እውቀትን የማስተላለፍና የማስተማር ስራ ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ተቋማቱ ተደጋጋፊ አስተዋፅኦ ያላቸው። ሕብረተሰቡ በማስተማሪያነት የሚጠቀምባቸው ስልቶች አጓጉና አዝናኝ በመሆናቸው እውቀቱ አንፃራዊ ዘላቂነት ይኖረዋል። በዚህ ቃላዊ የማስተማር ሂደት አንዱ ትውልድ ለሌላው ስነምግባርን ያስተምራል፡፡ ሙያን ያወርሳል። ሁሉም የማሕበረሰቡ አባላት አንድ ዓይነት ሙያና እውቀት ይኖራቸዋል ማለት ግን አይደለም፡፡ እያንዳንዱ ሙያ የኔ ብሎ የሚይዘው ሰው እንደሚፈልግ ጠንቅቆ ይገነዘባል። ግንዛቤውንም በተረትና ምሳሌና በሌሎቹ ስነቃላዊ ሃብቶች አማካይነት ይገልፀዋል። የማህሕበረሰቡ አባላትም እንደየፍላጎታቸውና የሰለጠኑበት ሙያ በተለያየ የስራ መስክ ተሰማርተው ኑሯቸውን ሲመሩ ይታያል።

ለምሳሌ ትግራዋይ ሕብረተሰብ ራሱንና እንስሳትን የሚያክምበት እውቀት እንዳለው ታይቷል። የራሱንና የአካባቢውን ንፅህና በመጠበቅ በሽታ የሚከላከልበት እውቀት እንዳለውም ታይታል። አካልንና አእምሮን የሚያዳብሩ ጨዋታዎች፣ ነገሮችን በትክክል መለካት ወይም መስፈር የሚችሉ መሳሪያዎችና ተግባራቱን የሚገልፅ ቋንቋ እንዳለው ተመልክቷል። የወቅቶችን ሁኔታ የሚገልፁ፣ ህፃናት ደፋርና ልበሙሉ ሆነው እንዲያድጉ የሚያበረታቱ ስነቃላዊ አገላለፆች እንዳሉትም የቀረቡት ኣብነቶች ያረጋግጣሉ። በአገር ወይም በአካባቢ ደረጃ የተለያየ ጀግንነታዊ ተግባር የፈፀሙ ሰዎችን በዘፈን፣ በሙሾ፣

በፉከራና ሽለላ ያወድሳል። አድማጪም ተመሳሳይ ክብርና ማሕበረሰባዊ ተቀባይነት ለመግኘት ሲል የጀግኖቹን አብነት ለመከተል ይነሳሳል። እንዲሁም በህብራተሰቡ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ግምት ውስጥ ያስገባና እያንዳንዱ ሰው የራሱንና የሌላውን ደህንነት ጠብቆ እንዲሄድ የሚያስገድድ የህግ እውቀት እንዳለው ታይቷል።

ከቀረቡት አብነቶች ትግራዋይ ሕብረተሰብ የኔ የሚላቸውና ጠቃሚ የሆኑ በርካታ እውቀቶች እንዳሉት መገንዘብ ይቻላል። እነዚህ እውቀቶችና የማስተማሪያ ስልቶች አሁን ስራ ላይ ባለውና በመደበኛው የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ውስጥ ተካትተው ከሆነ የበለጠ ጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል።

## 1.2. ጥናቱን ያነሳሱ ችግሮች

ብዙ ሰዎች በተለይም የእድሜ ባለፀጋ አያቶችና ወላጆች፡- ወጣቱንና በመካከለኛ እድሜ ውስጥ ያለውን ትውልድ ሲኮንኑት፤ አካባቢያዊ እውቀትን እንደ አለመሰልጠን የሚቆጥር፤ የባእዳን ባህልና እውቀትን የሚያስተጋባ፤ በራሱ ባህልና እውቀት የሚያፍር፤ ለራሱ ቋንቋ ያለው ክበሬታና በቋንቋው ላይ ያለው ዕውቀትና ክህሎት ዝቅ ያለ፣ እንደሆነ ሲናገሩ ይሰማል፡፡ "የፈረንጅን እንጂ የራሱን ባህል አያውቅም፤ እድሜን፣ ደረጃንና ግንኙነትን መሰረት ያደረገ የቋንቋ አጠቃቀም አያውቅም፤ ወይም መገልገል አይፈልግም፤" እያሉም ይተቹታል፡፡ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰውም ወጣቱ የምዕራቡ ዓለም ናፋቂ ትውልድ መሆኑ ነው።

በእርግጥ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በተለያየ መንገድ ይንፀባረቃሉ። የጥናቱ አቅራቢም አብዛኞቹ ችግሮች መኖራቸውን እገነዘባለሁ። በምክንያቱ ላይ ግን አልስማማም። በመጀመሪያ ችግሩ ከምዕራቡ አለም ባህል ናፋቂነት የመጣ ለመሆኑ ማረጋገጫ የለም። ወጣቱ፤ ከማህበረሰቡም ሆነ ከትምህርት ቤት በቂ ግብአት ስለማግኘቱም የተረጋገጠ ነገር የለም። የቅኝ ገገርዎች ተፅእኖ፣ የኣውሮፓውያን ስልጣኔ እና የኣለም ኣቀፋዊነት ኣስተሳብ (Globalization) ስለተጫኑነውና ኣውሮፓውያን፤ የኣፍሪካ ኣገር በቀል ዕውቀት የኣህጉሪቱን እሴቶችና ህዝቡ ለዘመናት ያከማቸውን እውቀት ለማስተላለፍ የሚያገለግል መሳሪያ ስለመሆኑ መናገር ጊዜ ማባከን እንደሆነ ስለሚያሳምኑት እንደሆነና በዚህ ምክንያት ቸል ስለሚለው ወደ ምዕራባውያኑ ዕውቀት ስለሚያደላ እንደሆነ የሚያምኑም ኣሉ (Zulu, 2006; Banda, 2008)።

ዓለምአቀፋዊነት ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ገፅታዎች (Banda, 2008:81) ሲኖሩት የኢኮኖሚው ዓለምአቀፋዊነት ዋነኛ ተዋንያን የተለያዩ ጥሬ እቃዎች እጥረት ያጋጠማቸው በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ ኩባንያዎች ናቸው። ባህላዊ ዓለምአቀፋዊነት (cultural globalization) ደግሞ አገር በቀል ዕውቀትንና አገር በቀል ቋንቋን ለመሸርሸር ያለመ ግንኙነት ነው። ባህላዊ ዓለም አቀፋዊነትም ከቅኝ ግዛት ማስፋፋት ምንጭ የተቀዳ መነሻና ዓላማ ነው ያለው። ቅኝ ገዢዎች አገር በቀሎቹን ከባህላቸው ከመሬታቸውና ከቋንቋቸው እንዳፈናቀሏቸውና ቅርሶቻቸውን እንደዘረፏቸው ሃብታም ባህላቸውን እንደበረዙባቸው ሁሉ ዓለምአቀፋዊነትም በአገር በቀል ዕውቀት ላይ ተመሳሳይ ተግባር ለመፈፀም ያለመ ድብቅ አጀንዳ ነው። የወጣቱ የአገር በቀል ዕውቀት ግንዛቤ ዝቅ ያለውም በዚሁ የዓለም አቀፋዊነት ጫና ምክንያት እንደሆነ የሚጠቅሱም አሉ (Banda, 2008)።

እኔም (የዚህ ጥናት አቅራቢም) ዓለምአቀፋዊነት እንደችግር ሊነሳ አይችልም የሚል አቋም የለኝም። ቅኝ ግዛትም ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ። አብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች በተለያዩ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ስር የነበሩ እንደ መሆናቸው የትምህርት አቅጣጫቸውም በቅኝ ገዢዎች አስተሳሰብና ፍልስፍና የተበረዘ ነው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያ ግን ቅኝ ተገዢ ካልነበሩ ጥቂት የአፍሪካ ሃገራት አንዷ ስለሆነች ከቅኝ ገዢዎች የወረሰችው ስርዓተትምህርት የላትም። በተለይ በአሁኑ ጊዜ ቋንቋው ብሄራዊ ጫና አለበት የሚያስብል ሁኔታም የለም። ምክንያቱም ከ1987 ዓ.ም. ወዲህ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ተስማሚ ሆኖ ባገኙትና በመረጡት ቋንቋ የመማርና ባህላቸውን የመግለፅና የማሳደግ መብት ተጎናፅፈዋል። የደርግን ስርአት ለመጣል ሲታገሉ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች (በተለይ ህወሓት) በትግርኛ ቋንቋ ማስተማር፣ ሰዎችን በተለያዩ ሙያዎች ማሰልጠን፣ የትምህርት መሳሪያዎችንና የማሰልጠኛ ጽሑፎችን (ማንዋሎችን) ማዘጋጀት ችለው ነበር። ስለዚህ በተለይ በትግሉ ወቅት የትግርኛ ቋንቋ ሰፊ ግልጋሎት ይሰጥ እንደነበረ ይታወቃል። በትግራይ ክልል መርሃትምህርቶች፣ የመማሪያ መፃህፍትና የመምህሩ መምሪያ የሚዘጋጁት በክልሉ የስርዓተትምህርት ባለሙያዎች አማካይነት ነው። አዘጋጆቹም የማህበረሰቡ አባላትና በቋንቋው አፍ የፈቱ ናቸው። የማህበረሰቡን ዕውቀት የተሸከሙ ተረትና ምሳሌዎችን፣ ተረቶችን፣ ፉከራዎችን፣ ሙሾዎችን፣... በመሳሪያነት በመጠቀም የተፈለገውን ዕውቀትና ቋንቋ ወደተማሪዎች ማስተላለፍ ስለመቻላቸው ግን በእርግጠኝነት መናገር

አይቻልም። ስለዚህ እነዚህ የቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች ኣገር በቀል እውቀቱንና ቋንቋውን ማስተማር ችለው ይሆን? የሚለው ጥያቄ አንዱ ኣነሳሽ ምክንያት ነው።

ሁለተኛው ኣነሳሽ ምክንያት ተማሪዎቹ ኣፋቸውን ለፈቱበት ቋንቋ ያላቸው ኣተያይ ነው፡፡ በትግርኛ ቋንቋ ኣፋቸውን የፈቱና ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ብሎም ዩኒቨርሲቲ ገብተው ቋንቋውን የሚያጠኑ ልጆች ከሚማሯቸው የትምህርት ኣይነቶች ይበልጥ ይከብደናል የሚሉት የትግርኛ ቋንቋ መሆኑን መምህርም ኣማካሪም ሆኜ መታዘብ ችያለሁ። ስለባህላዊ ህክምና ወይም ጨዋታ፣ ስለእፀዋት፣ ስለእርሻ የሚያወሳ ጉዳይ አንስቶ ለመወያየት ያላቸው እውቀትም በጣም ዝቅተኛ ነው። የዚህ ችግር ምክንያትም ተማሪዎች በክፍል የሚቀስሙት እውቀት /ክህሎት በቋንቋው ለመገልገል ስለማያበቃና የተማሪዎቹን ልምድና ኣገር በቀል እውቀት መነሻ ስለማያደርግ ሊሆን ይችላል። እውቀቱ የሚመነጨው ከህብረተሰቡ ቢሆንም በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ወደሚገኝ ህፃን ሊደርስ የሚችለው በስርዓተትምህርቱ ውስጥ የተካተተ እንደሆነ ነው። ስለሆነም ስርዓተትምህርቱ፤ (መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሃፍና የመምህር መምሪያ) የተተኳሪውን ህብረተሰብ ሃገር በቀል እውቀት ማስረፅ መቻል ኣለመቻሉን መፈተሽ አስፈላጊና ወቅታዊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 1.3. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ጥናቱ- በትግራይ ክልል የሚገኘው የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህብረተሰብ ኣገር በቀል እውቀት፤ በክልሉ በሚዘጋጀው የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት (መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሃፍና የመምህር መምሪያ) ውስጥ ተካቷል ወይ? ለሚለው ዐቢይ ጥያቄና ከዐቢዩ ጥያቄ ለመነጩና ቀጥሎ ለቀረቡት ሶስት ዝርዝር ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፤

ሀ. በስርዓተትምህርቱ ውስጥ ኣገር በቀል እውቀትን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎች ቀርበዋል?

ለ. ትግራዋይ ህብረተሰብ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች ኣገር በቀል ናቸው ብሎ ያምናል?

ሐ. ለመለማመጃነት የቀረቡት ተግባራትና ክንውኖች (መልመጃዎች፣ የቡድንና የጋራ የፕሮጀክት ስራዎች) የቀረቡት ኣገር በቀል እውቀትን ማዳበር በሚያስችል መንገድ ነው?

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ጥናት የሚካሄድባቸው መፃህፍት የተዘጋጁት ገና ከቤት ለሚመጡና በማህበረሰቡ መሃል በማደጋቸው ምክንያት ያገኙትን ኣገር በቀል ዕውቀት ይዘው ወደ ኣዲሱ ዓለም (ትምህርት ቤት) ለሚመጡ ህፃናት ነው፡፡ ከኣንደኛ እስከ ኣራተኛኛ ባሉት የክፍል ደረጃዎች ለሚማሩት ህፃናት የሚዘጋጁት ስርዓተትምህርቶች፤ ህፃናት ከቤት ይዘውት የመጡትን የማህበረሰብ እውቀት መነሻቸው ሊያደርጉ ይገባል። ቀዳሚውን እውቀት መነሻ ማድረግ ማለት ህፃናቱ ከሚያውቁት ነገር በመነሳት ኣዳዲስ እውቀቶች/ ክሂሎች መጨመር ማለት ነው። ይህ ኣይነቱ ኣደረጃጀት፤ ህፃናቱ ከትምህርት ቤት የሚያገኙት እውቀት ቀድሞ ከሚያውቁት ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ መማርን ያቀላጥፉል። እንዲሁም እውቀት/ ክህሎት ተያያዥነት ባለው መንገድ (ሳይበጣጠስ ) መገንባት ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

ኣገር በቀል እውቀት፤ ትውልዶች ለዘመናት ያከማቿቸውን በርካታ ውስብስብና ጥልቅ እውቀቶችን የሚገልፅ ፅንሰሃሳብ ነው። በኣንድ ኣካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ በሚንቀሳቀስበት የስራ መስክ፣ በማህበራዊ ግንኙነት፣ በእምነት ቦታና በእለትተእለት ግንኙነት ውስጥ ሁሉ ይገለፃል። ከምርት፣ ከጤንነት፣ ከኣስተዳደር፣ ከተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ከእንስሳት ርባታ ጋር የተያያዙ እውቀቶች ኣሉ። ከኣፈር ጥበቃ፣ ከኣየር ሁኔታ፣ ራስን ከመመገብ፣ ራስን ከተፈጥሮ ጋር ኣስማምቶ ከማኖር ጋር የተያያዙም ኣሉ።

ኣንዳንድ ዕውቀቶች በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚታወቁ፣ በምሥጢር የሚያዙና በተግባር (በክወና) ካልታዩ በቀር ለመገንዘብም ሆነ ወደቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስቸግሩ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ሁሉም የማህበረሰቡ ኣባላት የሚያውቋቸው ሆነው ኣውዶችን ጠብቀው በቃል የሚቀርቡ ናቸው።

ይህ ጥናት ከላይ የተዘረዘሩትን ዕውቀቶች ሁሉ ለመመርመር ኣይሞክርም። የጥናቱ ትኩረት፤ ለኣፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያነት በተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ በቀረቡት የተጋሩ እውቀቶች/ ክሂሎች ላይ ብቻ ነው። በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የሚገኙት ይዘቶች ምን ያህል የማህበረሰቡን እውቀት ለማስተማር እንዳገለገሉ ወይም ህፃናቱ ከቤት ይዘውት የመጡትን ዕውቀት በመነሻነት ተጠቅመው ተጨማሪ ዕውቀት እንዲያገኙና ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማገዝ መቻላቸውን መፈተሽ ነው። የይዘት ትንተና የተካሄደውም ለኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን በተዘጋጁ የትግርኛ ቋንቋ መርሃትምህርቶች፣ የተማሪ መፅሃፍና

የመምህር መምሪያዎች (ስርዓተትምህርቶች) ላይ ብቻ ነው። ከዚህ አልፎ ጥናቱ በነዚህ ስርዓተትምህርቶች ውስጥ ያሉ ይዘቶችን አደረጃጀትና መጣኝነትን አልገመገመም። እንዲሁም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የኩናማና የኢሮብ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርአተትምህርቶችን አልፈተሸም።

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች ውስጥ አገር በቀል እውቀት የየትኛውም እውቀት መሰረት ነው ማለት ይቻላል። አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ፊደል ያልቆጠረ በመሆኑ ግንኙነቱ ቃላዊ ነው። እምነቱን፣ ፍልስፍናውን፣ ፖለቲካዊ አቋሙን፣ በግብርና ስራ በጤናና በመሳሰሉት ላይ ያለው ግንዛቤ የሚገልፀውና ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፈው በቃል ነው። የአገር በቀል እውቀት ማስተላለፊያ ዘዴዎች በርካታ ናቸው። ለምሳሌ ያህል ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን፣ ሙሾዎችን፣ ዘፈኖችንና የመሳሰሉትን የስነቃል ተዋቃሪዎች መጥቀስ ይቻላል። ህፃናት ከላይ በተዘረዘሩትና በሌሎች መሳሪያዎች አማካይነት አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡና ስለአካባቢያቸው እንዲያውቁ ይደረጋል። በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርአተትምህርት ዋነኛው የአገር በቀል እውቀት ማስተማሪያ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። የአገር በቀል እውቀት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ከመማር በላይ ነው። በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የቋንቋውን የድምፅ ስርአት፣ የቋንቋውን መዋቅር፣ ቃላትና ፍቺዎቻቸውን አውቆ ለመገልገልና የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ ለመግባባት ያስችላል። አንድ ህፃን አፍ በፈታበት ቋንቋ ስለተማረ ብቻ የህብረተሰቡን አገር በቀል እውቀት ተምሯል ብሎ መደምደም ግን ያስቸግራል። አንድ የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ አገር በቀል እውቀትን የማስተማር አቅም እንዲኖረው ከተፈለገ ገና ከስርዓተትምህርቱ ቀረፃ ጀምሮ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዘጋጅ ይገባል። የህብረተሰቡ ዋና ዋና እውቀቶችን ለይቶ ማውጣትና መገለጫዎቻቸውን ማወቅ ያስፈልጋል። ይዘቶቹን እንደየክብደት ቅለታቸው በጊዜና በክፍል ደረጃ መሰረት ማዋቀር ያስፈልጋል። በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ስርአተትምህርት ላይ የተካሄደው ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊያስገኝ እንደሚችል ይገመታል፤

- መካተት የሚገባቸው አገር በቀል እውቀቶችን ያካተተ የቋንቋ ስርዓተትምህርት ለማዘጋጀት ያግዛል።

- አዲሱ ትውልድ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ጠቃሚ አስተሳሰቦችን፣ ባህሎችን፣ አተያዮችን፣ የአካባቢ ጥበቃ ስልቶችን፣ አገር የመውደድና የመጠበቅ ፋይዳዎችን፣ እሴቶችን ተገንዝቦ እንዲያድግ ያግዛል።

- የምዕራባውያን እውቀት በራሱ ጉጂነት ባይኖረውም ከራስ እውቀት ተነስቶ የሌሎችን እውቀት መጨመር እፀና መሰረት ላይ ቤት እንደመገንባት የሚቆጠር መሆኑን አውቆ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ፤ የቋንቋና የባህል ባለሙያዎች ደግሞ በተለይ ኣገር በቀል እውቀትን በመሰብሰብ፣ በማስተዋወቅና በመጠበቅ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ሊያነሳሳ ይችላል።

- አገር በቀል እውቀትን መገንባትና ማስተዋወቅ ማለት የሌሎችን ማንነት መቀበልና ማድነቅ ማለት መሆኑን ሊያስገነዝብ ይችላል።

- ኣገር በቀል እውቀት ሰፊ ፅንሰ ሃሳብ ነው። ይህ ጥናት ከቋንቋ መማር ማስተማር ጋር የተዛመደውን ግልጋሎት ብቻ ነው የዳሰሰው። በማህበራዊና በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ውስጥ ምን ድርሻ እየተጫወተ እንዳለ ወይም መጫወት እንዳለበት ማጥናት ለሚፈልጉ ወገኖች በመነሻነት ሊያገለግል ይችላል። የግብርና፣ የህክምና፣ የፍትሕ፣ የታሪክ ባለሙያዎችም ከየሙያቸው ኣያይዘው ቢያጠኑት በርካታ ጠቀሜታዎች ሊያስገኝ ይችላል።

- ይህ ጥናት በትግራይ ውስጥ እየተሰራባቸው ባሉ የኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ስርዓተትምህርቶች ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ ውጤቱ መላውን ኣገር በቀል ህብረተሰብ፣ ተማሪዎችን፣ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ሊያረካ እንደሚችል ይገመታል።

- ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ የሌሎች የትምህርት ዓይነቶች መምህራንንና ተማሪዎችን ሊያነቃቃ፣ ተመራማሪዎችን ለጥናት ሊያነሳሳ ይችላል። ህብረተሰቡም ኣገር በቀል ቋንቋውን ብቻ ሳይሆን ኣገር በቀል እውቀቱንም በቋንቋው ውስጥ ገብቶ እንዲማረው ቢደረግ ለማንነቱ መጉላት፣ መከበርና ለቋንቋው ማደግ ድርሻ እንዳለው ኣውቆ ለራሱ እውቀት ክብር ሊሰጥ ይችላል።

## 1.6. በጥናቱ የቃላትና ሓረጋት ኣጠቃቀም ፍቺ

**ኣገር በቀል እውቀት** *(ኣበእ)፡-* በዚህ ጥናት፤ ታላላቆች ወይም የእድሜ ባለፀጋዎች በተለያዩ ዓውዶች ውስጥ የፈጠሯቸውን፣ ከቀደምቶቻቸው የቀሰሟቸውንና መስፋፋት ወይም ወደቀጣዩ ትውልድ መሸጋገር አለባቸው የሚሏቸውንና በተግባራዊ እንቅስቃሴ፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ በፉከራ፣ በሙሾ፣ በተረትና ምሳሌና በመሳሰሉት ዘዴዎች የሚተላለፉትን  እውቀቶች ሁሉ የሚገልፅ ነው። **ኣገር በቀል እውቀት** የሚለው ሃረግ ከላይ

ለማመልከት እንደተሞከረው ተጋሩ የህልውናቸውና የማህበራዊ ኑሯቸው መሰረቶች በመሆናቸው በቃል ወደ ተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ የሚፈልጓቸውን እውቀቶች ያጠቃልላል።

**እውቀት፡-** ተጋሩ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ይንቀሳቀሳሉ። በእንቅስቃሴው ወቅት ከሰው፣ ከእንስሳትና ከተፈጥሮ ጋር ይገናኛሉ። በዚህ ግንኙነት ውስጥ ልምድ ይካበታል፤ ክህሎት ይገኛል፤ ግንዛቤ ይሰፋል። እውቀት የሚለው ቃልም ከግንኙነቱ የፈለቁትን የመስራት፣ የማስላትና የማገናዘብ ልምዶችን ሁሉ የሚገልፅ ነው።

በዚህ ጥናት ውስጥ ለትንተና አመቺነት ሲባል ክህሎትና እውቀት ተለያይተው ቀርበዋል። ተጋሩ ግን ለያይተው አያዩዋቸውም። ንባብ፣ ድግር ጠረባ፣ ስሌት፣ የከብት ህክምና፣ ወቅትን ለይቶ የተለያዩ ተግባራት ማከናወን መቻል፤ ሁሉም መማርን የሚፈልጉ እውቀቶች ናቸው። **የምእራባውያን እውቀት፡-** እያንዳንዱ ህብረተሰብ  በራሱ አካባቢ፣ የአየር ንብረት፣ ባህል፣ ፍልስፍና፣ የአመራረት እና የምርት አከፋፈል ውስጥ ነው የሚኖረው። እውቀቱ የሚመሰረተውና የሚዳብረውም በዚህ እሱ በሚኖርበት አውድ ውስጥ ነው። በዚህ ጥናት ስር ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ያልዳበረ፣ ከተቀባዩ ሃገር ባህል፣ ልምድ፣ እምነት፣ የእድገት ደረጃ ጋር ሳይገናዘብ በስመ ዘመናዊነት ወይም ስልጣኔ በአገር በቀል ህዝቦች ላይ የተጫነ ያደጉት ሃገሮች ባህልን ወይም እውቀትን ለመግለፅ አገልግሏል።

**ስርዓተትምህርት፡-** የዚህ ጥናት አቅረቢ ስርዓተትምህርትና መርሃትምህርት የተለያዩ እንደሆኑ ያምናል። ስርዓተትምህርትም ሰፊ ትርጉም እንዳለውና በርካታ ነገሮችን በውስጡ እንደሚይዝ ይገነዘባል። በዚህ ጥናት ውስጥ ግን ስርዓተትምህርት፤ መርሃትምህርትን፣ የተማሪ መፅሐፍንና የመምህር መምሪያን አጣምሮ ለመጥራት ብቻ አገልግሏል። ስያሜው ከእንግሊዘኛው ካሪኩለም አቻ ስለሆነ በፅሁፉ ውስጥ 'ካሪኩለም' የሚለው ቃልም አልፎ አልፎ ገብቶ ይገኛል። አገባቡም ከላይ የተጠቀሰውን የስርዓተ ትምህርት ፍቺ እንደጠበቀ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. *መግቢያ*

በዚህ ምእራፍ ስር ሁለት አበይት ነገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸው ተብራርተዋል። **አንደኛው፣** "*በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት የአገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ*" ከሚለው ርእስ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ጥናቶች ተቃኝተዋል። ቅኝቱ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ የተሰሩትንና አጥኚው ሊደርስባቸው *የቻላቸውን ሁሉ አካቷል፡፡* ***ሁለተኛው፣*** *የጥናቱን ንድፈሃሳብ አቅጣጫ በሚቃኙ ዕሁፎች ላይ የተካሄደ የድርሳናት ክለሳ ነው።* በመጨረሻም የጥናቱ ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ (Conceptual Framework)፣ የግንባታዊነትና እውናዊነት /Constructivism and Objectivism/ አተያይ አንድነትና ልዩነት እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለማብራራት ተሞክሯል።

## 2.2. የንድፈሃሳባዊ ፅሑፎች ዳሰሳ

### 2.2.1. የስርዓተ ትምህርት ምንነት

ስርዓተትምህርት በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ትምህርት ከመስጠት በፊት የሚነደፍ የትምህርት እቅድ ነው። ወይም ትምህርት ቤቶች፣ ምን ይዘት? በምን ያህል መጠን? ለምን ያህል ጊዜ? በምን ሁኔታ ማስተማር እንደሚችሉ የሚወሰንበት የትምህርት ሰነድ ነው (Abreha, 1998)። ወይም ተማሪዎች ሊያውቋቸው ወይም ሊለምዷቸው ይገባል ተብለው የተመረጡ ይዘቶችን የተማሪዎቹን እድሜና ደረጃ በሚመጥን መልክ አደራጅቶ የሚያቀርብ የትምህርት ሰነድ ነው። እውቀት ተያያዥነት ባለው መንገድ የሚዳብር ቢሆንም ስርዓተትምህርት ግን የእውቀቱን መጣኝነት በመለኪያነት በመጠቀም ይዘቶችን ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደረቂቅ ያደራጃል። ህፃኑ ማህበረሰብ መሃል ሆኖ ያለገደብና ምጠና ይቀስመው የነበረውን እውቀት፣ ከእድሜ፣ ከብስለት፣ ከማህበረሰቡ የእድገት ሁኔታ ጋር እየተነፃፀረ ተመጥኖ እንዲቀርብ የሚያደርግ የመደበኛ ትምህርት መሳሪያ ነው(Hooley, 2009; Mwadime, 1999)።

እንዲሁም የትምህርት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ፖሊሲና ፕሮግራሞቹ በክፍል ውስጥ ተግባር ላይ የሚውሉበትን መንገድ የሚያመለክት የትምህርት ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱ ሊተላለፍ

የተፈለገውን እውቀት በመወሰን፣ በመምረጥና በማደራጀት በክፍል ውስጥ ለሚካሄደው የመማር ማስተማር ክንውን የይዘት ምንጭ በመሆን ያገላግላል (Mwadime, 1999)።

ስርዓተትምህርት፤ ትምህርት ቤቶች ምን ማስተማር፣ እንዴት ማስተማርና ለምን ማስተማር እንዳለባቸው የሚወሰንበት ሰነድ ነው። በአጭሩ የትምህርት እቅድ ነው። ህፃናት በታለመም ሆነ ባልታለመ መንገድ የቀሰሙትን እውቀት (ክህሎት መነሻ በማድረግ አዳዲስ እውቀቶችን) ክሂሎችን ለማስተማር የሚዘጋጅ የትምህርት እቅድ ነው (Abreha, 1998; Pinar, 2003; Ornstein and Hunkins, 2004)። የተማሪን፣ የማህበረሰብንና የትምህርት ባለሙያዎችን ፍላጎት በማካተት በትምህርትነት ሊቀርብ የሚገባው ይዘት የሚገለፅበት ሰነድ ነው። ይዘቱ የሚገለፀው የተማሪውን እድሜ፣ ችሎታ፣ የቋንቋ ሁኔታ፣ የሚገኝበት የእድገት ደረጃና ባህል ላይ ሳይንሳዊ ጥናት ከተካሄደበት በሁዋላ ነው፡፡ ስርዓትምህርት በጥቅል ሲታይ ይህንን ቢመስልም ህዝቦችና የትምህርት ባለሙያዎች ከሚያራምዱት ፍልስፍና አኳያ የተለያየ ይዘት፣ መልክና አላማ ይዞ ሊቀርብ ይችላል።

### 2.2.2. የስርዓተትምህርት ፍልስፍናዎች

ስርዓተትምህርት በዓለም ደረጃ የተለያየ ብያኔ እንደሚሰጠው ሁሉ የተለያየ አቀራረብም አለው። ልዩነቱ የሚከሰተው በየሃገሩ ከሚኖረው የትምህርት ፍልስፍና መለያየት ነው። የትምህርት ፍልስፍና፣ ትምህርት ነክ ብያኔዎችን ያስተላልፋል። ፍልስፍናውን ለማራመድ የሚችሉ የትምህርት አማራጮችንም ይወስናል። እንዲሁም የፍልስፍናው ማራመጃ የሆነው ትምህርት ቤት ተግባር ምን እንደሆነ፣ ምን አይነት ትምህርት ተቀባይነት እንዳገኘ፣ ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩና ምንአይነት የትምህርት መሳሪያዎችና የማስተማር ዘዴ ሊጠቀሙ እንደሚገባ መረጃ በመስጠት የትምህርት ባለሙያዎችን ያግዛል። እንዲሁም የትምህርቱ ግብ ምን እንደሆነና ከግቡ አኳያ የሚመረጠው ትምህርት ይዘት እንዴት መደራጀት እንዳለበት ያመላክታል።

የትምህርት ፍልስፍናዎቹ መለያየት የትምህርት ተቋማት ወይም የትምህርት ባለሙያዎች ለትምህርት የሚሰጡት ብያኔ እንዲለያይ ምክንያት ይሆናል። በዚህ የፍልስፍና መለያየት ምክንያት በዓለማችን የተለያዩ ስርዓተትምህርቶች ስራ ላይ ውለዋል (McNeil, 1996; Ornstein and Hunkins, 2004)። አንድ ሰው ተማረ የሚባለው ምንጊዜ ወይም ምን ለውጥ ሲያሳይ እንደሆነ፣ የተፈለገውን ውጤት ሊያሳይ የሚችለው ምን ይዘት በምን ሁኔታ

ሲቀርብለት እንደሆነ ይበይናል፡፡ ቀጥሎም ውሳኔውን እግብ ሊያደርስ የሚችል ስርዓተ ትምህርት ይነደፋል። በአንድ አካባቢ፣ ሃገር ወይም አህጉር ስምምነት ያገኘው የመማር ብያኔ በሌላው አካባቢም ሆነ ሃገር ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል። ለስርዓተትምህርት መለያየት ምክንያት የሚሆነው የትምህርት ፍልስፍናው ነው የሚባልበት ምክንያትም ይኸው ነው። ዋና ዋና የሚባሉት የስርዓተትምህርት ዓይነቶች አራት ሲሆኑ (McNeil, 1996) እነሱም፡-

- ሰብአዊ ስርዓተትምህርት (Humanistic)
- የማህበራዊ መልሶ ግንባታ ስርዓተትምህርት (Social Reconstruction)
- የቴክኖሎጂ ስርዓተትምህርት ( Technological) እና
- የአካዳሚ ስርዓተትምህርት (Academic Curriculum)በመባል ይታወቃሉ

**ሰብአዊ ስርዓተ ትምህርት፡** በዚህ ስርዓተትምህርት ፍልስፍና መሰረት፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ነፃነት ሊሰማቸውና ነፃ አስተሳሰብ ሊያዳብሩ ይገባል። በራሳቸው የሚተማመኑና ራሳቸውን የሚያውቁ ሆነው መቀረፅ አለባቸው። የዚህ ፍልስፍና አራማጆች ስርዓተትምህርቱ ራስን ወደእድገት፣ ነፃ አስተሳሰብና ተግባቢነት የማምራት ፍላጎትን የሚያሟላ መሳሪያ እንደሆነ ይገልፃሉ።

**ማህበራዊ ግንባታውያን፡** ከግላዊ (የተማሪ) ፍላጎት ይልቅ ለማህበረሰባዊ ፍላጎት ቅድሚያ ይሰጣሉ። በስርዓተትምህርቱ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የማህበረሰቡን መጪ ህይወት የተሻለ እንዲሆን የማድረግ ግዴታና ሃላፊነት አለበት ብለው ያምናሉ። የማህበረሰቡ እሴቶች በሚያድጉበትና ግልጋሎታቸው በሚሰፋበት ሁኔታ ላይ ማተኮር እንዳለበት ያሳስባሉ። ካሪክለሙ የቀረቡትን የትምህርት ዓላማዎች እግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ወይም ይዘቶችን መምረጥ የሚችሉት ማህበራዊ ግንባታውያን ብቻ እንደሆኑ ለማሳየት ይሞክራሉ።

**የቴክኖሎጂ (ውጤት ተኮር) ስርዓተትምህርት፣** የቴክኖሎጂ ስርዓተትምህርት አተያይ አራማጆች፣ በማምረቻ ተቋማት ውስጥ ምርታማነትን ሊያሳድግ የሚችል ዘዴ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ መካተት አለበት ይላሉ። የትምህርት ይዘቱ ወይም ምን መማር አለባቸው የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ግን በትምህርት ባለሙያዎች ሳይሆን የማምረቻ ተቋማቱ ዓይነትና ፍላጎት በማጥናት ነው (McNeil, 1996)። ተማሪዎች ይደርሱበታል ተብሎ

የተነደፈውን ዓላማ ለማሳካትና አምራችነታቸውን ለማሳደግ በምን ዓይነት ዘዴ ቢማሩ እንደሚሻል ለመወሰን በቅድሚያ ጥናት መካሄድ አለበት።

ቴክኖሎጂያዊ ስርዓተትምህርት 'ውጤት ተኮር' እየተባለም ይጠራል። ሂደቱ ሊለኩ የሚችሉ የተወሰኑ ክንውኖችን ለማሳካት ዓልሞ ይነሳል፡፡ ሊደረስባቸው የሚገቡ ግቦችንም በግልፅ ያስቀምጣል። ከትምህርቱ በኋላ ተማሪዎች በጋራ ወይም በቡድን አይገመገሙም። ከተቀመጠላቸው ግብ መድረስ ዘአለመድረሳቸው በተግባርና በተናጠል ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። በመጨረሻም ያሳኳቸው ግቦች ታይተውና ተቆጥረው የምዘና ውጤት ይገለፅላቸዋል። ምዘናው በዓላማው ላይ ያተኩራል ቢባልም እንደሌሎቹ ስርዓተትምህርቶች በሚገኙበት የክፍል ደረጃ የተማሩትን ክህሎት /እውቀት ማዳበር ወይም መገንዘብ መቻላቸው ብቻ አይለካም። ማህበረሰቡ መሃል በሚገቡበት ወቅት የተማሩትን እውቀት በመጠቀም በብቃት ለመግባባት የሚችሉ፣ ረቂቅ አስተሳሰቦችን የሚገነዘቡና የሚያፈልቁ፣ ሃላፊነት መሸከም የሚችሉ፣ በጥሩ ስነምግባር የታነፁና ጥራት ያለው ስራ መስራት የሚችሉ ዜጎች መሆናቸውን የሚያመለክቱ ብቃቶች ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

**የአካዳሚ ስርዓተትምህርት ፍልስፍና አራማጆች**፣ እንደ የፍልስፍናው አራማጆች እምነት፣ ተማሪው ሊቀስመው የሚገባውን እውቀትና ለወደፊት ሊያጠናው የሚፈልገውን የትምህርት ዘርፍ የሚተዋወቀው ስርዓተትምርቱ በሚያደራጃቸው ይዘቶች አማካይነት ነው። ፍሰታቸውን ጠብቀው የተደራጁት ይዘቶች፣ ግላዊና ማህበረሰባዊ ችግሮችን ለማየት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎች ሳይሆኑ ተማሪው ሊከተላቸው የሚገባ የመጨረሻዎቹ አማራጮች ናቸው። የተማሪውን አእምሮ ለማስፋትና በቀረበለት የትምህርት መስክ የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖረው ለማድረግ የአካዳሚ ስርዓተትምህርት ተመራጭ ብቻ ሳይሆን ተወዳዳሪ አልቦ እንደሆነም ያምናሉ። ስለሆነም ሊያውቃቸው የሚፈለጉ ይዘቶች በአጠቃላይ በስርዓተትምህርቱ ውስጥ በአግባቡ ተደራጅተው መቅረብ አለባቸው።

የአካዳሚ ስርዓተትምህርት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ለይዘት መረጣና አደረጃጀት ነው። ተገቢና በቂ ይዘት ካልተመረጠ ተማሪው በደረጃው ማግኘት የሚገባውን እውቀት/ ክህሎት ሊያጣ ይችላል። በሚቀጥለው የክፍል ደረጃ የሚቀርብለት ይዘትም በስፋትም በጥልቀትም ከቀዳሚው የላቀ ስለሆነ ሊገነዘበው አይችልም። የአደረጃጀት ችግርም እንዲሁ ሌላው ሊተኮርበት የሚገባ ነጥብ ነው። በአግባቡ ያልተደራጀ ይዘት፣ ተማሪው ከአቅሙ በታችና

በላይ እንዲያስብ፣ ኣስተሳሰቡ እንዲዋኸርቅና ጭብጡን እንዲስት ያደርጋል (McNeil, 1996)። በኣጠቃላይ የይዘት መረጣም ሆነ የኣደረጃጀት መዛባት ለደረጃው የተመረጠውን ይዘት ለመገንዘብ ካለማስቻሉም በላይ በቀጣዩ የክፍል ደረጃ የሚቀርቡ ይዘቶችን ለመከታተልም ኣያስችልም (McNeil, 1996; Ornstein and Hunkins, 2004)። ይህ ፍልስፍና፤ የትምህርቱ ጠቀሜታ፣ የኣቀራረብ ዘዴ፣ የይዘት ኣደረጃጀትና የግምገማ ስልት የሚሉ የስርዓተትምህርት ተዋቃሪዎች የሚያካትት ቢሆንም የተማሪው እውቀት የሚወሰነው በስርዓተትምህርቱ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች በመሆኑ ለይዘት መረጣና ኣደረጃጀት ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጥ ቀደምሲል ተጠቅሷል።

"በኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት የሃገር በቀል እውቀት ኣካትቶ ፍተሻ" በሚል ርእስ ስር የሚካሄደው ጥናት ከኣካዳሚ ስርዓተትምህርት ፍልስፍና መሰረታዊ ሃሳቦችን ይወስዳል። ጥናቱ በስርዓተትምህርት ላይ ፍተሻ ያካሂዳል። ፍተሻው የሚያተኩረው በይዘት መረጣ ላይ ነው። በትግርኛው ስርዓተትምህርት ውስጥ የኣገር በቀል እውቀት ይዘት መካተት ኣለመካተቱን ማየት ነው። ኣገር በቀል እውቀት በተለይ የኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ይዘት ነው። ኣስፈላጊ መረጣ ከተካሄደ በኋላ በስርዓተትምህርት ውስጥ የሚቀመጠው ይዘት ከቤት ይዘውት ለመጡት እውቀት መነሻ ሆኖ ካላገለገለና ከሚያውቁት ነገር ወደማያውቁት እንዲሸጋገሩ ካልተደረገ ኣዲሱን እውቀት ለመገንዘብ እንደሚቸገር ምሁራኑም ያስረዳሉ (McNeil, 1996)።

የኣካዳሚ ስርዓተትምህርት፤ እውቀት ቀድሞ በተገኘ ልምድ ላይ እንደሚመሰረት ያስረዳል። በቀዳሚው እውቀት ላይ ካልተመሰረተ ግን ተያያዥነት ስለሌለው ለመሸምደድ ቢሞከር እንኳ ቶሎ ይጠፋል። ይህ ኣተያይ ከግንባታውያን ኣተያይ ጋርም ይመሳሰላል። የቀረበው ጥናትም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ሳይንስንም ሆነ ስነፅሑፍ ለማስተማር መነሻ ሆነው ማገልገል ያለባቸው ህፃኑ ቤት ውስጥ ይሰማቸው የነበሩ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ተረትና ምሳሌዎች እና ተግባራዊ ክንውኖች ናቸው። እነዚህ ደግሞ የማህበረሰቡን እውቀቶች በውስጣቸው ደብቀው የያዙ ናቸው። እነዚህ ይዘቶች ወደቋንቋ ስርዓተትምህርት ለማስገባት ኣለመቻል መነሻ ሊሆን የሚችለውን እውቀት ለመጠቀም ኣለመቻል ነው። የዚህ ኣይነቶቹ ይዘቶች በኣንደኛ ደረጃ ስርዓተትምህርት ውስጥ ባለመካተታቸው ምክንያት ህፃናት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ይገደዳሉ /LittleBear,

2009/። በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ስርዓተትምህርትም ከቤት የመጣውን እውቀት መነሻው ቢያደርግ ህፃናት የበለጠ ሊማሩና ስርዓተትምህርቱም ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

### 2.2.3. የአገር በቀል እውቀት ምንነት

ከመደበኛውና በፅሑፍ ከሚገለፀው ወይም በተለየ ትምህርት ከሚገኘው እውቀት ውጪ የሆነ፣ በቃልና በትግበራ የሚተላለፍ እውቀት ሁሉ ያጠቃልላል። አገር በቀል እውቀት፣ በጋራ ወሰን ወይም ክልል የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ከተፈጥሮ፣ ከፈጣሪና እርስበርስ በሚደረግ ግንኙነት የሚያዳብሩት ግንዛቤ ሆኖ በቅርስነት የሚተላለፍ (wise legacy)፣ ባህላዊ፣ ከባቢያዊና አንዱ ህብረተሰብ በሌላ አካባቢ ከሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚለይበት እውቀት ነው (Grenier, 1998; LittleBear, 2009; Msuya, 2007; Ossai, 2010; Semali and Kincheloe, 1999; የቅርስ ጥበቃና ምዝገባ ባለስልጣን ቅጥምባ፣ 2002 ዓ.ም.)። ይህ እውቀት የአንድ ሰው፣ የአንድ ዘመን፣ የአንድ ትውልድ ውጤት ሳይሆን በተደጋጋሚ ሙከራና እርማት የዳበረና የነጠረ የዘመናትና የትውልዶች እውቀት ድምር ውጤት ነው (Mawere, 2010)።

አበእ፣ ከአጠቃላይ (ዓለም አቀፋዊ) እውቀት ይለያል።የአንድ አካባቢ ህዝብ እውቀት በሌላው አካባቢ ህዝብ ዘንድ ላይታወቅ፣ ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል። አበእ በገጠሩ አካባቢ በሚገኝ ህብረተሰብ ዘንድ የአስተራረስ፣ የጤና አጠባበቅ፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ የትምህርት፣ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና ጥበቃ ስራ ላይ ከባቢያዊ ውሳኔ ለማስተላለፍ የሚያገለግል፣ ከትውልድ ወደትውልድ በቃል የሚተላለፍ እውቀት ነው። በማሕበረሰቡ አባላት የሚጠበቅ የጋራ ሃብት ሆኖ በአፈታሪክ፣ በመዝሙሮች፣ በትውፊት፣ በባህላዊ እሴቶች፣ እምነቶች፣ ከበራዎች፣ የማህበረሰብ ህጎች (ቃላዊ)፣ በተለምዶአዊ የእርሻ ስራ አማካይነት የሚገለፅ ነው (Ossai, 2010)።

ልማዳዊ እውቀት (traditional knowledge)፣ ከህብረተሰቡ ውስጥ ፈልቆ እዚያው የዳበረ ከባቢያዊ (Local) እውቀት ነው። የማህበረሰቡ አባላት አብረው በኖሩባቸው ዘመናት ያዳበሩትና የሚያዳብሩት የዘመናትና የትውልዶች ግኝት ነው። በህብረተሰቡ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ (environmental)፣ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ የሚዳብር፣ ከለውጦች ጋርም ራሱን አስማምቶ የሚጓዝ ሃብት ነው።

ልማዳዊ እውቀትና አገር በቀል እውቀት የሚሉት ስያሜዎች ብዙ ጊዜ በተለዋዋጭነት ሲገቡ ይታያል። ሆኖም በመሃላቸው ትንሽ የሚመስል ግን በጣም ጠቃሚ የሆነ ልዩነት አለ። ልማዳዊ እውቀት ባህልን የሚገልፅ ሰፊና አንድ ሁለት ተብሎ ሊቆጠር የማይችል ሲሆን፣ አገር በቀል እውቀት ግን የልማዳዊ ባህል አንድ አካል ሆኖ በተለይ ህብረተሰቡ የሚታወቅባቸውና አካባቢውን የሚገነዘብባቸው ዋና ዋና እሴቶችንና (core values) እውቀቶችን ብቻ የሚይዝ ነው። የእነዚህ ዋና ዋና እሴቶችና እውቀቶች ህልውና የሚወሰነው በቋንቋ ነው። የትኛው እውቀት በምን አውድ፣ ለምን አገልግሎት፣ በምን ሁኔታ እንደሚቀርብ የሚታወቀው በቋንቋ መሳሪያነት ነው። የሚተረጎመውና ከሰው ሰው ወይም ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፈውም እንዲሁ በቋንቋ አማካይነት ነው። አበእ በጥቅል ሲታይ ከዘመናዊው የእውቀት መስክ ተለይቶ እንዲታይ የሚያደርጉ ነጥቦች አሉት። እነሱም **ከባቢያዊነት፣ ሁሉን አቀፍነትና ቃላዊነት** ናቸው (Grenier, 1998; Msuya, 2008; Zulu, 2006)።

**ከባቢያዊ ወይም ወሰን መለስ ነው፣** አገር በቀልነቱ ለተፈጠረበት አካባቢ ብቻ ነው ማለት ነው። ወይም በተፈጠረበት ባህልና አውድ ውስጥ የታጠረ ነው። አድማሱ በባህልና አውድ ይወሰናል። ይህ ማለት ግን ያ እውቀት ከተፈጠረበት ክበብ ፈፅሞ መውጣት አይችልም ማለት አይደለም። ከባህሉ ከወጣ አገር በቀልነቱ ሊጠፋ ይችላል ለማለት እንጂ።

**ሁሉን አቀፋዊ ወይም ወላዊ፡-** የአፍሪካውያን አገር በቀል እውቀት ምንጩ የግለሰብ ግንዛቤ ወይም ስነእውቀት ሳይሆን የወል ስነእውቀታዊ ግንዛቤና ማህበረሰባዊ አሳማኝነት ነው። በጥናቱ ዳራ ስር ለማሳየት እንደተሞከረው ግለኛ አስተሳሰብንና ባለቤትነትን አያንፀባርቅም። ሰውን እና ተፈጥሮን አጣምሮ ያያል። የግል ህይወት እንዲኖር ዋና ምክንያቱ ማህበረሰብ እንደሆነ ይቀበላል። የእውቀቱ ፈጣሪም ህበረተሰብ እንጂ ግለሰቦች እንዳልሆኑ ያምናል።

**ቃላዊ ወይም አፍአዊ፡-** አገር በቀል እውቀት፤ ከሰው ወደሰው፣ ከትውልድ ወደትውልድ በቃል ነው የሚተላለፈው። በሰነድ ላይ ላይገኝ ይችላል። አበእ፤ ታዳሽ፣ አዳጊና ተለዋዋጭ ነው። የህብረተሰቡ ባህል፣ ፖለቲካ ፣ ማህበራዊ መዋቅር፣ ወዘተ. ሲለወጥ አብሮ ለውጥ ያሳያል። በዚህ ለውጥ ውስጥ ቋንቋ አለ። ለውጡን ይገልፀዋል፣ አስፈላጊ ከሆነ ራሱንም ከለውጡ ጋር ያስማማል።

ኣውሮፓውያን ለኣበእ የሚሰጡት ግምት በጣም ዝቅ ያለ ነው፡፡ ኣገር በቀል እውቀትን ሁዋላ ቀር፣ ያልሰለጠነ፣ ተፈጥሮኣዊ፣ ያልታሸ ወይም ያልተገራ በማለት ይበይኑታል። (Grenier, 1998; Semali and Kincheloe, 1999)። ይህ ብያኔ ኣገር በቀል ህዝቦች ራሳቸውን ዝቅ ኣድርገው እንዲያዩና የበታችነትን ኣምነው እንዲቀበሉ ማድረጊያ መሳሪያም ነው፡፡ ህዝቦች በቀዬኣቸው፣ በሃገራቸው፣ ወይም በኣህጉራቸው የበቀለን እውቀት እንዲንቁ ማድረጊያ ነው።

እንደ ኣፍሪካ፣ ላቲን ኣሜሪካ፣ እስያ ለመሳሰሉት ሃገራት ሃገር በቀል እውቀት (IK or Native way of knowledge) እራሳቸውን የሚገነዘቡበት፣ ከተፈጥሮ ወይም ከኣካባቢ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገልፁበት መሳሪያ ነው። የኣንድ ኣካባቢ ነዋሪዎች ስለ ኣካባቢያቸው ተጨባጭ የሆነ መረጃ የሚያገኙበት እንዲሁም ራሳቸውን ለሌሎች የሚያስተዋውቁበትም ነው። ስለ ሰው፣ ስለ እንስሳትም ሆነ ስለ እፀዋት የደረሱበትን ግንዛቤ የሚያደራጁበት፣ ባህላዊ ሃይማኖታዊ እምነታቸውን የሚያሳዩበት፣ የኣኗኗር ዘይቤኣቸውን ለመለወጥ ወይም ለማሳደግ ሲሉ ያካሄዱትን የትግል ታሪክ የሚገልፁበት መሳሪያ ነው።
የኣገር በቀል እውቀት ባለቤትም ፈጣሪም ህብረተሰቡ ስለሆነ ከህብረተሰቡ የተነጠለ ህልውና የለውም። ይህንን እውቀት ለመገንዘብና ስለሱ ለመናገርም ከህብረተሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመስረትና ጠልቆ ማወቅ ያስፈልጋል (Semali and Kincheloe, 1999)። ኣበእ በቃልና በተግባር እንጂ በቤተመዛግብት ወይም ቤተመዘክር ውስጥ ኣይደለም። ኣገር በቀል እውቀት ወይም ኣገር በቀል ባህል ከሌሎች ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህርያት ኣሉት። **ኣንደኛው** :- በኣንድ ወቅት ተፈጥሮ የሚከስም ሳይሆን ከጠቀሜታው ኣኳያ ትውልዶች የሚቀባበሉት ሃብት መሆኑ ነው። ማህበረሰቡ ወይም ቡድኖች ከተፈጥሮና ከታሪክ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ለኣካባቢ ሁኔታዎችና ድርጊቶች ምላሽ ለመስጠት ሲሉ በቀጣይነት የሚፈጥሩት መሆኑ ነው። የእውቀቱ ባለቤት የሆነውን ህብረተሰብ ማንነት፣ ስሜትና ቀጣይነት ማመልከት በመቻሉም ይለያል። **ሁለተኛው** የኣገር በቀል ህዝቦች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች እርስበርስና ከሌሎች ህዝቦች መከባበርና ኣገር በቀል እውቀት ለዘላቂ ልማት የሚለው ኣስተሳሰብ የኣለም ኣቀፍ የሰብኣዊ መብት ድንጋጌዎች ድጋፍ ያለው መሆኑ (UNHCHR declaration 1994/45) ነው።

አገር በቀል እውቀት በተወላጁ ህብረተሰብ የሚፈጠርና የሚዳብር ቢሆንም ከምእራባውያኑ "ሳይንሳዊ እውቀት" ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ማህበረሰቡ የከዋክብትን አቅጣጫና ድምቀት በማየት በማስተዋል፣ የነፋሱን ሃይልና ድግግም፣ ሽታ፣ የከባቢ አየር ሁኔታ (ጭጋጋማነት፣ አቧራማነት፣ ጥቁረት ወይም ንጣት) በማየት ቀጣይ ክስተቶችን ይተነብያል። እርሻ መሬት ውስጥ የበቀሉ አበባዎችን፣ የአረም አይነቶችን በማስተዋል የትኛው መሬት ምን አይነት ዘር መዘራት እንዳለበት፤ የትኛው መሬት ሳይዘራ መክረም እንዳለበት ይወስናል (Semali and Kincheloe, 1999) ። ይህንን የሚያከናውነው ሳያስተውል፣ ሳይመራመርና ሳያገናዝብ አይደለም። የተለያዩ አካባቢዎችና የአየር ንብረቶችን፣ሰ የመሬት አቀማመጦችን፣ የአፈር አይነቶች እና ሌሎች ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን ከሚኖርበት አካባቢ ጋር በማገናዘብ መገልገል የሚያስችል ስር የሰደደ እውቀት/body of knwledge/ ባይኖረው ኖሮ እራሱንና ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል መቀለብ ባልቻለም ነበር።

ለምሳሌ በትግራይ የገጠር አካባቢ የሚገኝ ህብረተሰብ፤ የመብረቅ ብልጭታ ሲበረታ አመድና ከሰል ወይም ረመጥ በገል አድርጎ ወደደጅ ይረጫል። ሰይጣን መብረቁን ይዞ ወደ ቤት እንዳይጠጋ ይከላከላል ብሎ ያምናል። ሳይንስም ከሰል(ካርቦን) መብረቅን እንደሚስብ በማመን ከትላልቅ ህንፃዎች ስር በመቅበር ህንፃ ላይ ከማረፉ በፊት ወደመሬት ስቦ እንዲያስገባው ያደርጋል። ልዩነቱ ገጠሬው ሰይጣንን ለመከላከል ሲል ሳይንሱ ደግሞ ከአየር ግጭት ጋር ማያያዙ ነው። በተለይ ከ60 እና 70 ዓመታት በፊት በትግራይ አካባቢ፤ ፈንጣጣ እና ኩፍኝ ዋነኛ የህፃናት ገዳይ በሽታዎች ነበሩ። ህብረተሰቡ እነዚህን በሽታዎች በክትባት መከላከል ይችል ነበር። በአንድ መንደር በኩፍኝ ወይም ፈንጣጣ የተያዙ ህፃናት መኖራቸው ሲታወቅ ከታማሚዎቹ ህፃናት ቁስል ፈሳሽ በመውሰድ ላልተያዙት ህፃናት ክትባት ይሰጡ ነበር። በአሁኑ ጊዜ አውሮፓውያኑ ኩፍኝና ፈንጣጣን ለማጥፋት የቻሉት ህፃናትን ከአገር በቀሉ ጋር የሚመሳሰል ክትባት በመስጠት ነው።

እንዲህም ሆኖ እያለ አገር በቀል የሚለው ስያሜ እስከ 1970ዎቹ ከነበረው የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ፍቺ ይዞ ቆይቷል። በቅኝ ገዢነት አገርን የያዙ እና በቅኝነት የተያዙ ተወላጅ ህዝቦች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ተወላጆቹ አገር በቀል ይባሉ ነበር። ፍቺውም ያልሰለጠኑ፣ ኋላቀሮች፣ የተናቁ የሚል ነበር። ተወላጆቹ የሚገለገሉበትና በቃል የሚተላለፈው እውቀትም እንደእውቀት ማስተላለፊያ ሳይሆን እንደ የሁዋላ ቀርነት

መግለጫ ይቆጠር ነበር (Battist, 2002)። አገር በቀል የሚለው ስያሜ አሁንም እንዳለ ሆኖ ፅንሰሃሳቡ ግን ለውጥ በማሳየት ላይ ያለ ይመስላል፡፡ ቅኝ ገገር፣ የውጪ፣ የኛ ያልሆነ የሚለውን ፍቺ ጥሎ ብዙህነትን የሚያመለክት ሆኗል። በአሁኑ ጊዜ የአገር በቀልነት ጥያቄ በአንዲት ሃገር ውስጥ በቀበሌ፣ በዞን፣ በጎሳ ደረጃ ሊከሰት የሚችል ነው። ከነዚህ ደረጃዎች በአንዱ የሚገኙ የማህበረሰብ አባላት ተጨቁነናል፣ የራሳችን እድል በራሳችን ልንወስን ይገባል፣ ፖለቲካዊ ነፃነት ባለው መንግስት ስር ዴሞክራሲያዊ ግንኙነታችን ሊጠበቅ ይገባል የሚል አቋም ያላቸው ጎሳዎች የሚጠሩበት ስያሜ እየሆነ ነው። ዋና እና ንኡስ የሚባሉ ጎሳዎች፣ ነገዶች፣ ብሄረሰቦች ባሉበት አካባቢ አናሳዎቹ ስያሜውን ሲገለገሉበት ይታያል።

የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ድንጋጌም፤ አገር በቀል የሆኑት ህዝቦች ስያሜውን የመገልገል ብቻ ሳይሆን በሌሎች ዘንድ እንዲከበርላቸው የማድረግ መብትም እንዳላቸው፣

> *አገር በቀል ህዝቦች፤ የእነሱነት መለያና መገለጫዎቻቸው የሆኑ ባህሎችንና እውቀቶችን ቀጣይነት የማስጠበቅና የማሳደግ የጋራና የግል መብት አላቸው። ራሳቸውን አገር በቀል ህዝብ ነን ብለው የመናገር፤ በሌሎችም እውቅና የማግኘት መብታቸውም የተጠበቀ ነው* (UNHCHR declaration 1994/45)

በማለት ያስረዳል።

ከአዲሱ ፍቺ ጋር በተያያዘ የተባበሩት መንግስታት ያወጣው የአገር በቀል ህዝብ ድንጋጌ ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ አገር በቀል ህዝብ ማለት ከአንድ የዘር ግንድ የተገኘ ሆኖ የጋራ የሆነ ግንዘባቤ፣ የጋራ የሆነ የአፍ ታሪክ፣ ስለ ህብረተሰቡ ጥንተአመጣጥና ስለተገኘበት ምድር የሚያወሱና ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት አምነው የተቀበሏቸው ታሪኮች ያለው ህዝብ ነው (Wiessner, 2007)።

### 2.2.4. የአበእ መለያ ባህርያት

የአገር በቀል ህዝቦች፤ በተለይ የአፍሪካውያን እውቀት የሚመነጨው ከቃላዊው ባህል በመሆኑ ከምዕራባውያኑ እውቀት የተለየ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል። መገለጫዎቹ በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- በበቀለበት ማሕበረሰብ ውስጥ የተፈጠረ፣ ስር የሰደደ፣ በስፋት የሚታወቅና የሚተገበር መሆኑ፣
- በጥቅል የሚገነዘቡት እንጂ ተዘርዝሮና ተቆጥሮ በሰነድ የተቀመጠ አለመሆኑ፣
- በንድፈሃሳብ ደረጃ ያለ ሳይሆን በልምድ የሚገኝ፣ በህይወት ቤተሙከራ /በሙከራና እርማት/ ነጥሮ የሚወጣ መሆኑ፣
- ኣበእን ለማስረፅ ዋነኛ መሳሪያ ደጋግሞ መስራትና መናገር መሆኑ፣
- በቦታና በባህል መለስ ኣጥር የተቀነበበ መሆኑ፣
- ውሳኔ ለማስተላለፍና የኑሮ ዘይቤ ለመቀየስ መሰረት ሆኖ ማገልገሉ፣
- ስለሰዎችና እንስሳት ህይወት፣ ስለኣካባቢው ተቀዳሚ ምርትና ስለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ኣስተዳደር በእጅጉ የሚጨነቅ (ጥብቅና የሚቆም) መሆኑ ናቸው (Ossai, 2010)።

እንካስላንቲያዎች፣ ተምሳሌቶች፣ ተረቶች፣ እንቆቅልሾችና ልዩ ልዩ ጨዋታዎች በቃል ከሚተላለፉት የኣገር በቀል እውቀት መገለጫዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ ከሰው ልጅ፣ በተለይ ከኣገር በቀል ህዝብ ህይወት ጋር በእጅጉ የተሳሰሩና ሊነጠሉ የማይችሉ ናቸው። ኣንዳንድ ምሁራን (Mosha, 1999.; Semali and Kincheloe, 1999) ትስስሩ ምን ያህል ጥብቅ እንደሆነ ለማሳየት፡- ከላይ የተዘረዘሩትን የትውፊት ኣላባዎች በማስተማሪያነት ከመገለገል መቆጠብ ወይም መታገድ ማለት ኣገር በቀሉን ሰው ከህልውናው ለመነጠል፣ ወይም የሁሉም ታሪኮች ባለገድል (ገፀባህሪ) ራሱ ሰው ነውና ስለራሱ ሲወራ እሱ እንዳይኖርበት ለማድረግ እንደመሞከር እንደሚቆጠር ያስረዳሉ።

ቃላዊ ሃብቶች ማህበረሰቡን እራሱን ለመግለፅና የማህበረሰቡን እውቀት ለማስተላለፍ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች መሆናቸውና ማስቀጠል የሚቻለውም በነሱው መሳሪያነት መሆኑ ከገለፃው መገንዘብ ይቻላል። በተለይ ፅሁፍ ባልዳበረባቸው ሃገራት ወይም ኣህጉር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች እውቀት የሚተላለፈው በቃል ነው። በጣም ውስብስብ የሆኑ ህጎችና መተዳደሪያ ደንቦች በቃል ይነገራሉ፣ የህብረተሰቡ ኣባላትም ይሰሟቸዋል፣ ያጠኗቸዋል፣ ይተዳደሩባቸዋልም። በዳኝነት የሚሰየሙ ሰዎችም ያለምንም ማዛባት ሲዳኙባቸው ኖረዋል፣ ኣሁንም እየሰሩባቸው ይገኛሉ። ይህንን ለማድረግ በመሳሪያነት ያገለገላቸው ፅህፈት ሳይሆን ኣገር በቀሉ የቃል እውቀት ነው።

በዚህ የቃል እውቀት አማካይነት ከአንዱ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ሲተላለፉ ኖረዋል፤ አሁንም እየተላለፉ ነው። የመሬት ስሪት፣ የህብረተሰቡ የእርስ በርስ ግንኙነትን የሚወስኑ ህጎች፣ የተፈጥሮ ህጎች፣ የውርስ ስርአት፣ የተለያዩ የፀሎት ስርአቶች መድሃኒቶች ተጠብቀው ያለምእራባውያኑ ድጋፍ በቃል ከትውልድ ወደትውልድ ሲሸጋገሩ ኖረዋል፤ አሁንም ቢሆን ተመሳሳይ ድርጊት የሚፈፀምባቸው ሃገሮች፣ ጎሳዎችና ብሄረሰቦች በርካታ ናቸው (Mosha, 1999; Semali and Kincheloe, 1999)።

**አገር በቀል ህዝብ፤** ቀጣይ የሆነ የጋራ ታሪክ፣ የሚታወቅ ወሰን ያለውና ከህዝቡ ውስጥ ከፊሉም ቢሆን የኔ በሚለው ቦታ ውስጥ የሚኖር፤ ከአያት ቅድመአያት ያገኘውን ማንነትና ወሰን አስጠብቆ የሚኖር፣ የኔ የሚለው ባህል፣ ማህበረሰባዊ መዋቅርና የሚተዳደርበት ቃላዊ ህጋዊ ማእቀፍ ያለው ህዝብ ነው። በተለያዩ ዘመናት ያሳለፏቸው በጎና መጥፎ አጋጣሚዎችን የሚገልፁት በነዚህ የአፍ ታሪኮች ወይም ቃላዊ ሃብቶች አማካይነት ነው። ስነቃሉንና በስነቃሉ የሚገለፁትን ጠቃሚ ቁሳዊና መንፈሳዊ እውቀቶች ተገቢ ጥበቃና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው ነባሩንና አዲሱን ትውልድ የሚያቆራኘው ገመድ ተበጠሰ ማለት ነው ጉጅለ ምስፍሕፋሕ ኪነጥበባትን መፅናዕቲ ቋንቋን(ጉምኪጥመቋ፣ 1997 ዓ.ም.)። ብዙዎቹ የአፍሪካ የአፍ ታሪኮች፤ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ወጎች፣ ወዘተ. ስለቅኝ ግዛት፣ ስለቅኝ ገገርወች ጨካኝነት፣ የጨካኝነታቸው መገለጫዎች፣ ከገገርዎቹ ጋር ስለተደረገው መራራ ትግልና ውጤቱ የሚያወሱ ናቸው። እነዚህ ደግሞ የአህጉራቱ ታሪኮች ናቸው። ስለሆነም አዛውንቶች እነዚህን ታሪኮች ከመተረክ፤ ተተኪው ትውልድ (ተማሪው) እነዚህን ታሪኮች ከመስማት ማገድ አይቻልም። በቃላዊ ወጎቹ አማካይነት የመተባበርን ጠቃሚነት፣ ተባብሮ ጠላትን የመከላከልና ድል የማድረግ አስፈላጊነትን ያስተምሩበታል።

በምእራባውያኑ ዘንድ የኋላ ቀር ህዝቦች መለያ ተደርጎ የሚወሰደው ቃላዊ ሃብት፤ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ በቋንቋ አጠቃቀምና በአውድ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማስተማር በመሳሪያነት ያገለግላል። ትእምርቶችን እና ውክልናቸውን ለማወቅ ያግዛል። ስነምግባርና ስርአት የተላበሰ ንግግርን አውቆ ለመገልገል፣ ቃላት ከተነገሩበትና ከገቡበት አውድ አኳያ ዋጋቸው (value) የተለያየ መሆኑን ለመረዳት፤ በቅኔያዊ፣ ዘይቤያዊ፣ ስእላዊ አገላለፃቸው አማካይነት አካባቢን ለማየትና ለማድነቅ ያስችላል። እንቆቅልሾቹም የተማሪውን አእምሮ ያሰፋሉ። በተምሳሌቶቹ ውስጥ

የተሸፈኑትን ሚስጥሮች በጥልቀት ማሰብን ስለሚፈልጉ የተማሪውን ነገሮችን የመመርመር እና የማገናዘብ አቅም ያዳብሩለታል (Brock-Utne, 2000; ጉምኪጥመቋ፣ 1997 ዓ.ም.)። ከዚህ ገለፃ በመነሳት ቃላዊ ሃብቱ ድርብ ጠቀሜታ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። ይኸውም፡ በአንድ በኩል ቋንቋውን ለማወቅና ለመገልገል፤ በሌላ በኩል በቋንቋው አማካይነት አካባቢን ለመገንዘብ፣ ለማድነቅና እውቀት ለመሸመት በመሳሪያነት ያገለግላል።

የቋንቋ ተግባር፤ ቃላትን በመደርደር፣ ወይም ቅዐበታዊ የሆነ መልእክትን በማስተላለፍ ብቻ አይገለፅም። ሁኔታዎችንና ነገሮችን ጠልቆና ርቆ ለማየት፣ ያለፉ ተግባራትንና ሁኔታዎችን ለማስታወስና መጪ ተግባራትን ለማቀድ በመሳሪያነት ያገለግላል። እንቆቅልሾች፣ ምሳሌዎች፣ ተረቶች፣ ፉከራና ቀረርቶዎች፣ መዝሙሮች፣ የአገር በቀል እውቀት (ትምህርት) ማስተላለፊያ መሳሪያዎች ናቸው። እነዚህ ቃላዊ ሃብቶች ከነበረው ወይም ካለው ትውልድ ወደ አዲሱ ሲተላለፉ አዲሱ ትውልድ ማንነቱን እንዲያውቅና ስብእናውን እንዲገነባ በማድረግ ትልቅ ድርሻ ይጫወታሉ (Semali, and Kincheloe 1999)። አባት ወይም እናት ልጆቻቸውን ይዘው ወደ እርሻ፣ ወንዝ፣ አውድማ ወይም ዘመድ ጥየቃ ሲሄዱ እግረ መንገዳቸውን ያስተምራሉ፤ ከአያት ወይም ከቅድመአያት ያገኙትን እውቀትና ልምድ ያስተላልፋሉ። ስለ አዝመራው፣ ስለ እፀዋቱ፣ የእፀዋቱ ልዩ ልዩ አገልግሎት ያወጋሉ። እፀዋቱን በመድሃኒትነት መገልገል ቢያስፈልግ ምን ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ያስረዳሉ። የትኛው ለሰው፣ የትኛው ደግሞ ለእንስሳት፤ የትኛው እፅና የእፅ አካል የትኛውን በሽታ እንደሚፈውስ ያብራራሉ። ገለፃውም ሆነ ማብራሪያው የሚተላለፉት በአገር በቀሉ ቋንቋ ስለሆነ የልጆቹን በቋንቋው የመገልገል ክሂል ያዳብርላቸዋል።

### 2.2.5. አገር በቀል ትምህርት

የአገር በቀል ትምህርት ምንነት ከማየታችን በፊት ትምህርት ከአውሮፓውያንና ከአፍሪካውያን አኳያ እንዴት እንደሚበየንና ልዩነቱ እስከምን ድረስ እንደሆነ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ዘመናዊ በመባል እየተሰጠ ያለው ትምህርት የምዕራባውያን ቅጂ እንጂ የአፍሪካውያን ሊባል አይችልም (Hurreiz 2006:55)። አገር በቀሉ የትምህርት ፅንሰሃሳብ ግን አንድም ጠፍቷል፤ አሊያም ስላልተፈለገ ገለል ተደርጓል። በምዕራባውያኑ የትምህርት አተረጓጎም እውቀትና ትምህርት ከንባብና ከፅሁፈት ጋር ተጣምሯል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉት መዝገበቃላት የሰጧቸውን ብያኔዎች እንይ፤

- Oxford Advanced Learners Dictionary of Current English (728)

  Literate የሚለውን ቃል " able to read and write" በማለት ይፈታዋል።

- Encarta Dictionary (online)

  a. Able to read and Write

  b. Well- educated and well- read

  c. Showing skill in the techniques of writing

የሚሉ ፍቺዎችን ያቀርባል።

- *መዝገበ-ቃላት ትግርኛ--አምሓርኛ* (1948 ዓ.ም.) **መሃረ** የሚለውን ቃል **ነገረ** የሚል ፍቺ ነው የሰጠው።
- *መዝገበ- ቃላት ትግርኛ* (2000 ዓ.ም.) ደግሞ **መሃረ=ዓለመ፣ አረድአ፣ አሰልጠነ፣ ገርሐ** (አሳየ፣ አሰረዳ፣ አሰለጠነ፣ ገራ) የሚል ፍቺ ሰጥቶታል።

በአውሮፓውያኑ እና በአፍሪካውያኑ (ኢትዮጵያውያን) መዛግብተቃላት መካከል ጉልህ የሆነና ከላይ ሲገለፅ የቆየውን የትምህርት ብያኔ ልዩነት በተጨባጭ የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል። በትግርኛ ቋንቋ የተዘጋጁት፤ ትምህርትን ከማወቅ፣ ከመረዳትና ከመገራት (መሰልጠን) ጋር አያይዘውታል። መማር ማለት መፃፍና ማንበብን ብቻ የሚያመለክት አለመሆኑ አስረግጠዋል። በአውሮፓውያን የተዘጋጁት ግን ከራሳቸው አካባቢና የእድገት ደረጃ ብቻ በማያያዝና የአፍሪካውያኑን እውቀት ከጉዳይ ባለመቁጠር መማር፤ መፃፍና ማንበብን መቻል ብቻ የሚያመለክት ፍቺ ሰጥተዋል። ይህ ብያኔ በምዕራብውያኑ ዘንድ ትክክልና ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይችላል። ዓለም አቀፋዊ ብያኔ ሆኖ መቆም ግን አይችልም። ይህ **ትምህርት = ማንበብ + መፃፍ** የሚለው ቀመር አብዛኛውን እውቀት በቃል በሚያስተላልፉ አፍሪካውያን ዘንድ የሚሰራ አይመስልም።

በአፍሪካ ልማዳዊ ትምህርት ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ያላቸው ቃላዊና እይታዊ ተግባቦቶች ናቸው። ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው፣ በአፍሪካውያን ዘንድ ትላልቆቹ ቤተ መፃህፍት የእድሜ ባለፀጎቹ ናቸው። ያከማቹትን እውቀት በቃል ወይም በተግባር እያሳዩ ለሌሎች ያስተላልፋሉ። የፅህፈትና የንባብ ክህሎት ግን ላይኖራቸው ይችላል። በምእራባውያኑ ቀመር መሰረት እነዚህ ሰዎች አያውቁም (አልተማሩም) ሊባሉ ነው።

የአፍሪካ ትምህርት (Education) የራሱ የሆነ ባህላዊ ፍቺ አለው። መበየን ያለበትም ከአፍሪካውያን የትምህርት መነሻ ሃሳብ አኳያ ብቻ ነው። በአፍሪካውያን እምነት አንድ ሰው 'የተማረ' የሚባለው በምዕራባውያኑ ቀመር መሰረት ፊደል ስለቆጠረ /ማንበብ ወይም መፃፍ ስለቻለ አይደለም። በሃገሩ የልማዳዊ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ሃገራዊ እውቀትን ቀስሟል። ባገኘው ትምህርትም ምእራባውያኑ ሊያነቧቸው የማይችሏቸው በርካታ መልእክቶችን "ማንበብ" ይችላል። ወቅትን፣ አዝርእትን፣ ነፋስን ያነባል። በሰዎች አካላት ያሉ ስንጥቦችንና ጠባሳዎችን አይቶ የየትኛው ጎሳ አባል እንደሆኑ መለየት ይችላል። ከደወል፣ ከጥሩምባና ከከበሮ ድምፆች በርካታ መልእክቶችን ያነባል ተብሎ ሲታመን ነው ተማረ የሚባለው።

አገር በቀል ትምህርት የሚፀነሰው በስነምህዳር (ኢኮሎጂ) ውስጥ ነው። ቤቶች፣ ወንዞች፣ ደኖች፣ አዝርእት የአገር በቀል እውቀት መቼቶች ወይም መመንጫዎች ናቸው። እውቀቱ የሚቀሰመውም ከተፈጥሮ ጋር በሚደረግ ምልልሳዊ ግንኙነት (dialogical relationship) ነው። ህፃናት በቅድሚያ የተፈጥሮን ህልውና ይማራሉ። የሚኖሩባት ምድር በውስጧ በርካታ የአምልኮ አይነቶች መያዝዋን ያስተውላሉ። ሰዎች ልዩ ልዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ (ሲበሉ፣ ሲተኙ፣ ከእንቅልፍ ሲነሱ) ከአማልክት ወይም ከመናፍስት ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት ይታዘባሉ። ያታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል መኖሩን ይረዳሉ። ወላጆቻቸው ስራ ሲጀምሩ መልካም ጅማሬና ፍፃሜ እንዲሆንላቸው አማልክትን ሲማፀኑ ይሰማሉ። የአገር በቀል ትምህርት በዚህ ሁኔታ ይጀመራል። ቀስ በቀስ ደግሞ ቤተሰብ በተሰማራበት የስራ መስክ መሳተፍ ይጀምራሉ። በእርሻ፣ አረም፣ አጨዳ፣ ውቂያ፣... ስራዎች ይሳተፋሉ። የከብት ጥበቃ፣ የአደን፣ የአሳ ማጥመድ ስራዎችን ይለማመዳሉ (Grenier, 1998)። የመጀመሪያዎቹ መምህራን አባት፣ እናት፣ ወይም ቤተሰቦች ናቸው። ከፆታ መሰሎቻቸውም ፆታ ነክ ትምህርትን ያገኛሉ። የቀሰሙዋቸውን እውቀቶች በተረት፣ በእንቆቅልሽና በመሳሰሉት ወጎች አማካይነት ያጠናክሩላቸዋል (George, 1999; Semali and Kincheloe, 1999)።

አበእን ነጥለው ካዩት፣ መደበኛ ትምህርት ቤት ከሚገኝ እውቀት በአደረጃጀት የተለየ ነው። በመደበኛ ትምህርት ቤት የሚቀርብ እውቀት ስርአተትምህርት ይቀረፅለታል፤ የደረጃ ምጣና አለው፤ በየደረጃው እየሰፋና እየጠለቀ የሚሄድ አደረጃጀት አለው። በማህበረሰቡ መሃል በመገኘት የሚቀሰመው ዕውቀት (አበእ) ግን እነዚህን ሁሉ ላያሟላ ይችላል (Grang

2004)። ከትምህርታዊ ጠቀሜታ አኳያ ግን ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው። ኢ-መደበኛው ይዘት፣ ለመደበኛው ትምህርት መነሻው ነው። አንድ ህፃን ቤት ከሚባለው እውቀ አለም ትምህርት ቤት ወደሚባል አዲስ አለም ሲሸጋገር የእውቀትም የክህሎትም መነሻ ሆኖ የሚያገለግለው ከቤት ይዞት የመጣው እውቀት ነው። እንደ ግንባታውያን እምነት፣ እውቀት የሚገነባው ቀድሞ በተገኘው ልምድ እና እውቀት ላይ ነው (Perkins, 1992; Semali, and Stambach, 1993)። በተግባር የሚታየው ግን የዚህ ተፃራሪ ነው። አገር በቀል እውቀት በስርዓተትምህርት ውስጥ አይካተትም። ያ ቦታ ለቀለም እውቀት የተተወና በትምህርት ባለሙያዎች የተያዘ፣ ለባእድ ባህል የተፈቀደ፤ ለአገር በቀል እውቀት ግን የተከለከለ ይመስላል (George, 1999:80)። ተማሪዎች እየተማሩ ያሉት የገዛ ባህላቸውን ዝቅ አድርጎ በሚያይና የታላላቆቻቸውን ክብር በሚያንኳስስ (መከባበርን በማይቀበል) ስርአተትምህርት ነው። የወላጆቻቸውንና የአያቶቻቸውን አስተራረስ ዘዴ ምንያህል ሁዋላቀር እንደሆነ የሚገልፅ ዘገባ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ይህ ሁኔታ በወላጅና ልጅ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲላላ፣ ህብረተሰቡ በስርዓተትምህርቱ ላይ አመኔታ እንዲያጣ ልጅ ደግሞ የመጣበትን ህብረተሰብ እንዲንቅ ያደርጋል (Semali and Stambach, 1993)።

እያንዳንዱ ህብረተሰብ፤ በጣም አስፈላጊ የሚላቸው እውቀቶችን፣ እምነትን፣ ክህሎትን፣ ባህሪን እና ዝንባሌን ስራየ ብሎ ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል (Pai, 1990)። ለምሳሌ አባት ከስራ መልስ እሳት ዳር ወይም በበአላት ቀናት አፋፍ ላይ ቁጭ ብሎ ሞራል ነክ፣ ፍትህ ነክ፣ ስራ ነክ፣ ወዘተ. የሆኑ ወጎችን ለልጆቹ ይተርክላቸዋል። እናትም በተለይ ሴት ልጆቿን፤ ሙያን፣ ስነስርአትን፣ ሴትነትንና ከሴትነት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ታስተምራለች። እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የህብረተሰቡ አባሎች በተለያዩ አውዶች በመገናኘት ለእከሌ ሳይሉ ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን እውቀቶች ለማስረፅ ጥረት ያደርጋሉ። የዚህ አይነቱ ሆን ብሎ አገር በቀል እውቀትን (ባህልን) የማስተላለፍ ተግባር ማስተማር ይባላል።

ባህልን ከአንዱ ትውልድ ወደሌላኛው የማሸጋገር ተግባር የታቀደ (መደበኛ) አለዚያም ኢ-መደበኛ ሊሆን ይችላል። ወላጆችም ሆኑ በየመድረኩ ተገኝተው የሚያስተምሩት የማህበረሰቡ አባላት 'ጥሩ ነው' ብለው ያመኑበትን ለማስተላለፍ ጥረት ያደርጋሉ። ሆኖም ምን ይዘት፣ በምን መልክ፣ ለማን ማስተማር እንዳለባቸው በመመዘንና በመወሰን

ላያቀርቡት ይችላሉ። በተለይ ፊደል ያልቆጠረ ህዝብ በሚበዛባቸው እንደኢትዮጵያ በመሳሰሉ ሃገራት የትምህርቱ አሰጣጥ ኢመደበኛና ቃላዊ ነው። ተተኪው ትውልድ ዕውቀቱን የሚያገኘው፣ ታላላቆቹ፣ ጓደኞቹና ሌሎች አባላት ከሚናገሯቸውና ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ነው። ትምህርት የሚቀስምባቸው ቦታዎች መንገድ፣ ሰርግ ቤት፣ ገበያ፣ ለቅሶ ቤትና ሌሎች አውዶች ሊሆኑ ይችላሉ።

አገር በቀል እውቀትን ለማስተላለፍ አልሞና ስርአተትምህርት ቀርፆ ማስተማር፣ ከላይ ከታየው እውቀትን የማሸጋገር ተግባር ይለያል። መደበኛ ትምህርት፣ ምን ይዘት፣ በምን ያህል መጠን፣ ለየትኛው የክፍል ደረጃ፣ ለምን ያህል ጊዜ፣ ምን ለማግኘት እንደሚሰጥ ታስቦበት የሚዘጋጅ ነው። መደበኛ መምህር ተመድቦለት፣ በተማሪው ላይ የተፈለገውን ለውጥ ለመምጣት በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ የተመጠነ እውቀት/ ክህሎት ነው። ለምሳሌ አንድ የሰባት ዓመት ህፃን ስለ የጋብቻ አፈፃፀም ስርአት የሚያወሳ ተረት ወይም ምክር ቢቀርብለት በእድሜው ያልደረሰባቸው ፅንሰሃሳቦች ስለሚኖሩበት ላይገነዘበው ይችላል። ቤተሰብን የመርዳት ምንነት፣ አስፈላጊነትና የህፃናት ድርሻ የሚመለከት ተረት ቢቀርብለት ግን ወቅታዊና አስፈላጊ በመሆኑ እሱም በአቅሙ ለቤተሰቡ ማድረግ የሚገባው ነገር እንዳለ ሊያውቅ ይችላል (Pai, 1990)። መደበኛ ትምህርት (Schooling) የሚባለው የዚህ አይነቱ የታቀደ የትምህርት ሂደት ነው። ህፃኑ ስለጋብቻም ሆነ ስለሌሎች ከአቅሙ በላይ የሆኑ ጉዳዮች ባልታቀደ ሁኔታ አይሰማም ማለት ግን አይደለም። ሂደቱ ግን የታቀደ ማስተማር ሊባል አይችልም ።

ስርአተትምህርት በአንድ ክልል፣ ዞን፣ ቀበሌ፣ ወይም ጣቢያ የሚገኝ ህብረተሰብ እውቀትን ወደተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲገለገልበት የተቀረፀ ከሆነ የተወላጁን ታሪክ፣ እውቀት፣ ፍልስፍና ቋንቋ፣ ማንፀባረቅ አለበት፡፡ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ሲቀርቡ የተፈጠሩበትን አውድና ባህል ሳይለቁ ካልቀረቡ፣ ስርአተትምህርቱም ከቀለም በተጨማሪ ሌሎች ማህበረሰባዊ ጉዳዮችን የማያይ፣ የተወላጁን እውቀት በግብአትነት የማይጠቀም ከሆነ ከትምህርት ቤት የሚገኘው እውቀት ማህበረሰባዊ ተቀባይነት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል (Semali and Stambach, 1993)።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት አገር በቀል እውቀትን ለማስተላለፍና ጠብቆ ለማቆየት እንደሚያገለግል ቢታመንም፣ እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት የሚያመለክቱ ጥናቶች ግን ያሉ አይመስልም፣ ወይም አጥኚውን አላጋጠሙትም። የቋንቋ

ስርዓተትምህርት በእውቀት ስም የባእድ ባህልን፣ እምነትን፣ ፍልስፍናን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ሊያስፋፋና ሊያሰርፅ የሚችል ዋነኛ መሳሪያ በመሆኑ የሌላ ባህል መግለጫ እንዲሆን መተው እራስን ለቅኝ ግዛት ወይም ለዘመናዊ ቅኝ ግዛት አሳልፎ መስጠት ይሆናል (Grang, 2004)። (ኦበእ) ሊጠፋ የሚችለውም ገብ የሆነው እውቀት ሲጫነውና የአዲሱ እውቀት ግፊት መቋቋም ሲያቅተው ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደትምህርት ቤት የመጣ ልጅ በቋንቋው ራሱንና አካባቢውን መግለፅ ይችላል፡፡ በባህሉ የሚባልና የማይባለውን በከፊል ለይቷል፡፡ በቋንቋው ማድመጥና መናገር ይችላል፡፡ እነዚህንና ሌሎች እውቀቶችን ይዞ ወደ ትምህረት ቤት ለመጣ ልጅ በማስተማሪያነት የሚመረጡት መሳሪያዎች፣ የመማሪያ ቋንቋና በቋንቋው የሚገለፀው ባህል ትልቅ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ልጁ አፍ ከፈታበት ቋንቋ የተለየ መማሪያ ቋንቋ ካጋጠመው ለማድመጥና ለመናገር ጀማሪ ይሆናል (የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ባቱሚ፤ 1998ዓ.ም.)፡፡ በዚህ ላይ እንግዳ ባህል በይዘትነት ሲቀርብ ይበልጥ ይደናገራል፡፡ ትምህርቱም የማያውቀው ይዘት (ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ስያሜ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ወዘተ.) በማያውቀው ቋንቋ ስለሚቀርብ የተማሪው ድርሻ የተገነዘበውን መተግበር መሆኑ ይቀርና ማነብነብ ወይም መሸምደድ (rote memory) ይሆናል፡፡ በማነብነብ ደግሞ ዘላቂነት ያለው እውቀትም ሆነ ክህሎት ማዳበር አይቻልም (Semali and Kinchiloe, 1999)።

በቅድመ 1967 ዓ.ም. የነበረውን የኢትዮጵያ የቋንቋ ትምህርት ሁኔታን በአብነት ማየት ይቻላል። የዚህ ጥናት ባለቤት ተወልጄ ያደግኩት የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በሌለበትና ቋንቋው ለህብረተሰቡ ጆሮ እንኳ አዲስ በሆነበት ገጠር ውስጥ በመሆኑ ቋንቋውን የለመድኩት በትምህርት ቤት ውስጥ ነው። እገለግልበት የነበረውም ከመምህራን ጋር ስገናኝ ብቻ ነበር። በመምህርነት ለመሰልጠን ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ እስከገባሁበት ጊዜ ድረስ በፍቺ ደረጃ የማላውቃቸው **"ቅምብቢት፣ ጮጮ፣ እምቧይ፣ ግት፣ ጓል፣ አንኳር፣ ወዘተ."** የሚሉ ቃላት አነብ እንደነበረ አስታውሳለሁ። **"ለማና ዘመዶቹ፣ ለማ በገበያ፣ አረንጓዴው ጓደኛየ፣ ሶስተኛው የንባብ መፅሃፌ "** የሚባሉ መፃሕፍት ይዘታቸውን ሳላውቅ ፊደል ስለለየሁ ብቻ አነባቸው እንደነበረ አስታውሳለሁ። ከዚህ አብነትም በእንግዳ ቋንቋ እንግዳ ይዘት ለመጨበጥ መሞከር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

መማር፣ ቀድሞ ከተካበተ እውቀት /ክህሎት ላይ አንድ ነገር መጨመረን (ግብአት + 1) ነው የሚያመለክተው (Krashen, 1982)። በተለይ ለጀማሪ ተማሪ ግብአቱ ከአካባቢ የተገኘ ልምድና እውቀት ነው። የግብአት ትወራ፣ ተማሪ በመምህር የሚሞላ ባዶ እንስራ አለመሆኑና ከኖረበት ማህበረሰብ ይዞት የሚመጣ መነሻ እውቀት እንዳለው የሚያመለክት ነው፡፡

አገር በቀል እውቀት (አበእ) የተወላጆች ባህል ውጤት ሆኖ ቀስ በቀስ በትውልዶች ውስጥ የሚዳብር፣ አንዱ ትውልድ ከቀዳሚው የሚረከበውና አዲሱ ትውልድ የራሱን ማሻሻያዎች በመጨመር የሚገለገልበት ሃብት ነው፡፡ ስርዓተትምህርት ይህን እየሰፋና እየጠለቀ የሚመጣውን ሃብት ለመጠበቅና በትምህርት መልክ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ወሳኝ ድርሻ ይጫወታል (Woube, 2004)። የአገር በቀል ስርዓተትምህርት ተቀዳሚ አላማም በትምህርት (Education) መሳሪያነት የህብረተሰቡን ባህል ወደቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ መሆን ይኖርበታል።

አገሮች፣ ኢትዮጵያም ጭምር በተለያዩ ምክንያቶች የአንድ ቋንቋ የበላይነት ለማጉላትና ሌሎቹን ለማዳከምና ለማጥፋት ምክንያት ሲሆኑ ታይተዋል (Germa, 1964)። የአንድ ቋንቋ መሞት የዚያ ቋንቋ ባለቤት የሆነው ህዝብ ሞት የሚያስከትል መሆኑ ትልቁ አደጋ ነው። ከቋንቋው ጋር ማህበረሰቡን የሚገለፁ ልማዶች፣ ወጎች፣ የአፍ ታሪኮች፣ የሰብል አይነቶች፣ እምነቶች ሁሉ ይጠፋሉ። የእነዚህ የማንነት መግለጫ የሆኑ ተግባራት፣ ቁሶችና ሁኔታዎች መጥፋት የህብረተሰቡ መጥፋትን ያስከትላሉ።

በሃገራችን የብሄራዊ አንድነት ማስከበር ወይም አንዲት ሃገር፣ አንድ ህዝብ፣ አንድ መንግስት የሚለውን አስተሳሰብ ያራምዱ የነበሩት ገገር መደቦች፣ በእግረመንገድ አንድ ቋንቋ (አማርኛ) ገኖ እንዲወጣ ምክንያት ሆነዋል። በሌላ በኩል ህዝቦች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ማስጠበቅ ይፈልጋሉ። እነዚህ ሁለት ፍላጎቶች እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ ቅራኔ ውስጥ የነበሩ ጫፎች ናቸው። በወቅቱ የነበረው ፖለቲካዊ አተያይ፣ ብሄረሰቦች፣ በየራሳቸው ቋንቋ እየተገለገሉና በየራሳቸው ቋንቋ እየተማሩ ብሄራዊ አንድነትን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ያለማመን ችግር የነበረ ይመስላል። ይህ 'የአንድ ቋንቋ አንድ ህዝብ' አስተሳሰብ በርካታ ሃገራዊ ቋንቋዎች እንዲዳከሙ፣ የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ ህዝቦች ቋንቋቸውን ትተው ሌላ ቋንቋ እንዲለምዱ የተገደዱና (Germa, 1964) ስማቸውን እንኳ እስከመቀየር የደረሱ

ሰዎች እንደነበሩ አጥኚው ያስታውሳል። ቋንቋቸውን ተዉ ማለት ደግሞ መገለጫቸው የሆነውን ባህል ብሎም እነሱነታቸውን ተዉ ማለት ነው።

### 2.2.6. ኣገር በቀል እውቀትና የቋንቋ ትምህርት

የኣገር በቀል ህዝቦች ቋንቋ፤ ለህዝቦች ህልውናና ባህል ቀጣይነት መረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ ይጫወታል። የቋንቋው ህልውና የሚረጋገጠው ደግሞ ተወላጁ የሚቆጣጠረው የትምህርት ስርኣት ሲዘረጋ፣ በቋንቋው ግልጋሎት የሚሰጡና ባህሉን የሚያንፀባርቁ መገናኛ ብዙሃን እና ቋንቋውን ማዳበር ዓላማቸው ያደረጉ የኣገር በቀል ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ሲኖሩ ነው (Wiessner, 2007) ። ህብረተሰቡ፤ በነዚህ የትምህርት መሳሪያዎች ኣማካይነት ቋንቋውን፣ ቃላዊ ሃብቱን (ወጉን፣ ተረቱን፣ ዘፈኑን፣ እንቆቅልሹን፣...)፣ የዕህፈት ስርኣቱንና ስነዕሁፉን ያዳብራል። ዕውቀቱንም ለተከታዩ ትውልድ ያስተላልፋል።

ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ግን በህብረተሰቡ እንዲሁም በትውልድ መካከል የእውቀቱ መቀባበል ሲኖር ነው። ቅብብሉ ኣንድ ስልት ወይም መልክ የተከተለ ላይሆን ይችላል። ከመቀባበያ ስልቶቹ ውስጥ ትኩረት መስጠት፣ ጠቀሜታውን ማሳየት፣ መዘገብና መሰነድ፣ ይፋ ማድረግና ማውረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Ossai, 2010)።

**ትኩረት መስጠት-** በተለያዩ የስነቃል ኣላባውያንና ተግባራት የሚተላለፈውን እውቀት በሚገባ እንዲገነዘቡት፣ ጠቀሜታውን እንዲያውቁት የማድረግ ስራ ነው።

**ጠቀሜታውን ማሳየት፡-** ኣበእ የማህበረሰቡን ችግር ከመፍታት ኣኳያ ያለውን ድርሻ በጉልህ እንዲታይ፣ ተቀባይነቱ ከፍ እንዲል ማድረጊያ ሌላው ዘዴ ነው። ህፃናት በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያለው እውቀት ምንነትና ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ ሲገነዘቡ የበለጠ ለመማር ይነሳሳሉ።

**መዘገብና መሰነድ፡-** በተለያዩ ጣቢያዎችና ቀበሌዎች ያለውን ኣበእ በድምፅና በምስል በመሰብሰብ ማስቀመጥ ተተኪው ትውልድ በቀላሉ እንዲገነዘበው ያግዛል፡፡

**ይፋ ማድረግ፡-** (dissemination) ኣበእን ባለቤቱም ሆነ ከዚያ ውጪ የሆኑ ህዝቦች እንዲያውቁት ማድረግ፣ በህዝቦች መካከል የእውቀት ቅብብል እንዲኖርና ሽግግሩ ፈጣን እንዲሆን ማገዝ ነው፡፡

**ማሻገር (ማውረስ)፡-** ይህ ተግባር ሌሎች የማህበረሰቡ ኣባላት እንዲያውቁት ከማድረግ የዘለለ ጠቀሜታ ኣለው፡፡ እውቀቱ በኣዲሱ ትውልድ ወይም በኣዲሱ ኣካባቢ ምን ያህል

ተቀባይነት እንዳገኘና ሊተገበር እንደሚችል የሚሞከርበትም ተግባር ነው (Ossai, 2010)። ወደተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍ (ለማውረስ) ከሚያገለግሉ ዘዴዎች አንዱ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ እንዲካተትና ህፃናት የቤት እውቀታቸውን በትምህርት ቤት እንዲያዳብሩት ማለማመድ ነው፡፡

አገር በቀል እውቀት በአጠቃላይ ደንብ ወይም ስርአት ነው ማለት ይቻላል። የጋብቻ ስርዓት፣ ከልደትና ሞት የተያያዘ ስርአት፣ የአስተዳደር ስርአት፣ እድሜን፣ ፆታን፣ ደረጃን መሰረት ያደረገ ግንኙነት ስርዓት፣ የአመራረትና የምርት አከፋፈል ስርአት፣ የአካባቢ ደህንነት አጠባበቅ ስርአት፣ የምግብ አዘገጃጀትና የአመጋገብ ስርዓት፣ የእምነትና የመሳሰሉት ስርአቶች ተጣምረው የገነቡት እውቀት ነው። ህብረተሰቡ፤ እነዚህን የዕውቀት መገንቢያ ስርአቶች የሚገልፃቸው በቋንቋው ነው። ህብረተሰብን ከባህል፣ ባህልን ከቋንቋ ነጣጥሎ ማየት አስቸጋሪ የሚሆነውም ለዚህ ነው።

እነዚህን አገር በቀል ስርዓቶች የሚገልፁ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ወደ ትምህርት ቤት ወስደው በማስተማሪያነት ከተገለገሉባቸው ትምህርቱ ላይ ህይወት ዘሩበት፤ እውቀቱ እንዳይጠፋና ወደትውልድ እንዲሸጋገር በማድረግም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አደረጉ ማለት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ህፃናት ካሉበትና ከሚያዩት አለም ውጪ የሆኑ ፅንሰሃሳቦችንና ቦታዎችን እንዲያዩና እንዲገነዘቡም በር ይከፍቱላቸዋል። ህፃናቱ በማህበረሰቡ መሃል በማደጋቸው የቀሰሟቸው አገር በቀል እውቀቶች አሉ ። በነዚህ መሳሪያዎች አማካይነት የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርትም በሚያውቁት ነገር ላይ ስለሚመሰረት አዝናኝና ቀላል ይሆንላቸዋል (LittleBear, 2009)።

የአገር በቀል ዕውቀት ትምህርት ሲታሰብም ቀድሞ የሚታሰበው ቋንቋ ቢሆንም የህብረተሰቡ እውቀት፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ አተያይ ሁሉ የአበእ ተዋቃሪዎች በመሆናቸው እኩል ትኩረት ሊያገኙ ይገባል። ቋንቋ ራሱ እውቀት ነው፤ የሌሎች እውቀቶች መቅሰሚያ መሳሪያም ነው። በትምህርት ላይም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል። ህፃናት፤ የሚማሩት አፍ በፈቱበት ቋንቋ ከሆነ የትኛውንም ለደረጃው የተመጠነ ይዘት ለመረዳት አይቸገሩም። ቋንቋው አዲስ ከሆነና እውቀቱም ከልምዳቸው ውጪ ከሆነ ግን ቋንቋውና የትምህርት ይዘቱን መገንዘብ ስለሚያቅታቸው ትምህርቱን ሊጠሉት ይችላሉ። በአገር በቀል ህዝቦች ዘንድ እውቀት የሚባሉት፤ ህብረተሰቡ ከደረሰበት የብስለት ደረጃ አኳያ ስለ አለም፣ ስለተፈጥሮ፣ ስለ ፈጣሪና ስለ ራሱ ያለው ግንዛቤና ግንዛቤውን

የሚገልፅበት የቋንቋ ክህሎት ናቸው። ከካናዳና አውስትራሊያ የተገኘ ልምድ የሚያመለክተውም፣ ለአገር በቀሎቹ የተዘጋጁት ስርዓተ ትምህርቶች የየማህበረሰቡን ባህል፣ ታሪክና የአኗኗር ሁኔታ ስለማያንፀባርቁ ብዙዎቹ ተማሪዎች ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ መሆናቸው ነው (LittleBear, 2009)።

ከላይ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው ስርዓተትምህርት፣ ትምህርት ቤቶች ምን ማስተማር፣ እንዴት ማስተማር፣ ለምን ያህል ጊዜና ለምን ማስተማር እንዳለባቸው የሚወሰንበት ሰነድ ነው፡፡ በአጭሩ የትምህርት እቅድ ነው፡፡ ህፃናት በታለመም ሆነ ባልታለመ መንገድ የቀሰሙትን እውቀት/ ክህሎት መነሻ በማድረግ አዳዲስ እውቀቶችን/ ክሂሎችን ለማስተማር የሚዘጋጅ የትምህርት እቅድ ነው (Abreha, 1998; Pinar, 2003; Ornstein and Hunkins, 2004)። ከአበእ ትምህርት አኳያ ካየነው ደግሞ አንድ ህብረተሰብ ጠቃሚና የኔ የሚላቸውን እውቀቶች ወደተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ታልሞና ታስቦበት የሚዘጋጅ የትምህርት ሰነድ ነው (Pai, 1990)። እውቀቱ እንዳይረሳ፣ እንዳይጠፋና አንፃራዊ የሆነ ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረጊያም ነው። ለምሳሌ በትግራይ ውስጥ **ጥሕሎ** ባህላዊና ተወዳጅ ምግብ በመሆኑ ህብረተሰቡ ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍለት ይፈልጋል እንበል። እስከተወሰነ ጊዜ በቃል እየተላለፈ፣ በተግባርም እየተከወነ ሊቆይ ይችላል። ሆኖም ሽግግሩ የስርጭት ስፋቱም ሆነ እድሜው የተወሰነ ነው። ሃገራዊ ያልሆነ ወይም አዲስ የአመጋገብ ስርአት ቢያጠላበትና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መልሶ መስራት ቢፈለግ ማስታወሱ ሊቸግር ይችላል። በትግርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ወይም አጋዥ የንባብ መፅሃፍ ውስጥ በምንባብ መልክ ቢቀርብ ግን ስርጭቱ ይሰፋል። አዲሱ ትውልድ ከባህሉ ጋር ስለሚተዋወቅ ቀጣይነቱም አስተማማኝ ይሆናል።

**ጥሕሎን** ለማስተዋወቅ በሚደረገው ጥረት እግረመንገድ ከምን እንደሚሰራ፣ መገልገያና መመገቢያ መሳሪያዎቹ፣ የአመጋገብ ስርአቱ፣ ከምግቡ ጋር መቅረብ ያለባቸው የወጥ ቅመማቅመምና የመጠጥ አይነቶች ይዘረዘራሉ። ስለዚህ ጥሕሎን አስመልክቶ የቀረበው ምንባብ የጥሕሎን አሰራር፣ አቀራረብና መገልገያ መሳሪያዎች ስለሚያቀርብ ሙሉ ስእል መፍጠር ይችላል።

ይሁንና የቋንቋ ስርአተ ትምህርት በአብነት የቀረበውን የሚመስሉ እውቀቶች ማቅረብ እንዳለበት ቢታወቅም ባህላዊ የሆነውን ዕውቀት ሁሉ ሊያካትት አይችልም፡፡ አበእ የእውቀት፣ የክህሎት፣ የዝንባሌ፣ የእምነትና የቁሳዊ ሃብቶች ክምችት ነው፡፡ የቋንቋ

ስርዓተትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች እነዚህን ሃብቶች የማስተላለፍ ግዴታ እንዳለበት ቢታወቅም አላማው ቋንቋን ማስተማር እንደመሆኑ እነሱን ብቻ ይዞ አይቀርብም (Woube, 2004)። በዋናነት የቋንቋ ክሂሎችንና እውቀትን ማቅረብ አለበት።

ከላይ የተጠቀሱት የቋንቋ አላባዎች ግልጋሎት ላይ የሚውሉት በህብረተሰቡ የእለት ተእለት እንቅስቃሴና የመገናኛ አውዶች ውስጥ ነው፡፡ የቋንቋ ስርአተ ትምህርት እነዚህን የህብረተሰብ መገለጫ የሆኑትን አውዶች በቋንቋ ማስተማሪያ ግብአትነት ይገለገልባቸዋል። አንብቦ መረዳትን፣ አዳምጦ ተግባራት መፈፀምን ለማለማመድ፣ የህብረተሰቡን ማህበራዊ መዋቅር፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ እምነት፣ ውበት፣ አመራረት የሚገልፁ ተረቶችን ወይም ወጎችን ሊወስድ ይችላል። ተማሪው በተወለደበት ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን የአመራረት፣ የሞት ወይም የልደት ስርአት አስመልክቶ ንግግር እንዲያደርግ፣ ፅሁፍ እንዲያዘጋጅ የሚጠይቁ ተግባራትን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ እያንዳንዱን አውድ ለመግለፅ የሚያገለግሉ ቃላትን፣ ዘይቤዎችን፣ ፈሊጦችን እንዲገነዘብ፣ እሱም በተገነዘበበት መንገድ እንዲገለገልባቸው የሚያደርጉ መልመጃዎችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ስርዓተትምህርቱ እነዚህን ነጥቦች የሚገልፁና ህብረተሰቡ በጣም አስፈላጊ በመሆናቸው ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚፈልጋቸው እውቀቶችን ማካተት አለማካተቱን በማየት ላገር በቀል እውቀት ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው መገምገም ይቻላል (Semali, and Kincheloe 1999)። ህፃናት በህብረተሰቡ መሃል ያደጉ እስከሆኑ ድረስ እቤት እያሉ የሚያውቁት፣ የለመዱትና ይገለገሉበት የነበረው ቋንቋ፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲያገኙት የበለጠ ለማወቅ ይበረታታሉ (Settee, 2007)። አዳዲስ እውቀቶችን በቀላሉ ለመጨበጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። አፍ የፈቱበት እንደመሆኑ የሚተላለፈውን መልእክት ለመረዳት አይቸገሩም። ማህበረ-ባህላዊና ህዝባዊ እሴቶችን ለይቶ ለማወቅም ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል። የይዘቱ ማቅረቢያ የሆኑት ቃላዊ ሃብቶችም (ተረቶች፣ ትረካዎች፣...) ቀድሞውኑ የሚያውቋቸው ስለሆነ የመማር ሂደቱ አዲስ አይሆንባቸውም።

የግንባታውያን አተያይ የሚመዘዘው ከዚህ አይነቱ የትግበራ ሂደት ነው፤አገር በቀል እውቀትን በመሰረትነት ተጠቅሞ አዲሱን አስተሳሰብ ማስረፅና መገንባት። የተማሪዎችን (የህፃናትን) ቀዳሚ እውቀት ምን እንደሆነ አውቆ ካሪኩለሙን ማዘጋጀት ማለት ቃላዊ በሆነ መንገድ ከማህበረሰቡ ያገኙትን እውቀት በመነሻነት መገልገል ማለት ነው። ይህም ህፃናት፤ የሚቀርብላቸውን አዲስ ፅንሰ ሃሳብ ካለፈ ልምዳቸው ጋር አያይዘው ለመገንዘብ

ያግዛቸዋል። በተለይ በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የህፃናቱ ቀዳሚ እውቀት የሚያገኙት ከቤትና ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ነው። በየግንባታውያን አስተሳሰብ እውቀትን መገንባት፤ በነበረው ላይ መጨመርን ብቻ አያመለክትም። ቀዳሚው እውቀት ህፃኑ ከበቀለበት ማህበረሰብ የተገኘና በሚገባ የሚታወቅ መሆኑ፣ አዲሱ እውቀትም ከነባሩ ጋር ተያያዥነት ባለው መንገድ መቅረቡ መረጋገጥ አለበት (Semali and Kincheloe, 1999)።

አገር በቀል እውቀት (ሰው፣ ባህል፣ ቋንቋ፣) ከመሬትና ከመሬት በላይ ካሉ ነገሮች፣ ክስተቶች፣ ሁነቶችና ድርጊቶች ጋር የጠበቀ ትስስር ያለው ዕውቀት ማለት ነው / Elleny, 1996; Hooley, 2009; Settee, 2007/። አገር በቀል ህዝቦች ከመሬትና ከአካባቢ ጋር ለተያያዙ ስያሜዎችና ፅንሰሃሳቦች ልዩ ግምት የሚሰጡትም ለዚህ ይመስላል። ለምሳሌ በተጋሩ ዘንድ **ገዛና፣ ዓድኻን ዓውድኻን፣ መረበትካ፣ ዓደይ በለ ህበይ ጋራ፣ ዓዲ ኣይብሉ፤ ዓውዲ ኣይብሉ፤ መዳሕንተይ ዝተቐብረሉ፣...** (ቀያችን፣አገርህና አውድማህ፣ የትውልድ መንደሬ፣ ገደል አፋፍ ላይ የሚኖር ዝንጀሮም እንኳ አገሬ ይላል፣ አገር የለው አውድማ የለው፣ እትብቴ የተቀበረበት፣...) የሚሉት አነጋገሮች የተጠቃሾቹን ተወላጅነት ወይም ኢተወላጅነት የሚገልፁና ከተወለዱበት መንደርና አካባቢ ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ **ዓዲን ዓውዲን** (አገርና አውድማ) የያዟቸውን ነገሮች ሁሉ መንከባከብ አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም የመሬትና በመሬት ላይ ያሉ አገር በቀል እንስሳት፣ እፀዋት፣ የእህል ዘር፣... መጥፋት ወይም በሌላ መተካት፣ የቋንቋውን የህብረተሰቡን አገር በቀልነት ይሸረሽረዋል። በአገር በቀል ህዝብ፣ በተፈጥሮ፣ በፍጡርና በፈጣሪ መካከል ያለውን ግንኙነትንም ያላላዋል።

አገር በቀል ህዝብ፤ ከላይ ፈጣሪ ከታች ደግሞ ፍጡር (ሰው፣ እነስሳት፣ እፀዋት) እንዳሉ ያምናል (Settee, 2007)፡፡ ፍጡራኑን የሚያውቃቸውም በጋራ ነው፡፡ የእንስሳትና የእፀዋት ህልውና ለሰው ልጅ ህልውና አስፈላጊ እንደሆኑ ያምናል፡፡ አገር በቀል ህዝብ ማህበራዊነትን እንጂ ግለኝነተን አያቀነቅንም። ማህበራዊነቱ በጅጊ፣ በወንፈል፣ በፀሎት ጊዜ፣ በመኣድ፣ በትምህርት፣ በበሽታ ሽኝት፣ ወዘተ.  ይገልፀዋል። ለምሳሌ አንድ የትግራዋይ አባወራ፣ የአካባቢ ሽማግሌ ወይም የሃይማኖት አባት ለስራ ሲሰማሩ ወይም መልካም ምኞታቸውን ሲገልፁ "እኔ"ን ወይም "የእኔ"ን ብቻ አያስቡም። ሰውን ብቻም ሳይሆን ፈጣሪንም ፍጡርንም ሁሉ ያስባሉ፡፡

ሰላም ዘሕደረ ሰላም የውዕለና(ፈጣሪ) ፤ዝሓመመ ይምሓረልና፤ ዝወፈረ ይኣክበልና፤ ሃገርና ሰላም ይግበረልና፤ መንግስትና የዕንዐልና፤ ማይ ብዕርያት እኸሊ ብፍርያት ይሃበና፤ ሰናይ ዘበን ይግበረልና፤... (ሰላም ያሳደረ ሰላም ያውለን፣ የታመመን ይማርልን፣ ከቤቱ የወጣን በሰላም ይመልስልን፣ አገራችንን ሰላም ያድርግልን፣ መንግስታችንን ያጥናልን፣ ዝናቡን ጤናማ ምርቱን ፍሬኣማ ያድርግልን፣ የጥጋብ ዘመን ያድርግልን፣...) በማለት ይፀልያሉ፡፡ ልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚሰጡ እንስሳትም ይታሰባሉ፡፡ አንዲት እማወራ ለገበሬ ባልዋ መልካሙን ስትመኝ በሬዎቿንና ላሞቿንም አትረሳም፡፡ **ሓረስታይ ሰብኣየይን ተስታይ ብዕራየይን ማዕተብ ላሕመይን ደው የብለለይ** (ገበሬ ባሌን፣ አባት በሬየንና ላሜን ያኑርልኝ) በማለት በሰው፣ በእንስሳትና በፈጣሪ መካከል ያለውን ግንኙነት አጉልታ ታሳያለች፡፡ ከነዚህ ምሳሌዎች መረዳት የሚቻለው ከ"እኔ" ይልቅ "እኛ"፣ ከ"የኔ"ይልቅ "የኛ" ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑ ነው። ቀጥሎ የሚቀርበው የህዝብ የዘፈን ግጥም ይህንን እውነት ያጠናክራል።

| | |
|---|---|
| **ኣቦኻ እንተሞተ ሰሙን ሓዘን፣** | *አባት የሞተ እንደሆን ሳምንት ነው ሃዘኑ* |
| ***ኣደኻ እንተሞተት ሰሙን ሓዘን፣*** | *እናትም ብትሞት ሳምንት ነው ሃዘኑ* |
| ***ሓፍትኻ እንተሞተት ሰሙን ሓዘን፣*** | *እህትም ብትሞት ሳምንት ነው ሃዘኑ* |
| ***ሓውኻ እንተሞተ ሰሙን ሓዘን፣*** | *ወንድምም ከሞተ ሳምንት ነው ሃዘኑ* |
| ***ዓድኻ እንተሞይታ ሕማም መርዘን።*** | *ኣገር ከሞተች ግን **መርዘን**[3] ነው ህመሙ* |

የአባትም የእናትም ሆነ የሌላ ዘመድ ሞት ግለሰባዊ ጉዳት ከመሆኑም ሌላ ጥቂት ጊዜ አዝነው የሚረሱት ነው። ሌላው የህብረተሰብ አባልም አፅናኝ ሆኖ ሃዘንተኛውን ሊያረሳሳው ይችላል። የአገር ጥቃት የሁሉም ሰው ሞት፣ የሁሉም አባል ሞት ነው። አፅናኝ የለም፣ ስለሆነም ሃዘኑ እንደ **መርዘን** አሰቃቂና ራስን የሚያስት ነው። **መርዘን** የተነሳበት ሰው ከስቃዩ ገደብ ማጣት የተነሳ ራሱን መቆጣጠር አይችልም። የሚወስዳቸው እርምጃዎችም ራስን እስከ ማጥፋት የሚደርሱና አሰቃቂዎች ናቸው። ኣገር የሞተችበት ሰውም ራሱን የሚያኖርበት ቦታ የለውምና መቼ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት ኣያውቅም። በኣጠቃላይ፣

[3] በሳምንት ወይም በተወሰኑ ቀናት ልዩነት የሚከሰት ከፍተኛ የራስ ምታት

እንደ ኣገር የመሳሰሉ የጋራ መኖሪያ የሆኑት ሁሉ በጋራ ሊጠበቁ እንደሚገባ የሚያሳስብና የወላዊነትን አስተሳሰብ የሚያጠናክር ነው።

በተለይ የፅሁፍ መግባቢያ በሌላቸውና የፅሁፍ የቅርብ ተሞክሮ ባላቸው ህዝቦች ውስጥ፣ እውቀትን ለማስረፅ፣ ባህልን ለማስተዋወቅና ለመጠበቅ ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የንግግር ቋንቋ ነው (Settee, 2008)። ስለሆነም ኣገር በቀል ህዝቦች፤ በተለይ የእድሜ ባለፀጎች ቋንቋችን ከጠፋ ባህላችን ብቻ ሳይሆን እኛነታችንም ኣብሮ ይጠፋል የሚል እምነት ኣላቸው (Settee, 2007)፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ፤ የግንኙነት መመስረቻ፣ በግንኙነት ውስጥ የተፈጠረን እውቀት፣ ባህል፣ እምነት ማስተላለፊያ፣ መውረሻና ማውረሻ ሆኖ የሚያገለግል መሳሪያ በመሆኑ ነው፡፡ በኣገር በቀል ቋንቋ ላይ የሚደረግ የሃገር ውስጥም ሆነ የውጪ ተፅእኖ በኣገር በቀል ህዝብ ህልውና ላይ ያነጣጠረ ተፅእኖ እንደሆነም ይታመናል። ኣንድ ቋንቋ ይበልጥ መግለፅና ማጉላት የሚችለው የመጣበትን ኣካባቢና ህዝብ እንጂ በተውሶ እየተገለገለበት ያለውን ኣካባቢና ህዝብ ኣይደለም (ተስፋዬ ፣ 1994 እና Settee, 2007;)፡፡ ቋንቋው ከተፅእኖ ወጥቶ ለትውልድ እንዲተላለፍ፣ ለትምህርት፣ ለጥናትና ምርምር ኣገልግሎት እንዲውልና ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እገዛ እንዲያደርግ በታቀደ መልኩ ኣደራጅቶና ጠብቆ መገልገልን ይፈልጋል (ቅጥምባ 2002 ዓ.ም.)፡፡

የቋንቋ ግልጋሎት የሚገለፀው ደግሞ በዘይቤዎች፣ ፈሊጦች፣ አውዳዊ ፍቺዎች፣ ተረቶችና በመሳሰሉት የቋንቋ አጠቃቀሞች ነው። ኣገር በቀል እውቀትንና ቋንቋን ለማቀብ፣ ከጥፋት ለመታደግና ወደቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ሌላው መወሰድ የሚገባው እርምጃ፣ የእድሜ ባለፀጋ ሰዎች ትረካዎችን፣ ተረቶችና ወጎችን፣ በድምፅና በፅሁፍ መዝግቦ መያዝ ነው። እነዚህን ኣገር በቀል ጥሬ ሃብቶች በመጠቀም የቋንቋ ስርዓተትምህርት ወይም መማሪያ መፅሐፍ ማዘጋጀት ቀጣይ ተግባር ይሆናል።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በኣገር በቀል ህዝቦች ዘንድ ቤተሰባዊ ግንኑነት ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ እያንዳንዱ ኣባል የተገኘበትን የዘር ሃረግ ማወቅና ማክበር ይጠበቅበታል (Settee, 2007)። በትግራይ ውስጥ የሚገኘውና ትግርኛ ተናጋሪ የሆነው ኣገር በቀል ህዝብ የቤተሰብን ጎናዊ እና ኣምዳዊ ግንኙነት ጠንቅቆ ማወቅ ማክበር በጎ አመለካከት ማሳየት ኣለበት። ለምሳሌ ኣንድ ሰው የኣጎቱን ልጅ 'ዘመዴ ነው' ቢል ኣድማጭ በሁለቱ መካከል ጠብ ኣለ ብሎ ይገምታል፡፡ እንደባህሉ ግን በጣም ካቀረበው፤ ወንድሜ ነው ይላል። ካልሆነም የኣጎቱ ልጅ ነው ይላል፡፡ ወላጆችም ልጆቻቸውን ቤተሰባዊ ግንኙነቶቹን

**ኣቦ፣ ኣደ፣ ኣባሕጎ፣ እናሕጎ፣ ሓወቦ፣ ኣሞ፣ ሓትኖ፣ ኣኮ፣ ወዲሓወቦ፣ ወዲሓትኖ፣ ወዲኣሞ፣ ወዲኣኮ፣...** (ኣባት፣ ወንድ አያት፣ ሴት አያት፣ የአባት ወንድም፣ የአባት እህት፣ የእናት እህት፣...) ማስለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የእንደነዚህ አይነቶቹ ገላጭ ቃላት ግልጋሎት ዝምድናን ለመቁጠር ማስቻል ብቻ ሳይሆን በነገሮች መካከል ያለን ግንኙነት እንዲያውቁና ለተገቢ ቦታ ተስማሚ ቃል(ቃላት) መርጦ መገልገል የሚያስችል እውቀት እንዲገበዩም ጭምር ነው።

ኣገር በቀል እውቀት (ኣበእ) የቁሳዊና መንፈሳዊ ህይወት ትእምርት በመሆኑ አንዱ ህብረተሰብ ከሌላው ህብረተሰብ ተለይቶ ይታወቅበታል። በአንድ አበ ህዝብ ውስጥ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ እምነት፣ አመራረትና ምርት ለውጥ ሊመጣ ይችላል። በነዚህ ላይ ለውጥ ሲመጣ የነሱ መግለጫ የሆነው ቋንቋም ይለወጣል። የምዕራባውያኑ ባህል መስፋፋትና የአበእ ቦታ እያጣ መምጣት በቋንቋም ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያደርሳል። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ የሚታየውን የተረት አቀራረብ ስርኣት ብንመለከት የኣውሮፓውያን ቋንቋ በኣገር በቀል ቋንቋዎችና እውቀት ላይ ጥላውን እያጠላባቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ነባሩ አቀራረብ

**"ነበረያ ነበረ** ተረት ተረት"

**"እንታይ ነበረ** የላም በረት (የመሰረት)"

**"ቀደም ሓደ ኣባ.... ዝበሃሉ ፈላሲ ነበሩ** በድሮ ጊዜ ኣባ ... የሚባሉ ሰው ነበሩ፣..." የሚል ነበረ።

ይህ ተረት አሁንም በህፃናት ሲነገር ይሰማል። አቀራረቡ ግን ከነባሩ ይለያል። ምክንያቱም ህፃናቱ **"አንድ ኣባ... ነበረ፤ አንድ መነኩሴ ነበረ"** ሲሉ ይሰማል።

ኣገር በቀሉ ኣተራረክ ይህንን አይቀበልም። ምክንያቱም "ኣባ" በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ የተከበሩ መነኮሳት መጠሪያ በመሆኑ ነው። ስለሆነም "በኣንተታ" የሚገለፅ ሰው አለመሆኑ ይነገራል። በቋንቋው ስርኣት አክብሮታዊ አገላለፅ (ደረጃን፣ እድሜን፣ ሙያን ፣...መሰረት ያደረገ አጠራር) መጠበቅ እንዳለበት ያመለክታል። ነገር ግን ህፃናቱ ሃገራዊ ያልሆነ የተረት አቀራረብ (Once upon a time there was a Man, a Priest, Pope,...) ስርኣትን ተከትለው የትግርኛውን የአቀራረብ ስርኣት ሲቀይሩት ይታያል። በተለይ ጥናቱ በሚካሄድበት፣ ኣጥኚው በተወለደበትና ባደገበት ክልል (ትግራይ) የአክብሮት መግለጫዎቹ የተጠሪውን ብቻ ሳይሆን የጠሪውንም ማንነት ያመለክታሉ። በባህሉ፤ የጠሪው ሰው እድሜ

ከተጠሪው(ዋ) ዕድሜ የሚበልጥ ቢሆን እንኳ ክህነት የተቀበለን ሰው፣ የወለደችን ሴት፣ መምህርን በአንተ/ቺታ መጥራት እንደነውር ይቆጠራል። ስርአተአጠራሩ ሲለወጥና የአክብሮት ፅንሰሃሳብ ሲጠፋ ስርአቱን ይገልፁ የነበሩ ቃላትም ይጠፋሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ የምርት አይነት ሲለወጥ የአመጋገብ ስርአት አብሮ ሊለወጥ ይችላል። በመግለጫነት ያገለግሉ የነበሩ ቃላትም አብረው ይጠፋሉ። የነዚህ ድምር ውጤትም የአገር በቀል እውቀት መጥፋትን ያስከትላል።

በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ፤ ተረቶችና የአፍ ታሪኮች የቋንቋ ክህሎትንና እውቀትን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። የህብረተሰቡን ፍልስፍና፣ እምነት፣ ታሪክ፣ ወዘተ. ከማስተማራቸውም በላይ በታሪኩ ውስጥ ልዩ ልዩ የአገላለፅ ስልቶችን፣ ስርአተአገባብን፣ የቃላት አውዳዊ ፍቺን እና የንግግርና የማድመጥ ክሂሎችን የማስተማር ድርሻ ይጫወታሉ። ተማሪውም እነዚህን የቋንቋ አጠቃቀሞች በመቅሰም በእለት- ተእለት ግንኙነትና በመማር ማስተማር ሂደት ይገለገልባቸዋል።

ይህ ጥናት በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን መማሪያ መፃህፍትና መርሃትምህርት ላይ ያተኮረበት ምክንያትም የህፃናቱ ከቤት ይዘው የመጡት እውቀት ከመደበኛው ትምህርት ለሚቀስሙት እውቀት መነሻ ሆኖ ማገልገል መቻሉን ለመፈተሽ ነው። የመደበኛው ትምህርት ጀማሪ የሆኑት ህፃናት በመነሻነት የሚያገለግላቸውና የበለጠ ለማወቅ የሚያነሳሳቸው ከአካባቢያቸው ይዘው የመጡት እውቀት ነው። ስርዓተትምህርቱም ህፃናቱ ከቤት ይዘው የመጡትን የብስለት ደረጃ ተጠቅሞ አዲስና ላቅ ያለ እውቀት የሚያስጨብጥ ሆኖ ሊዘጋጅ ይገባል።

አገር በቀል ያልሆነ ወይም ገብ ስርአተትምህርት በሚገለገሉ ሃገሮች ውስጥ በትግበራ ወቅት ለቋንቋው የተለየ ጥንቃቄ ሲደረግለትና አገር በቀል የሆኑትን ቋንቋዎች ለመዋጥ የሚያስችለው ጉልበት እንዲያገኝ ሲደገፍ ይታያል (Mule, 1999)። ተማሪዎች፣ የአገር በቀል እውቀት ማቅረቢያ መሳሪያ የሆነውን ቋንቋ መጠቀም ካልቻሉ ደግሞ አገር በቀል እውቀቱን ሊማሩት፤ ራሳቸውን ወይም ማንነታቸውን ሊያውቁ አይችሉም፤ ባለማወቃቸው ደግሞ መወቀስ ያለባቸውም አይመስልም። ምክንያቱም በተገለፁት ተግባራት አማካይነት ህፃናቱ ስለራሳቸውና ራሳቸውን እንዳያውቁ ማንነታቸውን እንዲንቁ ግፊት እየተደረገ ያለ ስለሚመስል ነው።

## 2.2.7. የትውፊት ሚና በአገር በቀል እውቀት ትምህርት ውስጥ

ትውፊት የህብረተሰብን ባህል ከመጠበቅና እውቀትን ከማዳረስ አኳያ የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ የእውቀትና ክህሎት ትምህርትን በማስተላለፍ ረገድም ሰፊ ግልጋሎት ያበረክታል፡፡ ትረካው ሲቀርብ ከመነገሪያ አውዱ፣ ከተናጋሪው ማንነት፣ ከአቀራረብና ከተነገረበት ጊዜ አኳያ ፍቺ የሚሰጥባቸው መልእክቶች ይተላለፋሉ፡፡ የማህበረሰቡን ታሪክ የማስተዋወቅ ሚናም ይጫወታል። የትውፊቱ አቅራቢዎች እድሜ ከፍ ሲል ታሪኩም የዚያኑ ያህል ሩቅ ዘመን ወደሁዋላ ተመልሶ የሚያወሳ ይሆናል። ከአባቶች ይልቅ አያቶች፣ከአያቶች ይበልጥ ደግሞ ቅድመአያቶች አገር በቀሉን ታሪክ በምልአት ሊያቀርቡት ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም እነሱም ከአባት፣ አያት ወይም ቅድመአያቶቻቸው ያገኙትና በዚያ ዘመን የነበረውን ሁኔታ የሚያስታውስ ስለሚሆን ነው። የዚህ አይነቶቹ የእድሜ ባለፀጋዎች በትልቅ ሙዚየም ወይም ቤተመፃህፍት የሚመሰሉት በዚህ ምክንያት ነው (Settee, 2007)።

የአፍ ታሪኮች፣ ተረቶች፣ ቀልዶችና ጭውውቶች በህብረተሰቡ ውስጥ የአጠቃላይ እውቀት ማስተላለፊያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በመደበኛው ትምህርት ውስጥ ደግሞ የማድመጥንና የመናገርን ክሂል ለማስተማርም ተመራጭ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ተዝናንተው ስለሚከታተሏቸውና ከፍ ያለ የአሳታፊነት ሚና ስላላቸው ነው። ማድመጥና መናገር፤ መቀበያና ማፍለቂያ ክሂሎች ስለሆኑም ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለመከታተልና በመጠየቅና ምላሽ በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆኖ ለመገኘትም በመሳሪያነት ያገለግላሉ፡፡ በሚቀርቡት ትረካዎች፣ ተረቶችና የቃል ግጥሞች ውስጥ በፈርጥነት የሚያገለግሉ ዘይቤዎች፣ ትእምርቶችና የቋንቋ መዋቅሮች ደግሞ ተማሪው በፈርጦቹ ከመደነቅ አልፎ በንግግርና በፅሁፍ ተግባቦት ጊዜ መገልገል የሚችልበትን ዕድል ይፈጥሩለታል።

ትምህርት (Education)፤ በባህል ላይ ቆሞ ተፈላጊውን የባህል ለውጥ ለማምጣት የሚጥር ሲሆን አገር በቀል እውቀት ደግሞ እንደ አንድ የትልቅ ህንፃ መሰረት ሊወሰድ ይችላል፡፡ መሰረቱም የቀጣዩ ትምህርት መነሻና ምቹ ሁኔታ መፍጠሪያ ሆኖ ያገለግላል (Pai, 1990)። ህፃኑ ከቤት ይዞት የመጣ መሰረታዊ እውቀት ከሌለ አዲሱን እውቀት የማስጨበጡ ተግባር ከባድ ሊያደርገው ይችላል።

ትምህርት፤ አንድን የእውቀት ወይም የክህሎት ዘርፍ ብቻ ለማስተማር ተብሎ አይሰጥም። ለዕህፈት፣ ለንባብ፣ ለስሌት... ብቻ የሚል ገደብ የለውም። ህብረተሰቡ ወደ ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት መተላለፍ አለበት፤ ወይም ቀጣዩ ትውልድ ሊወርሰው ይገባል የሚለው እውቀት፣ ክህሎት ወይም ዝንባሌ ካለ በልዩ ልዩ የስነቃል ክፍሎች (Pai, 1990) ያቀርባቸዋል። ተረቶች፣ እንቆቅልሾች እና ሌሎች ወጎች በሚነገሩበት ጊዜ ቋንቋ እና የቋንቋው አቀራረብ ውበት፣ ምስጢራዊነት፣ የቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርአት የትምህርቱ አካላት ሆነው ይቀርባሉ። በሚተላለፈው መልእክት አማካይነት ደግሞ የህብረተሰቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እውቀቶች ይነሳሉ። ተማሪውም እነዚህን ሁሉ ይቀበላል፤ ይማራል። አስተማሪዎቹ ግን አብዮተ ፀሎት፣ መደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ ገበያ፣ ወላጆች፣ ጓደኞች፣ የሃይማኖት አባቶች ሊሆኑ ይችላሉ። በተለያዩ ሰዎች፣ በተለያዩ ተቋማትና አውዶች የሚቀርበው ትምህርት የተለያየ ቢመስልም ዓላማው ግን የአንድን ህብረተሰብ አገር በቀል እውቀት ለመቀበል የሚያስችል ባህርይን ማላበስና እንዲተውኑት ለማድረግ የሚያስችል መሳሪያ ማስታጠቅ ነው።

አዲሱ የኢትዮጵያ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (TGE 1994) መግቢያ ትምህርት የሰው ልጅ ለመኖር ሲል ለዘመናት ባደረገው ትግል ውስጥ ያካበተውን ልምድ፣ አዳዲስ ግኝቶችን፣ እሴቶችን ለተተኪው የማስተላለፍ ሂደት መሆኑ ያስረዳል። ገለፃው፤ ትምህርት የባህል፣ የማህበረሰብና የአካባቢ መግለጫ ሆኖ እንደሚያገለግል ያመለክታል፡ መንግስትም በእኩልነት ላይ ተመስርቶ የዜጎች ባህልንና ልምዶችን የማሳደግ፤ የማበልፀግና መሰረታዊ መብቶችን፣ ሰብአዊ ክብርንና ዲሞክራሲያዊ ባህልን የማስጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ያብራራል፡፡ በተለይ በአንደኛ ደረጃ ህፃናት አፍ በፈቱበት ቋንቋ ሊማሩ እንደሚገባ ይጠቁማስል።

የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ 1987 ዓ.ም. ብሄር ብሄረሰቦች በቋንቋቸው እንዲገለገሉና ቋንቋቸውን እንዲያሳድጉ የሚያግዝ ዝርዝር ፖሊሲ አውጥቷል፡፡ ማንኛውም ብሄረሰብና ህዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለፅ፣ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው። ባህልን ሳያገናዝቡ የሚነድፉት የልማት እቅድ ውጤታማ አይሆንም። በአጠቃላይ ፖሊሲው ከቀድሞዎቹ በተለየ ሁኔታ ለብሄረሰቦች ቋንቋዎች እድገትና ለአገር በቀል እውቀት መስፋፋት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው (ባቱሚ 1998 ዓ.ም.)፡፡ የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀፅ 5 እና አጠቃላይ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ

አንቀፅ 3.5 (TGE, 1994)ለትምህርታዊ ጠቀሜታና ለብሄሮችና ብሄረሰቦች በመረጡት ቋንቋ የመገልገል መብት መከበር ሲባል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በብሄረሰብ ቋንቋ እንዲሰጥ ደንግጓል (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ 1987)።

በሃገራችን እስከ 1984 ዓ. ም. ድረስ ይሰራባቸው የነበሩት የቋንቋ ስርዓተትምህርቶች አንድን ቋንቋና ባህል ብቻ የሚያንፀባርቁ ነበሩ። በሁለቱም ስርአቶች የነበሩት ህጎችም የአፍ መፍቻ ቋንቋ አገልግሎትን የሚያግዱ ነበሩ። በዚህ ምክንያት የቋንቋ ትምህርት መርሃ ትምህርትና መማሪያ መፃህፍቱ አገር በቀል እውቀትን ማካተት የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ አልነበረም።

መደበኛ ትምህርት፤ የአንድን አገር በቀል ህዝብ አገር በቀል እውቀት ለማስፋፋት፣ ጠብቆ ለማቆየትና ወደቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ በመሳሪያነት ያገለግላል። አገር በቀል እውቀትን አጥፍቶ አዲስና የራስ ያልሆነ ባህል ለማስረፅም (Pai, 1990) ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ አውሮፓውያን መምህራንና አውሮፓዊ የትምህርት መሳሪያዎች ብቻ ግልጋሎት ይሰጡ በነበሩባቸው ዓመታት የታየው ነገር ኢትዮጵያዊ ባህል በአውሮፓዊ የመተካት ስራ ነበር። አማርኛ ቋንቋ በመላ ኢትዮጵያ የአፍመፍቻ ቋንቋን ተክቶ እንደ ትምህርትና እንደ ማስተማሪያ ቋንቋ ባገለገለባቸው ዘመናትም ተመሳሳይ ነገር ነበረ የታየው። ኦሮሞውም፣ ትግራዋዩም፣ ጉራጌውም፣ ሶማሌውም… የአማርኛ ቅኔ፣ የአማርኛ ፈሊጦች፣ የአማርኛ ተረትና ምሳሌ፣ የአማርኛ የተረት መፃህፍት፣ የአማርኛ ልቦለዶች እንዲያነብ በዚያውም የአማራውን እውቀትና ባህል እንዲያጠና ነበር ሲደረግ የነበረው። ይህንን እውቀት መቅሰሙ በራሱ ችግር አይደለም። ችግር የሚሆን የራሱን እንዳያውቅ የሚከላከሉ ወይም በራስ ቋንቋ የመማር ፍላጎትን የሚገቱ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ነው።

ህዝቦችም ቋንቋዎቻቸውን የማሳደግ፣ ባህሎቻቸውን የመግለፅ፣ የማዳበር፣ የማስተዋወቅና ታሪካቸውን የማቆየት መብት አላቸው። የተለያዩ ባህሎች ባላት ሀገር አንድን ባህል ብቻ ይዞ በመነሳት ከላይ የተገለፁትን መብቶች ማረጋገጥ፣ አገር በቀል እውቀትን ማስረፅና የተፈለገውን የትምህርት ውጤት ማግኘት ስለሚያስቸግር ነው (Teklehaimanot, 1999)።

የማእከላዊና ክልላዊ መንግስታትም በአዋጅ ቁጥር 41/1993፣ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ስርዓተትምህርትን እንዲያዘጋጁና በተግባር ላይ እንዲያውሉ፣ መብቱ ተሰጥቷቸው (TGE, 1994) የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶችና ማስተማሪያ መፃህፍት ማዘጋጀታቸው ይታወቃል፡፡ በትግራይ ክልልም የትግርኛ፣ የሳሆና (ኢሮብ) የኩናማ አፍ ፈት የሆኑት ህዝቦች የየቋንቋቸው ስርዓተ ትምህርቶች በማዘጋጀት ህፃናትን ማስተማር ጀምረዋል። የዚህ ጥናት ትኩረትም በክልሉ የትግርኛ ቋንቋን ለማስተማር በተዘጋጁት የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ካሪኩለሞች (መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሃፍና የመምህሩ መምሪያ) ውስጥ የህገር በቀል እውቀት ትኩረት ተሰጥቶትና ታስቦበት እንዲማሩትና እንዲያውቁት እየተደረገ መሆኑን መፈተሽ ነው።

## 2.2.8. የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በኣራቱ የትምህርት ዓምዶች ውስጥ

በዩኔስኮ ዘገባ መሰረት በ21ኛው ክፍለዘመን ትምህርት (Education) በኣራት መሰረታዊ ዓምዶች ተከፍሎ ሊሰጥ ይገባል (UNESCO on line)። እነዚህ ኣራት የእውቀት ምድቦች፣ **ለማወቅ፣ ለመቻል፣ ማሕበራዊነትን ለመልመድ፣ እና ስብእናን ለመገንባት መማር** (learning to know, to do, to be and *to live together*) የሚሉ ናቸው። እነዚህ እውቀቶች በህይወት ዘመን በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ ሰዎችና ነገሮች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የሚዳብሩ እንጂ በኣንድ ጊዜ፣ በኣንድ ውሱን ቦታ፣ በኣንድ የህይወት ልምድ የሚገኙ ኣይደሉም። ስለዚህ ሰዎች እንደችሎታቸው፣ እንደሚውሉባቸው ቦታዎችና የሚገናኟቸው ሰዎች ኣይነት በተለያየ ጊዜና መጠን እውቀቶቹን ሊቀስሟቸው ይችላሉ።

ኣራቱ የትምህርት ኣምዶች ዓላማን እግብ የሚያደርሱ ይዘቶችን ለመምረጥ፣ ለማመጣጠንና ሂደቱን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችሉ ናቸው (Amare, 2008; UNESCO on line)። ዓምዶቹ፣ በጥቂት ምንባቦች ወይም በኣንድ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ባሉ ምንባቦችና ይዘቶች የሚገለፁ ኣይደሉም። በጣም ሰፋፊና እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የቻሉ የትምህርት ኣተያዮችን የሚወክሉ ናቸው። በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱትም የኣኣራቱን የትምህርት ኣተያዮች ለመግለፅ ሳይሆን ምንነታቸው ቀላል በሆኑ ምሳሌዎች በምንባቦች ተክቶ ለማሳየት ነው። እንዲሁም ምንባቦቹ በየትኛው የትምህርት ኣምድ ሊመደቡ ችንደሚችሉና በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የትኞቹ ዓምዶች ቦታ እንዳገኙና እንዳላገኙ ለማሳየት ነው።

ከቀረበው አብነት፣ የትምህርት ባለሙያዎችና መምህራን ማስተማርን ሲያስቡ የሚመርጧቸው ግብአቶች የትኛውን የይዘት ዘውግ ሊያሳኩ እንደሚችሉ ጠንቅቀው ይገነዘባሉ፤ ለመሳካታቸውም አቅደው ሊሰሩ ይችላሉ። በሌላ አገላለፅ በአራቱ የትምህርት ዓምዶች አማካይነት በተመጣጠነ ሁኔታ የተማሪውን የተሟላ ስብእና መገንባት ይችላሉ ማለት ነው። ይህ ከአጠቃላይ ትምህርት ዓላማ አኳያ ሲታይ ነው።

በተጋሩ ዘንድም ሆነ በሌላ ማህበረሰብ የሚተላለፍ አበእ በአምድ ተለይቶና ይህንን ወይም ያንን ለማስተማር ተብሎ ተከፋፍሎና ተለይቶ የተቀመጠ አይደለም። በአብዛኛው ኢመደበኛና ሁሉም ሰው ሊቀስመው በሚችል መልክ የሚቀርብ ሆኖ ችሎታና እድሜ መሰረት ያደረገ ምጠናም የለውም (Hurreiz, 2006)። ህብረተሰቡ ከተገኘበት አውድ፣ ከተሰለፈበት የስራ መስክ፣ ካጋጠመው ችግር፣ ወዘተ. አኳያ ከነገሩ ወይም ከሁነቱ የሚስማማና የሚመጣጠን የሚያስጠነቅቅ፣ መፍትሄ የሚጠቁም፣ የሚመክር፣ ወይም የሚዘልፍ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ምሳሌያዊ አነጋገር ሲያቀርብ ይታያል። ወይም በእንዲህ ያለ አጋጣሚ እንዲህ ተብሎ ተዘፈነ፣ ተለቀሰ፣ ተገጠመ እያለ ማስተላለፍ የሚፈልገውን መልእክት ያቀርባል። ከዚህ ንግግር፣ ግጥም ወይም ሌላው የአቀራረብ ስልት በአካባቢው የተገኘው ሰው ሁሉ ላይማርበት ይችላል። በወቅቱና በእለቱ ተዋናይ የሆኑት ግን ከማስጠንቀቂያው፣ ከመፍትሄ ጥቆማው፣ ከምክሩም ሆነ ከዘለፋው በቂ ትምህርት ያገኛሉ። ካገኙት ትምህርት በመነሳትም እርምጃ ሊወስዱ ወይም እርምጃ ከመውሰድ ሊታቀቡ ይችላሉ።

በወቅቱ ወይም በእለቱ ተዋናይ ያልነበሩት ሰዎች ደግሞ እውቀቱን በልቡናቸው መዝግበው ሌላ ጊዜ ተመሳሳይ ሁኔታ ወይም ተግባር ሲያጋጥማቸው በመፍቻነት፤ ወይም ተመሳሳይ ድርጊት ላለመፈፀም በማስጠንቀቂያነት ይገለገሉበታል። ህፃናትም እውቀትን (ዖታ ተኮር የሆኑ ስራዎችም ጭምር) የሚሸምቱት ታላላቆቻቸው አባት እናቶቻቸውና መላ የህብረተሰቡ የእድሜ ባለፀጋዎች የሚያቀርቧቸውን ወጎች በማድመጥና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በመመልከት፣ በመቅዳትና አስመስሎ በመተወን ነው (Hurreiz, 2006)።

ህብረተሰቡ እውቀቱን በአምድ ከፋፍሎ ባያስቀምጠውም አስፈላጊ በሆነበት ሁሉ ይጠቀምበታል፤ የማህበረሰቡ ወይም የቤተሰቡ አባላት ያሉባቸውን ክፍተቶች ለመሙላት ይገለገልበታል። ህብረተሰቡ እውቀቱን የሚቀባበለው በአንድ አይነት መንገድ ብቻ አይደለም። አብዛኛው ህብረተሰብ የቃላዊ ተግባቦት ተጠቃሚ እንደመሆኑ በቃል መልእክት

ለማስተላለፍ የሚያገለግሉት የስነቃል ዘርፎች ሁሉ ይጠቀምባቸዋል። ለማስተማር ከሚገለገልባቸው ስልቶች ውስጥ ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን በየአምዱ ስር እንመልከት።

❖ *ለማወቅ መማር* (Learning to know)፡- ወላጆች፣ አያቶች ወይም የእድሜ ባለፀጎች ከቀደምቶቻቸውና ከኑሮ ልምድ ያገኙትንና በተደጋጋሚ ሙከራና እርማት ያዳበሩትን የነጠረ እውቀት ለተከታዩ ትውልድ ሲነግሩ አዲሱ ትውልድ አካባቢውንና በአካባቢው ያሉ ውስብስብ ዕውቀቶችን በተሻለ ሁኔታ እንዲገነዘብ በማሰብ ነው (Mawere, 2010)። እንዲሁም ስለዓለም እና በውስጧ ስለያዘቻቸው ግዙፍና ረቂቅ ዕውቀቶች ለማወቅ የሚያስችል መሰረት እንዲጥል ወይም የማወቂያ መሳሪያ እንዲታጠቅ ነው። እውቀቱ የሚገኘውም በቤተመዛግብት ወይም ቤተመዘክር ውስጥ ሳይሆን በህብረተሰቡ የእለት ተእለት እንቅስቃሴና በባህሉ ውስጥ ነው (Semali and Kincheloe, 1999)። ማስተላለፊያ መሳሪያዎቹም ተረቶች ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ እንቆቅልሾች፣ ወዘተ. ናቸው። ለዚህም ነው እነዚህን የስነቃል ሃብቶች በማስተማሪያ መሳሪያነት ከመገልገል መቆጠብ ወይም መታገድ ማለት አገር በቀሉን ሰው ከህልውናው ለመነጠል እንደመሞከር የሚቆጠረው (Mosha, 1999.; Semali and Kincheloe, 1999) ። በዚህ መልክ የቀረበ ትምህርት ህፃኑን እያዝናና እና እያጫወተ (LittleBear, 2009) ወደተፈለገው ግብ ያደርሰዋል።

በነዚህ ማስተማሪያ መሳሪያዎች አማካይነት ታላላቆች፤ ስለአዝርእት፣ ስለእንስሳት፣ እፀዋትና የሰው ልጅ ጤና ያስተምራሉ። ከእምነትና ስነምግባር የተያያዙ እውቀቶችን ለማስጨበጥ ይጥራሉ። በሰው፣ በተፈጥሮና በፈጣሪ መካከል ያለውን ትስስር ለማሳየት ጥረት ያደርጋሉ።ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት። **ከድርጊት መማር (ድንበርን ማስከበር)** በተጋሩ ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ በኣላት አንዱ ገና ነው። በእለቱም ሆነ በዋዜማው ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ተግባራት ይከናወናሉ። በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ዕለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ህዝብን ለማዳን ሲል የተወለደበት እለት እንደሆነ ስለሚታመን መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጣል። ከዚህ ጎን ለጎን አለማዊ እውቀትም በጨዋታ መልክ ይተላለፋል። መተላለፊያው በንግግር የታጀበ ተግባራዊ ክንውን ነው።

የአንድ ቀበሌ ወይም ጎጥ ወጣቶች "ሆያ ሆየ" እያሉ የጌታ መወለድን ለማብሰር በየቤቱ ይዞራሉ። የቤቱን ባለቤቶች ስም በመጥራት በዜማ ያሞግሳሉ። ባለቤቶቹም የተለያዩ ስጦታዎችን ያበረክቱላቸዋል። አምባሻ፣ ሁለት እንጀራና ድስት ወጥ፣ ገንቦ ጠላ፣ ፍየል

ወይም በግ፡ ሊሆን ይችላል። ወጣቶቹም በዜማ አመስግነው የመጪው አመት የስጦታ ስለት ተቀብለው ወደሌሎች ቤቶች ይሄዳሉ።

በጎጡ ከሚገኙ ቤቶች ሁሉ ልዩ ትኩረት የሚሻ ቤት አለ (ቤቶችም ሊሆኑ ይችላሉ)። ይህውም  በሁለት ጎጦች (ቀበሌዎች) መሃል የተሰራ በመሆኑ የሁለቱ ጎጦች ወጣቶች እኔ ልውሰድ እኔ ልውሰድ ይሽቀዳደሙበታል። ቤቱ እንደማንኛውም የገጠር ቤት በአጥር የተከበበ ሆኖ ዋናው ቤት (ሰቀላና እድሞ) በቀበሌ 'ሀ' መሬት ላይ ያረፈ፣ ሊሆን ይችላል። ማድቤቱና በረቱ ደግሞ በቀበሌ 'ለ' ያረፈ ነው። ስለዚህ የሁለቱ ቀበሌዎች ወጣቶች በየዓመቱ የኛ ነው፤ አይደለም የሚል የይገባኛል ጥያቄ  ስለሚያነሱ ቀድሞ ለመውሰድ ይሽቀዳደማሉ። እሽቅድምድሙ ጥበብ የተሞላበት ነው። አንድም ድምፅ ሳያሰሙና ሊላ አካባቢ "ሆ.ያ ሆየ" የሚል ድምፅ የሚያሰሙ ወጣቶችን በመመደብ እዚያ ቤት መድረስና ስጦታውን ይዞ ማምለጥ ነው። አለዚያም አንዱ ቡድን የሌላውን ቀበሌ ወጣቶች እንዳያልፉ መንገድ በመዝጋትና በሃይል በመከላከል ሌላው ቡድን ስጦታውን ይዞ እንዲያመልጥ ማድረግ ነው። ሶስተኛው ደግሞ የሁለቱ ቀበሌዎች ወጣቶች በተለያየ አቅጣጫ አድብተው በመምጣት እተባለው ቤት ሊደርሱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ከፍተኛ ግጭት ሊነሳ ይችላል። ቀድሞ የደረሰው ቀበሌ 'ለ' ከሆነ የተቀበለውን ስጦታ ተቀብለው ሊወጡ ሲሉ የሌላው ቀበሌ ቡድን የግቢውን በር በመዝጋት አላስወጣ ይሏቸዋል። የቀበሌ 'ለ' ወጣቶችም "ከመሬታችን ያገኘነው ስጦታ ነው፤ አይመለከታችሁም" ይሏቸዋል። ቀበሌ 'ሀ' ደግሞ " ንብረታችሁን ውሰዱ፤ እኛ ንብረት አንፈልግም። መሬታችንን ረግጣችሁና አርክሳችሁ ማለፍ ግን አትችሉም" በማለት ይሞግቷቸዋል።

ቀበሌ 'ሀ' ቀድሞ ከገባ ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀበሌ 'ለ' በሩን ይዞ አላስወጣ ይላቸዋል። ቀበሌ  'ሀ' እኛ ያለነው መሬታችን ላይ ነው፤ እናንተን እዚህ ውስጥ ምን አገባችሁ" ይሏቸዋል። "እኛ መሬታችሁን ፈልገን አልመጣንም፤ የያዛችሁት ንብረት ግን ከኛ ቦታ የተዘረፈ ነው። ስለዚህ ንብረታችንን አስቀምጣችሁ በሰላም መውጣት ትችላላችሁ" ስለሚሉ ተፋጠው ይቆማሉ። የሁለቱ ጎጦች ነዋሪዎች በየዓመቱ ጭቅጭቅና ጠብ እንደሚነሳ ያውቃሉ። ስለሆነም የየጎጡ ታዋቂ ሽማግሌዎች ይመጡና የያዙትን ንብረት እንዲያስቀምጡ፣ በእድሜ ትንንሽ የሆኑት ዳር ሆነው ንብረት እየጠበቁ እንዲመለከቱ ያዛሉ። ሌሎቹ ከቀበሌዎቹ መሃል በሚገኝ ሜዳማ ቦታ እንዲደባደቡ ያደርጋሉ።

ሽማግሌዎቹ ከባድ ጉዳት እንዳይደርስ እየተከታተሉ አንዱ ወገን ደክሞ ከድንበሩ ወደኋላ ማፈግፈግ እስኪጀምርና ሌላው ጥሶ እስኪያልፍ ድረስ ይጠብቃሉ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ ይነሱና ድብድቡ እንዲቆም ያደርጋሉ። በሁለቱ ቡድኖች መሃል ይቆሙና፣ *ግርማችሁ የአንበሳ፣ ጉልበታችሁ የብረት፣ አንድነታችሁ ጠንካራ መዝጊያ ይሁን፣ በህብረታችሁ ፅኑ፣ ለሃገራችሁ ኑሩላት* በማለት መርቀው ያስታርቋቸዋል።

ከዚያም ለአንዱ ወገን የተበረከተውን ያህል ስጦታ ለሌላውም ቡድን ይሰጡታል። ለምሳሌ ቡድን 'ሀ' ቀድሞ ገብቶ አምባሻ፣ ገምቦ ጠላ ወይም በግ ተሰጥቶት ከሆነ ቡድን 'ለ'ም ተመሳሰይ ስጦታ ይበረከትለታል። በመጨረሻም የሁለቱ ጎጥ/ቀበሌ ወጣቶች ተቃቅፈው ይሳሳሙና መጪው ዓመት በሰላም እንዲያገናኛቸው ተመኝተው ይለያያሉ። ይህ ተግባር አሁንም በጥቂት የትግራይ ቦታዎች እየተፈፀመ እንደሆነ ይነገራል።

ይህ ክንውን የሃገርና የድንበር ምንነት ማስተማሪያ ነው። አንድ ሰው ሃገርህ ተወረረች ቢሉት በቁጭት የሚነሳው ከዚህ ጨዋታ መሰል ተግባር ትምህርት ስለሚቀስም ነው። ድነበር ተደፈረ ማለት ከድንበር ወዲህ ያለው ሃብት፣ንብረት ተዘረፈ ማለት ነው። ሰውም የወራሪው ሃይል ተገዥ ይሆናል። አልገዛም ካለም ይሞታል ወይም ይሰደዳል። መፍትሄውም ገና ይህ ከመሆኑ በፊት መከላከል መሆኑ ያስተምራል። የዚህ አይነቱ ተግባራዊ እውቀት በማእከላዊና ምስራቃዊ ዞኖች የተለመደ ነው። በራያ አካባቢም ተመሳሳይ ድርጊት ይፈፀማል። ልዩ የሚሆነው፡-

- በጎራዴ፣ በጦር በጨቤና በተተኳሽ መሳሪያዎች የሚታገዝ መሆኑ፤
- እስከሞት የሚደርስ ቢሆንም በወንጀል እንደማያስጠይቅና በአካባቢ ሽማግሌዎች በእርቅ እንደሚያልቅ፤
- ከልምምዱ በኋላ ግን ወጣቶች በተለያዩ ዘመቻዎች የሚሳተፉ መሆናቸው ነው።

ትግራዋይ ህብረተሰብ ክፉን በክፉ መመለስ ክፋትን ደመኛነትን ይበልጥ ያስፋፋል። ክፉ የተባለውን ሰው ርህራሄ ካሳዩት ግን እሱም ተፀፅቶ ክፋቱን በደግነት ይቀይራል የሚል እምነት አለው። በአግባቡ የሚያስተምር ብቻ ነው የሚያስፈልገው በማለት የርህራሄን አስፈላጊነት ያስተምራል። (ማስተማሪያውን ተረት ከአባሪ ኘ ይመልከቱ)

በተረቱ ሊተላለፍ የተፈለገው እውቀትም ይቅር ባይነት ይበልጥ ፍቅርን፣ ሰላምንንና ደስታን የሚፈጥርና የሚያበዛ መሆኑ ነው። ስለዚህ የበደላችሁን ይቅር በሉት፤ የገደለን

መግደል ሚችን ኣያስነሳም፤ ቂመኝነትን የባብሳል እንጂ። ምህረት ቢሰጡት ግን (በይቅርታ ፍቅር መግዛት) ከጥፋቱ ተፀፅቶ ርህሩህና ጥሩ ወንድም ሊሆን ይችላል። በሌላ ኣባባል መገዳደል መቆም እንዳለበት ያስተምራል። ማስተማሪያ ዘዴው ግን ተረትና "ኣሉ" በሚል ኣዝናኝ ኣቀራረብ ነው።

በሌላ በኩል የህዝብ ኣንድነትና ደህንነት ተጠብቆ የሚኖረው በሽማግሌዎችና በሽምግልና ሃይል ነው ብሎ ያምናል። በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ስላላቸው ሊከበሩ ሊደመጡ ይገባል የሚል ኣቋም ኣለው። ኣፈንጋጮችንም ስልታዊ በሆነ መንገድ ይመልሳቸዋል። ይህንን እምነቱን በእውቀትነት ወደ ተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍም የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል። (ይህንን ለማስተማር የሚጠቀምበትን ተረት ከኣባሪ **አ** ስር ይመልከቱ፡፡)

ህብረተሰብ ማህበራዊነቱ እንዳይናጋና ተጠብቆ እንዲኖር ለማድረግ የተለያዩ ህጎችን ያወጣል። በጋራ ያወጣውን ህግ በጋራ ይጠብቀዋል። ህገመንግስት ሲጣስ የገንዘብ፣ የኣካል ቅጣቶችን በማስተላለፍ የማስከበር ስራ ይሰራል። ኣብዛኛው የትግራይ ቃላዊ ህብረተሰብ ግን ራሱ ያወጣውን ህግ የሞራል የማህበራዊ ቦታ፣ የግንኙነት ገደብ በማስቀመጥ ጥፋተኛውን ይመልሰዋል። ሌሎችም በጥፋተኛው ላይ ከተወሰደው እርምጃ ይማራሉ። ድርጊቱንና ቅጣቱን ሁሉም ሰው ማየት ኣይጠበቅበትም። "በኣንድ ኣገር ኣንድ/ዲት …" በሚል ተረታዊ ኣቀራረብ ምን ጥሰት እንደተፈፀመና ኣጥፊው ምን ቅጣት እንደተቀጣ ይተረታል፤ ሁሉም ይቀባበለዋል። በዚህ ኣገባብ ህግ እንዳይጣስ ጥበቃ ይደረግለታል። ኣፈንጋጭነት ይወገዛል። ህፃናትም በየደረጃው ያለውን ህግ በተረቱ ኣማካይነት ይተዋወቂታል። ለህግ ተገዢ ይሆናሉ። በዚሁ ተረት የሃገር ሽማግሌዎች ቦታ ይጎላል፣ ሰው ሲጨንቀው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ምን ያህል ኣስቸጋሪ ሊሆኑ እንደሚችሉም ከሴትዮዋ ተግባር መረዳት ይቻላል።

❖ **ለመቻል መማር** (Learn to do) ፡ ትምህርት ብቃትን ወይም ሙያን ወደ ተማሪው ማሸጋገር መቻል አለበት። ተማሪውም ከትምህርት እንደወጣ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ገብቶ የቻለውን ነገር በተግባር ሲፈፅም መታየት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ክህሎት ተማሪው ለመስራት ባለው ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ በችግር ፈቺነቱና በተግባቢነቱ ወይም ደግሞ በተሰማራበትና ህብረተሰቡን በሚያገለግልበት የሙያ ዘርፍና በሙያው በሚየሳየው ብቃት ሊገለፅ ይችላል። ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን የተጋሩ የኣፍ ታረክ እንመልከት።

*በአንድ አካባቢ አንድ በብልህነታቸው የሚታወቁ አዛውንት ነበሩ። የአካባቢው ነዋሪዎች የቸገራቸውን ነገር በማዋየት መፍትሄ ያገኛሉ። እንዲሁም ልዩ ልዩ ቁምነገሮችን ይሸምታሉ። ከእለታት በአንድ የበአል ቀን ገበሬዎች ተሰብስበው ከአዛውንቱ ጋር ይጨዋወታሉ። በዚህ መሃል አንዱ ወጣት ገበሬ እንዲህ ሲል አዛውንቱን ጠየቃቸው፣*

*"ድሮ፣ ድንጋይ ዳቦ በነበረበት ዘመን በረሃብ የሚሰቃዩ ሰዎች ነበሩ ይሆን አባቴ?"*

*"አዎን ነበሩ ። ደጃፋቸው የነበረን ድንጋይ ሳብ አርጎ ለመብላት ታክተው በረሃብ አለንጋ የሚገረፉ ሰዎች ነበሩ። አሁንም እኮ የልጅ ልጆቻቸው ከኛ ጋር አሉ ።"*

*"እንዴት ያሉ ናቸው?"*

*"መሬት አላቸው፣ በሬ ግን የላቸውም። ወሩ ሃምሌ ነው (ፅድያ)። ሃብታም ቤት ይሄዱና "በሬ ስጡን" ይላሉ። ባለቤት ያጉረመርማል፣ ምክንያቱም ያቺ ወቅት የመጪውን ዓመት ኑሮ የምትወስን ስለሆነች። ሚስት ደግሞ "መቼስ አማራጭ ቢያጣ ነውና የመጣው ይውሰድ እንጂ ትላለች። ባልም ይሁን ብሎ ይሰጣቸዋል። በሮቹን ይወስዱና በረት ውስጥ ዘግተው ሞፈር ካንዱ፣ ቤት ቀንበር ከሌላው፣ እርፍ ከዚያኛው፣ ቅትርት ከ... እያሉ ሲዞሩ ረፋድ ይሆናል። መሳሪያውን እስኪያዋድዱና እርሻ ቦታ ደርሰው ማረስ እስኪጀምሩ ድረስ እኩለቀን ይሆናል። አንድ ሰዓት ሳያርሱ ዝናብ ይመጣና በሮች ተፈትተው ወደቤታቸው ይሄዳሉ። በዚህ ምክንያት የፅድያ ዘር ሳይዘሩ ጊዜ ያመልጣቸውና ዓመቱን በረሃብ፣ በስደትና በልመና ያሳልፉታል። (**በፅድያ፡** አንዷት ሰዓት የአንድ አመት ያህል የምታንገበት ወቅት ስለሆነ ደቂቃም እንድትባክን አይፈለግም)*

*ከደጃፋቸውና ከጓሮአቸው ግን ወይራው፣ እምብሱ፣ ክትክታው አፀድ ሰርቷል። በጋውን ቁጭ ብሎ ከማሳለፍ ዛፉን ቆርጠው ድግር፣ ቅትርት፣ ሞፈር ቀንበሩን ማዘጋጀት ይችላሉ ። ግና የነዚያ ሃካዮች የልጅ ልጅ ስለሆኑ ከአመት አመት ተርበው 'ድሃ' እየተባሉ ይኖራሉ።*

በዚህ ተረት ሊተላለፍ የተፈለገው እውቀት፡-

- የጊዜ ክቡርነት፣ የስራ ጊዜ ለስራ መዋል አለበት፣
- ሃካይ ምንጊዜም ቢሆን አያልፍለትም፣ ድህነት ቤት የሚሰራው እሰነፍና ሃካይ ሰው ውስጥ ነው፣
- ድህነትን ማባረር የሚቻለው ጠንክሮ በመስራት ነው፣ ሰራተኛ ሰው ደግሞ ሊበረታታ ይገባል የሚል ነው።

❖ **ስብእናን ለመገንባት መማር** (Learning to be)፡- ትምህርት አንድን የተወሰነ አካል ብቻ አይለውጥም ህፃኑ ፊደልን ሲማር የፊደሉን ቅርፅ ከተለያዩ ቁሶች ጋር እያመሳሰለ ለመጨበጥ ይጥራል። ቃል ይመሰርታል በቃሉ የሚወክሉ እንስሳትን፣ ሃውልትን፣ ስእሎችን፣ ደኖችን፣ ጌጦችን፣ ወዘተ. በአእምሮው ይስላል። ያያቸውንና የታዘባቸውን ነገሮችና ሁኔታዎች ማድነቅ፣ መውደድ፣ መጥላት ይጀምራል። የስብእና ግንባታ፣ ህዝባዊ ሃላፊነትን፣ በጎ ስራን፣ ትህትናን፣ ቅንነትን፣ ውበት አድናቂነትን፣ መንፈሳዊነትንና ህዝባዊ ተቀባይነትን ሁሉ ያጠቃልላል (Elleni, 1996)። ተጋሩ በጋራ ጥሩ ወይም መጥፎ የሚሏቸው ተግባራትና አስተሳሰቦች አሉ። ህፃኑ ወይም ተተኪው ትውልድም መጥፎዎቹን እንዲጠየፍና ከመተግበር እንዲወገድ፣ ጥሩዎቹን ደግሞ እንዲያደንቅና በተግባር እንዲያሳይ በተለያዩ መንገዶች ትምህርት ይሰጠዋል። ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ሰናይና እኩይ ምግባራትን ለማስተማር ከሚያገለግሉ መሳሪያዎች አንዱና ዋነኛው ደግሞ ስነቃል ነው (Pai, 1990; Mosha, 1999.; Semali and Kincheloe, 1999)።

ትምህርቱም ኣድርግ ኣታድርግ የሚል ትእዛዛዊ ኣቀራረብ የለውም። እየተማርኩ ነው ብሎ እንዲያስብና እንዲጨነቅም ኣያደርግም። ህፃኑ ተረቱን እያደመጠ ይስቃል፣ ይዝናናል፣ ገፀባህርዩን ያደንቃል። ወይም በገፀባህርዩ ድርጊት ያዝናል ወይም ይናደዳል። በታሪኩ ውስጥ የነበረውን ገፀባህሪ እንዲደነቅ እንዲሸለም ያደረጉትን እውቀቶች ወይም ባህርያት እውቀቱና ባህሪው ለማድረግና በተግባር ለማሳየትም ጥረት ያደርጋል። በኣንፃሩ ሰውን የሚያሳዝኑና የሚያናድዱ ተግባራትን ላለመፈፀምና ላለመነቀፍ ጥረት ያደርጋል። ቀስ በቀስ ባህሪው ይሆናል። ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን የተጋሩ ተረት እንመልከት፣

*ተረት ተረት የላም በረት (የመሰረት)*

*ድኩላና ነብር በኣንድ ጫካ ውስጥ ይኖሩ ነበር። ነገር ግን ሁሌም ተስማምተው ኣያውቁም። ኣጥፊና ጠፊ ናቸው። ድኩላ ነብርን እያሰበ ሁሌም እንደበረገገ፣ ነብር ደግሞ ድኩላን ባየ ቁጥር ለመብላት እንደቋመጠ ነው። ሁሌም ነብር እንዳባረረ፣ ድኩላ ነፍሱን ለማዳን እንደበረረ ይኖሩ ነበር።*

*ሁለቱም በዚህ መልክ ሲኖሩ ኣንድ ጊዜ ኣያ ነብሮ ድኩላን ለጓደኝነት ጠየቀው። "ሁሌም በጠላትነት ከምንተያይ ለምን ጓደኝነት ኣንመሰርትም?" ኣለው። ድኩላም ጓደኝነቱን*

*ቢፈልገውም ፈራ። "እንዴት እኔና አንተ ጋደኞች ልንሆን እንችላለን? ያንተ ቀለብ ስጋ፣ የኔ ደግሞ ሳር፤ እንዴት ይሆናል?"*

*ነብርም በተራው ፍቅርና ቃልኪዳን ካለ ምንም ችግር እንደማይኖርና የምግብ መለያየት ሊለያይ እንደማይችል አስረዳው። ድኩላም "እሺ" አለው። በመቀጠል ቃል ኪዳን ተገባቡ። ድኩላ ነብርን ባየ ጊዜ ላይሸሽ፣ ነብርም ድኩላን ባየ ጊዜ ለመብላት ላይጓጓ ተማማሉ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በጠላትነት መተያየት ቀረ። ድኩላ ያለሃሳብና ያለስጋት ያገኘውን ቅጠል እየቀረጣጠፈ እየበላ በጣም ተመቸው። ነብር ደግሞ የድኩላን ዘር ላለመብላት ስለማለ ከቀን ወደቀን እየከሳ ሄደ። ረሃቡ የጠናበት ነብር መሃላውን ለማፍረስ ፈለገ።*

*አንድ ቀን ማለዳ ድኩላ ሃረግ ላይ ተንጠላጥሎ ለምለም ቅጠል እየቀጠፈ ሲበላ ነብር ደግሞ አጠገቡ ካለ ድንጋይ ላይ ተኝቶ ፀሓይ እየሞቀ ነው። ነብር ድኩላን ከኋላው ሆኖ ሲያየው ሽንጡ የመደብ ያይል ሰፍቶ ታየው። ታፋዎቹም አሞንድለዋል። ሆዱ መሬጦህ፣ ምራቁ ቶሎ ቶሎ መምጣት ጀመረ።   እናም ድኩላን ጠራው። ድኩላም ቁርሱን እየበላ ዞር እንኳ ሳይል "አቤት" አለው።*
*ነብርም "መሃላ ያፈረሰ ምን ይሆናል?" ሲል ጠየቀው።*
*"መሃላ ያፈረሰው ራሱ ምንም ላይሆን ይችላል። ልጆቹ ግን ትልቅ መቅሰፍት ይወርድባቸዋል።"*
*"በቃ ይኸው ነው?"*
*"አዎ ይኸው ነው።" አለው። ነብርም "ልጆቼስ እንደፍጥርጥራቸው ይሁኑ፣ እነሱ እንዳይጎዱ ብየ እኔ በረሃብ መሞት የለብኝም" ብሎ እላዩ ላይ ሊከመርበት ሲዘል፣ ነብር ደግሞ ኮሽታ የሰማ መስሎት ለማረጋገጥ ዞር ሲል ድንገት የድኩላ ቀንዶች እነብር ሆድ ተሰኩ። ቀንዶቹ ሙሉ ለሙሉ ሰምጠው ስለነበረ ነብር ማጣጣር ጀመረ። ድኩላም ቀንዶቹን አወጣና በድንጋጤና በግርምት ያየው ጀመር። ነብርም የሞት ሞቱን "ድኩላ የአባት ሃጢአት ልጆችን ነው የሚቀጥፈው አላልከኝም እንዴ?" አለው። አዎን እነደዛ ብየሃለሁ። ግን ኢየ ነብሮ አንተምኮ ካባትህ የወረስከው ሃጢአት ኖርብህ ይሆናል" ብሎ ጥሎት ሄደ ይባላል (እያሱ፤ 2004 ዓ.ም. ገፅ 62-3)።* ትርጉም የራስ

ከሃይማኖት አኳያ ከአሰርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ሁለቱ እዚህ ተጠቅሰዋል (ኣትማል እና ጓደኛህን እንደራስህ ውደድ) የሚሉት ናቸው። እነዚህን ትእዛዛት መጣስ በፈጣሪ ዘንድ ያስኮንናሉ። ይህ አንዱ የህፃኑ መንፈሳዊ ህይወት መገንቢያ መንገድ ነው። ቃል አለማፍረስ (አለመካድ፣

ኣለመዋሸት፣ ኣለመማል፣) ቃል ኪዳንን ማፍረስ ትልቅ ክህደት መሆኑ ለማሳየትም ተጋሩ፣ **ካብያ ዝበልካዮ ዝጥለምስ ዝወለድካዮ ይጠለም** (የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ) በማለት የክህደትን ፀያፍነት ያስተምራሉ። ክህደት የነፍስ መኮነንን ያስከትላል። ነፍስ ከምትኮነን ግን ማንኛውም ነገር ቢቀር እንደሚመረጥ ያሳስባሉ።

ከዓለማዊው ህይወት ኣኳያ ደግሞ ጓደኝነት የሚመሰረተው ስለተፈለገ ብቻ ሳይሆን የእድሜ፣ የስሜት፣ የደረጃ፣ የሃይል ወዘተ. ተመጣጣኝነትም ሲኖር ነው። ድኩላና ነብር ግን የኣጥፊና ጠፊ ተምሳሌቶች ናቸውና መጀመሪያውኑ የማይሰምር ጓደኝነት ነበር የመሰረቱት። በዚህ ተረት ኣማካይነትም ልጆች ጓደኞቻቸውን ሲመርጡ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያሳስባል። ተጋሩ ይህንን ተረት በምሳሌ ሲያስደግፉት

| | |
|---|---|
| ***ሳእንኻ ማዕረ እግርኻ*** | *(ጫማህ በእግርህ ልክ ይሁን)* |
| ***እንተፀበበ ይመልጠካ*** | *(ከጠበበ ያቆስልሃል)* |
| ***እንተገፍሐ ይመልቄካ*** | *(ቢሰፋ ይወልቅብሃል)* |

ጫማ፤ የተጓዥ ኣጋር ሆኖ እፈለገበት ቦታ ሊያደርስ የሚችል ታማኝ ኣገልጋይ ነው። ይህ ግልጋሎት የሚወሰነው ግን እግር ጋር ባለው ግንኙነት ወይም መመጣጠን ነው። መመጣጠን ከሌለ ኣብሮነታቸው ይቋረጣል። የኣንዳቸው ደህንነት ኣደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። በሰዎች መካከል ሚፈጠር ጓደኝነትም በኣቅምም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ እርከኖች መመጣጠንን ይፈልጋል።

- ***ማሕበራዊነትን ለመልመድ መማር***

ትምህርት ከግለሰብ ከቡድንና ከማህበረሰብ ጋር አብሮ መኖርንና የሰዎችን ስሜት መገንዘብ ማስተማር አለበት (Amare, 2008; UNESCO-Online)። ህፃኑ በቤተሰቡ ውስጥ የሚያስተውላቸው የመወያየት የመከባበር የመተጋገዝ ባህሎች አሉ። በመነጋገርና በመግባባት ችግር መፍታት አንደሚቻል በመጠኑም ቢሆን ያውቃል። ይህ ከቤት የመጣ እውቀት በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሊንፀባረቅና ሊጠናከር ይገባል። ከክፍል ጓደኞች፣ ከቡድን ከትምህርት ቤት ማህበረሰብና ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ጋር መኖር ወደሚያስችለው ደረጃ ማደግ አለበት። ብዙዎቹ የኣገር በቀል እውቀት ማስተላለፊያ ወጎችና ተረቶች ከስነምግባርና ከእምነት ትምህርት ጋር ተያይዘው ይቀርባሉ። የዚህ ኣይነቱ ኣቀራረብ የማህበራዊና ስነምግባራዊ (Hurreiz, 2006) ትምህርት ይባላል። ኣንዳንዱ በህግና ስርዓት የተሞላ ሆኖ ይገኛል። ህግና ስርኣት ኣንዱ የማህበራዊነት

ማጠናከሪያ መንገድ ነው። ግለሰቡ ቢፈልግም ባይፈልግም ብዙዎች የተቀበሉትን አሰራር፣ አነጋገር፣ አለባበስ እንዲከተል ያደርጋል። ጥቂቶች የብዙሃኑን ፍላጎት አክብረውና ተባብረው እንዲኖሩ ያደርጋል። ከማህበረሰቡ ፍላጎት ማፈንገጥ ደግሞ የመገለልን ቅጣት የሚያስከትል ሊሆን ይችላል።

ህብረተሰቡ፣ በህግና በስርዓት የሚያምን፣ አፈንጋጭነትን፣ ጥቃትንና አመፅን የማይቀበል መሆኑ ለማሳየትና እምነቱን ለማጠናከርም የሚከተለው ምሳሌያዊ አነጋገር ያቀርባል፣

*ካብታ ብፍርዲ ዝተወሰደት መሬተይ፣* *(በፍርድ ካጣኋት መሬቴ)*

*ብሓይለመልጢ ዝኸደት ቆርበተይ።* *(በሃይል የተወሰደች ቆርበቴ)*

ምሳሌአዊ ንግግሩ፣ ትግራዋይ ከህግ ውጪ የሆነ ተግባርን ወይም ጥቃትን የማይቀበል መሆኑ፣ ጥቃት ከተፈፀመበት ሁሌም ሲቆጠቁጠውና ሲያንገበግበው እንደሚኖር ያሳያል። ከጠቀሜታ አኳያ ቁርበትና መሬት አይመጣጠኑም፣ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሬቱ ነው። ነገር ግን መሬት የተወሰደው ህጋዊ በሆነ መንገድ ነው። ቁርበት አይጠቅምም ባይባልም የመሬትን ያህል አይሆንም። እንደሚያንገበግብ የተገለፀው ግን የቁርበት መወሰድ ነው። አሳዛኙም መወሰዱ ሳይሆን አወሳሰዱ በሃይል ወይም በማን አለብኝነት መሆኑ ነው። ይህም ህብረተሰቡ ለተተኪው ትውልድ ጥቃትንና ተፅእኖን ህጋዊነትንና ፍትሃዊነትን ለይቶ እንዲያውቅ የሚያስተምር ነው። በአጠቃላይ ለህግና ስርዓት መገዛትን፣ አመፅንና ማንአለብኝነትን አለመቀበልን ይብዛም ይነስ፣ በሃይል የተወሰደ ነገር ካለ እስኪመለስ ድረስ የሚያንገበግብ፣ እንቅልፍ የሚነሳ መሆኑን የሚያስተምር ነው።

ህፃናት፣ ለብዙሃን ፍላጎት መገዛትን ማህበራዊ ደንብን አክብሮ በህብረት መኖርን የሚማሩትና የሚለማመዱት ከህፃናት ጨዋታ ነው። ህፃናት በህብረት ለመጫወት የጨዋታውን ህግና ደንብ ማወቅና ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ "የብሪሞ" (ሰኞ-ማክሰኞ) የሚባለው ጨዋታ ውስጥ መከበር ያለባቸው ህጎች አሉ። እያንዳንዱ ልጅ ህጎቹን አክብሮ መጫወት ይጠበቅበታል (Hurreiz, 2006; Tesfaye, 2010)። መስመር ጠብቆ መርገጥ፣ ሚዛን ጠብቆ በአንድ እግር እየነጠሩ መጫወቻውን ገል ወይም ድንጋይ ወደተፈለገው አቅጣጫ መግፋት፣ ጨዋታውን ባሸነፈች ልጅ የተሰራን ቤት አለመርገጥ፣ መጫወቻውን ገል መስመሮችን አለማስነካትና የመሳሰሉ ደንቦችን ማክበር የግድ ነው ።

ኣንድ ሴትም ሆነች ወንድ ልጅ ይህንን ደንብ ሲጥሱ ከጨዋታ ውጪ (ፋርሽ) ይባላሉ (Tesfaye, 2010)። በፈፀሙት ጥፋት የተቀጡ ልጆች ኣላጠፋሁም ብለው የሚክዱ፣ የሚጨቃጨቁ፣ ለጠብ የሚጋበዙ ከሆነ የመገለል ቅጣት ሊወሰንባቸው ይችላል። ጓደኞቻቸው 'ህግ ስለማታከብር/ሪ ካንተ/ቺ ጋር ኣንጫወትም' ሊሏቸው ይችላሉ። ጥፋት መፈፀማቸውንን ካመኑና ባህሪያቸውን ካሻሻሉ ደግሞ የመልሶ ቅበላ እድል ይሰጣቸዋል። ሌሎቹ ኣባላትም ላለመገለል ሲሉ ተገቢ የተባሉትን ስርኣቶች ያከብራሉ። በዚህ ቀላልና ቀልድ በሚመስል ጨዋታና ኣፈፃፀም ሂደት ውስጥ ህፃናቱ ለስርኣት መገዛትን፣ እውነተኝነትን ይማራሉ። እራሳቸውን ለስርኣቱ በማስገዛት ከራሳቸው ይማራሉ። ከማህበር መገለል ትልቅ ቅጣት መሆኑ ይገነዘባሉ። ስለሆነም በቀጣዮቹ ተግባሮቻቸው ከጨዋታ መገለልንና ከማህበር መውጣትን የሚያስከትሉ ተግባራትን ላለመፈፀምና ህግን ላለመጣስ ጥንቃቄ ያደርጋሉ።

በኣራቱም ኣምዶች ስር ተጋሩ ኣገር በቀል እውቀትን ለማስተማር የሚገለገሉባቸው ተረቶችና ምሳሌኣዊ ኣነጋገሮች በኣብነት ቀርበዋል። እነዚህ ወነች እውቀትን ብቻ ሳይሆን ትህትናን፣ እውነተኛነትን፣ እምነትን ሁሉ ያስተምራሉ። በኣጠቃላይ ኣንድ የማህበረሰቡ ኣባል በማህበረሰቡ መሃል ገብቶ ለመኖር የሚያስችል ስብእና የሚገነቡ ናቸው። የህፃናቱንም ሆነ የወጣቱን ስብእና በመገንባቱ ሂደት ቤተሰብም አካባቢም ህብረተሰብም የየራሳቸው አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ህፃኑ እራሱን ችሎ መቆም የሚችልና የራሱ መለያ ያለው ግለሰብ እንዲሆን፣ በቤተሰብ ወይም በማህበረሰብ መሃል ገብቶ ለመኖር የሚያስችል ባህሪ ያለው፣ ሃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ኣድረገው ይቀርፁታል።

## 2.2.9. ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ

የዚህ ጥናት ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ የሚመነጨው ኣዲስ እውቀት መገብየት የሚቻለው ተቀባዩ ወይም ተማሪው ቀድሞ ከሚያውቀው ጋር የሚገናኝ ይዘት ሲቀርብለት ነው ከሚል ግንባታዊ ኣተያይ (constructivism) ነው። ኣንድ ተማሪ በመምህሩ የቀረበለትን ይዘት ተገንዝቦ ሊጨብጠው ወይም ወደተግባር ሊለውጠው የሚችለው፤ ይዘቱ የተማሪውን ቀዳሚ ልምድ መነሻው ያደረገ እንደሆነ ነው (Hein, 1991; Holzer, 1994)።

### 2.2.9.1. የግንባታዊ ኣተያይ ምንነት

ግንባታዊ ኣተያይ እውቀት በሰው ልጅ ኣእምሮ ውስጥ እንዴት እንደሚገነባና እውቀትን መሸመት/መማር የሚቻለው እንዴት እንደሆነ (Epistemology and Learning theory) የሚያይ ንድፈ ሓሳብ ነው (Hein, 1991)፡፡ ይህ ኣተያይ፣ በምልከታና በሳይንሳዊ ምርምር ላይ ተመስርቶ ሰዎች እውቀትን እንዴት እንደሚያከማቹ በማጥናት ምላሽ ይሰጣል፡፡ ስለሆነም በግንባታውያን ኣተያይ መሰረት፣ ሰዎች በራሳቸው ልምድና ግንዛቤ ኣካባቢያዊና ዓለምአቀፋዊ እውቀት ይሰበስባሉ፡፡ በሂደት ኣዲስ ነገር፣ ኣዲስ ሃሳብ፣ ኣዲስ እውቀት ሲያጋጥምም ከቀዳሚውና ከሚስማማው ይዘት ጋር ያዋህዱታል እንጂ ዝም ብለው ኣይመዘግቡትም። ቀዳሚውን እውቀታቸውን የሚያስለውጥ ከሆነም ኣምነው ይቀበላሉ፡፡ (Perkins, 1992; EBC, 2004; Petty, 2004)።

መማር ልምዶችን በኣይነት የመለየትና በየራሳቸው መዋቅር የማደራጀት ስራ ነው (Perkins, 1992)። ለምሳሌ ኣንድ ተማሪ እሳትን በማብሰያነቱ ያውቀዋል። ቃሉ ሲጠራ የሚፈጥረው ኣእምሮኣዊ ምስልም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። ከገበያ ውድነት፣ ከነገረኛነት፣ ከቃሪያ መፋጀት፣ ከቀልጣፋነት ጋር ያለውን ግንኙት ቢነገረው እንኳዋን፤ እራሱ ፍቺውን እስካልተገነዘበው ድረስ በእውቀትነት ኣይቀበለውም። ከጊዜ በኋላ ግን ውክልናውን ይገነዘባል። ፍቺውንም ከኣእምሮ ምስል ጋር ያያይዘዋል። ቀጥሎም እውቀት ይሆናል። የግንባታዊያን ኣተያይ ከእውናዊነት(objectivism) የሚለየውም መምህር፤ ተማሪው ሊማረው ይገባል ብሎ ያመነበትን ብቻ ሊማር እንደማይገባው ማመኑ ነው (Duffy, and Jonassen 1992)። የእውናውያን ኣተያይ:- ተማሪው የሚማረው ይዘት በውጪ ሃይል ሊወሰን ይችላል የሚለውን ሃሳብ ኣይቀበልም።

እውቀት (ግንዛቤ)፤ የማያቋርጥ ለውጥ የሚያሳይ ሂደት ነው። ህፃናት ከተወለዱበት እለት ጀምሮ በየጊዜው የግንዛቤ ለውጥ ያሳያሉ። የሚያሳዩት ለውጥም የተለየ ምክንያት ካልኖረ በቀር ተመሳሳይ(ተመጣጣኝ) ነው (Kim, 2006)። ለምሳሌ:- በዝቅተኛ የግንዛቤ ደረጃ የሚገኙ ህፃናት መስታወት እንዲያዩ ቢደረግ ሁሉም በመስታወቱ ውስጥ ያለውን ልጅ ለመያዝ፣ እሱን ለማጫወት፣ ለመገፍተር ሊሞክሩ ይችላሉ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ህፃናቱ ሳያውቁ ፊታቸው (ግንባራቸው) ላይ በደማቅ ቀለም ምልክት ቢደረግባቸውና መስታወቱን እንደገና እንዲያዩ ቢደረግ ሁሉም ተመሳሳይ እርምጃ ይወስዳሉ፤ እጃቸውን ወደፊታቸው ኣቅጣጫ በመዘርጋት ቀለሙን ለመያዝ ይሞክራሉ። እነዚህ ህፃናት፣ ራሳቸውን (Self)

ማወቅ ጀምረዋል ማለት ነው፡፡ በአንፃሩ እራስን የመለየት ደረጃ ያልደረሱት ምልክቱን ለመያዝ እጃቸውን ወደመስታዎቱ ይዘረጋሉ። ይህ ሁኔታ፣ እውቀት ባለፈ ልምድ ወይም ግንዛቤ ላይ የሚገነባ እና ቀስ በቀስ የሚያድግ ነው ለሚለው የግንባታውያን አተያይ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

ህፃናት ከሚያውቁት አለም (ቤት) ወደአዲሱ አለም (ትምህርት ቤት) የሚመጡት ባዶአቸውን ሳይሆን ከላይ እንደተጠቀመው በአግባቡ የተደራጀ እውቀት (Knowladge)፣ ሃሳብ (Idea) እና ግንዛቤ (Understanding) ይዘው ነው (Cunningham, 1992; EBC, 2004)። በተለያዩ ጊዜያት ከታላላቆቻቸው የሰሟቸውን ተረቶች ያውቃሉ፡፡ መምህር የተረትን ጠቀሜታ ማስተማር ቢፈልጉ ጠቀሜታዎቹን አስቀድሞ ከመዘርዘር ህፃናቱ የሚያውቁትን ተረትና ጠቀሜታው እንዲናገሩ ለውይይት ማዘጋጀት። ህፃናቱ እስካሁን የገነቡትን በመነሻነት ከተጠቀሙ በኋላ መምህሩ መጨመር አለበት ብለው ያሰቡትንና የተዘጋጁበትን ይዘት ሊያክሉ ወይም በማጠቃለያ መልክ ሊያርቡ ይቻላሉ። ቀዳሚው እውቀት ለተከታዩ መነሻ የመሆን ሰንሰለታዊ ኡደቱ ከፍ ሲል ህፃናቱ ራሳቸውን የተሻለ ጥልቀት፣ ርቀትና ስፋት ባለው እውቀት ውስጥ ያገኙታል። ግንባታው እንዴት እንደሚካሄድ ለማሳየት የቀረበውን ኣፄር መግለጫና ምስል እንመልከት፤

- **ያለፈ እውቀት፡-** ከተረት ነጋሪው አተራረክ የተነሳ በህፃንነት ጊዜ ይሰሙት የነበረው ተረት በጣም ያስቃቸው ነበር፡፡
- **አሁን የተደረሰበት እውቀት፡-** የሚያስተላልፈውን መልእክት መገንዘብ ይጀምራሉ፡፡ ተረቱ ከማሳቅ በላይ ላቅ ያለ አላማ እንዳለው መገንዘብ ችለዋል፡፡
- **ወደፊት የሚደረስበት እውቀት፡-** የተረቱ ስነፅሁፋዊ ዋጋ፣ አሁን ላለው ስነፅሁፍ የሚኖረው ፋይዳና የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ያለውን ጠቀሜታ ሊገነዘብ ይችላል።

ምስል 1፡- የአሁንም ሆነ መጪ እውቀት የሚመሰረተው ባለፈ ልምድ ላይ መሆኑ አመልካች




(EBC, 2004)

ከሶስተኛው የብስለት ደረጃ ሲደርሱ "ለካ ተረቶች በልጅነቴ አስበው እነደነበረው ዓላማቸው ማሳቅ ብቻ አልነበረም " የሚል አስተሳሰብ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ ሌላው የእውቀት ዘርፍም ተመሳሳይ ግንዛቤአዊ እድገትን ጠብቆ ይሄዳል፡፡

የስነልቡና ልሂቃንም የግንባታውያንን የመማር ንድፈ ሃሳብ የሚያጠናክር አተያይ አላቸው። አንድ ህፃን እውቀቱን የሚቀስመው በሁለት ቁልፍ ሂደቶች ውስጥ በማለፍ ነው። ይኸውም በማዋሃድ (Assimilation) እና ለውጥን በመቀበል (Accommodation) ነው። የእውቀት ግንባታ የሚለው ፅንሰሃሳብ መሰብሰብን፣ ማከማቸትን ብቻ የሚያመላክት ተደርጎ መወሰድ የለበትም። በመቀበል መሞላት አይደለም። በውስጡ መገንዘብን፣ መምረጥን፣ ካለፈ ልምድ ጋር ማጣጣምን ሁሉ ያካትታል። ሂደቱ ምን እነደሚመስል ከሚከተለው አብነት መገንዘብ ይቻላል፤

- ምስለት (Assimilation)፣ አዲሱ መረጃ ከነባሩ እውቀት ጋር ተመሳሳይ ይሆንና ህፃኑ የማዋሃድ ስራ ይሰራል፡፡ አዲሱ ዕውቀት ከየትኛው ቀዳሚ እውቀት ጋር እንደሚመሳሰል የመለየትና ተገቢ በሆነ መልኩ የማያያዝ ስራ ነው።

- ለውጥን መቀበል (Accommodation) የተገኘው መረጃ ከህፃኑ ነባር እውቀት የማይጣጣም፣ ግን አሳማኝ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ ህፃኑ በመነሻነት የያዘውን እውቀት እንዲያሻሽል ወይም እንዲለውጥና ሌላ መነሻ እንዲኖረው የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል። ይህ ህፃኑን በእጅጉ የሚፈትን፣ ከማመሳሰል ከፍ ያለ ከባድ ሂደት ነው (Bigge and Shermis; 2004; EBC, 2004)።

- አለመቀበል፡- የተገኘው መረጃ ከነባሩ እውቀት ጋር ፈፅሞ አይጣጣምም፡፡ ህፃኑም ሊገባው ስላልቻለ አልተቀበለውም፡፡ የዚህ አይነቱ መረጃ ሙሉ በሙሉ ከህፃኑ አእምሮ ሊጠፉ ይችላል፡፡አለዚያም የህፃኑ ግንዛቤ እስኪፈቅድ ወይም ከምን ጋር እንደሚጣጣም እስኪያውቅ ድረስ ተንሳፎ ሊቆይ ይችላል፡፡ /EBC, 2004/።

## 2.2.9.2. በግንባታዊ አተያይ የመማር- ማስተማር መርሆዎች

የግንባታዊ ንድፈ ሐሳብ መሰረተሃሳብ፤ እውቀት መቃኘትና መገንባት ያለበት በተማሪው ጥረት እንጂ በመምህር በሚቀርብ ስጦታ አይደለም፡፡ ሁሉም ተማሪ በውሃ ምንጭ ይመሰላል፡፡ ሁሉም የአቅሙን ያህል ውሃ ማመንጨት አለበት (Holzer, 1994 Hain, 1991)። እያንዳንዱ ተማሪ የሚያመነጨው እውቀት ከመጣበት ማህበረሰብ ወይም ካደገበት አውድ የተቀዳ ነው፡፡ የተማሪው የመጀመሪያ ግንዛቤ ከባቢያዊ እንጂ አለምአቀፋዊ (Global) አይደለምና። የምንጮቹ ድምር ውጤት ደግሞ ጅረት /አንድ የተሟላ እውቀት ይሆናል። በዚህ ሂደት ውስጥ የመምህር ሚና ተማሪው ፍቹ ለማግኘት በሚያሳየው ጥረት የአገነባብ ስልቱን ማሳየት ይሆናል (Hain, 1991)። ፍቹ ፍሊጋ የአእምሮ ስራ ቢሆንም ስርፀት የሚያገኘውና የሚዳብረው በተግባራዊ እንቅስቃሴ (በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በመፃፍ) ሲታገዝ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ለዚህ ግልጋሎት የሚውሉ መለማመጃዎች ሊኖሩ ይገባል።

መማርን ከአውድ ነጥሎ ማቅረብ ያስቸግራል። ትምህርትን ከማህበረሰቡ ኑሮና የአኗኗር ስርአት ነጥሎ ማቅረብ፣ ተማሪዎች ፍፁም ረቂቅ የሆነን ነገር እንዲጨብጡ ማስገደድ ይሆናል (Hein, 1991)። የህብረተሰብ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ በህፃናቱ ውስጥ ያልፋል። አስተላለፉ ግን የውሃ እና የቧንቧ አይነት ስላልሆነ ልምድ እውቀት ያስቀሩበታል። ከህብረተሰቡ የቀሰሙትን ልምድ በጨዋታ መልክ ይተውኑታል። ስለሆም

በጨዋታ የሰላው አካልና አእምሮ አውዱን መሰረት አድርጎ በትምህርት መልክ የቀረበውን ይዘት ለመገንዘብ አይቸገርም (Hein, 1991; Holzer, 1994; Wikipedia)።

ማህበራዊ ግንባታም (Social Constructivism) ተማሪው እውቀት የሚፈጥርበትንና የሚቀስምበትን ሁኔታ የሚገልፅ ትወራ ነው (Kim, 2006)። እውነታ (Reality) ቀድሞ የተፈጠረና ሰዎች በአሰሳ የሚያገኙት ሳይሆን በሰዎች የእለት ተእለት ተግባራት ውስጥ የሚገነባ ነው። ባጭሩ፣ እውነታውን የሚፈጥሩት ሰዎች ናቸው፤ እውቀትም በሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚፈጠር ምርት ነው። የአንድ ማህበረሰብ አባላት እርስበርስና ከአካባቢ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት መልክአምድርን፣ የአየር ሁኔታን፣ አዝመራን፣ ቤተሰብን፣...የሚገልፅ ፍቺን ይፈጥራሉ። ፍቺዎች ተቀናብረው የህብረተሰቡ እውቀት ይሆናሉ። ከዚህ ውጪ በሆነና በግል የተፈጠረ ወይም ከማህበረሰቡ ህይወት ውጪ ሆኖ የተደራጀ እውቀት በማህበረሰቡ ላይ እሚያመጣው የአሰራርም ሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ አይኖርም።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ እውቀት የሚዳብረው በማህበረሰቡ ወይም በጎሳው ውስጥ እንደመሆኑ፤ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያድገው ህፃንም በምልከታም፣ በተሳትፎም የራሱ ያደርገዋል። ለመደበኛው ትምህርት መነሻ ሆኖ የሚያገለግለውም ይኸው እውቀት ነው። በመደበኛ ትምህርት ውስጥ "መገንዘብ" ማለት መምህር የተናገረውን ወይም ያቀረበውን ሃሳብ ከራስ ልምድ ፍቺ ጋር ማዛመድ እንጂ እንዳለ ተቀብሎ የራስ ማድረግ ማለት አይደለም (Petty, 2004)። ሃሳቡን በአብነቶች ተጨባጭ ለማድረግ እንሞክር።

መምህር፣ ገና ከቤት የመጣውን ህፃን "ማካፈል" የሚለውን ፅንሰሃሳብ ማስተማር ፈልገዋል። ህፃኑ ቀደም ሲል ቃሉን ያውቀዋል። ከያዘው እንጀራ፣ ቆሎ፣ ወይም ሌላ ነገር ለወንድም፣ እህት፣ ወይም ጓደኛ ማጋራት፣ ተካፍሎ መብላት መሆኑን ይገነዘባል። መምህር ደግሞ ሃሳባዊ የሆኑ ቁጥሮች ለሌሎች ሃሳባዊ ቁጥሮች በእኩል ማዳረስ የሚል ፍቺ ነው ማስረፅ የፈለጉት። ህፃኑ ግን ይህንን ፍቺ እንዳለ ሳይሆን እርሱ ከሚያውቀው ጋር አያይዞ ነው የሚገነዘበው። ይህ አይነቱ የመማርና የመገንዘብ ሂደት ነው ግንባታዊነት የሚባለው።

በPetty (2004:5) የቀረበው ተረት ሌላው ጥሩ አብነት ነው። አንዲት የእንቁራሪት ጫጩትና አሳ በአንድ ትንሽ ገንዳ ውስጥ ይኖሩ ነበር። ህይወታቸውን በደስታ ሲያሳልፉ የእንቁራሪት ጫጩት ድንገት ጭራዋን አጥፍታ አራት እግር አወጣችና ከገንዳው ወጥታ

ጠፋች። ከሳምንታት በኋላ ተመልሳ መጣችና በመስክ ውስጥ ስላገኘቻት ወፍ ተረከችላት። ወፍ ማለት ሁለት እግርና ሁለት ክንፍ ያላት በራሪ እንደሆነች ነገረቻት። አሳም በመሰልዋ (ዓሳ) ላይ የእንቂራሪትን ሁለት እግር ቀጠለችበት። ሁለት ክንፍ አለው ብላ አሰበች። ወፍ ማለት ይህቺ ነች ብላ ደመደመች። ድረጊቱ የተፈፀመው በህፃናት ተማሪዎች ነው ቢባል ህፃናት ከቤትና አካባቢው የሰበሰቡት እውቀት አለ። ያንን እውቀተ ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ከመምህር ወይም ከወላጅ የሚቀርብ አዲስ እውቀት ሲኖር ቀደም ሲል ከሰበሰቡት እውቀት ውስጥ የሚዛመደውን በመፈለግ ለማገናኘት ጥረት ያደርጋሉ።

ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ህፃናት በመምህራቸው ስለዝሆን ገለፃ እየተደረገላቸው ነው። ዝሆን ግዙፍ፣ ሰፋፊ ጆሮዎች ያሉትና ረጅም ኩምቢ ያለው እንስሳ እንደሆነ ተገለፀላቸው። መምህሩ ትልቅ ሲሉ አንዱ ተማሪ ግመልን ነበር ያሰበው። ግመል ላይ ሰፊ ጆሮና ረጅም ኩምቢ ቀጥሎ ዝሆን ማለት ይህ ነው ብሎ ፍቺ ሰጠ። ሌላው ፈረስ ላይ ሰፊ ጆሮና ኩምቢ በመቀጠል በአእምሮው ዝሆንን ሳለ። ሶስተኛው ህፃን ከበሬ የተለቀ እንስሳ አይቶ ስለማያውቅ በሬ ላይ ትላልቅ ጆራዎችና ረጅም ኩምቢ ጨምሮ ዝሆን ማለት ይህ ነው ብሎ አሰበ። ሶስቱም ከየመጡበት አካባቢና ከሚያውቋቸው እንስሳት ጋር ነው ለማመሳሰል የሞከሩት። እነዚህ ኣብነቶች እውቀት የሚገበየው ከራስ ልምድ ጋር የተያያዘ ፍቺ መስጠት ሲቻል መሆኑ ሊያመለክቱ ይችላሉ። አዲሱ እውቀት ከራስ ልምድ የራቀ ከሆነ ደግሞ ሊያያዝ ስለማይችል የዝሆንና የበሬ ቅርፅ የያዘ አዲስ ፍጥረት ይወለዳል።

የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአገር በቀል ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍትም ህፃኑ ከማህበረሰቡ ያገኘውን እውቀት መነሻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ምንባቦችና ልዩ ልዩ መለማመጃ ተግባራት በቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያነት ያገለግላሉ። በተለይ ምንባቦች አንብቦ መረዳትን ለማዳበር ተመራጭ ናቸው። ሆኖም በምንባቦቹ አማካይነት የሚቀርቡት ታሪኮች፣ ወጎች፣ ተረቶች፣ ወዘተ. ከህፃናቱ ዕውቀት ውጪ ከሆኑ ትምህርቱ ሽምደዳ እንጂ ተጨባጭ እውቀት ሊሆን አይችልም። ከዚህ አኳያ፣ በትግራይ ክልል የተዘጋጀው የአገር በቀል ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት በማህበረሰቡ ውስጥ የዳበረውን ተጨባጭ እውቀት መነሻው ሊያደርግ እንደሚችል ይገመታል። የዚህ ጥናት ትኩረትም ስርዓተትምህርቱ የማህበረሰቡን የእውቀት ግንባታ ሂደት ተከትሎ መደራጀቱን መፈተሽ ነው።

መርሃትምህርቱም ተማሪዎች ምን ይዘት፣ በምን ያህል፣ ምን ለማግኘትና እንዴት እንደሚማሩ በሚያሳይ መልኩ መደራጀት ይኖርበታል። በመርሃትምህርቱ ውስጥ ያሉይ ዓላማዎችናይዘቶች ወደመማሪያ መፅሓፍ ተሸጋግረው፣ ምንባብና መልመጃ ሆነው ከትውውቅ ወደልምምድ፣ ከዚያም ወደ ማፍለቅ በሚመራ ሁኔታ ሊቀርቡ ይገባል።

የዚህ ጥናት ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ እንደ ድልድይ ሆኖ መምህራንን፣ ተማሪውን፣ የትምህርት ባለሙያዎችን፣ የስርዓተትምህርት ባለሙያዎችንና፣ ፖሊሲ አውጪዎችን ከአንድ ጫፍ፤ ከሌላኛው ጫፍ ደግሞ ህብረተሰብንና የህብረተሰቡ ባህላዊ እሴቶችን ያገናኛል። የሁለቱ አካላት መገናኘት አገር በቀል እውቀትን ያካተተ ስርአተትምህርት እንዲወለድ ምክንያት ይሆናል። ግንኙነቱ እንዴት ሊከናወን እንደሚችልና ምን ከምን ወይም ከማን ጋር ሆኖ ምን ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ለማሳየት የሚከተለው ሞዴል ቀርቧል።

ምስል፡- 2፣ የጥናቱ ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ አመልካች ንድፍ




ከቤት ወደትምህርት ቤት ለሚመጡ አገር በቀል ህፃናት (1ኛ -4ኛ ክፍል)፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መፅሃፋቸው ውስጥ እቤት እያሉ የሚያውቁትን እውቀት በመነሻነት እንዲያገለግል መካተት ያለበት የበለጠ እንዲማሩና በእድሜ ሲበስሉም በማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ለመኖርና በመረጡት የስራ ዘርፍ ለመሰማራት መሳሪያ ሆኖ ስለሚያገለግል ነው።

በዕንሰሃሳባዊ ማእቀፉ መሰረት የቋንቋ ትምህርት፣ ህፃናት ከቤት ይዘውት የመጡትን እውቀት መነሻው ማድረግ ይጠበቅበታል። ደረጃ ስርዓተትምህርት ሲዘጋጅ መምህራን፣ ህብረተሰብ፣ ተማሪ፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ ሊሳተፉ እንደሚገባ ሲነገር ይሰማል። በተግባር እየተሰራበት ስለመሆኑ ግን አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም። ሞዴሉ እንደሚያሳየው የስርዓተትምህርት ዝግጅት ከፍላጎት አሰሳ ሊነሳ ይገባል። አሰሳው የህብረተሰቡን አበአ ለመለየትና በመደበኛ ትምህርት በኩል ወደልጁ እንዲተላለፍ የሚፈልገውን እውቀት ለይቶ ለማወቅ ያስችላል። ተማሪው ምን እውቀት እንዳለው፣ ተቋንቋ ትምህርት ደግሞ የትኞቹን እውቀቶችን ሊሻከም እንደሚገባው ለማወቅና ውሳኔ ለማስተላለፍ ያስችላል። አበአን ከማስተማር አኳያ የተማሪ፣ የህብረተሰብና የቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ከታወቀ በኋላ የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ሊወጣ ይችላል። በመቀጠል ፖሊሲውን የሚያስፈፅም ስርዓተትምህርት ይነደፋል። የሶስቱ አካላት ፍላጎትና አበአን መሰረት በማድረግ ፖሊሲ ከነደፉ በኋላ ስርዓተትምህርት መንደፍም ሌላው አማራጭ መንገድ እንደሆነ ሞዴሉ ያመለክታል።

ይህ ሞዴል ምንጭ አልተጠቀሰለትም። የዚህ ጥናት ባለቤት በመምህርነትና በስርዓተ ትምህርት ባለሙያነት አገልግያለሁ፤ አሁንም ከትምህርትና ትምህርት ነክ ስራዎች አልወጣሁም። በመሆኑም ስርአተ ትምህርት እንዴት ቢነደፍ የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ለመገመት የምችል ሆኖ ይሰማኛል። ሞዴሉም ከዚህ ግምት የመነጨ የራስ አተያይ እንጂ ከማንም ልሂቅ ፅሁፍ ስላልተወሰደ መረጃ ሊጠቀስለት አልቻለም።

### 2.2.9.3. ስነኑረታዊ (Ontological) አመለካከትና ስነዕውቀታዊ (Epistemological) ግንባታ

ስነኑረታዊ እና ስነእውቀታዊ ግንባታ አተያዮች አለማችንን ለማየትና ለመተርጎም የሚያስችሉ ፍልስፍናዎች ናቸው (Banda, 2008; Creswell, 2009)። ስነኑረት፣ መታወቅ ስላለበት ፍጥረት (Entity) ወይም እውነታ (Reality) ምንነት፣ እንዴትነት፣ ስንትነትና የትነት (ምድብ) የሚያጠና ፍልስፍና ነው። **ስነእውቀታዊ ግንባታ** ደግሞ ስለ የእውቀት ግንባታና ስለማወቅ መቻልና አለመቻል የሚያስረዳ ፍልስፍና ነው። ሁለቱም ልዩ ልዩ አተያዮችን የያዙ ናቸው። ከሚያተኩሩባቸው ውስጥ ፍትነታዊ እና ገለፃዊ (Positivism and Interpretivism) የሚሉ አተያዮች ይገኙባቸዋል።

**ፍትነታዊ** (Positivism)፡- ስለ ኑረት ወይም ህልውና ሲያስረዳ በምንኖርባት አለም ውስጥ ከሰው ልጅ እውቅና ውጪ የሆኑ በርካታ ተጨባጭ እውነታዎች እንዳሉና በሳይንሳዊ ምርምር ሊደረስባቸው እንደሚችል ይገልፃል። ለምሳሌ፡- የሰው ልጅ እንዴትና በምን ምክንያት እንደተፈጠረ ቀደም ሲል መታወቁን ያስረዳል።

**ገለፃዊ**፡- ማህበራዊ እውነታ በሰዎች የሚዋቀርና የሚገለፅ እንደመሆኑ ከሰው ልጅ እውቅና ውጪ ሊኖር እንደማይችል ያስረዳል። ሁለቱም አተያዮች ከእውቀት ግንባታ አኳያ የሚያቀርቧቸው ሃሳቦች የሚጣጣሙ አይደሉም።

**ፍትነታዊ**፡- ሁሉም ጥናቶች (ማህበራዊ ሳይንስም ጭምር) በሳይንሳዊ ዘዴና መሳሪያ ሊጠኑ እንደሚገባ ያሳስባል። ካልሆነ ግን ድምዳሜዎቻቸው ተቀባይነት እነደማያገኙ ነው። ትክክለኛ ወይም እውነተኛ እውቀት የሚባለው በሳይንሳዊ ዘዴ ተፈትሾ እውነትነቱ የተረጋገጠለት ብቻ ነው ብሎ ያምናል።

**ገለፃዊ**፡- በማንኛውም ዘዴ ተጠንቶ እውነትነቱ የተረጋገጠለት ውጤት በሌላ ጊዜ፣ በሌላ ተመራማሪ ወይም መሳሪያ ተፈትሾ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ስህተት ሆኖ ሊገኝ ይችላል። በተለይ የማህበራዊ ሳይንስን ጥናት በመጠናዊ ምርምር መሳሪያዎች መርምሮ ሁልጊዜ ትክክለኛ ውጤት ላይ መድረስ ያስቸግራል። እንደ ደስታ፣ ሃዘን፣ ፍቅር የመሳሰሉት ስሜቶችን ለማጥናት መጠናዊ መረጃ ላያስፈልግ ይችላል። በአንፃሩ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደተገለፀ ማብራራትና መተንተን ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች የሚገነቧቸው የየራሳቸው የሆኑ እውቀቶችና እውነታዎች አሉ። ተመራማሪውም አውዱ ውስጥ ተገኝቶ የሰማውንና የተመለከተውን ሁሉ ለሱ በተሰማው መንገድ ማብራራት፣ መተርጎምና አንድምታውን ማስቀመጥ ይኖርበታል። በተለያዩ አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶች ስለእውቀትም ሆነ ስለኑረት የሚሰጡት ትርጉም የተለያየ ሊሆን ይችላል። ልዩነቱ የተገኘው ግን ከአጠናን ዘዴ ወይም ከመሳሪያዎች ሳይንሳዊ አለመሆን ሳይሆን ከማህበረሰቡ የአተያይና አተረጓጎም ልዩነት ነው (Banda, 2008; Creswell, 2009)።

ለምሳሌ የትግራይ ህብረተሰብ ውሎና አዳሩ በአንድ አካባቢ በመሆኑ አንድ አይነት የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የአስታራረስ፣ የሰርግ፣ የቀብር፣ የእምነት፣ ወዘተ. ስርአት ይኖረዋል። ከነዚህ ባህላዊ ክንውኖች የሚመነጩ አተያዮች፣ ስነልቡና፣ ፍልስፍናዎችና

ስነምግባሮች ስር እየሰደዱ ይሂዱና ህብረተሰቡ ከሌላው የሚለይባቸው እውቀቶች ሆነው ይቆማሉ። በሌላው ጫፍ የሚገኘው ህብረተሰብም እንደትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ ሁሉ የተለያዩ ባህሎችን፣ አተያዮችን ፍልስፍናዎችንና ስነምግባሮችን ያዳብራል። በሁለቱ አካባቢዎች የዳበረው እውቀት ተመሳሳይነት ሊኖረው ቢችልም እንኳ ፍፁም አንድ አይነት ሊሆን ግን አይችልም። ልዩነቱ የመጣው ከአጠናን ዘዴና ከማጥኛ መሳሪያዎች መለያየት ሳይሆን ከማህበረሰቦቹ የአኗኗር ዘይቤና ከሚኖሩበት አካባቢ መለያየት ነው። በዚህ ላይ የሚታይ ልዩነት ደግሞ የአጠናን ዘዴ ልዩነትንም ሊያስከትል ይችላል።

ከገለፃውያኑ አተያይ መገንዘብ የሚቻለው ሁሉንም የእውቀት መስኮች አንድ አይነት ዘዴ ወይም መሳሪያ ተጠቅሞ ማጥናት የማይቻል መሆኑ ነው። ስለሆነም ፍትነታዊው መጠናዊ ምርምርን፣ ገለፃዊው ደግሞ አይነታዊ ምርምርን ለማካሄድ  ተስማሚ አተያዮች መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል።አሁን ለሚካሄደው ጥናት ገለፃዊ የምርምር ስነዘዴ የተመረጠውም  ከዚህ አኳያ ነው።

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ

"በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት የሃገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ" የሚለው የጥናት ርእስ ሲመረጥ በቅድሚያ በርእሱም ሆነ ከርእሱ ጋር በሚመሳሰሉ ጉዳዮች ዙርያ ጥናቶች መደረግ አለመደረጋቸውን ለማረጋገጥ በቃል ደረጃ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ውይይት አካሂጃለሁ። እንዲሁም ተገቢ የፍተሻ ንባብ አድርጌአለሁ። በተደረገው ፍተሻ በተለይ በሶስተኛ ዲግሪ ደረጃ ርእሱን የሚደግም ወይም በከፊል የሚመስል በትግርኛም ሆነ በሌላ ቋንቋ የተካሄደ ጥናት አላጋጠመኝም። በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስርዓተ ትምህርት ላይ የተደረገና በመጠኑም ቢሆን ከጥናቱ ጋር የሚመሳሰል የAlmayehu Jote (2012) ጥናት ነው። ከኢትዮጵያ ውጪ የተካሄዱ ጥናቶችንም ለማየት  ጥሬአለሁ። በተወሰነ መልኩ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ ስራዎች አግኝቻለሁ።

አገር በቀል እውቀት የሚለውን ሃረግ መነሻ ያደረጉ ከአየር ንብረት ጥበቃ፣ ከመድሃኒት፣ ከአዝርእት ጥበቃ፣ አገር በቀል ከሆኑና ለምግብነት ከሚውሉ ፍራፍሬዎችና ቅጠላቅጠሎች፣ ወዘተ. ጋር የተያያዙ ጥናቶች ተካሂደዋል። ከትምህርት ጋር የተያያዙ ጥናቶችም አጋጥመዋል። ስለሆነም ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስል ባህሪ ያላቸውን በሃገር ውስጥና

በውጪ የተሰሩ "ተዛማጅ" ጥናቶችን ከአጫጭር ማብራሪያዎች ጋር በሚከተለው መልክ አቅርቤአቸዋለሁ።

በኢትዮጵያ ከተሰሩትና ካጋጠሙ ጥናቶች ውስጥ Eshete Gemeda (2007) የPh.D. መመረቂያ ፅሁፍ አንዱ ነው። "የአፍሪካ ህብረተሰብ የጋራ እሴቶች፣ የኦሮሞ ትውፊት፣ ስነፅሁፍና ባህላዊ ጥናት አሁን ከሚገኝበት ሁኔታ አኳያ" የሚል ርእስ አለው። በጀርመን ሃገር የተሰራ ሆኖ ሙሉ ፅሑፉን ማግኘት ስላልተቻለ መረጃ የተወሰደው ከመግቢያውና ከአህፅሮተ ጥናቱ ብቻ ነው። የጥናቱ ትኩረት፡- የመጥፋት አደጋ እያንገርበበት ያለውን የኦሮሞ ትውፊትና ስነፅሁፍ በመሰብሰብ የህዝቡን ብሄራዊ ማንነት ስሜት መመለስ የሚል ነው። ጥናቱ በአገር በቀል እውቀት ላይ የተደረገ ስለሆነ መጠነኛ ግንኙነት አለው ማለት ይቻላል። ስርዓተትምህርት ትኩረቱ ስላልሆነ ደግሞ ከኔ ጥናት ይለያል።

**ሁለተኛው፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደ Grenier (1998) ክለሳ ያካሄዱበት አገር በቀል መድሃኒቶችን የማወቅ አላማ ያለው ጥናት ነው። በውጭ ሰዎች የተካሄደ እንደሆነና አገር በቀሎቹ በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ እነዳልነበሩ ይጠቅሳል። ጥናቱ፣ የት አካባቢ ወይም በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እንደተካሄደ ግን ፅሁፉ አይጠቁምም። ጥናቱ አገር በቀል እውቀትን ትኩረቱ ስላደረገና እውቀቱን ለመለየት ፍተሻ ስለሚያካሂድ ተመሳሳይነት አለው። ሆኖም የኔ ጥናት አበእ በስርአተትምህርት ውስጥ መካተት አለመካተቱን በመፈተሽ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ መሰረታዊ ልዩነት አላቸው።

**ሶስተኛው፡-** የAlmayehu Jote Tullu(2012) ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት በአገር በቀል እውቀት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ጥናቱ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ሲሆን አጠቃላይ ዓለማ በኦሮሚያ ባሌ ዞን የአንደኛ ደረጃ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት፣ ህብረተሰቡ በእርሻ ላይ ያለውን አገር በቀል እውቀት የማስተዋወቅ ድርሻው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉት የጥናት ጥያቄዎችን ይዞ ተነስቷል፡-

- በባሌ ዞን ተጠቃሽ የሆኑ የእርሻ አገር በቀል እውቀቶች ምን ምን ናቸው? ከትውልድ ወደትውልድ እንዴት ይሸጋገሩ ነበር? እንዴትስ እየተጠበቁ ነው?
- የኦሮሞ ቋንቋ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ በመሆኑ የህዝቡን ባህልና እሴት የመጠበቅና የማስተዋወቅ ድርሻውን ህብረተሰቡ እንዴት ይመለከተዋል?

- ለአንደኛ ደረጃ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ ከእርሻ.ጋር የተያያዙ አገር በቀል ልምዶችን ምን ያህል ማካተት ችሏል?
- የኦሮሞ ቋንቋን እንደማስተማሪያ የመገልገሉ ሁኔታ ተማሪው በክፍል ውስጥ ምን መማር እንዳለበት ከመወሰን አኳያ ህብረተሰቡን ምን ያህል አሳትፏል?

**የጥናቱ ግኝቶች፡-**

- አገር በቀል የእረሻ እውቀታቸውን ከዘመናዊ አሰራር ጋር እያቀናጁ በመጠቀም ላይ መሆናቸው፣
- ቋንቋው የእርሻ አበእ ለማስተዋወቅ ባያገላግልም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት መዘጋጀቱ ራሱ ጥሩ ነገር መሆኑ፣
- በዚህ ጥናት ውስጥ የተሳተፉ ወላጆች፣ መምህራን፣ የስርዓተትምህርት ባለሙያዎች የኦሮምኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ሆኖ ማገልገሉ የህብረተሰቡን ስነልሳናዊ መብት ማረጋገጥ ስለሆነ በአዎንታ እንደሚያዩት፡፡
- ኦሮምኛን በመማሪያ ቋንቋነት መገልገሉ ተማሪዎችና ወላጆች በባህላቸው እንዲኮሩ፤ ወላጆችና ተማሪዎች ስለትምህርት እንዲወያዩ ማስቻሉ፤
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ገጠሩንና የገጠሩን ህይወት ጥሩነት የሚያጎሉ መልመጃዎችና ይዘቶች ሊኖሩት እንደሚገባ፣
- ህብረተሰቡ ልጆቹ ምን መማር እንዳለባቸው የመወሰን፣ በመፃህፍት ዝግጅትና መሻሻል ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ የማድረግ እድል እንዳላገኘ አመልክቷል።

የአለማየሁ ጆቴ ጥናት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትን እና አገር በቀል እውቀትን ጉዳዩ አድርጎ ስለተነሳ ከኔ ጥናት ጋር ያለው ተመሳሳይነት ከሌሎቹ ይልቅ የሰፋ ነው። ነገር ግን ከዓላማዎቹ መገንዘብ እነደተቻለው፤ የአለማየሁ ጥናት የህብረተሰቡ አገር በቀል እርሻ እውቀት ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚተላለፍ ይፈትሻል። በመፅሓፉ ውስጥ አገር በቀል ልምዶች መካተታቸውንም ይመረምራል። ህብረተሰቡ በስርዓተትምህርቱ ቀረፃ ወቅት የነበረው ድርሻ ምን ይመስል እንደነበረ ማየትም የጥናቱ አንድ ትኩረት ነው።
የኔ ጥናት ደግሞ መበማሪያ መፅሃፉ ውስጥ አበእ መኖሩ፡ በምን ያህል እንደቀረበና በምን መልክ እንደቀረበ ማየት ነው። በስርዓትትምህርት የህብረተሰብ ተሳትፎ የዚህ ጥናት ትኩረት አይደለም። እንዲሁም የኔ ጥናት አበእ ሲል ከእርሻ ጋር የተያያዙትን ብቻ ሳይሆን በመማሪያ መፅሓፉ ውስጥ ያሉትን አበእ ነክ ጉዳዮች ሁሉ ስለሚመለከት በሁለቱ ጥናቶች መካከል መሰረታዊ ልዩነት መኖሩ መገንዘብ ይቻላል።

**አራተኛው፡-** Settee (2007) " Indigenous Knowledge System, Our Time Has Come " በሚል ርእስ የቀረበ ሆኖ ጥናቱ ሁለት የጥናት ጥያቄዎችን ነው ይዞ የተነሳው። እነሱም፡-

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሃገር በቀል እውቀት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ምን ያህል ነው ?
- የማህበረሰቡ እውቀት (ኣበእ) በከፍተኛ ትምህርትና በማህበረሰቡ እድገት ላይ ምን ኣይነት ተፅእኖ ይፈጥራሉ? የሚሉ ናቸው።

**የኣጠናን ዘዴ፡-** ኣሳታፊ ተግባራዊ ምርምር ዘዴን (Participatory Action Research)

የተከተለ ነው።

**የጥናቱ ግኝት**

- የማህበረሰቡ የኣኗኗር ሁኔታ በመለያየቱ ኣገር በቀል እውቀትም  የተለያየ መልክ እንደ.ያዘ፤
- ዩኒቨርሲቲዎች በውስጣቸው የኣገር በቀል እውቀት ትምህርት ስርዓት እንዲኖር ካላደረጉ፤ ኣገር በቀል ተማሪዎችንና እነሱን ተከትለው የሚነሱ ጥያቄዎችና ችግሮችን በኣግባቡ ማስተናገድ እንደማይችሉ፤
- ዩኒቨርሲቲዎች የፆታም ሆነ የጎሳ መድልዎንና መገለልን እንዲሁም ዘረኝነትን ለማስወገድ በሚችል መልክ ኮርሶቻቸውን መቃኘት እንደሚጠበቅባቸው፤ ይህንን ማድረግ ግን ለተቋማቱ ፈታኝ እንደሚሆን፣
- ወጣቱን በፈጠራና ባህላዊ ስራዎች ማሳተፍ ለማህበረሰብ ኣቀፍ ተቋማት መኖር ወሳኝ መሆኑ፤
- ቋንቋና ባህላዊ ኣገላለፆች (ሙዚቃ፣ ተውኔት፣ ተረቶች፣ ስእል፣) የእውቀቱ ማስተላለፊያ መሰረያዎች መሆናቸው ይገልፃል።

የSettee ጥናት ኣላማ፤ ኣገር በቀል ዕውቀት በእድገት ላይ ያለውን ተፅእኖ መፈተሽ ነው። በመካሄድ ላይ ያለው ጥናት ዓላማ ግን የህብረተሰቡን ኣገር በቀል እውቀት መለየትና በስርዓተትምህርቱ ውስጥ መካተቱን መፈተሽ ነው። በሁለቱ ጥናቶች መሰረታዊ የሆነ የኣላማ ልዩነት ኣላቸው።

**ኣምስተኛው፡-** የ Banda (2008) "ትምህርት ለሁሉም እና የኣፍሪካ ኣገር በቀል እውቀት ስርዓት" በሚል ርእስ የቀረበ የዶክተርነት ትምህርት ማሚያ ጥናት ነው።

**ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፡-** "የቼዋ ኣፍሪካ ኣገር በቀል እውቀት ስርኣትና የመደበኛው ስርዓተትምህርትን በማዋሃድ በተለይ በቼዋ(ዛምቢያ) ህዝብ ውስጥ ትምህርት ለሁሉም የሚለውን ግብ ማሳካትይቻል ይሆን?" የሚል ኣብይና በርካታ ንኡሰን ጥያቄዎችን

የያዘ ነው። ከቀረቡት ዝርዝር የጥናት ጥያቄዎች ውስጥ ለኣብነት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል፤

- ዛምቢያ የትምህርት ለሁሉም በ2015 ግቦችን ታሳካ ይሆን?
- ዛምቢያ የትምህርት ለሁሉም በ2015 ግቦችን ለማሳካት የሚያጋጥሟት ፈተናወች ምን ምን ናቸው?
- የቼዋ ህዝብና የአፍሪካ ኣገር በቀል እውቀት ስርዓት፤ ግቡን ለማሳካት እገዛ ያደርጋሉ?
- የትምህርት ለሁሉም ግብ ለማሳካት የቼዋ አፍሪካ አገርበቀል እውቀት ስርዓት (ኣኣበእስ) ኣካታችነቱና ኣደረጃጀቱ ብቃት ኣለው?

የባንዳ ጥናት ኣገር በቀል እውቀት፤ በተለይ ደግሞ በኣገር በቀል ትምህርት ላይ በማተኩሩ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። ጠቃሚ ሃሳብም ተገኝቶበታል። ሆኖም ባንዳ የተነሳበት የጥናት ዓላማ የተለየ በመሆኑ ሁለቱ ጥናቶች መሰረታዊ የትኩረት ኣቅጣጫ ልዩነት ኣላቸው። የባንዳ ትኩረት ለ'ትምህርት ለሁሉም' ግቦች መሳካት ከዘመናዊው ጋር የተዋሃደው የአፍሪካ ኣገር በቀል እውቀት ስርዓት ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚችል ማየት ሲሆን የኔ ጥናት ኣላማ ደግሞ የህብረተሰቡን ኣበእ ከለዩ በኋላ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ኣገር በቀል እውቀት መካተት ኣለመካተቱን ማረጋገጥ ነው።

ከላይ ከቀረቡት ኣጫጭር ማብራሪያዎች መረዳት እንደሚቻለው በሃገር ውስጥም ሆነ በውጪ የተካሄዱት ጥናቶች ኣገር በቀል እውቀትን በመዳሰሳቸው ካልሆነ በቀር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስል ነገር የላቸውም። ስለዚህ ርእሱ ምርምር ያልተካሄደበት በመሆኑ አንድ ክፍተት ሊሞላ እንደሚችል ኣምናለሁ።

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስር ሁለት ጉዳዮች በዝርዝር ተብራርተዋል ። በመጀመሪያ:- የጥናቱ አመራር ሂደት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ተሞክሯል። ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። ለምን አይነታዊ ዘዴ መከተል እንዳስፈለገ በአጭሩ ተገልጿል። ምርምሩ አይነታዊ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ቀላል የሆኑ ስሌቶችና የመቶኛ ውጤት ማሳያ ቁጥሮች ስራ ላይ ውለዋል። የጥናቱ አጠቃላይ ሂደት ንድፍ፣ የመረጃ አቀባይ ሰዎች ናሙና አወሳሰድ ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ምን እነደሚመስሉ በዚህ ምእራፍ ስር ተገልፀዋል። ሁለተኛ፣ ለጥናት በተመረጡት የትግርኛ ቋንቋ መርሃትምህርቶች፣ የመማሪያ መፃህፍትና የመምህር መምሪያዎች ላይ በምን መልክ የይዘት ትንተና እንደተደረገ በዝርዝር ተመልክቷል።

## 3.2. ጥናቱ የተከተለው ስነዘዴ

ይህ ጥናት የተመራው በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ነው። የአንድ ህብረተሰብ እሴቶች፣ ባህል፣ እውቀት፣ እምነት ለማወቅ ጥናት የሚያካሂድ ሰው ክፍት ጥያቄዎችን በማቅረብ ከተጠኚው ህብረተሰብ አኳያ ሆኖ ለመረዳትና ምላሽ ለመስጠት የሚጥር ከሆነ ጥናቱ የአይነታዊ ምርምር ዘዴን የተከተለ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል (Dornyei, 2007; Mack, 2005)። የተገኙት መረጃዎችና ውጤትም በቁጥር፣ በሰንጠረዥና በስታትስቲካዊ ውጤት ተደግፈው ሳይሆን በገለፃና መብራሪያ ነው የሚቀርቡት። እኔ ያካሄድኩት ጥናትም እነዚህንና ሌሎች ዓይነታዊ ምርምር የሚያሟላቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ ስለሆነ ሙሉ በሙለ ዓይነታዊ ምርምር ነው። የተከተልኩት የጥናት ዘዴ ሁለት ዓይነት ሲሆን አመቺ የንሞና ዘዴና ህሉው ጠቃሽ (Grounded theory) የሚባለውን ንድፈ ሓሳብ ነው።

የህሉው ጠቃሽ ንድፈ ሓሳብ መነሻ:- በማህበራዊ ሳይንስ ጥናት የሚያካሂድ ወይም ለማካሄድ የሚነሳ ተመራማሪ ቀዳሚ ተግባሩ መሆን ያለበት በተለያዩ ሃገሮች ወይም አካባቢዎች እየተሰራበት ያለ ንድፈ ሃሳብ በዚህ ጥናት ማገልገል መቻል አለመቻሉን መሞከር ሳይሆን በመስክ ተገኝቶ መረጃ መሰብሰብ ነው (Cohen; et al. 2007;

Dornyei, 2007)። የተለያዩ ተመራማሪዎች የነደፏቸውን ትወራዎች ይዞ የአንድ የተወሰነ አካባቢ አገር በቀል እውቀትን ለመመርመር መሞከር፣ ልብሶችን በአንድ አይነት መጠን ካሰፉ በኋላ የተለያየ መጠን ላላቸው ሰዎች ተስማሚ ይሆናል ብሎ እንደማሰብ ነው። ጥረት የሚደረገውም የልብሶቹን መጠን ለማስተካከል ሳይሆን እያንዳንዱን ሰው አስተካክሎ ከልብሶቹ ጋር እንዲስማማ ለማድረግ ነው። በአንድ ጉዳይ ላይ የተካሄደን ጥናት መሰረት አድርጎ የተፈጠረን ንድፈ ሐሳብ በሌላ ጉዳይና አካባቢ ለሚካሄድ ጥናት በመለኪያነት ለመገልገል፣ ወይም አዲሱ ጥናት ከነባሩ መለኪያ ጋር ስለመስማማቱ ለማረጋገጥ (Willig, 2008) መልፋት አያስፈልግም፣ የማይስማማ መሆኑ የተረጋገጠው ገና ከጅምሩ ነውና።

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት ህሉው ጠቃሽ፣ ትወራን በስነዘዴነት የሚገለገል የማህበረሰብ ሳይንስ ተመራማሪ፣ ጥናት ለማካሄድ ተገቢ መሳሪያዎችን መርጦ መረጃ መሰብሰብ እንጂ ትወራ ይዞ መነሳት አይኖርበትም። ለምሳሌ ጎረቤት ከሆኑት ክልሎች በአፋር አገር በቀል እውቀትን የተመለከተ ጥናት ተካሂዶ የተደረሰበት መደምደሚያና ከመደምደሚያው የፈለቀው ትወራ፣ በትግራይ ውስጥ ለሚካሄድ ጥናት በመረጃነት እነጂ በመስፈርትነት ሊያገለግል አይችልም። የሁለቱ ክልሎች ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ የአኗኗር ዘይቤዎችና መልክዓ ምድር የተለያየ ነው። ሁለቱን ክልሎች የሚያስተሳስር የጋራ ጭብጥ ካልኖረ በቀር ከአፋር የተገኘውን ትወራ መነሻ በማድረግ ከትግራይ የተሰበሰበውን መረጃ ለመለካት በመሳሪያነት ሊያገለግል አይችልም ።

ህሉው ጠቃሽ አተያይን ለመጀመሪያ ጊዜ ስራ ላይ ያዋሉት Glaser and Strauss (1967) የተባሉ ሁለት አሜሪካዊ የስነማህበረሰብ ሊቃውንት (Sociologists ) ናቸው (Dornyei, 2007; Willig, 2008)። በዚያ ዘመን የስነማህበረሰብ ጥናቶች ይከተሏቸው የነበሩት ንድፈሐሳቦች አርኪ ሆነው ስላላገኟቸው ነበር አዲስ ትወራ ማራመድ የጀመሩት። የዚህ ንድፈ ሐሳብ አራማጆች ሌሎች ተመራማሪዎች ካመነጩት ንድፈ ሃሳብ አለመነሳታቸው መለያቸው ነው (Cohen, et al. 2007; Dornyei, 2007; Willig, 2008)። የምርምሩ ዓላማም ቀድሞ የተቀመጠ ትወራን ይዞ በመነሳት ከጥናቱ ውጤት ጋር ማመሳከር ሳይሆን ከመስክ የተገኘ ውጤት ማጠቃለያ መሰረት ያደረገ ንድፈ ሐሳብን ማፍለቅ ነው። የስነማህበረሰብ ተመራማሪዎቹም ቀድሞ የወጣን ትወራ ለማረጋገጥ ሳይሆን ጥናቱ የተካሄደበትን አውድ መሰረት ያደረገ መደምደሚያና ንድፈ ሐሳብ ለማውጣት ይሰራሉ።

ህሉው ጠቃሽ ንድፈሐሳ የማህበራዊ ሳይንስ ውስጥ ዓይነታዊ ምርምር ለማካሄድ የሚያገለግል ነው (Cohen et al. 2007; Patton, 2002, Dorney, 2007)። የምርምር ዘዴው የሚወሰነው በጥናቱ አመራር ሂደት ነው። የአመራር ሂደቱ ወደእውኑ ዓለም የሚወስድና እውኑን ዓለም ተጠግቶ ለማየት የሚያስችል ከሆነ ጥናቱ ሲጠቃለል አውዱንና እውኑን ዓለም መሰረት ያደረገ ትወራ ይመነጫል። በህሉው ጠቃሽ ትወራ፤ አንድን ጉዳይ ከመረመሩ በሁዋላ የተደረሰበትን ማጠቃለያ በንድፈሃሳብ መልክ ማውጣት ተገቢ የምርምር ሂደት ነው። ከዚህ ጥናት በተገኘው ንድፈሃሳብ በተለየ አውድ ያለን እውነታ ፈትሾ ለማረጋገጥ መሞከር ግን ስህተት ነው። ምክንያቱም ሁለቱም በተለያየ አውድ ስለሚገኙ ልዩነት እንዳላቸው ስለሚታወቅ ነው። ህሉው ጠቃሽ፣ ቀድሞ የተገኘን ትወራ መነሻ አያደርግም። ይህ ጥናትም ፍተሻን የሚያስቀድም፣ ከመረጃ ትንተና በኋላ ማጠቃለያና ትወራን የሚያቀርብ ስለሆነ ህሉው ጠቃሽ ንድፈ ሓሳብን ተከትሏል።

የህሉው ጠቃሽ ትወራ፣ ጠማሪ (inductive) ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚያድግ ካብ (ግንባታ) እንጂ ዘርዛሪ (Deductive) ከጥቅል ትወራ ወደ ዝርዝር የማረጋገጥ ስራ የሚሄድ አይደለም፡፡ ይህ ጥናትም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚያድግ /ጠማሪ/ የአመራር ስርዓትን የተከተለ ነው፡፡ መረጃዎች ከመስክና ከሰነዶች ተሰብስበዋል፡፡ ለትንተና የሚሆኑ ይዘቶች ተመርጠዋል፡፡ በትንተና ይዘቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችና ግንኙነቶች ተፈትሸዋል፤ በአይነት ተለይተዋል። ግንኙነቶቹ በምን ምክንያት እንደተመሰረቱ ተብራርተዋል። የምርምሩ ሂደት ምን ይመስል እንደነበረና ስለእያንዳንዱ ምድብ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖርና ግንኙነቱም በግልፅ እንዲታይ ተደርጓል (Cunningham, 1992)፡፡

## 3.3. የመረጃ ምንጮችና የናሙና አወሳሰድ ዘዴ

የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃትምህርቶች፣ መማሪያ መፃህፍቱና የመምህሩ መምሪያ አገር በቀል እውቀትን ሊያስተምሩ እንደሚገባ ይታመናል። ከዚህ አኳያ መሳሪያዎቹ የህብረተሰቡን አገር በቀል እውቀት ምን ያህል ማንፀባረቅና ወደ አዲሱ ትውልድ ማስተላለፍ እንደቻሉ ለማወቅ ፍተሻ ተካሂዷል። አገር በቀለ እውቀት፤ በጉርብትና፣ በሌሎች ህዝቦች ተፅእኖ፣ ወዘተ. ምክንያት ከሌሎች ባህሎች ጋር ሊቀላቀል፣ በመጤ ባህል ሊተካና ነባሩ ባህል ጨርሶ ሊጠፋ ይችላል። ለምሳሌ ከተሞች

ከተለያዩ አካባቢዎችና ባህሎች የተገኙ ህዝቦች መኖሪያ እንደመሆናቸው የህዝቦች ባህሎች ሊቀላቀሉና ሊዳቀሉ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት አገር በቀል የሆነውን ካልሆነው መለየት ሊያስቸግር ይችላል። የዚህ አይነቱን ችግር ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ መረጃ አቀባዮችን በጥንቃቄ መምረጥ አስፈልጓል። ለዚህ ሲባልም የሚከተሉትን የመረጃ ምንጮችና የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ስራ ላይ ውለዋል።

በአይነታዊ ምርምር ውስጥ ሁለት የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎች አሉ። እነሱም የነሲብ (Probablity) እና የይሁንኝ ወይም ኢግምታዊ (Purposive) ናቸው። የነሲብ (አቦሰጡኝ) ናሙና የሚወሰድባቸው ብዙሃን (ሰዎች፣ እንስሳት፣ እፀዋት፣...) እነማን እንደሆኑ ይታወቃሉ። ስለሆነም ከብዙሃኑ ውስጥ አንዱን፣ ሁለቱን ወይም የተወሰኑትን በእጣ ወይም በሌላ አጋጣሚያዊ ዘዴ በመምረጥ ውክልና ማግኘት ይቻላል። ሁሉም አባላት እኩል የመመረጥና ናሙና የመሆን እድል አላቸው። ይህ ከዚህ ይበልጣል ወይም ያንሳል በሚል ምክንያት የሚመረጡ ወይም የሚቀሩ አባላት አይኖሩም (Cohen, et al. 2007; Marczyk, 2005; ያለው፤1998ዓ.ም.)። በዚህ ጥናት ውስጥ ከህብረተሰቡ መሃል ከተመረጡ የዕድሜ ባለፀጋዎች መረጃ ለመሰብሰብ አጋጣሚያዊ ያልሆነ ወይም የይሁንኝ (Purposive) የንሞና ዘዴ ንኡስ ክፍል የሆነው **ሰንሰለታዊ ጥቆምታ** (Snowball or Chain Referral ) የንሞና ዘዴ ነው ስራ ላይ የዋለው። በዚህ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተገኙ መረጃ አቀባዮች በተወሰነ ጉዳይ ላይ ላቅ ያለ እውቀት፣ ግንዛቤ ወይም ልምድ ያላቸው ናቸው። የንሞና ዘዴው ትኩረቱም ብዙሃኑን መወከል ላይ ሳይሆን ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጥልቅ የሆነ መረጃ ማግኘት ነው።

ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ናሙና፣ በአይነታዊ ምርምር ውስጥ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት (ለመምረጥ) ከሚያገለግሉ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ በይሁንኝ (Purposful) የንሞና ዘዴ ስር የሚመደብ ነው፡፡ የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች የትግራይ ህዝብ አገር በቀል እውቀትን በሚገባ ያውቃሉ ተብለው የሚገመቱ አገር በቀል ሰዎች ናቸው፡፡ ከህብረተሰቡ መሃል በእጣ ወይም ለሆን ለወረዳ ወይም ለጣቢያ የተመጣጠነ ውክልና በመስጠት፣ አለዚያም በነሲብ ንሞና (probability sampling) እነዚህ አይነቶቹን ሰዎች ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ውሱን ቦታዎች ወይም ሰዎች በናሙናነት ከተወሰዱ በኋላ ወካይ ከተባሉት ሰዎች ተፈላጊው መረጃ ላይገኝ ይችላል። ስለሆነም የሰንሰለታዊ ጥቆምታ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ለዚህ ጥናት ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል።

ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ናሙና ከሌሎቹ የአይነታዊ የምርምር ዘዴ የናሙና አይነቶች በተለየ ለዚህ ጥናት ተመራጭ የሆነባቸው ምክንያቶች **አንደኛ፡-** የምርምር ርእሱ የጥናቱ መረጃ ምንጮች አስቀድሞ መገመት ወይም መወሰን የማያስችል ስለሆነ ነው። የተመረጠው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ደግሞ ጥናቱን አስመልክቶ መረጃ ለመስጠት የሚችሉ ወይም ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ማግኘት ወይም ለይቶ ማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት አጋጣሚ የሚወሰድ የናሙና አይነት በመሆኑ ነው (Cohen, et al. 2007; Mack, et al. 2005)። **ሁለተኛው ምክንያት፡-** በሌሎቹ የአይነታዊ ንሞና ዘዴዎች ለማግኘት የማይቻሉ መረጃዎችንና የመረጃ ምንጮችን ፈልፍሎ ለማውጣት የሚያስችል መሆኑ ነው። **ሶስተኛው ምክንያት፡-** ከህብረተሰቡ ጋር ባላቸው ልዩ ግንኙነትና ባካበቱት ልምድ ተመራጭ የሆኑ፤ ነገር ግን ተመራማሪው በቀላሉ ሊያገኛቸው የማይችል መረጃ አቀባዮችንና የመረጃ ምንጮችን ማውጣት የሚያስችል በመሆኑ ነው (Patton, 2002, Mack, et al. 2005)።

አጥኚው ወደ ሌሎች መረጃ አቀባዮች ሊመሩኝ ይችላሉ ብሎ የሚገምታቸው የእድሜ ባለፀጋዎችንና በክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተወካይ ሆነው በሶስቱ ዞኖችና በቆላ ተምቤን ወረዳ የተመደቡትን የባህልና ቋንቋ ጥናት ባለሙያዎችን (Experts) አነጋገረ። እነዚህ ሰዎች የመጀመሪያዎቹ መረጃ አቀባይ (Informants) ሆነው አገለገለዋል። በተለይ ጥናቱን አስመልክተው ከሚሰጡት መረጃ ይልቅ ስለጉዳዩ የተሻለ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችን በመጠቆም እገዛ አድርገዋል፡፡ ብቁ ተብለው የተጠቆሙት ሰዎች በተራቸው የሚያውቁትን መረጃ ከሰጡ በኋላ ሌሎች የተሻለ ዕውቀት አላቸው የሚሏቸው ሰዎችንና ሰነዶችን እንዲጠቁሙ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። በዚህ መሰረት አጥኚው መረጃ አቀባዮች ይገኙበታል ከተባለ ወረዳ፣ ጣቢያና መንደር ወደሌለው በመሸጋገር የትግራይ ህዝብ መታወቂያ የሆኑት ተረቶች፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ እንቆቅልሾችና ሌሎች የስነቃል ሃብቶች በተለይ የህብረተሰቡን ዕውቀት ከማስተማር አኳያ ድርሻቸው ምን እንደሆነ፤ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉት ምንባቦች የተጋሩን አበእ ማስተማር ስለመቻላቸው ለማየት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃ ተሰብስቧል። ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ናሙና የሚባለውም ይህንን ስልት የሚከተል የንሞና ዘዴ ነው (Cohen, et al. 2007; Patton, 2002; Mack et al. 2005)፡፡

ሰንሰለታዊ ጥቆምታ የንሞና ዘዴ፤ በግምት የሚመራ ሳይሆን አጥኚው፡ በቅድሚያ ከማን ጋር ብገናኝ ነው በአይነትም በመጠንም ተገቢ መረጃ አቀባዮችን ማግኘት የምችለው ብሎ አቅዶ የሚገባበት ነው፡፡ እነዚህ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፤ በእድሜም በልምድም የበሰሉ መረጃ አቀባዮችን የትና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል የሚጠቁሙ አጋዥ ሰዎች ሆነው ተገኝተዋል። ከማህበረሰቡ ጋር ባላቸው የጠበቀ ግንኙነት ተገቢ ሰዎችን የሚያውቁ መሆናቸው በተግባር ታይቷል። አስቀድሞ ማቀድና ጥቂትም ቢሆኑ ተገቢ ቀዳሚ መረጃ አቀባይ ሰዎችን መምረጥ አስፈላጊ የሆነውም የቀጣዮቹ መረጃ አቀባዮች አይነትንም ስለሚወስን ነው።

ሰንሰለታዊ ጥቆምታ የንሞና ዘዴ እንደአመቺነቱ ስራ ላይ የሚውሉ ሶስት ንኡሳን የናሙና አወሳሰድ ክፍሎች አሉት (Castillo, 2009)። አንደኛው መስመራዊ ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ንሞና (linear) በመባል ይታወቃል። አንዱ መረጃ አቀባይ ሌላ አንድ መረጃ አቀባይ ብቻ የሚጠቁምበት ስልት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ብዜታዊ ኢ-አግላይ ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ንሞና (Exponential non Discriminative) ይባላል። አንድ ሰው ሁለት ሰዎችን ይጠቁማል። ሁለቱ ሰዎች ደግሞ በተራቸው ጥንድ ጥንድ ሰዎችን፣ ... እየጠቆሙ ቁጥሮቹን በእጥፍ የሚያሳድጉበት ስልት ሲሆን ሁሉም ተጠቋሚዎች በመረጃ አቀባይነት የሚያገለግሉበት አይነት ነው፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ብዜታዊ አግላይ ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ንሞና (exponential Discriminative) የሚባለው ሲሆን ከአንዱ መረጃ አቀባይ ወደ ሌሎች መረጃ አቀባዮች የሚሸጋገር ቢሆንም ጠቃሚ የሆኑና ያልሆኑ በማለት የሚያገላቸውና የሚያካትታቸው መረጃ አቀባዮች ስላሉት ከኢአግላይ ይለያል፡፡
በዚህ ጥናት በስራ ላይ የዋለው፤ ሶስተኛው ብዜታዊ አግላይ ሰንሰለታዊ ጥቆምታ የሚባለው ነው። ይህ የተመረጠበት ምክንያትም ከተጠቆሙት ሁሉ ቃለመጠይቅ ማካሄድ አስፈላጊ ላይሆን ስለሚችል ነው። በመጀመሪያ፣ በሁለተኛ ወይም በሶስተኛ ደረጃ የሚገኙት መረጃ አቀባዮች በርካታ ሰዎችን ሊጠቁሙ ይችላሉ። ሁሉም ተጠቋሚዎች ግን ስለ አገር በቀል እውቀት እኩል ግንዛቤ ላይኖራቸው ይችላል። አንዳንዶቹም በስህተት ሊጠቆሙ ይችላሉ። ስለሆነም ተጠቋሚዎቹን ስለመጡበት ሁኔታ በማነጋገር፣ ግንዛቤአቸውን በመገምገም ጠቃሚ የሆኑትን ብቻ በመለየት የማያስፈልጉትን ወይም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን ሰዎች ከቃለ መጠይቁ ማግለል (purposeful inclusion and exclusion of members) ያስፈልጋል። ጥናቱ ብዜታዊ አግላይ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን

የተከተለበት ምክንያትም ወሳኝ የሆኑ መረጃ አቀባዮችን ብቻ ለመምረጥ ስለሚያመች ነው።

መረጃ የተሰበሰበው ደቡብ፣ ምስራቅና ማእከላዊ በመባል ከሚታወቁ የትግራይ ዞኖች ነው። ዞኖቹ በህዝብ ብዛትም በቆዳ ስፋትም ትላልቅ ቢሆኑም የተመረጡት ግን ክልሉን ይወክላሉ በሚል ሃሳብ አይደለም። ዞኖቹ የተመረጡት በይሁንኝ የንሞና ዘዴ ሆኖ በሶስቱም ዞኖች ያሉ ህዝቦች የተለያየ የቋንቋ ዘየ ስለሚገለገሉ፣ በዞኖቹ መሃል የነበረው ግንኙነት በመገናኛ መሳሪያወች እጥረት ምክንያት ፈጣን ስላልነበረ ምናልባትም የቋንቋ ዘየው ልዩነት የአበእ ልዩነት ይኖረው እንደሆነ ለማየት ስለሚያስችል ነው። ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩና ሰፊ አከባቢዎችን መዳሰሱ ሰፊ ሃሳብና አተያይ ለማግኘትም ስለሚያግዝና እያንዳንዱ ዞን የኔ በሚላቸው እውቀቶች ውስጥ ከሌሎቹ ጋር የሚመሳሰሉ ወይም የሚለዩ  እውቀቶች መኖር አለመኖራቸው ለማየትም ስለሚያስችል ነው። በዚህ ዘዴ ከማህበረሰቡ አባላት በተገኘው መረጃ መሰረት በስርዓተትምህርቱ ላይ የይዘት ትንተና ተካሂዷል። ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ለሚገኙ ህፃናት የተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች፣ የተማሪ መፃህፍትና የመምህር መምሪያዎች፣ የማህበረሰቡን እውቀት ማስተማር የሚችሉ ይዘቶች መያዝ አለመያዛቸው ለማረጋገጥ ፍተሻ ተካሂዷል።

በማህበራዊ ሳይንስ ጥናት ውስጥ በአንድ ብቸኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተደግፎ ውጤት ላይ መድረስ አስቸጋሪ ይሆናል። ውጤት ላይ ቢደረስም እንኳ የተለያዩ ችግሮችን ያልፈተሸ፣ ለብዙ ጥያቄዎች የተጋለጠ፣ ደካማ (vulnerable) ማስረጃ የሚያጥረው ውጤት ሊሆን ይችላል (Cohen, et al. 2007)። ይህ ጥናት የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ በመሆኑና ተጠኚዎቹም ሰዎች በመሆናቸው፤ የሰው ልጅ ደግሞ በተፈጥሮው ውስብስብ ስለሆነ በሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ ማመሳከር (Triangulation) አስፈልጓል። እነሱም ቃለመጠይቅና የቡድን ውይይት (FGD) ናቸው። በነዚህ መሳሪያዎች አማካይነት በተገኙት መረጃዎች መለኪያነት  በስርዓተትምህርቶቹ ውስጥ በቀረቡት ምንባቦችና ዓላማዎች ላይ የይዘት ትንተና ተካሂዷል።

ምንባቦች አገር በቀል እውቀትን ማስተማር ስለመቻላቸውና በየትኛው ዓምድ ውስጥ መመደብ እንዳለባቸው ለመወሰን ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል። በአራቱ የትምህርት ዓምዶች ስር የቀረቡት ይዘቶች በህብረተሰቡ ቃላዊ ሃብትም ሆነ በሌላ ዘዴ ቀርበው የማህበረሰቡን እውቀት (አበእ) ለማጉላት የቻሉት ምን ያህሉ ናቸው? የሚለውን

ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ ኣገር በቀል ኣቀራረብ ኣላቸው፤ ኣገር በቀል እውቀትንም ያንፀባርቃሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ምንባቦች ለይቻለሁ። በመቀጠልም ኣበእን ኣያንፀባርቁም ካልኳቸው ምንባቦች ጋር በማቀላቀል ባለሙያዎች ኣስተያየት እንዲሰጡባቸው ኣድጌኣለሁ። ይኸውም ከ2ኛ ክፍል መማሪያ መፅሓፍ የመጀመሪያዎቹን 10 ምንባቦች (50%) በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ለሁለት የትግረኛ ቋንቋ መምህራን ሰጥቼ ኣገር በቀል ኣቀራረብና ይዘት ያላቸውን ምንባቦች እንዲለዩልኝ ኣድርጌኣለሁ።

መምህራኑ በምንባቦቹ ዝርዝር ፊት ለፊት የ '√' ምልክት በማድረግ እንዲፈርጁ ተደርጓል። በዚህ መሰረት ከተሰጧቸው ምንባቦች ውስጥ ኣገር በቀል እውቀትን ማስተማር ዓላማቸው ያረጉ የሚመስሉ ኣራት ምንባቦች እንዳሉ ኣመልክተዋል። እኔ ካቀረብኩት መጠን (3) ጋር ሲነፃፀርም ተቀራራቢነት ኣለው። እኔ ከኣስሩ ምንባቦች ሰባቱ ኣበእ ኣቀራረብ የላቸውም ብዬ ኣምናለሁ። መምህራኑ ደግሞ ስድስቱ ምንባቦች ኣበእ ኣቀራረብ እንደሌላቸው ኣመልክተዋል። የሚታየው ልዩነት 1 በመሆኑና ከፍተኛ ስምምነት ስለተገኘ ኣጥኚው፣ ውሳኔው ኣስተማማኝ ነው ብሎ ተቀብሎታል። እንዲሁም ምንባቦቹ ከየትኛው የትምህርት ዓምድ እንደሚመደቡ እንዲያመለክቱ ተጠይቀው ምደባው ኣጥኚው ከሰራው ምደባ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስለተገኘ ባለበት ሁኔታ ቀጥሏል።

## 3.4. *መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች*

በዚህ ጥናት ውስጥ የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ የመሳሪያዎቹ ዓይነትና የተመረጡበት ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.4.1. *ቃለመጠይቅ*

ኣንድ ተመራማሪ የሚያጠናበትን ርእስ ከለየ በኋላ ቀጣይና ዋና ዋና ከሚባሉት ተግባራቱ ኣንዱ፣ ከሚጠናው ጉዳይ ጋር የሚስማማ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መምረጥ ነው። የጥናቱን ውጤታማነት ከሚያመለክቱ ነገሮች ኣንዱም የመሳሪያው ተገቢነት ነው (ያለው 2001 ዓ.ም.)። ቃለመጠይቅ በዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢ መሳሪያ ነው (Cohen et al, 2000)። በሰዎች ኣእመሮ ውስጥ ያለን ጉዳይ ለማውጣት ያስችላል። የተጠያቂዎቹን እውቀት፣ የሚወዱትንና የሚጠሉትን ነገር (እሴቶችና ምርጫዎች) ዝንባሌዎቻቸውንና እምነታቸውን ፈልፍሎ ለማውጣት የተመቸ ነው። ቃለመጠይቅን ተመራጭ የሚያደርጉት ሌሎች ምክንያቶችም ኣሉ (Cohen et al, 2000; Marczyk, et

al. 2005)። አንደኛው ጥናቱ ሰባዊ በመሆኑ፤ ተመራማሪው ከመረጃ አቀባዮች ጋር በወረቀት ሳይሆን በአካል ተገናኝቶ ሃሳብ እንዲለዋወጥ ስለሚያስችለው ነው። ጠያቂውና ተጠያቂው በስሜትም እየተደማመጡ የሚያካሂዱት ውይይት ስለሆነ አንዱ የሌላውን ስሜት ለመረዳትና ለመጠበቅ ያስችላቸዋል። በመስክ ተገኝቶ በተለያዩ ደረጃዎች ከሚገኙ የህብረተሰብ አባላት ጋር አገር በቀል እውቀትን የተመለከተ በአይነትም በመጠንም ሰፊ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያመች መሳሪያ መሆኑ ሌላው ተፈላጊ የሚያደርገው ነጥብ ነው።

እነዚህን ጠቀሜታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለዚህ ጥናት በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት መረጃ መሰብሰብ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ተወልዶ ያደገና እዚያው የኖረ ሰው ሁሉ ባህሉን በተመለከተ አጭር ገለፃ ሊሰጥ ይችል ይሆናል። ከዚህ አልፎ ሁሉም አባል የማህበረሰቡን አጠቃላይ ባህል ምንነት፣ ዝርዝር አፈፃፀም፣ አገልግሎት፣ ሚስጥራዊ አገላለፆች ሁሉ ማወቅ አይችልም (Pai, 1990)። የዚህ ጥናት አቅራቢም ምንም እንኳን በማህበረሰቡ ውስጥ ተወልጄ ያደግኩ ብሆንም በተወለድኩበት መንደር ያለን የህብረተሰቡ አገር በቀል እውቀት ለመግለፅ እንኳ ይከብደኛል። ስለሆነም ነው በማህበረሰቡ መሃል ተገኝቶ ከተለያዩ ሰዎች መረጃ መሰብሰብና ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት መገልገል ያስፈለገው።

በተለያዩ የምርምር ስራዎች ውስጥ በተግባር ላይ የሚውሉ ሶስት ዋና ዋና የቃለመጠይቅ አይነቶች:- **የተዋቀረ ፣ ያልተዋቀረና ከፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ** በመባል ይታወቃሉ (Dornyei, 2007; Patton, 2002)፡፡ በዚህ ጥናት በተለይ ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ከፊል የተዋቀረ (The General Interview Guide Approach or Semi- Structured) የሚባለው ስራ ላይ ውሏል፡፡ ከፊል የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ በተዋቀረና ባልተዋቀረ ቃለመጠይቆች መሃል የሚገኝ ነው፡፡ መረጃ አቀባይ የሆኑት ሰዎች በተነሳው ጉዳይ ላይ ልቅ በሆነ መልክ ሃሳብ እንዲሰጡ ስለማያበረታታ ካልተዋቀረ መጠይቅ ይለያል፡፡ ተሳታፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ ጠለቅ ያለ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ ደግሞ እንዲናገሩ እድል ይሰጣል። መቅረት የለባቸውም የሚሏቸው መረጃዎችን እንዲያካትቱ ስለሚፈቅድም ከተዋቀረ ቃለ መጠይቅ ይለያል፡፡ እንደ ተጠያቂዎቹ ሁኔታና የተገኙበት አውድ ጥያቄዎችን በመለዋወጥና በማቀዳደም ለማቅረብም ምቹ ሆኖ ተገኝቷል።

ክፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ በተለይ በተግባራዊ ስነ ልሳን ላይ ለሚካሄድና ከመስክ ለማሰበሰብ መረጃ ተስማሚ በመሆኑ ተመርጧል፡፡ ጥያቄዎቹ ለውይይትና ለጥያቄና መልስ በሚያመች መንገድ ተደራጅተዋል። የተጠያቂዎች ምላሽ በመቅረፀ ድምፅና በመስክ ኣጭር ማስታወሻ ተመዝግቧል።

በሰንሰለታዊ ጥቆምታ የንሞና ዘዴ በቃለ መጠይቁ የሚሳተፉ ሰዎች ከየትኞቹ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሚመረጡና እንዴት ያሉ ሰዎች እንደሆኑ (የሃይማኖት ኣባቶች፣ የእድሜ ባለፀጎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ገበሬዎች፣ ወዘተ.) ከያንዳንዱ ክፍል ምን ያህል ሰው እንደሚሳተፍ ኣስቀድሞ መወሰን ኣልተቻለም። ምክንያቱም የተጠያቂዎችን ዓይነትና ቁጥር የሚወሰነው በየደረጃው የሚገኙት መረጃ ኣቀባዮች በሚሰጡት ጥቆማ ስለሆነ ነው። ወደ ተግባር ሲገባ የታየውም የመረጃ ኣቀባዮች ቁጥር ኣስቀድሞ መገመት የማይቻል መሆኑ ነው። ኣንዳንድ ኣካባቢዎች በቂ መረጃ ኣቀባዮች እንደሚገኙበት ይጠቆማል። ከቦታው ሲደረስ ግን የተጠቆሙት ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች (በህመም፣ በኣካባቢው ባለመገኘት፣ ስለጉዳዩ የሚያውቁት ነገር ባለመኖሩ) ባዶ እጅ መመለስ ኣጋጥሟል። በኣንዳንድ ኣካባቢዎች ደግሞ ከታሰበው ቁጥር በላይ መረጃ ኣቀባዮችን ማግኘት ተችሏል። ኣገር በቀል እውቀት፣ ብዙ ዘመን ያስቆጠረና ቃላዊ እውቀት በመሆኑ በየዘመኑ የመጥፋት፣ የመረሳት፣ በኣዲስ የመተካት፣ ኣደጋ ሊያጋጥመው ይችላል። በቃለመጠይቅ የተሳተፉት ሰዎችም ሁሉንም ነገር እያስታወሱ መናገር ችለዋል ብሎ መደምደም ይከብዳል። ለቃለመጠይቅ የሚጠቆሙት ሰዎች ወጣቶች ከሆኑ ደግሞ በእድሜኣቸው ያልነበሩበትና ያልደረሱበት ስለሚበዛ የመረጃ ኣቀባዮች ዕድሜ 60 ዓመትና ከዚያ በላይ እንዲሆን ኣጥኚው ወስኗል።

በክልሉ የስርኣተትምህርት መምሪያ የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ዝግጅት ሃላፊ ኣማራጭ ኣልቦ በሆነው የወሳኝ (nonprobability) የንሞና ዘዴን (Marczyk, 2005; ያለው፣ 1998 ዓ.ም.) በመጠቀም በቃለመጠይቅ መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል። ከኣንደኛ ደረጃ የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ባለሙያው ጋር የተደረገው ቃለምልልስ የመማሪያ መፃህፍትን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ኣገር በቀል እውቀትን ከግንዛቤ ውስጥ ኣስገብተው የሚፅፉ ስለመሆናቸውና የሚኖራቸው ነፃነት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እገዛ ኣድርጓል።

ከዚህም ሌላ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ መምህራን፣ መማሪያ መፃህፍቱና የመምህር መምሪያዎቹ አገር በቀል እውቀትን ከማስተማር አኳያ ምን አስተዋፅኦ እያበረከቱ እንደሆነ ለማወቅ በቃለመጠይቁ እንዲሳተፉ ተደርጓል። መምህራን የተመረጡት በአመቺ (Convenience) የንሞና ዘዴ ነው (ያለው፣ 1998 ዓ.ም.)። አጥኚው ከእድሜ ባለፀጎች ጋር ቃለምልልስ ለማካሄድ በተሰማራሁባቸው ወረዳዎችና የገጠር ቀበሌዎች ባሉ ትምህርት ቤቶች ከተገኙ የትግርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ቃለምልልስ ለማካሄድ አቅጄ ነበር። ሆኖም ከየዞኑ የተውጣጡ መምህራን በዓብዪ ዓዲ እና በውቅሮ ከተማ ስለተገኙ ቃለመጠይቁ እሁለቱ ቦታዎች ብቻ ተካሂዷል፡፡ በአጠቃላይ በአንድ የቡድን ውይይት ስምንት፣ በቃለመጠይቅ ደግሞ አስራ ሁለት መምህራን ተሳትፈዋል።

በሁሉም የመረጃ ስብሰባ ሂደት ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለው ዘመናዊ /Digital/ መቅረፀ ድምፅ ነው። የያንዳንዱ ተሳታፊ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ የተቀረፀ ሲሆን ቃለጉባኤ መያዝ ያስፈለገው በኮምፒውተር መበላሸት ወይም በተሃዋሲያን የመጠቃት አደጋ ስጋትን ለመቀነስ ሲባል ነው። ከቃለመጠይቆችና ከተኮር የቡድን ውይይት የተገኙት መረጃዎች ወደ ፅሑፍ የተቀየሩት በሙያው በሰለጠነች ፀሓፊ ሲሆን የፈጠነው በ48፣ እጅግ የዘገየው ደግሞ በየ84 ሰዓታት ልዩነት ወደ ፅሑፍ ተቀይሯል። ወደ አማርኛ የተተረጐመው ግን ከመስክ መልስ ነው። ከድምፅ ወደ ፅሑፍ የማሻገርና ወደጥናት ቋንቋ የሙተርጎም ስራ የሚካሄድበት ጊዜ ባጠረ ቁጥር፣ በንግግር ወቅት የነበረ ስሜት ሃሳብ፣ በአህፅሮት የተቀመጠ ሃሳብ ሳይረሳና ሳይጓደል የመመዝገብ እድል እንደሚያሰፋ ቢታወቅም (Mack et al, 2005) ከነበረው የቦታ ርቀት የተነሳ ከዚህ ባጠረ ጊዜ መፃፍ አልተቻለም።

ይህ ጥናት የተካሄደው በትግራይ ክልል እንደመሆኑ በመረጃ አቀባይነት ላገለገሉት ሰዎች የቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉም በትግርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ናቸው። ውይይቱም ሆነ ቃለመጠይቁም የተካሄደው በትግርኛ ነው። ጥናቱ የቀረበው ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ነው። ስለሆነም በቃለመጠይቅም ሆነ በተኮር የቡድን ውይይት የተኙት መረጃዎች በሙሉ ከድምፃዊ ወደ ፅሑፋዊ ተቀይረዋል፡፡ ቀጥሎ ከመገኛ ቋንቋ ወደ የጥናት ቋንቋ ተተርጉመዋል፡፡ እነዚህ ከድምፅ ወደፅሑፍ የመለወጥ የመተርጎም ስራ በቋንቋው አፍ በፈቱና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች መካሄድ ነበረበት፡፡ ሆኖም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የፈቀደው በጀት ባለሙያዎችን ቀጥሮ ለማሰራት ይቅርና የመጀመሪያውን የሙከራ ጥናት ለማካሄድ እንኳ በቂ ሆኖ ስላልተገኘ የትርጉም ስራውም በራስ ማካሄድ የግድ ሆኗል፡፡

### 3.4.2. የተኮር የቡድን ውይይት ምንነትና አስፈላጊነት

ተኮር የቡድን ውይይት (FGD)፤ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ተገኝተው ስለአንድ ጉዳይ የሚወያዩ ሰዎች ስብስብ ነው (Cohen, et al. 2007; Dornyei, 2007; Marczyk, 2005; ያለው፣ 2001 ዓ.ም.)። በተለይ በማህበራዊ ሳይንስ ምርምር፡ የተለመደና ከተለያዩ አካባቢዎች የተገኙ እና የተለያዩ ልምዶች ያሏቸውን ሰዎች በማወያየት የነጠረ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል በመሆኑ በዚህ ጥናት በመሳሪያነት አገልግሏል።

ከአንድ ወገን፣ በአንድ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተገኘን መረጃ ፣ በሌላ ወገንና በተለየ መሳሪያ በመሞከር መረጃን ማጠናከር የተለመደ የምርምር አካሄድ ነው። በዚህ ጥናትም በተናጠላዊ ቃለምልልስ የተገኘውን መረጃ፤ ተኮር የቡድን ውይይት በማደራጀትና ለቃለመጠይቅ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በማቅረብ መረጃዎቹን ለማጠናከር በመሳሪያነት አገልግሏል። የቡድን ውይይት የተካሄደው፤ በህብረተሰቡ ውስጥ አገር በቀል እውቀትን የተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው ከታመነባቸው የዕድሜ ባለፀጋዎችና ከ1ኛ -4ኛ ክፍል ትግርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ነው። ከእድሜ ባለፀጋዎች ጋር የተደረገው ውይይት ዓላማ፤ ተጋሩ የኛ ናቸው የሚሏቸው አገር በቀል እውቀቶች ምን ምን እንደሆኑ ለይቶ ማወቅና በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ጋር በማነፃፀርና በማወዳደር ምልአት ቀርነታቸውን መገምገም ነው፡፡

ውይይቱ የተካሄደው ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ትግርኛ ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ነው። ዓላማው፣ ከላይ ለተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶችና መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአገር በቀል እውቀት ስለመካተቱ፣ ተካትቶ ከሆነም የማህበረሰቡን እውቀት ወደ ህፃናቱ ማስተላለፍ በሚያስችል መልኩ ስለመቅረቡ መረጃ ማግኘት ነው። ለተመረጡት የእድሜ ባለፀጋዎችና መምህራን የመወያያ ጥያቄዎች በማቅረብና በማወያየት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ውይይቱ በትኩረት ቃኚ (focused interview) ስርአት ነው የተመራው። ይህ አመራር ተወያዮች ከርእስ ውጪ በሆኑ ነጥቦች ላይ እንዳያተኩሩ መቆጣጠር የሚያስችል በመሆኑ ተመርጧል (Cohen, et al. 2007)።

**ተኮር የቡድን ውይይቱ የተመራበት ሂደት፡-** በቅድሚያ ስለአጥኚውና ስለጥናቱ ዓላማ ከተገለፀ በኋላ በዚህ ውይይት ለመሳተፍ ፈቃደኛነታቸው ተጠይቆ ሙሉ ፈቃድ ስላሳዩ ወደውይይት ተገብቷል። ለሁሉም ተሳታፊዎች የተነበበው የስምምነት መግለጫም በአባሪነት ተያይዞ ይገኛል። የውይይቱ አመራር ለአመቺነት ሲባል በአቀማመጥ ቅደም ተከተል ተራ ጠብቀው በውይይቱ እንደሚሳተፉና የተለየ ሃሳብ ከሌላቸው ተራውን ሊያሳልፉት እነደሚችሉ፤ የተለየ ሃሳብ ሲኖር ደግሞ ተራ ጠብቀው ሃሳብ መስጠት እንደሚችሉ ስምምነት ላይ ተደርሷል። በመጨረሻም ስለአሰራሩ ማንሳት የሚፈልጉት ጥያቄ አለመኖሩ በማረጋገጥ ወደውይይት ተገብቷል።

ከዚህ የቡድን ውይይት፣ ከአንድ ለአንድ ቃለ መጠይቅ የማይገኙ ሶስት ጠቀሜታዎች (Dornyei, 2007) ተገኝተዋል ። ጠቀሜታዎቹ፤ አንደኛ፡- በአንድ ጊዜ በርካታ ሰዎችን ስለሚያሳትፍ ጊዜ መቆጠብ መቻሉ ነው። ሁለተኛ፡- ውይይቱ የተካሄደው በተወያዮቹ መሃል በመሆኑና የአወያዩ ሚና አቅጣጫን ከማስያዝ ያልዘለለ ስለነበረ በነፃነት በመወያየት ሃሳብ እንዲያመነጩ ማገዙና ሶስተኛ፡- የተለያየ ልምድና አመለካከት ካላቸው ተወያዮች ተጨምቆና ነጥሮ የወጣ ሃሳብ ማስገኘቱ ናቸው።

### 3.4.3. የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ

**የዕድሜ ባለፀጋዎች አመራረጥ ሁኔታ፡-** በቃለመጠይቅ መረጃ በመስጠት የተሳተፉ የዕድሜ ባለፀጋዎች 49 ሲሆኑ አራቱ ሴቶች ናቸው። 20ዎቹ ከደቡባዊ ዞን፣ ራያ ዓዘቦ፣ እንዳምኾኒ፣ ገጠር ኣላማጣና ኣላማጣ ከተማ ከሚባሉት ወረዳዎችና በስራቸው ከሚገኙ ንኡሳን ጣቢያዎችና ከተማዎች የተገኙ ናቸው፡፡12ቱ ምስራቃዊ ዞን ውስጥ ከዓዲግራት፣ ውቕሮ፡ሓውዜን፡ ክልት ኣውላዕሎ፣ ኣፅቢ ወምበርታና ጉሎምኻዳ ወረዳዎች የተገኙ ናቸው። 17ቱ ደግሞ ከማእከላዊ ዞን፤ ወርዒ ለኸ፣ ቆላ ተምቤን፣ ናዕዴር ዓዴት፣ ውቕሮማራይና ኣሕፈሮም ወረዳዎች የተገኙ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ በቡድን ውይይት የተሳተፉ ሰዎች በድምሩ 27 ናቸው፡፡ ቡድን አንድ፡- ከራያ ዓዘቦ ወረዳ፣ ቡድን ሁለት፡- ከታሕታይ ምጋሪያ ፀምሪ፣ ሶስተኛው ከእምባስነይቲ ንኡስ ወረዳ ጣቢያ ማይነብሪ የተገኙ ሲሆን እያንዳንዳቸው ሰባት አባላት የያዙ ናቸው። አራተኛው ደግሞ ከቆላ ተምቤን ወረዳ ሆኖ ስድስት አባላት የያዘ ነው፡፡

ዓውድ፣ የአይነታዊ ምርምር ዋነኛው የመረጃ ምንጭ በመሆኑ ተሳታፊዎቹ ከኖሩበት አካባቢ ሊንቀሳቀሱ አይገባም (Creswell, 2009)፡፡ ሁሉም የዕድሜ ባለፀጋዎች ቃለመጠይቆች የተካሄዱት ተሳታፊዎቹ በሚኖሩበት መንደርና አካባቢ ነው። የተከተልኩት የምልመላ ዘዴ አጋጣሚያዊ ያልሆነ ወይም የይሁንኝ (Purposive) ንሞና ዘዴ ንኡስ ክፍል የሆነው ሰንሰለታዊ ጥቆምታ ነው። የአፈፃፀም ሂደቱም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በቅድሚያ የክልሉን የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማነጋገር የየዞኑን የቢሮው ተወካዮች ዝርዝር ለማግኘት ችያለሁ። የየዞኑ ተወካዮችም ከየወረዳዎች ተጠሪዎች ጋር በማገናኘት ተባብረውኛል። በሶስቱ ዞኖች ካሉ ወረዳዎቸ ውስጥ የተሻለ መረጃ ሊገኝባቸው የሚችሉትን ቦታዎች እንዲጠቆሙ ተደርጓል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሻለ እውቀት አላቸው የሚሏቸውን መረጃ አቀባዮች እንዲጠቁሙ በማድረግና ለቃለመጠይቅ እንዲተባበሩ በመጠየቅ መረጃ ተሰብስቧል (Creswell, 2009)። የሁሉም ወረዳዎች የባህልና ቱሪዝም ተወካዮችን በማነጋገር የህብረተሰቡን ባህል ያውቃሉ የሚሏቸውን የዕድሜ ባለፀጋ ሰዎች ዝርዝር እንዲሰጡ በመጠየቅ መረጃ አቀባዮችን መለየት ተችሏል። በተለይ በገጠር አላማጣ ወረዳ አጥኚው፣ በአካባቢው ታዋቂነት ካላቸው ሽማግሌዎች ጋር በመወያየት ስለተጠቆሙት ሰዎች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ችሏል።

ሁሉም መረጃ አቀባዮች በቃለመጠይቁ ለመሳተፍ ፈቃደኝነታቸው ከገለፁ በኋላ ወደ ዋናው ጥያቄና መልስ ከማስገባት በፊት ራስንና የጥናት ዓላማን የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል። ምልልሶቹን በመቅረፀ ድምፅ ለመቅዳት ፈቃደኛነታቸው ተጠይቋል። በተለይ በተኮር የቡድን ውይይት ጊዜ ተሳታፊዎች በየመሃሉ ግልፅ ያልሆኑላቸው ጥያቄዎች ሲያጋጥሙና ከርእስ የወጡ ሲመስል ብቻ ጣልቃ በመግባት መሪ ያልሆኑ ማብራሪያዎች የመስጠት ስራ ተካሂዷል።

- **በተኰር የቡድን ውይይት እና በቃለመጠይቅ የተሳተፉ መምህራን አመራረጥ**

***መምህራን የመጡባቸው አካባቢዎች፡-***ሰልጣኞቹ፣ መረጃ ይወሰድባቸዋል ከተባሉት (ከደቡብ፣ ከምስራቅና ከማእከላዊ) ዞኖች ብቻ ሳይሆን ከመላ ትግራይ የመጡ ናቸው። ሶስቱ ዞኖች በናሙናነት የተመረጡት ጊዜንና ገንዘብን ለመቆጠብ ነበር። መምህራኑ ግን ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በሚፈታ መንገድ በአንድ ማእከል ስለተገኙ እንዲሳተፉ ተደርጓል። ሁሉም ተሳታፊ መምህራን በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የሚገኙ ህፃናትን ለማስተማር በሰርቲፊኬት የተመረቁና በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ (ከ1-4)

የትግርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ በመሆናቸው (homogeneous Sample- Patton, 2000)፣ ከሌሎች ዞኖች የመጡትን ማሳተፉ በጥናቱ ላይ የሚፈጥረው ተፅእኖ እንደሌለ በማመን በውይይቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

**ተኮር የቡድን ውይይት፡-** በውይይቱ የተሳተፉት መምህራን የተለያየ የአገልግሎት ዘመንና ፆታ ያላቸው ናቸው። በመካከላቸው የሙያ አንድነት እንጂ የአዛዥና ታዛዥ ግንኙነት እንደሌለም (Marczyk, 2005) ተረጋግጧል። የዚህ አይነቱ ስብጥር መኖር አንድ ወይም ጥቂት ሰዎች በብዙሃን ድምፅ ላይ ተፅእኖ እንዳያሳርፉ፣ እነሱ ብቻ ተናጋሪ እንዳይሆኑ ይከላከላል። የበላይና የበታች፣ የቀጣሪና ተቀጣሪ፣ የጌታና የሎሌ አይነት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ከሆኑ ግን 'ከአንድ የውይይት መድረክ የብዙ ሰዎች አስተያየት ማግኘት' የሚለውን አላማ ሊያዛባ ይችላል። በዚህ ጥናትም ከላይ የተጠቀሱትን ተኮር የቡድን ውይይት መሰረተ ሃሳቦች የተከተለና 3 ሴትና 5 ወንድ በድምሩ ስምንት መምህራን የያዘ የቡድን ውይይት ተካሂዷል።

**የአመራረጥ ሁኔታ፡-** በዓብዪ ዓዲ መምህራን ኮሌጅ በክረምት መርሃግብር ደረጃቸውን ወደ ዲፕሎማ ለማሳደግ ከሚማሩ የሶስተኛ ክረምት ተማሪ መምህራን፣ ስምንት ሴክሽኖች ውስጥ በይሁንኝ (purposive) የንሞና ዘዴ የክፍል ተወካዮች ብቻ ተወስደዋል። ስምንቱ ሰልጣኝ መምህራን ቀደም ሲል ክፍሉን እንዲወክሉ በየክፍሉ አባላት ተመርጠው የቆዩ ናቸው፡፡ ከየክፍሉ አንድ ሰው፣ በድምሩ ከስምንቱ ሴክሽኖች በእጣ ስምንት ሰዎችን ለመውሰድ ታስቦ ነበር፡፡ ሆኖም ቀደምሲል የተመረጡትን መውሰዱ በጥናቱ ላይ ለውጥ የማያመጣ ከመሆኑም በላይ የሰልጣኞቹንም ሆነ የአጥኚውን ጊዜና ጉልበት ስለሚቆጥብ ቀደም ሲል በክፍል ተወካይነት የተመረጡት መምህራን በውይይቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡
ከላይ እንደተመለከተው በቃለመጠይቅ የተሳተፉት መምህራን 12 ናቸው፡፡ ስምንቱ ዓብዪ ዓዲ መምህራን ኮሌጅ፣ አራቱ ደግሞ ውቅሮ መሰናዶ ትምህርት ቤት ይሰለጥኑ የነበሩ የ3ኛ ዓመት የክረምት (ዲፕሎማ) ተማሪዎች ናቸው፡፡ አመራረጣቸውም፡- የእጣ ናሙና ዘዴ የተከተለ ነው፡፡ ይኸውም በዓብዪ ዓዲ መምህራን ኮሌጅና በውቅሮ መሰናዶ ትምህርት ቤት ከነበሩት 12 ሴክሽኖች ለያንዳንዱ ሴክሽን ዜሮ እና አንድ ቁጥር የተፃፈባቸው እጣዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ ከክፍሉ አንድ ቁጥር የደረሰው ሰው ብቻ ለቃለመጠይቅ ይመረጣል፡፡ በዚህ የምልመላ ዘዴ ከዓብዪ ዓዲ፣ 8፣ ከውቅሮ ደግሞ 4፣ በድምሩ 12 መምህራን ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 4ቱ ሴቶች ሲሆኑ 8ቱ ወንዶች ናቸው፡፡

➢ **የስርዓተትምህርት ባለሙያ አመራረጥ፡-**

ከ1ኛ -8ኛ ክፍል ያሉት የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርቶች የሚዘጋጁት በአንድ ባለሙያ አማካይነት ነው። ስለሆነም ከተጠቀሱት ባለሙያ ውጪ ሌላ አማራጭ ስለሌለ የወሳኝ የንሞና ዘዴን (Cohen et al, 2007; ያለው፣ 2001 ዓ.ም.) በመጠቀም ብቸኛ ተመራጭ ሆነው ቀርበዋል።

### 3.4.4. ፍተሻና ትንተና የተካሄደባቸው ሰነዶቸ

የይዘት ትንተና፡- በአንድ ፅሁፍ ፣ ንግግር፣ ትረካ በራዲዮ በተላለፈ መልእክት ወይም መፅሃፍ ውስጥ የተተከረበትን ጉዳይ ስልታዊና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለመመርመር የሚካሄድ ፍተሻ ነው። ሂደቱ ሳይንሳዊ ከመሆኑ በቀር ይህ አይነቱ ፍተሻ ሰዎች በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ሲከውኑት ይታያል (Amare, 1998)። በየቀኑ ያዩትን ነገር ሲያደንቁ፣ ሲነቅፉ፣ ስለጣእም፣ ስለሽታ፣ አስተያየት ሲሰጡ ይሰማል። በሳይንሳዊ ምርምር የይዘት ትንተና የሚካሄድባቸው ሰነዶች ፡- ልቦለዶች፣ ተውኔቶች፣ ካርታዎች፣ ስእሎች፣ መፃህፍት፣ የህይወት ታሪኮች፣... ሊሆኑ ይችላሉ (Patton, 2002; May, 1993; Cohen et al. 2007)። በተለይ በፅሁፎቹ ውስጥ የሚገኙት ቃላት፣ አረፍተነገሮች፣ አንቀፆች ምእራፎች ወይም መፅሓፍ ለትንተና በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ ይችላሉ። በዚህ የአገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ ዓላማው ያደረገ ጥናት፤ ከእቅድ ጋር የተያያዙ የፌደራልና የክልል ሰነዶች ተፈትሸዋል፡፡ ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን በመማሪያነት የተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ካሉት 71 ምንባቦች በ44ቱ ምንባቦችና በርካታ መልመጃዎች በአይነት ከተለዩ በኋላ ትንተና ተካሂዶባቸዋል።

ትንተናው የተመራውና ውጤቱ የተገለፀው በአይነታዊ የምርምር ዘዴ (በገለፃ) ቢሆንም መጠንን የሚያመለክቱ ቁጥሮችም ስራ ላይ ውለዋል። ሆኖም ይህ ጥናት በአይነታዊ ምርምር ቢመራ ይበልጥ ተጨባጭነት እንደሚኖረው አጥኚው ያምናል። የነገሮች፣ የሁነቶች፣ ወይም ሌሎች ቁሳዊ ነገሮች መጠነ-ድግግም፣ የቃላትን፣ የሃረጎችንና የአንቀፆችን መጠን ማወቅ የፅሁፉን ጠቀሜታ ሊያስረዳ አይችልም። አይነታዊ የይዘት ትንተና ማካሄድ ግን ጭብጦችን በማብራራት አንባቢንና ደራሲን የሚያገናኝ (የሚያግባባ) ድልድይ መስራት እንደማለት ነው (May, 1993)። ከመማሪያ መፃህፍቱ ተለቅመው ለትንተና

የቀረቡት ምንባቦችም በውስጣቸው የያዟቸው ማህበረሰባዊ እውቀቶችን ሊያሳዩ በሚችል መልክ ተተንትነዋል።

በብዙ ሺሕ ቃላት በተገነባ መፅሃፍ ውስጥ አንዲት ቃል ከብዙዎቹ ጎልታ ብዙ ልታነጋግርና ልታስፅፍ ትችላለች። ስርጭትና ድግግሙን ብቻ ወስዶ መተንተን ግን ፋይዳው ዝቅተኛ ይሆናል (May, 1993)። ይቺ ቃል በፅሁፉ ውስጥ ያላትን ድርሻ (ፍቺ፣ የፅንሰ ሃሳብ ስፋት) የተመለከተ ትንተና ሊካሄድ ይችላል። የይዘት ትንተናው በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ እንዲታይ የተፈለገበት ምክንያትም ይህው ነው።

## 3.5. የመረጃ ምንጮች

ጥናቱ ምን ምን የጥናት ዘዴዎችን እንደተከተለ ቀደም ሲል ተጠቁሟል። የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎችም ተዘርዝረዋል። የመረጃ አቀባዮችና ምንጮች የንሞና ዘዴም ተመልክቷል። ቀጥሎ የሚቀርበው ማብራሪያ ደግሞ የተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለማን እና እንዴት እንደቀረቡ፣ ምን አይነት ጥያቄዎች እንደቀረቡና የትኛውን የጥናት ጥያቄ ለመመለስ እንደሚያስችሉ ያሳያል። ከሰነዶች የተገኙት መረጃዎች የትኛውን የጥናት ጥያቄ መመለስ እንደሚችሉ ለማመልከትም ጥረት ተደርጓል።

"**በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት የአገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ**" በሚል ርእስ የቀረበው ጥናት ዋና ዓላማ በስርዓተትምህርቱ ውስጥ የተጋሩ አገር በቀል እውቀት መካተት አለመካተቱን ማየት ነው። ተካትቷል ወይም አልተካተተም ለማለት የሳይንሳዊ የምርምር ሂደት ተከትሎ ፍተሻውን ማካሄድ አስፈለጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታ ነው። ለዚህ ሲባል የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል። የተለያዩ ሰነዶች ተፈትሸዋል። መጠይቆች ተዘጋጅተዋል። መሰብሰቢያ መሰሪያዎቹን በመጠቀም ከተለያዩ አካላት መረጃዎች ተሰብስበዋል። በነዚህ ስብስብ መረጃዎች አማካይነትም፡-

ሀ. በስርዓት ትምህርቱ ውስጥ፣ አገር በቀል እውቀትን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎች ቀርበዋል?
ለ. ትግራዋይ ህብረተሰብ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች አገር በቀል ናቸው ብሎ ያምናል?

ሐ. ለመለማመጃነት የቀረቡት ተግባራትና ክንውኖች የቀረቡት አገር በቀል እውቀትን ማዳበር በሚያስችል መንገድ ነው?

የሚሉት የጥናት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ማግኘት እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ የጥናት ጥያቄዎቹ ከሚከተሉት ምንጮች ተገቢ መረጃ ይፈልጋሉ፡፡

ሀ. **ከመምህራን**፣ ስርዓተትምህርቱ የተጋሩን አገር በቀል እውቀት ስለማካተቱ የሚገልፅ መረጃ፣ **(የጥናት ጥያቄ ሀ)**

ለ. **ከመምህራን**፣ የምንባቦችና መለማመጃዎች አቀራረብ አገር በቀል እውቀትን ለማዳበር ያላቸው ብቃት የሚገልፅ መረጃ፣ **(ጥ.ጥ. ሐ)**

ሐ. **ከስርዓትትምህርት ባለሙያዎችና ከሰነዶች**፣ የስርዓትትምህርቱ እቅድ አገር በቀል እውቀትን ስለማካተቱና የአቀራረብ ተገቢነቱ **(ጥ.ጥ. ሀ)**

መ. **ከእድሜ ባለፀጋዎች**፣ በስርዓትትምህርቱ ውስጥ ያሉትና አበእን ለማስተማር የቀረቡ የሚመስሉት ምንባቦች (ይዘቶች) አበእ ስለመሆናቸው፣ **(ጥ.ጥ. ለ)**

ከላይ እንደተመለከተው ጥናቱ ከሰነዶች፣ ከቃለመጠይቅና ከተኮር የቡድን ውይይት መረጃዎችን ይወስዳል፡፡ ከሰነድ የሚገኘው መረጃ የቋንቋ ስርዓትትምህርት ሲታቀድ የአበእ ትምህርት አስፈላጊነት ታምኖበት የተካተተ መሆን አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ በቃለመጠቅና በተኮር የቡድን ውይይት የሚሰበሰበው መረጃ ደግሞ አበእ በስርዓትት ምህርቱ ውስጥ ትኩረት ስለማግኘቱና እውቀቱን ለማዳበር የሚያስችል አቀራረብ ያለው ስለመሆኑ የሚጠቁም መረጃ ይሰጣል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በሚቀርበው ሰንጠረዥ፣ በጥናት ጥያቄዎች፣ በመረጃዎች አይነት፣ መረጃዎቹ ትኩረት ባደረጉባቸው የጥናት ጥያቄዎችና በአፈፃፀም ቅደም ተከተላቸው መካከል ያለውን ግንኙነት ደግሞ እንመልከት፡፡

የጥናት ጥያቄ፣ የመረጃ አይነት፣ የትኩረትና የአፈፃፀም ቅደም ተከተል ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ መልክ በጥቅል የቀረበውን ሃሳብ በዝርዝርና እያንዳንዱን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመጠቀም፣ ምን ጥያቄ በማቅረብ፣ ከማን፣ ምንዓይነት መረጃ እንደተሰበሰበ የሚያሳይ ገለፃ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 3 የጥናት ጥያቄ፣ የመረጃ ኣይነት፣ የትኩረትና የኣፈፃፀም ቅደም ተከተል ኣመልካች**

| የጥናት ጥያቄ | የመረጃ ዓይነት | የኣጠቃቀም ቅደም ተከተል | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የሰነድ ፍተሻ | ቃለ መጠይቅ | ተበው. ይይት |
| ጥ.ጥ. ሀ | ኣበእ በእቅድ ስለመያዙና በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ስለመካተቱ | √ | √ | √ |
| ጥ.ጥ. ለ | ስርዓተትምህርቱ ውስጥ ያሉ ይዘቶች ኣበእ ስለመሆናቸው | | √ | √ |
| ጥ.ጥ. ሐ | ኣበእን ለማስተማር በሚችሉበት ስልት ስለመቅረባቸው | √ | √ | √ |

## 3.5.1. የእቅድ ሰነዶችና ስርዓተትምህርቶች

መረጃ የተሰበሰበባቸው ሰነዶች ኣስራ-ስድስት ሲሆኑ እነሱም፡-

- የገንዘብና ኢኮኖሚያዊ ልማት ሚኒስቴር- ገኢልሚ የ5 ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ፣
- Educational Secter Development Plan ESDP IV (2010/11-2014/15)፣
- የትግራይ ክልል የእቅድና ፋይናንስ ቢሮ የእድገትና ሽግግር እቅድ (2003-2007 ዓ.ም.)፣
- የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ የ5 ዓመት የትምህርት እድገትና ሽግግር እቅድ (2003- 2007 ዓ.ም.)
- የ1ኛ ክፍል መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሓፍና የመምህር መምሪያ
- የ2ኛ ክፍል መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሓፍና የመምህር መምሪያ
- የ3ኛ ክፍል መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሓፍና የመምህር መምሪያ እና
- የ4ኛ ክፍል መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሓፍና የመምህር መምሪያ ናቸው፡፡

በፌደራልና በክልል ደረጃ ከተዘጋጁት የመጀመሪያዎቹ ኣራት የእቅድ ሰነዶች ውስጥ ሁለቱ (ESDP IV እና የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ የ5 ዓመት የትምህርት እድገትና ሽግግር እቅድ) ሙሉ በሙለ በትምህርት ላይ ያተኮሩና የኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን

ትምህርትን እንደ አንድ ንኡስ ጉዳይ የሚያነሱ ናቸው። የገኢልሚ የኣምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድና የትግራይ ቢትፋ የእድገትና ሽግግር እቅድ (2003-2007 ዓ.ም.) ደግሞ በሃገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ ትምህርትን እንደ አንድ ንኡስ ጉዳይ የሚያነሱ ናቸው። አራቱ ሰነዶች፣ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርትን ጉዳያቸው አድርገው አቅደዋል፡፡ በእቅዶቹ ውስጥ ኣገር በቀል ቋንቋና ኣገር በቀል እውቀትን በማስመልከት ምን ምን ጉዳዮች እንደተነሱና ለወደፊት ምን እንዳቀዱ ሊጠቁም የሚችል ሃሳብ ካለ መፈተሹ አስፈላጊ እንደሆነ ስለታመነበት በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል።

የአራቱ የክፍል ደረጃዎች የትግርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሓፍና የመምህር መምሪያዎች (ስርዓተትምህርት) ደግሞ ሆን ተብሎ የሚዘጋጁ የመምህርና የተማሪ ዋነኞቹ መሳሪያዎች በመሆናቸው በጥልቀት ተዳስሰዋል። ሶስቱ ለየክፍል ደረጃው የተነደፉት ስርዓተትምህርቶች ኣገር በቀል እውቀትን ወደ ተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍና ጠብቆ ለማቆየት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ናቸው (Grang, 2004; Woube, 2004)። ተቀዳሚ ኣላማቸውም በትምህርት መሳሪያነት የህብረተሰቡን እውቀት (ባህል) ወደቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ (Woube, 2004; Wiessner, 2007) በመሆኑ ይህንን ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት መቻል አለመቻላው ተፈትሿል።

በስርዓተትምህርቱ ላይ የተካሄደው የይዘት ትንተና ገላጭ (descriptive) እና ጠቅላይ (inductive) የተባሉ ዘዴዎችን (Amare, 1998; Patton, 2000) የተከተሉ ናቸው። ጠቅላይ የትንተና ዘዴ፣ በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ውይይት የተሰበሰበ መረጃን ለመተንተን ያገለግላል። ኣካሄዱም ከላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በየደረጃቸው በመተንተን ወደ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና ንድፈሃሳብ ወደማውጣት የሚያድግ ነው (Patton, 2000) ። ከበያኝ (inferential) ወይም ገምጋሚ (evaluative) ይበልጥ ገላጭ የተመረጠበት ምክንያትም በካሪኩለሙ ውስጥ ኣገር በቀል እውቀቶች፣ ኣሉ -የሉም፣ ናቸው - ኣይደሉም ከማለት በላይ ስለያንዳንዱ ነጥብ ማብራሪያና ምክንያት ለመስጠት ስለሚያስችል ነው (Amare, 1998)።

ለአራቱ የክፍል ደረጃዎች/1-4/ በተዘጋጁት የትምህርት መሳሪያዎች ላይ የይዘት ትንተና ለማካሄድ በቅድሚያ መርሃትምህርቱ ምን ለማግኘት ምን ዓይነት ዓላማዎችና ይዘቶች ይዞ እንደተነሳ የማወቅ ፍተሻ ተካሂዷል። በመቀጠል ዓላማዎቹን ለማስፈፀም በመማሪያ

መፅሓፉ የተካተቱት ምንባቦችና መለማመጃ ተግባራት ተለይተዋል። ህፃናቱ ከትምህርት በኋላ ምን ክህሎትና እውቀት እንደሚያዳብሩ የሚያሳዩትና በመምህር መምሪያ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከአገር በቀል እውቀት ጋር ያላቸውን ዝምድና ሊያሳይ በሚችል መልክ በሰንጠረዥ 7፣ 8፣ 9 እና 10 ስር ቀርበዋል።

### 3.5.2. መምህራን

#### 3.5.2.1. በቃለመጠይቅ

ለመምህራን የቀረበው ቃለመጠይቅ ሰባት ጥያቄዎች የያዘ ነው። ጥያቀዎቹ በተለያየ መልክ ቢቀርቡም ዓላማቸው ለጥናት ጥያቄ ሀ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ፣ አገር በቀል እውቀትን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎች ቀርበዋል? እና ሐ. ለመለማመጃነት የተመረጡት ተግባራትና ክንውኖች፣ መልመጃዎች፣ የቡድንና የጋራ የፕሮጀክት ስራዎች አቀራረብ አገር በቀል እውቀትን ማዳበር የሚያስችል ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ማስገኘት ነው። አቀራረባቸው በአምስት የተከፈለ ነው። ጥያቄ አንድ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች በተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ውስጥ ተረቶች፣ ምሳሌዎች፣ እንቆቅልሾችና ሌሎች ባህላዊ ወጎች አሉ ወይም የሉም ብሎ ለመናገር የሚያበቁ ማስረጃዎችን በመጥቀስ እምነትዎን ያስረዱ የሚል ነው፡፡ አራተኛው ጥያቄ ደግሞ ተማሪዎች፣ በመፃህፍቱ ውስጥ ያሉትን ባህላዊ ይዘቶች የሚማሯቸው በምን መልክ ነው? የሚል ነው፡፡

እነዚህ ጥያቄዎች በመፅሓፉ ውስጥ በተረት ወይም በሌሎች የስነቃል መልክ የቀረቡ ምንባቦች ስለመኖራቸውና ወደ ተማሪዎች የሚቀርቡበት ስልት ምን እንደሚመስል ለማወቅ የሚያስችሉ ናቸው። ጥያቄ ሁለት እና አምስት ደግሞ ስነቃሎች፣ ተግባራትና መልመጃዎቹ አገር በቀል እውቀትን ለማስተማር ስለማገዛቸው ለማወቅ የሚያስችሉ ናቸው። ጥያቄ ሶስት ደግሞ አገር በቀል እውቀት የተማሪዎቹን አስተሳሰብ፣ እውቀትና የቋንቋ ክህሎት ከማሳደግ አኳያ ምን ድርሻ እንዳለው ማየትን ያለመ ነው። ጥያቄ ሰባት ደግሞ የተጋሩ መታወቂያ የሆኑት እውቀቶች በቋንቋ ስርአተትምህርት ውስጥ መካተት ለተማሪው የሚያስገኙት ጠቀሜታ ማወቅን ያለሙ ናቸው። ጥያቄ ስድስት አበእ በስርዓተትምህርቶቹ ውስጥ መካተት አለመካተቱን የሚጠይቅ ነው።

#### 3.5.2.2. በተኮር የቡድን ውይይት

ለተኮር የቡድን ውይይት የቀረቡት ጥያቄዎች ለቃለመጠይቅ ከቀረቡት ጋር አንድ አይነት ናቸው። እንዲሁም በአደረጃጀትም በትኩረታቸውም ተመሳሳይ ናቸው።

### 3.5.3. የስርዓተትምህርት ባለሙያ

በዚህ ቃለመጠይቅ የተሳተፉ ባለሙያ እንድ ብቻ ናቸው። ምክንያቱም በክልሉ ስርዓተትምህርት የስራ ሂደት ውስጥ ከ1ኛ- 8ኛ ያሉት የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርቶች የሚዘጋጁት በአንድ ባለሙያ ብቻ ስለሆነ ነው። ባለሙያው ከመርሃትምህርት ጀምሮ እስከ መፃህፍት ዝግጅትና ስርጭት ያለውን ስራ ያስተባብራሉ።

ለባለሙያው የቀረቡት ጥያቄዎች መጠን ዘጠኝ ሲሆኑ ሁሉም የሚያተኩሩት (*ትግራዋይ ሀብረተሰብ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች ኣገር በቀል ናቸው ብሎ ያምናል?*) በሚለው የጥናት ጥያቄ ለ ላይ ነው። ከባለሙያው ጋር የተደረገው ውይይት መምህራኑ ሊመልሷቸው በማይችሉ ከስርዓተትምህርት ዝግጅት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ያተኰረ ነው። በዚህ ቃለመጠይቅ የተሳተፉት ባለሙያ፦ የመርሃትምህርቱ፣ የመማሪያ መፅሓፉ እና የመምህር መምሪያው አዘጋጅ ናቸው፤ በኮንትራት ፀሓፊዎች የሚሰራ ከሆነም ዝግጅቱን በባለቤትነት የሚቆጣጠሩና የአርትኦቱን ስራ የሚያከናውኑ ሰው ናቸው።

ለነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች በኣምስት የትኩረት ነጥቦች ተጠቃልለው ቀርበዋል። ጥያቄ ኣንድ በተጋሩ የሚነገሩት ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ምሳሊኣዊ ኣነጋገሮችና ሌሎች ወጎች የህብረተሰቡን እውቀት ማንፀባረቅ ስለመቻላቸው እንዲያብራሩ የሚጠይቅ ነው። ጥያቄ ሁለት እና ሶስት የደረጃው ተማሪዎች በመፃህፍቱ ውስጥ ሊኖሩ ከሚችሉት ስነቃላዊ ሃብቶችና በውስጣቸው ከሚይዟቸው ኣገር በቀል እውቀቶች ምን ጠቀሜታ እንዳገኙ ወይም ሊያገኙ እንደሚችሉ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚያስገኙ ናቸው። ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡ መልሶች በመፅሃፉ ያለውን የይዘት ኣቅርቦት ሊጠቁሙ እንደሚችሉ በማመን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄ ኣራት እና ኣምስት በካሪኩለሙ ውስጥ ኣገር በቀል እውቀትን ለማስገባትም ሆነ ላለማስገባት የተቀመጡ መመሪያዎች መኖር ኣለመኖራቸውን የሚፈትሹ ሲሆኑ ጥያቄ ስድስት ደግሞ ስርዓተ ትምህርት በሚቀረፅበት ጊዜ ኣገር በቀል እውቀት እነደ ኣንድ ይዘት ሆኖ እንዲገባ እቅድ የሚያዝ ስለመሆኑ የሚጠይቅ ነው። ጥያቄ ሰባት፣ ስምንት እና ዘጠኝ፣ ኣሁን ባለው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የተጋሩ ኣበእ

ስለመካተቱና ይዘቱ በአግባቡ እንዲቀርብ የመልመጃዎችና የመምህሩ መምሪያ ድርሻቸውን ስለመወጣታቸው የሚጠይቁ ናቸው።

### 3.5.4. የህብረተሰቡ አባላት ከሆኑ የእድሜ ባለፀጋዎች

ይህ መጠይቅ በአጠቃላይ አስራ ሶስት ጥያቄዎችን የያዘ ነው። የተዘጋጀውም በአራቱም መማሪያ መፃህፍት ያሉ ይዘቶችን ለመፈተሽ ነው። ሁሉም ጥያቄዎች፣ "ትግራዋይ ህብረተሰብ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች አገር በቀል ናቸው ብሎ ያምናል?" ለሚለው የጥናት ጥያቄ ምላሽ እንደሚያስገኙ ታምኖባቸው ቀርበዋል። ጥያቄዎቹ የተመሰረቱት ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋን ለማስተማር በተዘጋጁት መፃሕፍት ላይ ነው፡፡ በመፃሕፍቱ ውስጥ የሕብረተሰቡን ባህልና አገር በቀል እውቀት የሚያንፀባርቁ የሚመስሉ ምንባቦች አሉ፡፡ ምንባቦቹ በትክክል የሕብረተሰቡን እውቀት ስለማንፀባረቃቸው ለማወቅ የባህሉን ባለቤቶች በመጠየቅ ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ጥያቄዎችም ይህንን የማረጋገጥ አላማ ለማሳካት የተዘጋጁ ናቸው፡፡

የሚከተለው ሰንጠረዥ በቃለመጠይቅና በተኩር የቡድን ውይይት ይሳተፋሉ ተብለው በእቅድ የተያዙና በተግባር የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች ሁኔታ የሚያመለክት ነው።

ሰንጠረዥ.- 4 በእቅድ የተያዙና በተግባር በተኮር የቡድን ውይይትና በቃለመጠይቅ የተሳተፉ የመረጃ አቀባይ ሰዎች መጠን አመልካች

| ዞን | ተሳታፊዎች | በቃለመጠይቅ | | በተኮር የቡድን | | የተሳታፊዎች መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የታቀደ | የተፈፀመ | የታቀደ | የተፈፀመ | የታቀደ | የተፈፀመ |
| ደቡብ | የእድሜ ባለፀጎች | ----- | 20 | 1ቡድን | 1 ቡድን 7 ሰው | | 27 |
| | መምህራን | 4 | 1 | ---- | 2 | | 3 |
| ምስራቅ | የእድሜ ባለፀጋዎች | | | | | | |
| | | ----- | 12 | ---- | | ----- | 12 |
| | መምህራን | 4 | 4 | --- | 2 | 4 | 6 |
| ማዕከላዊ | | | | | | | |
| | የእድሜ ባለፀጎች | --- | 17 | --- | 3 ቡድን 20 ሰው | | 37 |
| | መምህራን | 4 | 4 | | -- | | 4 |
| ምዕራብ | መምህራን | --- | | -- | -- | -- | |
| ክልል ስ. ትምህርት | የስ.ትም. ባለሙያ | 1 | 1 | -- | -- | -- | 1 |
| ሰሜን | መምህራን | ------ | 4 | ----- | -- | ----- | 4 |
| ሰ.ምዕራብ | መምህራን | --- | 1 | | 1 | --- | 2 |
| መቐለ | መምህራን | --- | 1 | --- | | --- | 1 |
| ድምር | | | 65 | | 32 | | 97 |

## 3.6. ትክክለኛነትና አስተማማኝነት

አንድ ጥናትም ሆነ የጥናት ውጤት በመረጃ ተጠናክሮ ሲቀርብ ተኣማኒነት ይኖረዋል። መረጃዎቹን ለመሰብሰብም የተለያዩ መሳሪያዎችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም ሆኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች፣ በጥናቱ ውጤት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራሉ (Marczyk, 2005; Dornyei, 2007; Creswell, 2009, ያለው፣ 2006)። ስለሆነም መረጃዎቹም ሆኑ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ጥናቱን ወደተሳሳተ መደምደሚያ እንዳይመሩት ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት የተገቢነት ፍተሻ ሊደረግባቸው ይገባል። በተለይ በዓይነታዊ ምርምር፣ ከመፈተሻና የህፀፃት ማስወገጃ መንገዶች አንዱ መስቀልኛ የማመሳከሪያ ዘዴን (Triangulation) መጠቀም ነው (ያለው፣ 2006)።

የመስቀልኛ ማመሳከሪያ ዘዴ ተግባር፣ በጥናቱ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የአንዱን መሳሪያ ትክክለኝነት በሌላው መሳሪያ ፈትሾ ማረጋገጥ ነው። ይህ

ጥናትም ዓይነታዊ እንደመሆኑ የመስቀልኛ ማመሳከሪያ መርህን በመከተል የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ስራ ላይ አውሏል። እነዚህን መሳሪያዎች በመጠቀም የጥናቱን ውጤት ትክክለኝነትና አስተማማኝነት ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል። እንዲሁም ከጥናቱ አማካሪ ከስራ ባልደረቦችና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስርዓተትምህርት ባልደረባ ከሆኑ መምህር የተሰጡ አስተያየቶችንና እርማቶችን በመቀበል የመሳሪያዎቹን አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ባለሙያዎችና የስራ ባልደረቦች መሳሪያዎቹን አይተው አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥም ሌላው ዘዴ ነው።

በጥናት ውስጥ የአጠናን ዘዴና የመረጃ ምንጮች መለያየት ውጤቱን በመስቀልኛ ማመሳከሪያዎ ሲደገፍ የውጤቱ አስተማማኝነት ከፍ ይላል (Cohen et al, 2000)፡፡ አንድ ብቸኛ ዘዴ ከተጠቀመ ይልቅ የተለያዩ ዘዴዎችን የተጠቀመ የጥናት ውጤት አስተማማኝነቱ የጠነከረ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከሶስት የተለያዩ ምንጮች (ከሰነድ ፍተሻ፣ ከቃለመጠይቅና ከተኮር የቡድን ውይይት) ነው፡፡ በአንዱ መሳሪያ የተገኘው መረጃ በሌላው ማሳሪያ እየተመሳከረ መቅረቡ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛና ተአማኒ ያደርጋቸዋል (Banda, 2005; Cohen et al, 2000)፡፡ አንድ መለኪያ መሳሪያ የተለያዩ ነገሮች ተለክቶበት ተመሳሳይ ውጤት ካስገኘ (መለካት የሚገባውን ነገር በትክክል መለካት ከቻለ) መሳሪያው ትክክለኛ ነው ይባላል (ያለው፣ 2006)። በዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉት መሳሪያዎች በሙከራ ጥናት በሶስት መቶና ከዚያ በላይ ኪሎ ሜትር ተራርቀው ለሚገኙ መምህራንና የእድሜ ባለፀጋዎች ቀርበው ተመሳሳይ ምላሽ አስገኝተዋል፡፡ የመሳሪያዎቹ አስተማማኝነት ተፈትሿል፤ እንዲሰበሰብ የታለመውን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ሆነው ስለተገኙ መለኪያዎቹ ትክክለኛ ናቸው ብየ አምናለሁ።

በቃለመጠይቅም ሆነ በተኮር የቡድን ውይይት ጊዜ መረጃዎች የተሰበሰቡት በመቅረፀ ድምፅ በመሆኑና ንግግሮቹም በባለሙያ ቃል በቃል ወደፅሑፍ የተሸጋገሩ ስለሆነ ተአማኒነታቸው ከፍ ያለ ይሆናል። በመረጃ ስብሰባ ወቅት አጋዥ መረጃ ሰብሳቢዎችን አሰልጥኖ ማሰማራት ሊከሰት የሚችለውን **ኢሚዛናዊነት/ አድሏዊነት** ሊቀንሰው እንደሚችል ይታመናል። ሆኖም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበው እጅግ በጣም አነስተኛ በጀት ምክንያት ረዳቶችን አሰልጥኖ ለማሰማራት አልተቻለም። ስራው አድካሚ ቢሆንም በአማራጭነት አጥኚው የማህበረሰቡ አባል በመሆኔ በሁሉም ቦታዎች በአካል በመገኘት

መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተገድጃለሁ። ሓሳቦችን ላለማዛባት የመረጃ አቀባዮቹን ንግግር መቅረፀድምፅ በመጠቀም ቃል በቃል ወስጃለሁ፣ እንግዳ የሆኑ ቃላትና ሃረጎች ወይም ሃሳቦች ሲያጋጥሙኝ ማብራሪያ በመጠየቅ ግልፅ መረጃ ለመያዝ ጥረት አድርጌያለሁ። ይህም **ኢሚዛናዊነቱን/ አድሏዊነትንና ግምታዊ ብየናን** ሊቀንስና አስተማማኝነቱን ከፍ ሊያደርገው እንደሚችል አምናለሁ።

በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ ኣገር በቀል እውቀትን ለማስተማር የቀረቡ የሚመስሉትን ከማይመስሉት አስቀድሞ የመለየት ስራ ተከናውኗል። እነዚህን ምንባቦች በማቀላቀል ለሁለት የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የትግርኛ ቋንቋ መምህራን ሰጥቶ ተመሳሳይ የልየታ ስራ እንዲያከናውኑ በማድረግ በኣጥኚው የተካሄደውን የልየታ ስራ ትክክለኝነት የማረጋገጥና ኣስተማማኝ የማድረግ ስራ መካሄዱ ቀደም ሲል ተጠቁሟል።

## 3.7. ከምርምር ስነምግባር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች

የምርምር ስነምግባር፣ የሚባለው አንድ ተመራማሪ ከተለያዩ ምንጮች ጥናቱን የተመለከተ መረጃ ለማግኘት ሰዎችን በሚያነጋግርበት፣ መጠይቅ በሚያስሞላበት፣ ምልከታ በሚያደርግበት ወይም ሰነዶችን በሚፈትሽበት ጊዜ ሊከተለው የሚገባውን ስርዓት የሚያመለክት ነው (Cohen et al 2ooo; Willig, 2008.)። የምርምር ስነምግባር መጓደል አጠቃላይ ጥናቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል። ተገቢ የሆኑና ያልሆኑ የሚባሉት የስነምግባር መርሆዎች በዝርዝር ማቅረብ አዳጋች ነው። ምክንያቱም በአንድ የጥናት ወቅት ተገቢ የተባሉ ተግባራት በሌላ ወቅት፣ በሌላ ርእሰጉዳይና አውድ ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ ሊባሉ ይችላሉ፡፡ በአንድ ቃለመጠይቅና አውድ የተተቸ አቀራረብ በሌላ አውድ ውስጥ ችግር የማያስከትል ሆኖ ሊገኝ ይችላል (Cohen et al 2ooo)።

ይህ ሲባል ግን የተመራማሪዎች ስምምነት ያገኙ በጎጂነታቸው የሚመደቡ ተግባራት የሉም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉት ነጥቦች ጉዳት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (Willig, 2008.)።

- የመረጃ አቀባዮችን ስም ይፋ ማድረግ፣
- የሰበሰቡትን መረጃ አሳልፎ ለሌላ መስጠት፣ ያለቦታው ይፋ ማድረግ፣
- ጥናቱ፣ የጥናቱ ዓላማና ጠቀሜታ ሳይገባቸው መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ጥናቱ፣ ምን ጠቀሜታ ሊያስገኝላቸው እንደሚችል ሳይነግሩ መረጃ መውሰድ፣

• ጥናቱ ለማን እንደሚቀርብ ሳይነግሩ መረጃ መሰብሰብ፣
• መረጃ አቀባዮች፣ ለመሳተፍ ፈቃደኛነታቸው ሳይረጋገጥ መረጃ መውሰድ።

በዚህ ጥናት ውስጥም መረጃ አቀባዮች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ስጋት ውስጥ ሊጥሉ ከሚችሉ ሁኔታዎች ውስጥ የመረጃ ሰብሳቢው ማንነት ያለማወቅ ነው። ይህንን ስጋት ለማስወገድም በተገኘሁባቸው ቦታዎች ሁሉ ቀድሞ የማውቃቸውና የአካባቢው ነዋሪዎችን በአገናኝነት ተጠቅሜአለሁ። ራሴን፣ የመጣሁበትን አካባቢና የመጣሁበትን ዓላማ አስተዋወቃለሁ። በመቀጠልም ጥናቱ ምን ጠቀሜታ እንዳለውና ጠቀሜታውን እውን ለማድረግ የተሳታፊዎቹ አስተዋፅኦ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስረዳለሁ። የሚሰጡት መረጃ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው፣ ሆኖም ለታለመለት አገልግሎት ብቻ የሚውል መሆኑ፤ ከዚህ ውጪ ለሌላ አካል እንደማይተላለፍና ከዚህ ጥናት ውጪ ለሆነ ጉዳይ ግልጋሎት እንደማይውል እገልፃለሁ።

መረጃ አቀባዮች፣ መረጃ በመስጠታቸው ጉዳት ሊደርስባቸው እንደሚችል ሊያስቡ ይችላሉ። ይህንን ስጋት ለማስወገድና ነፃ ሆነው መረጃ መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ መረጃዎቹ በሚስጥር የሚጠበቁ ከመሆናቸውም በላይ የያንዳንዱ መረጃ አቀባይ ስም የማይጠቀስ መሆኑ በማስረዳት ጥረት አድርጌያለሁ። በዚህ ሁኔታ በትግራይ ሶስት ዞኖችና በርካታ ወረዳዎች ከሚገኙ የእድሜ ባለፀጋና የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን መምህራን ጋር በመወያየት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

## 3.8. ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች በርካታ ናቸው። በዚህ ርእስ ስር ሁሉንም ችግሮች መዘርዘር ያስቸግራል። ዋና ዋናዎቹንና ለሌሎች አጥኚዎችም የማስተጠንቀቂያ መረጃ ሊሰጡ እንደሚችሉ ያመንኩባቸውን ብቻ እጠቅሳለሁ።

ካጋጠሙኝ ችግሮች ውስጥ አንዱ በጥናቱ የናሙና መምረጫ ዘዴ ምክንያት የተከሰተ ነው ማለት ይቻላል። በተለይ የማህበረሰቡ ወካይ የሆኑ የእድሜ ባለፀጋዎችን ለማግኘት ሰንሰለታዊ ጥቆምታ (Chain Referal) የንሞና ዘዴ ነው ስራ ላይ የዋለው። የመጀመሪያዎቹ መረጃ አቀባዮቹ የተሻሉ የሚሏቸውን ሰዎች ይጠቁማሉ። በዚህ ጥቆማ መሰረት በሄድኩባቸው ቦታዎች  የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል።

- ጠቋሚዎቹ ስለተተጠቋሚዎች የቅርብ ጊዜ መረጃ የላቸውም። እተባለው ቦታ ስደርስ ሰዎቹ በእድሜ ወይም በህመም ምክንያ መስማትም ሆነ መናገር እማይችሉበት ደረጃ ውስጥ ናቸው (ናዕዴር ዓዴት ጣቢያ ሕለት፣ አክሱም ከተማ ቀበሌ 03)።
- አንዳንድ የሄድኩባቸው ቀበሌዎች ደግሞ ተጠቋሚዎቹ በህመም፣ በስራ ወይም በሌላ ማህበራዊ ጉዳይ ምክንያት ከአካባቢው ስለራቁ ባዶ እጅ የተመለስኩባቸው ጊዜያት ነበሩ (ወርዒ ለኸ - ዕዳጋ ዓርቢ)።
- ቀጠሮ ከሰጡኝ በኋላ በቦታውና በጊዜው የታጡ ሰዎችም አጋጥመውኛል (ጨርጨር ሓደ አልጋ)።

ሌላው አጥኚውን በጥርጣሬ አይን የማየት ችግር ነበረ።

- ለምሳሌ በዓብዪ ዓዲ ሁለት የእድሜ ባለፀጋዎች ቀጠሮ ከሰጡኝ በኋላ የየትኞቹ የፖለቲካ ድርጅት አባል እንደሆንኩ ማወቅ እንደሚፈልጉ ጠይቀውኝ ነበር። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆኖ ነፃ የሆነ አስተያየት መስጠት ምን ያህል ሊከብድ እንደሚችል መገመት ይቻላል።

በነዚህ ምክንያቶ በእግር እስከሁለት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ድረስ ተጉዤ መረጃ ሳላገኝ የተመለስኩባቸው ጊዜያት ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ተደጋጋሚ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ኪሳራ አጋጥሞኛል።

- ምን ያህል እንደምትከፍለን ካላወቅን መረጃ አንሰጥም ያሉኝ ሰዎችም ነበሩ። በመስክ ስራ ወቅት ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት ተስፋ አስቆራጭ ፈተናዎች ቢያጋጥሙኝም አበረታች ሁኔታዎችም ነበሩ።

ለምሳሌ በህመም ምክንያት መረጃ ሊሰጡኝ ባለመቻላቸው አዝነው ለመሳፈሪያ ሓምሳ ብር እንድቀበላቸው የለመኑኝ አባት አጋጥሞኛል (ማእከላዊ ዞን፣ ዓዴት- ሕለት)። እንዲህ አይነት ቅን ወላጆች ሲያጋጥሙ አስቸጋሪ ሁኔታዎቹ ይዘነጋሉ፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ቀጥሎ እዚህ ደረጃ ሊደርስ ችሏል።

## 3.9. የሙከራ ጥናት

በዚህ ርእስ ስር የጥናት አስፈላጊነትና የጥናቱ አመራር ሂደት በዋናው ጥናት ላይ ስለተገለፀ እዚህ አልተካተተም። እዚህ ላይ ሶስት ጉዳዮች በትኩረት ተብራርተዋል። ከሙከራ ጥናቱ

ምን ጠቃሚ ልምድ ወይም ትምህርት እንደተገኘ ተገልጿል። የተገኘው ትምህርት መሰረት በማድረግ በዋናው ጥናት ምን ምን ለውጦች እንዳስከተለ ተብራርቷል። እንዲሁም የሙከራ ጥናቱ ግኝት ምን እንደሆነ ተገልጿል።

### 3.9.1. ከሙከራ ጥናቱ የተገኘ ትምህርት

እንደየጥናቱ አይነት፣ የሙከራ ጥናት የሚካሄድባቸው በርካታ ምክንያቶች ሊቀርቡ ይችላሉ። በዚህ ጥናት ስር የተካሄደው የሙከራ ጥናትም የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎችን ከመፈተሽ አልፎ የተለያዩ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ አስችሏል። የምርምሩ ትልመ-ጥናት በቀረበበት ጊዜ ተነድፈው የነበሩ አንዳንድ እቅዶችን ለመለወጥና ለማሻሻል አስችሏል። አዳዲስ የመረጃ ምንጮች እንዲካተቱ ምክንያት ሆኗል።

- **የሰነዶች ፍተሻ፡** ትልመጥናቱ ውስጥ ፍተሻ ይካሄድባቸዋል ተብለው የተያዙ ሰነዶች፣ መርሃ- ትምህርት፣ የተማሪ መፅሐፍና የመምህር መምሪያ ብቻ ነበሩ። ነገር ግን በንባብ ጊዜ የተገኙና ለነዚህ መፃሕፍት መዘጋጀት መነሻ የሆኑ ሰነዶችን አስቀድሞ ማየት ችግሩ የት አካባቢ እንደሆነ ለመረዳት ስለሚያስችል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ5 ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ ESDP IV (2010/11- 2014/15)፣ የትግራይ ክልል የእቅድና ፋይናንስ ቢሮ የእድገትና ሽግግር እቅድ (2003- 2007 ዓ.ም.) እና የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ የአምስት ዓመት የትምህርት እድገትና ሽግግር እቅድ (2003- 2007 ዓ.ም.) ፍተሻ ከሚካሄድባቸው ሰነዶች ውስጥ ተካትተዋል።

- **የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፡** ቀደም ሲል በወጣው እቅድ መሰረት ወደ መስክ ሄጄ የተጋሩን አገር በቀል እውቀት ለመሰብሰብና በተሰበሰቡት መረጃዎች መሳሪያነት በመፃህፍቱ ውስጥ የተካተቱና ያልተካተቱ እውቀቶችን ለመፈተሽ አልሜ ነበር። በዚህ መሰረት ለአርባ ቀናት ያህል በሶስት ዞኖችና በርካታ ወረዳዎች በመገኘት የተጋሩን አገር በቀል እውቀቶች መሰብሰብ ችዬ ነበር፡፡ በእቅዱ መሰረት እውቀቶች ከተሰበሰቡ በኋላ መፅሃፉ ውስጥ አሉ የሉም እያሉ ለማረጋገጥ የተደረገው ሙከራ የአቅጣጫ ስህተት እንዳለበት ስለተገነዘብኩ የአቅጣጫ ለውጥ አድርጌአለሁ። በአዲሱ እቅድ መሰረት በቅድሚያ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉ አገር በቀል እውቀቶችን የሚያስተምሩ የሚመስሉ ምንባቦችን የመለየት ስራ በባለሙያዎች እገዛ አከናውኛለሁ። ምንባቦቹን

መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች የማዘጋጀት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ መስክ በመውጣት በአዲስ መልክ መረጃ ሰብስቤአለሁ።

- **የጥናት ጥያቄ ላይ ለውጥ ማድረግ፡** በተራ ፊደል 'ሀ' የተመለከተው የጥናት ጥያቄም በዚህ ለውጥ መቃኘት ስላለበት "በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው ህብረተሰብ እንዲጠበቁና ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲሸጋገሩ የሚፈልጋቸው አገር በቀል እውቀቶች እንዴት ያሉ ናቸው?" ይል የነበረውን የጥናት ጥያቄ "ትግራዋይ ሕብረተሰብ በተጠኚዎቹ መፃሕፍት ውስጥ ያሉትን እውቀቶች አገር በቀል ናቸው ብሎ ይቀበላቸዋል?" በሚል ጥያቄ ተተክቷል።

- **የጥያቄዎች አቀራረብ፡-** በትልመጥናቱ ውስጥ ለማህበረሰቡ አባላት የተዘጋጁት ጥያቄዎች በቁጥር ከአሁኑ ጋር ተመጣጣኝ ነበሩ። በይዘት ግን ቀደም ብለው የወጡት የተጋሩን አገር በቀል እውቀት ለመዳሰስ ያለሙ ነበሩ። በተደረገው ለውጥ መሰረት ስራ ላይ የዋሉት ጥያቄዎች በስርዓተትምህርቱ ውስጥ ባሉት አገር በቀል እውቀትን ለማስተማር ያለሙ በሚመስሉት ይዘቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

- **ጥያቄ ስለመሰረዝ፡** ለመምህራን በቀረበው ቃለመጠይቅ ውስጥ *ኣሁን በስራ ላይ ያሉት የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት (1-4) በአገር በቀሉ ተማሪ ያላቸው ተቀባይነት ምን ያህል ነው?* የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር። መምህራኑ፤ ተማሪዎቹ ህፃናት በመሆናቸው መፅሓፉን "እወደዋለሁ" ወይም "እጠላዋለሁ" ሊሉ አይችሉም። ቢሉ እንኳ ምክንያቱ ከመፅሓፉ ይዘት ጋር የተያያዘ ላይሆን ይችላል። የሚል ሃሳብ አቅርበዋል። አጥኚውም በመምህራኑ የቀረበው ሃሳብ አሳመኝ ሆኖ ስላገኘው ጥያቄውን ሰርዞታል። ለመምህራን የቀረቡት ጥያቄዎች ቁጥርም ወደሰባት ዝቅ ብለዋል።
- ***መሳሪያዎችን መሞከር፡*** የተዘጋጁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተፈለገውን መረጃ ማስገኘት መቻላቸውን፣ ለቃለመጠይቅም ሆነ ለቡድን ውይይት የቀረቡት ጥያቄዎች ግልፅና ኣሻሚነት የሌለባቸው መሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል።

- ***መሳሪያዎችን መምረጥ፡*** የሙከራ ጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያን ለመምረጥ አስችሏል። በትልመጥናቱ ውስጥ ካሴት የሚጠቀም ቴፕ (walkman recorder) እና

መዘክር ለመጠቀም ታስቦ ነበር። ሆኖም በቴፕ የተቀረፀን መረጃ ወደ ኮመፒውተር ማሻገር በጣም ከባድና ብዙ ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ የሚፈጅ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ይልቅ ዘመናዊ (Digital Recorder) መቅረፀ ድምፅ መጠቀም በተለይ በባለሙያዎች ልዩ መሳሪያ በመጠቀም ወደፅሑፍ ለመቀየር ምቹ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በቴፑ ምትክ ዘመናዊው መቅረፀድምፅ ስራ ላይ ውሏል።

*የሙከራ ጥናቱ ግኝት*

*የጥናቱ ርእስ ለማስታወስ፡-* "**በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተ-ትምህርት የሃገር በቀል እውቀት አካትቶ ፍተሻ**" *የሚል ነው።የሙከራ ጥናቱ ያተኮረውም የዚህ ስርዓተትምህርት አካል በሆነው የሁለተኛ ክፍል ስርዓተትምህርት ላይ ነው። ለሙከራ በተመረጡት መርሃትምህርቶች፣ የተማሪ መፅሓፍና የመምህር መምሪያ ውስጥ የተጋሩ ኣገር በቀል እውቀት እንዴት እንደተንፀባረቀ ለማየት የተለያዩ ሰነዶች ተዳስሰዋል።*

**የምርምር ጥያቄ 'ለ' ስርዓተትምህርቱ ኣገር በቀል እውቀትን ስለማካተቱ፡-** የቀረበው ጥያቄ *"በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ፣ ኣገር በቀል እውቀትን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎችና ይዘቶች ቀርበዋል?" የሚል ነው።*

ለ2ኛ ክፍል የተዘጋጀው መርሃትምህርት ካነሳቸው ዓላማዎች ውስጥ ለቃላትና ዓረፍተነገር ምስረታ 71፣ ኣራቱን የቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር 50 መመሪያዎችን ለመገንዘብና ሃሳብን የማሳጠር ዕውቀት 21 ክፍለጊዜ የተመደበላቸው ሲሆን ስነቃል (ተረቶች፣ ምሳሌኣዊ ንግግር፣ እንቆቅልሽ) በሚል መለያ ለቀረቡት ይዘቶች ደግሞ 6 ክፍለጊዜ ተመድቦላቸዋል። ከዚህ መረዳት የተቻለው ለኣገራዊ እውቀት ማቅረቢያ መሳሪያዎች የተሰጠው ግምት እጅግ ኣናሳ መሆኑ ነው። ለክፍሉ በተዘጋጀው መማሪያ መፅሓፍ ወስጥ 21 ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ድርሻ ይዞ የሚገኘው ደግሞ ኣበእ ሳይሆን ከተፈጥሮ ሳይንስ ሊገኝ የሚችል ጥሬ እውነታ ወይም እውቀት ነው። ኣቀራረቡም የህፃኑን ቀዳሚ እውቀት መነሻ በማድረግ በማሳደግ ፈንታ ተማሪውን እንደ የእውቀት ማከማቻ ባንክ የሚቆጥርና ስብእናውን የዘነጋ ነው። የምንባቦቹ ኣቀራረብ ህብረተሰቡ፣ ኣንዳች ጠቃሚ የሚባል ልምድና እውቀት እንደሌለው ኣድርገው የሚስሉ በመሆናቸው ለኣገር በቀል እውቀት ጥበቃም ሆነ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ቀዳሚ እውቀትን መነሻ ኣድርጎ የተሻለ ለማወቅ ለሚደረግ ግንባታ ኣስተዋፅኦ የላቸውም።

የመምህር መምሪያ ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ውስጥ የትምህርቱን ዓላማ ማስተዋወቁ ነው። የትምህርቱ ትኩረት ምን ላይ እንደሆነና ዓላማውን ለማሳካት ተማሪውና መምህሩ ምን ምን ተግባራት ማከናወን እንዳለባቸው የሚገለፀው በመምህር መምሪያው ውስጥ በሚቀርቡ ዝርዝር ማብራሪያዎችና ዓላማዎች አማካይነት ነው። የ2ኛ ክፍል የመምህር መምሪያ ግን ይህንን ተግባር ለመፈፀም በሚያስችል መንገድ የተዘጋጀ አይደለም። የአገር በቀል እውቀቶችን ማጉላት የሚችሉ ምንባቦች (ተረቶች፣ እንቆቅልሾች) ቢኖሩም እንኳ ተማሪዎች እንዲያከናውኗቸው የታለሙት ተግባራት የማስተዋል ጥያቄን ከመመለስ የዘለሉ አይደሉም። በአጠቃላይ፣ ለጥናት ጥያቄ 'ለ' የተሰጠው ምላሽ አሉታ ነው። አገር በቀል እውቀትን ማስተማር ዓላማቸው ያደረጉ አይደሉም።

**የጥናት ጥያቄ 'ሐ' የመልመጃዎችና ተግባራት አቀራረብ አበእን ከማዳበር አኳያ፡-** ሌላው የጥናት ጥያቄ፡- *ለመለማመጃነት የቀረቡት ተግባራትና ክንውኖች (መልመጃዎች፣ የቡድንና የጋራ የፕሮጀክት ስራዎች) የቀረቡት አገር በቀል እውቀትን ማዳበር በሚያስችል መንገድ ነው?*

መበዕሐፉ ውስጥ በተረትና በእንቆቅልሽ መልክ የቀረቡ ምንባቦች ቢኖሩም እነሱን ተከትለው የሚመጡት መልመጃዎችና ተግባራት ግን አንድም የአንብቦ መረዳት አለዚያም የስነልሳንና የሰዋስው ጥያቄዎች ናቸው። በአጠቃላይ መልመጃዎቹ ያተኮሩት በተረቱ ይዘትና ሊተላለፍ በተፈለገው አበእ ላይ አይደለም።

**የጥናት ጥያቄ 'ሀ' በመፃህፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች የማህበረሰቡ እውቀቶች መሆናቸውን ስለማረጋገጥ፡-** *ትግራዋይ ህብረተሰብ በተጠኚዎቹ መፃሕፍት ውስጥ ያሉትን እውቀቶች አገር በቀል ናቸው ብሎ ያምናል?*

በመፃህፍቱ ውስጥ በቁጥር አናሳ ቢሆንም የህብረተሰቡን እውቀት ማስተላለፍ የሚችሉ ምንባቦች ቀርበዋል። ከእድሜ ባለፀጋዎችና ከመምህራን በተገኘው መረጃ መሰረት የቀረቡት ምንባቦች የህብረተሰቡ እውቀት ማስተላለፊያ መሳሪያዎች መሆናቸው መገንዘብ ተችሏል። ምንባቡን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች ግን ተማሪው በምንባቡ የተላለፈውን እውቀት እንዲገነዘብ የሚያደርጉ እንዳልሆኑና ከህብረተሰቡ እውቀት ጋርም ግንኙነት እንደሌላቸው ታይቷል።

# ምዕራፍ አራት
# መረጃዎች፣ የመረጃዎች ትርጕማ እና ትንተና

## 4.1. መግቢያ

ይህ በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ውስጥ ኣበእን የተመለከቱ መረጃዎች የቀረቡበት ምዕራፍ ነው። መረጃዎች የተሰበሰቡት ከእቅድ ሰነዶች፣ ከመማሪያ መፃሕፍት፣ ከመምህራንና ከህረተሰቡ ኣባላት ጋር ከተካሄደ ቃለመጠይቅና ተኰር የቡድን ውይይት፣ ከስርዓተትምህርት ባለሙያ ጋር ከተካሄደ ቃለመጠይቅ ነው። መረጃዎቹ በዓይነት ተለይተው ተተንትነውና ተተርጉመው ቀርበዋል። በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ ትንተናን እና ትርጕማን መለየት በጣም አስቸጋሪ ነው (Cohen et al, 2007)። ምክንያቱም ሁለቱም ተጣምረው የሚቀርቡ ከመሆናቸውም በላይ ትርጕማው ትንተና፣ ትንተናው ደግሞ ትርጕማ እየሆኑ ስለሚከሰቱ ነው። እንደዚያም ሆኖ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች፣ ትንተና እና ትርጎማ ሂደት በግልፅ እንዲታዩ፣ ተገቢ ትኩረት እንዲያገኙና፣ እንዲሁም መረጃ አቀባዮች በያንዳንዱ ይዘት ምን ምላሽ እንደሰጡ ለማሳየት እንዲቻል ታስቦ መረጃዎቹ የሚከተለውን ቅደም ተከተል ይዘው ቀርበዋል።

በመጀመሪያ አበእ በትምህርት እቅዶች ውስጥ ምን ቦታ እንደተሰጠው የሚፈትሸው ትንተና ቀርቧል። ከመርሃትምህርት፣ ከመማሪያ መፅሓና ከመምህር መምሪያ የተገኙ መረጃዎችም ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቀርበዋል። በስርዓተትምህርቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች አገር በቀል ስለመሆናቸውና ምንባቡቹና መልመጃዎቹ አበእን ማዳበር በሚያስችል መንገድ የቀረቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተናም በተከታታይ ቀርቧል። የመረጃ አቀራረብ፣ ትንተና እና ትርጕማው የይዘቶቹን ቅደም ተከተል ጠብቆ ቀርቧል። በትንተናው ውስጥ ኣልፎ ኣልፎ የተደጋገሙ ሃሳቦች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ድግግሞቹ ከጥያቄዎቹ መመሳሰል የሚመነጩ መሆናቸው በቅድሚያ ለመጠቆም እወዳለሁ። ትንተና የተካሄደባቸው መሪ ይዘቶች፣ መረጃ አቀባዮች እምነታቸውን፣ ኣተያያይና ፍላጐታቸውን እንዲገልፁባቸው ከቀረቡት ጥያቄዎች የወጡና የጥናት ጥያቄዎቹን መሰረት ያደረጉ ናቸው።

## 4.2. የአበእ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ መካተት አስፈላጊነት

ለመረጃ አቀባዮቹ የቀረበው ጥያቄ "የአበእ በቋንቋ ስርአተትምህርት ውስጥ መካተት ለተማሪው ምን ጠቀሜታዎች ያስገኝለታል?" የሚል ነበረ። ሁሉም ተሳታፊዎች የአበእ በስርዓተትምህርቱ ውስጥ መካተት ጠቀሜታ እንዳለው ያምናሉ። የአበእ ከትውልድ ወደትውልድ መተላለፍ ጠቀሜታና መተላለፊያ መንገዶች በማስቀደም የማካተቱ አስፈላጊነት በሚከተለው መንገድ ገልፀውታል።

ከቃለመጠይቅና ከተኮር የቡድን ውይይት የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት የዚህ እውቀት ወደ አዲሱ ትውልድ መተላለፍ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ይገልፃሉ።

> *በተለይ ህፃናት፣ የአእምሮ ብስለትን፣ ተጠየቃዊ አስተሳሰብን፣ ነገሮችን ቶሎ ተረድቶ ፈጣን ምላሽ መስጠትን፣ ትንክል አዘልና ቅን አስተሳሰቦችን የሚለዩት በእንስሳት፣ በእፀዋትና በነፍሳት ገፀባህርያት እየተመሰሉ በሚቀርቡ ተረቶችና ሌሎች ወነች አማካይነት ነው። ልዩ ልዩ ሙያዎችን ተምረው ራሳቸውን ሊመሩ የሚችሉትም አገር በቀሉን እውቀት ከተግባር መገንዘብ ሲችሉ ነው። ከያንዳንዱ ገፀባህሪይም ህብረተሳቡ የሚቀበላቸውንና የሚያወግዛቸውን አስተሳሰቦች፣ ተግባሮችና ስነምግባር ይገነዘባሉ። እነዚህ እውቀቶች የተቀባዩን ሰው አቅም ገንብተው ከማህበረሰቡ ጋር ለመኖር የሚያስችል ስብእና ይፈጥሩለታል። ስለዚህ ጠቀሜታው ብዙ ነው ብዬ አምናለሁ። ቃመ. መም* 2.12፣ *26/12/2004 ዓ.ም.*
>
> *የማህበረሰቡን እሴቶች በሚገባ ይገነዘባሉ፣ ይወርሳሉ። ጠቃሚና ጎጂ ልማዶችን ለይተው ያውቃሉ። የኔ የሚሉት ጠቃሚ ባህል እንዳላቸው አውቀው በማንነታቸው ይኮራሉ፣ በራሳቸው ይተማመናሉ።* (ቃ.መ. ስባሙ. 28/12/2004 ዓ.ም.)

ከተገኙት መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው የአበእ ከትውልድ ወደትውልድ መተላለፍ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት መሆኑ ነው። አበእ የሚተላለፈው በተግባርና በንግግር አማካይነት ነው። ስለዚህ ህፃናት በንግግር ከሚተላለፈው ይዘት የሚማሩት እውቀት አለ፣ በተግባር ከሚከናወነውና ከሚያዩት ትግበራም እንዲሁ አሰራሮችንና ልዩ ልዩ ሙያዎችን ሊያውቁና በአንዱ ሙያ ተሰማርተው ራሳቸውን ሊመሩ ይችላሉ። ጥሩ አራሽ፣ ጥሩ ወጌሻ፣ ጥሩ የሸክላ ወይም የብረታብረት ስራ ባለሙያ ሆኖ ሊቀረፅ ይችላል። እውቀቱ በቋንቋ በሚገለፅበት ጊዜ የቋንቋ ክህሎትንም ያዳብርበታል። ስለዚህ የአገር በቀል እውቀት ትምህርት ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚታይ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ እውቀትና የቋንቋ ክህሎት የሚቀሰምበት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። እውቀቱ በተለያዩ መንገዶች ከተሰበሰበና በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ከተካተተ ጠቀሜታው የማሳወቅና ስብእና የመገንባት ብቻ ሳይሆን እንዳይጠፋና በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅ የማድረግ ስራም ይሆናል።

የስርዓተምህርት ባለሙያውም ሆኑ መምህራኑ የአገር በቀል እውቀት ወደአዲሱ ትውልድ መተላለፍ ጠቀሜታ እንዳለው ያምናሉ። በተኮር የቡድን ውይይት የተሳተፉት መምህራኑ ጠቀሜታውን በሁለት መልክ ያዩታል። የእውቀቱ ወደ አዲሱ ትውልድ መተላለፍ በዋናነት እውቀቱን እየተረከበ ያለውን ትውልድ የተለያዩ አገራዊ እውቀቶች ባለቤት ያደርገዋል። እንዲሁም በማንነቱ የሚኮራና ማንነቱን ያለማፈር ሊናገር የሚችል ሰው አድርጎ ለመቅረፅም ይጠቅማል። እውቀቱ በተለያዩ መንገዶች ከተሰበሰበና በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ከተካተተ ጠቀሜታው የማሳወቅና ስብእና የመገንባት ብቻ ሳይሆን እንዳይጠፋና በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅ የማድረግ ስራም ይሆናል።

ይህ እውቀት የስነቃል ልዩ ልዩ አላባዎች በሆኑት ተረቶች፣ ምሳሌዎች፣ እንቆቅልሾች፣ የስራ ላይ ግጥሞች እና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች እንደሚተላለፍ መረጃ አቀባዮቹ ጠቁመዋል፤

> *... ህፃናቱ እየተማሩ መሆናቸውን ሳያውቁ የሚማሩባቸው፣ እየተዝናናን ነው ብለው በሚያስቡበት ወቅት እውቀት የሚሸምቱባቸው ናቸው።* (*ቃመ.መም* 2.8፣ 22-12-2004 ዓ.ም.)

> *እውቀትንም ሆነ ስነምግባርን ለማስተላለፍ ተመራጩ መሳሪያ ስነቃል ነው። ለምሳሌ ጅብና ሶስቱ በሬዎች በሚለው ተረት ውስጥ ከግለኝነት ይልቅ ማህበራዊነት ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውና አንድነት ሃይል እንደሆነ ማስተማር ነው የፈለገው። አንድነት ሲላላ ደግሞ በጠላት መጠቃት ሊከተል እንደሚችል እያዝናና ያስተምራል።* (ቃ.መ. ስባሙ. 28-12-2004 ዓ.ም.)

ከፍ ብሎ ከቀረበው ገለፃ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪ ጠቃሚ ስለሆነ ብቻ እውቀትን እንደውሃ አይጠጣውም። ማቅረቢያና ማዋዣ ነገር ያስፈልገዋል። በቅድሚያ እውቀቱ ሲቀርብለት ከልምዱ ጋር ነው ለማያያዝ የሚሞክረው። ከሚያውቀው ነገር ጋር ካልተያያዘ ለመረዳት ይከብደዋል፤ በጊዜው የገባው ቢመስለውም እውቀቱ ከሱ ጋር የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ይሆናል። በሌላ በኩል እውቀቱ በቀልድ፣ በጨዋታ፣ በተረት ወይም በዜማ መልክ ቢቀርብ ህፃኑ ቶሎ ይቀበለዋል፤ እየተጫወተ ይማራል።

> *ኣበጀ የሚገለፀው ህብረተሰቡ የኔ በሚላቸው ኣዝርእትና ኣዘራር፣ በየእርሻ፣ በመመገቢያ፣ በመዋቢያ፣ በበሽታ ዓይነትና መድሃኒቶች፣ በፍትህ ስርዓትና በመሳሰሉት መሳሪያዎችና ክንውኖች ኣማካይነት ነው። ተማሪዎች፣ የኒዚህን መሳሪያዎች ምንነትና ከምንነታቸውና ከኣጠቃቀማቸው ጋር የተያያዙ ፅንሰሃሳቦችን*

*ለመግለፅ ሲሞክሩ ኣዲስ እውቀት እና ክህሎት ይማራሉ፤ ከኣዳዲስ ፊደላት ጋር ይተዋወቃሉ። በፊደላት ኣዳዲስ ቃላት ይመሰርታሉ፤ የንባብና የፅሕፈት ክሂል ያዳብራሉ። እውቀቱ በምሳሌ፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ የሚገለፅ ከሆነ ደግሞ እየተጫወትን ነው ብለው በሚያስቡበት ሁኔታ እውቀቱን፣ የቋንቋውን ለዛና ኣጠቃቀም ይማራሉ። በተረቶቹ ውስጥ ከሚገኙት ገፀባህርያት በጎና መጥፎ ምግባሮችን ይለያሉ። ስለዚህ ኣገር በቀል እውቀትን በስርዓተትምህርት ማስገባት ማለት ቋንቋውንና የቋንቋውን ክህሎት ማዳበር ማለት ነው። (ቃመ. መም 2.9፣ 22/12/2004 ዓ.ም.)*

*የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ እውቀቶች በቋንቋ ማስተማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ቢቀርቡ ስለኣካባቢው በሚነገርበት ጊዜ ተማሪው ከኣካባቢው ጋር ይተዋወቃል። ስለኣንድ የማህበረሰቡ ኣባል ጥበበኛነት፣ ጀግንነት፣ ኣዋቂነት፣ ኣዳኝነት ሲነገረው፤ የወለደውንና ያሳደገውን ማህበረሰብ ይወዳል፣ ያደንቃል፣ ያከብራል። በተለያዩ ገፀባህርያት ከሚፈፀሙ ተግባራትና ከሚፈልቁ ለየት ያሉ ኣስተሳሰቦችም የሚቀስማቸው እውቀቶች ይኖራሉ። የማንነት መግለጫ የሆኑ ኣለባበስ፣ የምግብ ኣዘገጃጀት፣ ኣመጋገብ፣ ኣጊያጊያጥ፣ ኣሰራር፣ እንዲጠበቁና የነዚህ መግለጫ ከሆነው የቋንቋ ኣጠቃቀም ጋር እንዲተዋወቅ ያግዘዋል። ትምህርቱ በሚያውቀው ተረትና እውቀት ላይ ስለሚመሰረት ተማሪው በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ያነሳሳዋል።* (ተቡው 27-12-2005 ዓ.ም.)

*ተማሪዎች ትግራዋይ እውቀትን ሲቀስሙ ባህላቸውን ያውቃሉ። የኣስተሳሰብ ኣድማሳቸውን ያሰፋሉ። የማህበረሰቡን እሴቶች በሚገባ ይገነዘባሉ፤ ይወርሳሉ። የኔ የሚሉት ጠቃሚ ባህል እንዳላቸው ኣውቀው በማንነታቸው ይኮራሉ።* (ቃ.መ. ስባሙ. 28/12/2004 ዓ.ም.)

ኣበእ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ገብቶ በሚያውቁት ተረት ኣማካይነት ኣዲስ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ለመማር ሲያግዛቸው ተማሪዎቹ ይበልጥ ለማወቅ እንደሚነሳሱ መረጃ ኣቀባዮቹ ያረጋግጣሉ። የተማሪዎቹ በቋንቋው የመገልገል ችሎታም ይዳብራል። ስለዚህ ኣበእ በመማሪያ መፃሕፍት ማስገባት ኣስፈላጊ የሚሆነው የቋንቋውን ትምህርት ስለሚያግዝ፣ የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት ስለሚያነሳሳና ይበልጥ እንዲማሩ ስለሚያደርግ ነው። የተለያዩ የመስኩ ልሂቃንም ይህንን ሃሳብ ይደግፉታል። ለምሳሌ

LittleBear (2009)፡- እነዚህን ኣገር በቀል ስርዓቶች የሚገልፁ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ወደ ክፍል አምጥቶ በማስተማሪያነት መገልገል በትምህርቱ ሂደት ላይ ህይወት መዝራት እንደሆነ ያስረዳሉ። እንዲሁም ወደክፍል ማምጣት ማለት እውቀቱ እንዳይጠፋ መጠበቅና ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሆነ በመግለፅ ነው ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች የሚያጠናክሩት።

LittleBear ከዚህ በተጨማሪ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ህይወት የመዝራት ጠቀሜታ እንደሚገኝም ገልፀዋል። የቋንቋ ትምህርት ህይወት ተዘራበት የሚባለው በክፍል ውስጥ የተማሪ-ተማሪ ግንኙነት ሲሰፋና ተማሪዎች በጥንድ፣ በቡድንና በጋራ ስራ ተጠምደው የተለያዩ ተግባራት በማከናወን በቋንቋው ሲገለገሉ ሲታዩ ነው።

የስርዓትትምህርት ባለሙያውና በተኰር የቡድን ውይይት የተሳተፉት መምህራን ባቀረቡት ሃሳብ ውስጥ ሁለት ነገሮች ጐልተው ይታያሉ። አንዱ፡- ህፃኑ ከህብረተሰብ ይዞት የመጣው እውቀት ፊደልን ለይቶ ከመጥራት ጀምሮ ከንባብ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ክሂሎችን ለመሸመት እንደሚያስችለው ያስረዳሉ። ሁለተኛው ሃሳብ ከእውቀት ግንባታ ጋር የተያያዘ ነው። አንድ ህፃን ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ ከአካባቢው ማህበረሰብ የተገኘ ስለሆነ በመጠኑም ቢሆን የተደራጀ እውቀት ይዞ ነው የሚመጣው። ይህ ከቤት ይዞት የመጣው እውቀት የተለያየ መልክና ቅርፅ ይዞ በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ሲያገኘው የሚያውቀው ይዘት መሆኑ ሲገነዘብ "አውቃለሁ" የሚል እምነት ያሳድራል፤ ቀጥሎ የሚቀርበው አዲስ እውቀትም በዚህ ላይ ተመስርቶና ደረጃውን ጠብቆ ስለሚያድግ ለመረዳት አይቸገርም።

ይህ ማብራሪያ፣ የሰው ልጅ እውቀትን እንዴት እንደሚገነባ የሚያመለክተውን የጥናቱን ፅንሰሃሳባዊ ማእቀፍ የሚያንፀባርቅ ነው። ህፃኑ ከትምህርት ቤት የሚያገኘውን እውቀት ካለፈውና ከቤት ይዞት ከመጣው ጋር በማዛመድ ነው የሚገነዘበው። እውቀት የሚገነባው ቀድሞ ከሚያውቁት በመነሳትና አዲሱን ከነባሩ እውቀት ጋር በማዋሃድ እንደሆነ ለማሳየት ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የPetty (2004) ተረት ማስታወስ ይበቃል።

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ LittleBear (2009)፣ Settee (2007)፣ Hein (1991) እና Holzer (1994) እንዳመለከቱት በኣገር በቀል ህዝቦች ዘንድም አንድ ሰው እውቀቱን እያሰፋ ነው የሚባለው፤ ህብረተሰቡ ከደረሰበት የብስለት ደረጃ አኳያ ስለ አለም፣

ስለተፈጥሮ፣ ስለ ፈጣሪና ስለ ራሱ ያለው ግንዛቤና ግንዛበቤውን የሚገልፅበት ቋንቋ ማሳደግ ሲችል ነው። የህፃናት እውቀትም መገንባት ያለበት መነሻ እውቀታቸውን በመጠቀም ነው። ካልሆነ ግን ሁሉ አዲስ ነገር ይነገራቸዋል፤ ሆሌም የሚያውቁት ነገር አይኖርም። እንደ Banda (2008) አገላለፅ እውቀቱ ዘላቂነት ከሌለውና በኑሮ ውስጥ በመሳሪያነት የማይገለገልበት ከሆነ ተማሪው ፈተና ማለፍ በሚያስችል መንገድ ይሸመድደውና ፈተናውን ያልፋል። የእውቀቱ አገልግሎትም ከፈተናው ጋር ያበቃል። ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የአበእ መካተት ለህፃናት ትምህርት ምንያህል ወሳኝ እንደሆነ ለማመልከት ነው።

ይህ ጥናት ከላይ የቀረቡትንና የግንባታውያን አስተሳሰብ የሚያራምዱትን አስተሳሰቦች የሚቀበል ቢሆንም 'እውቀትን መገንባት የሚቻለው ቀድሞ ከተማረው ላይ አዲስ እውቀት በመጨመር' እንደሆነ የሚገልፀውን የKrashen (1982) የመማር ንድፈሃሳብን ግን አይቀበልም። ምክንያቱም ሁለቱ ንድፈሃሳቦች መሰረታዊ ልዩነት ስላላቸው ነው። የKrashen ንድፈሃሳብን አንድ ተማሪ የተወሰኑ ቁጥሮችን ከለየ በኋላ የመደመር ትምህርት ማስተማር እንደሚገባ ነው የሚያስረዳው። ይህም ተማሪው ቀድሞ የተማረው የቁጥር እውቀት እስካለ ድረስ ነው ስሌቱን መጀመር የሚቻለው የሚል መልእክት አለው። ተማሪው ቀዳሚ ግብአት አለው፤ በዚያ ላይ አንድ አዲስ ነገር ተጨምሯል። የሁለተኛ ክፍል ትምህርት ለመስጠት የአንደኛ ክፍል ትምህርት በቀዳሚ ግብአትነት ያገለግላል እንደማለት ነው።

የግንባታዊነት አስተሳሰብ ዋና ጉዳይ ግን ቀዳሚው እውቀት ሳይሆን ቀዳሚው እውቀት የተገኘበት ምንጭ ነው። ቀዳሚ እውቀት አዲስ እውቀትን ለመቀበል አስፈላጊ መሆኑ እርግጥ ነው። ነገር ግን ያ እውቀት ህፃኑ ካደገበት ማህበረሰብ የተገኘና ከእሱነቱ የተዋሃደ ካልሆነ መነሻውም ሆነ ቀጣዩ እውቀት የህፃኑ ዘላቂ እውቀት ሊሆኑ አይችሉም። ቀዳሚው እውቀት አበእ ሆኖ አዲሱ እውቀትም ከቀዳሚው ተያያዥነት ባለው መንገድ ሲቀርብ ነው ዘላቂነት ያለው እውቀት የሚገነባው።

በተለይ ከቤት ወደትምህርት ቤት ለሚመጡ አገር በቀል ህፃናት (1ኛ -4ኛ ክፍል)፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መፅሃፋቸው ውስጥ አበእ መካተት ያለበት የህፃናት የመማር ፍላጎት ስለሚያነሳሳና የበለጠ እንዲማሩ ስለሚያደርግ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ ለመኖርና በመረጡት የስራ ዘርፍ ለመሰማራትም ያግዛል። "የኔ" የሚሉት እውቀት እንዳላቸው

የሚገነዘቡትም በዚህ ብቻ ነው ባይባልም አንዱ መንገድ ይኸው መሆኑ ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል። የሚያውቋቸው ቁሶች የማያውቋቸውን ፊደሎች ለማወቅም በመሳሪያነት እንደሚያገለግሉ ታይቷል። እውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፍ የሚችለውና ከመጥፋት የሚድነው በፅሑፍ ላይ ሲውል ነው። በመፃሕፉ ውስጥ በማካተቱ መጠበቅ እንደሚቻል መገንዘብ ተችሏል።

## 4.3. ከእቅድ ሰነዶችና ከመፃሕፍት የተገኙ መረጃዎች

በዚህ ርእስ ስር መረጃ የተሰበሰበባቸውና ትንተና እና ትርጉማ የተካሄደባቸው ሰነዶች በጥቅል ሲታዩ ሰባት ናቸው። እነሱም፡-

- የፌደራል ገንዘብና ኢኮኖሚያዊ ልማት ሚኒስቴር እቅድ፣
- የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር እቅድ
- የትግራይ ክልል እቅድና ፋይናንስ ቢሮ፣
- የትግራይ ክልል የትምህርት ቢሮ እቅድ፥
- ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ መርሃትምህርቶች
- ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት
- ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የትግርኛ ቋንቋ የመምህር መምሪያዎች ናቸው።

የመጀመሪያዎቹ አራት ሰነዶች የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርትን በተመለከተ ያቀዷቸውን ተግባራትና አፈፃፀም በማየት ብቻ ትንተና ተካሂዶባቸዋል። የአራቱም የክፍል ደረጃ መርሃትምህርቶችም ዓላማዎቻቸውን በማየት ትንተና እና ትርጉማ ተካሂዶባቸዋል። በመማሪያ መፃሕፍቱና የመምህር መምሪያዎቹ ላይ ግን ከይዘት ግምገማው በተጨማሪ ከመረጃ አቀባዮች የተገኙ መረጃዎች የትንተናው አንድ አካል ሆነው ቀርበዋል።

### 4.3.1. በሃገር ደረጃ በወጡ እቅዶች ውስጥ ኣበእ የተሰጠው ቦታ

የሃገራችን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የትምህርት ሴክተርን ጨምሮ የመነጨው ከሚሊንየሙ የእድገት ግቦች ውስጥ ነው (MoE, 2005)። ይህንን ሰነድ መነሻቸው ያደርጉት የትምህርት እቅዶችና ስርዓት ትምህርቶች አገር በቀል እውቀት ማካተት አለማካተታቸውን እናያለን።

የገኢ.ልሚ ባዘጋጀው የአምስት ዓመት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ከተነሱት በርካታ የትኩረት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ትምህርት በመሆኑ በገኢ.ልሚ ቀዳሚ እቅዱ (1998-2002 ዓ.ም) ምን እንደተከናወነና ምን ውጤት እንደተገኘ፣ በቀጣይ የ5 አመት እቅዱ /2003-2007 ዓ.ም / ምን ለማድረግ እንደተዘጋጀ እንመለከታለን። በ1998-2002 ዓ.ም. እቅድ መሰረት ከገኢ.ልሚ ቀዳሚ ግቦች አንዱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ተደራሽነትና ተሳትፎ ማሳደግ ነው። የዚህ ግብ መገለጫ ሆነው የቀረቡት የተማሪዎች ጥቅልና ንጥር ተሳትፎ ናቸው /ገኢ.ልሚ 2003 ዓ.ም/። ውጤቱም በሁለቱም በኩል ከፍተኛ ለውጥ መታየቱን ይጠቅሳል። የአዳዲስ ተመዝጋቢዎችና ተምረው ለፈተና የተቀመጡ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ቁጥር ማደጉን ያሳያል። ትምህርት ቤት ባልነበራቸው አካባቢዎች ትምህርት ቤት መሰራቱ ያመለክታል። ከዚህ ውጪ የሆነና ከትምህርት ይዘት ጋር ተያይዞ የተገለፀ የክህሎት ወይም የብቃት ማሳያ የለም። ከ2003 -2007 ዓ.ም ባሉት አምስት ዓመታት ይደረስበታል ተብሎ የወጣው የትምህርት ዓላማ መገለጫ አሁንም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በጥራት ማዳረስ የተማሪዎቹን ብቃት ማሳደግና ቀጣይ ማድረግ ነው (MoFED, 2010)። እንዲሁም የትምህርት ጥራትን እውን ለማድረግ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ርእሰ መምህራንና ሱፐር ቫይዘሮች እንዲኖሩ ለማድረግ ታልሟል።

በሰነዱ ላይ እንደተመለከተው ዓላማው፡- የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በጥራት ማዳረስ፣ የተማሪዎቹን ብቃት ማሳደግና ብቃቱን ቀጣይ ማድረግ የሚሉ ናቸው። ዓላማዎቹን ለማሳካት የቀረቡት መሳሪያዎች (ግብአቶች) 'ለእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና መስጠት' ከሚል ነጥብ ሌላ ተማሪው ምን ይዘት ቀርቦለት ዓላማዎቹን እንደሚያሳካ አልተመለከተም። ስለ ኣበእ ወይም ስለ ኣበ ህዝብና ቋንቋም የተጠቀሰ ነገር ኣላጋጠመም

### 4.3.2. በክልል ደረጃ በተዘጋጁ የትምህርት እቅዶች ውስጥ ኣበእ የተሰጠው ቦታ

በክልል ደረጃ በተዘጋጁት እቅዶች ለባህልና ለኣበእ የተሰጠው ተኩረት ምን እንደሚመስል በግልፅ መታየት ነበረበት። ሆኖም የክልሉ የእቅድና ፋይናንስ ቢሮም ሆነ ትምህርት ቢሮው ከሃገር አቀፉ የትኩረት ነጥቦች የተለየ ያካተቱት ይዘት የለም። ለምሳሌ የእቅድና ፋይናንስ ቢሮ፣ የ1998 -2002 ዓ.ም የእቅዱ አፈፃፀም በፈተሸበት ምዕራፍ የተማሪ ቁጥር መጨመሩ የመማሪያ ክፍሎች መስፋፋታቸው የመፃህፍት ስርጭት መሻሻሉ የሚያመለክት በአሃዝ የተደገፈ መረጃ ቀርቧል። የቢሮው እቅድ ከዚህ አልፎ ስለ ስርዓተ ትምህርትም ሆነ ስለ ክልሉ ቋንቋዎች ያነሳው ነገር የለም።

የክልሉ ትምህርት ቢሮ የ5 ዓመት (2003- 2007 ዓ.ም) የትምህርት እድገትና ሽግግር እቅድም የ1998 -2002 እቅድ አተገባበርን በመገምገም ነው የሚጀምረው። ግምገማው በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት፣ የተማሪ ቅበላና ተሳትፎ እድገት ማሳየቱን ይጠቅሳል። የስርዓተ ትምህርትና የመፃህፍት አዘገጃጀትም ተገምግሞ በሃገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን ካሪኩለም ክልላዊ መልክ እንዲይዝ ተደርጎ መዘጋጀቱን ይገልፃል (ቢ.ትክት 2003 ዓ.ም)። ከ2003-2007 ዓ.ም ዕቅድ መነሻ ሃሳብ ደግሞ 'ያለፉት ዓመታት የትምህርት ጥራት ዝቅተኛ ነበር' የሚል ነው። በመፍትሄነትም "ከአካባቢና ከልዩ ፍላጐት ጋር የሚጣጣም ስርዓተ ትምህርት ስራ ላይ ማዋል" የሚል ሃሳብ ተቀምጧል /ቢ.ትክት፣ 2003/። የትምህርት ቢሮውም ሆነ የክልሉ እቅድና ፋይናንስ ቢሮ የተስማሙበት አንድ ጉዳይ በ1998- 2002 ዓ.ም. አምስቱ ዓመታት የትምህርት ጥራት ለውጥ ያላሳየ መሆኑ ነው (ቢ.ትፋ፣ 2003 ዓ.ም.፣ 28)።

በክልሉ ትምህርት ቢሮ እቅድ አንድ ለየት ያለ ሃሳብ እናገኛለን። ይኸውም የስርዓተ ትምህርትና የመፃህፍት አዘገጃጀት ተገምግሞ በሃገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን ካሪኩለም ክልላዊ መልክ እንዲይዝ ተደርጎ መዘጋጀቱ መገለፁ ነው (ቢ.ትክት 2003 ዓ.ም 290)። ሆኖም በክልሉ ከ1996- እስከ 2007 ዓ.ም. አንደኛ መንፈቅ ድረስ አዲስ የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርትም ሆነ መፃህፍት ስራ ላይ ያልዋሉ ለመሆናቸው እየተጠኑ ያሉት መማሪያ መፃህፍትና መርሃትምህርቶች ዋቢዎች ናቸው።

ከዚህ አልፎ በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተዘጋጁት እቅዶች የትግርኛ አበእ የተመለከተ ዝርዝር መረጃ እንዲያቀርቡ አይጠበቅም፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳ በሰነዶቹ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ስርዓተ ትምህርት የተቃኘ ቢሆንም የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርትን ነጥሎ ማየት የዚህ ሰነድ ትኩረት ስለማይሆን ነው። ነገር ግን እቅድ አውጪዎቹንና የስርዓተትምህርት አዘጋጆችን ሊያሳስብ የሚችል፣ ግን የታሰበበት የማይመስል ችግር በእቅዱ ውስጥ ተጠቅሷል። ይኸውም፣ ስርዓተትምህርቱ በተለይ ለገጠር ህፃናት ከትምህርት ገበታ መለየት ምክንያት መሆኑ ነው። ሰየአገር በቀል መምህራኑም ሆኑ አገር በቀሉ ህረተሰብ በስልጠናውም ሆነ ካሪኩለም በማሻሻል ተግባር እንዲሳተፉ መደረጉ ሰነዶቹ አያመለክቱም። በአጠቃላይ አገር በቀል እውቀቱም ቋንቋውም ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ማለት አይቻልም።

ከካናዳና አውስትራሊያ የተገኘው ልምድ እንደሚያመለክተው ሁሉ (LittleBear, 2009) ለአገር በቀል ህፃናት የሚዘጋጅ ስርዓተትምህርት የማህበረሰቡን ባህል፣ ታሪክና የአኗኗር ሁኔታ ካላንፀባረቀ ህፃናት ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ ይችላሉ። በአንፃሩ የስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎቹ እንደጠቀሱት የአፀደህፃናት ስርዓተትምህርት ሳይቀር የሚመራው ምርጥ በተባሉ ዓለም አቀፍ ልምዶች (CDICP, 2010) ነው። ህፃኑ ያደገበት ማህበረሰብ ምርጥ ልምድ በመነሻነትም የሚያገለግል ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ ህፃናቱ ከቤት ይዘውት የመጡት እውቀት በትምህርት ቤት ውስጥ ጠቀሜታ የለውም ማለት ነው። በገጠሩ አካባቢ ያሉ ህፃናት ትምህርታቸውን የቋርጣሉ የተባለበት ምክንያትም ስርዓተትምህርቱ ልጁ ይዞት የሚመጣውን እውቀት መነሻ ባለማድረጉ ሊሆን ይችላል። የንቋውን ዘይቤ፣ ፈሊጥ፣ ቅኔና ዓውዳዊ የቃላት አጠቃቀም የአበእ ማስተላለፊያ መሳሪዎች ናቸው። የቃላት፣ የሰዋስው፣ የዕሕፈት፣ የንባብ፣ ወዘተ. ማስተማሪያም ናቸው። እነዚህን የቋንቋ ክፍሎችና አበእን ለማስተማር ካልታቀደ ደግሞ ቋንቋን ለማስተማር ታቅዷል ማለት ያስቸግራል። ከዚህ በመነሳት ትኩረት የተነፈገውም አበእ ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ትምህርቱም ጭምር ነው ማለት ይቻላል።

### 4.3.3. ከመርሃትምህርት፣ ከተማሪዎች መፃሕፍትና ከመምህር መምሪያዎች የተገኙ መረጃዎች

ከላይ በተጠቀሱት ምንጮች አበእ መካተቱን ለማወቅ፣ "*በስርዓተትምህርቱ ውስጥ የተጋሩ መታወቂያ የሆነው አገር በቀል እውቀት ተካቷል ብለው ያምናሉ?*" የሚል ጥያቄ ለመረጃ አቀባዮቹ ቀርቦላቸው ነበር። ከቃለመጠይቅና ከተኰር የቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎች ከተለያዩ ልሂቃን ከተገኙ ንድፈሃሳባዊ መረጃዎች ጋር በማዋሃድ ትንተና ተካሂዶባቸዋል።

በመደበኛ ትምህርት ውስጥ የአንድ ማህበረሰብ እውቀትና እሴት በአጠቃላይ ባህል ወደቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያገለግል ትልቁ መሳሪያ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተትምህርት ነው (Wiessner, 2007; Liu, 2005)። ይህ እውን የሚሆነው ግን መፃህፍቱ ታስቦባቸውና አበእ ማስረፅን ዓልመው የተዘጋጁ ከሆነ ነው (Liu, 2005)። በአንደኛ ደረጃ፤ በተለይ ደግሞ በመጀመሪያ እርከን (1ኛ-4ኛ ክፍል) የሚገኙ ተማሪዎች (ህፃናት) ከአካባቢያቸው ርቀው የሚገኙ ክፍለዓለማትና ሃገራት ባህልና ዕውቀት ቀርቶ በአካባቢያቸው የሚገኙ ክልሎችና ዞኖች ባህልና ዕውቀት ለመገንዘብ እንኳ ሊቸገሩ ይችላሉ። የራስ ባህልና እውቀትን ሳያውቁ

የሌሎች ሃገሮችን ባህልና እውቀት እንዲማሩ ቢገደዱ ደግሞ ከጊዜ በኋላ የማንነት ጥያቄ ቀውስ ሊያስከትልባቸው ይችላል። የማንነት ጥያቄ ቀውስን ለመፍታት ከሚያገለግሉ መሳሪያዎች አንዱና ዋነኛው አገር በቀል ስርዓተትምህርት ነው (Hurreiz, 2006)። ምክንያቱም አበእን ለማስረፅ የሚመርጣቸው ይዘቶች የተማሪውን ማንነት፣ አመጣጥ፣ ባህልና ስነምግባር የሚያጎሉ ስለሚሆኑና በነሱ አማካይነትም የህፃኑ የማንነት ጥያቄ ምላሽ ስለሚያገኝ ነው። ከዚህ አኳያ በትግርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ውስጥ አበእን ለማስረፅ ምን ምን ይዘቶችን እንደተካተቱና እንዴት ለማቅረብ እንደታቀደ እንመለከታለን።

### *4.3.3.1. በመርሃትምህርት ውስጥ አበእን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎችና ይዘቶች*

የስርዓተትምህርት ተዋቃሪ ከሆኑት ሰነዶች ውስጥ መርሃ ትምህርት አንዱ ነው፡፡ ከ1ኛ- 4ኛ ላሉ ክፍሎች እንዲያገለግል በአንድ ላይ ተጠርዞ የቀረበው የትግርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት መግቢያ፤ የማስተማር ዘዴዎችን የማስተማር አስፈላጊነትን ይጠቁማል። ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ ሊደራጁ እንደሚገባና ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ አጋዥ የትምህርት መሳሪያዎችን ማዘጋጀት እንደሚያሻም ያስረዳል። በመጨረሻም ህፃናቱ ወደ ሁለተኛው እርከን ለማሸጋገር የሚያበቃ መሰረታዊ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ሊሸምቱ እንደሚገባ ያስገነዝባል።

በዚህ የአራቱ ክፍሎች የመርሃትምህርት ጥራዝ መግቢያ ውስጥ ሁለት ጠቃሚ ጉዳዮች ተነስተዋል። እነሱም የትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችና ተማሪዎች አራተኛ ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ የሚኖራቸው ብቃት ምን እንደሚሆን የሚጠቁሙ መዘርዝሮች ናቸው። ዓላማዎቹ አምስት ሲሆኑ በቋንቋ ክህሎትና እውቀት ላይ ያተኩሩ ናቸው፡፡ እነሱም ተማሪዎች፡-

| | |
|---|---|
| 1. የማዳመጥ፣ | 4. የመፃፍ ክሂልን ያዳብራሉ፤ እና |
| 2. የመናገር፣ | 5. የስነልሳንና የስነ ፅሁፍ እውቀታቸውንም ያጎለብታሉ |
| 3. የማንበብና | (ሲቋት፣ 1994 ዓ.ም. መግቢያ) የሚሉ ናቸው። |

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት አጠቃላይ ዓላማዎች በዚህ መልክ መቅረባቸው ተገቢ ነው። ምክንያቱም መርሃትምህርት የስርዓተትምህርት አካል በመሆኑ የህዝብ እውቀትን የማስተላለፍ ግዴታ ቢኖርበትም (Pai, 1990) ተቀዳሚ ኣላማው ቋንቋን ማስተማር (Woube, 2004) አጠቃላይ የትምህርቱ ግብም በቋንቋው በሚገባ መገልገል ማስቻል ስለሆነና አበእን ብቻ ለማስተማር አልሞ መነሳት ስለማይችል ነው። በዝርዝር ዓላማዎቹ

ውስጥ ግን ንኡሳን ክሂሎች መታየት ይገባቸዋል። እነዚህ ንኡሳን ክሂሎች ተደምረው ነው የቋንቋ ክህሎትንና እውቀትን የሚያስገኙት። ከአገር በቀል እውቀት ውስጥ የትኛውን የእውቀት ዘርፍ ለማስተማር እንደተፈለገ ማወቅ የሚቻለውም በዝርዝር ዓለማዎች ውስጥ ምን ያህል ቦታ እንደተሰጠው በማየት ነው። ሆኖም ለአራቱም የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁት መርሃትምህርቶች ዝርዝር ዓላማ ውስጥ አበእን ማስተማር ትኩረቱ ያደረገ ዓላማ ማግኘት አልተቻለም (ሰንጠረዥ 6 እና 7ን ይመልከቱ)።

**ሰንጠረዥ 5፡- በመርሃትምህርት ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች አይነትና መጠን የሚያመለክት**

| የምንባብ ዓይነቶች | 1ኛክፍል | 2ኛ ክፍል | 3ኛ ክፍል | 4ኛ ክፍል | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| የእውቀት ግንባታ | 6+1* | 16 | 14 | 16 | 52+1* |
| የክህሎት ግንባታ | 1 | 1 | 2 | ______ | 4 |
| ስብእና ግንባታ | 2 | 3 | 1 | 3 | 9 |
| ማህበራዊ ግንባታ | 2+1* | ___ | 2 | _____ | 4+1* |
| ድምር | 13 | 20 | 19 | 19 | 69+2* |

* እነዚህ በስእል ብቻ የቀረቡ ሃሳቦች ናቸው።

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እነደሚያመለክተው በአራቱም የትምህርት አምዶች ስር የተለያየ መጠን ያላቸው ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ሁሉም የትምህርት ዓምዶች የአገር በቀል እውቀት ማስተላለፊያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በየዓምዶቹ የቀረቡት ምንባቦች አበእን ለማስተላለፍ ምን ያህል እንዳገለገሉ ማሳየት ነው፡፡ ቀጥሎ የሚቀርበው ሰንጠረዥም በመርሃትምህርቱ ውስጥ ምን ምን ዓላማዎች እንደተነደፉና እያንዳንዱን ዓላማ ለማስፈፀም ምን ይዘት እንደተመረጠ የሚያመለክት ነው። ምንባቦች ምን ዓላማ ለማስፈፀም እንዳገለገሉ ለማሳየት ከመርሃ ትምህርት ለአብነት ያህል የሚከተሉት ዝርዝር ዓላመዎችና ይዘቶች ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ6፡- *ከመሃትምህርት የተወሰዱ ዓላማዎችና ይዘቶች አመልካች* (በቅንፍ ውስጥ ያሉት ቁጥሮች የሚገኙበት ገፅ አመልካች ናቸው።)

| ተ.ቁ | የትምህርቱ ዓላማ | የትምህርቱ ይዘት |
|---|---|---|
| 1 | *የዳመጡትን ተረት ወይም ታሪክ መልሰው ይናገራሉ* (1) | *አዳምጦ መልሶ መናገር* |
| 2 | *የዳመጡትን ፊደል ቅርፅና ድምፅ ለይተው ይጠራሉ* (1) | *የፊደላት ቅርፅና ድምፅ* |
| 3 | *ፊደሎችን በማገጣጠም ቃላትን ይመሰርታሉ* (1) | *ፊደላትን አገጣጥሞ ቃላትን መመስረት* |
| 4 | *ተመሳሳይና ተፃራሪ ቃላትን ለይተው ይናገራሉ* (14) | *ተመሳሳይና ተፃራሪ ቃላትን መለየት* |
| 5 | *ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን፡ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይናገራሉ፣ ይጠያየቃሉ* (21) | *ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን፣ ተረትና*<br>• *ምሳሌዎችን መናገር ፣* |

ከላይ የቀረቡት ዓላማዎችና ይዘቶች ስለአገር በቀል እውቀት ያነሱት ነጥብ የለም። ምናልባት በተረቶች አማካይነት የሚተላለፍ የማህበረሰቡ እውቀት ይኖራል ብሎ ማሰብ ተገቢ ነው። ሆኖም የዓላማዎቹ አቀራረብ ሲታይ አበእን በዕውቀትነት ለማስተዋወቅ ያቀዱ አይደሉም። ምክንያቱም ከቀረቡት ዓላማዎች የመጀመሪያውንና አምስተኛውን ስንመለከት ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ያደመጡትን መልሰው እንደሚናገሩና እንደሚጠየቁ እንጂ በተረቱ፣ በእንቆቅልሹ ምን መልእክት ለማስተላለፍ እንደተፈለገ እንዲናገሩ ወይም በመልእክቱ ላይ እንዲወያዩ አልተደረገም። ትኩረቱ በአዳምጦ መረዳት እና የመናገር ክሂል ላይ ነው። ይዘቶቹም አድምጦ መልሶ መናገር እና ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችንና፣ ተረትና ምሳሌዎችን መናገር ናቸው። በአጠቃላይ ዓላማዎቹም ሆኑ ይዘቶቹ ከአበእ ማስተማር ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም። ስለሆነም መርሃትምህርቱ ህብረተሰቡን የሚገልፁ ወይም ህብረተሰቡ በጣም አስፈላጊ በመሆናቸው ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚፈልጋቸው እውቀቶችን አለማካተቱ ሲታይ አገር በቀል እውቀት ትኩረት እንዳልተሰጠው መረዳት ይቻላል። በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዓላማዎችና ይዘቶች ወደተማሪው ለማስረፅ ደግሞ ምንባቦች፣ ተግባራትና ክንውኖች ተመርጠዋል። በአራቱም መማሪያ መፃሕፍ(ከ1ኛ-4ኛ) 69 ምንባቦች ቀርበዋል። ሁሉም በመርሃትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ዓላማዎች እግብ እንደሚያደርሱ ታምኖባቸው የቀረቡ ናቸው። ምንባቦቹ ከተለያዩ የእውቀት መስኮች የተወሰዱ ቢሆኑም **ለማወቅ፣ ለመቻል፣ ስብእናን ለመገንባትና ማህበራዊነትን ለመልመድ** በሚሉና ዩኔስኮ ባስቀመጣቸው አራት የትምህርት ዓምዶች (Four pillars of Learning) አጠቃልዬ አቅርቤአቸዋለሁ (AMAre,

2008; UNESCO on line)። በያንዳንዱ አምድ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ስርጭት፣ አቀራረብና ምን ለማስተማር እንዳለሙ የሚያሳዩ ሰንጠረዦች ቀጥሎ ቀርበዋል።

#### 4.3.3.2. በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ አበእን ማስተማር ተኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና መልመጃዎች

በመፃሕፍቱ ላይ ከተካሄደው የይዘት ትንተና በተጨማሪ 'በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ አበእን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና መልመጃዎች አሉ?' የሚል ጥያቄ በማቅረብ መረጃ ተሰብስቧል። አራቱም መፃሕፍት ከፊት ለፊት ሽፋናቸው የተለያዩ መረጃዎችን ይዘዋል። በውስጥ ገበራቸውም አዘጋጆቻቸውና የተዘጋጁባቸው ዓመተ ምሕረት ሰፍሯል። አራቱም መፃሕፍት 'A5' በሚባለው የወረቀት መጠን የታተሙ ሲሆን ዋጋቸው፣ የታተሙበት ቦታና አታሚ ድርጅት ከመፃሕፍቱ ጀርባ ተፅፈዋል። ውስጣዊ ይዘታቸው ሲታይ፡- መፃሕፍቱ 71 ምንባቦችን እና የተለያዩ መልመጃዎችን ይዘዋል። በሰንጠረዥ 5 ውስጥ እንደ ተመለከተው፣ በመፅሃፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ስርጭት ሲታይ፡- 53 ምንባቦች ማሳወቅን ዓላማቸው ያደረጉ ናቸው።ማስቻልን ዓላማቸው ያደረጉ 4፣ ስብእና ግንባታን ዓላማቸው ያደረጉ 9፤ እንዲሁም ማህበራዊነትን ለማስተማር ደግሞ 5 ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በ1ኛ ክፍል 2ቱ በስእል ብቻ የቀረቡ ናቸው። በ2ኛ ክፍል ማህበራዊነትን፣ በአራተኛ ክፍል ክህሎትንና ማህበራዊነትን የሚያስተምሩ ምንባቦች አልቀረቡም።

በአንድ የትምህርት ዘመን ምን ያህል ይዘት (እውቀት ወይም ክህሎት) ምን ለማግኘት መማር እንደሚያስፈልግ፣ እንዴት መቅረብ እንዳለበት የሚወስነው ለደረጃው የተዘጋጀው መርሃትምህርት ነው። ተማሪዎች አገር በቀል ቋንቋውን እንዴት እንዲማሩት እንደታሰበ የሚገለፀው በመርሃትምህርት ነው። በመርሃትምህርቱ ውስጥ የተነደፉት ዓላማዎችና ይዘቶች፣ በተማሪ መፅሓፍ ውስጥ ምንባቦችና መልመጃዎች ሆነው ተማሪውን ከትውውቅ ወደ ልምምድ ከዚያም ወደ እውቀት ወይም ወደ ክህሎት ይመሩታል።

ከዚህ አኳያ ከመርሃትምህርት የተወሰዱ ዓላማዎችንና ይዘቶችን የያዘው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው፣ አበእን የሚያዳብሩ/ የሚያዳብሩ የሚመስሉ ይዘቶች ተጠቅሰው ይገኛሉ። እነሱም "ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን መናገር" በሚል መልክ የተገለፁት ናቸው። እነዚህ ይዘቶች ወደ ምንባብ ሲለወጡና ከምንባቦቹ የተለያዩ ተግባራትና መልመጃዎች ሲወጡ ሊገለፅ የተፈለገው አበእ ሊወጣ ስለሚችል ትንተናው

በእነሱ ላይ አትኩሯል። እንዲሁም በመፃሕፍቱ ውስጥ ካሉት ምንባቦች ትኩረት ተሰጥቷቸው የታዩ ምንባቦችም አሉ። እነሱም በተረት ወይ በሌላ የስነቃል መልክ ባይቀርቡም ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ስለሚያነሱ የተመረጡ ናቸው።

#### 4.3.3.2.1. እውቀትን ትኩረታቸው ባደረጉ ምንባቦች

በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ከአራቱም የክፍል ደረጃዎች የተወሰዱ ናቸው። ሁሉም ምንባቦች እውቀትን ለማስተማር የቀረቡ ናቸው። ከየምንባቡ ስርም ከመምህር መምሪያዎች የተገኙ ዓላማዎች ተዘርዝረዋል።

**ሰንጠረዥ 7፡- እውቀትን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና ዓለመዎቻቸው አመልካች**

| ተ.ቁ | 1ኛ ክፍል | 2ኛ ክፍል | 3ኛ ክፍል | 4ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ርእስ፡ የተለያዩ እንስሳት ድምፅ<br>በአካባቢ የሚሰሟቸውን የማን (የምን) እንደሆኑ ይናገራሉ።<br>የሰሙትን ድምፅ የሚመስል ድምፅ ያመነጫሉ። (1) | ርእስ፡ እንበሳና ጦጣ (2)<br>የሚያውቁትን ተረት ይናገራሉ<br>የተረት መልእክት ይናገራሉ<br>ያዳመጡትን ተረት መልሰው ያወጋሉ<br>በቀረቡ ፊደላት ቃላት ይመሰርታሉ | ርእስ፡ ከባቢያዊ ክስተቶች (12)<br>ድህረንባብ የምንባቡን መልእክት ይገልፃሉ<br>በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸውን ነገሮች በፅሁፍ ይገልፃሉ<br>የተሰጡ ዓ.ነገሮችን በቅደም ተከተል ይፅፋሉ | ርእስ፡ ትልቁ የዓለም ሃብት (1)<br>ትልቁ የዓለማችን ሃብት ትምህርት ለመሆኑ ማሳመኛ ሃሳብ ያቀርባሉ<br><br>ከገንዘብና ከእውቀት የትኛው ይበልጣል? በሚለው ነጥብ በቡድን ተከፋፍለው ይከራከራሉ |
| 2 | ርእስ፡ ዳቦ ለህፃናት (50)<br>ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የማስተዋል ጥያቄዎችን ይመልሳሉ። በስእል የቀረቡ ነገሮችን ስም ይጠራሉ።<br>በሰንጠረዥ ከቀረቡ ፊደላት ቃላት ይመሰርታሉ። | ርእስ፡የማያስመልስ መልእክት (5)<br>ያዳመጡትን ተረት መልሰው ይናገራሉ<br>የተረቱን መልእክት ይገልፃሉ<br>ቃላትን በፍቺ ያዛምዳሉ | ርእስ፡ የዱር እንስሳት (67)<br>የዱር እንስሳት ምንነትና ሊደረግላው የሚገባ እንክብካቤ አስመልክታው ሃሳባቸውን ይገልፃሉ<br>የዱር እንስሳትን ዓይነት ይጠራሉ ጎጂና ጠቃሚ እንስሳትን ይለያሉ<br>የፅሁፉን መልእክት ይናገራሉ | ርእስ፡ የተቅማጥ በሽታና መከላከያው (24)<br>ፅሁፉን በአግባቡ ያነባሉ<br>የምንባቡን መልእክት ይገልፃሉ<br>ከአውድ አኳያ የቃላትን ፍቺ ይናገራሉ |
| 3 | ርእስ፡ የቤት እንስሳ(54)<br>የምንባቡን መልእክት ይገልፃሉ። ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ ያዛምዳሉ።<br>የቀረቡላቸውን ስእሎች ያነፃፅራሉ። | ርእስ፡ ስርዓተ ነጥብ (12)<br>አራት ነጥብንና የጥያቄ ምልክትን ለይተው ግሊጋሎት ላይ ያውላሉ<br>ቃላትን በተፃራሪ ያዛምዳሉ<br>በተሰጡ ቃላት ዓ.ነገር ይመሰርታሉ | ርእስ፡ እኔ ማን ነኝ (72)<br>የግጥሙን ዜማ ጠብቀወ ያነባሉ<br>የስምና ግስ ገላጮችን ለይተው ያሳያሉ<br>ባለ 6 መስመር ግጥም ይፅፋሉ | ርእስ፡ የወባ ፈረስ (43)<br>ግጥሙን ካነበቡ በኋላ ትንኝ የወባ አስተላላፊ መሆንዋን ይገልፃሉ<br>ለተሰመረባቸው ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | ርእስ፡ ጤናችን (56)<br>የምንባቡን መልእክት ይናገራሉ።ስእሎችን ከስያሜዎች ጋር ታዛምዳሉ።ቃላትን በጊዜ ቅደም ተከተል ይፅፋሉ። | ርእስ፡ እንቆቅልሽ (19)<br>የእንቆቅልሽ ምንነት ተገንዝበው<br>የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ<br>ከአካባቢያቸው እንቆቅልሽ ሰብስበው በክፍል ያቀርባሉ | ርእስ፡ ስራ (78)<br>የምንባቡም ይዘት በቃል ይገልፃሉ (78)<br>ወላጆቻቸውን እንዴት እንደሚያግዙ በቃል ይገልፃሉ<br>የተሰጡ ዓ.ነገሮችን በጊዜ ቅደም ተከተል ይሰድራሉ | ርእስ፡ ቃለምልልስ (54)<br>የቃለምልልስን ምንነት ይገልፃሉ<br>የምንባቡን መልእክት ይናገራሉ<br>በቃልና በቅጥያ መሃል ያለውን ልዩነት ናገራሉ |
| 5 | ርእስ፡ ተማሪዎች ክረምት ጊዜ (67)<br>የክረምት ጊዜ የሚያሳልፋበትን ሁኔታ ይናገራሉ ከስእሎች የተገነዘቡትን ሃሳብ ሰብስበው ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ። | ርእስ፡ ሕርሻ (39)<br>የእርሻን ምንነት አስመልክቶ ባለሙያ ካነጋገሩ በኋላ በሃሳቡ ላይ ክፍል ውስጥ ይወያያሉ<br>ከምንባቡ፤ ግብርና የሚያጠቃል ላቸውን የስራ መስኮች ይዘረዝራሉ፤<br>ልዩ የሆኑ ቃላትን ለቅመው ያወጣሉ | ርእስ፡ ቃጠሎ (83)<br>ስለቃጠሎ የሚያውቁትን ይናገራሉ<br>የምንባቡን ይዘት ባጭሩ በቃል ይናገራሉ<br>የማስተዋል ጥያቄዎችን ይመልሳሉ | ርእስ፡ የገና ጨዋታ(82)<br>የሚያውቋቸው ባህላዊ ጨዋታዎችን ይዘረዝራሉ<br>ግጥሙን በአንጓ ከፋፍለው ያነባሉ<br>ያነበቡት አንጓ መልእክት ይናገራሉ |
| 6 | ርእስ፡ ማንን እንምረጥ (62)<br>እንደየአገባባቸው ቃላትን በማጥበቅና በማላላት ያነባሉ።<br>በተሰጡ ቃላት ዓ. ነገር ይመሰርታሉ። የተሰጡትን ቃላት በጊዜና በድርጊት ቅደምተከተል ያስቀምጣሉ። | ርእስ፡ ደብዳቤ (43)<br>ደብዳቤውን አይተው ማን ለማን እንደፃፈው ይናገራሉ<br>ለዘመዳቸው አጭር ደብዳቤ ይፅፋሉ<br>ጎደሎ ዓ.ነገሮችን አሟልተው ይፅፋሉ | ርእስ፡የአይጥ ደወል (95)<br>የሚያውቁትን ተረት ያቀርባሉ<br>ተረቱን አሳጥረው ያቀርባሉ<br>በተረቱ ውስጥ ያሉ እንስሳ ገፀባህርያት ስም ይዘረዝራሉ | ርእስ፡ ተሞክሮ (89)<br>በማስተዋል ያነባሉ<br>የዳሰሳ ንባብ የነባሉ<br>የፍጥነት ንባብ ያነባሉ<br>በተሰጡ ቃላት ዓነገር ይመሰርታሉ |

ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው እውቀትን ለማስተማር ለ1ኛ ክፍል ከቀረቡት ስድስት ምንባቦች ውስጥ በተረት መልክ የቀረበ ምንባብ የለም። ሁሉም በነገራ መልክ የቀረቡ ናቸው። ተረቶችና መሰል ስነቃል ነክ ፅሁፎች ኣበእን እና ቋንቋን ለማስተማር ተመራጭ እንደሆኑ ይታወቃል። በተለይ በዝቅተኛው የክፍል ደረጃ ህፃናት ከቤት ይዘውት የሚመጡትን እውቀት በትምህርት ቤት ከሚያገኙት ጋር ለማያያዝና በለመዱት ኣቀራረብ ኣዲሱን እውቀት ለመቅሰም የሚያስችሉ ናቸው (Perkins, 1992; Semali & Stambach, 1993)። በተመሳሳይ ሁኔታ ከ2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍሎች ውስጥ ማሳወቅን ዓላማቸው ያደረጉ አስራ ስምንት ምንባቦች ለኣብነት ተወስደዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ኣምስቱ በተረት መልክ የቀረቡት ሆነ ተብሎ የተመረጡ ሲሆን የተቀሩት ግን በኣጋጣሚ የተወሰዱ ናቸው። ህብረተሰቡም በተረቶቹ ኣማካይነት እውቀቱን ለማስተላለፍ ችሏል፡፡ ለምሳሌ

**ጠጣና አንበሳ** በሚለው ተረት ውስጥ ሃይልና ብልሃት የየራሳቸው ጠቀሜታዎች እንዳላቸውና በሃይሉ የሚመካ ሰው በጥበብ ሊሸነፍ እንደሚችል ያስተምራል። **የማያስመልስ መልእክት** የሚለው ተረት ደግሞ ለጥቅም ሲባል ወገንን መክዳት ተገቢ አለመሆኑ ያስተምራል።

በነዚህ ምንባቦች አማካይነት እግብ ይደርሳሉ ተብለው የተቀመጡት ዓላማዎች ግን አበእን እንደ አንድ ጉዳይ የወሰዱት አይመስልም። በመልመጃዎቹ አማካይነት የቀረቡት ይዘቶች ህፃናቱ ቀድሞ የሚያውቁትን መነሻ ያደረጉ ሳይሆኑ ፍፁም አዲስ እውቀትን የሚያስተምሩ ሆነው ተገኝተዋል። ለምሳሌ ያህል **ጠጣና አንበሳ፣ የማያስመልስ መልእክት** ለሚሉት ምንባቦች በመምህር መምሪያ የተነደፉላቸው ዓለማዎች በቅደም ተከተል ሲታዩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

- *የሚያውቁትን ተረት ይናገራሉ፤ ያነበቡት ተረት መልእክት ይናገራሉ፤ ያዳመጡትን ተረት መልሰው ያወጋሉ፤ በተለየዩ ፊደላት ቃላትን ይመሰርታሉ /ገፅ 2/፤*
- *ያዳመጡትን ተረት መልሰው ይናገራሉ፤ የተረቱን መልእክት ይገልፃሉ፤ ቃላትን በፍቺና በትኩረት ያዛምዳሉ /ገፅ 5/።* የሚሉ ናቸው።

ዓላማዎቹ፣ ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው ወይም አዳምጠው ምን እንደተገነዘቡ ለመፈተሽ የቀረቡ እንጂ ህብረተሰቡ በተረቶቹ አማካይነት ማስተላለፍ የፈለገውን እውቀት ለማስተማር የሚያስችሉ አይደሉም። በአራተኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ፤ **ተሞክሮ፣ የዓለማችን ትልቁ ሃብት፣ ቃለምልልስ** በሚሉ ርእሶች ስር የቀረቡት ምንባቦች፤ ተማሪዎች ከእድሜ ባለፀጋዎች ልምድ እንዲቀስሙና ከልምዱ ጠቃሚ ትምህርት እንዲያገኙ ታስቦ የቀረበ ይመስላል። ከዚህ አይነቱ አቀራረብ ተማሪዎች ብዙ እውቀት ሊሸምቱ እንደሚችሉ ይታመናል። ትምህርት ሰጪ ሆነው የቀረቡት ሰዎች በምዕራባውያኑ የእውቀት መለኪያ መሰረት ሁሉም ፊደል የቈጠሩ፤ አንድ ነጭ የስራ ልብስ ያጠለቁ 'አስተዋይ ሊቅ' በሚል ስም የሚጠሩ፣ አንድ የግብርና ባለሙያ እና አንድ ጡረታ የወጡ መምህር ናቸው። ልምዳቸውን የሚያካፍሉ ሰዎች ማንነት ሲታይ አገር በቀል ከሆኑ የእድሜ ባለፀጋዎች ጠቃሚ እውቀት ሊገኝ እንደሚችል የተዘነጋ ይመስላል፡፡ የህብረተሰቡ አባላት ከህክምና፣ ከግብርና፣ ከፍትሕ፣ ከንብረት አስተዳደር ጋር የተያያዘና በልምድ የዳበረ ሰፊ እውቀት እንዳላቸው ይታወቃል። የስርዓተትምህርቱ አዘጋጆች ግን ተማሪው እውቀት ማግኘት

የሚችለው ቀለም ከቆጠሩ ወይም 'ዘመናዊ' የሚባለውን እውቀት ከቀሰሙ ሰዎች ብቻ እንደሆነ የሚያምኑ ይመስላል። ይህ የተሳሳተ እምነት ነው። ምክንያቱም እንደማንኛውም የአፍሪካ ህዝብ የትግራይ ህዝብም ቃላዊ ህብረተሰብ ነው። በአፍሪካውያን ዘንድ ትላልቆቹ ቤተ መፃህፍት ያሉት የያዙትን እውቀት በትረካና በተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያስተላልፉ የእድሜ ባለፀጋዎች ውስጥ ነው (George, 1999; Hurreiz, 2006; Semali & Kincheloe, 1999)፡፡ ተሞክሮ የማስተላለፉ ተግባርም ቀለም ከቈጠሩት ሰዎች ብቻ ከሚሆን በእድሜ ከደረጁት የኣካባቢው ሽማግሌዎችም ቢሆን ተማሪው ኣበእ ለመቅሰም ያስችለው ነበር።

ከታች የተዘረዘሩትና በኣራቱ መማሪያ መፃሕፍት ያሉት ምንባቦችም ቢሆኑ የሚያነሷቸው ጉዳዮች የቋንቋ ማስተማሪያ ሳይሆኑ ጥሬ የተፈጥሮ ሳይንስ እውቀት ሆነው ህፃኑ በነገራ እንዲቀበላቸው የሚያስገድዱና የሚሰብኩ ናቸው። ለምሳሌ **“የግል ንፅህና፣ ኣምባሻ ለህፃናት፣ ጤናችን፣ ደብዳቤ፣ ስርዓተነጥብ፣ ከባቢያዊ ክስተቶች፣ ስራ፣ የተቅማጥ በሽታና መከላከያው፣ የወባ ፈረስ“ የሚሉት ምንባቦች ኣቀራረባቸው ኣሰልቺ ነው። መምህር መራሽ በሆነና ከባቢያዊነትን ባልተላበሰ የሳይንስ ክፍል የሚተላለፍ የነገራ ትምህርት** (lecture) **ሆኖ ነው የቀረበው።** ለምሳሌ **የግል ንፅህና** የሚለው ምንባብ፤ የግል ንፅህና ምንነት ከገለፀ በኋላ 'እኛ ካልታጠብን፣ ፀጉራችንን ካላበጠርን፣ እጃችንን ሳንታጠብ ከበላን፣... በሽተኞች እንሆናለን፤ ጤና ካጣን ደግሞ እንደኸያለን' የሚል ምክር ያቀርባል። ከዚህ ገለፃ ጤና ነክ እውቀት ማግኘት ይቻላል። ሆኖም ህፃኑ ካለበት የክፍል ደረጃ ኣኳያ ይህ ሁሉ መረጃ ተቀብሎ የማቆየት ኣቅም የለውም። ለቋንቋ ትምህርት ያለው ጠቀሜታም በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህ ጋር የተያያዘ ቀዳሚ እውቀት ከሌለው ደግሞ የተነገረውን መረጃ በቃል ሊሸመድደው፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ሊረሳው ይችላል።

በኣንፃሩ ህብረተሰቡ ይህንን እውቀት በተረትና ምሳሌ ስእላዊ በሆነ ገለፃ ያቀርበዋል እንጂ ኣይነግርም። ህብረተሰቡ ተረትና ምሳሌውን፤ ኣጭርና መሳጭ በሆነ መንገድ በራሱና በኣካባቢው ያለውን ግንዛቤ ይገልፅበታል። ሰፋፊና ዝርዝር ሃሳቦችን ጨምቆና ውበትን ኣላብሶ ለማስተማር ይጠቀምበታል (Dorson, 1972; Dundes, 1994.)። ተተኪውን ትውልድ በመምከር፣ ሰናይ ምግባራትን በማወደስና እኩይ ምግባራቱን ደግሞ በመኮነን፣

በማህበረሰቡ መሃል ለመኖር የሚያስችል እውቀት ይዞ እንዲያድግ በማስተማሪያነት ይገለገልበታል።

ለምሳሌ የንፅህናን አስፈላጊነት የሚያስተምር አንድ ተረትና ምሳሌ እንይ፡፡ ህብረተሰቡ በግልና በአካባቢ ንፅህና ጉድለት ምክንያት የጤና መታወክና የሞት አደጋ ሊመጣ እንደሚችል ይገነዘባል። ደህንነቱ ያልታወቀ ምግብ መብላትም ተመሳሳይ አደጋ እንደሚያስከትል ጠንቅቆ ያውቃል። እውቀቱንም ምንባቡ ከቀረበበት የነገሩ ዘዴ በተለየ ለተተኪው ትውልድ ያስተላልፋል። ከላይ በDorson እና Dundes (1972; 1994) እንደተገለፀው ሃሳቡን ጨምቆና አስውቦ በሚከተሉት ተረትና ምሳሌዎች ነው ያቀረበው፡- ***ናብ ማይያ ከይኽዱስ ናብ ሰብ (ቀሺ) ይኽዱ።*** *(18) (ወደውሃ እንዳይሂዱ ወደሰው ይሂዱ)* ምንባቡ ንፅህና አስፈላጊ መሆኑን ይነግራል። የመጀመሪያው ተረትና ምሳሌ ግን የመታጠብ (እራስን በንፅህና መጠበቅ) አስፈላጊነት ብቻ አይደለም የሚያስተምረው። ወደሰውና ወደ ውሃ መሄድ ነው እየተነፃፀሩ ያሉት። በዚህ አገባብ ሰው ማንኛውንም ሰው ሳይሆን ህመምተኛን ሊያድን እንደሚችል የሚታመንበት ሰው የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ማንኛውም የታመመ ሰው ከላይ ወደ መድሃኒት አወዋቂዎች ከመውሰድ ንፅህናውን እንዲጠብቅ ማድረጉ ተመራጭ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ማንም ሰው እራሱን በንፅህና የሚጠብቅ የሚታጠብ፣ ከሆነ በበሽታ ሊጠቃ እንደማይችል ያስረዳል።

የግል ንፅህና የሚለው ምንባብ አካባቢያችንና እጆቻችን ካልፀዱ መመገቢያ እቁሳቁሶች ካልፀዱ የግል ንፅህና በመጠበቅ ብቻ የጤንነት ዋስትና አይሆንም የሚል መልእክት አለው። የአገር በቀሉ ህዝብ እውቀት ግን ከዚህ ላቅ ያለ ነው። አካልም፣ አካባቢም፣ መመገቢየ ቁሳቁስም ማፅዳት አስፈላጊ ነው። በተረቱ የተጠቀሰው ውሃ ግን በሽታን የሚከላከል ብቻ ሳይሆን የሚያድንም ነው። ህፃኑም በውሃ በሽታን መከላከልና መፈወስ እንደሚቻል እየተነገረው ያደገ ነው። ስለዚህ **የግል ንፅህና** የሚለው ምንባብ ሳቢ ካለመሆኑም በላይ የሚያስተላልፈው እውቀትም ህፃኑ ቀድሞ ከሚያውቀው ያነሰ ነው።

ህፃኑ ከመንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) አስተምህሮ ያዳበረው እውቀት ደግሞ ከዚህ ላቅ ያለ ነው። ህብረተሰቡ ውሃን ለመድሃኒትነት ይጠቀምበታል። የማህበረሰቡ አባል በሚታመምበት ጊዜ ቶሎ ብሎ ወደ ጠበል ይሄዳል፤ አቅሙ የማይችል ከሆነም በሸክም ይወሰዳል። ህፃኑ ውሃ የግል ንፅህና መጠበቂያ ብቻ ሳይሆን መድሃኒት መሆኑ ጭምር እያየ ነው ያደገው። ታሞ የነበረው ሰው ጠበል አዳነኝ" እንጂ "ውሃ ታጥቤ ዳንኩኝ" አይልም። ለመልአኩ ስለት ገብቶ፣

ሓጢኣቱን ተናዞና ፈጣሪው ይቅር እንዲለው ተማፅኖ ከጠበሉ ስለሚወጣ ንፅህናው አካላዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም ነው። ምክንያቱም ተጠባዩ፣ ጠበሉ (ዘምዘም) በፈጣሪ የተባረከና በመላእክት የሚጠበቅ በመሆኑ አዳኝነቱ ሰዎቹ ከሚሰጡት ህክምና በላይ እንደሆነ ስለሚያምን ነው፡፡ ወደሰው ከመሄድ ወደውሃ መሄድ ተመራጭ የሚያደርጉትም እነዚህ ምስጢሮች ናቸው።

*ሕማምያ ዘይብሉስ ሕምምቲ ጥየል በሊዑ ይመውት። (በሽታ የማያውቀው ሰው በሽተኛ ፍየል በልቶ ይሞታል።)*

ኣብዛኛው የትግራይ ህዝብ የሚተዳደረው የምግብ ሰብል በማምረትና እንስሳትን በማርባት ነው። የሚያረባቸው ከብቶች በተለያየ ምክንያት ይታመማሉ፤ ይሞታሉ። አንድ ገበሬ በድንገት በሬ ወይም ላም ከሞተበት የአካባቢው ሰው በሙሉ ያዝናል፤ በሚችለው ሁሉ ለመርዳትም ጥረት ያደርጋል። እርዳታ ከሚያበረክትባቸው መንገዶች አንዱ የከብቱን ስጋ በመቃረጥ ዋጋውን ለመመለስ መሞከር ነው። በዚህ አጋጣሚ የሚፈጠሩ አደጋዎች በርካታ ናቸው። ከብቱ የሞተው ገደል ገብቶ፣ ማረሻ ወይም በሬ ወግቶት ሊሆን ይችላል። ወይም ምክንያቱ ሳይታወቅ ድንገት ሞቶ ሊሆን ይችላል። ለተወሰኑ ቀናት የመፍዘዝ ወይም ምግብ ያለመብላት ምልክት ኣሳይቶም ሊሆን ይችላል። በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ለመሞት ሲያጣጥር ይታረድና ለቅርጫ ይቀርባል። ሰዉም የቻለውን ያህል ገዝቶ ከነቤተሰቡ ይበላል።

በዚህ ስበብ ሰዎች ሊታመሙም ሊሞቱም ይችላሉ። ምክንያቱ ደግሞ ከብቱ ከእንስሳ ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች ተለክፎ ሊሆን ይችላል። በዚህ የከብት በሽታ የተለከፈው ሰው ሁሉ ሊሞት ወይም በቀላሉ በማይድን በሽታ ሊያዝ ይችላል። ይህንን የታዘቡት ተጋሩ ሌሎችን የሚያስጠነቅቅና የሚያስተምር ተረትና ምሳሌ ያቀርባሉ። ተረትና ምሳሌው አጭር ነው። የያዘው መልእክት ግን ሰፊ ነው። ሌላው ድርጊቱ ሲከወን ሲያዩ፣ "ተደረገ አሉ" ሲባል ሲሰሙ፣ ወይም ኣንዳችም ችግር ያልነበረበት ሰው የችግር መፍትሄ ይሆናል ብሎ የፈፀመው ተግባር ጉዳት ሲያስከትልበት ተረቱን በማስጠንቀቂያነት ወይም በትምህርትነት ያቀርቡታል።በአጠቃላይ ከአውድ ጋር እየተጣጣመና እየተተረጎመ ሰፊ መልእክት ያስተላልፋል።

ይህ ተረትና ምሳሌ ስስት የሚያስከትለውን አደጋም ይጠቁማል። ለምሳሌ አንድ ሰው ፍየሉ ምን በሽታ እንዳላት ባያውቅም ስታታጣጥር አይቶ ያርዳታል። ንብረቱን ላለመጣል ሲል ስጋዋን ይበላና በዚህ ምክንያት ሊሞት ይችላል። የሞቱና የአሟሟቱ ሁኔታ ያወቁና የሰሙ ሰዎች ደግሞ **"ሕማምያ ዘይብሉስ ሕምምቲ ጥየል በሊዑ ይመውት"** (ጤነኛ ሰው በሽተኛ ፍየል በልቶ ይሞታል) በማለት ይመስላሉ።

ከላይ የቀረበውና የግል ንፅህናና ጤንነት ላይ ያተኮረው ምንባብ በቅርፁ ሰፊ ነው። የያዘው መልእክት ግን በተረቱ ከቀረበው ይዘት የጠበበ ነው። ልዩነቱ ምንባቡ ሁሉንም ነገር ዘርግፎ የሚነግር ሲሆን ምሳሌው ግን ሁሉም ሰው እንደየተገኘበት አውድና ሁኔታ ሊፈታው የሚችል የታመቀ ሚስጥር የያዘ ነው።

በመፃሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት ምንባቦች የአንዳንዶቹ ርእሶች አበአ ላይ ያተኮሩ ይመስላሉ። ውስጣዊ ይዘታቸው ሲታይ ግን ብዙዎቹ፣ በነገራ በምክርና በትእዛዝ መልክ የቀረቡና አበአን ትኩረታቸው ያላደረጉ ናቸው። ለምሳሌ ከአንደኛ ክፍል ድምፂ ዝተፈላለዩ እንስሳት የሚለውና ሌሎች ፊደላትንና ቃላትን ለማስተማር የቀረቡ ስእላዊ መግለጫዎች (ገፅ 3-99) በሚያውቃቸው ስእሎቹ የማያውቃቸው ፊደሎች ለማስተማር ያገለገሉ ጥሩ ኣብነቶች ናቸው። በተማሯቸው ቃላትና ፊደላት የተመሰረቱት ዓረፍተነገሮች ግን ህፃኑ ከቤት ይዞት የመጣውን እውቀት የሚፃረሩ ናቸው። ኣንዳንዶቹ ህብረተሰቡ የማይላቸው፣ ቢሰማቸውም "ምን ማለት ነው?" የሚያሰኙት ኣይነት ናቸው። ኣንዳንዶቹ ቃላት ደግሞ ትግርኛ ኣይደሉም፤ እንዲሁ መሃል ላይ የገቡና ፍቺን የሚያዛቡ ናቸው። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- ርግኦ **ኣብታኒካ** ኣሎ። ገፅ 36 (እርጎ ጣሳ ውስጥ ኣለ)
- ርግሀ **ትእክብ** ኣላ። ገፅ 41 (ኣክርማ ትሰበስባለች)
- ኣብጫካ **ገበል** ኣሎ። ገፅ 73 (ጫካ ውስጥ ዘንዶ ኣለ)

በተጋሩ ዘንድ በእርጎ ማስቀመጫነት የሚታወቁ ቁሶች፡- ላጋ፡ ቀርጮ፣ ዋንጫና ዝብዲ ናቸው። ታኒካን ግን በእርጎ መያዣነት ኣይጠቀምም። ልጃገረዶች መስከረም ኣካባቢ ለስፌት የሚያገለግል ኣክርማ ይቀጫሉ። በትግርኛው ደግሞ ጨዲዳ ይባላል። ተግባሩ በመሰብሰብ ኣይገለፅም ወይም ማህበረሰቡ ኣይለውም። ማህበረሰቡ የማይለው ከሆነ ደግሞ የቋንቋው ትምህርት ትርጉም ኣልባ ይሆናል። ሶስተኛው ዓረፍተነገር ደግሞ ጫካ የሚል የኣማርኛ ቃል ነው ያስገባው። የኣንደኛ ክፍል ትግራዋይ ህፃን ዱር፣ ጣሻ እንጂ ይህንን

ቃል አያውቀውም። በቋንቋው መግባባት ለሚችል ሰውም ቢሆን በዚህ መልኩ አዳቅሎ ማቅረብ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም የዚህ ትምህርት ዋና ዓለማ አገር በቀሉን ቋንቋ ማስለየት ስለሆነ ነው። በእብነት የቀረበው የቋንቋ አጠቃቀም ግን አገር በቀሉ ህዝብ የማይጠቀምበትና ህፃኑም ሰምቶት የማያውቅ አዲስ አጠቃቀም ነው። የዚህ አይነቱ አጠቃቀም ደግሞ አበእን ብቻ ሳይሆን ቋንቋውንም ለማስተማር ጠቀሜታ አይኖረውም።

በዚህ የክፍል ደረጃ "ዳቦ ለህፃናት"(104)፣ "የቤት እንስሳት"(112)፣ "ጤናችን"(116) ፣ "ተማሪዎች በክረምት ጊዜ"(120)፣ "ማንን እንምረጥ" (127) የሚሉ ርእሶች ይዘው የቀረቡት ምንባቦችም በየትኛውም አካባቢ ያለ ህፃን ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት የሚያገኘውን እውቀት በነገራና በምክር የሚያቀርቡ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የህብረተሰቡን እውቀት የሚያኮስሱ ሆነው ይገኛሉ። "እህልና አጠቃቀሙ ግብርና" (2ኛ ገፅ 72፣ 101)፣ እና "የገና ጨዋታ" (4ኛ ገፅ 90)፣ የሚሉትን እንመልከት።

## *እህልና አጠቃቀሙ* (72)

ምንባቡ፣ ምግብ ከመሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱ መሆኑ፣ ለጤንነት ጥበቃም አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡ ሆኖም ህብረተሰቡ ያመረተውን እህል በአግባቡ እንደማይዝ፣ ዓመቱን ሙሉ የለፋበት ምርት በነቀዝ፣ በአይጥና በተለያዩ ተባዮች ምክንያት እንደሚበላሽ ይገልፃል፡፡ ህብረተሰቡ ቆጥቦ መጠቀም እንደማይችልም ያትታል፡፡

> *ለተዝካር፣ ለሰርግ፣ ለበዓለ ንግስ እያለ የአመት ቀለቡን በአንድ ቀን ድግስ ያጠፋዋል፡፡... መላ ቤተሰብ ለረሃብና ለችጋር ይጋለጣል። /2ኛ፣ 72/።*

በማለት ሃሳቡን ያጠናክራል፡፡ በመጨረሻም ህፃናቱ ወላጆቻቸውን የመምከርና የማስተማር ሃላፊነት እንዳለባቸው በሚከተለው መንገድ ያስገነዝባል፡፡

> *እኛም ይህንን ተገንዝበን ቤተሰቦቻችንን እንምከር። ምርታችንን በቁጠባና በጥንቃቄ መጠቀም ከቻልን ለረሃብ አንጋለጥም። ከቀየችንና ከሃገራችን አንሰደድም። እንጀራ ፍለጋ የትም ስንንከራተት አንኖርም። ለባሰ ችግር እንዳንጋለጥ ደግሞ የምናገኘውን እህል በጥንቃቄ ልንጠቀምበት ይገባል።* (ገፅ72-3)

አሁንም እርሻ በሚል ርእስ ስር የቀረበ ሌላ ምንባብ እናገኛለን፡፡ ምንባቡ የእህል ምርት ከእርሻ እንደሚገኝ በመግለፅ ይጀምራል፡፡ በመቀጠልም የእርሻን ምንነትና በሱ ስር የሚጠቃለሉ የስራ ዘርፎችን ይገልፃል፡፡ በተለይ ለእንስሳት መደረግ ያለበትን እንክብካቤ

ይዘረዝራል፡፡ ጥሩ ምርት ለማግኘት የእርሻ ማሳን እንዴት ማልማትና ምርት እንዴት መሰብሰብ እንዳለበት ያስረዳል፡፡ *በመቀጠልም፡-*

> *በሃገራችን የእርሻ ስራ ኋላ ቀር ነው። እንስሳት ተገቢ እንክብካቤ አይደረግላቸውም። እርሻ በጥንታዊና ባልተሻሻሉ የእረሻ መሳሪያዎች ይካሄዳል። በዚህ ምክንያት ገበሬዎች የሚፈለገውንና የለፉትን ያህል አያገኙም። ... ካለ በኋላ ነባሩ አስተራረስ እንዲሻሻል ትምህርትና ስልጠና ልንሰጣቸው ይገባል። በተቻለ መጠን በትራክተር መጠቀም የተሻለ መሆኑ እንዲገነዘቡት ማድረግ ያስፈልጋል። ...* (101-4) በማለት ሃሳቡን ያጠቃልላል፡፡

ሁለቱም ምንባቦች የአብዛኛው የህብረተሰብ ኑሮ መሰረት ስለሆነው ግብርና የሚተርኩ ስለሆኑ በተለይ ከገበሬው ለወጡት ህፃናት እንግዳ አይደሉም። ከአጠቃላይ የትግራይ ህዝብ ውስጥ 3,471,733 (80.5%) የሚኖረው ገጠር ውስጥ ነው (FDREPCC, 2008)። አብዛኛው የከተማው ነዋሪም ከገጠር ፈልሶ የመጣ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ተማሪውም ከዚሁ የገጠር ህብረተሰብ የተገኘ እንደመሆኑ ርእሱ ሲነሳ ስሜቱ ሊነቃቃ ይችላል።

ሁለቱም ምንባቦች ስለ የምግብ ሰብልና የእንስሳት እርባታ ጠቃሚነትና ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ያወሳሉ። ይህ እውቀት ተማሪው ቀድሞ ከገነባው እውቀት ጋር የሚጣጣምና፣ (Cunningham, 1992; EBC, 2004; Perkins, 1992; Petty, 2004) ወላጆቹ ይከተሉት የነበረውን አሰራር የሚያሳድግ ከሆነ አዲሱን እውቀት ከነበረው ጋር ያዋህደዋል። እውቀቱም ፈጥኖ ወደ ህብረተሰቡም ሊሰርፅ ይችላል። ተማሪው ምንባቦቹን በንቃት በሚከታተልበት ጊዜ የሚያገኛቸው ጭብጦችና እውነታዎች እሱ ቀድሞ ከሚያውቀው እውነት ጋር የማይጣጣሙ ከሆነ ደግሞ ጥያቄ ያነሳል። የትኛው ትክክል ወይም ስህተት እንደሆነ ለማወቅ ይሞክራል። አንድም ቀዳሚውን አለዚያም አዲሱን እውቀት ለመያዝ ሌላውን ለመጣል ይገደዳል። (Perkins, 1992; EBC, 2004; Petty, 2004)።

ቀደም ሲል ስርዓተትምህርት በማህበረሰቡ ውስጥ የዳበረውን ተጨባጭ እውቀት መነሻው ሊያደርግ እንደሚገባና የማህበረሰቡን የእውቀት ግንባታ ሂደት ተከትሎ መደራጀት

እንዳለበት መጠቀሱ ይታወሳል። ከመማሪያ መፃህፍቱ የወጡት ምንባቦች ጭብጦች ግን ህፃኑ ከማህበረሰቡ ከቀሰመው እውቀት ጋር የሚፃረሩ ናቸው።

- ህብረተሰባችን ያመረተውን እህል በአግባቡ አይጠቀምበትም፣
- ቆጥቦ መጠቀም አይችልም፣
- በሚገባ ተንከባክቦ አይዘውም፣
- ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ በነቀዝ በአይጠችና በእርጥበት ይበላሻል፣

እነዚህ መልእክቶች ለዘመናት በግብርና ለሚተዳደረውና ይህንን ሙያ ጠንቅቄ አውቀዋለሁ ለሚለው የትግራይ ገበሬ የሚዋጥለት አይሆንም። ህፃኑም አባቱም ሆኑ ሌሎቹ አራሾች ጥሩ ገበሬዎች እንደሆኑ ሊያምን ይችላል። ምንባቦቹ ህብረተሰቡ ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳለው ሳይሆን የግብርና ስራውን የሚጎዱ ስህተቶችን እየፈፀመ እንደሆነ ያብራራሉ። ይህ ሃሳብ ከተማሪው ቀዳሚ እውቀት ጋር ስለሚፃረር አንድም የወላጆቹን ኋላቀርነት አምኖ አዲሱን እውቀት መቀበል፣ አለዚያም ነባሩን ተቀብሎ አዲሱን መሻር ሊኖርበት ነው።

ምንባቡ በመፍትሄነት ያስቀመጣቸው ነጥቦች አሉ። አንዱና ዋነኛው ቁጠባ ነው። ሁለተኛው በተባዮች እንዳይበላ በጥንቃቄ መያዝ ነው። የመፍትሄ ሃሳቦቹ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ይህንን እውቀት የማስረፅ ሃላፊነት የተሰጠው ግን በሰባትና በስምንት ዓመት መካከል ለሚገኘው ህፃን ነው፣ "እኛ ይህንን ተገንዝበን ወላጆቻችንን እንምከር" በማለት ሃሳቡን ያጠቃልላል።

**እርሻ፡-** የሚለው ምንባብም በጭብጡም ሆነ በአቀራረቡ **እህልና አጠቃቀሙ** ከሚለው ምንባብ ጋር ይመሳሰላል። ይህ ምንባብ ሁለት ዋና ዋና ነጥቦችን ማጉላት ይፈልጋል። **አንዱ፡-** ግብርና ከእርሻ በተጨማሪ የሚያካትታቸው ሙያዎች መኖራቸውን፣ **ሁለተኛው፡-** የሃገራችን የግብርና ስራ ኋላ ቀር መሆኑን ማሳየት ነው። በመጀመሪያው ነጥብ፣ ግብርና ሰፊ ሙያ መሆኑን ያስረዳል። ግብርና፣ እርሻ ብቻ ነው ብሎ ያምን ለነበረ ህፃን አዲስ እውቀት ነው። **ሁለተኛው** ነጥብ፣ የሃገራችን የእርሻ (የግብርና) ስራ ኋላ ቀር መሆኑን ማስተማር ነው። መገለጫወቹም ገበሬው አሁንም ጥንታዊና ያልተሻሻለ የእርሻ መሳሪያ እየተጠቀመ መሆኑና ለእንስሳት ተገቢ እንክብካቤ አለማድረጉ፣ ናቸው። በመፍትሄነትም ሶስት ነጥቦች ቀርበዋል፡፡ እነሱም፡-

- ዘመናዊ አስተራረስን እንዲከተሉ ማገዝ፣
- ነባሩ አስተራረስ እንዲሻሻል ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣
- በትራክተር መጠቀም የተሻለ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ፣ ይላል።

የመጀመሪያዎቹ ሁለት የመፍትሄ ሃሳቦች አገር በቀል ወይም ገብ መሆናቸው ሳይሆን ምን ችግር መፍታት እንደሚችሉ ግልፅ አይደለም። ከየት ወዴት ቢታረስ ዘመናዊ፣ የትኛው አቅጣጫ ደግሞ ኋላ ቀር እንደሚባል አይታወቅም። ሁለተኛውም ተመሳሳይ ነው። ምን ችግር እንደነበረበትና ችግሩ በምን እንደሚፈታ አይታወቅም። ሶስተኛው መፍትሄ የህብረተሰቡን የመሬት ስፋትና የመሬት አቀማመጥ እግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። እንዲሁም አንድ ገበሬ ለስራ የደረሱ ልጆችና ሁለት ጥንድ በሬ ካለው ትራክተር መከራየቱ ኪሳራ እንጂ ትርፍ አይኖረውም። ስራፈት ልጆች፣ ስራፈት በሬዎች፣ ስራፈት አባት ገበሬ ይኖራሉ። ተገቢ ያልሆነ የማሳረሻ ዋጋ ደግሞ ይጨመርበታል።

እንዲህ አይነቱ ትምህርትና ዘመናዊነት ገበሬውን በእጅጉ የሚጎዳና በዘመናዊነት ስም ከፍተኛ የስራ እውቀትና ፍቅር የነበረውን ህብረተሰብ ወደ ስራ ፈትነት የሚመራ ይሆናል። እንዲሁም የተለያዩ ምሁራን (Semali and Stambach, 1993) እንደጠቀሱት የቀረቡት ምንባቦች ህፃናቱ ባህላቸውን ዝቅ ድርገው እንዲያዩና የማህበረሰባቸውን አስተራረስ ዘዴ ጊዜ ያለፈበት መሆኑን እንዲያውቁ ለማድረግ ያለሙ ይመስላል። ለአበጀ የሰጡት ቦታ የለም፡፡ የያንዳንዱ ህፃን መነሻ እውቀት ደግሞ ይኸው የማህበረሰቡ እውቀት ነው፡፡ ስለሆነም አዲሱን እውቀት መቀበሉ ሊከብደው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ህብረተሰቡ እንዲትም አዎንታዊ አሰራርና እውቀት እንደሌለው የሚቆጥር ስለሆነ ነው። ህፃኑ፤ የአመት ቀለቡን በሞኝነት በአንድ ቀን ከሚያጠፋ ማህበረሰብ ነው የተገኘው። ቆጥቦ ባለመብላቱ ለረሃብ፣ ለእርዛትና ለስደት ከሚጋለጥ ህብረተሰብ የተገኘ መሆኑ እንዲያውቅ ነው የተፈለገው። በየሃገሩ ተሰዶ ያለው ወገኑም በድግስ፣ ምርቱን በአግባቡ ባለመያዙና ለአይጥና ለነቀዝ አሳልፎ በመስጠቱ መሆኑ እንዲያምን ነው የሚማረው። በአጠቃላይ ህፃኑ ከላይ የቀረቡትን ሁለት ፅሑፎች ካነበበ በኋላ፡-

- የተገኘበትን ማህበረሰብ ኋላ ቀር ነው በሎ ሊፈርጅ፤
- የራሱንና የህብረተሰቡን እውቀት ሊንቅ፤
- ትክክለኛ እውቀት የምእራባውያኑ ብቻ እንደሆነ አምኖ ሊቀበል፤ እና

- ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ከራሱ ማንነት ስለሚወጣ በማንነት ጥያቄ ቀውስ ሊንገላታ ይችላል።

እነዚህ ነቀፌታዎች ህፃኑና ህፃኑን ያሳደገው ማህበረሰብ፣ ራሳቸውንም ሌላውንም ሳይሆኑ መሃል ቤት ሊያስቀሯቸው ይችላሉ። ተማሪው የሚማረው ማንነቱን እንዲያጣ ወይም እንዲጠላ አይደለም። ከትምህርት በኋላ የሚጠበቀው ውጤት፣ ተማሪውን የማያውቅ መሆኑን እየነገሩ ኑሮውን እንዲጠየፍ ማድረግ ሳይሆን እንደ Banda (2008) አገላለፅ ትምህርቱ የተማረውን ሰው፡-

- ከትንሿ እርሻውና ከደሳሳ ጎጆው ጋር ተስማምቶ እንዲኖር በማገዝ በዚሁም ተደስቶና ረክቶ እንዲኖር፣
- ጥቂቶችን ደግሞ ከእንደዚያ አይነት ኑሮ አምልጠው የተሻለ ኑሮ እንዲመሩ፣
- ሌሎቹን ደግሞ ያሉበትን ኑሮ እኛ በፈለግነው ሳይሆን እነሱ ባመኑበት መንገድ አሻሽለውና አዳብረው እንዲገለገሉበት ማስቻል አለበት።

በምንባቡ ውስጥ የታዩት ሃሳባች ግን ተማሪውን ከባህሉ፣ ከኑሮውና ከኖረበት ማህበረሰብ እንዲያፈነግጥ የሚያደርጉ ናቸው።

በቃለመጠይቅና በተኰር የቡድን ውይይት የተሳተፉት መምህራን አበእን ለማስተማር የሚያገለግሉ በጣም ጥቂት የስነቃል አላባዎችና ስለማህበረሰቡ ኑሮ የሚያወሱ ምንባቦች እንዳሉ ያምናሉ። ፈፅሞ አልቀረቡም ላለማለት ብቻ የገቡ በማለትም ይገልጿቸዋል። ነገር ግን እውቀቱን በማስተላለፍ ረገድ ተሳክቶላቸዋል ብለው አያምኑም። ለምሳሌ ከቃለመጠይቅ የተገኘውን መረጃ እንይ። ለምሳሌ አንድ መምህር፡-

> *መፃህፍቱ በጥቂቱም ቢሆን ተረቶችና እንቆቅልሾችን ይዘዋል። ህፃናት ሳይንስ ወለድ የሆኑ እውቀቶችን በቁማቸው ከሚቀርቡላቸው፣ በአካባቢያቸው ከሚሰሟቸውና ከሚያዩት ሁኔታ እያገናዘብን ስናቀርብላቸው ለማንበብም በተለያዩ ተግባራት ውጥ ለመሳተፍም ይነሳሳሉ። ስለሆነም ተረቶቹም ሆኑ ሌሎች ወንች በርከት ብለው ቢገቡና በማስተማሪያነት ቢያገለግሉ ጥሩ ይመስለኛል።* (ቃመ. መም.1.1፣ 22-12-2004 ዓ.ም.)

የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከተሰጠው ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው የቀረቡት የስነቃል ክፍሎች በጣም ጥቂቶች ናቸው። እነዚህን በመጠን ከፍ ማድረግ ማለት ደግሞ ህፃናት እየተዝናኑ ይበልጥ እንዲችሉና እንዲያውቁ ማድረግ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ህፃናቱ ከእነዚህ የስነቃል ክፍሎች ቋንቋውንም ማህበረሰባዊ እውቀቱንም ሊማሩ እነደሚችሉ ቢታወቅም የሚፈለገውን ያህል እንዳልቀረቡ ይገልፃሉ።

ከተኩር የቡድን ውይይት የተገኘው መረጃም ተመሳሳይ ሃሳብ ነው የሚያንፀባርቀው። ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት ከመምጣታቸው በፊት ከባቢያዊ እውቀትን ለመረዳት የሚያግዙ በርካታ ተረቶች፣ ቀልዶች፣ እንቆቅልሾችና ሌሎች ወጎችን እያደመጡ ቆይተዋል። ከእለት ተእለት ተግባራት የሚማሯቸው አበ እውቀቶችም ይኖራሉ። መማሪያ መፅሃፉ ግን ልጆቹ ይዘውት በመጡት ልምድና ባህል ላይ የሚነሳ አይደለም። ቀጣይነት ወይም ተለጣጣቂነት አይታይበትም። ህፃኑ ከማህበረሰብ ያገኘውና ከመማሪያ መፃሕፍት የሚያገኘው አዲሱ እውቀት የማይደጋገፉና የማይዋሃዱ ከሆነ አንዱን መጣል የግድ ይሆናል(Perkins, 1992; EBC, 2004; Petty, 2004)። ቀዳሚውን እውቀት ከጣሉት ደግሞ እጥሩ መሰረት ላይ የተገነባና ከቀላል ወደ ከባድ የሚያድግ የእውቀት ግንባታ አይኖርም። ህፃኑም የቻለውን ያህል እንዳያመነጭና በመማር ማስተመማሩ ሂደት ውስጥ ድርሻ እንደሳይኖረው፣ ከማህበረሰብ በቀሰመው እውቀት እንዲያፍር፣ የሚያውቀውን ሳይሆን የተነገረውን ብቻ የሚቀበል ሰው ሆኖ እንዲወጣ ያደርጋል።

> *ለምሳሌ በትረካ የቀረበውና ስለእርሻ የሚያወሳው ምንባብ በበሬ ማረስ ኋላቀርነት እንደሆነና ሁሉም ገበሬ በትራክተር ሊያርስ እንደሚገባ ያስገነዝባል። በትራክተር ማረስ ዘመናዊነት ስለሆነ ተጠቀሙበት የሚል ምክር ያቀርባል። ምክሩ ግን በየትኛው አካባቢ ለሚኖር ህዝብ እንደሚያገለግል አይነግርም። ህፃኑ በአካባቢው የሚያየውን አሰራር እንዲንቅና አማራጭ አልቦ ሆኖ እንዲንሳፈፍ የሚያደርግ ነው* (ተቡው.፣27-12-2005 ዓ.ም.)።

ህፃኑ ምንባቡን ካነበበ በኋላም ስለእርሻም ሆነ ስለአስተራረስ ምን እውቀት እንዳለው አይጠየቅም። የሚያውቀው ነገር ቢኖርም "ኋላቀር" ስለሆነ ጠቀሜታ የለውም። በአንፃሩ የህብረተሰቡ መተዳደሪያ የሆነውን ግብርና እና የግብርናን እውቀት እንዲንቅና እንዲጠላ የሚያደርግ ይዘት እየቀረበለት እንደሆነ ከተሰጠው ምላሽ መገንዘብ ተችሏል። ከቀረበው ምንባብ መረዳት የተቻለውም ይኸው ነው። አብዛኞቹ ህፃናት ከገበሬው ህብረተሰብ የተገኙ

እንደመሆናቸው ስለግብርና መጠነኛ እውቀት እንዳላቸው ይገመታል። ምንባቡ የቀረበው ግን ስለግብርና ምንም ዓይነት ግንዛቤ ለሌላቸው ሰዎች ይመስላል። የእርሻ ስራ የሚከናወነው ሰፋፊ የመንግስት እርሻዎች ባሉበት ብቻ ያስመስለዋል። ወይም ደግሞ የትግራይ ገበሬ በአጠቃላይ ሜዳማና ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባለበት ቦታ ብቻ የሚኖር ያስመስለዋል። ከዚህ በመነሳት መፃሕፍቱ የማህበረሰቡን እውቀት አያንፀባርቁም አዘጋጆቹም ማህበረሰቡን አያውቁትም ማለት ይቻላል።

ለስርዓተትምህርት ባለሙያ የቀረቡ የመጀመሪያ ሶስት ጥያቄዎች በስርዓተትምህርት ውስጥ ኣበእ እንዲካተት ወይም እንዳይካተት የሚያዝ መመሪያ ስለመኖሩ እና የትግርኛ ቋቋ ስርዓተትምህርት ሲነደፍ ኣበእ እንደ ኣንድ ይዘት ታቅዶ እንዲካተት የሚደረግ ስለመሆኑ ለማወቅ ያለሙ ነበሩ። በባለሙያው የተሰጡት ምላሾች በተከታታይ ቀርበዋል።

> *ኣበእ ላይ ያተኮረ ይዘት እንዲኖር የሚፈቅድ፣ ወይም እንዳይኖር የሚያግድ ኣንድም መመሪያ የለም። ነገር ግን በቀጥታም ባይሆን በመርሃትምህርት ውስጥ ያለው የሰዓት ሽንሽና ኣንዱ ይዘት ሰፊ ሽፋን እንዲያገኝ፣ ሌላው ደግሞ እንዲደበዝዝ ሊያደርግ ይችላል። በዚህ ምክንያት ስነቃሉ ዝቅ ያለ ድርሻ ይዞ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እገዳው የሚገለፀው በክፍለጊዜ ሽንሽና ኣማካይነት ብቻ ነው።*
> (ቃ.መ. ስባሙ. 28-12-2004 ዓ.ም.)

የሁሉም ቋንቋዎች ይዘትና ክፍለጊዜ የሚወሰነው በሃገር ኣቀፍ ደረጃ በኣማርኛ በሚዘጋጀው መርሃትምህርት ስለሆነና የክልሎች ድርሻ ወደየራስ ቋንቋ ከመተርጎም ስለማያልፍ ይህ ራሱ እገዳ ይባል ይሆናል። ኣንዱ ማህበረሰብ ያለውን እውቀት ማስተማር ቢፈልግ እንኳ የኣገር ኣቀፉ እቅድ የሰኣት ለውጥ እንዳይደረግና የተፈለገው እውቀት እንዳይተላለፍ ስለሚያግዝ ይታገድ ይሆናል። ስርዓተትምህርት ከሌሎች ሃገሮች ወይም የተለየ ማንነት ካላቸው ብሄሮች የተገኘን ስርዓተትምህርት በመተርጎም መገልገል፤ የምእራባውያኑን ካሪኩለም ከመውሰድ ባላነሰ በህዝቦች ላይ የራስ ያልሆነን ሃሳብ በግድ ለመጫን የቆመ መጨቆኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል (Grenier, 1998)።

ሆኖም ይህ በኣገር ኣቀፍ ደረጃ በክፍለጊዜ ድልድል በኩል እገዳ ይደረግበታል የሚለው መልስ በመፃሕፍቱ ውስጥ ኣበእ እንዳይኖር ምክንያት ሆኗል ብሎ ሙሉ በሙሉ መቀበል ያስቸግራል። የክፍለጊዜ ድልድሉ መጠንን ሊወስን ይችል እንደሆነ እንጂ በመፅሓፎቹ

ውስጥ የተካተቱትን በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ኣያግድም። ለምሳሌ በተሰጡት ክፍለጊዜያትም ኣበእን ማስተላለፍ ለሚችሉት ምንባቦች ትኩረት ኣልተሰጣቸውም። መልመጃዎቹም ሊተላለፍ በተፈለገው እውቀት ላይ እንዲያተኩሩ ኣልተደረገም። ስለዚህ ችግሩ ከክፍለጊዜ ድልድል ጋር ብቻ ሳይሆን የኣበእን ጠቀሜታ ተገንዝቦ መገልገል ካለመቻልም ጋር የተያያዘ ነው።

ኣበእን ለመጠቀም የሚታቀድ ስለመሆኑ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽም የክፍለጊዜ ማነስ ኣበእን ለመጠቀም እንቅፋት እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ ነው።

> *በኣፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር የሚል ፍላጎትና ግፊት ስለነበረ ብቻ ነው የተጀመረው። በሃሳብ ደረጃም ትምህርቱ በኣካባቢ ጉዳዮች፣ ባህልና እምነት ላይ ማተኮር እንደሚገባ እንነጋገራለን። በተለይ ኣበእን ለመጠቀም ተብሎ የሚወጣ እቅድ ግን የለም።...* (*ቃ.መ. ስባሙ.* 28-12-2004 *ዓ.ም.*)

በትግራይ ደረጃ የትግርኛ ቋንቋን በኣፍ መፍቻ ቋንቋነት ለማስተማር ሲታሰብ ኣስቀድሞ የተቀመጠ ግብ ኣልነበረም። በመነሻነት ያገለገሉትም በህወሓት የተዘጋጁና በትግል ወቅት ኣዋቂ ሰዎች (ታጋዮች) እንዲማሩባቸው የተዘጋጁ መፃህፍት ናቸው። ከዚህ ኣልፎ በኣፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ኣስፈላጊነት፣ ስለኣዘገጃጀቱም ሆነ ሊተኮርባቸው ስለሚገባ ጉዳዮች የተሰጠ ስልጠናም ሆነ መመሪያ እንዳልነበረ ተገልጿል።

ከተሰጠው ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው በትግርኛ ቋንቋ ማስተማር የተጀመረው በፍላጎትና ፍላጎቱ በፈጠረው ግፊት ብቻ ነው። መማሪያ መፃሕፍቱ የሚዘጋጁት ህፃናት በቋንቋቸው በመማራቸው የሚያገኟቸው ጥቅሞች ተለይተውና በእቅድ ተደግፎ ኣልነበረም። ምንም እንኳን ህፃኑ ኣፍ በፈታበት ቋንቋ መማር እንደሚገባው ቢታመንም ምን፣ እንዴት፣ ምን ለማግኘት ማስተማር እንደሚገባ የሚያመላክት መመሪያ የለም። ኣበእን ለማስተማር እቅድ ቢወጣ እንኳ ተተግባሪነቱ በኣዘጋጆቹ ፍላጎት ሊወሰን ይችላል። በምክንያቱ የሚያምኑት ሊያስገቡ፣ሌሎቹ ደግሞሊያስቀሩት ስለሚችሉ ነው።

*በሌላ በኩል በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ከኣበእ ማስተዋወቅ የሚችሉ መልመጃዎች ስለመኖራቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ በቂ መልመጃዎች እንዳሉ ያስረዳሉ።*

> *ተረቱን፣ እንቆቅልሹንም ሆነ ሌላውን ወግ ተከትለው የሚመጡ ጥያቄዎች፣* ***"ከምንባቡ ያገኛችሁት ትምህርት ምንድነው? የተረቱን መልእክት ኣሳጥራችሁ***

*ተናገሩ" የሚሉ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ተማሪዎች ሊተላለፍ የተፈለገውን ዕውቀት ፈልፍለው እንዲያወጡ ያስችሏቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የተማሪውን አእምሮ ለማስፋትና የመመርመር አቅሙን ለማሳደግ የሚቀርቡ እንቆቅልሾችም አሉ። ስለዚህ መልመጃዎቹ ድርሻቸውን ተወጥተዋል ብየ ነው የማምነው። (ቃ.መ. ሰባሙ. 28/12/2004 ዓ.ም.)*

ባለሙያው በአብነት ያቀረቧቸውና አበእን ፈልፍሎ ለማውጣት ያስችላሉ የኋቸውን ጥያቄዎች *"ከምንባቡ ያገኛችሁት ትምህርት ምንድነው? የተረቱን መልእክት አሳጥራችሁ ተናገሩ"* የሚሉ ናቸው። ሆኖም እነዚህ ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ብቃት መፈተሻዎች እንጂ ማህበረሰቡ ሊለው የፈለገውን እውቀት ለማውጣት የሚያስችሉ አይደሉም። በምንባቡ (*... ብሎ የተናገረው ማን ነው? እንደዚያ ብሎ የተናገረው ለምንድነው? የምንባቡ ጭምቅ ሃሳብ ምንድነው?*) ከሚሉና አስተውሎ ማንበብን ብቻ ከሚፈትሹ ጥያቄዎች የተለዩ አይደሉም። በዚህ መልክ የቀረቡትን መልመጃዎችም በአጠቃላይ አገር በቀል እውቀትን የማስረፅ ድርሻቸውን ተወጥተዋል ብሎ ለመናገር የሚያስችሉ አይደሉም።

*ቀጥሎ፡-በቃለመጠይቅና በተኰር የቡድን ውይይት ለተሳተፉት የማህበረሰቡ አባላት የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች (1 እና 2) ማህበረሰቡ ከግብርናና፣ ከግብርና ምርት አጠባበቅና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ፤ የኔ የሚላቸው እውቀቶች ያሉት መሆኑን ለመፈተሽ የሚያስችሉ ናቸው።*

እነዚህ ጥያቄዎች እውቀትን መገንባት አላማቸው ባደረጉና **"እህልና አጠቃቀሙ፣ ግብርና"** (2ኛ ክፍል፣ 72፣ 101)፣ በሚሉ ርእሶች ስር በቀረቡ ምንባቦች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ተሳታፊዎቹ የሰጧቸው መረጃዎች በሰብል እህል አመራረትና አጠባበቅ፣ 1በአስተራረስ ፣ በእንስሳት ጤንነት አጠባበቅ ላይ ምን እውቀት እንዳላቸውና በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ጭብጦች ጋር ያለቸው አንድነት/ ልዩነት የሚያመለክቱ ናቸው።

*በቅድሚያ የቀረበው ጥያቄ፡- የትግራዋይ ገበሬ የእርሻ እውቀት፣ በእርሻ መኪና ላይ ያለው አተያይና የመጠቀም ፍላጎቱ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ፤ እንዲሁም በምርት አሰባሰብና አጠባበቅ ላይ ያለው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለመረዳት የሚያስችል ነው።*

ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ የሆኑት በውይይት መሃል ያቀረቡትን ***ሸውዓተ ግዘያ ከይሓርሱስ ሸውዓተ ግራት ይሓርሱ*** (አንዱን ሰባት ጊዜ ከማረስ ይልቅ ሰባት የተለያዩ የእርሻ መሬቶች ያርሳሉ።) *ቃመ.ማ.*7 12-12-2004 የሚል የህዝብ ተረትና ምሳሌ፣ እንደ መነሻ

ስንመለከት፣ የአበእ ማቅረቢያ የሆኑት ቃላዊ ሃብቶች የህብረተሰቡ እውቀት፣ እምነትና ግንዛቤ ተሸካሚ መሆናቸው ይጠቁመናል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ተረትና ምሳሌ አማካይነት የእውቀቱ ባለቤቶች እንደጠቀሱት አንድን የእርሻ መሬት በሚገባ አለስልሶ መዝራት ሰባት የተለያዩ የእርሻ መሬቶችን እንደነገሩ አድረጎ አርሶ ከመዝራት የበለጠ ጠቀሜታ አለው። የምርት ውጤት የሚለካውም በመሬት ስፋት ሳይሆን በመሬቱ ላይ ባፈሰሱት ጉልበትና አያያዝ ልክ መሆኑ ያስረዳል።

አስተራረሱም ውሃን ከመቆጣጠር፣ አረምን ከማጥፋት፣ የአፈር በጎርፍ መከላትን ከመከላከልና ከምርት መጨመር ጋር የተያያዘ ነው። ትግራዋይ ገበሬ ሲያርስ እነዚህን ሁሉ ግምት ውስጥ ያስገባል። ይህንን ሃሳብ ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ፡-

> *መጀመሪያ በሀሃይ ጊዜ በጥርና የካቲት የግምሻ መጋቢት የማየም እርሻ ይካሄዳል። የተለያየ የአረም ዘርም ሆነ ስር እንዲነቀልና ለፀሃይ እንዲጋለጥ በማድረግ አረምን ያስወግዳል(የአረም ማጥፊያ ወጪ ይቀንሳል)። መሬቱ ኣባጣ ጎርባጣ ከሆነ እንዲስተካከልና የመስኖ ወይም የጎርፍ ውሃ እኩል እንዲተኛበት ለሶስተኛ ጊዜ ወደጐደጐደው አቅጣጫ ሲያፍ ይታረሳል። ለአራተኛ ጊዜ ማረስ ካስፈለገ ሲያፍ ሆኖ የሶስተኛው ሲያፍ በተቃራኒ አቅጣጫ ይሆናል። ይህ ዘዴ ከቅድመአያቶች የወረስነውና በዘመናት የዳበረ ተሞክሮ ሆኖ ውጤታማ የሆንንበት አስተራረስ ነው። ባሁኑ ጊዜ የልማት ሰራተኞችም አሰራራችንን እየተቀበሉና እየደገፉልን ነው።* (ቃመ.ደቡ. 15፣ 10-08-2004 ዓ.ም.ዓ.ም.) *በማለት ገልፀውታል።*
>
> ***ደጋግሞ ማረስ*** *:- ቡቃያው እንዲፋፋ፣ ብዙ ራስ እንዲኖረውና ምርት እንዲጨምር ያደርጋል። ለምሳሌ **ሶስተኛ** የበሰበሰው አረም ከመሬቱ ጋር እንዲዋሃድ፣ 4ኛ ጊዜ እርሻ ደግሞ ፍግ ከተበተነ በኋላ ከአፈሩ ጋር ለማስማማት ይጠቅማል። **ረውሓ** **(ቅብቅብ)** አምስተኛ እርሻ ደግሞ መሬቱ ለዘር ዝግጁ የሚሆንበት ደረጃ ነው። ቀጣዩ እርሻ በዘር ጊዜ የሚካሄድ ነው። እንደ የእህሉ አይነት እየዘሩ ማረስ ወይም ከእርሻ በኋላ መዝራት ሊሆን ይችላል። እንደ ጤፍ የመሳሰሉት ከእርሻ በኋላ ይዘራሉ፤ ጥራጥሬ ደግሞ ከእርሻ በፊት ይዘራሉ።*
>
> *የበቀለው እህል ሓምሌ ወር ይሸለሸላል። የሽልሻል ዋና ጠቀሜታ ጎርፍ በየቡቃያው ስር እንዲተኛ፣ ቡቃያው እንዲጎመራና ዛላው እንዲበዛ ማድረጊያ ነው። አልፎ አልፎ የበቀለ አረም ቢኖር ለማጥፋትም ይጠቅማል። ቡቃያው በጣም ያደገ ከሆነ ከሓምሌ ዝናብ በፊት፤ ገና ከሆነ ደግሞ ከዝናብ በኋላ ይሸለሸላል።* (ተቡው.ራዓ. 1፤ 14-04- 2005 ዓ.ም.)

ትግራዋይ ገበሬ፣ ጥሩ ምርት የሚገኘው መሬቱ በተደጋጋሚ ታርሶ ሲለሰልስ ነው፤ በቂ ውሃ ሲያገኝ ነው፤ ምግቡን የሚሻማው አረም ሲጠፋ ነው፤ እነዚህን ለማሟላት ደጋግሞ ማረስ ወሳኝ ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም እስከ ዘር መዝሪያ ወቅት ድረስ ከአምስት እስከ ሰባት ጊዜ ያርሳል፡፡ ከዚም ሌላ የትግራይ ደቡብም ምስራቅም ሆኑ የማእከላዊ ዞን ገበሬዎች

በጥሩነቱ የሚያምኑበትና የሚከተሉት የአስተራረስ ዘዴ አላቸው። ይኸውም አንድ የእርሻ መሬት ሶስት ምክንያቶች ሲባል ተደጋግሞ ይታረሳል። **አንዱ ምክንያት** የእርሻ መሬት በማረሻ በለሰለሰ ቁጥር (ደጋጊምካ እንትውጋእ) መሬት ይሰባል፣ ቡቃያ ይፋፋል፣ ዛላው ስለሚበዛም ምርቱ ይጨምራል። ስለሆነም አቅምና ጊዜ በፈቀደ **ፅግኢ፣ ኣይሚ፣ ተስላስ፣ ረብዓ፣** (ግምሻ፣ ማየም፣ ሶስተኛ፣ አራተኛ) እያሉ ወቅትን ጠብቆ እስከ ስድስት ወይም ሰባት ጊዜ ድረስ ማገላበጥ ይጠቅማል። **ሁለተኛው፡-** አቅጣጫ ጠብቆ በማረስ መሬቱ እኩል ውሃ እንዲያገኝ ለማድረግና **ሶስተኛው ምክንያት** ደጋግሞ በማረስ አረምንና ከአረም ጋር የሚመጡ ተባዮችን ለመከላከል ነው። የአረም ማጥፊያ መድሃኒት ወጪንም ያስቀራል፡፡ የአፈፃፀም ሂደቱም እንደሚከተለው ተገልጿል።

> *ኣንድ የእርሻ መሬት የሚሰጠው ምርት እየቀነሰ ከመጣ ሳይዘራ እንዲከርም ይደረግና በነሓሴ ወር በጠባብ ድግር ይገመሳል። ይህም **ፊግዓ** ወይም **ፅግኢ** (ግምሻ) ይባላል። ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የኣረም ዓይነት ሁሉ ኣንድም ሳይቀር ይበቅላል። መስከረም መጀመሪያ በሰፊ ድግር ይታየምና ኣረሙ ገና ከማፍራቱ ስሩ ተነቃቅሉ ይቀበራል። መጋቢት ላይ ይሰለሳል። በፀሃይ ደርቆ የበሰበሰው ኣረም ከኣፈር ጋር ይዋሃዳል። በዚህ ዘዴ ኣረሙ ማዳበሪያ ሆኖ ያገለግላል። በሚያዝያና ግንቦት እንደ ዳጉሳ፣ ማሽላ የመሳሰሉ **የእዝመራ** ኣዝርእት ይዘራሉ። በኣረም ወቅት እህሉ ቀድሞ ስለሚወጣና ኣረሙን ስለሚያሸንፈው ለኣረም የሚወጣ ጉልበትና ጊዜ ኣይኖርም። የኣረም ማጥፊያ መድሃኒት መጠቀምም ኣያስፈልግም።* (ተቡው. ታምፀ 2.1፣ 07-05-2005 ዓ.ም.)

ይህንን ሃሳብ ሌሎች መረጃ አቀባዮችም እንዲህ በማለትም ያጠናክሩታል፣

> *መሬት ኣንዴ ጥር ላይ ከታረሰ በኋላ **በፉርማ ማይ** (የመጋቢት መግቢያ ዝናብ) ኣረሙ ግልብጥ ብሎ ይበቅላል። ያኔ (ቀድሞ ከታረሰበት ኣቅጣጫ በተቃራኒ) በሰያፍ ወይም በኣግድም ይገለበጣል። የኣረም ስር ተነቃቅሎ ይደርቅና ይጠፋል። በተለይ ሚያዝያ ወይም ግንቦት ለዘር በሚታረስበት ጊዜ ኣረሙ መጥፋት ብቻ ሳይሆን ወደኣፈርነት ተለውጦና ማዳበሪያ ሆኖ ያገለግላል። **ኣፉ ጨሊጡ ቀርዩ** (ሙሉ በሙሉ ኣረሙ ጠፋ) ይባላል። እህሉ ለኣረም ከደረሰ በኋላ ኣልፎ ኣልፎ የሚታይ ካለም **ጭላጥ** (እንጥፍጣፊ) ይባላል። ቡቃያው እህል ከኣረሙ ቀድሞ ስለሚያድግ እንጥፍጣፊው በሙቀት ታፍኖ ይጠፋል።* (ቃመ. ደቡ. 3፣ 06-12-2004 ዓ.ም.) ይላሉ።

ከገለፃው መረዳት እንደተቻለው ትግራዋይ ገበሬ፣ ከኣለፉት ትውልዶች የተረከባቸው ውሃ ማጠጣት፣ አረም ማጥፋት፣ ፍግ ማደባለቅ፣ መሬቱን ማለስለስ፣ ቡቃያውን ማፋፋት ዓላማ ያለቸው የእርሻ ዘዴዎችን ይጠቀማል። ይህ ኣሰራር ህብረተሰቡ በተደጋጋሚ ሙከራ ያገኘው እውቀቱ ሲሆን በዘመናዊው የኣስተራረስ ዘዴም ተቀባይነት ያገኘ ኣበእ መሆኑ

ሁለቱ አካላት ከሰጧቸው ምላሾች መገንዘብ ይቻላል። እንዲሁም ህብረተሰቡ በነሓሴና በመስከረም ለሚካሄደው እርሻ ተመሳሳይ ድግር እንደማይጠቀም ተጠቁሟል። ምክንያቱ ደግሞ የነሃሴው እርሻ ዓላማ፣ መሬት ውስት ውሃ እንዲሰርፅ ማድረግ ስለሆነ በጠባብ ድግር፣ የመስከረሙ እርሻ ዓላማ ደግሞ የአረምን ስር ነቃቅሎ መጣል ስለሆነ በሰፊ ድግር ያርሳሉ። ይህ እውቀትም የህብረተሰቡ የዘመናት የሙከራ ውጤት ነው።

ሌላው የህብረተሰቡ እውቀት ሽልሽላ ነው። የግብርና ባለሙያዎች እህል በመስመር መዘራት እንዳለበት ያስተምራሉ፡፡ መረጃ አቀባዮቹ እንደገለፁት፣ የትግራይ ገበሬ ለየት ያለ አማራጭ ያለው ይመስላል። መረጃ አቀባዮቹ እንደገለፁት ዝናብ አጠር በሆነ አካባቢ በመስመር የተዘራ እህል ዝናብ ሲያንስ ቶሎ ይደርቃል፣ ምርቱም አጥጋቢ አይሆንም። በተለይ እንደ ዳጉሳ፣ ማሽላ በቆሎ የመሳሰሉት ቡቃያዎች በሽልሽላ (ጉስያ) ነው መስመር መያዝ ያለባቸው። አንዴ ከተሸለሸለና የዝናብም ይሁን የጎርፍ ውሃ ከተኛበት አጥጋቢ ምርት ሊሰጥ ይችላል። ዝናብ አጠር በሆነ አካባቢ እህል በመስመር ከተዘራና በቂ ዝናብ ካላገኘ ከስሩ ነፋስ ስለሚገባበት ቶሎ ይደርቃል። ታፍኖ ቆይቶ ዝናብ ሲበረታ ቢሸለሸል ግን ቡቃያው መስመር ይይዛል፤ ዛላውም ይበዛል። ይህንን የህዝቡ እውቀት የሆነው በሽልሽላ መስመር የማስያዝ ተግባር በመስመር ከመዝራት የበለጠ ጠቃሚ የሚሆንባቸው አካባቢዎች እንዳሉ መገንዘብ ተችሏል። ይህም እርጥበት በትነት እንዳይወሰድ መከላከል የሚያስፈልግባቸው አካባቢዎች እንዳሉ የሚጠቁምና ራሱ የቻለ ጥናት የሚያስፈልገው እውቀት ነው።

ከቃለምልልሱም ከቡድን ውይይቱም መረዳት የተቻለው በደቡብና በሌሎቹ ዞኖች መካከል የእርሻ ወቅት ልዩነት መኖሩ ነው። ይኸውም፡- በማእከላዊ ዞን የግምሻ ስራ የሚከናወነው በነሃሴ ወር ሲሆን አረሙ በሚገባ ለምቶ ከወጣና ማፍራት ከመጀመሩ በፊት በመስከረም ወር ይታየማል። በዚህ የእርሻ ሂደት አረሙ ይቀበራል። በመጋቢት ወር የደረቀው አረም ከአፈር ጋር እንዲስማማ ይደረጋል፡፡ በደቡብ ዞን ደግሞ ጥር ወይም የካቲት ላይ ይገመስና በመጋቢት ዝናብ መልሶ ሲበቅል ቀድሞ ከታረሰበት አቅጣጫ በተቃራኒ ይታየማል። ይህ የእርሻ ወቅት ልዩነት ከመሬት ለምነት መለያየት ጋር የተያያዘ ነው። የምስራቅና የማእከላዊ ዞኖች መሬቱ ስስ ስለሆነ ከነእርጥበቱ እያለ መስከረም ካልታረሰ በበጋ ማረሻ ስለማይወጋው ነው። የደቡቡ ደግሞ ወፍራም ስለሆነና ስለማያስቸግር አስቀድሞ ማረስ

አላስፈለገም። የሁሉም አካባቢዎች የግምሻና የማየም ዓላማ ግን አረምን አስቀድሞ ማጥፋት ነው።

መረጃ አቀባይ አካላት፣ ትግራዋይ ገበሬ ስለትራክተር ያለው ግንዛቤ ምን እንደሆነና በበሬ ምትክ ለምን ትራክተር እንደማይጠቀም ተጠይቀው ሁሉም መረጃ አቀባዮች የእርሻ መኪናን ጠቀሜታ ቢያውቁም ለመጠቀም የማያስችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ ጠቁመዋል፡-

> *በትራክተር ማረስ ያለው ጠቀሜታ ግልፅ ነው። በተለያዩ ቦታዎች በትራክተር እንደሚታረስ እናውቃለን። ምርታቸውን ወደውጪ ሳይቀር እንደሚልኩ እንሰማለን። በትራክተር ማረስ ባለማወቃችን አይደለም የተውነው፤ አልሆን ብሎን እንጂ። ባሉት ጥቂት ሜዳማ ቦታዎች ለማረስ ቢሞከር እንኳ በድቦች (ደረት) መፍረስ ምክንያት ህብረተሰቡ ማቆሚያ በሌለው ጭቅጭቅ፣ ሙግትና ጠብ ውስጥ ገብቶ ሊቀር ይችላል።* (ቃመ. ደቡ. 1.3፣ 06-12- 2004 ዓ.ም.) በማለት ምክንያታቸውን ያቀርባሉ።
>
> *መሬትን በትራክተር ማረስ እኛ ባንሞክረውም በሞከሩት ዘንድ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው እንሰማለን፤ እናያለን። እኛ ግን ትራክተር ለመጠቀም አልታደልንም። ከመሬታችን አቀማመጥ የተነሳ ትራክተር መጠቀሙ አይታሰብም። የእርሻ መሬቱ መጥበብ፣ የመሬቱ ድንጋያማ መሆን በበሬ ለማረስ እንኳ አስቸጋሪ የሚሆንበት የእርሻ መሬት በጣም ብዙ ነው። የድቦች መፍረስና የእርሻ መሬቶች መቀላቀልም ሌላው ትራክተርን የማያስመርጥ ምክንያት ነው።* (ተቡው. 2፣ 07-05-2005፣ ተቡው- 3፣ 08-05-2005)

በቃለመጠይቅና በተኰር የቡን ውይይት የተሳተፉት መረጃ አቀባዮች የእርሻ መኪና ጠቀሜታ ያውቃሉ፤ የመጠቀም ፍላጎትም አላቸው። ለምሳሌ፡- በክልሉ ካሉት ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች የተመረተ እህል ለሽያጭ ወደነሱ አካባቢ እንደሚመጣና ለውጪ ገበያም እንደሚቀርብ ያውቃሉ። በአሁኑ ጊዜ የበሬ ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑም ትራክተር ተከራይቶ ማረስ እንደሚቀል ገልፀዋል። ሆኖም የአካባቢው መሬት ወጣገባና ድንጋያማ፤ የእርሻ መሬቱ ደግሞ ጠባብ መሆን በትራክተር ለማረስ አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ጠቁመዋል። የተወሰነ ሜዳማ የእርሻ መሬት ቢኖር እንኳ በትራክተር ለማረስ ቢሞከር ጠባብ ስለሆነና ድቡ ስለሚፈራርስ ገበሬው እርስ በርሱ ሲካሰስና ሲጋደል ሊኖር ይችላል። በዚህ ምክንያት

ለብዙ ዘመናት ተጠብቆ የኖረው አብሮና ተጋግዞ የመኖር ባህል ሊናድ፣ የማህበረሰቡ አንድነት ፈተና ላይ ሊወድቅ ይችላል።

ምንም እንኳ ምንባቡ ገበሬዎቹ ያልተሻሻለና ኋላ ቀር መሳሪያ የሚጠቀመው የእርሻ መኪና ጠቀሜታ ስላልገባቸው ነው እና ዘመናዊ አስተራረስ እንዲከተሉ ማስተማር አለብን ቢልም የህብረተሰቡ ችግር ግን ይህ አይደለም። ህብረተሰቡ የእርሻ መኪናው በአጭር ጊዜ ሰፊ መሬትን ስለሚያርስ በተለይ ሰፋፊ እርሻ ላላቸውና በማህበር ለሚያርሱ፣ አረምን በመድሃኒት ማጥፋት ለሚፈልጉና ሁሉንም ነገር በገንዘብ ለሚያሰሩ ሰዎች ጠቃሚ ነው። ተራው ገበሬ ግን የራሱ የልጆቹና የበሬዎቹ የተትረፈረፈ ጉልበት ስላለው፣ አብዛኛው የእርሻ መሬት በሬ እንኳ የማይገባበት በቁፈራ የሚዘራ በመሆኑ ቀድሞውኑ በበሬ ማረስ ምርጫ ሳይሆን አማራጭ የሌለው የኑሮ ግዴታ እንደሆነ መረዳት ተችሏል።

የእርሻ መኪናን ለመጠቀም የሚያስችሉና የማያስችሉ ተብለው የቀረቡት ማሳመኛ ነጥቦች ህብረተሰቡ ከየትኛውም ዘመናዊ ትምህርት ቤት ሳይሆን ከራሱ ልምድ ያገኛቸው መሰረታዊ እውቀቶቹ ናቸው። በተለይ ገበሬው ለምን "ኋላቀር" አስተራረስ ይጠቀማቀል ለሚለው ጥያቄ በምንባቡ ከቀረበው ሃሳብ ይልቅ ከህብረተሰቡ የተገኘው ምላሽ አሳማኝነት አለው።

በሰፋፊ የመንግስትና የአውራቾች (Inevstors) እርሻ ውስጥ ብለው ባይገልፁትም የትራክተር ተፈላጊነት የት አካባቢ እንደሆነ ማመልከት ችለዋል። እንደዚህ አይነቶቹ ሰፋፊ እርሻዎች አረም ለማጥፋትም፣ ለማጨድና ለመውቃትም ዘመናዊ መሳሪያዎችን ለመገልገልም እንደሚያመቹ በሚገባ አብራርተዋል። በጠባብ የግል ይዞታዎች ውስጥ የእርሻ መኪና መጠቀም የሚያስከትለው ጉዳትንም አሳይተዋል። ለምሳሌ ሁለትና ሶስት ጥማድ መሬት ያለው ገበሬ ለአቅመ አዳም የደረሱ ሶስት ልጆች፣ ሁለት ጥንድ በሬ ካለው፣ የእርሻ መኪና የሚፈልግበት ምንም ምክንያት አይኖረውም።

አገር በቀል ህዝቦች (አበህ) ለማህበራዊነት (ወላዊነት) ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጡ ተደጋግሞ ተገልጿል። ከመገለጫዎቹ አንዱ የእርሻ መሬት ወሰንን በጋራ መጠበቅና እዚያ የሚበቅለውን ሳር በመተሳሰብ በጋራ መገልገል መቻል ነው። አንድ ገበሬ በበሬ ሲያርስ አንድ ፊር ዘልቆ ለመዞር ሲፈልግ የጎረቤቶቹን እርሻ መርገጡ የግድ ነው። ድቡ በማረሻ ሊወጋው ይችላል። ነገር ግን ሆነ ብሎ እስካልፈፀመው ድረስ ይቅርታ በመጠየቅ ሊታለፍ

ይችላል። በዚህ ጠባብ መሬት የእርሻ መኪና ከገባ ለመዞር የብዙዎቹን አጎራባቾች እርሻ ሊያበላሽ፣ ወሰን ሊያፈርስ ይችላል። ተዘርቶ ከሆነም ሰፊ ቡቃያ ሊጠፋ ይችላል። ህብረተሰቡ ይህንን በትእግስት አያልፈውም። ደም ሊያፋስስ በጋራ ተጠብቆ የኖረውን ማህበራዊ ኑሮ ሊያናጋና ሊያፈርስ ይችላል። የእርሻ መኪና ላለመጠቀም ከሚያግዱት ማህበረሰባዊ ግዴታዎች አንዱም ይኸው የመሬት ጥበትና ለእርሻ መኪና ምቹ አለመሆን ነው።

በምርት ስብሰባ ወቅት ህብረተሰቡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል። የደረሰ እህልን ለማጨድ እርጥበት አስፈላጊ እንደሆነ ያምናል። ምክንያቱም እህሉ መቁሙ ስለደረቀ በአጨዳ ጊዜ እየተሰባበረ እንዳይረግፍ ስለሚከላከል ገና ጤዛው ሳይረግፍ በሌሊት ያጭደዋል። ሲወቃ ደግሞ እህሉ እንዳያምል በቂ ፀሓይ አግኝቶ መድረቅ አለበት። በሚገባ ከደረቀ ምርትና ገለባውም ቶሎ ይለያያል። ነገር ግን ከአጨዳ ጀምሮ የፀሃይ ሙቀት የሰበሰበው ምርት እንዳለ ወደጎተራ ሲከተት ሙቀቱ ለነቀዝ መፈጠር ምክንያት ይሆናል። ይህንን ተባይ ለመከላከልም ምርቱን ለውርጭ ሰጥቶ አድሮ በማለዳ ያፍሰዋል። እህሉ ተወቅቶ እቤት ከገባ በኋላም በተለያዩ ተባዮች እንዳይጠቃ ለመከላከል የሚያስችሉ አገራዊ እውቀቶች አሉት፡፡ እውቀቶቹ ምን ምን እንደሆኑና እንዴት ተግባር ላይ እንደሚውሉ መረጃ አቀባዮቹ በሚከተለው መንገድ ገልፀውታል።

> *ከአጨዳ ጀምሮ የምናደርገው ጥንቃቄ ኣለ፡፡ ይኸውም እህል ሲታጨድ በደንብ መድረቁ ይፈተሻል፡፡ እርጥበት ያለው ዘለላ ወይም ቅጠል ኣብሮ እንዳይከማች ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡ በኣጨዳ ወቅት ተሰባብሮ እንዳይረግፍም በሚያጤዝበት ሰዓት ይታጨዳል፡፡ ወደ ኣውድማ ወስደን ስንከምርም በምስጥ እንዳይጠቃ ጉልቻ ላይ የእንጨት ርብራብ እናዘጋጃለን፡፡ ከዚያም የብሳና ቅጠል እናደርግበታለን፡፡ እላዩ ላይ እህሉ ይከመራል፡፡* (ቃመ. ደቡ.1፣ 6-12-2004 ዓ.ም.)

የቃለመጠይቅ ተሳታፊ ገበሬዎች፣ ምርት እንዳያምል ጥንቃቄ የሚደረግለት ገና ከአጨዳ ጀምሮ እንደሆነ ያስረዳሉ። በአጨዳ ጊዜ በደንብ ያልደረቀ ወይም እሸት ዘለላ እንዳይኖር ጥንቃቄ ይደረጋል። የዚህ አይነት ዘለላ ካጋጠመም ተለቅሞ ይወጣል። እህሉ በዝናብና በጤዛ ምክንያት እርጥበት ሊይዝ ስለሚችል ከታጨደ በኋላ ሶስት ደረጃዎችን አልፎ በአራተኛ ደረጃ ይከመራል።

ከኣጨዳ በኋላ በእቅፍ በእቅፍ መጠን እርሻው ላይ ተዘርሮ ለነፋስና ፀሃይ ይጋለጣል። ይህ ተግባር **ምግብላው** ይባላል። በመቀጠል ሶስትና ኣራት እቅፍ ሊይዙ በሚችሉ **ቅሚጦዎች** ትናንሽ ክምሮች ይከመራል። ከጥቂት ቀናት በኋላ ቅሚጦዎች **ወደናዕሪ** (መካከለኛ ክምር) ያድጋሉ። ናዕሪም በቂ ፀሓይና ነፋስ ማግኘቱ ሲታመንበት ወደሚወቃበት ኣካባቢ ተወስዶ የመጨረሻ **ኩልሳስ** (ክምር) ይከመራል። ክምሩ ሳይወቃ ሊቆይና በመሃሉም ዝናብ ሊዘንብ ስለሚችል ከላይ ውሃ እንዳያሰርፅ በሳር ቤት ኣሰራር መልክ ይከደናል። ከስር ደግሞ እርጥበት እንዳይሰማው ከስር ድንጋይ በመደርደር እላዩ ላይ የእንጨት ርብራብ ይሰራል፡፡ ምስጥ ለመከላከል ደግሞ የብሳና ቅጠል ይጎዘጎዝበትና እህሉ ይከመራል፡፡

> *ምርት ከገለባ ተለይቶ ለመታፈስ ዝግጁ ሲሆን እንዲቀዘቅዝ የምሽት ወይም የማለዳ ውርጭ እንዲያርፍበት ይደረጋል፡፡ እህል ነቀዝ ሊፈጥር የሚችለው በውስጡ ሙቀት ሲኖር ነው፡፡ የታፈሰበት ወቅት ቀዝቃዛ ከሆነ፣ እቤት ያለው ማከማቻም ቀዝቃዛ ከሆነ ነቀዝ ሊፈጠር ኣይችልም፡፡ (ቃመ.ማ.* 3 07.7.2005)

ህብረተሰቡ እነዚህን ከልምድ ያገኛቸው እውቀቶች ተጠቅሞ ምርቱን ከብክነት ጠብቆ ይሰበስባል። እህሉን በውርጭ ኣቀዝቅዞው ካፈሱት በኋላም በተለያዩ ምክንያቶች በማከማቻው ውስጥ ነቀዝ ሊፈጠር ስለሚችል የመከላከያና ማጥፊያ መድሃኒት ይጠቀማል።

> *ኣመድ የነቀዝ መከላከያ መሳሪያችን ነው። የፍየል በጠጥ ኣመድ ኣለዚያም የእንጨት ኣመድ ከተነፋ በኋላ ውርጭ ላይ ያድራል።ከነቅዝቃዜው እያለም ከእህሉ ጋር ይቀላቀልና ቀፎው ውስጥ ይገባል። በዚህ መልክ ቅዝቃዜው ተጠብቆለት የተቀመጠ እህል በነቀዝ ኣይበላም። የኣመዱ ድርሻም በቀፎው ውስጥ ሙቀት እንዳይፈጠር መከላከል ነው። የጠላ ኣተላና ጮቤም በኣካባቢያችን የተለመዱ የነቀዝ መከላከያና ማጥፊያ መድሃኒቶች ናቸው። (ቃመ.* ምብ. 7፣ 25.08.2004 *ዓ.ም.)*

እህሉ የሚከተትበት ጎተራ፣ ቀፎ፣ (ጉድጓድ በራያ፣ ለማሽላ ብቻ) ከእርጥበት ነፃ መሆኑ ይረጋገጣል። ሌላው በነቀዝ እንዳይበላ መከላከል ነው። እህሉን በኣመድ እያሹ ጎተራ ውስጥ ማስገባት ኣንዱ መከላከያ መንገድ ነው። ጎተራው ውስጥ የጠላ ኣተላ በማስቀመጥም ነቀዝን ማጥፋት ይቻላል። መረጃ በተሰበሰበባቸው ሶስት ዞኖች የነቀዝ መከላከያም ማጥፊያም ሆኖ የሚያገለግል መድሃኒት ደግሞ **ጮቤ** የሚባል ቅጠል ነው። ቅጠሉ ከተጨቀጨቀ በኋላ

ከነውሃው በመያዣ ተደርጎ ትትራው ወይም ጉድጓዱ ውስጥ በአንደኛው ጥግ ይቀመጣል። የፈሳሹ ትነት ነቀዝ እንዳይፈጠር ይከላከላል፤ ተፈጥሮ ከሆነም ያጠፋዋል።

ከላይ የተጠቀሱት የነቀዝ መከላከያና ማጥፊያ መድሃኒቶች ህብረተሰቡ ምርቱ እንዳይባክንበት ሲል የፈጠራቸው፣ በሙከራ ያዳበራቸውና ለዘመናት የተገለገለባቸው እውቀቶቹ ናቸው። ስለዚህ በምንባቡ፡- ህብረተሰቡ "ምርቱን በአግባቡ አይንከባከብም፣ አይጠቀምበትም፣ በአያያዝ ጉድለት ምክንያት በነቀዝ፣ በአይጥ፣ በእርጥበት ምክንያት በማመል ተበላሽቶ ይቀራል" የሚሉት ሃሳቦች ህብረተሰቡ ከላይ በቀረቡትና ቀጥሎም በምናየው መረጃ ምክንያት አይቀበላቸውም።

> *ምርታችን በአይጥ እንዳይበላ ከምንከላከልባቸው ባህላዊ ዘዴዎች አንዱ አመድ ነው። ምርት ታፍሶ ቀፎ ውስጥ ከገባ በኋላ ከላይ ጭድ ይነዘነዘበታል። ጭዱ ላይ ደግሞ አመድ ይደረግበታል። አመዱ አይጧን እንደልብ እንዳትንቀሳቀስ ስለሚያግዳትና ለመሰርሰር ብትሞክርም ስለሚያሰምጣት አትደፍረውም።* (*ቃመ.ማ* 1፡12.12. 2004*ዓ.ም.*)

ከዚህ ገለፃ መረዳት የሚቻለው፣ ምርት ሊያጠቁ የሚችሉ ተባዮች ቢኖሩም ህብረተሰቡ ከልምዱ ያገኛቸው መከላከያ እውቀቶች ያሉት መሆኑ ነው። አይጥ የእህል ማስቀመጫ ቁሶችን በመብሳት ከፍተኛ የምርት ብክነት እንደምታደርስ ይታወቃል። ገበሬውም ይህንን አደጋ የሚከላከልበት እውቀት አለው። የአይጥ እግሮች ቀጫጭን ናቸው። ስለዚህ እጅግ በላመ ዱቄት ውስጥ ገብታ አደጋ ማድረስ እንደማትችል ታዝቧል። ስለዚህ ሌላውንም እህል እንዳትበላ የቀፎውን አፍ በአመድ በመሙላት ይከላከላታል።

ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ህብረተሰቡ የሚያረባቸውን እንስሳት እንደማይንከባከብ ተጠቅሷል። ይህ አባባል ትክክል መሆኑ ለማረጋገጥ በቃለመጠይቅና የቡድን ውይይት ለተሳተፉት የእድሜ ባለፀጋዎች ጥያቄ ቀርቦ ነበር። ይኸውም የእንስሳት መታመም እንዴት እንደሚያውቁና ምን ህክምና ወይም እንክብካቤ እንደሚያደርጉላቸው ለማወቅ የሚያስችል ነበር። ከሁለቱም አካላት የተገኘው ምላሽም ቀጥሎ ቀርባል።

> *አንዳንዱ በሽታ ከሰውነታቸው በሚወጣ ፈሳሽ፣ በፀጉራቸው፣ በአካሄዳቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በአካላቸው ላይ በሚታይ እብጠት ወይም ቁስለት ይታወቃል።* (*ቃመ.* ምብ.2፣ 25-08- 2004ዓ.ም.፣ *ቃመ.ማ*.1፣ 12-12-2004ዓ.ም.፣ *ቃመ.* ደቡ. 2፣ 06-12-2004 ዓ.ም.)

*ከብቶች ሲታመሙ እንደየበሽታው አይነት የተለያዩ ምልክቶች ያሳያሉ። ምልክቶቹም ከአየት ቅድመአየት ጀምሮ ያየናቸው ስለሆኑ የትኛው በሽታ እንደያዛቸው ማወቅ እንችላለን። አንዳንዱ በሽታ፡- ከሰውነታቸው በሚወጣ ፈሳሽ ይታወቃል። አንዳንዱ በፀጉራቸው ሁኔታ ይለያል። ሌላው ደግሞ በሚያሳዩት ባህሪ ይታወቃል። ለምሳሌ ጎንብሳ/ ሓላፌን መስከረም ወር አካባቢ የሚከሰት የከብት በሽታ ነው። በዚህ በሽታ የተያዘ ከብት ፀጉሩ ይቆማል፤ ጢስ የጠላበት ይመስላል። አፉ አካባቢ በጣም ይሞቃል። መብላትም ማመስኳትም (መኹስዕ) ያቆማል። አይሸናም፣ እበቱንም አይጥልም፡፡ መድሃኒት ሳያገኝ ከቆየ ደግሞ ጉልበቱ ስለሚከዳው አልንቀሳቀስ ይላል። ከብቱ ታሞ እያለ ውሃ ከጠጣና እርጥብ ሳር ከበላ ወድያውኑ ሊሞት ይችላል። (ተበው 2፣ 07-5-2005)*

እነዚህ ምላሾች በተለያየ መልክ ቢገለፁም በቃለመጠይቅ በተሳተፉትና በአራቱም ተኮር ቡድን ውይይት ውስጥ የተንፀባረቁ ናቸው። ማህበረሰቡ ባዳበረው እውቀት መሰረት የትኛው በሽታ ምን ምልክት እንዳለው ጠንቅቆ ያውቃል። ምልክቶቹን በትክክል ይለያል። ስለሆነም መድሃኒት የማወቅና በአግባቡ የመጠቀም ካልሆነ የአሻሚነት ችግርም አይከሰትም። ሁሉም ተሳታፊዎች ከብቶችን የሚያጠቁ የተለያዩ በሽታዎች እንዳሉና በተለያየ ቦታ የተለያየ ስም እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ (1) ቆምቶ ወይም ቆፋ፣ (2) ጎንብሳ ወይም ሓላፌን፣ (3) አቅልጥ፣ ጉልሓይ ወይም ደግሃበ ሶስቱ የበሽታ አይነቶች ሆነው የተለያየ ስም አላቸው፡፡ ጣፊያ ጭልዓምና እባጭም በሁሉም አካባቢ በተመሳሳይ ስም የሚታወቁ የበሽታ አይነቶች ናቸው፡፡

***የጎንብሳ (ሓላፌን)፡-*** *መድሃኒቱ አፍንጫው፣ ቋንጃው ወይም እምብርቱ አካባቢ መብጣት ነው፡፡ ለሶስት ቀን ውሃ እንዳይጠጣ፤ እርጥብ ሳር እንዳይግጥ ይከለከላል። ባለሙያው ከሚገባ በላይ ያበጡትን የደም ስሮች አይቶ ይበጣቸዋል፡፡ ከሰል መሰል ጥቁረት ያለው ደም ከፈሰሰ እንስሳው ወድያውኑ ለውጥ ያሳያል፣ መመገብም ይጀማራል፡፡ ሓላፌን ከከብት ወደከብት አይተላለፍም፡፡ ስለሆነም ማግለል ሳያስፈልግ ይታከማል። (ተበው 1፣ 14-04-2005፣ ተበው 2፣ 07-05-2005)*

ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ባደረግኩት ውይይት ጎንብሳም በየዞኑ የተለያየ ስያሜ አለው። ነገር ግን ምልክቶቹ ሲጠቀሱና መድሃኒቱ ሲዘረዘር ስለአንድ የበሽታ ዓይነት እየተናገሩ መሆናቸው መገንዘብ ችያለሁ። በማእከላዊና ምስራቅ ዞን አካባቢ ሓላፌን የተባለው በሽታ በደቡብ ጎንብሳ፣ ጎንይሳ የሚል ስያሜ አለው። ሁሉም የሚስማሙበት ጉዳይ ሕክምናው ነው። ምንም እንኳን አብዛኛው ገበሬ ምልክቱን አይቶ በሽታውን የሚያውቅ ቢሆንም

የሚበጣው ግን ልምድ ባለው አበ ሃኪም ነው። ገበሬው በሽታው ምን እንደሆነ እያወቀ እንኳ ባለሙያን ያማክራል እንጂ ለማከም አይችኩልም።

ጣፋ (ጣፌ፣ ላልሽ) ሌላው የከብት በሽታ ነው። በሁሉም ወረዳዎች ያነጋገርኳቸው የቃለመጠይቅና የቡድን ውይይት መረጃ አቀባዮቹ እንደጠቀሱት ከብቱ በተደጋጋሚ ለመብላት እየሞከረ የሚተው ከሆነ፣ ሽንቱ ኮረፋት ከበዛበትና ትንፋሹም ቁርጥ ቁርጥ የሚል ከሆነ የጣፊያ በሽታ እንደያዘው ይታወቃል። እግሮቹም ይተሳሰሩና ስብራት እስኪመስል ድረስ ያነክሳል። በሽታው በመተኮስ የሚጠፋ ሲሆን የሚተኮሰውም ጣፊያ በምትገኝበት በግራ ጎኑ ነው። የሚተኮሰው ቦታ የሚለየው ደግሞ ከግራ ጎኑ የኋላ ክፍል ወደፊት ሶስት አጥንት በመቁጠር ነው። አራተኛ፣ አምስተኛና ስድስተኛ አጥንት ላይ በእበት ምልክት ይደረግና ከብቱን ጥሎ ምልክቱ ላይ በማጭድ ወይም በጉባ በባለሙያ ይተኰሳል።

> *ቆፋ (ቆምቶ)፡- በከብቱ ውጫዊ አካል ሊታይ የሚችል እብጠት ነው፡፡ ከብቶችን በስፋት ያጠቃል። እብጠቱ እከብቱ እግር አካባቢ ከሆነ ያነክሳል። ሌላው አካሉ ላይ ከሆነ ግን እብጠቱ ብቻ ይታያል፡፡ቆፋ መሆኑ ለማረጋገጥ እብጠቱን ሲዳብሱት የታመመው ክፍል ኩፍ የማለትና እንደኮረፋት የመንኮሻኮሽ ድምፅ ያሰማል። ገበሬውም በሽታውን ካረጋገጠ በኋላ ከብቱ ቤት እንዲውል ያደርጋ።* (ተበ·ው. 1፣ 14-04-2005)

ከብቶች የተለየ ስሜት ወይም አካላዊ ለውጥ ሲያሳዩ ህብረተሰቡ ዝም ብሎ መድሃኒት አይሰጣቸውም። ምንነቱን በተለያየ መንገድ ያረጋግጣል፤ ቀጣዩ ተግባር መድሓኒት መስጠት ነው። የቆፋ መድሃኒት መብጣትና መተኮስ ናቸው። እባጩ ይበጣና ቆሻሻውን ያወጡታል። በተበጣው በኩል ወተት ወደውስጥ ያስገቡና በእጅ እየተጫኑ መልሰው ወደውጪ ያስወጡታል። ከተበከለው ቆዳ የሚወጣ ፍሳሽ ሌላውን አካል እንዳይበክል እባጩ የነበረበት ቦታ ዙሪያው ይተኮሳል። ከሶስት ቀን በኋላ ከብቱ ጤንነቱ ይመለሳል፤ ወደ መንጋው ይቀላቀላል። ይህ የምርመራና ህክምና ስራም ካለፈው ትውልድ የተወረሰ አበእ ነው። በህብረተሰቡ ውስጥ የታየው እውቀት፣ ህክምና የመስጠት ብቻ ሳይሆን የከብቱ ህመም ወደ ሌላው አካሉ እንዳይተላለፍ የመከላከል ስራም ይጨምራል። ለምሳሌ በቆፋ በመያዙ የተበጣው ከብት ከቁስሉ የወጣው ፈሳሽ ሌላውን አካል እንዳይበክል ዙሪያው እንደሚተኰስ ተጠቅሷል። በዚህ መንገድ በንኪኪ ሊመጣ የሚችልን ጉዳት ይከላከላል።

*መገረም፡-* *እባጩ በከብቶቹ የትኛውም አካል የሚታይና ከቆዳ ጋር የሚመሳሰል የእባጭ አይነት ነው። መለየው የቆዳ በሽታ እብጠት ሲነኩት የመኩረፍረፍ ድምፅ ያሰማል። የመገረም ግን ሲነኩት የደደረ ነው። ከውጪ የሚታይ ቁስል ባይኖረውም ከውስጥ ስለሚጠዘጥዝ ከብቶቹ እባጩን ደጋግመው ሲየኩት ይታያሉ።* (ተቡው 4፣ 18- 02-2005)

ተጋሩ፤ እንደሌሎቹ በሽታዎች ሁሉ መገረምንም ለማከም የሚያስችል እውቀት አላቸው።

*የሁለቱ ህክምና ስለሚለየይ መጀመሪያ እባጩ የመገረም መሆኑ በባለሙያ ይረጋገጣል። ህክምናው ዳልጋ አካባቢ በመብጣት መድሃኒት በመቅበር ይከናወናል። ከተወሰኑ ሰዓታት ወይም ከአንድ ቀን በኋላ በየትኛውም አካባቢ የነበረው እብጠት መሟሸሽ፣ በዳልጋው አካባቢ ደግሞ መግልና ደም የቀላቀለ ፈሳሽ መፍሰስ ይጀምራል። እብጠቱ ሲጠፋ ፈሳሹም ይቆማል።* (ቃመ. 15፣ 03-10-2005)

ህብረተሰቡ ልክ በቆዳ ላይ እንዳደረገው የእብጠት ፍተሻ በመገረም ላይም ያካሂዳል። በትክክል በመገረም ምክንያት የመጣ እባጭ መሆኑ በእጁ ዳብሶ ያረጋግጣል። የመገረም እባጭ የደደረ ሆኖ ውስጡ ስለሚጠዘጥዝ ከብቱ ደጋግሞ ሲያክከው ይታያል። እነዚህ ሆኔታዎች ሲረጋገጡ መድሃኒት ይቀበርለታል። እብጠቱ ሙሉ በሙሉ ሲጠፋም የተበጣው አካል ሊያመረቅዝ ስለሚችል ለተወሰነ ጊዜ ጨው በበዛበት ለብ ያለ ውሃ ወይም በከብት ሽንት ይታጠባል። መገረም ከእንስሳት ወደሰው የሚተላለፍ በሽታ ስለሆነ በዚህ በሽታ ታሞ የሞተ ከብት ስጋ ይቀበራል እንጂ ሰው አይበላውም። ይህም በተሞክሮ ያዳበረው አገራዊ እውቀቱ ነው። ህብረተሰቡ በተለይ ስብራትና የአጥንት ውልቃት አሁንም ከአገር በቀል ሃኪሞች እንጂ በአካባቢው ካሉ "ዘመናዊ"የህክምና ተቋማት የማያገኛቸው ህክምናዎች ናቸው።

ከላይ እንደተመለከተው ህብረተሰቡ አንዱን በሽታ ከሌላው መለየት የሚስችል እውቀት አለው። በሽታዎችን ለማከም የሚያስችሉ አገር በቀል መድሃኒቶችም አለው። እነዚህ የበሽታ ምልክቶችም ሆኑ የህክምና እውቀቶች፣ ጥናት በተካሄደባቸው የትግራይ አካባቢዎች አንድ አይነት መሆናቸው እውቀቱ የጋራ ነው ለማለት ያስችላል። ለምሳሌ ከብቱ የሚተኮሰው ጣፊያ በምትገኝበት በኩል መሆኑና የጣፊያዋን ቦታ በትክክል ለማግኘት ሲባል የሚካሄደው የጎድን አጥንት ቆጠራ በሁሉም አካባቢ አንድ ዓይነት መሆን ህክምናው

በእውቀት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ያመለክታል። ተለክቶ የተገኘውን አካል በእበት መክበቡ ደግሞ ግምትን ለማስወገድና ያልታመመውን አካል ላለመተኮስ የሚደረግ ጥንቃቄና ምጠና ነው። በሙያው በሰለጠኑ ዘመናዊ የከብት ሃኪሞች የሚሰጠው መድሃኒት አገር በቀሉ ህዝብ ያገኘውና በሙከራ ያዳበረው አይደለም። ስለሆነም ገበሬው በባለሙያዎቹ ላይ እምነት በመጣል ብቻ ነው መድሃኒቱን ለከብቶቹ የሚሰጠው። አበ መድሃኒት ግን ቀደምት የህብረተሰቡ አባላት በኖሩባቸው ዘመናት ውስጥ እየተሞከረ የመጣ ስለሆነ ከብቶቹም ወዲያውኑ እንደሚድኑ እርግጠኛ ሆኖ ይሰጣቸዋል።

ከብቶቹ ህክምና ካላገኙ ገበሬው ከነሱ የሚያገኘው ጥቅም እንደሚጎድልበት ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ ዘመናዊው ህክምና በሚሰጥበትና ለዚህ ዓይነቱ ህክምና ቅርበት ባለው ቦታ ሆኖ ከብቱን መብጣትና መተኮስ እንስሳትን ማሰቃየትና የቆዳ ምርትን ማባከን ተደርጎ ስለሚወሰድ ድርጊቱ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን ቀደም ባለውና አማራጭ ባልነበረበት፣ አሁንም አማራጭ ባልቀረበባቸው አካባቢዎች የሚኖር ገበሬ በተለያዩ አገር በቀል ዘዴዎች ከብቶቹን አክሞ ከእልቂት መጠበቁና መንከባከቡ የኔ የሚለው እውቀት እንዳለው እንጂ ኋላቀርነቱን አያመለክትም።

ከላይ በተሰጠው ገለፃ መሰረት በምንባቡ የቀረበውና ህብረተሰቡ ለቤት እንስሳት እንክብካቤ እንደማያደርግ የሚያብራራው ሃሳብ ህብረተሰቡን ጠልቆ ካለማወቅ የመነጨ ይመስላል። መረጃዎች የሚያመለክቱት፣ ህብረተሰቡ እንስሳቱን ሲያረባ የእለት ተእለት ደህንነታቸውን የሚከታተል መሆኑ ተመልክቷል። በአጠቃላይ በእርሻ ስራው፣ በምርት አሰባሰብና አጠባበቅ በእንስሳት እንክብካቤና ህክምና የኔ የሚለው ነባር እውቀት እንዳለው መገንዘብ ተችሏል።

**ጦጣና አንበሳ፣ በሂዱበት የሚያስቀር መልእክት፣ እንቆቅልሽ** የሚሉት ምንባቦች ደግሞ በተለመደ የተረትና እንቆቅልሽ አቀራረብ ስልት የቀረቡ ናቸው። በምንባቦቹና ከምንባቦቹ በወጡ መልመጃዎች አማካይነት ወደ ተማሪዎች ምን ምን አበ እውቀቶች እንደተላለፉ እንመለከታለን።

*ጦጣና አንበሳ*

*ብዙውን ጊዜ ጦጣ በተንኮለኛነት፣ አንበሳ ደግሞ በሃያልነቱ ነው የሚታወቁት። አንድ ቀን አንበሳ እንደጦጣ ተንኮል አሰበ። ጦጣ ከዋለችበት ቦታ ሳትመለስ*

*እቤትዋ ገብቶ ተደበቀ። ሃሳቡም እስዋ ወደቤትዋ ስትገባ ቀረጣጥፎ ለመብላት ነበር።*

*ጦጣም እቤትዋ አካባቢ ስትደርስ ቅፍፍ አላት። ገና ሳትጠጋ "ቤቴ ውስጥ ያለው ማን ነው?" ስትል ጠየቀች። አንበሳ ደግሞ ቤት ውስጥ እስክትገባለት እየጠበቀ አደፈጠ። ጦጣ ደግሞ " ድሮ ድሮ የቤቴ እንግዳ እኔ ከበረሃ ስመለስ መኖሩን ለማረጋገጥ ጉሮሮውን እየጠራረገ ድምፅ ያሰማኝ ነበር። እኔም ገብቼ እህልና ውሃ አቀርብለት ነበር። የዛሬው እንግዳ ግን ድምፁም አይሰማ። ምኝ ነው መሰለኝ? አለች። አንበሳም "ይቺ ተንኮለኛ ድምፅ ካላሰማሁ አትገባም ማለት ነው" ሲል አሰበና ድምፁን አሰማ።*

*ጦጣም "በል በል አየ አንበሶ ደህና እደር፣ ቤቴን ሰጥቼሃለሁ እኔን ግን አታገኘኝም" በማለት ቤትዋን ጥላለት እብስ አለች። በብልጠትዋም ከሞት አመለጠች ይባላል።* (2ኛ ክ. ገፅ 1)

ከሁሉም በፊት ህፃናት እንዲያነቡት የቀረበላቸው ምንባብ ተረት በመሆኑ ሊደነቁም ሊደሰቱም ይችላሉ። ተረት በቤተሰብ መሃል እንጂ በትምህርት ቤት ውስጥ እውቀት ሆኖ እናገኘዋለን ብለው ላይገምቱ ይችላሉ። ከቤተሰቦቻቸው የሰሟቸው ተረቶች በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ሲያገኟቸው ለተረት የሚሰጡት ግምት ከፍ ይላል። ተረት እያዝናና የሚያስተላልፈውን እውቀት (LittleBear, 2009) ሲገነዘቡ ደግሞ ተረት ቀልድ ብቻ አለመሆኑ ያውቃሉ። ለምሳሌ ከላይ የቀረበው ተረት፤ ትግራዋይ ብልጠትንና ጉልበትን ለይቶ እንደሚያይና ሁለቱም ተፈላጊ የሚሆኑበት መድረክ እንዳላቸው ያስገነዝባል።

እያንዳንዱ ሰው የየራሱ ተሰጥኦ አለው። ያለተሰጥኦው የሚሰማራ ሰው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። አንድ ሰው አዘውትሮ በጉልበት ስራ ይሰማራል። ሌላው ሰው ደግሞ አንድም ቀን በጉልበት ስራ ተሰማርቶ አያውቅም። የጉልበት ሰራተኛው የሚሰራውን ስራ የሚነድፈው፣ የሚያቅደውና በትንሽ ጉልበት ብዙ ለማምረት የሚያስችል ስልት የሚቀይሰው የአእምሮ ሰራተኛ ሊሆን ይችላል። ሁለቱ ሰዎች አንዱ የሌላውን ስራ ለማከናወን ቢሞክሩ ላይሳካላቸው ይችላል። አንበሳ በብልጠት ቦታ እንዳልተሳካለት ሁሉ ጦጣም በጉልበት ቦታ ሊሳካላት አይችልም። ተጋሩ በእንስሳት ገፀባህሪነት መጥፎና ጥሩ ባህርያትን፣ ተግባራትን፣ እምነትን ሁሉ ያስተምራሉ። የሁለቱ እንስሳት የታወቀ ባህርይ የታወቀ የስራ ድርሻ እንዲኖራቸው አድርጓል፤ አንበሳ በሃይሉ መንገስ፣ ጦጣ በጥበብ መኖር። ህብረተሰቡ ሊያስተምር የፈለገው እውቀትም፤ ሁሉም ሰው የየራሱ የሆነ ተሰጥኦ አለው። በማይችሉት ሙያ ላይ መሰማራትም ውጤታማ አያደርግም። ጥበብና ሃይል

ተዋህደው ግን ጥሩ ነገር ሊያስገኙ ይችላሉ። **“ጎናይ ብዓይኑ ዕውር ብእግሩ ኣብድላዮም ይሓድሩ”** (ዓይነስውር በእግሩ፣ መፃጉእ በአይኑ ተደጋግፈው እፈለጉበት ያድራሉ።) ጤናማ እግርን እና ጤናማ አይን ተቀናጅተው የፈለጉትን መስራት እንደሚችሉ ያስተምራል።

በመልመጃ ሶስት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ግን *‘ጠጣ ከሞት እንዴት እንዳመለጠች ተናገሩ፤ ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ያገኛችሁትን ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው’* ይላሉ እንጂ ተረቱ ምን እውቀት ለማስተላለፍ እንደፈለገ ወላጆቻቸውን ጠይቀው በመምጣት  እንዲናገሩ እንኳ አያደርጉም። ምንም እንኳ ምንባቡ አበእን ለማስተማር የሚመች ቢሆንም በመፅሓፉ ውስጥ ግን ትኩረት ኣላገኘም። ተረቱ  እንደሌላው ምንባብ ሁሉ የቋንቋ ክሂሎችንና ስነልሳንን ለማስተማር ብቻ ነው ያገለገለው።

### *በሂዱበት የሚያስቀር መልእክት*

የተረቱ ሙሉ ይዘት ማቅረብ ስላልተቻለ እንደሚከተለው ተጨምቆ ቀርቧል፤

> *የዱር እንስሳት በብርድ ስለተሰቃዩ ውሻ እሳት እንዲያመጣላቸው ወደሰው ላኩት። እሱም ሊሊት እሳቱን ይዞ ለመውጣት እንዲችል ሰው ሳያየው ቤት ውስጥ ገብቶ ተደበቀ። ሊሊት ሙጭጭላ ሾልኮ ገባና የሰውን ወተት መጠጣት ጀመረ። ውሻም ሙጭጭላን ኣንቆ ገደለው። ሰው ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሳ ውሻ ሙጭጭላን ኣንቆ እንደያዘው ኣየ። ወተቱን ሲጠጣበት የኖረው ጠላት በመሞቱ ተደሰተ። ውሻንም ኣብሮት እንዲኖር ፈቀደለት። ውሻም የተላከበትን ዓላማ ረስቶ፣ ኑሮውን ከሰው ኣድርጎ ሳይመለስ ቀረ።* (ቢትክ፣ 1995 ዓ.ም.)ከ2ኛ ክፍል *መፅሓፍ ገፅ* 7-9 በጣም ኣሳጥሮ የተወሰደ።

በዚህ ተረት ሁለት የማህበረሰብ እውቀቶች ተንፀባርቀዋል። ኣንዱ የክርስትና ሃይማኖት እምነትን የጠቀሰ (ታሪክ ጠቃሽ) እውቀት ነው።  እውቀቱ ከማየ ኣይህ ታሪክ ጋር ተያይዞ የኖህ እና የቁራ ሁኔታን ያስታውሳል። በኖህ መርከብ ውስጥ ከተሳፈሩት የኣእዋፍ ዘር ኣንዱ ቁራ ነበር። ኖህም የመሬትን ሁኔታ ኣይቶ እንዲመጣ ቁራን ላከው። ቁራ በመርከብ ውስጥ ያለውን ፍጡር ሁሉ እድል የሚወስን ምላሽ ይዞ እንዲመጣ ትልቅ ሃላፊነት ተሰጥቶት ሄደ። እሱ ግን ሃላፊነቱን መወጣት ኣልቻለም። ከሱ በኋላ የተላከች እርግብ የምስራች ይዛ ስትመለስ ቁራ ግን በዚያው እንደወጣ ቀረ (ኦሪት ዘፍጥረት፣ ምዕ.8፤ቁ.1-12)።  ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ህብረተሰቡ ተልኮ በዚያው የቀረን ሰው **የቁራ መላክተኛ** በማለት ይጠራዋል።  የቀረበው ተረትም ውሻ፣ ለራሱ ስለተመቸው በጉጉት የሚጠብቀውን ምድረ እንስሳ ወገኑን ረስቶ በዚያው መቅረቱ በስነምግባር ደረጃ ሲታይ ትልቅ ስህተት መሆኑን ያስተምራል። ስለዚህ ህፃናት  እንደውሻው ወይም እንደቁራው

እንዳይወቀሱ የተላኩት ነገር በጊዜው ማድረስ እንዳለባቸው ያስገነዝባል። የተረቱ ሁለተኛው መልእክት ክህደትን እንዲጠየፉ የሚያደርግ ነው። 'በጥቅም ተገዝቶ ወገንን መክዳት ነውር መሆኑን ያሳያል። ህፃናቱ እነዚህን እውቀቶች የሚቀስሟቸው በነገራና በትእዛዝ ሳይሆን እየተዝናኑ የእንስሳውን መጥፎ ተግባር ይገነዘባሉ። እውቀቱ ሲሰርፅ ባህሪውን መጠየፍ ይጀምራሉ።

***እንቆቅልሽ***

*እንቆቅልሽ፣ ልጆችና ወጣቶች ተሰብስበው **ጊዜ ለማሳለፍ** የሚጫወቱት የጨዋታ አይነት ነው። ጨዋታው በጥያቄና መልስ የሚካሄድ ነው። ጠያቂ **"ሕንቅልሕንቅሊተይ"** (እንቆቅልሽ) ሲል መላሽ ደግሞ **"ሰናቢተይ"** (ምናውቅልሽ) ይላል። ከዚያም ጠያቂው መጠየቅ የሚፈልገውን ነገር ያቀርባል።*

*ለምሳሌ:-*

| | |
|---|---|
| ***ጠያቂ:- "እንቆቅልሽ"*** | ***መላሽ:- "ምናውቅልሽ"*** |
| ***ጠያቂ:- ልዕሊ ኹሉ ብርሃን ህይወት*** | *ከሁሉም በላይ ብርሃን የህይወት* |
| ***ድጋፍ ኣካል ምርኩስ ጉልበት*** | *የኣካል ድጋፍ ምርኩስ ጉልበት* |
| ***ድንቂ ነገር ናይተፈጥሮ*** | *የሚደንቅ ነው የተፈጥሮ* |
| ***ግፍትን ትብል ብጭራሮ።*** | *ገርበብ ምትል በጭራሮ።* |

(ቢትክት፣ 1995 ዓ.ም.)

እንቆቅልሽ የህፃናትንም ሆነ የኣዋቂዎችን ኣእምሮ ጅምናስቲክ በማሰራት የሚያነቃቃ የስነቃል ኣካል ነው። ጨዋታው የሚኖሩበትን ኣካባቢ በሚገባ ማወቅን ይጠይቃል። ገለፃው በተቻለ መጠን ተገላጩን ነገር እየደበቀ መጠነኛ ፍንጭ ጠቋሚ ሃሳብ እየሰጠ ነው የሚቀርበው። ተጠያቂው ፍንጮቹ ላይ በማተኮርና ከኣካባቢ ሆኔታ ጋር በማገናዘብ ስለምን ወይም ምን እየተነገረ እንደሆነ ማወቅ ኣለበት። ማህበረሰቡንና የማህበረሰቡን ባህል የማያውቅና ገለፃውን በሚገባ ኣድምጦ ማገናዘብ የማይችል ሰው እንቆቅልሽን መፍታት ኣይችልም። ተጠያቂ መልስ ሲጠፋው ኣላዋቂ መሆኑ እንዲሰማው የሚያደርጉ ስድቦችም ኣሉ። ስለዚህ ተጠያቂው ላለመሰደብ ሲል ምላሹን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

ለህፃናቱ የቀረበው ምንባብ ግን ገና ከመነሻው *"እንቆቅልሽ ልጆችና ወጣቶች ተሰብስበው **ጊዜ ለማሳለፍ** የሚጫወቱት..."* በማለት ነው የሚንደረደረው። ይህ ኣስተሳሰብ ትውፊት (ፎክሎር) በትምህርት ውስጥ ገብቶ እያዝናና ኣበእን ወደኣዲሱ ትውልድ በማስረፅ፣ በመምከር፣ መልካም ባህርያትን በመደገፍ፣ መጥፎ የሚባሉትን በመንቀፍ፣ ኣሰራሮችን ክወናዎችን በማሳየት፣ በስነምግባር የታነፀና በባህሉ የሚኮራ ህዝብ እንዲኖር በማድረግ የሚጫወተውን ጉልህ ሚና መዘንጋት ይሆናል (Bauman, 1983.) ። "ጊዜ ማሳለፊያ ነው" የሚል ጠንካራ ድምዳሜ ወደ ህፃናት ማስተላለፍ ማለት ህፃናቱ ካደጉ በኋላም ቢሆን

በእውቀት ማስተላለፊያነቱ እንዳያውቁትና እንዳይጓጉለት መጋረድ ማለት ነው። በመልመጃ ሶስት ስር የቀረበው ጥያቄም "**የምታውቁት እንቆቅልሽ ተጠያየቁ**" ይላል እንጂ በእንቆቅልሹ አማካይነት ምን መልእክት ማስተላለፍ እንደተፈለገ አይጠቁምም ምክንያቱም ከመነሻው ጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ ስለተፈረጀ ነው።

በሶስተኛ ክፍል መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ 13 ማሳወቅን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ሁሉም ምንባቦች የቀረቡት በገለፃ ነው፡፡ ለምሳሌ "**ኣካባቢያዊ ክስተቶች፣ የዱር እንስሳት፣ እኔ ማን ነኝ፣ ስራ፣ ቃጠሎ፣ የኣይጥ ደወል**" በሚሉ ርእሶች ስር ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ የኣይጥ ደወል የሚለው ምንባብ ብቻ ነው በገፀባሕርያት አማካይነት የማህበረሰቡን እውቀት ለማሳየት የሚሞክረው፡፡ በትረካው ውስጥ ህብረተሰብ በጋራ የሚያካሂደው ውይይት ዋነኛ የችግሮች መፍቻ እንደሆነ ለማሳየት ይሞክራል፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ ኣስቸጋሪ ሁኔታ ሲፈጠር ኣዛውንቶችን በማማከር መፍትሄ ማግኘት እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ ይኸውም የዕድሜ ባለፀጋዎች በርካታ ዕውቀቶችን የያዙ መፃሕፍት መሆናቸውን ይጠቁማል። ምንም እንኳ ምንባቡ ይህንን ሃሳብ የሚያጐላ ቢሆንም በመልመጃዎች ኣልተደገፈም፤ ሁሉም ጥያቄዎች ኣንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚያዳብሩ ናቸው። በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ከቀረቡት ዓላማዎች ውስጥ እውቀቱን ማስረፅ ግቡን ያደረገ ኣንድም ዓለማ ኣልቀረበም።

"ስራ" በሚል ርእስ ስር የቀረበው ምንባብ "ሁላችንም የምንችለውን ያህል ሰርተን ራሳችንና ቤተሳባችንን መርዳት ይገባናል" የሚል መልእክት ኣለው። ታሪኩ በስራ ራሱን መርዳት ስለሚፈልግ ተማሪ ይገልፃል። ተማሪው ዶሮ እያረባ ራሱን የመቻል ፍላጎት እንዳለው ያስረዳል። ሃሳቡንም ለኣንድ የእርሻ ባለሙያ እንዳማከረው፣ ባለሙያውም የዶሮ ቤት ከማዘጋጀት ጀምሮ እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል እንዳስረዳው ይገልፃል። ይህ እገዛ ግን የግድ '**ዘመናዊ ትምህርት የተማረ**' ያቅርበው ካልተባለ በስተቀር የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ለሚያካሂደው የዶሮ እርባታ ኣባት ወይም እናት ከልምዳቸው ተነስተው በቂ መረጃ መስጠት ይችላሉ። ህብረተሰቡ በረጅም የኑሮ ዘመኑ ያካበተው የዶሮም ሆነ የሌሎች እንስሳት እርባታ እውቀት ሊኖረው እንደሚችል የዘነጋ ምንባብ ነው።

**የገና ጨዋታ (ቃርሳ)** በሚል ርእስ ስር የቀረበው ምንባብ ስለ ባህላዊ የገና ጨዋታ የሚያወሳ ነው። ምንባቡ የገና ጨዋታ ህግና ስርዓት ሊዘጋጅለት እንደሚገባ በማሳሰብ ነው ሃሳቡን የሚያጠቃልለው።

*ቃርሳ (የገና ጨዋታ) እንዴት እንደሚከናወንና ህግና ስርዓት ያለው ስለመሆኑ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ መረጃ ኣቀባዮች የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ቀርቧል።*

> *የገና ጨዋታ ተወዳጅ ጨዋታ ነው። ስራ በማይኖርበት የበጋ ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ እንደ የኣካል ማጠንከሪያ፣ የጀግንነት መሞከሪያ፣ ድንበርን ያለማስነካት እልህ መፍጠሪያና መዝናኛ የሚያገለግል ጨዋታ ነው። ጨዋታው የራሱ የሆነ የኣፈፃፀም ሂደትና ስርዓት ኣለው።* (ቃመ.ምብ 7፣ 02-09-2004 ዓ.ም.)
>
> *እንደወይራና ክትክታ ከመሳሰሉ ጠንካራ እንጨቶች ስር ተፈልፍላ በክብ ቅርፅ የምትሰራና ከጭብጥ እጅ ኣነስ የሚል ቅርፅ ያላት ሩር ትዘጋጃለች። ይህቺን በኣየር ላይ በዱላ እየቀሉ ከኣንዱ ኣቅጣጫ ወደሌላው መውሰድ የገና ጫዋታ ይባላል። ጨዋታው ኣሸናፊና ተሸናፊ የሚታይበት ውድድር ሆኖ ህግና ስርዓት ያለው ነው። የቡድኑ ኣባላት የተለያየ የስራ ድርሻ ኣላቸው፤ ኣንድ ቡድን ከየት ተነስቶ የት ሲደርስ ተሸናፊ እንደሚባልም ይታወቃል። ውድድሩ በመንደሮች በቀበሌዎችና ጣቢያዎች መሃል ሊካሄድ ይችላል።* (ተቡው 2፣ 07-05-2005)

የገና ጨዋታ በሁለት ተጎራባች ጣቢያዎች ወይም ቀበሌዎች በሚገኙ ወጣቶች መካከል የሚካሄድ ከሆነ የጣቢያዎቹ ድንበር የጨዋታው መነሻ ይሆናል፡፡ ፉክክሩ ወደየራስ መንደር ሌላኛው ጫፍ መውሰድ ነው፡፡ ጨዋታው ጧት ተጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ሊቀጥል ይችላል፡፡ ኣሸናፊና ተሸናፊ የሚለየው ግን ሩርዋን እየመቱ ከድንበር ወደራስ መንደር ሌላኛው ጫፍ መውሰድና ተቀናቃኙን ኣድክሞ ወደራሱ መንደር እንዳይመልሳት ማቆም ነው፡፡ ከዚህ ፉክክር ማግስት ጎልማሶችና ኣዛውንቶች የማን መንደር እንዳሸነፈ፣ የማን እንደተሸነፈ ምን ተብሎ እንደተዘፈነ ስለሚጠይቁ ፉክክሩ እልህ የተሞላበት ይሆናል፡፡ ድንበርን ላለማስደፈርና ላለመሰደብ ሃይላቸውን ኣስተባብረው ይጫወታሉ፡፡ ላለመሸነፍ ሲባል የወጣቶቹ ብቃት መሰረት ያደረገ የስራ ድርሻ እንዳለና ሁሉም በየተመደበበት ቦታ ጠንክሮ እንዲሰራ ሃላፊነት እንደሚሰጠው የሁሉም ዞኖች መረጃ ኣቀባዮች ያስረዳሉ።

- ***ደጀን፡-*** *በጣም ጠንካራና ግፊያና ጉሽሚያን ተቋቁመው በር መዝጋት የሚችሉ ወጣቶችን ይይዛል።እሁለቱ መንደሮች ድንበር ላይ ይሰለፋሉ። ቡድናቸው ተገፍቶ ወደድንበር ከተጠጋ መሃል ገብተው ሩርዋን ወደመንደራቸው አቅጣጫ በመምታት መስመር ካስያዙ በኋላ ባሉበት ዘብ ይቆማሉ።*
- ***አማካዮች፡*** *እነዚህ ደግሞ በጥንካሬ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ናቸው። የስራ ድርሻቸውም የነሱ መሪ ሃይል ተገፍቶ ወደኋላ እንዳይመለስ መከላከል ነው። ሩር ወደነሱ አቅጣጫ ስትመጣ አባሎቻቸው ወዳሉበት አቅጣጫ በመምታት የማቀበል ስራም ይሰራሉ።*
- *ሶስተኛው ሃይል ደግሞ* ***ቀብቀብቲ*** *(መቺ) ይባላሉ። እነዚህ ፈጣን ሯጭ ናቸው። በፍጥነታቸው ስለሚታወቁ ከፊት ከፊት ይሆናሉ፡፡ከመሃል ያሉት ሩር ወደፊት ሲመቱላቸው ሮጠው በመያዝ፣ አከታትለው በመምታት ወደግብ የሚወስዱ ናቸው። እነዚህ ሶስት የቡድኑ አካላት በትክክል ከተቀናጁ ድል ያደርጋሉ። (ቃመ.ማ.* 5፣ 06-05-2004፤)

በዚህ መልክ የድርሻ ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ግጥሚያው ይጀመራል። ጨዋታው የራሱ ስነምግባር አለው፤ ሆነ ብሎ ሰውን ማንገላታት፣ መማታት፣ በስህተት የገፈተረህን ሰው ቂም ይዞ ለመጉዳት መሞከር ፈፅሞ የተከለከለ ነው። አሸናፊዎቹ ተሸናፊዎቹን የሚያናንቁ ግጥሞች እየደረደሩ እየዘፈኑ ሲመለሱ ተሸናፊዎች የአፀፋ ምላሽ አይሰጡም። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የ**ቃርሳ** /የገና/ ጨዋታ የህብረተሰቡ አባል የሚያውቀው ህግና ስርአት ኖሮት የሚመራ መሆኑ ነው። ስርአቱ፡- በሃይል አሰላለፍ፣ በቦታና ጊዜ መረጣና በአጨዋወት ስርዓትና ስነምግባር ይገለፃል። እልህና ያለመሸነፍ ትግል ያለበት በመሆኑ ደግሞ ዛሬ የተሸነፈው ቡድን በነጋታው ሃይሉን አስተባብሮና መንደር የቀሩ ወጣቶች ከነበሩም እነሱን ጨምሮ በጠዋት ለግጥሚያ ወደ ድንበሩ ይሄዳል፤ የቡድኑ አባላት በአጠቃላይ ለፍልሚያ ዝግጁ ሆነው ይጠባበቃሉ።

ምንም እንኳ የገና ጨዋታን ተጨማሪ ህግና ደንብ በማውጣት ማዘመን የሚቻል ቢሆንም በቃለመጠይቅ ከተሳተፉትና ከአራቱም የቡድን ውይይት አባላት በተገኘው መረጃ መሰረት የገና ጨዋታ በስርዐት እንደሚመራና ሁሉም ተጋጣሚ የሚያውቀው ያልተፃፈ ህግ ያለው ሰላማዊ ፉክክር እንደሆነ ታውቋል። የቡድኑ አባል እነዚህን ህጎች ያውቃቸዋል። እውቀቱ የሚያገኘው ከተግባርና አንዳንዴም በገና ጨዋታ የተፈጠረን ግጭት ለመፍታት ታላላቆች ከሚያቀርቡት ምክርና ተግሳፅ ጭምር ነው።

#### 4.3.3.2.2. ክህሎትን ትኩረታቸው ባደረጉ ምንባቦች

በሁለተኛው ዓምድ የቀረቡት ምንባቦች ክህሎት ማዳበር ዓላማ ያደረጉ ናቸው። በዚህ መሰረት ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ባሉት ክፍሎች አራት ምንባቦች (1ኛ ክፍል **የብእር አያያዝ**፣ 2ኛ ክፍል **ሬደዮ ማዳመጥ**፣ 3ኛ ክፍል **የእጅ ፅሕፈቴ እና ትምህርት ለምርት**) ቀርበዋል። ከነዚህ ውስጥ ትምህርት ለምርት የሚለው ምንባብ ከባቢያዊ የሸክላ አሰራርን ለማስተዋወቅ ያለመ ነው። ሶስቱ ምንባቦች ከአበእ ጋር ተያያዥነት ስለሌላቸው ትንተና የሚካሄደው '**ትምህርት ለምርት**' በሚል ርእስ በቀረበው ምንባብ ላይ ብቻ ይሆናል።

> *ርእስ፡ ትምህርት ለምርት (39)፣ የትምህርቱ ዓላማ፡- የምንባቡን መልእክት ይገልፃሉ፣ ቅድመ እና ድህረ ግንድ ቅጥያን ይጠቀማሉ።*

የሚል ሆኖ የሸክላ ስራ በመስራት ላይ መሆንዋን በሚያሳይ ስእል ተደግፎ ቀርቧል። እንደ አበእ መቅረቡ ጥሩ ነው። ለመስራት ምን ምን ጥሬ እቃ ወይም መሳሪያ እንደሚያስፈልግ ግን አልተገለፀም።

የክሂል ትውውቅም ሆነ ልምምድ በቋንቋ ክህሎት ብቻ አይወሰንም። ህፃኑ ከልዩ ልዩ ሙያዎች ጋር እንዲተዋወቅና ከትምህርት በኋላ በአንዱ ሙያ ተሰማርቶ ራሱን እንዲመራ ማድረጊያም ነው። ስለዚህ በምንባቡ ውስጥ የሚቀርበው ይዘት ተማሪው ወደፊት ራሱን ሊያኖርበት ወደሚችል የሙያ ዘርፍ መምራት መቻል አለበት (Amare, 2008)። የሚነበበው/ የሚደመጠው ስለ የቤት አሰራር፣ የሹራብ ስራ፣ የድግር አጠራረብ፣ ስለግብርና፣ ስለእንስሳት ህክምና፣ የሚያወሳ ከሆነ፣ ተማሪው ከንባቡ በኋላ የተነገሩትን ተግባራት መገንዘብ አለበት። ምንባቡም በተግባር ለማሳየት በሚያመች መንገድ መቅረብ ይገባዋል። ተማሪው ከልምምዱ በኋላ፣ ማህበረሰቡ መሃል ገብቶ ራሱን ለማኖር በተለያዩ የሙያ መስኮች ለመሳተፍ የሚያስችል አቅም መገንባት አለበት።

"ትምህርት ለምርት" በሚል ርእስ ስር የቀረበው ምንባብም ስለአንዲት የሰባተኛክፍል ተማሪ ባለሙያነት ያወሳል። በግሷ ባደረገችው ጥረት የሸክላ ስራ ባለሙያ መሆን እንደቻለች ይገልፃል። እንዴት እንደለመደችው፣ ሸክላውን በምን ጥሬ እቃና መሳሪያ እንደሰራችው አልታወቀም። ከህብረተሰቡ አባላት የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው የሸክላ ስራ፣ በሃገራችን ብዙ ዘመናት ያስቆጠረ ሙያ መሆኑ ነው። ሸክላ ለመስራትም ሁለት ዓይነት አፈር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል።

> *ኣንደኛው የኣፈር ዓይነት እንደየ ኣካባቢው ጥቁር ወይም ቀይ ዋልካ ሊሆን ይችላል። ይህ ለመቆፈር የሚያስቸግር ቢሆንም በቅርብ የሚገኝ ነው። ኣፈሩ ከባእድ ነገሮች ከፀዳ በኋላ ውሃ ይነከራል። ለዚህ ተግባር ተብሎ ለስልሶ በተዘጋጀ እንጨት እየተመታ በደንብ ይልማል። ሁለተኛው የኣፈር ዓይነት መስሓት ይባላል። ራቅ ካለ ቦታ መሬት ውስጥ ወደጐን ዋሻ በመቆፈር በብዙ ድካም የሚገኝ ነው። ቤት ከመጣ በኋላ በፀሓይ ይደርቃል። በእጅ ወፍጮ እየተፈጨ እየተነፋ በደንብ የላመ ዱቄት ይሆናል። ከዚያም በትንሽ በትንሽ ከዋልካው ጋር እየደባለቁ መልሶ በማቡካት የተፈለገው ዓይነት እቃ መስራት ይጀመራል።* (ቃመ.ማ.16፣ 02-10-2005 ዓ.ም.)

የመስሓት ጠቀሜታ በሚመለከት ሌላዋ መረጃ ኣቀበይ የሚከተለው ሃሳብ ሰጥተዋል፡-

> *በመሬት ውስጥ ለውስጥ እየሄድን የምናወጣው ኣፈር ለሸክላ ስራ ወሳኝ ነው። ዋልካ ብቻውን ኣይቆምም ይሰነጣጠቃል፤ እሳት ሲነካው ደግሞ ይፈራርሳል። የተሰራው እቃ ቶሎ የሚደርቀውም መስሓት ስለሚኖረው ነው። እቃው ከተሰራ በኋላ ውስጡ በኩበትና ገለባ ይሞላል። ጉድጓድ ይቆፈርና ውስጡ ገለባ ይጐዘጐዘበታል። ከውስጥም ከውጪም በእሳት ይያያዝና ጉድጓዱ በፍግና በገለባ ይደፈናል። እሳቱ ውስጥ ለውስጥ እየተያየዘ እቃውን ያበስለዋል፤ ከኣራት ቀን በኋላ ይወጣና ለሁለተኛ ጊዜ ይደገማል። ከዚያ በኋላ ኣውጥቶ በማፅዳት ለገበያ ይቀርባል። (ቃመ. ማ 17፣ 03-10-2005 ዓ.ም.)*

በመማሪያ መፅሓፉ ውስጥ ያለው ምንባብ የሸክላ እቃ እንዴትና ከምን እንደሚሰራ፣ ለመስራት ምን ምን መሳሪያዎች እንደሚያስፈልግ ኣይጠቁምም። የምንባቡ ዓላማ ህፃናት ከሙያው ጋር እንዲተዋወቁና ካስፈለጋቸውም እንዲሰለጥኑበት ለማነሳሳት ከሆነ ቢያንስ በባለሙያዎቹ የተጠቀሱት መሰረታዊ ቁሳቁሶቹና እውቀቶች መጠቀስ ነበረባቸው። ልጂቱ "የሸክላ እቃ የመስራት ፍላጐት ስላደረባት ሰራች" የሚለው ኣቀራረብ እውቀቱን ወደ ተማሪው ለማስተላለፍ ያለው ኣቅም ኣናሳ ነው።

#### 4.3.3.2.3. ስብእና ግንባታን ትኩረታቸው ባደረጉ ምንባቦች

ተማሪ በእውቀት በስሎና ልዩ ልዩ ክሂሎችን ኣዳብሮ ሊያድግ ይችላል። እነዚህ ግን የተሟላ ስብእናን ኣያመለክቱም። ማህበረሰቡ ውስጥ ገብቶ በክህሎቱም ሆነ በእውቀቱ ለመገልገል በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ስብእና ሊኖረው ይገባል። የስብእና መገለጫው ብዙ

ነው። እንደየባህሉም የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። የአእምሮ ብስለትን (እውቀት) ጨምሮ በጎ የተባለ ምግባር፣ ውበት አድናቂነት፣ መንፈሳዊነት ሁሉ የስብእና ግንባታ ትምህርት ይዘቶች ናቸው። ህብረተሰቡ እውቀቱን በተረትም ይሁን በሌላ ዘዴ ወደ ህፃኑ በማቅረብ መጥፎ የሚላቸው ተግባራትና እምነቶችን እንዲጠየፍና ከዚያ እንዲርቅ ማድረግም ሌላው የትምህርቱ አካል ነው /UNESCO on line/። በዚህ የግንባታ ሂደት ትልቅ ድርሻ የሚጫወቱት ተረቶች ናቸው (Pai, 1990)። ሁሉም አይነት ሰውና እንስሳት ገፀባህርያትን በመሳል ከበጎውም ከክፉውም ተግባር ጠቃሚ እውቀት ለመቅሰም በመሳሪያነት ያገለግላሉ።

**ሰንጠረዥ 8፡-** ስብእና ግንባታን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና ዓላማዎቻቸው አመልካች

| ተ.ቁ | 1ኛ ክፍል | 2ኛ ክፍል | 3ኛ ክፍል | 4ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ርእስ፡ የሌሊት ወፍ (131)<br>በቀረቡ ስእሎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ይናገራሉ።<br>አንድ ተረት በድራማ መልክ ያቀርባሉ። | ርእስ፡ ቤተሰብ (38)<br>ድህረንባብ አባት እናትና ልጆቻቸው ቤተሰብ እንደሚባሉ ይናገራሉ።<br>ለተሰጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ<br>ከስእሉ የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻ ይለያሉ | ርእስ፡ (65 ልጅነቴ) የምንባቡን ታሪካዊ ሂደት በቃል ያቀርባሉ<br>ገላጭ ቃላትን በተገቢው ቦታ በማስገባት ይገለገላሉ<br>ልጅነቴ በሚል ርእስ ስለ ራሳቸው 8 መስመር ፅሁፍ ፅፈው ያቀርባሉ | ርእስ፡ ለምን ሰርተን አንበላም (67)<br>የምንባቡን መልእክት ይገልፃሉ<br>የተሰጡ ቃላትን ከተፃራሪያቸው ያዛምዳሉ።<br>በቀረቡት ቃላት ዓ.ነገር ይመሰርታሉ። |
| 2 | ርእስ፡ ደወላችንን እናክብር (107)<br>ደወል ሰዓት እንደሚነግር ተገንዝበው ያከብሩታል።<br>በስእል ተሚታዩ ነገሮች ይጠራሉ። | ርእስ፡ ወፍና ዝሆን (107)<br>ተማሪዎች የሰሙትን ተረት በየተራ ይናገሩ።<br>ሃይል ከሕግና ብልሓት በላይ እንደማይችል ይገልፃሉ<br>የሰሙትንተረት ለጓደኞቻቸው ይነግራሉ | | ርእስ፡ አመተ ወይስ በሪሃ (74)<br>የፅሁፉን መልእክት ይገልፃሉ<br>ለቀረቡት አባባሎች ከተመሳሳዮቻቸው ጋር ያዛምዳሉ<br>በማህበረሰቡ የተለመዱ ስሞችን ማንቋሸሽ ይመስላል፡ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | | ርእስ፡ኣለመስማማ ት ለጠላት ይበጃል (78 የፅሁፉን መልእክት ይገልፃለሉ። ከምንባቡ በወጡ ቃላት ዓ.ነገር ይመሰርታሉ | | ርእስ፡ ቀበሮና ኣንበሳ (144) ተረቱን ካነበቡ በኋላ መልሰው ይናገሩታል የምንባቡን መልእክት ይናገራሉ የተረትን ኣቀራረብ ጠብቀው የሚያውቁትን ተረት ይናገራሉ |

ከኣንደኛ እስከ ኣራተኛ ክፍል ለሚማሩ ህፃናት በተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡና ስብእና ግንባታን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦች ዘጠኝ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ኣምስቱ በተለመደ የተረት ኣቀራረብ፤ ኣራቱ ደግሞ በነገሩ መልክ የቀረቡ ናቸው። በተረት መልክ የቀረቡት ምንባቦች ስርጭት በየክፍሉ የተለያየ ነው። ሶስተኛ ክፍል ግን ኣንድም በተረት መልክ የቀረበ ምንባብ የለውም። በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት መማሪያ መፃህፍት የቋንቋ ማስተማሪያ ናቸውና ሙሉ በሙሉ የኣበእ መግለጫ ሆነው መቅረብ እንደሌለባቸው ይታመናል (Woube, 2004)። በሌላ በኩል የኣፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ የኣበእ ማቅረቢያ መሳሪያ እንደመሆኑ (Wisener, 2007) እውቀቱ የተፈለገውን ያህል እንዲወጣና ትኩረት እንዲያገኝ የማያደርግ ከሆነ በህፃናቱም ሆነ በኣበ ህዝብ የሚኖረው ተፈላጊነት ዝቅተኛ ነው (Ossai, 2010)።

የያንዳንዱ ምንባብ ይዘት ምን እንደሚመስል ሲታይ፡- ለኣንደኛ ክፍል የቀረበው ምንባብ ባጭሩ ሲቃኝ ይዘቱ ይህንን ይመስላል፡፡

## የሌሊት ወፍ

ተረቱ በኣንድ ኣካባቢ በወፎችና በኣይጦች መካከል ከፍተኛ ግጭት ተነስቶ ኣንዴ ኣይጦች ሌላ ጊዜ ወፎች እያሸነፉ እንደነበረ ያወሳል፡፡ የሌሊት ወፍ ደግሞ ከመሃል ሆና ወፎች ሲያሸንፉ ክንፏን እያሳየች ወፍ ነኝ ትላቸዋለች፡፡ ኣይጦች ሲያሸንፉ ደግሞ ጡትዋን፣ ጆሮዎቿንና ጥርሷን በማሳየት የነሱ ወገን መሆንዋን ኣሳምና ከነሱ ጋር ትሰለፋለች፡፡ ከጊዜ በኋላ ሁለቱ ወገኖች ሲታረቁ የሌሊት ወፍ ታታልላቸው እንደነበረ ተገነዘቡ፡፡ እስዋም እንደዋሸች ኣመነች፡፡ በተግባርዋ ስላፈረችም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቀን ተደብቃ ውላ ሌሊት ብቻ ለመንቀሳቀስ እንደተገደደች ያስረዳል (1ኛ ክፍል 131-2)።

የተለመደው የተረት መግቢያ ባይኖረውም ተረታዊ አቀራረብን የተከተለ ነው፡፡ አትዋሽ ብሎ አይሰብክም፡፡ የዋሸ ሰው እንዲህ ይደረጋል እያለም አያስፈራራም፡፡ ውሸት መጥፎ እንደሆነ ግን ያሳያል። ትግራዋይ ይህንን እምነቱን ስንቂን ሓሳዊን እናፈኾሱ ይሓድሩ" (ስንቅና ውሸታም እያደር ይቀላሉ) በሚል ተረት ያጠናክረዋል። ተረቱ ዋሾን ሁሉም እነደሚጠየፈውና እንደሚገለል ማሳየት ችሏል፡፡ ሆኖም ይህ ምንባብ የተጠቀሰውን እውቀት ለማሳካት የቀረበ አይመስልም፡፡ እውቀቱን በተለያዩ መልመጃዎች በማጉላት ፋንታ በስነልሳንና በቋንቋ ክሂሎች ላይ ብቻ ነው ያተኮረው፡፡ ስለዚህ እውቀቱን ህፃናት ራሳቸው ካላገኙት በቀር በመልመጃዎቹ አማካይነት ወይም ወላጆቻቸውን ጠይቀው እንዲያዳብሩት አልተደረገም።

### *ወፍና ዝሆን*

ተረቱ ስለአንድ ዝሆንና ወፍ ያወሳል። ወፍ ዛፍ ላይ በሰራችው ጎጆ ውስጥ ጫጩቶች እንደፈለፈለችና ምግብ ፍለጋ ትታቸው እንደሄደች ይገልፃል። ዝሆንም ወደወንዝ ሲያልፍ ዛፉን በኩምቢው አወዛውዞ ጫጩቶቹን እንደጣላቸውና በእግሩ ጨፍልቆ እንደገደላቸው ይናገራል። ወፍም ልጆቿን መሬት ላይ ተጨፍልቀው እንዳየች ለምን እንደገደላቸው ስትጠይቀው በማን አለብኝነት 'እኳንም ጨፈለቅኳቸው' በማለት ያሾፍባታል። እስዋም ወፎችን አስተባብራ አይኖቹን እንዳጠፋችበትና እንቁራሪቶችን አስተባብራ ወንዝ ዳር ሆነው የሚያሰሙትን ድምፅ ገደል አፋፍ ላይ ሆነው በመዘመር ወንዝ አገኘሁ ብሎ ገደል ገብቶ እንዲንኰታኰት እንዳደረገች ያወሳል። ወፍም በተራዋ በጉልበት፣ በሃብትም ሆነ በስልጣን መመካት ውጤቱ ይህው እንደሆነ እንደነገረችው ያስረዳል። በመጨረሻም *"እና ተማሪዎች ስምምነትን፣ ህግና ስርዓትን ጥሶ በሃይል መመካት በጣም የከፋ ስህተት ነው። ስለዚህ እናንተም ችግሮችን በመግባባት ፍቱ፡ እንጂ ከህግና ስርዓት ውጪ መሆን የለባችሁም" (107-9)*። የሚል ምክር ሰጥቶ ሃሳቡን አጠናቋል።

የተረቱ ጭብጥ 'በጉልበት፣ በስልጣን፣ በሃብት ተመክቶ ደካማ፣ ስልጣን አልባ፣ ድሃ የሆኑ ሰዎች ላይ በደል መፈፀም ትልቅ ጥፋት ነው የሚል ነው። ወፍ በተለይ ከዝሆን ጋር ስትነፃፀር እጅግ በጣም ደቃቃ ፍጥረት ነች። ዝሆን ግፍ የፈፀመባትም ደቃቃነትዋን አይቶ ነው። ግድያውን በማን አለብኝነት የፈፀመው ለመሆኑ ማረጋገጫው ወፍ ስታነጋግረው የሰጠው ምላሽ፡- **"እና አሁን ምን አድርግ ነው የምትዪው? ደግ አደረግኩ እንኳንም ጨፈለቅኳቸው፣** *(በሳቅ እየተንከተከተ)* **ወፍ አንቺ ትዝቺብኛለሽ?"** የሚል መሆኑ ነው። ይህም በወፍ ላይ ያለውን ንቀትና ለራሱ የሚሰጠውን ከፍተኛ ግምት ያመለክታል።

ተጋሩ፣ ትዕቢት የውድቀት ምልክት ነው፣ ግፈኛ በፈጣሪ ዘንድ ስለማይወደድ መውደቁ አይቀርም ብለው ያምናሉ። ይህንኑ ሃሳብ **ዝንዓቕካዮ የጥንስ** (የናቁት ያስረግዛል) በሚል ተረትና ምሳሊ ያጠናክሩታል። የተናቀችው ወፍም ለሞት አበቃችው። ሊተላለፍ የተፈለገው እውቀትም ይኸው ነው፣ 'በማንም ላይ ግፍ አትፈፅሙ። ካልሆነ ግን መጥፎ አወዳደቅ ትወድቃላችሁ' የሚል ነው። **አለመስማማት ለጠላት ይበጃል** የሚለውና ለሁለተኛ ክፍል የቀረበው ምንባብም የአንድነትን አስፈላጊነት በድመቶቹ አማካይነት ማሳየት ችሏል። (ዝርዝር ሁኔታው በመምህራን ተኮር የቡድን ውይይት ስለተጠቀሰ እዚህ መድገሙ አላስፈለገም)።

ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀው መፅሓፍ "**ለምን ሰርተን እንበላም** 66፣ **ቀበሮና አንበሳ** 161" የሚሉ ሁለት ምንባቦች ይዞ ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ምንባብ ቁንጫ፣ ቅማልና ትኋን ገፀባህርያት የሆኑበት ተረት ነው፡፡ በገፃባህርያቱ አማካይነት የተላለፈው መልእክት የተጋሩን ስራ ወዳድነት የሚያጎላ፣ ሰርተው መብላት የማይወዱ ሰዎችን የሚነቅፍና ለስራ እንዲነሱ የሚገፋፋ ነው፡፡ ሶስቱም ተባዮች ሰው ከሚጠላቸውና ከሚጠየፉቸው (66) ሰርተው ለመብላት ተስማምተዋል፡፡ ሶስቱም ተባዮች በሰው ወዝና ደም የሚኖሩ የእውነ ሰው ተምሳሌቶች ናቸው። ይህ ተረት የህብረተሰቡን እውቀት ወደ አዲሱ ትውልድ ለማስተላለፍ አገልግሏል። እውቀቱ "**ሳዕስዕሞ ስራሕኻ አይትረስዕ፤**" (ተዝናና፣ ስራህን ግን አትርሳ) "**አብቅድሚ ስራሕ አይትፅናሕ**" (ወደስራ በሚሮጥ ሰው ፊት አትቁም) በሚሉ ተረቶች ተጠናክሮ ቀርቧል።

**ቀበሮ እና አንበሳ** በሚል ርእስ ስር የቀረበው ምንባብ በእንስሳት ገፃባህርያት አማካይነት የህፃናቱን ስብእና ለመገንባት አገልግሏል፡፡ ተረቱ አንበሳና ቀበሮ በሬና ላም እንደገዙ ያወሳል፡፡ የቀበሮ ላም ስትወልድ አንበሳ 'በሬየ ወለደ' በማለት ሊቀማት እንደሞከረና ፍትህ ፍለጋ ወደ ሌሎች የዱር እንስሳት ዘንድ እንደሄዱ ይተርካል፡፡ በዚህ ተረት አማካይነት ተጋሩ ህፃናት፤ የአንበሳን ሃይለኛነት፣ የጅብን ፈሪነትና ዋሾነት፣ የጦጣን ብልጠትና ፍትሃዊነት እንዲያዩ ተደርጓል፡፡ ህብረተሰቡ፤ ህፃናት ውሸትን፣ በሃይል መመካትን የሚጠየፍ፣ በአንፃሩ ፍትሃዊነትንና ብልህነትን የተላበሰ ስብእና እንዲኖራቸው ይፈልጋል፡፡ ፍላጎቱንም በገፀባህርያቱ አማካይነት አስተላልፏል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የስብእና ግንባታ ዓላማ ህብረተሰቡ መልካም የሚላቸውን ምግባራትና በጎ አስተሳሰቦችን ማዳበር ነው። ወይም በአገር በቀል ስነምግባር፣ ስነስርአትና ሙ.ያ መታነፅ ነው (Elleni, 1996)። በአያቶች ወይም አባቶች በቀረቡት ተረቶች አማካይነትም አዲሱ ትውልድ ሃቀኛ፣ በጉልበቱ ወይም በሃብቱ የማይመካ፣ ጥሮ ግሮ የሚበላ፣ በአንድነቱ የፀና እና ሸፍጥን የሚፀየፍ ስብእና እንዲኖረው ይፈልጋሉ። እነዚህን የበጎ ስብእና መገለጫዎችም መስበክ ወይም ማስገደድ ሳያስፈልግ ከተረቶቹና ከያንዳንዱ ገፀባህርይ ተግባር በነውን ተገቢ ነው ብሎ እንዲቀበለው፣ መጥፎውን ደግሞ የሚያስነውር መሆኑ ተገንዝቦ እንዲፀየፈው ነው የሚፈለገው (Grenier, 1998)።

ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎችና ክንውኖች ምንባቦቹ ውስጥ የተነሱትን እውቀቶች መግለፅና ዘላቂ ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር። በተለይ በመልመጃ ሶስት ስር በተካተቱ ተግባራትና ክንውኖች ተማሪዎች በቡድንና በጋራ ሆነው የማህበረሰቡን እውቀት ወደክፍል በማምጣት የጋራ እንዲያደርጉ የሚለማመዱበት ሁኔታ መፍጠር ይገባ ነበር። በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ግን ስነልሳንና የተወሰኑ የቋንቋ ክሂሎችን እንጂ በተለይ አገር በቀል እውቀትን ማስተላለፍ አልቻሉም። አንድ ስርዓተትምህርት ለአበእ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ የሚገመገመው ደግሞ ህብረተሰቡ በጣም አስፈላጊ በመሆናቸው ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚፈልጋቸውና በተለያዩ አጋጣሚዎች የተነሱትን የህብረተሰብ እውቀቶች በተለያዩ መልመጃዎች አማካይነት ማንፀባረቅ መቻል አለመቻሉ በማየት ነው (Semali and Kincheloe 1999)። ከዚህ አኳያ ምንባቦቹ በአጋጣሚ የተገኙ እንጂ አበእን ለማስተማር ታስቦባቸው የተመረጡ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ የግንባታውያን ንድፈሃሳብም ይህንን እውነት ነው የሚያጠናክረው፡-

ከላይ የተጠቀሱት ምንባቦች የህፃናቱ ቀዳሚ እውቀቶች ናቸው። እንደ ግንባታውያን እውቀት የሚገነባው ቀድሞ በተገኘው ልምድ እና እውቀት ላይ ነው (Perkins, 1992; Semali and Stambach, 1993)። በተግባር የሚታየው ግን የዚህ ተፃራሪ ነው፡፡ ተረቶች ቢቀርቡም ስርዓተትምህርቱ ግን እውቀቱን የማስተማር እቅድ የለውም። George (1999) እንደገለፁት ስርዓተትምህርቱ ለቋንቋ ሳይንስና ክህሎት ብቻ የተፈቀደ፣ ለአገር በቀል እውቀት ግን የተከለከለ መስሎ ታይቷል።

በቃለመጠይቅና በተኮር የቡድን ውይይት የተሳተፉ መምህራንም አገር በቀል እውቀትን ማስተማር ዓላማቸው ያደረጉ መልመጃዎችና ምንባቦች ስለመቅረባቸው ለማወቅ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

> *አበእን ማስተማር የሚችሉ በጣም ጥቂት ምንባቦች ቢኖሩም መልመጃዎቹ ግን የትግራዋይን ባህልና እውቀት እንዲታይ አያደርጉም። በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ምንባቦችና ሁሉም መልመጃዎች የህብረተሰቡን እውቀት አያንፀባርቁም። በዚህ ምክንያት ህፃኑ ከቋንቋው ትምህርት ስለራሱ ተምሮ እራሱን እንዲያውቅ የሚያደርግ ይዘት ቀርቦለታል ብሎ መናገር ያስቸግራል።*
> (ቃመ. መ.1.1፣ 22-12-2004 ዓ.ም.)

የመምህራኑ ምላሽም እያንዳንዱን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ ተግባራትና ክንውኖች አበእን የማስተዋወቅ ድርሻ እንደሌላቸው ነው የሚገልፁት። መልመጃዎቹ ያተኮሩት በቋንቋ መዋቅርና በአንብቦ መረዳት ላይ እንጂ በተረቱ ይዘትና ሊተላለፍ በተፈለገው አገራዊ እውቀት ላይ ባለመሆኑ በመፃሕፍቱ ውስጥ አገር በቀል እውቀትን ለማስተማር አልሞ የቀረበ መልመጃ አላጋጠመም።

በመልመጃ ሶስት ስር የሚቀርቡ ጥያቄዎች ዓላማቸው ተማሪዎች ከወላጆቻቸው፣ ከእድሜ ባለፀጋዎች ወይም ከታላላቆቻቸው ልምድ እንዲቀስሙና ከእውኑ የማህበረሰቡ ህይወት ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ነው። ሆኖም እንዲህ ዓይነት መልመጃዎች ስላልቀረቡ የእውቀት ሽግግሩ ሊታይ አልቻለም። ከመምህራን ተኰር የቡድን ውይይት የተገኘው ምላሽም ከላይ ከቀረበው የተለየ አይደለም።

መልመጃዎቹ፤ ተማሪዎች ህብረተሰቡ ሊያስተላልፍ የፈለገውን እውቀት እንዲገነዘቡ የሚያደርጉ አይደሉም። በአጠቃላይ መፃህፍቱ በትግርኛ ቋንቋ ክህሎትና እውቀት ላይ እንጂ በተጓዳኙ እውቀት ላይ ያተኰረ እንዳልሆነ መገንዘብ ተችሏል። አንዱ የቡድን አባል የሰጡት ሃሳብ ግን ከዚህ ላቅ ያለ ነው፤ "አፉቸውን በትግርኛ የፈቱና በትግራይ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ያዘጋጁቸው አይመስሉም" በሚል ጠንከር ያለ ሃሳብ ገልፀውታል። (ተቡው. 27-12-2005 ዓ.ም.) አገላለፁ፣ መልመጃዎቹ ምን ያህል ከማህበረሰቡ አበእ እንደራቁ ለማሳየት እንጂ የአዘጋጆቹ ትግራዋይነት በመጠራጠር የቀረበ አይመስልም።

ለማህበረሰቡ ኣባላት የቀረበው ቀጣይ ጥያቄ እውቀትን ለማስተማር ከቀረቡት ምንባቦች "ጠጣና ኣንበሳ" ስብእናን ለመገንባት ከቀረቡት ደግሞ "ወፍና ዝሆን" **"ቀበሮና ኣንበሳ"** በሚሉት ምንባቦች ላይ ያተኮረ ነው። በተለያዩ ዞኖች የሚገኙ የህብረተሰቡ ኣባላት መልስ በመስጠት የተሳተፉ ሲሆን የሰጡት መልስም ኣንድ ኣይነት ነው ማለት ይቻላል። ከተሰጡት መልሶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን እናያለን።

> *ኣገኘሁ ብሎ የሚመካ፣ ጉልበት ኣለኝ ብሎ ሰውን የሚበድል፣ ኣውቃለሁ ብሎ ሊሎችን የሚንቅ ሰው፣ ድሃ፣ ሞኝና ደንቆሮ ነው። እንዲህ ኣይነት ሰው ሃብታም ኣይባልም። ሃብታም ትምክህትና ትእቢት ሲያበዛ ሃብቱ በያለበት ባክኖ፣ በጠላት ተዘርፎ ሊቀርና ወደ ድህነት ሊመለስ ይችላል።* (ቃመ.ማ.1፣ 12-12-2004 ዓ.ም.)

በተጋሩ ዘንድ ሃብታም የሚባለው ሰው ምን ዓይነት ስብእና ነው ያለው? ለሚለው ጥያቄ ግልፅ መልስ ነው የተሰጠው። መጀመሪያ የባህርይ ሃብት ኣለው። የባህርይ ሃብታም፣ የሆነ ሰው ደግሞ በጉልበቱም፣ በእውቀቱም ኣይመካም። ሃብት የሚያስገኘው ጉልበት ወይም ዕውቀት ሳይሆን ፈጣሪ እንደሆነ ያምናል። ስለዚህ በሃብት ተመክቶ ሌሎችን ለመጉዳት መሞከር፣ ሃብት የሰጠውን ኣምላክ ማስቀየም ማለት እነደሆነ ይገነዘባል። ድህነትን የሚመኝ ሃብታም ደግሞ በኣስተሳሰቡም በይዞታውም ድሃ፣ ሞኝና ደንቆሮ እንደሆነ ያምናል። እንዲህ ዓይነት ሰው ሲያጋጥም ህብረተሰቡ በጣም በሚቀርበው ሰው ያስመክረዋል።

> *ኣንተ ሰውን ናቅክ ማለት ሃብት የሰጠህን ኣምላክ ካድክ ማለት ነው። ኣምላኩን ከካደ ሰው ጋር መግጠምና መዋል ራሱ ሃጢኣት ነው ስለዚህ ህብረተሰቡ ሊያገልህ ይችላል። በማለት ያስጠነቅቀዋል። (ቃመ.* ደቡ.13 10.08.2004ዓ.ም.)

ትግራዋይ ትምክህተኛን ሰው ይጠላል ብቻ ኣይደለም ይመክራል፤ ያስተምራል። ሲጠናም ከፈጣሪ ትእዛዝ ወጥቷልና የማግለል እርምጃም ይወስዳል። የፈጣሪን ትእዛዝ ከጣሰ ሰው ጋር መብላት መጠጣትና በክፉም ሆነ በበጎ ነገር መገናኘት ሃጢኣት መስራት ነው ብሎ ያምናል። ሚስቱ ከጎረቤት እሳት እንዳትጭር፣ ድግስዋ ማንም እንዳይቀምስ እስዋም የሊሎችን እንዳትቀምስ ትታገዳለች። ባልና ሚስት በኣካባቢው እድር እንዳይሳተፉ ማህበራዊ መገለል ይደርስባቸዋል። በዚህ የማግለል እርምጃ በትምክህተኞች የተናቁ ሰዎች፣ ሊጥሉ፣ ሊያዋርዱ እንደሚችሉ ያስተምራል። የደካሞች ህብረት ሃያላንና ትላልቅ የሚባሉትን ሊያሸንፍ እንደሚችል ያስገነዝባል። ሰውን ትንሽ ነው፣ ድሃ ነው ብሎ መናቅና ክብሩን መድፈር ውርደትን እንደሚያስከትል ያስተምራል።

በሶስቱ ምንባቦች አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገው እውቀትም የህብረተሰቡ አባላት ከጠቀሱት ጋር የሚመሳሰል ነው። ዝሆን በጉልበቱ ተመክቶ በወፍ ላይ ጥቃት ቢያደርስም ፈጣሪ በወፎች ተመስሎ ዓይኖቹን አጠፋበት። በእንቁራሪቶችን ተመስሎ ጉልበቱን ቀማው። ዝሆንን የገደለው የወፎች የእንቁራሪቶች ሃይል ሳይሆን የገዛ ትምክህቱና ግፈኛ ተግባሩ ነው። በሌላ መልኩ ወፎችም እንቁራሪቶችም በጉልበት ሳይሆን በብልሃት ዝሆንን አሸንፈዋል። ጠጣም ከአንበሳ ጥቃት በጥበብዋ አምልጣለች። ስለዚህ ህብረተሰቡ በተረቶቹ አማካይነት ብልህና ጥበበኛ ሁን፤ ግን አትመካ የሚል መልእክት አስተላልፏል። እነዚህን መልእክቶች በምሳሌያዊ አነጋገርም ያጠናክራቸዋል።

> **ዝነዓቕካዮ የጥንስ።** (የናቁት ያስረግዛል።)
> **እንቅዓ ምሸላ ዘይውዳእ ይመስላ** (*ቃመ.* ደቡ. 2 06-12-2004 ዓ.ም.)
> (ቁና ማሽላ የማያልቅ ይመስላል።)
> **ትሽዓተ ዝወለደት ኣድጊ ዝብኢ ዝደፍራ ኣይመስላን** (*ቃመ.ማ.* 712-12-2004) (ዘጠኝ የወለደች አህያ ጅብ የሚደፍራት አይመስላትም።)

በህብረተሰቡ ውስጥ የሃብት፣ የአኗኗር፣ የሃይል ልዩነት ቢኖር እንኳ 'እኔ ከ--- የተሻልኩ ወይም የበለጥኩ ነኝ' ብሎ እንዲኩራራ አያደርገውም። ይህ የአምላክ ስጦታ እንደሆነና የነበረው ሰው ሊያጣ፤ ያልነበረው ደግሞ ሊያገኝ እንደሚችል ያምናል። ስለሆነም ያለው በሌለው ላይ አይሳለቅም፤ ጉልበተኛም በጉልበቱ አይመካም። እሱ (ፈጣሪ) ካለው ሁሉም እንዳልነበረ ሊሆን ይችላል በሚል መንፈሳዊ እምነት ተከባብሮ ይኖራል።

በምንባቦቹ ውስጥ መልመጃ ሶስት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ግን ከላይ ከተጠቀሱትና ማህበረሰቡ ሊያስተላልፋቸው ከሚፈልጋቸው እውቀቶች የራቁ ናቸው። ጥያቄዎቹ፡-

- *"ከቀረበው ተረት በዓዩ ማን ይመስላችኋል? ክፍል ውስጥ ተወያዩበት።"*
- *"ከቤተሰብ ወይም ከአካባቢው ሰዎች ተረት አድምጣችሁ በመምጣት ክፍል ውስጥ አቅርቡ።" ( 2ኛ ክፍል ገፅ 112)*
- *ሰዎች ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ወይም የምታውቁትን ተረት ፅፋችሁ አቅርቡ*
- *ተረቱን በቃል ለጓደኞቻችሁ ንገሩ ( 4ኛ ክፍል፣ ገፅ 168)፡፡*

ተማሪዎቹ በንባቡ አማካይነት ወፍና ዝሆን ሲጣሉ አይተዋል። የጠቡ መነሻም ተነግሯቸዋል ከዚህ በመነሳት በደለኛ ማን እንደሆነ እንዲናገሩ ነው የተጠየቁት። ሁለተኛውና ያደመጡትን ተረት መልሳችሁ ተናገሩ የሚለው ጥያቄም ስለተላለፈው እውቀት እንዲያስቡ አያደርግም፡፡ አራቱም ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት የማዳመጥና

የመናገር ክሂልን ሊያዳብሩ እንደሚችሉ አያጠራጥርም። አንዳቸውም ግን ማህበረሰቡ ሊያስተላልፈው የፈለገውን እውቀት ማሳየት አልቻሉም። የተመረጡት ምንባቦች አበእን ማስተማር ስለሆኑ በዓላማ ተመርጠው ከሆነ ተማሪዎች፣ ማህበረሰቡ ሊያስተላልፉቸው በፈለጋቸው ነጥቦች ላይ ሲወያዩና እውቀቱን ይበልጥ ሲያጠናክሩ መታየት ነበረባቸው።

የስርዓተትምህርት ባለሙያው ግን በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት መልመጃዎች፣ ተማሪዎች ከአገር በቀል እውቀት ጋር እንዲተዋወቁና ይበልጥ ጠልቀው እንዲገቡ እንደሚያደርጉ ያምናሉ። በማያያዝም፦-

> *ተረቱን፣ እንቆቅልሹንና ሌላውን ወግ ተከትለው የሚመጡ ጥያቄዎች፤ "ምንባቡ* ***የሚያወሳው ስለምንድነው? ከተረቱ ምን ትምህርት አገኛችሁ?"*** *የሚሉ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ተማሪዎች ሊተላለፍ የተፈለገውን ዕውቀት ፈልፍለው እንዲያወጡ ያስችላቸዋል። ስለዚህ መልመጃዎቹ ድርሻቸውን ተወጥተዋል ብዬ ነው የማምነው።*
> (ቃ.መ. ስባሙ. 28/12/2004 ዓ.ም.)

የስርዓተትምህርት ባለሙያው የተዘጋጁት መልመጃዎች አበእን ለማስተማር አገልግለዋል ይበሉ እንጂ በመፃሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች የሉም። መምህራኑም በባለሙያው ምላሽ አይስማሙም። ከልምምድ በኋላ ምን ውጤት እንደሚገኝ የሚያመለክቱትና በመምህር መምሪያዎች ውስጥ ከሚገኙት ዓላማዎች አበእን ማስተማር ግቡ ያደረገ ዓላማ አልተገኘም። ባለሙያው በአብነት የጠቀሷቸው ጥያቄዎችም ቢሆኑ ከሌሎች ምንባቦች ቀጥሎ ከሚመጡ ጥያቄዎች የተለዩ አይደሉም። የትኛውም ዓይነት ምንባብ ከቀረበ በኋላ ግንዛቤአቸውን ለመፈተሽ የሚቀርቡ እንጂ የማህበረሰቡን እውቀት መገንዘባቸውን የሚፈትሹ አይደሉም። ይህ ክፍተት ምናልባትም አገር በቀል እውቀትን ለማዳበርና የአዳምጦ/ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለይቶ ካለመረዳት የተፈጠረ ሊሆን ይችላል።

### 4.3.3.2.4. ማሕበራዊነትን መገንባት ዓላማቸው ባደረጉ ምንባቦች

በአፍሪካውያን ዘንድ፣ ህብረተሰብ ልዩ ትርጉም አለው። "የየራሳቸው ፍላጎት ይዘው በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ግለሰቦች ስብስብ ነው" ከሚለው የምዕራባውያን ትርጉም ይለያል (Elleni, 1996)። በተጋሩ (ኢትዮጵያውያን) ዘንድ በማህበረሰብና በግለሰብ መካከል ያለው ግንኙነት በእናትና በሽል መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የሽሉ ህልውና እናት በእትብት በኩል በምታስተላልፈው ምግብ ይወሰናል፡፡ በእናት ላይ የሚደርስ ችግር የሽሉም ነው፡፡ የሽሉ ደህንነትም የእናት ደህንነት ይሆናል፡፡ በሌላ አገላለፅ በግለሰብ ላይ

የሚደርስ ችግር የማህበረሰብ ችግር ነው (Amare, 2008; Elleni, 1996; UNESCO-online)፡፡ ግለሰብ ቢራብ፣ ቢታመም፣ ቢያዝን ማህበረሰቡ ተካፋይ ነው፡፡ የግለሰብ ልጆች የሚጠበቁትና የሚታነፁት በህብረተሰብ ነው፡፡ ስለዚህ በአበ ህዝቦች ዘንድ የትኩረት ማእከሉ ግለሰብ ሳይሆን ህብረተሰብ ነው፡፡ ይህ ማህበራዊነት እንዳይሸረሸርና እንዳይጠፋ ህብረተሰቡ በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ በተረትና ምሳሌና በተግባር (በኣፈፃፀም) ወደ ተከታዩ ያስተላልፈዋል፡፡

ኣገር በቀል ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁ መፃሕፍትም ማህበረሰቡ የሚፈልገውን ዓይነት ማህበራዊነት ወደ ኣዲሱ ትውልድ በማስተላለፍ ማገልገል ኣለባቸው (Hurrieiz, 2006)፡፡ በዚህ መሰረት የትግርኛ ቋንቋን ለማስተማር በተዘጋጁት መፃሕፍት ውስጥም ማህበራዊነትን የሚያንፀባርቁ የተወሰኑ ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ለ1ኛ ክፍል፣ **"የሰላምታ ልውውጥ** (3)፣ **ሃይለ እና ከድጃ** (120)፣ **መጣላት ነውር ነው** (123)" ለ3ኛ ክፍል ደግሞ **"ሶስት በሬዎችና ጅብ** (1)፣ **ማሕበራት** (26)" የሚሉ ርእሶች ያሏቸው ምንባቦች ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ** 9፡- ማህበራዊ ግንባታን ትኩረታቸው ያደረጉ ምንባቦችና ዓላማዎቻቸው ኣመልካች

| ተ.ቁ | 1ኛ ክፍል | 2ኛ ክፍል | 3ኛ ክፍል | 4ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ርእስ፡ መጣላት ነውር ነው /123/<br>የንባቡን መልእክት በቃል ይናገራሉ።<br>የመጣላትን መጥፎነትና ተስማምቶ የመኖር ኣስፈላጊነት የሚያሳይ ተውኔት ያሳያሉ።<br>ህፃናት መጣላት እንደሌለባቸው ከተጣሉ ሊጐዱ እንደሚችሉ ወላጆችም ሊጣሉ እንደሚችሉና ሰላማዊ ህይወት ሊበላሽ እንደሚች ሰበካ ነው | | ርእስ፡ ሶስት በሬዎችና ጅብ /1/<br>ንባቡን ካደመጡ በኋላ መልሰው ይናገራሉ የሚያውቁትንተረት ይናገራሉ (1) መተባበር ሃይል ሞሆኑ ይናገራሉ የዕሁፉን ይዘት ይናገራሉ በተሰጡ ፊደላት ቃላት ይመሰርታሉ በተሰጡ ቃላት ዓ.ነገር ይመሰርታሉ (ልዩ ማብራሪያ በገፅ 2) | |
| 2 | ርእስ፡ የሰላምታ ልውውጥ/3/<br>የሰላምታ ልውውጥ ምንነት ተገንዝበው በተለያዩ ጊዜያት ተገቢ ሰላምታ ይለዋወጣሉ። (ጠዋት፣ ረፋድ፣ ቀትር፣ ምሽት)<br>በስእል የቀረበ ነው፡፡ ታዳጊዎቹ ባህላዊ አለባበስ የፀጉር አለሜጨት አሰራር የተከተሉ ሽማግሌዎቹም እንዲሁ ይታያል ወቅትን ግን ለይቶ ኣያሳይም | | ርእስ፡ ማሕበራት /26/ ከንባብ በኋላ መልእክቱን ባጭሩ ይናገራሉ በደረጃው ድርብ ቃላት ይመሰርታሉ የኣህፅሮት ቃላትን በዝርዝር ይፅፋሉ ንኡስ ጭረትን በተገቢ ቦታ ይጠቀማሉ<br><br>መልእክቱ የተላለፈው በነገራ ስለሆነ በህፃናቱ ኣእመሮ ተጨባጭ ስእል ኣይፈጥርም። | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ርእስ፡ ሃይለና ከድጃ /120/<br>የምንባቡን መልእክት ይናገራሉ።<br>የሰላምታ ስርዓት ተከትለው ጠዋት፣ ቀንና ምሽት ሰላምታ ይለዋወጣሉ።<br>ሁለት ተማሪዎች የዕረፍተ ጊዜያቸውን እንዴት እንዳሳለፉ የሚነግር ምልልስ ነው። የሰላምታ ልውውጥም ቀርቧል።<br>ሆኖም ጊዜን፣ ወቅትንና ዘመንን በሚያስተዋውቅ መልክ አልቀረበም | | | |

ከላይ ከተዘረዘሩት ርእሶች መካከል በቅድሚያ "የሰላምታ ልውውጥ" የሚለው ርእስ እንመልከት። በመርሃትምህርት ውስጥ የሰላምታ ልውውጥ በሚል ርእስ ስር ለቀረበው ይዘት የተነደፈለት ዓላማ "ጊዜን መሰረት አድርገው ሰላምታ ይለዋወጣሉ፣ በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ሰላምታ እየተለዋወጡ ንግግር ይለማመዳሉ" የሚል ነው። በተለይ የመጀመሪያው ዓላማ ጊዜን መሰረት ያደረገ የሰላምታ ልውውጥ እንደሚካሄድ ይገልፃል። በሰላምታ ልውውጥ አማካይነት እንዲያዳብሩት የተፈለገው ግን ንግግር ነው። በእርግጥ የሰላምታ ልውውጡ በቃል ስለሚካሄድ ንግግር ሊዳብር ይችላል። ትኩረት ማግኘት የነበረበት ግን አጠቃቀሙ ነው። ተጋሩ ጊዜን ለይተው ሰላምታ ሲለዋወጡ አንዱ ለሌላው ምን ይለዋል? በንግግሩስ ምን መልእክት ነው የሚተላለፈው? ይህ በመርሃትምህርቱ ውስጥ ትኩረት አልተሰጠውም።

መማሪያ መፅሐፍ በመርሃትምህርት ውስጥ የተነደፉ ዓላማዎች በምን ሁኔታ ወደ ተማሪ እንደሚተላለፉ በተግባር የሚታይበት ነው። ከላይ የቀረበው ዓላማ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በስእል ነው የተገለፀው። ስእሎቹ ግን እንደታለመው ጊዜን ሳይሆን ወጣቱ ከወጣት፣ ሽማግሌ ወላጆች ደግሞ ከህፃናት ጋር ሲገናኙ የሚያሳዩት የኣካል እንቅስቃሴን ነው የሚያሳየው። ስእሉ፡- ወጣቶች እጅ ለእጅ እንደሚጨባበጡ፣ ወላጆች ደግሞ የህፃናትን ግንባር በመሳም ሰላምታ እንደሚለዋወጡ ያመለክታል።

መርሃትምህርቱ 'ሃይለና ከዲጃ' የሚለው ምንባብ ዓላማ ምን እንደሆነ አያመለክትም። በመምህር መምሪያው ውስጥ ግን ሁለቱ ልጆች የጠዋት፣ የቀንና የማታ ጊዜን ተጠቅመው ሰላምታ ይለዋወጣሉ የሚል ዓላማ ተቀምጧል። ልጆቹ ሰኔ እንደተለያዩ በመስከረም ነው የተገናኙት። እንዲለማመዱ የታቀደው ግን የጠዋት፣ የቀንና የማታ ሰላምታ ነው። ከዚህ አኳያ ሲታይ በመምህር መምሪያው ውስጥ የተቀመጠው እቅድም ቢሆን ታስቦበት የተዘጋጀ ነው ለማለት ይከብዳል። ምክንያቱም ልጆቹ የተለያዩት ለሰዓታት ሳይሆን

ለወራት ነው። መለማመድ የነበረባቸውም ወቅትን መሰረት ባደረገ ሰላምታ ላይ ነው። በአጠቃላይ የይዘቱ አቀራረብ ከዓላማው ጀምሮ ትኩረቱ ይሄ ነው ብሎ መናገር ያስቸግራል። በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረበው ምንባብ ርእስ ከሰላምታ ልውውጥ ጋር የተያያዘ ቢመስልም መልመጃዎቹ ግን በምንባቡ የተመለከተውን የጊዜ ልዩነት መሰረት አድርገው የሰላምታ ቃላት ለመለዋወጥ አያስችሉም። ህብረተሰቡ ወቅትን መሰረት አድርጎ ሰላምታ ሲለዋወጥ የሚያስተላልፈው መልእክትም ትኩረት አላገኘም።

ከቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ግን ህብረተሰቡ በወቅቶች ላይ ያለውን እውቀት በሰላምታ አማካይነት እንደሚያስተላልፍ ነው። ቀጥሎ በቀረበው መረጃ መሰረት ህብረተሰቡ፣ ምን እውቀት፣ በምን ሁኔታ እንደሚያስተላልፍ እንመልከት፣-

> *በአንድ ቀን ውስጥ ያሉ አራት የሰላምታ መለዋወጫ ጊዜዎች ሰዎች፣ ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑባቸው፣ በመንፈስ ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙባቸው ናቸው። በዓመት ውስጥም ተፈጥሮ የምታሳያቸውን ለውጦች መሰረት ያደረጉና የአምላክ ሀልውና የሚገለፅባቸው የደህንነት መጠያየቂያ ወቅቶች አሉ። እነዚህ ወቅቶች የየራሳቸው የሆነ መታወቂያ አላቸው።*
>
> *ለምሳሌ፡- ክረምት፡- በዝናብ፣ በጎርፍ፣ በመሬት ናዳ ምክንያት በርካታ የሞት አደጋ የሚከሰትበት፣ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ዘመዳሞች የማይገናኙበት፣ በሃሳብ ግን አንዱ ስለሌላው ደህንነት የሚጨነቁበት፣ የምግብ እህል ስለሚሟጠጥ ረሃብ የሚፀናበት፣ ድሃ ገበሬ በረሃብ የሚገረፍበት ወቅት ነው። ስለዚህ ክረምት አልፎ ስንገናኝ ያ ሁሉ ችግር እንዴት አለፋችሁት (እንደምን ከረማችሁ) እየተባባልን እንጠያየቃለን፡፡* (ቃ.መ.ማ. 1፣ 12-12-2004 ዓ.ም.)

ከቃለመጠይቁ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው፣ ሰላምታ ስለፈለጉ የሚያከናውኑት፣ ካልፈለጉ የሚተዉት አለመሆኑ ነው። በሁለቱ ገፀባህርያት መካከል የሚካሄደው የሰላምታ ልውውጥ ግን "እንደምን አደርሽ" ከሚል የሃይለ ጥያቄ ውጪ ሌላ ሲናገሩ አልተሰማም። በተጋሩ ዘንድ ግን ሰላምታ፣ የመረጃና የእውቀት ማስተላለፊያ ዘዴ ከመሆኑም ሌላ በሰው በተፈጥሮና በፈጣሪ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ያለ መሆኑ ማሳያ ነው (Sette, 2007)።

> *ፍቅር ወላድ ነው፣ ይራባል። ጠብ ደግሞ መሃን ነው። በተግባሉ መሃል ፍቅርም የሰላምታ ልውውጥም የለም። የእግዚአብሄር ቀለብ ደግሞ ምስጋና፣ "እግዚአብሄር ይመስገን" ነው። በየቀኑ የሚቀርበው ሰላምታ ዓላማውም ወደእግዚአብሄር ምስጋና*

*ማቅረብ ነው። ፈጣሪ ደግሞ ፍቅራችንን እና ምስጋናችንን አይቶ ፍቅር፣ ሰላምና በረከት ይጨምርልናል።* (ተበው 4፣ 18-02-2005)

ከቀረበው ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው፣ የሰላምታ ልውውጥ ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ትርጉም ያለው መሆኑ ነው። ቤተሰብ ሲፋቀር ጎረቤት ይወደዋል። ጎረቤታሞች ሲፋቀሩ ህብረተሰቡ ይወዳቸዋል። ስለዚህ ፍቅር ሌላ ፍቅርን ይተካል። በአጠቃላይ ከፍቅር እንጂ ከጠብ ትርፍ እንደማይገኝ ያመለክታል።

> *ሰዎቹ የተለያዩት ለአንድና ለሁለት ሳምንታት ከሆነ "ከመይ ቀኒኻ/ኺ?" (እንደምን ሰነበትክ/ሽ?)ይባባላሉ፡፡ የተለያዩበት ጊዜ ረጅም ከሆነ ግን ወቅትን መሰረት አድርጎ መጠየየቅ ይከተላል፡፡ (ተበው 2፣ 07-05-2007)*

> *ሰላምታ የመቀራረብ፣ የመነፋፈቅ፣ የመፈላለግ መግለጫ ነው፡፡የኛ እህቴ፣ የ ወንድሜ... እያሉ ሲያስቡ ሲጨነቁ ይቆዩና ሲገናኙ በመሃል ያልተገናኙበትን ወቅት እየጠቀሱ፤ እንዴት እንዳሳለፉት እየተጠያየቁ ደህንነታቸውን ይገላለፃሉ፡፡ እያንዳንዱ ወቅት ደግሞ የየራሱ የሆነ መታወቂያ አለው፡፡ ወቅቱ በነዋሪው ዘንድ በጎ ወይም መጥፎ አሻራ ትቶ ሊያልፍ ይችላል፡፡ መጠየየቁ አስፈላጊ የሚያደርገውም ይህንን አሻራ በሩቅ ለነበረም ሆነ አብሮ ለሚኖር ጎረቤት ደህንነትን የተመለከተ መረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡* (ተበው. 3፣ 08-05-2005)

በተጋሩ ዘንድ ከእለታዊ የሰላምታ ልውውጥ ውጪ በዓመት ውስጥ ተፈጥሮ የምታሳያቸውን ለውጦች መሰረት ያደረጉና የአምላክ ህልውና የሚገለፅባቸው የደህንነት መጠየየቂያ ወቅቶች እንዳሉና የመጠየየቁ አስፈላጊነት ከነምክንያቱ አስረድተዋል።

**ሓጋይ** (በጋ)፡- **ከመይ ሓጊኹም?** (በጋውን እንደምን አሳለፋችሁት?) በገበሬው ዘንድ በጋ አንፃራዊ በሆነ መልኩ እረፍት የሚገኝበትና ለስራ የሚዘጋጁበት ወቅት ነው። ስለዚህ ጥየቃው እረፍቱና የመጪ የአዝመራ ወቅት ዝግጅት እንዴት እንደሆነ ማወቅን ያለመ ነው። በመኸር ጊዜ በቂ ዝግጅት ካልተደረገ በቀር ከብቶች በመኖ እጦት የሚቸገሩበት፣ ገበሬውም ችግሩን ለማቃለል ላይ ታች የሚልበት ጊዜ በመሆኑ በዚህ ላይ ያተኮረ ጥያቄም ይቀርባል።

**ዕድያ** (ፀደይ)፡- በገበሬው ዘንድ ዕድያ፣ የሃምሌን የመጀመሪያ ሁለት ሳምንታት የሚሸፍን ነው። ሁለቱ ሳምንታት የአዝመራ ያልሆኑ የእህል አይነቶች (ጤፍ፣ ገብስ፣ ስንዴ) የሚዘሩበት ወቅት ነው። ጊዜው አጭር በመሆኑ ገበሬው በስራ ይዋከባል። እግር ለመታጠብ እንኳ ፋታ አይሰጥም። **ሓረስታይ ዕድያ ዕባሕ ናብኡ እየ እናበለ ኣብእግሩ ጣፍ ኣብቆለ** (የዕድያ ገበሬ ነገም ወደዚያው ነኝ እያለ እግሩ ላይ ጤፍ አበቀለ) ይባልለታል። የዕድያ አንዷት ቀን የአመት ሙሉ ፀፀት ታስከትላለች እየተባለ ይነገራል። ስለዚህ የህብረተሰቡ ኣባላት ዕድያን መሰረት ያደረገ ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

**ክረምት**፡- **"ፀልማትን ክረምቲን ሓደ እዮም "** (ጨለማና ክረምት አንድ ናቸው) በመሆኑም "**ክረምቲያ ዝገይሽስ ካብከልቢ ኣይሐይሽ**" (በክረምት በእንግዳነት ሰው ቤት የሚሄድ ሰው ከውሻ አይሻልም) እየተባለም ይተረታል። ምክንያቱም የክረምት ወራት ትግራዋይ ብዙ ችግርና ፈተና የሚያይበት ነው። የዘር፣ የኣረምና የከብት ጥበቃ ስራ ኣለ። ያልተጠበቀ ዝናብና የጎርፍ ኣደጋ ኣለ። በመብረቅና በናዳ መሞትም ኣለ። ቤት ሊፈርስ፣ ቤተሰብ መጠለያ ሊያጣ ይችላል። በዚያ ላይ የነበረው እህል ለምግብነትና ለዘር ውሎ የሚያልቅበት፣ ኣዲሱ እህል ደግሞ ገና በቡቃያ ደረጃ ያለ በመሆኑ ህብረተሰቡ ለከፍተኛ የረሃብ ኣደጋ የሚጋለጥበት ወቅት ነው። እነዚህ ሁኔታዎች የገበሬውን ኑሮ በጣም ኣስቸጋሪ ያደርጉታል። ጥየቃውም  እነዚን ችግሮች እንዴት እያለፉቸው እንደሆነ /እንዳለፉቸው ማወቅን ያለመ ነው።

**መስቀል ብራ'ቕ (ፅባሕ - ጥቢ)** ሌላው የደህንነት መጠያየቂያ ወቅት ነው፡፡ መጥባት በትግራይ ማህበረሰብ ዘንድ የመስከረም ወር በተለይ ደግሞ የመስቀል መግባት ከመንጋት፣ ከጨለማ ከመውጣትና ኣዲስ ተስፋ ከማየት ጋር ይያያዛል። የክረምት ወራት የሚያስከትላቸው ችግሮች የሚቀንስበት፣ በጭቃና በዝናብ የቆረፈደ ገላ ፀሓይ የሚሞቅበት፣ ኣዲሱ እህል ለምግብነት የሚደርስበት ጊዜ በመሆኑ ተጋሩ ሲገናኙ እንደምን ነጋልህ? እየተባባሉ ይጠያየቃሉ፡፡ የጥቢ ወቅት፡- ክረምቱን ሙሉ የለፉበት ምርት ፍሬ የሚያሳይበት ወደ ጥጋብ የሚሸጋገሩበት ነው። ተፈጥሮኣዊ በሆኑ ችግሮች ምክንያት ከመገናኘት ታግደው የነበሩ ዘመዳሞች፣ ወንድማማቾች፣ ወዳጆች ሁሉ በጎርፍ፣ በናዳ፣ በመብረቅና በረሃብ ኣደጋ ከመሞት ኣምልጠው በመገናኘታቸው ደስታቸውን የሚገልፁበትና ለፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርቡበት ወቅት ነው። ጥያቄውም "**ከመይ ኢልካ**

**ፀቢሖኻ?**" ነው። ፍቺውም ያንን የጨለማ ጊዜ እንደምን አሳለፍከው? ነው። ወይም "ያንን ሁሉ አልፈን እንኳን ለመገናኘት አበቃን" የሚል የደስታ መልእክት አለው።

**ቀውዒ** (መኸር)፡- ገበሬው መሬት ላይ ያፈሰሰው ዘር ፍሬ አፍርቶ የሚታጨድበትና ተወቅቶ ወደቤት የሚጓጓዝበት ጊዜ ነው። በአጠቃላይ ገበሬው የልፋቱን ዋጋ የሚሰበስብበት፣ ቤተሰቡ ሁሉ በስራ የሚጠመድመትና የሚጣደፍበት ጊዜ ነው። በዚህ የስራ ውጥረት ምክንያት ተራርቀው የነበሩ ተጋሩ ሲገናኙ ሰላምታቸው **ከመይ ቀዊዕኻ?** መኸሩን እንደምን አሳለፍከው? ነው የሚሆነው። በእግረመንገድም አዝመራው እንዴት እንደነበረ፣ የአመት ቀለባቸውን ስለማግኘታቸው ሁሉ ይጠየየቃሉ። ምላሹም ፈጣሪን በማመስገን የታጀበ ሆኖ የመኸሩ ሁኔታም ይገለፅበታል።

ክረምቱን፣ ፀደዩን፣ ጥቢውን፣ መኸሩን፣ በጋውን እንደምን አሳለፍከው? እየተባባሉ በያንዳንዱ ወቅት የነበረውን ሁኔታ ይጠያየቃሉ። መላሾቹም በቅድሚያ ፈጣሪያቸውን ካመሰገኑ በኋላ በየወቅቱ ያጋጠሟቸውን መልካም ነገሮች፣ የስራ ሁኔታና መጥፎ አጋጣሚዎች ወይም አደጋዎች በማውሳት ይነጋገራሉ። ለምሳሌ፡- በነዚህ ወቅቶች ውስጥ መታመም፣ መራብ፣ በእዳ መቸገር፣ መጋጨት፣ መታሰር፣ ከየወቅቱ ጋር በሚመጡ በሽታዎች መለከፍ ሊኖር ይችላል። የህብረታሰቡ አባላት በሰላምታ አማካይነት እያንዳንዱ ወቅት ወይም ጊዜ የየራሱ የሆነ በጎና አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳለው ያስተዋውቃሉ፣ ለተተኪው ትውልድም እውቀቱን ያስተላልፋሉ።

በመረጃ አቀባዮቹ የተሰጠው ምላሽም የሚያስረዳው ሰላምታ የደህንነት መግለጫና መረጃ መለዋወጫ መሆኑ ነው። ማንኛውም ሰው ሰላምታ ሲቀርብለት ደህንነቱን ከምስጋና ጋር ይናገራል። ከዚህ የሰላምታ ልውውጥ ማህበረሰባዊ ከበሬታ እና ፍቅር ያገኛል። ከያንዳንዱ ወቅት የተያያዘ ሰላምታ ሲቀርብ ደግሞ በየትኛው ወቅት ምን ምን ተግባራት እንደሚከወኑ እና አንዱ ከሌላው በምን እንደሚለይ ያውቃል። ባገኘው እውቀት መሰረትም ከያንዳንዱ ወቅት የሚስማማ የስራ እቅድ ያወጣል ከወቅቶቹ ጋር እራሱን አስማምቶ ለመኖር ይዘጋጃል። በመማሪያ መፅሓፉ ውስጥም በከፊልም ቢሆን እነዚህ እውቀቶች መንፀባረቅ ነበረባቸው።

"**መጣላት ነውር ነው** 123" የሚለው ምንባብም ህፃናት ቢጣሉ ህብረተሰቡ እንደሚጠላቸውና በነሱ ምክንያት ወላጆቻቸው ከጎረቤቶቻቸው ጋር ሊጣሉ እንደሚችሉ

በሚያሳስ በልኩ ቀርቧል። የትምህርቱ ዓላማ እንደሚያመለክተው ህፃናቱ፣ የመጣላትን መጥፎነትና ተስማምቶ የመኖር አስፈላጊነት የሚያሳይ ተውኔት ማቅረብም ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም ምክሩም እንዳለ ሆኖ ተስማምቶ የመኖር ምንነትና ጠቀሜታ ሳይገነዘቡ በተውኔት መልክ ያቀርቡታል ብሎ ማቀድ የህፃናቱን ደረጃ መዘንጋት ይመስላል።

በ3ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ደግሞ "**ሶስት በሬዎችና ጅብ** 1፣ **ማሕበራት** 26" የሚሉ ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል። በተለይ ስለበሬዎች የሚያወሳው ምንባብ ሙሉ በሙሉ በተረት መልክ የቀረበና የህብረተሰቡን እምነት ያንፀባረቀ ነው። በአንድ ጫካ ውስጥ በነፃነት የሚኖሩ አንድ ቀይ፣ አንድ ጥቁር እና አንድ ነጭ በሬዎች እንደነበሩ ይተርካል። ሶስቱም ተስማምተው፣ ጠላትም ሳይደፍራቸው ይኖሩ እንደነበር ይገልፃል። አንድ ጅብ እርስበርስ አጣልቶና ነጣጥሎ ሊበላቸው ፈለገ። ስለዚህ ሁለቱን በሬዎች በመጥራት እናንተን የሚያስጠቃችሁ ነጩ በሬ ነው። በጠላት ከሩቅ የሚታየው እሱ ነው፤ ስለዚህ አግልሉት ኣላቸው። እነሱም በግድ ከቡድኑ ነጠሉት። ጅብ ነጩን በሬ ከበላ በሃላ ደግሞ ጥቁረን በመጥራት እርሱ በጨለማ ጊዜ እንደማይታይና ቀዩ ለጠላት እያጋለጠው መሆኑ ነግሮ ነጣጠለና ሁለቱንም በየተራ በላቸው።

ይህ ተረት ህፃናቱን የአብሮ መኖርን ጠቀሜታ ያስተምራቸዋል። ኣንድነት ሃይል መሆኑ፣ በህብረትና በሰላም የሚኖርን ህብረተሰብ በመነጣጠል ተጠቃሚ መሆን ከሚፈልጉ ጠላቶች መጠንቀቅ እንደሚገባ ያሳስባል። የሰዎች የቆዳ ቀለም (መጥቈር፣ መቅላት፣ መርዘም ወይም ማጠር) ተባብሮና ተጋግዞ ለመኖር እንቅፋት እንደማይሆን፣ ጠላት ግን ለመከፋፈል ሊጠቀምበት እንደሚችል ያሳያል።

"**ማሕበራት**" የሚለው ምንባብ ትኩረት በሙያ፣ በፆታና መንግስታዊ ባልሆኑ ረጂ ድርጅት ማህበራት ላይ ነው። የቀረበውም በነገራ ስለሆነ በህፃናቱ ኣእመሮ ተጨባጭ ስእል ኣይፈጥርም። ጭራሮዎች በኣንድ ላይ ደማቅ የችቦ ብርሃን እንደሚፈጥሩ የሚገልፀው ዐረፍተነገር ግን የሕብረትን ኣስፈላጊነት የሚያጕላ ኣገላለፅ ነው። ሆኖም ከንባብ በኋላ ስለይዘቶቹ የሚያወሱ መልመጃዎች ካልቀረቡ ተረቶቹ ብቻቸውን የተፈለገውን እውቀት ሊገነቡ ኣይችሉም።

ማሕበራዊ ኑሮ፣ የአበህ አንዱ መታወቂያ ነው። ተጋሩም ማህበራዊነትን የሚያስተምሩ ተረቶች፣ ምሳሌአዊ ንግግሮች፣ ወዘተ. አሏቸው። በነሱ አማካይነትም እውቀትና ልምዳቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፋሉ። የማህበራዊነት መገለጫዎች በርካታ ስለሆኑ የተወሰኑ ኣብነቶችን ብቻ እናያለን። በቅድሚያ ግን ከህብረተሰቡ ኣባላት በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎች በተከታታይ ኣቀርባለሁ።

> *መተባበር የኖረ ባህላችን ነው። መተባበር ስለተቸገሩ ብቻ የሚከወን ሳይሆን በጋራ መስራት የተጋሩ ባህል በመሆኑ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የእርሻ፣ የኣረም፣ የኣጨዳ ወይም የቤት ስራ ከአቅሙ በላይ ከሆነበት፣ ዝናብ አዝመራውን የሚያበላሽበት ከመሰለ፣ በእድሜ መግፋት ምክንያት ስራውን ማከናወን የማይችሉ ሰዎች ከሆኑ፣ በዙርያው ያለ አዝመራ ተሰብስቦ በአቅም ማጣት ሳይታጨድ የቀረና ለአደጋ የተጋለጠ ከሆነ እያንዳንዱ ገበሬ ተነጋግሮ ወደስራ ከመሰማራቱ ወይም ከስራ መልስ ቤት ከመግባቱ በፊት ወደተጠቀሰው ሰው እርሻ ቦታ ይሄዳል፡፡ ሁሉም የቻለውን ያህል ያጭዳል፣ ይከምራል፡፡ እርሻም ከሆነ እንዲሁ በጋራ ኣርሶ ወደየቤቱ ይመለሳል። ይህም ርፍዶት ወይም ምስዮት ይባላል።* (ተቡው 4፣ 18-022- 005)

> *ሃብትን መሰረት ያደረጉ መሰባሰቢያ መድረኮች በሁሉም ዘንድ ይወገዛሉ። የማህበረሰቡ ኣባላት በክፉም ሆነ በደግ ኢጋጣሚዎች አንለያይም። በዚህ ምክንያት አንድነታችን ይጠበቃል። ህፃናትም በተለየየ መንገድ እንዲወርሱት ይደረጋል።* (ቃ.መ.ደቡ፣ 06-12-2004 ዓ.ም.)

ከላይ የቀረቡት ሁለት መልሶች ሁለት የተለያዩ ጉዳዮችን ነው የሚያነሱት። አንዱ፣ በስራ መረዳደትና መተጋገዝ፤ ሁለተኛው ደግሞ ማህበራዊ አንድነቱ ሰዎች በመሆናቸው ብቻ (ሌላ መስፈርት ሳያስፈልግ) የሚፈጥሩት መሆኑ ነው። ተባብሮ መኖርና አንድነት በጣም አስፈላጊ መሆናቸው ይገነዘባሉ። ልጆቻቸውም ይህንን እንዲወርሱላቸው ስለሚፈልጉ አጥብቀው ያስተምራሉ። በተግባርም ያሳያሉ። የእርሻ፣ የኣረም፣ የአጨዳ፣ የቤት ስራ፣ ወዘተ ሁሉ በመተባበር ያከናውናሉ። ተባብረው የሚያከናውኑት የግለሰብ ስራ ነገ መልሶ ይሰራልኛል ከሚል ብድር ሳይሆን ከአቅሙ በላይ ስለሆነ እገዛ ልስጥ በሚል ተነሳሽነት ነው። ይህም የግለሰብ ችግር የጋራ ችግር ነው ከሚለው የማህበረሰቡ መርህ ይመነጫል። ተከታዩ ትውልድም ከእንደነዚህ ኣይነቶቹ ተግባራት የመተባበርና ኣብሮ የመኖር እውቀት እየተማረ ያድጋል።

ህብረተሰቡ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ከሚያዳክሙ ምክንያቶች አንዱ የሃብት መጠንን መሰረት ያደረገ ግንኙነት ነው። ለምሳሌ በተጋሩ ዘንድ አንዲት ልጃገረድ በተለያዩ

ምክንያቶች ሳታገባ ልትቀር ትችላለች። ለምሳሌ በጤና፣ በቤተሰብ ባህሪ፣ በግል ፍላጐት... ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህ በማህበረሰቡ የማይፈታ ችግር ነው። ወላጆቿ ገዝሚ (ለወንድ ሙሽራ የሚያቀርቡት የከብት ስጦታ) ባለማግኘታቸው ግን **ብጓላ ዝኣረገት** (ቆሞ ቀር) ኣትባልም። የዚህ ኣይነቱ ችግር በመተባበር የሚፈታ ነው።

> *ከብት የሌላት ልጃገረድ ኣካለመጠን ከደረሰች የአካባቢው ሃብታሞች ይሰባሰቡና ስለልጅቱ ይወያያሉ። ከብት ከሌላት ባል እንደማታገኝ በማመን ከብቶች ኣዋጥተው ይሰጧታል። ይህንን የሰሙ ሰዎች እሎኝንት ይጠይቃሉ። ስትዳርም ህብረተሰቡ እህል ኣዋጥቶና ደግሶ ጎጆ እንድትወጣ ያደርጋል።* (ቃ.መ. ደቡ. 13፣ 10/08/ 2004ዓ.ም.)

ይህንን ተግባራዊ እውነት ማህበረሰቡ በተረት፣ በተረትና ምሳሌና በሌሎች ወጎች ኣማካይነት ወደተተኪው ትውልድ ያስተላልፈዋል። 'ህብረት ኣስፈላጊ ነው፡፡' ብሎ ኣይነግርም ወይም ኣይሰብክም፤ ይህ እምነቱ በተረትና ምሳሌም ጎልቶ እንዲታይና ዘላቂ እውቀት እንዲሆን ያደርጋል እንጂ።

**'ዝሓበሩያ ኣፃብዕቲስ ኣርቃይ የፀምብዓ'** (የጣቶች ህብረት ቀርከሃን ያንሻፍፋል) ቀርከሃ በቀላሉ ከማይሰበሩና በቅንቅን ከማይበሉ ተክሎች ኣንዱ ነው። ከዘራ ሆኖም እንዳማረበት ወደትውልድ ይተላለፋል። ከዘራ ለብዙ ጊዜ ሲያዝ ጣቶች የሚያርፉበት የመያዣው የውስጥ ክፍል በመተሻሸት ብዛት ይበላል ጠፍጣፋ ቅርፅ ይይዛል። ይህም የጣቶች ህብረት ጠንካራውን ቀርከሃ እንዳስገበሩት ሁሉ የሰዎች ህብረትም ማንኛውንም ችግር ሊፈታ እንደሚችል ያስተምራል። በመጠይቁ የተሳተፉት መረጃ ኣቀባዮች ህብረትን በእውቀትነቱ ለማስትማር ከሚገለገሉባቸው ተረቶች የሚከተለው ኣንዱ እንደሆነ ጠቁመዋል። ይዘቱ እንደሚከተለው ኣጥሮ ቀርቧል ።

ኣንድ ሰባት ልጆች የወለዱ ኣባት ስለሽመገሉ ከመሞታቸው በፊት የኣንድነትን ጠቃሚነት ለማስተማር ፈለጉ። ሰባቱም የየራሳቸውን ዱላ እንዲሰብሩ ጠየቋቸው። ወጣቶቹም ያለምንም ችግር ሰበሩ። ደግመው ሌላ ዱላ እንዲያመጡና ኣንድላይ እንዲያስሩት ኣደረጉ። ሁሉም በየተራ እንዲሰብሩ ነገሯቸው፤ ሆኖም ኣንዳቸውም መስበር ኣልቻሉም። ኣባትም ልጆቹ እንደዱላዎቹ በህብረት ከቆሙ ማንም እንደማይደፍራቸው በተግባር ኣስተማሯቸው ይባላል ።

በተመሳሳይ ሁኔታ በ2ኛ ክፍል መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ "ስድራ" (ቤተሰብ) በሚል ርእስ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ሁሉም የቤተሰብ አባል መተባበርና የቻለውን በመስራት ቤተሰቡን ማገዝ እንዳለበት ያስገነዝባል። ሆኖም ምንባቡ በነገሩ በመቅረቡ አሰልቺ ነው። መልእክቱን የሚያጠናክሩ መልመጃዎችም አልቀረቡም። ስለሆነም ምንባቡ  አገር በቀል እውቀትን ለማስተማር የተመረጠ ነው ለማለት ያስቸግራል። ለምሳሌ በመልመጃ ሶስት ስር የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች እንመልከት፡-

1. *የቀረበውን ስዕል እያያችሁ የቤተሰቡ ኣባላት ምን ዓይነት ስራ እየሰሩ እንደሆነ በክፍል ሃሳባችሁን ግለፁ።*
2. *በቀረበው ምሳሌ መሰረት ሰዎቹ ምን ተብለው እንደሚጠሩ ግለፁ።*

| | | | |
|---|---|---|---|
| *ምሳሌ፡- የእናት ኣባት* | | ***ኣቦሓጎ (ኣያት ይባላል)*** | |
| *1. የኣባት እናት* | ---------- | *5. የእናት ወንድም* | ------ |
| *2. የኣባት ኣባት* | --------- | *6. የእናት እህት* | ------- |
| *3. የኣባት ወንድም* | -------- | *7. የኣባት እህት* | ------ |
| *4.የእናት እናት* | -------- | (ቢትክት፣ 1995 ዓ.ም. ገፅ 43) | |

የመጀመሪያው ጥያቄ በስእሉ የሚታየውን ተግባር እንዲገልፁ እንጂ ማህበረሰቡ ሊያስተላልፍ የፈለገውን የአንድነትና የመተባበር አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ ኣያግዝም። ሁለተኛው ጥያቄ ህፃናት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ኣምዳዊ ግንኙነት እንዲያውቁና ዝምድናን በሚያመለክት ኣገር በቀል ኣጠራር እንዲጠቀሙ የማድረግ ጠቀሜታ ኣለው። "ኣባየ ወንድምህ መጥቶ ነበር" ከማለትም ያድናል። ሆኖም ከምንባቡ ጋር ያልተዛመደና ድንገት ብቅ ያለ በመሆኑ ትኩረት ኣግኝቶ የተፈለገውን መልእክት ለማስተላለፍ ኣላገለገለም።

### 4.3.3.3. ከመምህር መምሪያ የተገኙ መረጃዎች

ኣበእን ከማስተማር ኣኳያ የመምህር መምሪያዎቹ ድርሻ፡- የተለያዩ ልሂቃን የመምህር መመሪያ ምንነት፣ ተግባር፣ እና ጠቀሜታ አስመልክተው የሰጧቸው ሃሳቦች ምዕራፍ 2 ውስጥ ተመልክቷል (Graves, 2000; Richards, 2001)። በልሂቃኑ ከቀረቡት ንድፈሃሳቦች ኣኳያ ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁት የመምህር መምሪያዎች ኣበእን ከማስተማር ኣኳያ ምን ድርሻ እንደተጫወቱ እንመልከት። በመጀመሪያ ደረጃ በአራቱም የትምህርት ኣምዶች ውስጥ የቀረቡት

ዓላማዎች በመምህር መምሪያው ውስጥ የሚገኙት ዓላማዎች ስለሆኑ ሰንጠረዦቹን መልሶ እዚህ ማምጣት አላስፈለገም።

መምህራን ዓመታዊ እቅድን ለማውጣት ከሚገለገሉባቸው መሳሪያዎች ዋነኛው የመምህር መምሪያ ነው። በመምሪያው ያለውን ዓላማ እና መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን በመጠቀም ዝርዝር ይዘቶችን ያወጣሉ። በመቀጠልም የዓመት፣ የመንፈቅ፣ የወርና የሳምንት እቅዳቸውን ያዘጋጃሉ። ትምህርት ሲጀመር መምህራን ከዋናው እቅድ የእለት የትምህርት እቅድ ያወጣሉ። እለታዊ እቅዱ የሚያዘጋጀው የቀረበውን ዓላማ መሰረት በማድረግና እሱን እግብ ለማድረስ ስለሆነ የሚመረጡት ምንባቦችና መልመጃዎችም ዓላማውን የሚያሳኩ መሆን አለባቸው። መምህራን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር ሆነው የሚያከናውኗቸው ተግባራትም ወደ ዓላማው የሚያደርሱ ናቸው። ለተማሪዎች የሚዘጋጁት መፃህፍት፣ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች ከተነደፉላቸው ዓላማዎች ውጪ የሆኑ ይዘቶችን በማቅረብና ተግባራትን በማከናወን ወደታለመው ግብ መድረስ አይችሉም። ከዚህ አኳያ ከ1ኛ-4ኛ ላሉት የክፍል ደረጃዎች የተዘጋጁት የመምህር መምሪያዎች ዝርዝር ኣላማዎችን አቅረበዋል። እያንዳንዳቸው ምንን ለማሳካት እንዳለሙ እንመልከት (ሰንጠረዥ 6 - 9 ይመለከቷል)።

አጠቃላይ የምንባቦች ብዛት (71) ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ለትንተና የተመረጡት 44 ናቸው በተረት መልክ የቀረቡት ምንባቦች ሁሉም ለትንተና ተመርጠዋል። የተመረጡበት ምክንያት የቋንቋ ክህሎትንና እውቀትን ለማስተማር ስለሚያገለግሉና የአበእ ማስተላለፊያ መሳሪያ በመሆናቸው ነው (Pai, 1990)። ስለዚህ የተነደፉትን ዓላማዎች በማየት አበእ በመምህር መምርያዎች ውስጥ ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው መገንዘብ ይቻላል። ለማሳያነትም የሚከተሉት ኣላማዎች ተጨምቀው ቀርበዋል፤

- የሚያውቁትን ተረት ይናገራሉ። (2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍል)
- ያነበቡትን ተረት መልእክት ይናገራሉ። (2ኛ እና 4ኛ ክፍል በድግግም)
- ያዳመጡትን ተረት መልሰው በቃል ይናገራሉ። (2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍል በድግግም)
- የእንቆቅልሽን ምንነት ተገንዝበው የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ። (2ኛ ክፍል)
- ከአካባቢያቸው እንቆቅልሽ ሰብስበው ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ።(2ኛ ክፍል)
- የተረቱን ይዘት አሳጥረው ያቀርባሉ፡፡ (3ኛ ክፍል 2ጊዜ)

ምንም እንኳ በሰንጠረዦቹ ውስጥ በርካታ ምንባቦች ቢቀርቡም ዓላማዎቹ ግን በስድስት ተጠቃልለው ቀርበዋል። የዓላማዎቹ ብዛት ስድስት ብቻ መሆን በእያንዳንዱ ምንባብ እግብ

ሊደርስ የተፈለገ የተለየ ዓላማ አለመኖሩን ያሳያል። ከያንዳንዱ ምንባብ የተለየ እውቀትና ክህሎት የማይገኝ ከሆነ በአንድ ምንባብ ቢተኩም ለውጥ እንደማይመጣ መገንዘብ ይቻላል። የእያንዳንዱ ዓላማ ትኩረት ሲታይም ከንባብ በኋላ የሚደረስበት አጠቃላይ ግንዛቤ እንጂ በውስጣቸው አበአ መያዛቸውን አያመለክትም። ይህ የሆነበት ምክንያት ዓላማዎቹ አንዱን እውቀት ከሌላው ለይተው እንዲያሳዩ ተደርገው የተነደፉ አለመሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ 'የሚያውቁትን ተረት ይናገራሉ።' የሚለው ዓለማ ግቡ ተረቱን ካነበቡ በኋላ እነሱም ተመሳሳይ ተረት መናገር ማስቻል ነው። *'ያነበቡትን' ወይም 'ያደመጡትን ተረት መልሰው ይናገራሉ'* የሚለው ዓላማም የተማሩትን የማስታወስ ችሎታ የሚያዳብር ነው። ተረቶቹ በውስጣቸው የያዟቸውን አበ እውቀቶች የትምህርቱ ዓላማ ሆነው አልቀረቡም። በእንቆቅልሽ መልክ የቀረበው የትምህርት ዓላማም የእንቆቅልሽን ምንነት እንዲናገሩ፣ እንቆቅልሽ እንዲሰበስቡ እንጂ ተደብቀው ያሉትን እውቀቶች እንዲለዩ አያግዝም። በአጠቃላይ ከዓላማዎቹ አቀራረብ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች ምንባቦቹን ካነበቡ በኋላ ስለምን እንዳነበቡ ማስታወስ ብቻ በቂ ተደርጎ መወሰዱ ነው።

በተለያዩ አጋጣሚዎች ተደጋግሞ እንደተገለፀው፡- እውቀት የሚገነባው ህፃኑ ከቤት ይዞት በመጣው እውቀት ላይ ነው (Perkins, 1992; Semali and Stambach, 1993)። ከቤት ይዞት የሚመጣው እውቀት ደግሞ በቀልድ፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ፣ ወዘተ. አማካይነት የተገኘ ነው። ምክንያቱም ህብረተሰብ ወደትውልድ መተላለፍ አለባቸው የሚላቸው እውቀት፣ ክህሎትና ዝንባሌ በልዩ ልዩ የስነቃል ክፍሎች ነው የሚያቀርባቸው (Pai, 1990)። ከትምህርት ቤት የሚገኘው አበ እውቀትም በዚህ መልክ መተላለፍ እንዳለበት ቢታመንም እየታየ ያለው ግን ከዚህ በፃራሪው ነው። ቀድሞ ያገኘው የሳይንስ እውቀት ሳይኖር (George, 1999) አዲስ የሳይንስ እውቀት እንዲቀበል ነው የተደረገው።

ከላይ እንደተመለከተው የአንደኛ ክፍል መፅሓፍ አስር ምንባቦችና በርካታ ስእሎችን ይዞ ቀርቧል፡፡ በስእሎቹና በተረት መልክ በቀረበው ምንባብ አማካይነት ህፃናቱ የገኟቸዋል ተብለው የታለሙት እውቀቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- በአካባቢ የሚሰሟቸውን ድምፆች የምን እንደሆኑ ለይተው ይናገራሉ።
- በስእል የቀረቡ ነገሮችን ስም ይጠራሉ።
- ቃላትን በጊዜ ቅደም ተከተል ይፅፋሉ።
- በክፍል ውስጥ አንድ ተረት በድራማ መልክ ያቀርባሉ።

እነዚህ አላማዎች ሁለት መልክ አላቸው። የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓላማዎች ህፃኑ ከሚያውቀው ተነስቶ አዲስ እውቀት እንዲጨምር የሚያበረታቱ ናቸው። የመጀመሪያው ዓላማ ህፃናት የሚሰሟቸውን ድምፆች ከሚያዩአቸው የእንስሳት ስእሎች ጋር ማገናዘብን የሚያስተምር ነው። ሁለተኛውና ሶስተኛው ዓላማዎች ህፃናቱ አዘውትረው በሚያዩአቸው ስእሎችና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ህፃናት ስእሎቹን አይተው፤ የሰው የእንስሳት፣ የመመገቢያ እቃዎች፣ አልባሳት፣ አዝርእት፣ ዛፎች፣ እያሉ መለየት መቻላቸው የሚረጋገጥበት ነው። እነዚህን ተግባራት ሲያከናውኑ ትምህርቱ የሚያውቁት መሆኑ በማመን በዚሁ ላይ የተመሰረተ አዲስ እውቀት ለመቀበል እንዲጓጉ ያደርጋቸዋል (Settee, 2007)።

አራተኛው ዓላማ ግን ህፃናቱ የሚገኙበትን ደረጃ ያገናዘበ አይመስልም። ተረቱን ካነበቡ ወይም ካደመጡ በኋላ የተላለፈውን እውቀት መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ ቢታቀድ የተሻለ ይሆን ነበር። በመፅሐፉ ውስጥ ያለው አንድ ተረት ብቻ ነው። እሱን ካነበቡ በኋላ ግን ሌላ ተረት በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ነው የሚጠይቀው። ስለድራማም ሆነ ስለመተወን የተማሩት ነገር ሳይኖር ዓላማውን ለማሳካት በተግባር ተውኔት እንዲያቀርቡ መጠየቁ ተገቢነት የለውም።

በአራቱም ክፍሎች የመምህር መምሪያዎች ውስጥ ህፃናት ከትምህርት በኋላ ልዩ ልዩ ንኡሳን ክሂሎችንና እውቀቶችን እንደሚገበዩ ተመልክቷል። ከትምህርት በኋላ ምን ምን ተግባራት እንደሚያከናውኑና ምን እውቀት እንደሚቀስሙ በአላማዎቹ አማካይነት ተገልጿል። የትምህርቱ ትኩረትም ምን ላይ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል። ተማሪዎች እንዲወያዩባቸውና እንዲያውቋቸው ባይደረግም በአራቱም መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ጥቂት አበእ ላይ ያተኮሩና የማህበረሰቡን እውቀት የያዙ ምንባቦች ቀርበዋል። የአራቱም ክፍሎች (1-4) የመምህር መምሪያዎች ግን ከአበእ ጋር የተያያዘ አንድም ዓላማ የላቸውም። ስለዚህ መማሪያ መፃሕፍቱ ዓላማ ያልተነደፈለትንና ትኩረት ያላገኘን ይዘት ሊያቀርቡ ይችላሉ ተብሎ አይጠበቅም።

*እያንጓንዱን ተረት፣ እንቆቅልሽ ወይም ሌላ ወግ ተከትለው የሚቀርቡት ተግባራትና መልመጃዎች ተማሪው ይበልጥ ከአገር በቀል እውቀት ጋር እንዲተዋወቅ የማድረግ*

ብቃታቸው የሚመለከት መረጃ እንዲሰጡ ለመምህራንና ለስርዓተትምህርት ባለሙያ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

የስርዓተትምህርት ባለሙያው፣ በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ ይዘቶች እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው በመምህር መምሪያው ውስጥ በዝርዝር መገለፁና የተማሪና የመምህር ድርሻ ምን መሆን እንዳለበት በግልፅ መቅረባቸውን ያስረዳሉ።

በቃለመጠይቅና በተኰር የቡድን ውይይት የተሳተፉት መምህራን ግን ባለሙያው በሰጡት ሃሳብ ላይ አይስማሙም። ይኸውም፣ መምህራኑ ተቸገርን ከሚሉበት ጉዳይ አንዱ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ይዘቶች ለምን እንደተመረጡና ወደተማሪው እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው የሚያስረዳ መረጃ አለመኖሩ ነው። ለምሳሌ ተረቶች እንዴት መቅረብ እንዳለባቸውና ከተለመደው ውጪ ምን ለማስተማር እንደሚያገለግሉ የሚያስረዳ መረጃ እንደሌለ ይጠቅሳሉ። ከመርሃትምህርቱ፣ ከተማሪው መፅሐፍና ከመምህሩ መምሪያ የተገኘው መረጃም የመምህራኑን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው። በመምህር መምሪያና በመርሃትምህርቱ ውስጥ አበእን ለማስተማር የተቀመጠ ዓላማና ግብ እንደሌለ ቀደም ሲል ተጠቁሟል። በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት መልመጃዎችም የቋንቋ ሳይንስ እውቀትና ክህሎትን እንጂ አበእን ለማስተማር እንዳልቀረቡ በፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ስለአበእ የሚያወሳ መልመጃ ባይኖር መምህራኑ ራሳቸው የመልመጃ ጥያቄዎች ለምን ማዘጋጀት እንደማይሞክሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ መረጃ አቀባይ መምህራኑ ከዚህ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ሁለት መሰረታዊ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ገልፀዋል። **አንደኛው ችግር** መምህራን ከቃላት፣ ከዓረፍተነገር ምስረታ፣ ከዕሕፈት፣... ጋር የተያያዙ መልመጃዎች እንደሚያዘጋጁና ስለ አበእ ግን ካሁን በፊት የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልፀዋል። ማሰልጠኛ ተቋም እያሉም ሆነ ከዚያ በኋላ ባገኟቸው ስልጠናዎች አበእን የተመለከተ መረጃ አግኝተው አያውቁም። **ሁለተኛው ችግር** የመምህሩ መምሪያ ትኩረቱ ቋንቋው ፊደላት፣ ቃላት፣ ሐረጋት፣ አንቀፅና ድርሰት ላይ ብቻ መሆኑ ነው። በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ አገር በቀል እውቀትን ማስተማር የሚችሉ ምንባቦች ቢኖሩም እንኳ እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው በሚያሳይ መልኩ ስላልተዘጋጀ በተለይ አበእን ከማስተማር አኳያ አጋዥ መሳሪያ መሆን እንዳልቻለ ይገልፃሉ። ስለሆነም መምህራን ስለ አበእ በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው በተረቱ ሊተላለፍ ከተፈለገው እውቀት አኳያ ተማሪዎቹን ለማወያየት ሙከራ እንደማያደርጉ መገንዘብ ተችሏል። የስርዓተትምህርት ባለሙያው ግን

የመምህር መምሪያው እያንዳንዱ ይዘት እንዴት መቅረብ እንዳለበት ማመልከት እንደሚችል የገለፁት ስለአጠቃላይ የቋንቋ መልመጃዎች አቀራረብ እያሰቡ ይመስላል።

### 4.4. በተጋሩ ዓይን በመፃሕሕፍቱ ውስጥ ያሉ እውቀቶች አገር በቀልነት

ለመረጃ አቀባዮች የቀረበው ጥያቄ፦ *በተጠኚዎቹ መፃሕፍት ውስጥ ያሉት እውቀቶች የህብረተሰቡ እውቀቶች ናቸው?* የሚል ነበር። ይህ ጥያቄ፤ ሁሉንም መረጃ አቀባዮች ያሳተፈ ነው። ከመረጃ አቀባቶች የተሰጠውን ምላሽና ትንተና ከማየታችን በፊት ለማስታወስ ያህል አገር በቀል የሚባለው እውቀት እንዴት ያለ እንደሆነ ባጭሩ እንመልከት።

አበእ፤ ምንም እንኳን ምዕራባውያኑ በሳይንስ ቤተ ሙከራ ምርምር ያልተገኘውን እውቀት እንደ እውቀት የማይቆጥሩትና ህዝቡንም ያልሰለጠነ፣ ኣላዋቂ፣ የተናቀ የሚል ፍቺ ቢሰጡትም ህዝቡ ግን አሁንም ራሱን እያስተዳደረበት ያለ እውቀት ነው (Battist, 2002)። ምዕራፍ አንድ ስር እንደተጠቀሰው፣ በአገር በቀል ህዝቦች ዘንድ ንባብ፣ ድግር ጠረባ፣ ስሌት፣ የከብት ህክምና፣ ወቅትን ለይቶ የተለያዩ ተግባራት ማከናወን መቻል፤ ሁሉም መማርን የሚፈልጉ እውቀቶች ናቸው። የህብረተሰቡ አባላትም በሰው፣ በእንስሳት፣ በእፀዋት ላይ የሚያዩዋቸውን ለውጦች ተገንዝበው እንደሁኔታው ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ አገር በቀል እውቀቶች አሏቸው። እነዚህ እውቀቶች ተቀባይነት የሚኖራቸው በተፈጠሩበት አካባቢና በፈጠራቸው ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ሊሆን ይችላል።

የምዕራባውያን ወይም ዘመናዊ የሚባለው እውቀት በየትኛውም የዓለም ክፍል ያለ ተማሪ የሚጋራው ሲሆን አበእ ግን የአንድ ህብረተሰብ መታወቂያ ነው። መንግስታት ህዝቦችን የተመለከተ ፖሊሲ ማውጣት ሲፈልጉም መነሻ የሚያደርጉት የየአካባቢውን እውቀት፣ ባህልና ፍላጎት ነው (Ossai, 2010)። ይህም የህብረተሰቡን ፍላጎት ጠብቆ ለማስተዳደርና ለሚነሱ ችግሮች አካባቢያዊ መፍትሄ ለመስጠት ስለሚያስችል ነው። አበእ ወደቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ አለበት። ወደ ቀጣዩ ትውድ ማስተላለፍ ማለት ግን አዲሱ ትውልድ የነበረውን እንዳለ እንዲቀበል ማስገደድ ሳይሆን ተረካቢው ትውልድ እንደሁኔታውና ለእሱና ለዘመኑ በሚስማማ መልክ አሻሽሎ ሊገለገልበት ማስቻል ነው። ለዚህም ነው አበእ ታዳሽ፣ አዳጊና ተለዋዋጭ እንደሆነና የህብረተሰቡ ባህል፣ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ መዋቅር፣ ወዘተ. ሲለወጥ አብሮ እንደሚለወጥ የሚገለፀው Grenier (1998)፣ Msuya (2008) እና Zuluስ 2006) ።

ለምሳሌ በምስራቅና ማእከላዊ ዞን ትግራይ ያለው የእርሻ መሬት ከደቡቡ ጋር ሲነፃፀር ስስ ነው። በዚህ የመሬት ልዩነት ምክንያት የእርሻ ወቅት ልዩነት እንዳለ ታይቷል። ይህ የሚያመለክተው ኣበእ በኣካባቢና በሁኔታ ውስጥ የሚዳብር መሆኑ ነው። ህብረተሰቡ የፈጠረው እውቀት ዘላቂ ሆኖ ወደ ተከታዩ ትውልድ የሚተላለፈው ጠቃሚ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ብቻ ነው። ለምሳሌ 'ሰባት ጊዜ እንዳያርሱ ሰባቱን ያርሱ' የሚለው ምሳሌኣዊ ኣነጋገር ደጋግሞ የማረስን ኣስፈላጊነት የሚያጐላ ነው። ደጋግሞ ማረስ ኣሁንም ኣስፈላጊ እንደሆነ ይታመንበታል። በሁለት በሬዎችና በነባር ሞፈር፣ ቀንበርና ማረሻ ማረስ ኣሁንም ያለ ቢሆንም በኣንድ በሬ፣ በበቅሎ ወይም ፈረስ፣ በተለየ ማረሻና ቀንበር ለማረስ ሙከራ እየተደረገ ነው። ኣዲሱ ኣሰራር ምርትን እስካሳደገለት ድረስ የማይቀበልበት ምክንያት ኣይኖርም። ይህ፣ ኣዲሱ ትውልድ የነበረውን እውቀት እንዳለ እንዲረከብ የሚገደድ ኣለመሆኑና ኣበእ ኣዳጊና ተለዋዋጭ መሆኑን ያመለክታል። ወቅትን ጠብቆ ማረስ፣ መዝራት፣ ማረም፣ መሰብሰብ፣ ወዘተ. ኣሁንም እየቀጠሉ ያሉ ጠቃሚ እውቀቶች ናቸው።

ትግራዋይ ገበሬ ምርት እንዳይባክንበት ከኣጨዳ ጊዜ ጀምሮ የሚያደርጋቸው ጥንቃቄዎች ኣሉ። እህሉ በሚገባ መድረቁን ማረጋገጥ፣ ምርት እንዳይረግፍ በጤዛ ማጨድ፣ ክምር በምስጥ እንዳይበላ ባህላዊ መከላከያ መጠቀምና የመሳሰሉት እርምጃዎችን ይወስዳል። እነዚህ እውቀቶች በህዝቡ ውስጥ የዳበሩ ናቸው። በሌላ በኩል ነቀዝ የሚከሰተው በምርት ማከማቻ ውስጥ በሚፈጠር ሙቀት እንደሆነ በሚገባ ይገነዘባል። ምርቱን ምሽት ወይም ንጋት ላይ በማፈስና የቀፎውን ቅዝቃዜ ለመጠበቅም ጥረት ያደርጋል።

> *ምርት ከገለባ ተለይቶ ለመታፈስ ዝግጁ ሲሆን እንዲቀዘቅዝ የምሽት ወይም የማለዳ ውርጭ እንዲያርፍበት ይደረጋል፡፡ እህል ነቀዝ ሊፈጥር የሚችለው በውስጡ ሙቀት ሲኖር ነው፡፡ የታፈሰበት ወቅት ቀዝቃዛ ከሆነ፣ የሚቀመጥበት ቦታም እንዲሁ ከሆነ ነቀዝ ሊፈጠር ኣይችልም፡፡* (ቃመ.ማ. 3 07.7.2005)
>
> *ኣመድ የነቀዝ መከላከያ መሳሪያችን ነው፡፡ የፍየል በጠጥ ኣመድ ኣለዚያም የእንጨት ኣመድ ከተነፋ በኂላ ውርጭ ላይ ያድራል፡፡ ከነቅዝቃዜው እያለም ከእህሉ ጋር ይቀላቀልና ቀፎው ውስጥ ይገባል፡፡ በዚህ መልክ ቅዝቃዜው ተጠብቆለት የተቀመጠ እህል በነቀዝ ኣይበላም፡፡ የኣመዱ ድርሻም በቀፎው ውስጥ ሙቀት እንዳይፈጠር መከላከል ነው፡፡ የጠላ ኣተላና ሎሚም በኣካባቢያችን*

*የተለመዱ የነቀዝ መከላከያና ማጥፊያ መድሃኒቶች ናቸው፡፡* (ቃመ. ምብ. 7፣ 25.08.2004 ዓ.ም.)

እነዚህ መከላከያዎች ለዘመናት አገልግለዋል። ሆኖም ዘዴው በጣም አድካሚና የምርቱን ጥራት የሚጐዳ ይመስላል። አስተማማኝነቱም ከተፈጥሮ አየር መለዋወጥ ጋር ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል። ስለዚህ አዲሱ ትውልድ አንድም የአየር ሁኔታውን የሚቋቋም ማከማቻ በመስራት ወይም አበ መድሃኒቱን በማዘመን አጠቃቀሙን ቀላል ማድረ ይችላል።

ትግራዋይ ገበሬ እንስሳትን በማርባት የገቢ ምንጬን ያዳብራል። እነዚን የገቢ ምንጬ የሆኑትን እንስሳት የሚንከባከብባቸው አገር በቀል እውቀቶች አሉት። ለምሳሌ እንስሳት መታመማቸውን የሚለይባቸውና የሚያክምባቸውን እውቀቶች መጥቀስ ይቻላል።

> *አንዳንዱ በሽታ ከሰውነታቸው በሚወጣ ፈሳሽ፣ በፀጉራቸው፣ በሚያሳዩት ለውጥ፣ በአመጋገባቸው፣ በአካላቸው ላይ በሚታይ እብጠት ወይም ቁስለት ይታወቃል።* (ቃመ. ምብ.2፣ 25-08-2004ዓ.ም.)
>
> *ከብቶች ሲታመሙ እንደየበሽታው አይነት የተለያዩ ምልክቶች ያሳያሉ። ምልክቶቹም ከአየት ቅድመአየት ጀምሮ ያየናቸው ስለሆኑ የትኛው በሽታ እንደያዛቸው ማወቅ እንችላለን። አንዳንዱ በሽታ፡- ከሰውነታቸው በሚወጣ ፈሳሽ ይታወቃል። አንዳንዱ በፀጉራቸው ሁኔታ ይለያል። ሌላው ደግሞ በሚያሳዩት ባህሪ ይታወቃል። (ተቡው 2፣ 07-05-2005ዓ.ም.)*

ገበሬው እነዚህን ምልክቶች ሲያይ እንደየበሽታው ዓይነት የተለያዩ አበ መድሃኒቶችን ሰጥቶ ያድናቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ አበእ፣ በአፈታሪኮች፣ በተረቶች፣ በመዝሙሮች፣ በከበራዎች፣ በአካባቢያዊ ሕጎች (ሕጊ ገረብ) እና በተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ይተላለፋል። የአገር በቀል ቋንቋ ማስተማሪያ ሆኖ በሚያገለግልባቸው ህዝቦች ውስጥ ደግሞ እነዚህን የትውፊት አላባውያን በመማሪያ መፅሐፉ ውስት በማካተት ህፃናት እንዲማሯቸው የሚደረግባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ። አንደኛው የትውፊት አላባውያኑ ቋንቋን ለማስተማር ምቹ ስለሆኑ ነው። በተረቶቹና በሌሎቹ ቃላዊ ሃብቶች አማካይነት ሰዋስውን፣ ንባብን፣ የአነጋገር ስልቶችን፣ ፍቺዎችን፣ ቅኔዎችን፣ ዘይቤዎችንና የመሳሰሉትን በተሻለ መንገድ ማስተማር ስለሚቻል ነው። ሁለተኛው ምክንያት ሁሉም ቃላዊ ሃብቶች ስለህዝቡ፣ ስለአካባቢውና ስለፈጣሪው የሚያወጉ ስለሆኑና እውቀቱ የሚተላለፈውም በነሱ ስለሆነ ነው።

የMosha (1999) ሃሳብ እንዳለ እዚህ ብጠቀምበት፡- በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የትውፊት አላባዎችን አለመጠቀም ማለት ትግራዋዩን ህፃን ስለራሱ፣ ስለባህሉ፣ ስለአገራዊ እውቀቱ እንዳይሰማ ማገድ መለት ነው። ከዚህ አኳያ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ላሉ ህፃናት የተዘጋጁት የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት የህብረተሰቡን እውቀቶች ማካተት አለማካተታቸው ለማረጋገጥ ፍተሻ ተካሂዷል።

ህብረተሰቡ ምንባቦቹ እና መልመጃዎቹ ምን መልክ ቢኖራቸው ነው " የኔ" የሚላቸው? ህብረተሰቡ ለዘመናት የተጠቀመበት አስተራረስ፣ ከአገርእት አጠባበቅ፣ ከህክምና፣ ከስነምግባር፣ ከፍትህ አሰጣጥ፣ ከምርት አያያዝና አከፋፈል፣ ወዘተ የተያያዙ እውቀቶች አሉት። በመፃሕፍቱ ውስጥ የሚቀርቡት ምንባቦችና መልመጃዎች በመገለጫዎቹ ውስጥ ያሉትን እውቀቶች የሚያንፀባርቁ ከሆነ፤ ወይም ደግሞ ስርዓተትምህርቱ፣ ህብረተሰቡ ወደ ቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ አለባቸው ብሎ የሚያምንባቸውን እውቀቶች የያዘ ከሆነ አበእ ትኩረት አግኝቷል ሊባል ይችላል። ህብረተሰቡም ስርዓተትምህርቱ የእውቀቱ ማስተላለፊያ ሆኖ አገልግሏል በሚል እምነት የኔ ነው ብሎ ሊቀበለው ይችላል።

የአበእ ማስተላለፊያ የሆኑት ተረቶች ጥቅል እና ዝርዝር መልእክት ይዘው ይቀርባሉ። ለምሳሌ የሚከተሉት ከየክፍሉ የተመረጡትን ተረቶች እንመልከት። 1ኛክፍል፣ "የሌሊት ወፍ" በሚለው ተረት አማካይነት "ቀን ይረዝማል እንጂ ውሸታም መጋለጡ አይቀርም" የሚል ጥቅል መልእክት ተላልፏል። እንዲሁም በየሌሊት ወፍ የተንፀባረቀው የማንነት ቀውስና የወፎችና አይጦች ማስተዋል የጐደለው የስሜት ፍትጊያ ወገንን ከጠላት ለመለየት እንዳላስቻላቸው ያሳያል። ከ2ኛ ክፍል "ወፍና ዝሆን" የሚለው ምንባብ "ትእቢት ሁሌም ውድቀትን ያስከትላል" የሚለውን የተጋሩን እምነት ይገልፃል። ተረቱ በዝርዝር ሲታይ ደግሞ ዝሆን፣ ጉልበቱን መከታ አድርጎ ግፍ የሚፈፅምን ሰው ይወክላል። ወፎችና እንቁራሪቶች ደግሞ የትም አይደርሱም የተባሉና የተናቁ፤ ነገር ግን በህብረትና በጥበብ ትምክህተኛውን ድል ሊያደርጉት እንደቻሉ ያሳያል።

ከ3ኛ ክፍል "ሶስት በሬዎችና ጅብ" የሚለው ምንባብ "አንድነት ሃይል ነው" የሚል ጥቅል መልእክት ያስተላልፋል። እንዲሁም በበሬወቹ የተመሰሉት የዋህ ሰወች በጅብ በተመሰሉት ተንኮለኞች እንዳይሞኙ የሚያስጠነቅቅ ነው። ከ4ኛ ክፍል ከተወሰደውና "አንበሳና ቀበሮ" ከሚለው ምንባብ እውነት ምንጊዜም አሸናፊ ነች የሚል ጥቅል መልእክት ተላልፏል። አንበሳ ጉልበቱን ተማምኖ በሃሰት ምስክሮች ያልሆነውን ሆነ ለማሰኘት ቢሞክርም

እውነትን ማጥፋት እንዳልቻለ፤ በመጨረሻም ተጠቂዋ ቀበሮ በፍትህ እንዳሸነፈች ያሳያል። ይህም፣ ሓቀኛ ሰው በዋሾዎች ድል ካልተደናገጠ ማሸነፉ እንደማይቀር የሚያስተምር ነው።

እነዚህ ምንባቦች ከህብረተሰቡ የተገኙ የአበእ ማስተማሪያዎች ናቸው። በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ አበእን ለማስተማር አላገለገሉም የተባለበት ምክንያት ምንባቦቹን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች ህፃናት ስለእውቀቱ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ስላልቀረቡና ትኩረት ስላልተሰጣቸው ነው። በአገር በቀል ህዝቦች ዘንድ የአገር በቀል ትምህርት (Indigenous Education) ምንጮች የእድሜ ባለፀጋ ሰዎች ወይም ተረት ተናጋሪ ሰዎች ናቸው። ካለፉት ትውልዶች የሰበሰቡትን እውቀት በተለያዩ ዘዴዎች ወደ አዲሱ ትውልድ ያስተላልፋሉ። በተተኳሪዎቹ መፃሕፍት ውስጥ እውቀት ሲተላለፍ የሚታየው ግን የምዕራባዊያኑ "ዘመናዊው" ትምህርት በቀሰሙ ሰዎች ብቻ ነው። በተጠቀሱት ሰዎች የተላለፈው እውቀት የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። አገር በቀል እውቀትን ከማስተማር አኳያ ግን ህብረተሰቡ፤ ስለኔ የሚናገር፣ የኔ ስርዓተትምህርትን ነው ብሎ ሊቀበለው አይችልም።

ለትምህርት ባለሙያ መረጃ አቀባዮች ምንባቦቹና መልመጃዎቹ የህብረተሰቡን እውቀት የሚያንፀባርቁ ስለመሆናቸው ለማወቅ የሚያስችል ጥያቄ ቀርቦ ነበር።

> *ህብረተሰቡ በፅሁፍ የመግባባት ደረጃው ዝቅተኛ ቢሆንም ቃላዊ ሃብቱ ግን ሰፊ ነው። በመፃሕፍቱ ውስጥ አበእን ማስተዋወቅ የሚችሉ ጥቂት ምንባቦች ቀርበዋል። ህፃናቱም እነዚህን ለማንበብ በጣም ይጓጓሉ። ምንባቦቹን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች ግን ቃላዊውን ሃብት ተጠቅመው የህብረተሰቡን እውቀት ማንፀባረቅ አልቻሉም። እያንዳንዱን ምንባብ ተከትለው የሚመጡት ተግባራትና ክንውኖች ትኩረትም በቋንቋ መዋቅርና በአንብቦ መረዳት ላይ ብቻ ነው። በአጠቃላይ በመፃሕፍቱ ውስጥ አገር በቀል እውቀትን ለማስተማር አልሞ የቀረበ መልመጃ አለ ለማለት ይከብዳል።* (ቃመ.መም1.7፣ 22-12-2004 ዓ.ም.)

ከመምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው አብዛኞቹ ምንባቦች የማህበረሰቡን እውቀት የሚገልፁ አይደሉም። አበእ ላይ ያተኮሩ ጥቂት ምንባቦች ቢኖሩም መልመጃዎቹ፣ ምንባቦቹ ውስጥ ያሉ እውቀቶችን ለማሳየት አላገለገሉም። ምንም እንኳ ህብረተሰቡ ሰፊ ቃላዊ ሃብት ቢኖረውም መፃሕፍቱ ግን ይህንን ሃብት መጠቀም አልቻሉም። በሌላ አገላለፅ ጥቂቶቹን ምንባቦች የኔ ናቸው ቢል እንኳ መልመጃዎቹን ግን ይህንን እውቀት አያዳብሩምና የኔ ሊላቸው አይችልም። "ለምሳሌ የሌሊት ወፍ" የሚለውን ምንባብ ተከትለው የመጡት መልመጃዎች፡-

*1. የምታውቋቸውን ተረቶች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።*

*2. የምታውቋትን ተረት በክፍል ውስጥ በተውኔት አቅርቡ።*(ገፅ 135)

እንዳቸውም በምንባቡ የተጠቀሰውን የማህበረሰቡ እውቀት ለማጉላት አልሞከሩም። በተኮር የቡድን ውይይት የተሳተፉት መምህራንም በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉ እውቀቶች አበእ ስለመሆናቸው ተጠይቀው፡

> *ምንባቦቹ ተረት መሆናቸው እኛ እንነግራቸዋለን እንጂ ህፃናቱ ተረት በመሆኑ ስሏቸው የሚያነቡትና ሃገራዊ እውቀት የሚቀስሙበት አይደለም። ተረት የተለመደና አካባቢያዊ የሆነ የአጀማመርና የአጨራረስ ስርዓት አለው። ለምሳሌ ተራኪው **ነበረያ ነበረ** (ተረት ተረት) ብሎ ሲጀምር ሁሉም አድማጮች ነቃ ባለና ለማድመጥ በጓጓ ስሜት **"እንታይ ነበረ?"** (የላም በረት፣)፣ በማለት ለማድመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣሉ። እንቆቅልሽ ከሆነም የራሱ የሆነ የአጀማመርና አጨራረስ ስርዓት አለው።... በመፃህፍቱ ውስጥ ግን አልቀረቡም። በአጠቃላይ መፃህፍቱ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱና በትግራይ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ያዘጋጇቸው አይመስሉም።* (ተቡው. 13-12-2004 ዓ.ም.)። የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

በውይይቱ ወቅት የተነሱት ነጥቦች ሁለት ናቸው። **አንደኛው ነጥብ**፡- መልመጃዎቹ የተማሪውን ቀዳሚ እውቀት በመነሻነት ተጠቅመው አካባቢውን እንዲያደንቅ፣ በተረቶቹ ወይም በምሳሌዎቹ አማካይነት ማህበረሰቡ ሊያስተላልፈው የፈለገውን እውቀት፣ ክህሎት ወይም ፍልስፍና እንዲገነዘብ የሚያግዙ አለመሆናቸው ነው። **ሁለተኛው ነጥብ**፡- ከቅርፅ ጋር የተያያዘ ነው። ተረትም እንቆቅልሽም የተለመደ የአጀማመርና የአጨራረስ ስርኣት ቢኖራቸውም በመፃህፍቱ ውስጥ ግን ስርዓቱን የተከተለ አቀራረብ አልታየም። ህፃናቱ ዕሁፉ ተረት መሆኑ አያውቁትም የተባለውም ለዚህ ነው፡፡ ስለዚህ ችግሩ የይዘት ብቻ ሳይሆን በቅርፅም ተገቢነት የጐደለው መሆኑ ነው። መልመጃዎቹም *"ፍቺ ስጡ?'፣ 'ዐ.ነገር መስርቱ?'፣ 'አስተካክላችሁ ፃፉ?'፣ 'የስንኝ መጠን ተናሩ?'፣ '--- ያለው ማን ነው?'፣ '--- ያደረገው ለምንድነው?"* በሚሉና በቃንቋው ክህሎትና እውቀት ላይ ብቻ ያተኮሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ለባለሙያው የቀረበው ቀጣይ ጥያቄ በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን (1-4) የቋንቋ ስርዓተትምህርት ውስጥ ኣገር በቀል እውቀት እንደ ኣንድ ይዘት እንዲገባ የሚታቀድ ስለመሆኑ ለማወቅ ያለመ ነው።

ከባለሙያው ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው፣ በትግራይ ደረጃ የትግርኛ ቋንቋን በማስተማሪያ ቋንቋነት ለመጠቀም ሲታሰብ ኣስቀድሞ የተቀመጠ ግብ እንዳልነበረ ነው። ትምህርቱ የተጀመረውም ለህወሓት ታጋዮች (ለኣዋቂዎች) በተዘጋጁ መፃሕፍት ነው። ከዚህ ኣልፎ በኣፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ኣስፈላጊነት፣ ስለኣዘገጃጀቱም ሆነ ሊተኮርባቸው ስለሚገባ ጉዳዮች የተሰጠ ስልጠናም ሆነ መመሪያ ኣልነበረም።

*በኣፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር የሚል ፍላጎትና ግፊት ስለነበረ ብቻ ነው የተጀመረው። በሃሳብ ደረጃም ትምህርቱ በኣካባቢ ጉዳዮች፣ ባህልና እምነት ላይ ማተኮር እንደሚገባ እንነጋገራለን። በፅሁፍ ግን የተዘጋጀ የመስሪያ ሰነድ ወይም መመሪያ ኣልነበረም ኣሁንም የለንም።* (ቃ.መ. ስባሙ. 28-12-2004 ዓ.ም.)

ከተሰጠው ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው በትግርኛ ቋንቋ ማስተማር የተጀመረው ዓላማና ግቡ ታውቆ፣ ህፃናት በቋንቋቸው በመማራቸው የሚያገኟቸው ጠቀሜታዎች ተለይተውና በእቅድ ተደግፎ ኣልነበረም። ምንም እንኳን ህፃኑ ኣፍ በፈታበተ ቋንቋ መማር እንደሚገባው ቢታመንም ምን፣ እንዴት፣ ምን ለማግኘት መማር እንዳለበት የሚያመላክት መመሪያ ኣልነበረም። መመሪያዎች ኖረው ለማስተማር ቢታቀድም ጠቃሚና ኣስፈላጊ የሚሏቸውን ይዘቶች ለማስገባትና የማያስፈልጉትን ለማስወጣት ወይም ለመቀነስ እንኳ የሃገር ኣቀፉ የይዘት ሽንሽና ሊገድባቸው እንደሚችል ከመርሃትምህርቱ የኣዘገጃጀት ሂደት መገንዘብ ይቻላል።

ትግራዋይ ህብረተሰብ በመማሪያ መፅሓፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች እሱን የሚገልፁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለመረጃ ኣቀባዮች 13 ጥያቄዎች ቀርበው ነበር። ከነዚህ ውስጥ ኣራቱ ጥያቄዎች (ከ1-3 እና 13) በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን ኣሉታዊ ኣገላለፃች ህብረተሰቡ የሚቀበላቸው መሆኑ፣ ዘጠኙ ጥያቄዎች (ከ4-12) ደግሞ በተረት መልክ ከቀረቡት ምንባቦች የወጡት መልመጃዎች ኣበእን ለማስተላለፍ መቻል/ ኣለመቻላቸውን ለማረጋገጥ የቀረቡ ነበሩ።

በአራቱም መማሪያ መፃሕፍት በተረት መልክ የቀረቡ ምንባቦች አስር ናቸው። ሁሉም የተለመደው የተረት መግቢያና መደምደሚያ ባይኖራቸውም የተጋሩን እውቀት የሚገልፁ ናቸው። ተረቶቹ፤ የፍትሃዊነትን፣ የስራ ክቡርነትንና የህብረትን አስፈላጊነት ያስተምራሉ፤ ክህደት፣ በሃይል መመካት፣ ማጭበርበር ደግሞ ሊወገዙ የሚገባቸው መጥፎ ምግባሮች መሆናቸውን ያሳያሉ። እነዚ፣ ማህበረሰቡ ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚፈልጋቸው እውቀቶች መሆናቸው ቀደም ሲል የህብረተሰቡ አባላት በሰጧቸው ምላሾች ማረጋገጥ ተችሏል።

ግብርና፣ እህልና አጠቃቀሙ፣ ቃርሳ በሚሉት ምንባቦች ስር ያሉትን ገለፃዎች ግን ማህበረሰቡ አይቀበላቸውም። ከላይ በተጠቀሱት ንኡሳን ምዕራፎች ስር እንደተመለከተው፤ ህብረተሰቡ ከመሬት አስተራረስ፣ ከመሬት ለምነት አጠባበቅ፣ ከአረምና ከተባይ መከላከል፣ ከምርት እንክብካቤ፣ ከሰውና እንስሳት ጤንነት አጠባበቅ የተያያዘ የዳበረ እውቀት እንዳለው መረጃ አቀባዮቹ አመልክተዋል። በተለይ የእርሻ መኪና መጠቀም ያልተቻለው ባለማወቅ ወይም ባለመፈለግ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ የመሬት አቀማመጡ አመቺ ባለመሆኑ እንደሆነም ተብራርቷል። ከተሰጡት ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች ህብረተሰቡ ወቅትን ጠብቆ ከማረስና እንክብካቤ ከማድረግ የተያያዘ ችግር እንደሌለበት መገንዘብ ተችሏል። የሚጠቀምበት የእርሻ መሳሪያን ግን በተሻለና ከአካባቢው ጋር በሚስማማ ሌላ መሳሪያ ቢቀየርለት ተጠቃሚ እንደሚሆን ያምናል።

በሌላ አገላለፅ፣ በመፃሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት ተረቶች የሚያስተላልፏቸው እውቀቶች ህብረተሰቡ ማስተላለፍ የሚፈልጋቸው እውቀቶች ሆነው ተገኝተዋል። ከግብርና ስራ ጋር ተያይዞ የቀረቡት ትችቶች ግን ከህብረተሰቡ የተውጣጡ መረጃ አቀባዮች የሰጧቸውን ማስረጃዎችና በመምህራን ከተሰጡት አስተያየቶች ጋር ሲነፃፀሩ የህብረተሰቡ እውቀቶች ናቸው ለማለት አያስደፍሩም። ስለገና ጨዋታ የሚገልፀው ምንባብም ጨዋታው ህግና ስርዓት ሊወጣለት እንደሚገባ ያሳስባል። ነገር ግን ህጉን ወደ ፅሑፍ መቀየርና አስፈላጊ ማስተካከያ ተደርጎበት በተወሰነ ቦታ እንዲሰጥ መድረግ ካልሆነ በቀር ያልተፃፈ ህግና ስርዓት ስላለው ህግና ስርዓት የለውም መባሉ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል።

በተረት መልክ የቀረቡት ምንባቦች የአገር በቀሉ ህዝብ ተረቶች እንደሆኑ አይተናል። በመፃሕፍት ውስጥ እንዲገቡ የሚደረገው፤ መልመጃዎችን በማቅረብ ምንባቡ

የሚያስተላልፈውን እውቀት ለማጉላት፣ የቋንቋ እውቀትንና ክህሎትን ለማስተማር ነው። ህፃናት የቤት እውቀታቸውን በትምህርት ቤት እንዲያዳብሩት ማለማመድ፤ ህብረተሰብ የኔ የሚለው እውቀት እንዳይረሳ፣ እንዳይጠፋና አንፃራዊ የሆነ ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረግ ነው (Ossai, 2010; Pai, 1990)። በተለይ በመልመጃ ሶስት ስር የሚቀርቡት ጥያቄዎች በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገውን እውቀት ሊያስተዋውቁ ይገባል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ምንባቦቹን ተከትለው የመጡት መልመጃዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ከአበእ ጋር ግንኙነት የላቸውም። ስለሆነም ዓላማውን የሚያሳኩ ሆነው አልተገኙም። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመልከት።

- *ጠጣ ከሞት እንዴት እንዳመለጠች ተናገሩ።*
- *ቤተሰቦቻችሁ የነገሯችሁን ተረት በክፍል ውስጥ አቅርቡ። (2ኛ ክ. ገፅ 6)*
- *የምታውቁት ተረት ተናገር።*
- *መፅሓፋችሁን ሳታዩ ተረቱን በቃል ተናገሩ። (3ኛ ክ. ገፅ 7)*
- *በአካባቢያችሁ ከሚከበሩ ባህላዊ ስፖርቶች ስለአንዱ ባለ 8 መስመር ግጥም ፃፉ። (4ኛ ክ. ገፅ 98)*

በመልመጃ አንድና ሁለት ስር የሚቀርቡ ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትንና ከስነልሳን ጋር የተያያዙ እውቀቶችን የሚማሩባቸው ስለሆኑ አበእ ላይ ያተኮሩ ይዘቶች ሊቀርቡ አይችሉም። ስለሆነም ምንባቦቹ አበእን ለማስተማር ታቅዶ የተመረጡ አለመሆናቸው መረዳት ይቻላል።

## 4.5. የምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ተገቢነት አበእን ከማስተማር አኳያ

የምንባቦችና የመልመጃዎች አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለማወቅ "በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉትን ባህላዊ ይዘቶች የሚማሯቸው በምን መልክ ነው?" የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር። በዚህ ጥያቄ መሰረት ከትምህርት ባለሙያዎቹ መረጃ ተሰብስቧል። የውይይቱ ዓላማም መልመጃዎቹ በምንባቦቹ አማካይነት የተላለፉትን እውቀቶች ጐልተው እንዲወጡና ተማሪዎች ዘንድ እንዲደርሱ በማድረግ በኩል የተጫወቱትን ሚና ማየት ነው። በመፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተደራጁት መልመጃ 1፣ 2 እና 3 በሚል ነው። በመልመጃ አንድ ስር ህፃናት በማስተዋል ማንበብን/ ማዳመጥን፣ መልመጃ 2 ከቃላት፣ ሓረጋትና ዓረፍተነገሮች ምስረታ ጋር የተያያዘ እውቀት የሚገበዩበት ነው። 3ኛው ደግሞ

በክፍል ውስጥ ያገኙት እውቀት ከቀዳሚ እውቀታቸው ጋር በማዋሃድ፣ ማህበረሰቡ ከሚኖርበት እውናዊ ዓለም ጋር ምን ያህል እንደሚዛመድ በማየት፣ ወይም በክፍል ውስጥ ያልተሞላ ክፍተት ህብረተሰቡን በማነጋገር በመመልከት እውቀታቸውን የሚያሟሉበት ነው። ከመረጃ አቀባዮቹ ጋር የተካሄደው ውይይት ያተኰረው አበእን ለማዳበር እንደሚችሉ በታመነባቸው ምንባቦችና የመልመጃ 3 ጥያቄዎች ላይ ብቻ ነው። መልመጃዎቹ በመማሪያ መፅሓፎቹ ውስጥ እንዴት እንደቀረቡና መምህራን ምንባቦቹንም ሆነ መልመጃዎቹን የሚያቀርቡበት የተለየ ዘዴ ካለ ለማየት የሚያስችል ነው።

በመጀመሪያ የቀረበው ከመምህራን በቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው።

> *አቀራረቡ እንደመምህራኑ ፍላጎትና ችሎታ ይለያያል። ለምሳሌ እኔ እቤት አንብበው እንዲመጡ፣ ያነበቡትን ለጓደኞቻቸው ቆመው እንዲናገሩ፣ አንድ ወይም ሁለት ተማሪዎች ደግሞ ተረቱን አሳጥረው እንዲያቀርቡ፣ በመጨረሻም እኔ ሳቢ በሆነ መንገድ ሳነብላቸው በፅሞና እንዲያደምጡ በማድረግ አቀርበዋለሁ።* (ቃመ.መም. 1.6፣ 22-12-2004 ዓ.ም.)

በመምህር የተሰጠው ሃሳብ ምንባቦቹን የሚያቀርቡበት ዘዴ ምን ያህል ግላዊ እንደሆነ ሲያመለክት በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን እውቀቶች የሚያስተምሩበት ዘዴ ግን አይጠቁምም፡፡ ስለሆነም አቀራረቡን የተመለከተ ምላሽ የሰጡ ሌሎች መምህራንም የተለያየ አስተያየት ነው ያላቸው። **አራት** መምህራን መማሪያ መፅሓፉ ውስጥ የተጠቀሰውን የአቀራረብ ዘዴ ተከትለው እንደሚያቀርቡ ሲገልፁ **ሁለቱ** ግን ጥሩ መስሎ የተሰማቸውን መንገድ ተጠቅመው እንደሚያቀርቡት ይገልፃሉ። ሌሎች **ሁለት** መምህራን ምንባቡን ራሳቸው ያነቡና ተማሪዎች ያደመጡትን በቃል እንዲናገሩ፣ **ሶስት** መምህራን ደግሞ ተማሪዎች እቤት አንብበው በመምጣት ያነበቡትን በቃል ለክፍሉ አባላት እንዲናገሩ በማድረግ ያቀርቡታል።

መልመጃዎችን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄም እያንዳንዱን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ ተግባራትና ክንውኖች አበእን ያስተምራሉ ብለው አያምኑም። ምክንያታቸውንም እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፣

> *መልመጃዎቹ ያተኩሩት በቋንቋ መዋቅርና በአንብቦ መረዳት ላይ እንጂ በተረቱ ይዘትና ሊተላለፍ በተፈለገው አገራዊ እውቀት ላይ ባለመሆኑ በመፃሕፍቱ ውስጥ የሌለን አበእ ለማስተማር አልሞከርም። አበእን የሚያዳብሩ ጥያቄዎች መኖራቸው ጠቃሚ ቢሆንም መፃሕፍቱ የሚያተኩሩት በቃላት ፍቺ፣ ዓረፍተነገር*

*ምስረታና ማስተዋል ጥያቄዎች ላይ ብቻ ነው። እኔም በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ ስላልነበረኝ የተለየ ጥረት አላደርግም ነበር።* (ቃ.መ.መም. 2.7፣ 22-12-2004 ዓ.ም.)

በተኰር የቡድን ውይይት የተሳተፉት መምህራንም ሁሉም ምንባቦች በመምህራን እንደሚነበቡ ተናግረዋል። ምክንያቱን ሲያስረዱም፡-

- *የህፃናቱ (4ኛ ክፍል የደረሱትም) የማንበብ ችሎታ በጣም ደካማ በመሆኑ የቀረበውን ምንባብ በአንድ ቀርቶ በሁለት ክፍለ ጊዜያት አንብበው ስለማይጨርሱት፣*
- *ሌሎቹን መልመጃዎች ለማሰራት የጊዜ እጥረት ስለሚያጋጥም፣*
- *በጊዜ እጥረት ምክንያት የአመቱን ይዘት ማጠቃለል ስለማይቻል፣* (ተቡው. 13-12-2004 ዓ.ም.) የሚሉ ነጥቦች ይዘረዝራሉ።

ያም ሆኖ፣ በሁሉም መምህራን የተንፀባረቀው አቀራረብ በመምህር የሚመራ እንጂ በቡድንም ሆነ ከቤተሰብ ጋር በሚደረግ ውይይት የማይደገፍ መሆኑ መገንዘብ ተችሏል። በምንባቦቹ ሊተላለፉ በተፈለጉት እውቀቶች ላይ የሚካሄድ ውይይት የለም። ምንባቡንም ሆነ መልመጃዎቹን ከተማሪው ቀዳሚ እውቀት እያያዙ ለመቅረብም የተደረገ ጥረት አልታየም።

ከዚህ አኳያ በተረቱ ወይም በእንቆቅልሹ ሊተላለፍ የተፈለገውን እውቀት ለማስተማር መምህራን የሚያደርጉት ዝግጅት እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህም ሌላ ግላዊ የትምህርቱ አቀራረብ የሚከተሉት ወጥ የማስተማር ዘዴ ሳይኖር የሚቀርብ ትምህርት አበእን ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ክሂሎቹንና እውቀቶቹን ለማስተማርም ጠቀሜታ አይኖረውም።

በቡድኑ አባላት የተሰጠው ምላሽ፣ ቋንቋን ከማስተማር አኳያ ሊፈቱ የሚገባቸው ችግሮች እንዳሉ በግልፅ ይታያል። ከክፍለጊዜ እጥረት ወጣ ያሉና የትምህርት ባለሙያዎችንና የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆችን ሊያሳስቡ የሚገባ ከመምህራን ስልጠና እና ከመምህር መምሪያ አዘገጃጀት ጋር የተያያዙ ሁለት መሰረታዊ ችግሮችን ማንሳታቸው ይታወሳል። ይኸውም የመምህር መምሪያው አበእን የሚያስተምሩ ይዘቶችን አለመያዙና ጥቂት ምንባቦች ቢኖሩም መምህራኑ እንዴት ሊያቀርቧቸው እንደሚገባ ስለማያመለክት አጋዥ ሆኖ አለመገኘቱ፣ እና መምህራኑም ግንዛቤው ስለሌላቸው አሻሽለው ሊያቀርቡት አለመቻላቸው ነው። ቀደም ሲል በዝርዝር የቀረበውና ከመምህር መምሪያ የተገኘው

መረጃም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቀረቡት ዝርዝር ዓላማዎች በአበእ ላይ ያተኮሩ እንዳልሆኑ ታይቷል። መምህሩም ያልተነደፈ ዓላማ እግብ ለማድረስ ወደክፍል ይገባል ተብሎ አይጠበቅም። የማስተማር ዘዴውም የአላማ ማስፈፀሚያ እንደመሆኑ አበእ ማስተማር የሚቻልበትን ዘዴ ሊጠቁም አይችልም።

በመፃሕፍቱ ውስጥ በተግባር ባይታይም የስርዓተትምህርት ባለሙያው ሃሳብ በተለይ የመልመጃ ሶስት ዓላማው ተማሪዎች በክፍል የተማሩትን ነገር ከአካባቢያቸው ጋር እንዲያገናዝቡት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን እውነታ እንዲያዩና እውቀቱን ወደተግባር እንዲያሳድጉት ማለማመድ እንደሆነ ጠቁመዋል። እንዲሁም አበእን በስርዓተትምህርት ውስጥ ማካተት ማንነትን ከማስተዋወቅና ከማጠናከር፣ እንዲሁም ቋንቋውን ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ያምናሉ። የመስኩ ምሁራንም (Ossai, 2010) የባለሙያውን እምነት የሚያጠናክር ሃሳብ አላቸው። አንድ ህብረተሰብ ከቃላዊ ተግባቦት ቀጥሎ እውቀቱን ለትውልድ ከሚያስተላልፍባቸው መሳሪያዎች ዋነኛው የአገር በቀል ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሓፍ ነው። መፅሓፉ በትውልዶች መካከል መቀባበል እንዲኖር ያደርጋል። በመማሪያ መፅሓፍ አማካይነት የሚካሄድ ቅብብል እውቀቱ **ትኩረት** እንዲያገኝ፣ **ጠቀሜታው** እንዲታይ፣ **በፅሑፍ** ላይ እንዲውል፣ ሁሉም ሰው **እንዲያውቀውና** (dissemination) ተተኪው ትውልድ **እንዲወርሰው** በማድረግ ሰፊ ግልጋሎት ያበረክታል። በመማረየ መፅሓፍ አማካይነት የሚደረገው ቅብብል የትምህርት ይዘት ምጠና እና ድረጃንም ያሟላል።

በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት ምንባቦች አብዛኞቹ ሃገር በቀል እውቀትን የሚያስተምሩ እንዳልሆኑ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ከዚህ አልፎ Semali and Stambach (1993) እንደጠቀሱት የተማሪዎቹን ባህል ዝቅ የሚያደርግ ይዘት መቅረብ እንደሌለበት ቢታወቅም በ2ኛ ክፍል መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ሁለት ምንባቦች የህብረሰቡን እውቀት የሚያንኳስሱ ይመስላል። የወላጆቻቸውንና የአያቶቻቸውን የአስተራረስ ዘዴ ሁዋላቀርነት እንዲያብራሩ የሚጠይቅ መልመጃ ቀርቦላቸዋል። ይህ ደግሞ ልጅ የመጣበትን ህብረተሰብ እንዲንቅ፣ ህብረተሰቡ በስርዓተ ትምህርቱ ላይ አመኔታ እንዲያጣ፣ ምክንያት ይሆናል። እንደምንባቦቹ ሁሉ በአራቱም መፃሕፍት ውስጥ አበእ ላይ ያተኮሩ መልመጃዎችን ለይቶ ለማውጣት በተደረገው ፍተሻ ጥቂት ጥያቄዎች ተገኝተዋል። በሁለተኛ ክፍል- 3፣ በሶስተኛ ክፍል-1፣ በአራተኛ ክፍል- 1፣ በድምሩ አምስት ጥያቄዎች ተለይተዋል።

ለ2ኛ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች፡-

- *የምንባቡን መልእክት ክፍል ውስጥ ተወያዩበት።* (ገፅ 13)
- *ተስማምቶ መኖር ምን ጠቀሜታ እንዳለው ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት።* (ገፅ 84)
- *የቀረበው ምንባብ ስለምን እንደሚተርክ አንድ በአንድ እየተነሳችሁ ሃሳባችሁን ግለፁ።* (ገፅ 106)

የመጀመሪያው ጥያቄ፣ ምንባቡ ስለክህደትና በጥቅም ተገዝቶ ወገንን የመጉዳት መጥፎነት እንደሚያስተምር እንዲናገሩና በተላለፈው እውቀት ላይ እንዲወያዩ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይዘቱ በመምህር መምሪያም ሆነ በመርሃትምህርቱ ውስጥ የዓላማ ግብ ሆኖ አልቀረበም። እንዴት መቅረብ እንዳለበትም አልተጠቈመም። መረጃ አቀባይ መምህራኑም እንደጠቀሱት በዚህ ሃሳብ ላይ አትኩረው ውይይቱን እንዲመሩ የሚጠቁም ፍንጭ ስላላገኙ አቀራረቡ ግላዊ ነው የሆነው። ሁለተኛው ጥያቄ በምንባቡ ሊተላለፍ ከተፈለለገው እውቀት ውጪ ነው። ምንባቡ የቤተሰብ/ የአንዲት ሃገር ህዝቦች መጣላት ለጠላት በር መክፈትና እራስን ማስጠቃት እንደሆነ ነው የሚገልፀው። ውይይቱ ማተኮር የነበረበትም በዚህ ላይ ነው።

ሶስተኛው ጥያቄ በቁሙ ሲታይ ተማሪዎች ያነበቡትን ፅሑፍ ይዘት ምን ያህል መረዳት እንደቻሉ ለማወቅ የሚቀርብ ተገቢ ጥያቄ ነው። እንዲገልፁት የተፈለገው ምንባብ ሲታይ ግን (እንዲህ አይነት ጥያቄ ሌላ አካባቢ ካለመከሰቱ ጋር ተያይዞ) ልጆቹ በማንነታቸው እንዲያፍሩ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ያስመስለዋል። ምንባቡ 'ግብርና' የሚል ርእስ ኖሮት ዋና ዋና ጭብጦቹ፡- በሃገራችን የእርሻ ስራ ኋላ ቀር መሆኑ፣ እንስሳት እንክብካቤ እንደማይደረግላቸው፣ ተጋሩ ኋላ ቀርና ያልተሻሻለ መሳሪያ እንደሚጠቀሙና ጥንታዊውን አስተራረስ እንዲተዉ ተማሪዎቹ ወላጆቻቸውን እንዲያስተምሩና እንዲያሰለጥኑ፣ በትራክተር ማረስ ጠቀሜታ እንዳለው ሊያስገነዝቧቸው እንደሚገባ የሚያሳስቡ ናቸው። ጥያቄው የቀረበውም ሁሉም ተማሪ እየተነሳ ይህንን ጭብጥ እንዲናገር ነው። ከልምምድ በኋላ የሚገኘው ውጤት ጠቀሜታው ምን ሊሆን እንደሚችል ግን አልታሰበበትም።

ለሶስተኛ ክፍል የቀረበና በአበእ ላይ አትኩረው እንዲነጋገሩ የሚያደርግ *"ከቀረበው ታሪክ ምን ትምህርት አገኛችሁ?"* (ገፅ 7) የሚል ጥያቄ እናገኛለን። ይህ ጥያቄ በምንባቡ ሊተላለፍ በተፈለገው መልእክት ላይ እንዲወያዩ የሚያስችል ነው። ሆኖም ተማሪዎቹ

የመሰላቸውን እንዲናገሩና በዚያ አጋጣሚ ሊተላለፍ ስለተፈለገው እውቀትም ይነጋገሩ እንደሆነ እንጂ በታቀደ መልክ የቀረበ ጥያቄ ስላልሆነ ወደተፈለገው ግብ የሚመራ አይደለም። ስለዚህ እንደምንባቡ ሁሉ በግል ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ አስተያየት ሊያሰጥ ይችላል። ለአራተኛ ክፍል የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች፤ ማንኛውንም ምንባብ ካነበቡ በኋላ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት እንጂ በተለይ አበ እውቀቱን ለይተው እንዲናገሩ ወይም ለመገንዘብ ጥረት እንዲያደርጉ የሚያለማምድ ሆኖ አልተገኘም። *"የምንባቡ መልእክት ምንድነው? ክፍል ውስጥ ተወያዩበት"* (ገፅ 73) ይላል። ይህ ጥያቄ ተማሪዎች ያነበቡት ሰፊ ፅሑፍ ጭምቅ ሃሳብ ወይም አሳጥሮ የማቅረብ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ልምምድ ነው። ህብረተሰቡ ግን ስነቃልን በማስተማሪያነት ሲጠቀም ለየት ያለ የአቀራረብ ዘዴ ይከተላል። ለምሳሌ የሚከተለውን ተረትና ምሳሌ እንይ፡-

> *"ካብ ሃገራ እትበልፅ ምሽላ ወይ ንጓፍ ወይ ንእምኒ ዋንጭፍ" (በማሽላ ማሳ ላቅ ብላ የምትታይ የማሽላ ራስ አንድም በወፍ አሊያም በወንጭፍ ድንጋይ ትጠቃለች)*
> (ቃመ.ማ 14፣ 19-07-2004 ዓ.ም.)

ይህ ተረትና ምሳሌ በቁሙ ሲፈታ ልቆ መታየት አያስፈልግም የሚል ይመስላል። ሚስጥሩ ሲፈታ ግን አንዲት የማሽላ አገዳ ግለሰብን፣ ማሳው ደግሞ ህብረተሰብን የሚወክል ሆኖ ከማህበረሰቡ የሚያፈነግጥ፣ የማህበረሰቡን ህግና ደንብ የማያከብርና ራሱን ለህብረተሰቡ የማያስገዛ ሰው በተለያዩ መንገዶች መጠቃቱ የማይቀር መሆኑን ነው የሚያመለክተው። ይህ ለህፃናቱ አዲስ እውቀት ሊሆን ይችላል። ትምህርቱ የተላለፈው የእለት ተእለት መገልገያ በሆኑና ከሱ ጋር ባሉ ቁሶች (ወፍ፣ ወንጭፍ፣ ድንጋይ፣ ማሽላ) አማካይነት ነው። ተማሪዎች በቃለቱ ዓረፍተነገር ሲመሰርቱ፣ ፍቺ ሲሰጡ፣ ምንነታቸውን ለማወቅ ከወላጆቻቸው ጋር ሲነጋገሩ የስነልሳን እውቀቱና ክሂሎቹም ይዳብራሉ። ጥናቱ አበእን ለማስተማር የግንባታዊ አስተሳሰብ ሞዴልን የተከተለበት ምክንያት የዚዓይነቶቹን የአቀራረብ ችግሮች ስለሚፈታ ነው። ለምሳሌ የሚከተለውን አብነት እንመልከት።

አንድ አባት የመተባበርን አስፈላጊነት ለልጆቻቸው ለማስተማር አንድ ተረት ነገሯቸው። በተናጠል ሰባት በትሮችን ፣ እና አንድላይ የታሰሩ ሰባት በትሮችን እንዲሰብሩ በመጠየቅ ልዩነቱን አሳዩአቸው፤ ህብረት ሃይል እንደሆነ አስተማሯቸው። ህፃኑ ይህንን ተረት እቤት እያለ የሚያውቀው ከሆነ መልሶ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲያገኘው አሰልቺ አይሆንበትም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

ይህ ይዘት አሰልቺ እንደማይሆን የሚታወቀው ተረቱ የቀረበበት ዓላማ ሲታይ ነው። ዓላማው የህብረትን ምንነትና አስፈላጊነት ማወቅ፣ አዳዲስ ቃላትን መለየት፣ በአዳዲስ ቃላት ዓረፍተነገር መመስረት፣ ሌሎች የህብረትን ጠቀሜታ ወይም የመነጣጠልን ጉዳት የሚያስተምሩ ተረቶችን፣ ምሳሌዎችን፣ ወዘተ. መሰብሰብ ሊሆን ይችላል። 'ህብረት' የሚለው ቃል የተደገመ ነው። ነገር ግን ህብረቱ ከወንድማማቾች ወደ ቤተሰብ፣ ወደ ጐረቤቶች፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ወዘተ. ህዝብ ህብረት በማስፋት ምን ምን ጠቀሜታ ማግኘት እንደሚቻል ሲገነዘቡ የቃል ፍቺ ስፋት ይማራሉ። ይህ አዲስ እውቀት በቀጣይ ለሚማሩት የፅሕፈት ልምምድ፣ ቃላት በአውድ ለሚያሳዩት የፍቺ ልዩነት፣ ለሰዋስው ትምህርት መነሻ ሆኖ ያገለግላል።

በጥናቱ ውስጥ የቀረበው ሞዴል አበእን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹን የቋንቋ ኣላባዎች ለማስተማር በመሳሪያነት እንደሚያገለግል ከቀረበው ምሳሌ መረዳት ይቻላል። የግንባታውያን አተያይሰ የሚያንፀባርቀውን ሞዴል ተከትሎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መፃሕፍትን የማዘጋጀት ጠቀሜታ መታየት ያለበትም በመነሻ እውቀት፣ በተደረሰበትና ቀጣይ በሆነው እውቀት መካከል ትስስርና ቀጣይነት ሲኖር መማርን ተጨባጭና ቀልጣፋ የሚያደርግ ከመሆኑ አኳያ ነው።

## 4.6. የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ፡- ከቃለመጠይቅ፣ ከተኰር የቡድን ውይይት፣ ከሰነዶች ፍተሻና ከመማሪያ መፃሕፍት የተሰበሰቡ መረጃዎች ከተለያዩ ልሂቃን ከተገኙ ንድፈሃሳቦች ጋር እየተጣቀሱ ቀርበዋል። መረጃዎቹ በውይይት ወቅት በመረጃ አቀባዮች ተደጋግመው በተነሱና ከሰነዶች በተገኙ መሪ ይዘቶችና የጥናት ጥያቄዎች ስር በርእስና ንኡስ ርእስ ተከፋፍለው ቀርበዋል። በውይይት ወቅት የተነሱ ስምምነቶችና ልዩነቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው ትንተና እና ትርጐማ ተካሂዶባቸዋል። የጥናቱን ተአማኒነት ከፍ ለማድረግ ሲባል መረጃ አቀባዮች በውይይት ጊዜ ያነሷቸው ቁልፍ መረጃዎች ቃል በቃል ተጠቅሰው በመረጃነት ቀርበዋል።

በሃገር ደረጃ በተዘጋጁትና ክልሎችም በመነሻነት በሚገለገሉባቸው ትምህርት ነክ እቅዶች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ሁሉም ይማር ለሚለውና ለሚማርበት ቦታ እንጂ ለሚማረው ይዘት እንዳልሆነ መረዳት ተችሏል። የስርዓተትምህርት አዘጋጆችም ምርጥ ዓለም አቀፍ ልምዶችን ብቻ እንጂ የህብረተሰቡን ምርጥ ልምድ በመነሻነት ተጠቅመው መፃሕፍቱን

እንደማያደራጁ መረጃዎች አሳይተዋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአገር በቀል ቋንቋውና ስርዓተትምህርቱ ምን ድክመት እንዳለበት አይቶ በማሻሻልና ለመምህራን ተገቢ ስልጠና በመስጠት የትምህርት ጥራት ሊመጣ እንደሚችል ያለማመን ችግር ታይቷል። በማስተማሪያነትና በትምህርትነት እያገለገለ ያለው ቋንቋና የቋንቋው መምህር ግን ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ከተለያዩ ምንጮች የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይ በገጠሩ አካባቢ ያሉ ተማሪዎች በብዛት ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ የተማሪዎቹ ቀዳሚ እውቀት (አበእ) መነሻ ሆኖ አለማገልገሉ እንደሆነም ከቀረቡት ሰነዶች መረዳት ተችሏል።

በዚህ ምዕራፍ የታየ ሌላ ግኝት፡- ትግራዋይ ህብረተሰብ፤ በእለት ተእለት እንቅስቃሴው ውስጥ የሚያሳያቸውና የሚገልፃቸው እውቀቶች አሉት። እነዚህን እውቀቶች ወደቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍም ይፈልጋል። ቋንቋውን ለማስተማር የተዘጋጁት መፃሕፍት ግን የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ይዘት ማቅረብ እንዳልቻሉ መረዳት ተችሏል። ሌላው አበእ በስርዓተትምህርት ውስጥ እንዳይካተት ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት አዘጋጆቹ፤ የአበእ ምንነት፣ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ስለሚኖረው ጠቀሜታና ሊካተት ስለሚችልበት ዘዴ ግንዛቤ አለመኖር መሆኑ ታውቋል። እውቀት ከሰዎች ልምድ ሊቀሰም ይችላል። የተለያዩ ሰዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ የሚያደርጉ ምንባቦች የቀረቡበት ምክንያትም እውቀት ከታላላቆች ልምድና ከተለያዩ የእውቀት ምንጮች ማግኘት እንደሚቻል ለማሳየት ነው። ሆኖም ልምዳቸውን ያቀረቡት ሰዎች ማንነት ሲታይ እውቀት ማግኘት የሚቻለው "ዘመናዊ ትምህርት" ከቀሰሙ ሰዎች ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ተገኝቷል። አበእ የሚተላለፈው በቃል መሆኑ ተገንዝቦ ልምድ፣ ታሪክ ወይም ተረት ነጋሪ የእድሜ ባለፀጋዎችን ተመክሮ በማስተማሪያነት ያለመጠቀም ችግርም ተስተውሏል።

በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ካሉት ምንባቦች አስሩ የህብርተሰቡን እውቀት ማንፀባረቅ የሚችሉ ቢሆንም ታስቦባቸው የተመረጡ ስላልሆኑ እውቀቶቹ በመልመጃዎች ተደግፈው ወደ ተማሪዎች እንዲተላለፉ አልተደረገም። ሁለት ምንባቦች ደግሞ የህብረተሰቡን እውቀት የሚነቅፉና የሚያንኳስሱ ሆነው ተገኝተዋል። ከዚህ አልፎ በመርሃትምህርትም ሆነ በመምህር መምሪያዎቹ አበእን ለማስተዋወቅ የቀረቡ ዓላማዎች እንደሌሉ ተስተውሏል። ከዚህ በመነሳት ህብረተሰቡ በመፃሕፍቱ ውስጥ ያሉትን እውቀቶች የኔ ናቸው ሊላቸው

እንደማይችል መረዳት ተችሏል። አበእን ማስተማር ይችላሉ የተባሉትም ሆኑ ሌሎች ምንባቦች ወደተማሪው ሲቀርቡ አንድ ወጥ የሆነ የሚመሩበት ወይም የሚከተሉት ዘዴ እንደሌለና መምህራኑ ባመኑበትና በየግላቸው ጥሩ በመሰላቸው መንገድ እንደሚያቀርቡት መረዳት ተችሏል። የዚህ አይነቱ አቀራረብ ደግሞ ለአገር በቀል ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላዩ የቋንቋ ትምህርትም ፋይዳ እንደሌለው መረዳት ይቻላል።

# ምዕራፍ ኣምስት

## ማጠቃለያና ጠቋሚ አስተያየቶች

### 5.1. የጥናቱ አቀራረብ ሂደት

የተካሄደው ጥናት በትግራይ ክልል የትግርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ህፃናት ከቤት ይዘውት የሚመጡት አበእ በተዘጋጁላቸው የትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ መነሻ ሆነው ማገልገል መቻላቸውን የማየት ዓላማ አለው። ህፃናት አፍ በፈቱበት ቋንቋ ስለተማሩ ብቻ አበእ ተምረዋል ብሎ መደምደም ያስቸግራል። ምክያቱም አበእን ለማስተማር ከመርሃትምህርት ዝግጅት ጀምሮ ታስቦበት ካልታቀደ ስለፈለጉት ብቻ የሚማሩት ወይም የሚያስተምሩት ስላልሆነ ነው። ስለሆነም በጥናቱ አበእን ለማስተማር ምንያህል እንደታቀደ፣ በተለያዩ የትምህርት እቅድ ሰነዶችና ስርዓተትምህርቶች ውስጥ እንዴትና በምን ያህል እንደተካተተ ለማየት ፍተሻ ተካሂዷል። ፍተሻው ቀጥሎ ለቀረቡት የጥናት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ የማስገኘት ዓላማ ነበረው።

ጥናቱ፣ በትግራይ ክልል የሚገኘው የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህብረተሰብ አገር በቀል ውቀት፣ በክልሉ በሚዘጋጀው የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የትግርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት (መርሃትምህርት፣ የተማሪ መፅሃፍና የመምህር መምሪያ) ውስጥ ተካቷል ወይ? የሚል ዓብይ የጥናት ጥያቄ፣ እንዲሁም ከዓብዩ ጥያቄ ለመነጩና

- በስርዓተትምህርቱ ውስጥ አገር በቀል እውቀትን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎች ቀርበዋል?
- ትግራዋይ ህብረተሰብ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች አገር በቀል ናቸው ብሎ ያምናል?
- ለመለማመጃነት የቀረቡት ተግባራትና ክንውኖች (መልመጃዎች፣ የቡድንና የጋራ የፕሮጀክት ስራዎች) የቀረቡት አገር በቀል እውቀትን ማዳበር በሚያስችል መንገድ ነው?

ለሚሉት ሶስት ዝርዝር የጥናት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ያለመ ነበር። ስለሆነም ትግራዋይ ህብረተሰብ ወደ ቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ አለበት የሚለው አበእ ያለው መሆኑና በመፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት እውቀቶች የህብረተሰቡ እውቀቶች መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በክልሉ ሶስት ዞኖች ከሚገኙ የእድሜ ባለፀጋዎች በቃለመጠይቅና በተኮር የቡድን ውይይት አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበዋል።

እንዲሁም በስርዓተትምህርቱ ውስጥ አበእን የሚያስተምሩ ይዘቶች ስለመካተታቸው ለማረጋገጥ ከመምህራን በቃለመጠይቅና በተኮር የቡድን ውይይት አማካይነት መረጃ ተሰብስቧል። ከስርዓተትምህርት ባለሙያም በቃለመጠይቅ አማካይነት የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል። እንዲሁም በስርዓተትምህርቱና በሌሎች የትምህርት እቅድ ሰነዶች ውስጥ አበእን የሚያስተምሩ ይዘቶች መካተት አለመካተታቸውን ለማረጋገጥ የይዘት ፍተሻ ተካሂዷል። ከተካሄደው የመረጃ ስብሰባ፣ ትርጉማና ትንተናም የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተገኝተዋል

## 5.2. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

**በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የአበእ መካተት አስፈላጊነት፡-** በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት መፃሕፍት በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለሚገኙ ህፃናት የተዘጋጁ ናቸው። ህፃናቱ ከለመዱት ቤታቸው ወደ አዲስ ዓለም (ትምህርት ቤት) የመጡ ናቸው። ይዘውት የሚመጡት እውቀትም ከሚኖሩበት መንደር፣ ሰፈርና እዚያው ካለው ህብረተሰብ የተገኘና ከዚያ ያልራቀ ነው። ትምህርት ቤት ከሚባለው ዓለም የሚያገኙት እውቀትም ይዘውት ከመጡት እውቀት ብዙም ያልተለየና ቀዳሚውን እውቀት መነሻው ማድረግ እንዳለበት ይታመናል። ይህም፤ እውቀት የሚገነባው ባለው ግብአት ላይ አንድ አዲስ ነገር በመጨመር ሳይሆን ቀድሞ ከሚያውቀው አገር በቀል ከሆነው ጋር የሚመሳሰል አዲስ እውቀት በመጨመር መሆኑን ያመለክታል።

ከመረጃ አቀባዮች የተገኙት መረጃዎች የሚያረጋግጡትም ህፃናት ይበልጥ የሚማሩት በሚያውቁት ነገር መነሻነት አዲስ እውቀት ሲቀርብላቸው ነው። በሚየውቋቸው ቁሶች አማካይነት ፊደላትን ንግግርን፣ ንባብን ማስተማር እንደሚቻል መረዳት ተችሏል። ህፃናቱ እቤት እያሉ የተለያዩ መገልገያ መሳሪያዎችን ከነስማቸው ያውቃሉ። እያንዳንዱ ፊደል ምን እንደሚመስልና ለምን እንደሚያገለግል ግን አያውቁም። ቁሶቹን ከፊደሎቹ ቅርፅ ጋር በማመሳሰል፣ ወይም የቁሶቹ ስያሜዎች በምን ፊደላት እንደተገነቡ በማሳየት ፊደልን እንዲለዩ፣ ንባብና ፅሕፈትን እንዲለማመዱ በመሳሪያነት ሊያገለግል እንደሚችል መገንዘብ ተችሏል።

የሚያውቁትን እንስሳ፣ አካባቢ፣ የእህል አይነት፣ የነገሮች አሰራር እንዲገልፁ ሲደረግ የንግግር ክሂላቸውን ያዳብራሉ። እቤት እያሉ የሰሟቸው ተረቶች በንባብ መልክ ሲቀርቡላቸው የበለጠ ለመማር እንደሚነሳሱና አዝናኝ በመሆናቸው እየተማሩ መሆናቸውን

ሳይገነዘቡ ኣዲሱን እውቀት ለመማር እንደሚያስችላቸው ታውቋል። ህፃናቱ፣ ቀደም ሲል የሚያውቁትን ሃሳብ ለመግለፅ ሲሉ ቋንቋውን ይጠቀማሉ። ሃሳባቸውን ኣደራጅተው ለሌሎች ለማስረዳት ሲለማመዱ የንግግር ክሂላቸውን ያዳብራሉ። በውስጣቸው የሚያውቁ/የሚችሉ መሆኑ ሲሰማቸው ይበልጥ ኣዳዲስ እውቀቶችንና ክሂሎችን ለማወቅ ይነሳሳሉ። ኣበእ በመፃሕፍቱ ውስጥ መካተት ያለበትም ተማሪውን የበለጠ እንዲማር ስለሚያነሳሳ መሆኑ መገንዘብ ተችሏል።

የቋንቋ ትምህርት ኣጠቃላይ ዓላማ፣ በቋንቋው ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መፃፍ እንዲሁም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓትና ሥነጽሑፍ ኣውቆ መገልገል መቻል ነው። ትግራዋይ ህፃን በኣካባቢው ስለሚገኙ እንስሳት፣ እፀዋት፣ ኣዝርእት፣ የስራ ዓይነትና የስራ መሳሪያዎች መናገርና ሲነገር ማዳመጥ ይችላል። እንዲማር የቀረበለት ኣዲሱ እውቀት **በዓላማ መናገርና ማዳመጥ** የሚል ቢሆን ከላይ ስለተጠቀሱት ተግባራት ወይም የተለመደ ተረት እያደመጠ ወይም እየተናገረ በዓላማ ማዳመጥ ምን እንደሆነ ሊማር ይችላል። በሚናገረውና በሚያደምጠው ተረት ወይም ታሪክ ውስጥ ያሉትን ፊደሎች ማስለየት ኣዲስ እውቀት ነው። ፊደሎቹ እቤት እያለ ከሚያውቃቸው ምስሎችና ቁሶች እየተዛመዱ ሲቀርቡ በቀላሉ ይለያቸዋል። ኣገር በቀሉ እውቀት ኣዲሱን ለማስተማር ኣጋዥ መሳሪያ ሆኖ ይቆማል። በኣጠቃላይ ኣበእ በየክፍል ደረጃው ማካተት  ኣዲስ እውቀት ለመማር፣ ቋንቋውን ለመቻል፣ በቋንቋው ለመገልገልና ከማህበረሰቡ ጋር ኣብሮ ለመኖር ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር መሆኑ መገንዘብ ተችሏል።

**ኣገራዊና ክልላዊ በሆኑት የትምህርት እቅድ ሰነዶች ውስጥ ኣበእ ትኩረት ስለማግኘቱ**

በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተዘጋጁት የትምህርት እቅዶች እንደሌሎቹ ሴክተር ቢሮዎች ሁሉ የምእተዓመቱን የልማት ግቦች የማሳካት ዓላማ ኣላቸው። በእቅዱ ውስጥ በተለይ በኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ዋነኛ ትኩረት ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ወይም ቅበላ፣ ተሳትፎ እና ተደራሽነት ናቸው (ገኢ.ልሚ፣ 2003 ዓ.ም.)። በትግራይ ክልል የተዘጋጀው እቅድም በጥቅል ተሳትፎ ላይ ያተኰረ ነው። ጥቅል ተሳትፎ ደግሞ በየዓመቱ ምን ያህል ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንደመጡ ብቻ ነው የሚያመለክተው። ከዚህ ኣልፎ ህፃኑ ምን እውቀትና ክህሎት ተምሮ ምን ለውጥ እንዳሳየ ኣያመለክትም። በሌላ በኩል እቅዶቹ የተማሪ ህፃናት ቁጥር ቢጨምርም ውጤታቸው ግን እየቀነሰ መሆኑ ያሳያሉ። ለተማሪዎች ውጤት ዝቅ እያለ ለመምጣቱ ስርዓተትምህርቱ የሚነደፈው የየኣካባቢው

ህብረተሰብ ተሞክሮ እና ፍላጎት ሳያገናዝብና የዓለም ዓቀፍ ተሞክሮን ብቻ ሞዴል ማድረጉ በምክንያትነት ሊወሰድ ይችላል።

የቋንቋ ትምህርት የዓውድ ትምህርት ነው ማለት ይቻላል። እያንዳንዱ ቃል፣ ሓረግም ሆነ ዓረፍተነገር ከገባበት ዓውድ አኳያ የፍቺ ለውጥ ሊያሳይ ይችላል። አንድ ኢትዮጵያዊ/ ትግራዋይ ህፃን የሚኖርበትን ዓውድና ቀዳሚ እውቀት ያላገናዘበ በምዕራባውያን ተሞክሮ የተቃኘ ስርዓተትምህርት አበእን ብቻ ሳይሆን ቋንቋውን በአግባቡ አስተምሮ ለውጥ ሊያስገኝ አይችልም። በትግራይ ክልል የተዘጋጀውና በተለይ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርትን የሚያመለከተው እቅድ በፌደራል ደረጃ ከተዘጋጁት እቅዶች ይበልጥ በአካባቢው ቋንቋ፣ ባህልና እውቀት ላይ ሊያተኩር እንደሚችል ቢገመትም የታየው ግን በፌደራል ደረጃ ከተዘጋጀው የማይለይና አበእ ላይ ያላተኰረ መሆኑ ነው።

**የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ስርዓተትምህርቶች ውስጥ አበእን ማስተማር ትኩረታቸው ያደረጉ ዓላማዎችና ይዘቶች ስለመካተታቸው፡-** የቋንቋ ስርዓተትምህርት ዓብይ ዓላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እና የስነልሳንና የስነፅሑፍ እውቀትን ማዳበር እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ግን እነዚህ የክሂልና የእውቀት ይዘቶች የሚቀርቡት ለማን ነው? እንዴት ቢቀርቡ ነው ተማሪው የበለጠ የሚማረው? የሚሉትን ጥያቄዎችንም መመለስ አለበት። በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ስርዓተትምህርቶች ዕድሜአቸው ከ7-10 የሆነ ህፃናት የሚማሩባቸው ናቸው። የነዚህ ህፃናት የእውቀት አድማስ ከሚኖሩበት ቀበሌና አካባቢ ብዙም አይርቅም። ስርዓተትምህርቶቹ የሚያቀርቧቸው ይዘቶችም የህፃናቱን ቀዳሚ እውቀት መነሻ አድርገው አዲስ እውቀት እንደሚጨምሩላቸው ይታመናል።

በመርሃትምህርቱ ውስጥ የተዘረዘሩት ዓላማዎች ግን አበእን የማስተማር ግብ የላቸውም። በሰንጠረዦች 6-9 ውስጥ እንደተመለከተው በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የህብረተሰቡን እውቀት የሚያስተላልፉ ጥቂት ተረቶችና እንቆቅልሽ በምንባብነት ቀርበዋል። ተረቶቹ አበእን ማስተላለፍ የሚችሉ ቢሆንም ሁሉም አንብቦ መረዳትን ከማዳበር ያለፈ ድርሻ እንዳላቸው በሚያሳይ መልክ አልቀረቡም። የቀረቡት ምንባቦ ጥቂት ቢሆኑም፣ ህፃኑን በጥሩ ስነምግባር የሚያንፁ፣ ስራ ወዳድነትን የሚያነሳሱ፣ ከህክምና ፣ ከግብርና ሙያ፣ ከፍትሕ፣ ከማህበራዊ ግንኙነት፣ ወዘተ. ጋር የተያያዙ እውቀቶችን የሚያስተምሩ ናቸው። መልመጃዎቹ ግን ተማሪዎች በእውቀቱ ላይ እንዲወያዩና ግንዛቤአቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ ፈንታ ተረቱን መልሰው እንዲተርኩና ተመሳሳይ ተረት እንዲናገሩ ነው

የሚጠይቁት። የመልመጃዎቹ በአበእ ላይ አለማተኰር ተረቶቹ አበእን ለማስተማር ታቅዶ እንዳልተመረጡ ያመለክታል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት ለ4ኛ ክፍል የቀረቡትና ከዕድሜ ባለፀጋዎች ተሞክሮ መማርን ዓላማቸው ያደረጉት ሶስት ምንባቦች ናቸው። በነዚህ ምንባቦች አማካይነት ተማሪዎች ከታላላቆቻቸው ጋር በመወያየት እውቀት እንዲቀስሙ ነው የተፈለገው። ሆኖም ሁሉም ተጋባዥ እንግዶች በ"ዘመናዊው" ትምህርት ያለፉ ብቻ መሆናቸው "ዘመናዊ ትምህርት" ያለገኙ አገር በቀል የእድሜ ባለፀጋዎች ያካበቱትን እውቀት በቃል ማስተላለፍና ማስተማር እንደሚችሉ የዘነጋ ያስመስለዋል።

የህብረተሰቡ የኑሮ መሰረት የሆነውን ግብርናን የሚገልፁት ምንባቦችም ስለህብረተሰቡ የተዛባ መልእክት ነው የሚያስተላልፉት። ትግራዋይ የሚሰደደው ምርቱን ስለማይንከባከብና ስለማይቆጥብ ነው የሚለው መደምደሚያ ሰው የተሻለ ኑሮ ለመምራት፣ ለመማር፣ ለማደግ፣ ድህነትን ለማሸነፍና በሌሎች ምክንያቶች ሊሰደድ እንደሚችል የዘነጋ ነው። እንዲሁም ምርቱን ለማዳበር ከመጀመሪያዋ የእርሻ ስራ እስከ ዘር መዝራት ድረስ የሚያካሂደውን ጥረት ያገናዘበ አይደለም። እህሉ ከበቀለበት ጊዜ ጀምሮ የሚያደርገው እንክብካቤ፣ ምርቱን ከማጨድ ጀምሮ ቤት ከገባ በኋላ እስከሚካሄደው ነቀዝን አይጥንና እርጥበትን የመከላከል ስራ ያለማወቅ ውጤት ነው። እንዲህ አይነቶቹ ምንባቦች ልጁ ትምህርት ቤት ገብቶ እውቀቱን በማዳበር ፈንታ የያዘውንም እንዲጠላ የሚያደርጉ ናቸው። አበእ የሚፈጠረውና የሚዳብረው ሰው ከተፈጥሮ እና ከፈጣሪ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ውስጥ ነው። ተፈጥሮ የሚባለው፤ የመሬት አቀማመጥ፣ የአፈር ሁኔታና የዝናብና የወንዞች ይዞታ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። በየአካባቢው የነዚህ ተፈጥሮአዊ ሃብቶች መለያየት የአሰራርና የእውቀት ልዩነት ሊያስከትል ይችላል። በምስራቅና ማእከላዊ ዞኖች የእርሻ ወቅት ከደቡቡ የተለየው በዚህ ምክንያት ነው። የደቡቡ የእርሻ መሬት ወፍራም ሲሆን የምስራቅና ማእከላዊ ግን ስስ ነው። ስለዚህ በሁለቱ ዞኖች አረምን ለማጥፋት መሬቱ በነሃሴና በመስከረም ካልታረሰ በበጋ ላይ ማረሻ ሊወጋው አይችልም። የደቡቡ ግን በበጋ ጊዜም ለማረስ የሚያስቸግር ስላልሆነ የግምሻ ስራ ጥር ላይ ሆኖ የማየም ስራ ግን በመጋቢት መግቢያ ላይ ለማካሄድ ተችሏል።

በስርዓተትምህርት ወስጥ የመምህር መምሪያ ዓላማ በአሰልጣኝ ተቋማት መለያየት፣ በሰልጣኞች ግንዛቤና በመምህራን አገላለፅ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን መሙላት ነው። አንዳንድ ፅንሰሃሳቦችን በማብራራት በመምህራን ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲኖር በማድረግም

ያግዛል። ተተኳሪው የመምህር መምሪያ ግን በምንባብ መልክ የቀረቡት ተረቶች ዓላማ ምን እንደሆነና እንዴት ሊገለገሉባቸው እንደሚችሉ እንኳ ማሳየት አልቻለም። ስለዚህ የተፈጠረውን ክፍተት መሙላት የሚችል ሆኖ አልተገኘም።

በአጠቃላይ በአገር በቀል የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የስርዓተትምህርት ዋነኛ ተግባር ህፃናት ከቤት ይዘውት እንደሚመጡ የሚገመተውን እውቀት በትምህርት ቤት ከሚሰጠው እውቀት ጋር ለማገናኘት ድልድይ ሆኖ ማገልገል ነው። በሌላ በኩል በተገኘ ቦታና ጊዜ፣ ለተገኘ ሰው ይቀርብ የነበረውን ተረት በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ጊዜ፣ ቦታና ደረጃ ተወስኖለት እየተመጠነ የሚቀርብበት ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ለአበእ ትኩረት መስጠቱ የሚታወቀውም በጣም አስፈላጊ በመሆናቸው ህብረተሰቡ ወደ ቀጣዩ ትውል መተላለፍ አለባቸው የሚላቸውን እውቀቶች ማካተቱ ሲረጋገጥ ነው። ህፃኑም ስለራሱ እየተማረ እራሱን የሚያውቅበት መሳሪያ ሆኖ ሲያገለግል ነው። ተጠኚዎቹ ስርዓተትምህርቶች ግን የተወሰኑ ተረቶችን በምንባብነት ከማስገባት የዘለለ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሆነው አልተገኙም።

**ትግራዋይ ህብረተሰብ በተጠኚዎቹ መፃሕፍት ውስጥ ያሉትን እውቀቶች የኔ ብሎ የሚቀበላቸው ስለመሆኑ፡-** የአበእ መገለጫዎች በርካታ ናቸው። የአፍ ታሪኮች፣ ተረቶች፣ መዝሙሮች፣ ከበራዎች፣ የአካባቢ ሕጎች (ሕጊ ገረብ)፣ የተለያዩ የስራ መስኮችና አሰራሮች መገለጫዎቹ ናቸው። እነዚህ መገለጫዎች በጥቅል ሲታዩ አንዱን አገር በቀል ህዝብ ከሌላው የሚለዩ አይመስሉም። ምክንያቱም የአበ ህዝቦች እውቀት በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት መገለጫዎች አማካይነት ስለሰው፣ ስለተፈጥሮና ስለፈጣሪ ነው የሚያወጉት። የተለያዩ ህዝቦች እውቀት መሆናቸው የሚታወቀው አንዱን ተረት በመምዘዝ በምን ሁኔታ (አውድ)፣ በምን ወቅት፣ ምን ለመግለፅ እንደተነገረ ሲተነተን ነው። በዚህ ትንተና አንዱ ህብረተሰብ ከሌላው በአተያይ፣ በእምነት፣ በፍልስፍና እንደሚለያይ መረዳት ይቻላል።

በአበ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ በምንባብነት የሚቀርቡ ፅሑፎች ዓላማቸው ቋንቋውን ማስተማር ነው። በምንባቦቹ ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር የሚቀርቡት ጥያቄዎች ደግሞ በምንባቦቹ የሚተላለፈውን የህብረተሰብ እውቀት ለማጉላት ያገለግላሉ። ተጠኚ በሆኑት አራቱ የክፍል ደረጃዎች ያሉት አብዛኞዎቹ ምንባቦች ግን የዚህ ሕብረተሰብ እውቀት ሊባሉ የማይችሉ ጥሬ ሳይንስና በነገራ የቀረቡ ሆነው ተገኝተዋል። መረጃ አቀባዮቹም የሚያረጋግጡት ይህንን ነው። በፍትህና ፍትሃዊነት፣ በስራ ክቡርነት፣

በማህበራዊነት፣ በክህደት፣ በሃይል መመካትና በማጭበርበር ላይ ህብረተሰቡ ያለውን እውቀት የሚያሳዩ ምንባቦች የገቡ ቢሆንም እንኳ ይዘታቸው በልዩ ልዩ መልመጃዎችና በውይይት ወደ ተማሪዎች እንዲሸጋገሩ አልተደረገም። በቅርፅ ደረጃም የተለመደው የተረት አጀማመርና አጨራረስ ስርዓትን የተከተሉ አይደሉም። በነዚህ ምክንያቶች ተቀባይነታቸው ዝቅ ይላል።

አገር በቀል የእድሜ ባለፀጋዎች በትረካ፣ በቃለምልልስና ተሞክሮ በመንገር ለዘመናት ያከማቹትን እውቀት ለተማሪው እንዲያካፍሉ ማድረግ ሌላው ማስተማሪያ ዘዴ ነው። በተተኳሪዎቹ መፃሕፍት ውስጥ የእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ቦታ ዘመናዊ ትምህርት በቀሰሙ ሰዎች ተይዟል። በ'ምሁራኑ' የተላለፉት መልእክቶችም ህብረተሰቡ መሃል ገብቶ ለመኖር በሚያስችሉ እውቀቶች፣ ክሂሎች፣ ማህበራዊነት ወይም መልካም ስብእና ላይ ያተኮሩ ስላልሆኑ አገር በቀሉ ህዝብ 'የኔ' እንደማይላቸው መረዳት ይቻላል። በተለይ ከተረት ውጪ የህብረተሰቡን የኑሮ ዘይቤ ለመግለፅ የገቡት ምንባቦች ህብረተሰቡንና የህብረተሰቡን እውቀት የሚያኮስሱ ናቸው። ህብረተሰቡ በግብርና ላይ ያለውን ጥልቅ እውቀት እንደእውቀት የማይቈጥሩና የህዝቡን ኣላዋቂነት የሚሰብኩ ሆነው ተገኝተዋል።

**ክህሎትንና እውቀትን ለማስተማር የተመረጡት መልመጃዎችና የቡድን ስራዎች ኣበእን ማዳበር በሚያስችል ዘዴ ስለመቅረባቸው፡-** የማስተማር ዘዴዎች የሚነደፉት የትምህርቱ ዓላማ ከታወቀ በኋላ ነው። በቅድሚያ ምን ለማግኘት ማስተማር እንደተፈለገ መታወቅ ኣለበት። በመቀጠል የዓላማ ማስፈፀሚያ ይዘት ይመረጣል ወይም የይዘቱ ምንነት ይታወቃል። ማስተማሪያ ዘዴውና የኣቀራረብ ስልቱ የሚመጣው ከዚህ በኋላ ነው። የተመረጠው ይዘት በምን ሁኔታ ቢቀርብ ነው የተቀመጠውን ዓላማ መሳካት የሚችለው የሚለው ጥያቄ ቀጣይ ሆናል። በሰንጠረዥ 7፣ 8ና 9 እንደተመለከተው በኣራቱም ስርዓተትምህርቶች ኣበእን ማስተማር ግቡ ያደረገ ኣንድም ዓላማ እንዳልቀረበ መገንዘብ ይቻላል። ከትምህርት በኋላ ምን እንዲሆን፣ ምን እንዲሰራ፣ ወይም እንዲያውቅ እንደታለመ ሳይታወቅ የኣቀራረብ ዘዴ ሊመረጥ እንደማይችል ይታወቃል። ሆኖም በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የማህበረሰቡ እውቀቶችን ማስተማር የሚችሉ ጥቂት ምንባቦች ስላሉ የቀረቡበትን ዘዴ መመርመር ግድ ነበር።

በቃለመጠይቅና በተኮር የቡድን ውይይት ከተሳተፉት መምህራን የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ የይዘቶቹ አቀራረብ የሚወሰነው በመምህራኑ የግል ፍላጎት ነው። አንዳንድ መምህራን እቤት አንብበው እንዲመጡ ተማሪዎችን ያዛሉ። ሌሎቹ ራሳቸው ክፍል ውስጥ ደጋግመው በማንበብ ያስደምጣሉ። ጥቂት ተማሪዎች ደጋግመው ሲያነቡ ሌሎቹ እንዲያደምጡ ያደርጋሉ። ተማሪዎች ያደመጡትን ምንባብ በቃል እንዲናገሩ ያለማምዳሉ። በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ያከናወኗቸው ተግባራት የተለያዩ ስለሆኑ የትኛውን የቋንቋ ክህሎት ማዳበር እንደሚቻል አይታወቅም። በምንባቦቹ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገው እውቀት በመምህራን ወይም በወላጆች ተብራርቶ ተማሪዎች ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አይደረግም። አበ እውቀቱ ተብራርቶ ካልቀረበ ደግሞ የተፈለገውን እውቀት ተገንዝበውታል ማለት ይከብዳል። መረጃዎቹ የሚያመለክቱትም መምህራኑ ከመምህር መምሪያውም ሆነ ከስልጠና ያገኙት እውቀት ስለሌለ የተከተሉት የአቀራረብ ዘዴ አበእን ለማስተማር የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል።

## *5.3. ይሁንታዎችና የቀጣይ ጥናት ጥቆማዎች*

### 5.3.1. ይሁንታዎች

ከክለሳ ድርሳናት፣ ከመረጃ አቀባዮችና ከሰነዶቹ በተገኘው መረጃ መሰረት ሁሉም የህብረተሰቡ አባል አገር በቀል እውቀትንና እሴቶችን የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት። በሌላ በኩል ከጋራ ሃላፊነት ሌላ በተጨማሪ ሃላፊነት የተሰጣቸው አካላት አሉ። እነዚህም የትምህርት ሚኒስቴር፣ የትምህርት ቢሮ፣ የስርዓተትምህርት ዝግጅት ክፍሎች፣ የመምህራን አሰልጣኝ ኮሌጆች፣ የባህልና ቱሪዝምና ማሕበር ባህሊ ትግራይ ናቸው። እነዚህ አካላት በያሉበት የሚከተሉትን ተግባራት ካከናወኑ እውቀቶቹ ሊጠበቁ፣ ወደትውልድ ሊተላለፉና ማስተማሪያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ ብየ አምናለሁ።

### የትምህርት ሚኒስቴር

- ህፃናት ይበልጥ እንዲማሩ በማድረግ የሚጫወቱትን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት ለአገር በቀል ትምህርትና ለህዝብ ባህል ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ የሚያመለክቱ እቅዶችን ቢያወጣ፣
- ክልል ትምህርት ቢሮ፣ የትምህርት ቤቶች መጠን መጨመር፣ የመፃሕፍት አቅርቦት ማሻሻል፣ የክፍል ተማሪ ጥመርታ ማሻሻል በጥራት ላይ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ቢታወቅም፣ ተማሪው በሚማረው ይዘት ላይ ለውጥ ካልመጣ የትምህርት ጥራት

እውን ሊሆን ኣይችልም። ኣብዛኛው የገጠር ልጅ ያደገበት ማህበረሰብ እውቀት በመደበኛው ትምህርት መነሻ ሆኖ እንዳላገለገለ ሰነዶቹ ኣመልክተዋል። ከማንኑቱ ውጪ የሆነ እውቀት ደግሞ ጊዚያዊ እውቀት ነው የሚሆነው። ስለዚህ የኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት ሲታቀድ ኣበእ ትኩረት ቢሰጠው፤

**ትምህርት ቢሮ / ስርዓትትምህርት**

- የትግርኛ ቋንቋ ስርዓትትምህርት ከመዘጋጀቱ በፊት ተማሪ ከህብረተሰብ ማወቅ የሚፈልገው የእውቀት ዓይነት ለመለየት፣ ህብረተሰብ ወደ ልጁ መተላለፍ ኣለበት የሚለውን እውቀት ለማወቅና የቋንቋው ትምህርት የትኛውን ኣበእ በምን መልክ ሊገለገልበት እንደሚችል ለመወሰን ጥልቅ የሆነ የተማሪ፣ የህብረተሰብና የቋንቋ ትምህርት የፍላጎት ኣሰሳ ቢያካሂዱ፤
- በኣንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ህፃናት ከቤት ይዘውት የመጡትን እውቀት መነሻው ካላደረገ ኣዲስ እውቀት ለመቀበል የሚቸገሩ መሆኑ፣ እውቀቱን ቢቀበሉትም ኣብሯቸው የሚቆየው እስከፈተና ጊዜ ድረስ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ የተጋሩ ኣበእ በቋንቋ ትምህርት በስርዓትትምህርት ውስጥ የሚካተትበትን ምቹ ሁኔታ ቢፈጥሩ፤
- በመፃህፍቱ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ከማሳየት ይልቅ በመስበክ፣ በመምከርና መንገር ላይ ያተኰሩ ናቸው። የዚህ ዓይነቶቹ ምንባቦች ኣገር በቀል እውቀትን ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ክህሎትና እውቀትን ለማስተማር ያላቸው ብቃትም ኣናሳ ስለሚሆን ኣቀራረቡ ቢለወጥ፤
- ህብረተሰቡ፣ ወደቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚፈልጋቸው እውቀቶች በመማሪያ መፃሕፍት ሲካተቱና ልጁ ስለራሱ ሲማር ሲያይ የባለቤትነት ስሜቱ ያድጋል፤ ትምህርትንና ትምህርት ቤትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ተሳታፊ ይሆናል። የህዝብና የትምህርት ቤት ትስስር ይጠነክራል። ስለዚህ ኣበእን የማካቱ ተግባር በእቅድ ቢከናወን፤

**የመምህራን ኮሌጆች፡-**

- በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የሚካተቱ ኣበ እውቀቶችን እንዴት መለየትና ወደተማሪ ማስተላለፍ እንደሚቻል ለማወቅ የሚያስችል ስልጠና ቢሰጡ፤

* መምህራን፡- በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ያሉት ስነቃል ነክ ምንባቦች ቋንቋ ለማስተማር፣ ኣዲስ እውቀት ለማስተላለፍም ሆነ የህብረተሰቡን ኣበእ ለማስተዋወቅ የላቀ ድርሻ እንዳላቸው በመገንዘብ ተገቢ ትኩረት ሰጥተው ተማሪዎች በቡድንና በጋራ እንዲሁም ከህብረተሰቡ ጋር በመገናኘት እውቀቱን ፈልፍለው የሚያወጡበት ስልት ቢቀይሱ፤

**ባህልና ቱሪዝምና ማሕበር ባህሊ ትግራይ**

* የቋንቋ ስርዓተትምህርት ኣዘጋጆች፣ ኣበ እውቀቶችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ፣ ተመራማሪዎች ስለተጋሩና ስለእውቀታቸው መረጃ እንዲያገኙ፤ የትግራይ የባህልና ቱሪዝም ቢሮና ማሕበር ባህሊ ትግራይ እውቀቶቹን በመሰብሰብና በዓይነት በመለየት በሰነድ መልክ ቢያስቀምጡ።

### 5.3.2. የቀጣይ ጥናት ጥቆማዎች

ከተለያዩ ሰነዶችና መረጃ ኣቀባዮች መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት በርካታ ቀጥታዊና ጉናዊ የሆኑ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ኣበእ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቢገባ ሊኖረው የሚችለውን ጠቀሜታ በመጠኑም ቢሆን ለማመልከት ተሞክሯል። ጠቀሜታው ግን በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች፣ በልማት ስራዎች፣ በማህበራዊ ግንኙነቶች፣ በስነምግባርና በግጭት አፈታትም ሊንፀባረቅ ይችላል። ስለዚህ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ለማስተማር የሚኖረውን ፋይዳ ለማየት የህብረተሰቡን እውቀት ለመጠበቅና ከተጠቀሱት ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጠቀሜታ ያለው መሆን አለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚከተሉት ጥናትና ምርምሮች ቢካሄዱ መልካም ነው።

* ይህ ጥናት የህብረተሰቡን እውቀት የፈተሸው በመማሪያ መፃሕፍቱ ከቀረቡት ምንባቦች ኣኳያ ነው። በቀጣይ የህብረተሰቡ እውቀት በጥልቀት ተጠንቶና ተለይቶ በስርዓተትምህርት ውስጥ የሚካተትበትና በየክፍል ደረጃው ሊገቡ የሚችሉበትን ሁኔታ ማጥናት፤
* የተጋሩ ኣበእ ግጭቶችን ከመፍታት ማህበራዊነትን ከማጠናከርና ስነምግባርን ከማስተማር ኣኳያ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። ስለዚህ የስነማህበረሰብና ስነሰብእ ባለሙያዎች ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለመንግስት የፖሊሲ ቀረፃም ሆነ ለክፍል ትምህርት ኣስተዋፅኦ ቢያደርጉ፤

- ህብረተሰቡ በእርሻ፣ በከብቶች ህክምና፣ በወቅቶችና ከወቅቶች ጋር ተያይዘው በሚከወኑ ስራዎች ላይ የራሱ የሆኑ እውቀቶች አሉት። በነዚህ እውቀቶች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ከዘመናዊው የግብርና ስራ ጋር ማጣጣምና ዘመናዊ መልክ ይዘው የሚቀጥሉበት ሁኔታ ቢፈጠር የህብረተሰቡን ኑሮ ከመለወጥ አኳያ የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል።
- አገር በቀል እውቀት ከቋንቋ ውጪ የሆኑ የትምህርት ዓይነቶችን ለማስተማር በመሳሪያነት መገልገል ምን ጠቀሜታ እንዳለው አልተፈተሸም። ስለዚህ ከኣበ ሕክምና፣ መስፈሪያ፣ ግብርና፣ የኣዝርእት ጥበቃ ወዘተ. ጋር የተያያዙ ጥናቶችን በማካሄድና ግልጋሎት ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ መፍጠር፤

## ዋቢ ፅሁፎች

### ሀ. በኣገር ውስጥ ቋንቋዎች የተፃፉ

ሃብተማሪያም ኣሰፋ። 1986 ዓ.ም.። *የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች።* ኣዲስ ኣበባ (ኣሳታሚ ያልተጠቀሰ)።

ሀይለገብርኤል ዳኘ። 1961 ዓ.ም.። "የኢትዮጵያ ትምህርት ፍልስፍና" *ውይይት፣* ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2፡2።

ልሳነወርቅ ገብረጊዮርጊስ (መሪጌታ)። 2002 ዓ.ም.። *ብሔረ ብፁዓን ኢትዮጵያ።* መቐለ፣ APE።

*መስፍን ዘርኣብሩክ መንገሻ።* 1997። *ካብ ኤርትራ ክሳብ ኢትዮጵያ ዛንታን ወለዶን።* ኣዲስ ኣበባ፤ ሰማያታ ፕረስ።

ሙሉጌታ ደባልቀው። 2002 ዓ.ም.። *ገሳሀቲ ሰገ፤ የህወሓት የትጥቅ ትግል ታሪክ (1967-1983 ዓ.ም.)።* ኣዲስ ኣበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት።

ቅርስ ጥናትና ምርምር ባለስልጣን (የ)። 2002 ዓ.ም. *የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች የኢንቨንተሪ ማንዋል።* ኣዲስ ኣበባ፣ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ከዩኔስኮ ጋር በመተባበር።

ቢሮ ትልምን ፋይናንስን። 2003 ዓ.ም. *ትልሚ ዕበየትን ትራንስፎርሜሽንን ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ።* መቐለ፣ ቤት ሕትመት ዘመን።

ቢሮ ትምህርቲ ክልል ትግራይ። 1995 ዓ.ም.። *ትግርኛ ን1ይ ክፍሊ (መፅሓፍ ተምሃሪ)።* ኣዲስ ኣበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

________። 1995ዓ.ም.። *ትግርኛ ን2ይ ክፍሊ (መፅሓፍ ተምሃሪ)።* ኣዲስ ኣበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

________። 1995ዓ.ም.። *ትግርኛ ን3ይ ክፍሊ (መፅሓፍ ተምሃሪ)።* ኣዲስ ኣበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

________። 1995ዓ.ም.። *ትግርኛ ን4ይ ክፍሊ (መፅሓፍ ተምሃሪ)።* ኣዲስ ኣበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

________። 1997ዓ.ም.። *ንቋንቋ ትግርኛ ካብ 1ይ - 4ይ ዝቐረበ መለክዒ* (MLC ያልታተመ)።

________ ። 2003 ዓ.ም. *ትልሚ ዕብየትን ስግግርን ትምህርቲ 5 ዓመት (2003-2007 ዓ.ም.)።* መቐለ፣ ፕላንን ፕሮጀክትን።

________ ። 1995ዓ.ም.። *ትግርኛ 1ይ ክፍሊ፤ መምርሒ ንመምህር።* መቐለ፣ ቤት ሕትመት ዘመናዊ።

________። 1995ዓ.ም.። *ትግርኛ 2ይ ክፍሊ፤ መምርሒ ንመምህር።* መቐለ፣ ቤት ሕትመት ዘመናዊ።

________። 1995ዓ.ም. ። *ትግርኛ 3ይ ክፍሊ፤ መምርሒ ንመምህር።* መቐለ፣ ቤት ሕትመት ዘመናዊ።

_________። 1995ዓ.ም.። *ትግርኛ 4ይ ክፍሊ፣ መምርሒ ንመምህር።* መቐለ፡ ቤት ሕትመት ዘመናዊ።

_________። 1994ዓ.ም.። *ሲለበስ ቋንቋ ትግርኛ (1-4)።* ያልታተመ።

ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር(የ)። 1998። *የኢፌዲሪ የቋንቋ ፖሊሲ መነሻ ጥናት።* አዲስ አበባ፡ በባህል ፖሊሲ ጥናትና የአፈፃፀም ክትትል መምሪያ የቋንቋና ስነፅሁፍ ቡድን። (ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሃይሉ። 2000 ዓ.ም. *የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሰሶች ጥበቃ ኮንቬንሽን ፅንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ።* አዲስ አበባ፣ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን (ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሸዋዬ። 1994። "በአገርኛ ቋንቋ የማስተማር ፋይዳ " በ *Prosidings of the Eleventh International Conference of Ethiopin studies.* Institute of Ethiopian Studies: Addis Ababa University. (VOL.II),665-680.

ኢትዮጵያ መፅሓፍ ቅዱስ ማሕበር (የ)። 1962። *መፅሓፍ ቅዱስ። ኦሪት ዘፍ. ምዕ.8 ቁ. 1-12፣* ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ትምህርት ሚኒስቴር። 1983 ዓ.ም.። *በብሄራዊ ቋንቋዎች መደበኛ ትምህርት ስለሚሰጥበት የቀረበ አጭር ጥናት።* አዲስ አበባ (በውስጥ ህትመት)።

_______ ። 1967፡፡ *በህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የትምህርት መመሪያ፣ ለውይይትና ለትችት መንደርደሪያ ሀሳብ* (ያልታተመ)፡፡

ኢትዮጵያ ንጉሰነገስት መንግስት የፅህፈት ሚኒስቴር(የ)። 1947 ዓ.ም.። *ነጋሪት ጋዜጣ (የተሻሻለ ሀገመንግስት)።* አዲስ አበባ፣ 15ኛ ዓመት፣ቁጥ 2 ዓንቀፅ 125።

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪተበሊክ ሕገ መንግስት። 1987 ዓ.ም.። *ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ።* አዲስ አበባ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ፣ 1ኛ ዓመት፡ ቁጥር1።

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪተበሊክ (የ)። 1990 ዓ.ም. *የባህል ፖሊሲ።* አዲስ አበባ፡ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር።

ኣብ ቢሮ ሓበሬታን ባህሊን ጉጅለ ምስፍሕፋሕ ኪነጥበባትን መፅናዕቲ ቋንቋን። 1997ዓ.ም. *ስነቃል ትግርኛ (ዝንቅ ቁ. 2)።* መቐለ፡ ሜጋ ሕትመት።

ኣሉላ ፓንክረስት እና ገብሬ ይንቲሶ። 2004 ዓ.ም.። "ሃገራዊ እውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ" በ *የማህበራዊ ጥናት መድረክ* ። አዲስ አበባ፣ Eclipse (77-95)።

እያሱ ገብረመድህን። 2004 ዓ.ም.። *ውርሲ፣ ላዛ ቋንቋ ትግርኛ።* መቐለ፡ ቤተ ሕትመት ዘመናዊ።

ካሳ ገብረሂወትን ኣማኑኤል ጋንኪንን። 2000ዓ.ም. ። *መዝገበቃላት ትግርኛ።*አዲስ አበባ፡ ኤማይ ፕሪንተርስ።

የማነ ገብረመስቀል። 2005ዓ.ም.። *ቀዳማይ ወያነ።* አዲስ አበባ፡ ርዋቦት ኣታሚዎች።

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር። 2003 ዓ.ም.። *ኢፌዴሪ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጥራዝ 2።* አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ። 2001ዓ.ም. *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና ሀአተገባበር (2ኛ እትም)*። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ደጋፊ ጕዲፊይ። 2001 ዓ.ም.። *ባህሊን ታሪኽን ህዝቢ ወጀራት*። መቐለ፡ ዘመናዊ ሕትመት መቐለ።

ፍስሐጊየርጊስ ዓብየዝጊ። 1887 ዓ.ም.። *ጦብላሕታ ብዛዕባ መንገዲ እንካብ ጦቢያ ንኢጣልያ*። ሮማ።

### ለ. በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፉ

Abebe, Z. and Vambe, M. 2009. *Close to the Sources: Essays on Contemporary African Culture, Poletics and Academy.* New York: Unisa Press.

Abrha Asfaw. 1998. 'Curriculum Integration vis-à-vis The Ethiopian Education and Its Implications for Text Preparations." In Proceedings of National Conference, Quality Education in Ethiopia: Visions for the 21st Century. Addis Ababa university: Institute of Educational Research (215-226)

Adane Taye. 1991. *A Historical Survey of State Education in Eritiera.* Addis Ababa: EMPDA.

Amare Asgedom. 1998. "Culture and Development" in *IER Flambeau, IER.* Addis Ababa Univeristy; 5(1) 1-5.

______. 1998. "Content Analisis Mthodology and Applications to Curriculum Evaluation." In *IER Flambeau , IER.* Addis Ababa Univeristy; 6(1) 1-15.

______.2008. *Beyond Knowledge Acquisition. A Plea for Knowledge Application: (quality and relevance of education expanding growth induced employment in Tigray).* Mekelle: Research submitted to REST.

Banda, Dennis. 2008. *Education for all and the African Indigenous Knowledge System(AIKS): The case of the Chewa People of Zambia* (Ph.D dissertation). Lussaka: The University of Nothingham.

Battist, M. 2002. *Indigenous Knowledge and Pedagogy in First Nation Education.* Ottawa: Apamuwek Institute.

Bauman, R. 1983. "The Field Study of Folklore in Context" in Dorson, R. (ed.) *A Handbook of American Folklore.* Bloomington: Indiana University Press.

Bell, J. 1993. *Doing your Resarch Project.* Philadelphia: Open University Press.

Bigge, M. L. and Shermis,S.S. 2004. *Learning Theories for Teachers (6th edn.).* New York: Pearson Education, Inc.

Brock-Utne, B. 2000. *Whose Education for All? The Recolllonization of the African Mind.* New York: Falmer Press.

Castillo, J. J. (2009). Snowball Sampling. Retrieved [28 April 2011 from ExperimentResources: http://www.expreimentresoruces.com/ snowball-sampling.html.

Caulk, R. A. 1975. "ErnestWork on Ethiopian Education." In *The Ethiopian Journal of Education.* Addis Ababa University, 8(1) 1-16.

Cohen, L.; Lawrence, M. and Keith, M. 2007. *Research Methods in Education.(6th edn.).* New York: Routledge.

Cowie, A.P. 1993. *Oxford Advanced Learners Dictionary (4TH Edition).* Oxford University Press.

Creswell,J. W. 2009. *Researc Design. (3rd edn.).* New Delhi: SAGE.

Cunningham, D.J. 1992. "Assessng Constructions and Constructing Assessments." In T.M. Duffy and D.H. Jonassen (Eds.). *Constructivism and the Technology of Instruction.* London: LAE Publishers.

Dixon, A.B. 2003. *Indigenous Managment of Wetlands: Experiance in Ethiopia.* Burlington:Ashgate Publishers Company.

Dornyei, Z. 2007. *Research Methods in Applied Linguistics. Quantitative, Quallitative and Mixed Methodologies.* Oxford: Oxford University Press.

Dorson, R. (Ed). 1972. Folklore and Folk life: An Introduction. Chicago: The University of Chicago.

Duffy, T.M. and Jonassen, D.H. 1992. *Constructivism: New Implication for Instructional Technology.* London: LAE Publishers.

Dundes, A. 1994. "On the Structure of Proverbs". In Miender, W and A. Dundes (eds). *The Wisdom of Many.* New York: Garland Publishing.

Educational Brodcusting Corporation. 2004. Concept to Classroom Constructivism as Paradigm for Teaching and Learning. <http://www. thirteen. rg/edonline/ on ept class/resources/htm

Elleni Tedla. 1996. *Sankofa: African Thought and Education.* New Yurk: Peter lang.

Emegwali, G. *"Afrikan Indigenous Knowledge Systems: Implications for the Curriculum"* WWW.AFRICAHISTORY.NET Retraived 05/07/2012.

